

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ቅፅ - 23

www.abyssinialaw.com

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች





ቅፅ - 23

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክረሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

# ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

# ቅጽ-23

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ታህሣሥ 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ድህረ-ገፅ፡-www.fsc.gov.et
ስልክ፡-+251-111-55-34-00
ፋክስ፡-+251-111-56-55-33
የመ.ሣ.ቁ. 6166
ነፃ የስልክ መስመር፡- 992

www.abyssinialaw.com



## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ኘሬዚዳንት መልዕክት

በአንድ ሀገር የህግ የበላይነት ሊረጋገጥ የሚችለው ህዝብና መንግስት በህግ የበላይነት መርህ ላይ እምነት ኖሯቸው ተግባራዊ ሲያደርጉት ነው፡፡ ቀልጣፋና ህግን መሠረት ያደረገ ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠትም ዳኞች ያለአንዳች ተፅዕኖ በነፃነትና በገለልተኝነት ከተጠያቂነት ጋር የሚቀርብላቸውን ጉዳይ መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡

የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው የህግ ትርጉም በመስጠት የሚሰጡት ውሳኔ በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ዘንድ አስገዳጅነት እንደሚኖረውና አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎችንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አሳትሞ ማሰራጨት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች ተከታታይነት ባለው መልኩ አሳትሞ በማሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡ አሁንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሳኔዎች በቅፅ 23 የሰበር ህትመት ታትመው እንዲቀርቡ የተደረገ መሆኑንና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ድረገፅ www.fsc.gov.et ላይ የምታገኙት መሆኑን እየገለጽኩ በውሳኔዎቹ ጥራትም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የምትሰጡን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ለዳኝነት አገልግሎት አሰጣጣችን መሻሻልና ብሎም በቅርቡ እንደሀገር የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ አስመልክቶ ፍ/ቤታችንም የለውጡ አካል በመሆኑ የዳኝነት ነፃነትን፣ ገለልተኝነትንና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ህዝቡ በፍ/ቤቱ ላይ የሚኖረው አመኔታ እንዲያድግ ለምናደርገው ጥረት ስለሚያግዘን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እገልፃለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለወደፊቱ አስገዳጅ ውሳኔ የተሰጠባቸው የፍ/ቤት ውሳኔዎች ህትመት ሳይጠበቁ በተወሰኑ በጥቂት ቀናት ውስጥ በፍ/ቤቱ ድህረ-ገጽ እንደሚለቀቁ ማሳወቅ እንሻለን፡፡

**ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ**

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት**

www.abyssinialaw.com

# የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ማውጫ/ቅፅ-23/

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ቤተሰብ** | | | | | **1** |
| 1. | ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ያላገባ የሚል ማስረጃ መውሰድ በራሱ በሁለት ሰዎች መካካል የነበረውን የትዳር ሁኔታ ግንኙነት መኖሩን የሚያረጋግጠውን ማስረጃ የሚያስተባብል ስላለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94-97 | 143325 | አቶ አለማየሁ ተድላ<br>እና<br>ወ/ሮ ሜሮን ፋንታዬ | ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም | 2 |
| 2. | የባልና ሚስት ፍቺ ተፈጽሞ የንብረት ክፍፍል እስከሚደረግ ድረስ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረትም ሆነ ከዚህ ንብረት የሚገኝ ገቢ የጋራ ሆኖ የሚቆይ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 89 | 153258 | አቶ አህፈሮም ግርማይ<br>እና<br>ወ/ሮ ሀበን ፍስሐዬ | መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ/ም | 6 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3. | • አባትነትን በሕግ ግምት ወይም በመቀበል መንገዶች ለመወሰን ክርክር ሲነሳ የባህሪ ወሳኝ ቅንጣት (DNA) ውጤት እንደ መከላከያ ማስረጃ እንዲቀርብ በሕጉ በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በሕጉ የተረዘረጋውን ስርዓት ተከትለውና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆኑን ሲያምኑበት ተግባራዊ ሊያደርጉት የሚችሉ ስለመሆኑ<br>• የዘር የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ ውጤት በሕጉ በተመለከተው አግባብ በሕጋዊ ምክንያቶች ለማስረጃነት የሚቀርብ እንጂ በሕግ የተቀመጠውን ግምት እናት ስለካደች ብቻ ለማስረጃነት የሚቀርብ ማስረጃ ነው ተብሎ ድምዳሜ የሚደረስበት ስላለመሆኑ<br>*የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95* | 148570 | ወ/ሮ ጃኖ ተሰማ<br>እና<br>አቶ አሊ ሰይድ | ግንቦት28 ቀን 2010 ዓ.ም | 12 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *አንቀፅ 181፣183(1) እና 155(1(ሀ))* | | | | |
| 4. | የባህሪ ወሳኝ ቅጣት ( DNA) ምርመራ አንድ ሰው የልጁ አባት ወይም እናት አይደለም ለማለት የሚቀርብ ማስተባበያ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ቢሆንም የሚከናወነው አባትነትን በሚመለከት የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚያስችሉ ቀዳሚ ሁኔታዎች ሲሟሉ ስለመሆኑ እና እናትነትን በተመለከተም በቤተሰብ ህግ ከአንቀፅ 153 እስከ 166 ድረስ የተዘረጋው ስርዓት የሚፈቅድ ሁኖ በፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱትን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓቶችን መሰረት በማድረግ ሲቀርብ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 167-179 | 152719 | ወ/ሮ ብርቱካን ታደሰ እና ወ/ሮ የሺእመቤት ታደሰ | መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም | 20 |
| 5. | ከባልና ከሚስት ባንዱ የተፈጸመውና ለፍቺው ምክንያት ሆኖ የተገኘው ጥፋት በሌላው ተጋቢ ላይ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ በዳዩ ላደረሰው ጉዳት ከጋራ ንብረት በካሳ መልክ ያንደኛውን ተጋቢ ድርሻ አብዛኛውን ወይም ሙሉውን በደል | 152968 | ሲ/ር ሐምዚያ ሱለይማን እና አቶ አያሌው በቀለ | መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም | 29 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለተፈጸመበት ወገን እንዲከፈል ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 111፣117 | | | | |
| 6. | በጋብቻ ውስጥ የተደረገ የብድር ውል ከአንደኛው ተጋቢ እውቅና ውጪ የተደረገና የጋራ እዳ መሆኑ ፍሬነገር የማጥራትና ማስረጃን የመመዘን መርህን በተከተለ መንገድ ተረጋግጦ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ ፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2472 | 147930 | ወ/ሮ ሰብለ ታምራ እና አቶ ግሩም ግዛቸው | 28/9/2010 ዓ/ም | 34 |
| 7. | በመርህ ደረጃ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚገባው ከባልና ሚስቱ አንደኛው ተጋቢ ወይም ሁለቱም ቢሆንም በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው ውክልና ማስረጃ ጋር የሚቀርብ የፍቺ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.58፤ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2199 | 150408 | ወ/ሮ አመለወርቅ ፍቅሬ እና አቶ ተስፋሁን ታፈሰ | ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም | 39 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ውርስ** | | | | 44 |
| 8. | • የፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 ስለ ኑዛዜ መነበብ እንዲሁም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው እንዲፈርስ አቤቱታ የሚያቀርቡበትን ሥርዓት እና ጊዜውን በሚመለከት የሚደነግግ እንጂ ኑዛዜ ከውርስ ተነቅለናል በማለት ኑዛዜው እንዲፈርስ የሚቀርብን ወይም የቀረበን አቤቱታን የሚመለከት ስላለመሆኑ<br>• አንድ ኑዛዜ ከውርስ የመንቀል ውጤት ያለው በመሆኑ እንዲፈርስ የሚል የዳኝነት ጥያቄ ሊታይ የሚገባው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1123 መሠረት እንጂ በፍትሐብሄር ህግ አንቀጽ 973 መሠረት ስላለመሆኑ | 152134 | ወ/ሮ ትግዕሥት ንጉሴ<br>እና<br>እነ አቶ አሰፋ ንጉሴ | ህዳር 24 ቀን 2011 ዓ/ም | 45 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 9. | የውርስ ንብረት ክፍያ ከተደረገ በኋላ በክፍያ ውስጥ ያልገቡ በውርሱ ንብረት ውስጥ ገብተው የሚቆጠሩ አዲስ ሀብቶች የተገኙ እንደሆነ አዲስ የክፍያ ስርዓት መፈፀም የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1103፣1104 | 153231 | እነ ወ/ሮ እልፌ ደበላ<br>እና<br>አቶ ንጉሴ ደበላ | መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም | 53 |
| 10. | የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ በሚል አቤቱታ በተከፈተ መዝገብ ላይ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም የሚል ተከራካሪ ወገን በሚቀርብበት ጊዜ ፍ/ቤቶች ወደ ኑዛዜው ይዘት እና ሕጋዊነት ሁኔታ ገብተው ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ያለባቸው በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን በሕጉ አግባብ በመስማትና በሚገባ በማጣራት ተገቢውን ዳኝነት መስጠታቸው ስነ ስርዓታዊ እንጂ በንብረት ክርክር ጊዜ የሚታይ ነው ተብሎ የሚታለፍ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 996 | 159474 | አቶ እንደገና ተሾመ<br>እና<br>አቶ ረታ መልካ | ህዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም | 59 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ውል | | | | 63 |
| 11. | የዉክልና ሰነዶችን ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተረጋገጠ ሰነድ ሙሉ እምነት የሚጣልበት ማስረጃ ሆኖ ቅቡልነት ያለዉ ስለመሆኑና የሰነዱን ቅቡልነት መቃወም የሚቻለዉም በበቂ ምክንያት ፍርድ ቤት ሲፈቅድ ብቻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ/922/08 አንቀጽ 23/1/ | 146457 | ወ/ሮ ዘቢባ ሙሳ<br>እና<br>አቶ አማን በሪሶ | ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም | 64 |
| 12. | በአደራ የተሰጠ ገንዘብ መኖርን ለማስረዳት ተቀባይነት የሚኖረዉ ማስረጃ በጽሑፍ የተደረገ የአደራ ዉል እንጂ በሌላ የሰዉ ወይም የሰነድ ማስረጃ ስላለመሆኑ<br>የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2782 እና 2472(1) | 149861 | አቶ ቶዉፊቅ ላሉ<br>እና<br>አቶ ስራጅ ጀማል | 30/09/2010 | 70 |
| 13. | በአንድ ውል ላይ የገደብ (የመቀጫ)ስምምነት በተደረገ ጊዜ ባለገንዘቡ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ውሉ እንዲፈፀም እንዲሁም የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል ለመጠየቅ የሚችል | 162776 | አቶ ሰለሞን መርደኪዮስ<br>እና | ታህሳስ 26 ቀን2011 ዓ.ም. | 74 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሲሆን ነገር ግን መቀጮ የሚከፈለው የውሉ መዘግየት ወይም ተጨማሪ ግዴታዎች ካሉ የእነሱ አለመፈፀም የመቀጮውን ክፍያ የሚያስከትል ሲሆን ስለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(1)(2) | | አቶ ሲሳይ ለበኔ | | |
| 14. | አንድ ንብረት የገዛ ሰው የገዛውን ንብረት በፈለገው መልኩ መጠቀም የማያስችል ሁኔታ መፈጠር ፤ ውሉ ከመደረጉ በፊት ችግሩ/ጉድለቱ እንዳለ ቢያውቁ ኑሮ ውሉን አይፈጽምም ነበር የሚያሰኝ በመሆኑ ጉድለት ያለበት ውሉ ነው ተብሎ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት መመለስ ያለባቸው ስለመሆኑ፡-<br>ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1815፣ፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2289 | 133398 | አቶ ጉልላት ግዛው<br>እና<br>አቶ ጥላሁን ኃይሉ | ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም | 80 |
| 15. | የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለዉ ልዩ ባህርይ አንፃር ንብረቱን ከአንድ ወደ ሌላ ሰዉ በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በሦስተኛ ወገን ላይ ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ ዉሉ | 153664 | ወ/ሮ አሻ ፋራህ<br>እና<br>እነ አብዱራህማን | መስከረም 29 ቀን 2011 ዓም | 86 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በህግ አግባብ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ካልተመዘገበ ውሉ ፈራሽ የሚሆን ሲሆን ሻጩም በዉሉ ምክንያት የተቀበለዉን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ይህን እንዲያደርግ ሌላ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልግ በዚያው መዝገብ ላይ መወሰን የሚቻል ስለመሆኑ<br>*በፍ/ሕ/ቁ አንቀጽ 2878* | | ጣሂር (ሦዎች 9 ) | | |
| 16. | አንድ የባንክ ሠራተኛ በሥራው አጋጣሚ ያገኘውን የደንበኛ ገንዘብ ከህግ ውጭ ቀንሶ በማስተላለፍና በማውጣት መውሰዱ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሰራተኛው የወሰደውን ገንዘብ ዋሶቹ ከእርሱ ጋር በአንድነትና በነጣላ ገንዘቡን የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ 1920፣1922 እና 1933 | 145456 | ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማሕበር<br>እና<br>እነ አቶ እዮብ ሙሉጌታ ቱሳና | 24/09/2010 ዓ.ም | 90 |
| 17. | በአንድ ውል ምክንያት ለደረሰ የጉዳት ኪሣራ ምክንያት ግራቀኙ ተዋዋይ ወገኖች መሆናቸው ከተረጋገጠ ለደረሰው | 145523 | ቻን ቹን ያን ኃላፊነቱ የተ/የግ/ማህበር | ሐምሌ 16 ቀን 2010 ዓ.ም | 94 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የጉዳት ኪሣራ ሁለቱም ሃላፊነቱን መሸከም ያለባቸው ስለመሆኑ<br>ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1799(1) ፣1802 (1)፣2090፣2091 | | እና<br>ወ/ሪት ሞሚና ሁሴን | | |
| 18. | አንድ ዉክልና በላዩ ተዘርዝረዉ የተመለከቱትን ጉዳዮችና የነዚሁ ተከታታይ እና ተመሳሳይ የሆነዉን እንደ ጉዳዩ አይነትና እንደ ልማድ አሰራር አስፈላጊ የሆነዉን ማከናወን የሚያስችል ሲሆን ወካዩ የፈጸመዉ ተግባር የወካይና ተወካይ ጥቅሞችን ግጭት የሚያስከትል በሆነ ጊዜ 3ኛዉ ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀና ሊያዉቅ የሚገባ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ<br>ፍ/ሕ/ቁ 2206፤2187 | 134663 | ጅማ ዩኒቨርሲቲ<br>እና<br>ቢሊሱማ ሚአ የዕፀዋት ዘር አቅራቢ ድርጅት | ጥር 21 ቀን 2010 | 98 |
| 19. | አንድ ጉዳይ ከውል መተካት አንፃር እንዲታይ ይተካል በተባለው እና ተተክቷል በሚባሉ ውሎች መካከል ያለው | 148158 | አቶ በትግሉ ከበደ<br>እና | ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም. | 105 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የውለታ ጉዳይም ሆነ የውለታው ምክንያት በይዘቱ አዲስ መሆን እንዳለበትና ይህንኑ በውለታውም አይነት ሆነ ከውለታው ምክንያት አንፃር ታይቶ አዲስ የሆነው ውል ቀደም ሲል ተደርጎ በነበረው ውል ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በማያጣራጥር አኳኋን ሊያስቀር የሚችል ፈቃድ ከተዋዋይ ወገኖች እንዲኖር አስፈላጊ ስለመሆኑ እና ውልን ከማሻሻል ጉዳይ አንፃር ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1826 እና 1828 | | ሸሬ እንዳስላሴ ማገሚያ ቤት | | |
| 20. | በአንድ የብድር ዉል ላይ ያለ ፊርማ የኔ አይደለም የሚል ክርክር በመነሳቱ በብድር ዉሉ ላይ ያለዉን ፊርማ ተበዳሪው በመካዱ በፎረንሲክ ምርመራ የእሱ ፊርማ አለመሆኑ የተረጋገጠ ሰነድ ላይ ፊርማው የተበዳሪው ስለመሆኑ አበዳሪው በሰዉ ምስክሮች ላስረዳ በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው | 156408 | አቶ አክሊሉ ጌታሁን እና ወ/ሮ ፍሪህይወት አሰፋ | 24/01/2011ዓ/ም | 109 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2006 እና 2472(1) | | | | |
| 21. | የፍርድ ማስፈጸሚያ ይሆናል የተባለን የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ሲጠቀምበት መቆየቱ የተረጋገጠበት የፍርድ ባለገንዘብ ለዚሁ ጊዜ ዉስጥ ከዋናዉ ገንዘብ በተጨማሪ የፍርድ ባለዕዳ ለባለገንዘቡ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ፤<br>የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ1803፣1751 እና 2478 | 136653 | አቶ ገ/ሚካኤል በርሀ<br>እና<br>አቶ ገ/ዮሃንስ ወ/ጊዮርግስ | ግንቦት 23 ቀን 2010 ዓ.ም | 113 |
| 22. | ስጦታ የሚደረገው ስጦታው በተደረገበት ቀን የአስተላላፊው /የሰጭው/ የራሱ በሆነ ሀብት ላይ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍትሓብሔር ህግ አንቀጽ 2427፤2451 /1/ | 149301 | ወ/ሮ ውዴ ደሴ<br>እና<br>እነ አወቀ ደሴ | ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ/ም | 118 |
| 23. | ገንዘብን በአደራ የማስቀመጥ ዉል (deposit fund) መነሻነት አደራ ያስቀመጠ ባንክ የአደራ አስቀማጩን ገንዘብ የመጠበቅ፣ ሲጠይቁ ወጪ አድርጎ የመክፈል እና | 154115 | ያዳኒ ራባ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ | *መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም* | 126 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከአስቀማጩ ዉጪ ለሌላ ሰዉ ያለመክፈል ከዉል የመነጨ ግዴታ ሲኖርበት ይህን ግዴታውን ባይወጣ አስቀማጩ ላይ ሊደርስ ለሚችል ጉዳት ከዉል የመነጨ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ባንኩ የሚቀርብለትን የክፍያ ጥያቄ ሲያስተናግድ፣ገንዘብ እንዲከፈለዉ ጥያቄዉን ያቀረበ ሰዉ በርግጥም አደራ አስቀማጩ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ 896 እና 897 | | ባንክ አንዋር መስጊድ ቅርንጫፍ | | |
| 24. | • አንድ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ መቀመጫ አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ ከሆነ፣ጉዳዩም ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ከሆነ፣የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና የአገሮች ልምድ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕጎች እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት ከሰጣቸዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተከራካሪ ወገኖች “የግልግል ዳኝነት | 128086 | የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና<br>ኮንስታ ጆይንት ቬንቸር | ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም | 130 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጉባኤው ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ" ብለው ቢስማሙም ዉሳኔዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ከሆነ በሰበር ከመታየት የሚከለክልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ፤<br>• በተንኮል የተደረገ ዉል ፈራሽ የሚሆነዉ ከተዋዋዮቹ አንደኛዉ ወገን ዉሉ እንዲደረግ ያደረገዉ በሁለተኛዉ ተዋዋይ ላይ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ ዉል የማያደርግ እንደነበረ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704(1)፤1808(1)<br>• የአንድ ዉል በፍ/ቤት ዉሳኔ የፈረሰ እንደሆነ የዉሉ መፍረስ የሚያስከትለዉ ዉጤት ተጣርቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704(1)፤ 1808(1)፤1815 | | | | |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | **153** |
| 25. | የአካል ጉዳት ካሳ በርትዕ ሲወሰን ባጠቃላይ የተጎጂው የመስራት አቅሙ ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን መነሻ በማድረግ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታዎች በተጎጂው የወደፊት ህይወት ላይ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት አሉታዊ ተጽእኖ፤ ወቅታዊ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት እና ተጨባጭ የገንዘብ /ብር/የመግዛት አቅም በየጊዜው እየቀነሰ መሄዱ፤ ወደፊት ሊታጣ የሚችለው ገቢ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተገናዝቦ መታየት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2102 እና 2153(ሀ)) | 152417 | ወ/ሮ ሚሚ አበበ እና አቶ ታምራት /ማሙሽ/ ባልቻ | ግንቦት 17 ቀን 2010 ዓ.ም | 154 |
| 26. | ከህግ አግባብ ውጪ ገንዘብ እንዲከፈል መደረጉን ተከትሎ የተሰጠ የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔን መሰረት በማድረግ ገንዘብ ያለአግባብ እንዲከፈል ያደረገውን አካል ከውል ውጪ ኃላፊነት የተደነገገውን መሰረት | 131804 | የሰሜን ወሎ ዞን የቆቦ ጊራና ሽለቆ ልማት ፕሮግራም እና | መጋቢት 25/2010 | 163 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በማድረግ ያላግባብ እንዲከፈል የተደረገው ገንዘብ እንዲመለስ ለመጠየቅ የሚቻል ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ህ/ቁ 2035 | | እነ አቶ አድነው አባተ (3 ሰዎች) | | |
| 27. | • አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ባይኖርም በራሱ ጥፋት በሌላው ሰው ላይ ጉዳትን ካደረሰ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ እና ማንም ሰው ከራሱ ጥፋት የተነሳ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረገው ጉዳት ኪሳራ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ<br>•የፌዴራል ፖሊስ አባላት አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት ተሸከርካሪዎችን የማስቆም እና የመፈተሽ ስልጣን እና ኃላፊነት ያላቸው ቢሆንም ይህንን ኃላፊነት በሚወጡበት ጊዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2031(1) ስር የተመለከተውንና የሙያ ስራው የሚመራበትን ደንብ ማክበር የሚጠበቅባቸው | 142630 | እነ ሳጅን ግርማ መርጋ (3 ሰዎች) እና ወ/ሮ ደህቦ መሐመድ | ሚያዚያ 11 ቀን 2010 ዓ.ም. | 169 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2031 (1)፣ 2027 (1) እና 2028 | | | | |
| | | ንግድ | | | 174 |
| 28. | አንድ የንግድ ምልክት አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ የሌላ ዕቃዎችን አገልግሎችን በሚመለከት በሚገባ በሚታወቅ ወይም ኢትዮጵያ ዉስጥ ግልጋሎት ላይ ከዋለ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን ከያዘ መመዝገብ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 7(2)፤ 36(1) | 143227 | ደርሂም ኢንዱስትሪስ ካምፓኒ ሊሚትድ እና አሁጃን ኢንዱስትሪስ | 21/09/2010 | 175 |
| 29. | በንግድ መደብር ውስጥ የሚገኙ ግዙፍነት ያላቸው እንደ መሳሪያዎች፣ የቤት ዕቃዎችና ሸቀጥ ያሉ ንብረቶች | 153890 | ወ/ሮ እመቤት ዳኛቸው | መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም | 179 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ባለሀብትነትን ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኃን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን በእጁ ባደረገው ጊዜ የሚተላለፍለት ስለመሆኑና ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ የእነዚሁ ንብረቶች ባለሀብት ስለመሆኑ በሕጉ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ<br>በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1186 (1)፤ንግድ ሕጉ በቁጥር 128 | | እና<br>እነ አቶ ይስማው ዘገየ<br>( 2 ሠዎች) | | |
| 30. | አንድ ባንክ በአደራ የተቀበለውን የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ ሕጋዊ ግዴታ ያለበትና ከሕግ ውጪ የደንበኛውን ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደረገ ሰው በባንኩ ገንዘብ ላይ ጉዳት ማድረሱ ከተረጋገጠ ደንበኛው ገንዘቡን ከባንኩ የማግኘት መብት በህግ የተጠበቀለት በመሆኑ ባንኩ ደንበኛውን በመተካት ወይም በራሱ ስም ሆኖ የደንበኛውን ገንዘብ ባልተገባ ወይም በወንጀል ተግባር ወጪ አድርጎ ለግል ጥቅሙ ባዋለው ሰው ላይ ክስ ቢያቀርብ ባንኩ | 158539 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ ምንዳይ ክፍሌ | ሕዳር 27 ቀን 2011 ዓ/ም | 185 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በቅድሚያ የደንበኛውን ገንዘብ ስለመክፈሉ ወይም በደንበኛው የባንክ አካውንት ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም በሚል ክሱ ውድቅ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ አንቀፅ 896-902፤አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 52(1) | | | | |
| 31. | በአንድ ክስተት ከሁለት በላይ በሆኑ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት መድረሱ በመድን ሰጪና ተቀባይ መካከል በተደረገ የመድን ዉል መሰረት የመድን ሰጪዉ ግዴታ የኃላፊነት መጠን በመድን ዉሉ ላይ ከተመለከተዉ መብለጥ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ አንቀጽ 665(2) | 149326 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና<br>ወ/ሮ መብራቴ ጤናዉ | 28/03/2011 | 192 |
| 32. | የንግድ ማህበር ስለሚፈርስበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 217፤218 እና 542 | 153981 | ሚሲስ ሲያዎ ዶንግ እና<br>እነ ሚስተር ዶንግዩ | መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም | 197 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቸን ( 2 ሰዎች) | | |
| **ንብረት** | | | | | 204 |
| 33. | በባህላዊ መንገድ የሚታረስ መሬትን በዉል ማከራየት የሚቻለዉ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ ዉሉም ዋጋ የሚኖረዉ በሚመለከተዉ አካል ተመዝግቦ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ<br>የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 10(2 እና 3) | 150773 | አቶ ሀይሉ ኪዳኑ እና<br>እነ አቶ ቀጭኑ ዱጉማ | ግንቦት 27/2010ዓ/ም | 205 |
| 34. | የከተማ መሬት ይዞታ አጠቃቀም ላይ የመወሰን ስልጣን በህግ ስልጣን በተሰጣቸዉ በሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታና በአስተዳደር አካል ያልተረጋገጠ መብት ይዞ ውሳኔ እንዲሰጥ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት | 134343 | እነ አቶ ቴዎድሮስ ዉብሸት (3ሰዎች) እና<br>እነ የአዳማ ከተማ ቀበሌ 06 መስተዳድር ጽ/ቤት(5ሰዎች) | ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ.ም | 210 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁ. 179/05 አንቀጽ 8 | | | | |
| 35. | አንድ ባለይዞታ ወሰን አልፎ በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ያለአግባብ በመግባት የሰራው ግንባታ በሌላኛው ባለይዞታ ንብረት አጠቃቀም ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ በባለሙያ ከተረጋገጠ ባለሙያው ባለበት ተለክቶ በዚያው ልክ ወሰኑን ያለፈዉን ግንባታ እንዲያፈርስ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1204፣1205፣1225/1/ | 159414 | አቶ ሚሬሳ አብሳ<br>እና<br>አቶ ፍቃዱ ደበሎ | ታህሳስ 22 ቀን 2011ዓ.ም | 215 |
| 36. | አንድ ሰዉ የኮንዶሚኒየም ግዥ ፈጽሟል ሊባል የሚችለዉ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ስምምነት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ብቻ ሲሆን ገዥዉ ቤቱን ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለዉ ቤቱን ከገዛ 5 ዓመት ሲሞላዉ ሲሆን ጊዜው የሚቆጠረዉ ዕጣ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን ገዥዉ የቤት ሽያጭ ዉል ከሚመለከተዉ የመንግስት አካል ጋር ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በአ/አ ከተማ አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች | 158899 | አቶ ክብሮም አደራ<br>እና<br>እነ ወ/ሪት ትዕግስት መንገሻ | 26/03/2011 | 219 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ *7(6-ለ)*፣14(2) | | | | |
| 37. | የመንግስት ቤት ህጋዊ ተከራይ የሆነ ወላጅ የኮንደሚኒየም ቤት በደረሰው ጊዜ ከመንግስት የተከራየውን ቤት ለመንግስት የማስረከብ ግዴታ ያለበት በመሆኑ የወረዳው አስተዳደር ፅ/ቤት የመንግስት ቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ለተከራዩ ልጆች ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሁከት ተግባር የማይስብለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የመንግስት ቤቶችን ለማስተዳደር የወጣው መመሪያ ቁጥር 4/2009 ዓንቀፅ 15(ሐ(መ)) | 155664 | አዲስ ከተማ ከተማ ወረዳ 9 ኮ/ቤቶች ልማት ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሻወል ወልዴ | ጥቅምት 30 ቀን 2011 ዓ.ም. | 224 |
| 38. | የከተማ ይዞታን የማስተዳደር ስልጣን በህግ አግባብ የተሰጠው አካል ስልጣንና ኃላፊነቱን በህግ አግባብ አልተወጣም የሚል ክርክር ያለው ወገን ጉዳዩን ለፍ/ቤት የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37፣ 40(3)(4)፣79(1) | 141625 | ወ/ሮ አድና መላኩ<br>እና<br>የወልዲያ ከተማ አገልግሎት | ሐምሌ 26 ቀን 2010 ዓ.ም. | 228 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እና 78(4) | | | | |
| 39. | • ማንኛዉም የቴሌኮሙንኬሽን ድርጅት የቴሌኮሙንኬሽን መስመር ሲዘረጋ መስመሩ የባለይዞታን ወይም የሌላ ህንጻ ላይ የሚዘረጋበት አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር አስቀድሞ ለባለይዞታዉ ወይም ለባለህንጻዉ በማስታወቅ የባለይዞታዉ ወይም የባለህንጻዉ ተቃዉሞ እንዳለ ሰምቶ ተገቢዉን የመወሰን ስልጣን ለኤጀንሲዉ የተሰጠ ስለመሆኑ<br>• የቴሌኮሙንኬሽን ድርጅት የአንድ ባለይዞታ ይዞታ ዉስጥ ገብቶ በቋሚነት ኮንቴነር ከተከለ ለተጠቀመበት ይዞታ ተገቢዉን ካሳ ለባለይዞታው የመክፈል ግዴታ አለበት<br>የቴሌኮሙንኬሽን አዋጅ ቁ/49/89 አንቀጽ 18፣20/1/፣22/2/፣እና አዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 6 | 144901 | ኢትዮቴሌኮም የሰሜን ምስራቅ ሪጅን<br>እና<br>ወ/ሮ በለጡ ወልደ ተገኘ | ሐምሌ 12 ቀን 2010 ዓ.ም | 234 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | | **238** |
| 40. | አንድ ተከሳሽ በሕግ አግባብ መጥሪያ የደረሰዉ እና እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ማወቁን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በሌለሁበት የተሰጠዉ ፍርድ ተነስቶ የመከላከያ መልስ ላቅርብ በማለት የሚያቀርበውን አቤቱታ በህግ በተቀመጠው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አልቀረበም በሚል ምክንያት ብቻ መከላከያ መልስና ክርክር አቅርቦ የመሰማትና ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት መንፈግ ያልተገባና ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ፡-<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78፣95 /2/ | 137704 | አቶ መሀመድ ከማል<br>እና<br>አቶ በቀለ ወልዴ | የካቲት 14 ቀን 2010 ዓ.ም | 239 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 41. | አንድ ውል አይፈርስም ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በተደረገው ውል መነሻነት የወጣ ወጭ ካለ በማጣራት በዚያው መዝገብ ላይ መወሰን የሚገባው እንጂ በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ቀርቦና እንዲከራከሩበት መወሰን ለተራዘመ የክርክር ሂደት ስለሚጋብዝ በዚህ መነሻነት መዝገቡን መዝጋት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | 139187 | አቶ መስፍን ዘርዓብሩክ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ የወርቅዉሃ አለማየሁ | ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም | 246 |
| 42. | በአንድ ክስ አጠቃሎ ክስ ማቅረብ የሚቻለው በተቋቋመ መብት ላይ ተመስርቶ እንጂ ዳኝነት በተጠየቀበት ጊዜ ያልበሰለ ወይም ያልተረጋገጠ መብት ጭምር ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/፣216 | 142242 | አይል ሊቢያ ኢትዮጵያ ሊሚትድ<br>እና<br>አቶ ኃይሉ ገ/ሕይወት | 16/09/2010 ዓ/ም | 253 |
| 43. | አንድ ኑዛዜ ከፀደቀ በኋላ በቀረበ ንብረት ክፍፍል ውስጥ ወራሾች ከአውራሻቸው በውርስ ሊያገኙት ከሚገባው ድርሻ ተገቢውን ያላገኙ መሆኑን ገልጸው በሚከራከሩበት ጊዜ ፍሬ | 146503 | ወ/ሮ ንጋቷ በየነ<br>እና<br>ወ/ሮ ሀረገወይን በየነ | ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም | 257 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ነገሩ ተጣርቶ ከሚለይ በስተቀር ኑዛዜው ፀድቋል በሚል ምክንያት ብቻ የሐብት ድርሻቸውን በተመለከተ የሥረ- ነገር ክርክሩ ቀድሞ ታይቷል ተብሎ ውድቅ ሊሆን የሚችልበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 | | | | |
| 44. | አንድ ሰው መብቴን ይነካል በሚል የመቃወም አቤቱታ ያቀረበበት ዉሳኔ በሌላ አግባብ ከተሻረ እና መብትን ሊነካ የሚችል ዉሳኔ በሌለበት የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>ፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 358ፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 358 | 148270 | እነ አቶ ቡልቻ ቱሉ<br>እና<br>አቶ ተመስገን ሙላቱ | 30/09/2010 | 262 |
| 45. | ክርክርን በመስማት ላይ ያለ ፍርድ ቤት ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ከሰጠ በኂላ፣ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ክርክሩ በየትኛዉም ደረጃ ላይ ቢሆን ጣልቃ | 144470 | ናይል ትራንዚት ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እነ ኒያላ ኢንሹራንስ | 30/11/2010 | 266 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ገቡ ከክርክሩ ዉጪ እንዲሆን ትዕዛዝ ከመስጠት የሚከለክለዉ ነገር የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ ከአንቀጽ 40-43 | | ኩባኒያ | | |
| 46. | አንድ ተከሳሽ የቀረበበት ክስ በይርጋ የሚቋረጥ መሆኑን ከጠቀሰ ከሳሹ ክሱ በሕጉ የተመለከተው ጊዜ ገደብ (ይርጋ) ያላለፈው መሆኑን፣ ጊዜው አልፎ ከሆነም ይርጋውን ሊያቋርጥ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩን በተገቢው ማስረጃ ለማስረዳት የሚችልበት እድል ሳይሰጠው የተከሳሽ መቃወሚያ ብቻ መሰረት ተደርጎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ ብይን የሚሰጥበት አግባብ ስነ ስርዓታዊ ስላለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር1000፣1846፣1852እና1853፤የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 241፣ 244 እና 245(1) | 154023 | እነ ወ/ሮ ካሰች በቀለ<br>እና<br>እነ ውቢት ዘውዴ | መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም. | 269 |
| 47. | ይግባኝ የማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን የመንግስት ስራ ዝግ በሆነበት ቀን ላይ ያረፈ ሲሆንና በቀጣዩ የሥራ ቀን ይግባኙ | 152845 | አቶ መሀመድ ሙህዲን እና | መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም | 274 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተዘጋጅቶ ሲቀርብ ይግባኙ እንዲከፈት መፍቀድ ሥነ-ሥርዓታዊ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1862፣ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323/2 ፣326 | | ዘምዘም አሊ | | |
| 48. | • አንድ ከሳሽ መብቱን ማግኘት የሚገባው ከየትኛው ተከሳሽ ላይ እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ የሚያጠራጥር ሁኔታ ያጋጠመው ሲሆን አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሰዎች በህብረት በመክሰስ ሀላፊነቱ የሚመለከተው የትኛው እንደሆነ ተለይቶ እንዲወሰንለት ማመልከት ስለመቻሉ<br>• ፍርድ ቤቶች በአንድ ክስ ላይ ስማቸው በተከሳሽነት ከቀረቡ መካከል ስማቸው ከመጠቀሱ ውጪ በግልፅ ዳኝነት አልቀረበባቸውም በሚል ምክንያት ብቻ አንዱን | 139313 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሰረት ፍቃዱ (2 ሰዎች) | መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም | 278 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወይም የተወሰኑትን ሀላፊነት የለባቸውም በማለት የሚደርሱበት መደምደሚያ ህጉን ያተከተለ ስለመሆኑ፡-<br>የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 36(5) | | | | |
| 49. | ለአንድ ጉዳይ ለምስክርነት የተቆጠረ ሰው በፍርድ ቤት ጥሪ መሠረት ቀርቦ የመመስከር ግዴታ ያለበት ሲሆን ምስክሩ ሊቀርብ ካልቻለም ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ በታየው መንገድ ትዕዛዝ በመስጠት ምስክሩ በሕግ አግባብ ተገዶ ወይም ታስሮ እንዲቀርብ በማዘዝ ምስክርነቱን በመስማትና ተገቢ ነው ካለም በሌላ ማስረጃም ጭምር በማጣራት የቀረበለት ጉዳይ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 116፣118(2)(ለ) | 153610 | ወ/ሮ ፊይዛ ከሚል እና አቶ አብዲ አህመድ | መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም | 284 |
| 50. | አንድ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ በመመርመር ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ መልሱን አዘጋጅቶ | 154727 | አቶ ተኽላይ ፍሰሃ እና | ህዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም | 296 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንዲያቀርብ የታዘዘው እና ቀጠሮ የተሰጠው ከ10 ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከሆነ የተከሳሹን የመከላከልና የመከራከር የመሰማት መብቱን የሚነፍግ በመሆኑ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት የመከላከያ መልሱን እና ክርክሩን እንዲያቀርብ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.240[2] | | ወ/ሮ ለታይ ለገሠ | | |
| 51. | • አንድ ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ ሲችል ቀንሶ ባስቀረው ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ የማይችል ስለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216(3)፣218 | 119851 | እነ ወ/ሮ ሶፊያ መሀመድ<br>እና<br>አቶ እንድሪስ ጋሹ | መጋቢት 26 ቀን 2011ዓ.ም | 300 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | • አንድ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343 መሰረት ወደ ስር ፍ/ቤት ተመልሶ ፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ በመቃወሚያው ላይ አስቀድሞ በተሰጠ ብይን ላይ ተጠቃሎ የሚቀርብ የሰበር አቤቱታ ህጉን መሰረት ያደረገና ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320(3)፤ **/የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 90810 ፣ 76963፣ 125165 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ውሳኔ ተለውጧል።/** | | | | |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ሥልጣን** | | | | | 319 |
| 52. | የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ በአንደኛው ወገን በቀረበ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሌላኛው ወገን በጋብቻ ጊዜ ካፈሩት ገንዘብና ንብረት ከፊሉ ከኢትዮጵያ ውጪ ይገኛል በማለት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ማቅረቡ ብቻውን ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግን ተፈጻሚነት ጉዳይን/ conflict of laws/ የሚያስነሳ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የማያደርስ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን የማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከመሆን የማያስቀረው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ቁጥር 9፣17 ፤አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) | 152590 | ወ/ሮ እየሩሳሌም አስገዶም እና<br><br>አቶ ተወልደ ኃ/ማርያም | ጥቅምት 13 ቀን 2011 ዓ.ም. | 320 |
| 53. | የቀበሌ የንግድ ሱቅ አላግባብ ተይዞብኛል ይመለስልኝ በሚል | 144242 | አቶ ገዛህኝ አየለ | ግንቦት 30 ቀን | 327 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለክስ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በግለሰቦች መካከል የተደረገ ውል ሲሆን ጉዳዩን ተቀብሎ የማየት የዳኝነት ስልጣን የከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ሳይሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 4፤የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1)(ሪ) | | እና<br>እነ አቶ ኑረዲን ዓሊ | 2009 ዓ.ም. | |
| 54. | በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 መሠረት አግባብ ባለው አካል አስተዳደራዊ እርምጃዎች የተወሰደበት ማናቸውም ሰው በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ቅሬታ ካለው ጉዳዩን ማቅረብ የሚገባው ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንጂ በቀጥታ ክስ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የማይገባ ስለመሆኑ<br>የንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 46፣47(2)፣47(3)፣ | 145733 | አቶ ኤበሳ አመንቴ ጃለታ<br>እና<br>እነ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት | ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 330 |
| 55. | በአዋጅ ቁጥር 147/91 መሰረት አንድ ማሕበር ሕልዉናዉ | 153617 | አቶ ደሱ ታምሩ | መስከረም 21 | 335 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ካበቃ በኃላ ወይም መብትና ግዴታዉ የሕብረት ሥራ ማሕበር ወደ አልሆነ የንግድ ማሕበር ተላልፎ በሚገኝበት ወቅት ጉዳዩ በሽምግልና ዳኝነት የሚታይበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ እና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 47 እና 49 | | እና<br>ፊያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር | ቀን 2011 ዓ.ም | |
| 56. | የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ አላግባብ ተሰርዞብኛል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ጉዳዩ በቀጥታ ከመሬት ይዞታ ባለመብትነት ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ የተከራካሪ ወገኖች መደበኛ ነዋሪነት ወይም የተከራካሪው ወገን የፌዴራል መንግሥቱ ተመዝጋቢ መሆን ግምት ውስጥ ሳይገባ የክርክሩን ልዩ ባህርይ በማየትና የጉዳዩን ዓይነት መሠረት በማድረግ ንብረቱ የሚገኝበት የከተማ አሥተዳደር ፍ/ቤት የቀረበውን ክስ ተቀብሎ የመወሰን የሥረ-ነገር | 142594 | የደሴ ከተማ ዓይነሥውራን ማሕበር<br>እና<br>የኢትዮጲያ ዓይነሥውራን ብሔራዊ ማሕበር | ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም | 340 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 25 ፤አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 | | | | |
| 57. | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን መርምሮ የማረም ስልጣን የሚኖረው በክርክር አመራር ረገድ ፍርድ ቤቶቹ የጣሱት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ መኖሩ ሲረጋገጥ እና ጥሰቱም መሰረታዊ የሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ<br>የሐረሪ ክልል ፍርድ ቤቶች እና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 3/1988 /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 28 | 145128 | እነ ወ/ሮ ኬሚያት ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር<br>እና<br>እነ አቶ አንዋር ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር | ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም. | 350 |
| 58. | ዉልን መነሻ ያደረገ ያልተከፈለ ገንዘብ ለማስከፈል የቀረበ ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የማይወድቅ ስለመሆኑ | 145053 | እነ ወ/ሮ ስኳሬ ለገሰ<br>እና<br>የአዲስ አበባ ዉሃና | *24/9/2010ዓ.ም* | 354 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 | | ፍሳሽ ባለስልጣን | | |
| 59. | • የአንድ ጉዳይ ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ መሆናቸዉ እስከ ተረጋገጠ ድረስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ዉል ወይም ንብረት የሚገኘዉ በክልል ዉስጥ መሆኑ አንድን ጉዳይ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑን የማያስቀር ስለመሆኑ<br>• አንድን ጉዳይ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሆኖ ነገር ግን የአካባቢ ስልጣኑ በክልሎች ስር የሚወድቅ ሲሆን እንደነገሩ ሁኔታ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉክልና ጉዳዩን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው ስለመሆኑ<br>የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2)፤80(3-ሐ) | 144613 | እነ አቶ ያሲን ኢብራሂም (2ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ኃይሉ ታዬ | 30/09/2010 | 358 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እና 80(4)፤ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2)፤የፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 24 እና 25 | | | | |
| 60. | ሥራ ላይ ባሉ ህጎች መሰረት በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የክልል ፍርድ ቤት ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት አለባቸው በሚል ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አልተቋቋመም፤ እንዲሁም በክልል የሰበር ስርዓት በዝርዝር ህጎች አልተቀመጠም በሚል ምክንያት ጉዳዮች በቀጥታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊቀርቡ የማይገባ ስለመሆኑና ሥራ ላይ ባሉት ህጎች አግባብ በክልል ሰበር ችሎት መታየት ያለባቸው ስለመሆኑ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ)፣የሐረሪ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ70(2)(ሀ)፣የሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መ/ ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988፤የሐረሪ ክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ | 157560 | እነ ወ/ሮ አለምሸዋ አባተ አበበ<br>እና<br>እነ አቶ ሚሊዮን አባተ አበበ | መጋቢት 23 ቀን 2011 ዓ.ም. | 363 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁጥር 3/1988 እና ማሻሻያ አዋጆች ቁጥር 8/1991 እና 17/1991 እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1999 **/የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 111887 ፣ 120858 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ውሳኔ ተለውጧል።/** | | | | |
| **አፈፃፀም** | | | | | **369** |
| 61. | አንድ ክርክር ያስነሳ ንብረት በአፈፃፀም ሂደት በጨረታ ከተሸጠና ገንዘቡም ለፍርድ ባለገንዘብ ከተከፈለ በኃላ በጨረታዉ ሂደት ጨረታዉን ሊያስፈርስ የሚችል ጉድለት ካልተገኘ እንዲሁም ንብረቱ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የተሰጠ ዕግድ በሕግ አግባብ ያልተመዘገበ መሆኑ ከተረጋገጠ | 156758 | የአብክመ ገቢዎች ባለስልጣን ዐ/ሕግ እና አቶ መስፍን ጥላሁን | *ሕዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም* | 370 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የቀዳሚነት መብትን ለመጠቀም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሰረት የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>*በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418፣426፣445* | | | | |
| 62. | ባልና ሚስት በጋብቻ ዉስጥ ያፈሩት ቤት ፍቺን ተከትሎ እንዲከፋፈሉ ዉሳኔ ተሰጥቶ በአፈጻጸም ሂደት አንደኛው ወገን ድርሻ ከፍሎ ለማስቀረት የጠየቀና የተወሰነ ገንዘብ ብቻ ይዞ ቀርቦ ቀሪዉን ለመክፈል ጊዜ ከመጠየቅ በቀር ግዥዉን ለመፈጸምና የቅድሚያ ግዥ መብቱን በጊዜው ሳይጠቀም ከቀረ የቅድሚያ ግዥ መብቱ ሊጠበቅ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 430(1) | 152339 | ወ/ሮ እድገት ፎጊ<br>እና<br>ም/ኢ/ር አሻግሬ<br>ወ/ማርያም | 22/01/2011 | 377 |
| 63. | አንድ ሰው የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 ከመውጣቱ በፊት የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጠይቆ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተዘጋጅቶ | 152185 | የቦሌ ክ/ከተማ<br>አስ/የመሬት ልማት<br>እና | 28/01/2011ዓ/ም | 381 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንዲሰጠው ውሳኔ ያገኘው አዋጁ በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ከሆነ የውሳኔው አፈፃፀም ሊቀጥል የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 37/1 መሠረት ሳይሆን በአዋጁ አንቀጽ 6/3/ በሊዝ ስሪት መሠረት ስለመሆኑ | | ማናጅመንት ጽ/ቤት | | |
| 64. | የፍርድ አፈጻጸምን የሚመራ ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት እንደፍርዱ ይዘት እና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ ፍርዱን ከማስፈፀም በቀር የፍርዱን ይዘት በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ፍርድን የመተርጎም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 372፤378 | 152172 | ኢትዮ ቴሌኮም ሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር የሕብረት ሥራ ማሕበር<br>እና<br>እነ ሰለሞን እሸቴ | ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 385 |
| 65. | አንድ ለክርክር ምክንያት የሆነ ንብረት በአፈፃፀም ምክንያት በሐራጅ እንዲሸጥ የአፈፃፀም መዝገቡን የያዘዉ ፍርድ ቤት ወስኖ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዥ ካልተገኘ ንብረቱን ባለ ገንዘቡ የመረከብ መብት ያለው ሲሆን ይህን ግምት | 144272 | የሻለቃ አሰፋ መንገሻ ህጋዊ ወራሾች<br>እና<br>አቶ ዮናስ ዳኜ | 24/11/2010 | 391 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ማስተባበል የሚቻለዉ ደግሞ ባለገንዘቡ ቤቱን እንዲረከብ በሚል ተሰጥቶ የነበረዉ ትዕዛዝ ስነ-ስርዓት ህጉ በሚፈቅደዉ አግባብ በሌላ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሻሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 428(2) | | | | |
| 66. | የዕርቅ ስምምነት ውል እንደዉሳኔ ተቆጥሮ በፍርድ ቤት ለአፈፃፀም አቅርቦ ለማስፈፀም ስምምነቱ ግልጽና የፈፃሚዉን አካል ግዴታ በማያሻማ ሁኔታ የሚገልጽ መሆን ያለበት ሲሆን ግልጽ ያልሆነ የእርቅ ስምምነት ሲቀርብ፣ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሌላ ተከራካሪ ወገን ክርክር እንኳ መስማት ሳያስፈልገዉ ክሱን ዉድቅ ማድረግ የሚችል ስለመሆኑ<br>ፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3312(1) | 146955 | እነ አቶ ብሩክ ኃ/መስቀል<br>እና<br>አቶ ነብዩ ኃ/መስቀል | 30/09/2010 | 398 |
| 67. | የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ የሆነ ሰዉ ላልተከፈለዉ የዉዝፍ ኪራይ ክፍያ አከፋፈል ሲባል ተከራዩ | 156389 | አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ | ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 402 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለቤቱ ማገጫነት ወይም ለስፍራ ማልሚያነት ከሚጠቀምባቸዉ ዕቃዎች ላይ ዕቃዎቹ የራሱ ባይሆኑም ይህንኑ አከራዩ እስካላወቀ ወይም ማወቅ ነበረበት እስካልተባለ ድረስ በሕግ የተቋቋመ የመያዣ መብት ያለዉ መሆኑና በልዩ ሁኔታ ንብረቱ ለአፈጻጸም መዋል መቻል አለመቻሉ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተጣርቶና ተረጋግጦ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924፣2925፣2926(2) | | ዩኒቨርሲቲ<br>እና<br>ወ/ሮ ሺወርቅ ሲባኒ | | |
| 68. | በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በመጀመሪያ ጨረታ ሽያጭ ላይ ተወዳድሮ አሸናፊ የተባለ ገዥ ዋጋ ከፍሎ ግዥዉን ባለመፈጸሙ ድጋሚ ጨረታ ሲደረግ የሽያጭ ዋጋ ቢቀንስ በሁለተኛዉ እና በአንደኛዉ ጨረታ መካከል ለተፈጠረዉ የዋጋ ልዩነትና ኪሳራ የመክፈል ግዴታ ሁለተኛውን ጨረታ ተወዳድሮ አሸናፊ የሆነው ሰው ላይ የማይወድቅ ስላለመሆኑ | 154222 | አቶ ረሽድ አደም<br>እና<br>አቶ ታሪኩ አማረ | ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም | 407 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ./429 | | | | |
| **የወንጀል ሕግ** | | | | | **413** |
| 69. | አንድ ምስክር በፖሊስ በወንጀል ምርመራ ወቅት የሚሰጠዉ ቃል እንደመደበኛዉ የዳኝነት አካል ወይም የዳኝነት ነክነትወይም መሰል /quasi-judicial/ ተቋም ቃለ መሃላ ፈጽሞ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ባለመሆኑ ምስክሩ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጠው የምስክርነት ቃል ፍ/ቤት ቀርቦ በመለወጡ ምክንያት የሀሰት ቃል የትኛዉ እንደሆነ በትክክል በሌላ ማስረጃ ሳይረጋገጥ የምስክሩ ቃል መለያየት ብቻዉን በቂ ማስረጃ በማድረግ ምስክሩ በሀሰተኛ የምስክርነት ቃል መስጠት ወንጀል የሚጠየቅበት የህግ መሰረት ስላለመኖሩ<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ | 153228 | የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>እነ ፈንቴ ንጉስ | መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም | 414 |
| 70. | አንድ ቼክ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር | 149071 | የፌደራል ጠቅላይ | መስከረም 24 | 421 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በቂ ስንቅ አለመኖሩ እየታወቀ ቼክ የተሰጠ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ከግል ተበዳዩ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው ስለሆነና ቼኩን የሰጠው በመተማመኛ መልኩ ነው በማለት ድርጊቱ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው በሚል በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) መሰረት የቀረበ ክስ ወደ ወንጀል ህግ አንቀፅ 693(2) በመቀየር ተከሳሹን ጥፋተኛ ማለት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23፤59 ድንጋጌ ያላገናዘበ ስለመሆኑ | | ዓቃቤ ህግ<br>እና<br>አቶ አሰግድ አባ ቦሬ | ቀን 2011 ዓ.ም. | |
| 71. | “በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 27 መሰረት አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል” በማለት የተቀመጠው ሀሳብ በሕጋዊ መንገድ ለተያዙ | 150803 | በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ<br>እና<br>አቶ ንጉስ ሀይሉ | ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ.ም | 428 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የከተማ ቦታዎችን ለማስለቀቅ የተቀመጠውን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የመስጠት እና ካሣ የመክፈል ሥርዓት ማሟላት ሳያስፈልግ በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን ማስለቀቅ የሚቻልበትን ሥርዓት የሚደነግግ እንጂ የከተማ ቦታን ወሮ ለያዘ ሰው የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26(4)፣27 | | | | |
| 72. | በወንጀል ጉዳይ ፍርድ ከተሰጠ በኂላ አዲስ የወጣ ህግ ተከሳሹን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ተከሳሹ አዲሱ ህግ ተፈፃሚ እንዲሆን አቤቱታ ባቀረበ ጊዜ አዲስ የወጣው ህግ ተፈፃሚ እንዲሆን መደረግ ያለበት ስለመሆኑና በዚሁ ጉዳይ አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ በባህሪው እንደመደበኛ የክርክር ጉዳይ የሚታይ ሳይሆን በቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚችል በመሆኑ ከተወሰነ ጊዜ በኂላ የቀረበ አቤቱታ ነው በማለት ተቀባይነት የለውም የማይባል ስለመሆኑ | 151034 | አማረ ረታ<br>እና<br>የፌዴራል ጠ/አቃቤ ህግ | ጥቅምት 28 ቀን 2011ዓ.ም | 432 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2)፣ የወ/ሕ/አንቀጽ 6 እና 9(1)፤ ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ15/1/ | | | | |
| 73. | የዳኝነት ስራ አካሄድ ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች በተለይም አንድ ችሎት በያዘዉ መዝገብ ላይ ችሎት መድፈርን በተመለከተ ወዲያዉኑ ቅጣት ሊወስን ስለሚችልበት አግባብ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 449 ፣ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/480 እና 481 | 158613 | ወ/ሮ ማስተዋል ሰፈረ እና የለም | ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም | 436 |
| 74. | የአንድ ቼክ ሕጋዊነት ጥያቄ ባላስነሳበት ፤በዋናነት ደግሞ ቼኩ ተጽፎ እና ተፈርሞ መሰጠቱ ባልተካደበት ሁኔታ እንዲሁም ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸምበት ሰነድ ከመሆኑ አንፃር በወንጀል ጉዳይ ያለው ተጠያቂነት ቼክ በወጣበት ወይም ለክፍያ ለቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ መኖር ያለመኖሩን መሠረት ያደረገ እንጂ ለዋስትና የተሰጠ መሆን ያለመሆን በወንጀል ጉዳይ እንደ ሕጋዊ መከላከያ የሚወሰድ | 152755 | የፌደራል ጠቅላይ አቃቢ ህግ እና አቶ አፍራኖ ሁሴ | መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም. | 439 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) | | | | |
| 75. | አንድ የአሽከርካሪነት ሙያ ያለዉ ሰዉ የትራፊክ ደህንነት ደንብን ተላልፎ በተሽከርካሪዉ የኋላ የዉጭ አካል ላይ ሰው አሳፍሮ ሲያሽከረክር ተሳፋሪው ለመዉረድ ሲል መዉደቁ ወይም ለመዉረድ ሲል ዘሎ በመዉደቁ ለደረሰበት ጉዳት አሽከርካሪውን በቸልተኝነት ተጠያቂ ከመሆን የማያስቀረው ስለመሆኑ<br>የወ/ሕ/አንቀጽ 24፣ 59፣543(3)፣ በትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 36(1) | 156420 | የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ ዐ/ሕግ<br>እና<br>አቶ ሙላቱ ያለዉ | ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 446 |
| 76. | አንድ ተከሳሽ በአንድ ቸልተኝነትና በአንድ ድርጊት በደረሱ ጉዳቶች በተደራራቢ ወንጀሎች ሲከሰስ ሌላ የተለየ ሀሳብና ድርጊት መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ አንዱን በቸልተኝነት ሌላዉን ደግሞ ሆን ተብሎ ታስቦ በተፈጸመ ወንጀል ጥፋተኛ የሚደረግበት አግባብ እና | 153690 | አቶ ሀብታሙ ደስታ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ | መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም | 452 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቅጣትን በሚመለከት ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመዉ ሲገኙ ቅጣት ሊወሰን የሚገባዉ ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኃላ እነዚህን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመለየት ስለመሆኑ የተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 22(1/ሀ) | | | | |
| **የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ** | | | | | **457** |
| 77. | • በአንድ የወንጀል ክስ ማመልከቻ ላይ ተጠቅሶ የቀረበ ድንጋጌና የክሱ ፍሬነገር ዝርዝር ላይ በስህተት የተጠቀሰ ወይም ሳይጠቀስ የታለፈ መሠረታዊ ነገር መኖሩ ሳይረጋገጥ ከወዲሁ አንቀጽ ካልተለወጠ በሚል ምክንያት ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ መስጠትና ይህ ካልተፈጸመ በሚል የክሱን መዝገብ መዝጋቱ ክስ እንዲሻሻል የሚደረግበትን ህጋዊ አላማ | 155789 | የፌዴራል ጠ/አቃቤ ህግ<br>እና<br>ተጠሪ፡- ነቢላ አህመድ | ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም | 458 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ያላገናዘበ ስለመሆኑ<br>• አንድ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ክስ ሁለት ሆኖ 1ኛዉ ክስ ቀደም ሲል ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተሻሽሎ ባለመቅረቡ የሚዘጋ ቢሆን ሁለተኛዉ ክስ ላይ ያለምንም ህጋዊ ምክንያት ዉሳኔ ሳይሰጥ ማለፍ ሥነ-ሥርዓታዊ ስላለመሆኑ<br>በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/112፣113/2/፣119 | | | | |
| 78. | የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ለይግባኝ ማቅረቢያና ተያያዥ ጉዳዮች የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥም በመታየት ላይ ያለ መዝገብ መዘጋቱ አስፈላጊ ሆኖ ከተዘጋ በኃላ እንደገና መከፈቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በምን ያህል ጊዜ ዉስጥ አቤቱታ ሊቀርብበት እንደሚገባ በግልፅ ስላላስቀመጠ የጊዜ ገደቡ የሚወሰነው የጉዳዩን ሁኔታዎችና የአቤቱታዉን ዓይነት በመመልከት እንጂ መዝገቡን ለማንቀሳቀስ የቀረበዉ አቤቱታ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ የቀረበ ነው በማለት አቤቱታውን ውድቅ | 156999 | አቶ ከበደ ተሠራ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ | ጥቅምት27/2011 ዓ/ም | 463 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ማድረግ የይግባኝ ባዩን መብት የሚጣብብ ስለመሆኑ<br>በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22(2)፤በወ/ሕ/አንቀጽ 6፣ 9(1) | | | | |
| 79. | በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2/ መሠረት አንድ ተከሳሽ ለፖሊስ የሚሰጠው የእምነት ቃል ለምርመራ ዓላማ ሲባል በምርመራ ጊዜ የተገኘ ማስረጃ በመሆኑ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤት ሊመረመር እና ሊመዘን የሚገባው እንጂ ከወዲሁ ተቀባይነት አለው ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት ስላለመሆኑ<br>በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2/ | 152038 | የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ<br>እና<br>ምንተስኖት ደሩ | ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 468 |
| 80. | • የአንድ ተከሳሽ ያለፈ የቅጣት ውሳኔ አሁን ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በማያያዝ በዋስ ቢለቀቅ ተመሳሳይ ወንጀል ሊፈጸም ይችላል የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና ጥያቄን አለመቀበል አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | 132055 | አቶ አህመድ ደርባቸው<br>እና<br>ፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ጥቅምት8/2009 ዓ.ም. | 473 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | • በሕግ በግልጽ ካልተደነገገ በቀር አንድ ተከሳሽ በፍርድ ዳኝነት በግልጽ እስካልታወቀ ድረስ የቀድሞ ጥፋተኝነቱ የማይገለፅ ስለመሆኑ<br>በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ)፣138 (1) | | | | |
| | **ልዩ ልዩ** | | | | **477** |
| 81. | የመጥፋት ዉሳኔ ከተሰጠና የጠፋው ሰው ንብረት ለወራሾቹ ከተላለፈ በኋላ የመጥፋት ዉሳኔ የተሰጠበት ሰዉ በህይወት ከተመለሰ ሌላ ማረጋገጫ ሳያስፈልገዉ ንብረቶቹ በሚገኙበት አኳኋን መልሶ መዉሰድ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህግ 168-173 | 153418 | አቶ ጉደታ አሰፋ<br>እና<br>እነ ወ/ት ወደሬ ጉደታ | ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም | 478 |
| 82. | አንድ የመሰረታዊ ማህበር አባል ሲሞት ዕጣው ወይም ጥቅሙ በማህበሩ መዝገብ ውስጥ በወራሽነት ለሰየመው ወይም ሟቹ ወራሽ ያልሰየመ ከሆነ በሕግ ለመውረስ ለሚችል ወራሹ የሚተላለፍ ሲሆን ይህም የሚሆነው ወራሹ | 143045 | እነ ወ/ሮ እሌኒ ወ/አማኑኤል<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ወርቅነሽ | ግንቦት28 ቀን 2010 ዓ.ም | 483 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማህበሩ አባል ከሆነ ወይም ለመሆን ፈቃደኝነቱን ሲገልፅ ሲሆን ወራሹ የማህበሩ አባል ካልሆነ ወይም አባል ለመሆን የማይፈልግ ወይም የማይፈቀድለት ከሆነ የሚቹ የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም የሚከፈለው ስለመሆኑ<br>የኀብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁ.147/1991 አንቀጽ 19፣ 32 | | ብዙነህ | | |
| 83. | የሰውን ምስል ያለባለቤቱ ፈቃድ ለማስታወቂያ ሥራ በቴሌቭዥን በማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ያዋለ አካል ምስሉን ከባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በመጠቀም ለሰራው ማስታወቂያ ተገቢውን ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 14፣የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27፣28፣ 29 | 156425 | ዳሽን ባንክ<br>እና<br>ዶሪና አቫኪያን | ህዳር 14 ቀን 2011 ዓ.ም | 488 |
| 84. | ከቅጅ መብት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች የሚጣሩበት አግባብም ሆነ ክርክሮቹን መሠረት በማድረግ የሚሰጡ ዉሳኔዎች የቅጅ መብት ጥበቃ አጠቃላይ ዓላማ መሠረት | 153736 | እነ አረቡ አብደላ ( 3 ሰዎች)<br>እና | መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም | 493 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በማድረግ የቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ለማግኘት ስራዎቹ ማሟላት የሚጠበቅባቸዉ መመዘኛዎች መሟላታቸው አለመሟላታቸውን ስለ ቅጅ መብት ዕዉቀትና ልምድ ያላቸዉ ባለሙያዎች የተካተቱበትን አጣሪ ቡድን በማቋቋም እንዲያጣሩ በማድረግ የቅጅ መብት ጥሰት የተፈፀመ መሆን አለመሆኑን በማጣራት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 91(3) ፤አዋጁ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 2(8)፣2(30)፣ 4(1)(ለ)፣ 6(1) | | አዱኛ ጓዴ | | |
| 85. | በሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሠጣጥ፤አያያዝ እና አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር 78/2004 መሠረት ለኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጥቆማ ሲቀርብ ወሮታ ስለሚከፈልበት አግባብ<br>መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 16/1እና2፤17 | 153527 | አቶ ስንዴው ታደሰ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ | መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም | 503 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 86. | አንድ የሥራ ውሉ በገዛ ፈቃዱ የተቋረጠበት የሥራ መሪ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የሕግ አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2563 | 151082 | ሚ/ር አሂም ማርቲን ብራዉን<br>እና<br>ሜድሮክ ፋዉንዴሽን ስፔሻሊስት ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ/ም | 509 |
| 87. | አንድ ጠበቃ ደንበኛው ላይ በቀረበ ክስ “በተመሳሳይ ጉዳይ ሁለት ፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብ አይገባም ” በሚል በህግ የተፈቀደን መቃወሚያ ማቅረቡ የጥብቅና ሙያን የሚያጎድፍ ተግባር ፈፅሟል ተብሎ በዲስፕሊን የሚያስቀጣው ተግባር ስላለመሆኑ<br>የትግራይ ክልል የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁ/ 262/2007 አንቀጽ 30/23/ | 154371 | አቶ አስፋዉ ተኽለ በሽሩ<br>እና<br>የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ | ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም | 516 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 88. | የመንግሥት አካል ፊት ቀርቦ የተረጋገጠና የተመዘገበ ሰነድ በውስጡ የሚገኘው ይዘት ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀጽ 27 /1/ | 142851 | እነ ወ/ሮ ወርቅነሽ ጌታቸው (2 ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ ኮሬ ባዩ(2 ሰዎች) | ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም | 520 |

# ቤተሰብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 143325

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አለማየሁ ተድላ- የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሜሮን ፋንታዬ -ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳይ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክሳቸው ይዘትም፡- ከአመልካች ጋር ጥር 22 ቀን 2003 ዓ.ም በባህላዊ መንገድ ጋብቻ ፈጽመው አብረው የቆዩ መሆኑን አሁን ግን በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት በትዳር መቀጠል የማይችሉበት ደረጃ ላይ ስለደረሱ ፍርድ ቤቱ የማሰላሰያ ጊዜ መስጠት ሳያስፈልጋቸው በመካከላቸው ያለው ጋብቻ ፈርሶ የፍቺ ውሳኔ እንዲወሰንላቸው አመልካች ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም ለቀረበው ክስ የሰጡት መልስ ተጠሪ ጋር የፈጸሙት ጋብቻ እንደሌለ ነገር ግን ተጠሪ ጋብቻ ተፈጸመበት ባሉበት እለት ለተጠሪ ቀለበት ሲያደርጉ

www.abyssinialaw.com

የተዘጋጀው ዝግጅት የቀለበት ስነስርዓት እና ወደፊት እንደሚጋቡ ቃልኪዳን የገቡበት የመተጫጨት ስርዓት አለመሆኑን እና ይህ እውነትም ተጠሪ በራሳቸው ጥቅምት 27 ቀን 2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ጽ/ቤት ቀርበው ያላገቡ መሆናቸውን ገልጸዋል፤ ይህም ማስረጃ አለማግባታቸውን የሚገልጽ በተጠሪ እጅ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ማስረጃ የሚያረጋግጡ መሆኑን ሌሎች ማስረጃዎች የሚያሳዩት ከተጠሪ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የመተጫጨት ግንኙነት መሆኑን ለመተጫጨት መፍረሱ ምክንያት ተጠሪ ስለሆኑ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ለአመልካች ወጪና ኪሳራ ሊከፍሉ ይገባል በማለት የመከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ በቀን 9/2/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአመልካችና ተጠሪ መካከል የትዳር ሁኔታ መኖሩን ስለተረጋገጠ በሁለቱም መካከል ጋብቻ አለ ብሎ ከወሰነ በኋላ ለዚህ ውሳኔ መነሻ የሆነው የፍቺ ጥያቄ በተመለከተ የአሁን አመልካች ከጅምሩ ምንም ጋብቻ የለንም ብለው የሚከራከሩ በመሆኑ የፍቺ ጥያቄው ላይ አዲስ መልስ እንዲሰጡበት ቀጠሮ መስጠት ሳያስፈልግ እንዲሁም የማሰላሰያ ጊዜ መስጠት ሳያስፈልግ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 82 መሰረት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ሲል የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 13 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ነሐሴ 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ

www.abyssinialaw.com

ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ በመሠረቱ ጋብቻ ስለመፈፀሙ በቀዳሚነት ሊቀርብ የሚገባው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94 ድንጋጌ ሲያስቀምጥ ጋብቻ ስለመኖሩ ይኸው ማስረጃ ከሌለ የጋብቻ ግንኙነት ስለመኖሩ በትዳር ሁኔታ ማረጋገጥ ስለመቻሉም የተጠቀሰው ሕግ በአንቀጽ 95 ደንግጓል፡፡ ይህ የጋብቻ መኖር አለመኖርን በተመለከተ ሊቀርብ የሚገባው የማስረጃ አይነትና ቅደም ተከተሉ ነው፡፡ የትዳር ሁኔታ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነም ሕጉ በአንቀጽ 96 ስር አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት የትዳር ሁኔታ ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት የትዳር ሁኔታ አላቸው የሚባሉት ራሣቸውን እንደባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሁነው ሲገኙ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ በሕጉ የተመለከተውን ትርጓሜ ማስረዳት ከተቻለ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት እንደሚወሰድ ተጠቃሹ ሕግ በአንቀጽ 97/1/ ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ይህ የሕግ ግምት በማስረጃ መረጋገጥ በሚገባቸው ፍሬ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በዚህ አግባብ የተወሰደውን የሕግ ግምት ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ማፍረስ የሚችልበት አግባብም በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 97/2/ ተመልክቷል፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያሰሟቸው ምስክሮች ጥር 22 ቀን 2003 ዓ.ም አመልካችና ተጠሪ በባህላዊ መንገድ ጋብቻ መፈጸማቸው፤ጋብቻው ከመፈጸሙ በፊት አመልካች በአካባቢው ባህልና ወግ መሰረት መስከረም 22 ቀን 2003 ዓ.ም የአገር ሽማግሌዎችን ወደ ተጠሪ ቤተሰቦች በመላክ ሽማግሌዎቹ ልጃችሁን ለልጃችን ስጡ በማለት ጥያቄ አቅርበው የተፈቀደላቸውና የሰርጉ ቀን የተወሰነ መሆኑ፤በሰርጉ ላይ ቀለበት የማድረግ ስነስርዓት ሲፈጸም አመልካች የዘላለም ሚስቴ ናት በማለት ቃልኪዳን ገብተው የተዘጋጀው ምሳ ከተበላ በኋላ አመልካች ወደ ተከራዩት ቤት መሄዳቸው ከዚያ ግዜ ጀምረው ከአሜሪካ ወደ አገር ቤት ሲመለሱም አብረው በዚሁ ቤት አንድ ላይ ይኖሩ እንደነበር በዝርዝር ያስረዱ ስለመሆናቸው ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ተጠሪ በቀን 27/02/2007 ዓ.ም ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ያላገባ የሚል ማስረጃ መውሰዳቸው በራሱ በአመልካች እና ተጠሪ የጋብቻ ግንኙነት አለመኖሩን ያረጋግጣል የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ከጥቅምት 27 ቀን 2007 ዓ.ም በፊት በአመልካችና

www.abyssinialaw.com

በተጠሪ የነበረውን የትዳር ሁኔታ ግንኙነት መኖሩን በማስረጃ የተረጋገጠውን የሚያስተባብል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 126385 ጥቅምት 9 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 185798 ግንቦት 17 ቀን 2009 ዓ.ም በውሳኔ ያጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/አ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 153258

መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አህፈሮም ግርማይ -ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ሀበን ፍስሐዬ የቀረበ -የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት ነው፡፡ በአሁን አመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ የአሁን ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ በአሁን ተጠሪ ስም ከተመዘገበው የአስመጪና ላኪ ንግድ በተገኘ ገቢ እንዲሁም በብድር በተገኘ ገንዘብ የተገዛ የሰሌዳ ቀጥር ኮድ-2-21508 አ.አ የሆነው መኪና እንዲሁም ሌሎች ንብረቶችን በመጥቀስ ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካችም በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከንግድ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ ለትራንስፖርት፣ ለግብር እና ለትዳር ጥቅም ወጪ ወጥቶ የሚተርፍ ነገር የለም፡፡ ተሽከርካሪው እዳ ያለበት በመሆኑ እዳው ታሳቢ ተደርጎና አመልካች የከፈሉት ግምት ውስጥ ገብቶ ክፍፍሉ ቢደረግ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት ግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ እንዲሁም አግባብ ካላቸው አካላት መግለጫዎችን ጠይቆ ከመረመራቸው በኃላ ከአስመጪነትና ላኪነት ተገኘ ከተባለው ገቢ ለትዳር ጥቅም እና ለተለያዩ ጉዳዮች ያወጡዋቸው ወጪዎች ተቀናሽ ተደርገው ሊከፈሉ የሚገባው ገቢ ምን ያህል እንደሆነ በግልጽ በአሁን ተጠሪ አቤቱታ ላይ ያልሰፈረ በመሆኑ ጥያቄው ታልፏል፡፡ በሰሌዳ ቁጥር 2-21506 አዲስ አበባ ለሆነው መኪና በጋራ ከተከፈለው ብር 11,530.72 /አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም/ ውስጥ ብር 5,765.15 /አምስት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስራ አምስት ሳንቲም/ የአሁን አመልካች ለአሁን ተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታ የተሰማቸው የአሁን ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ቅሬታቸውም መሠረት ያደረገው ከአስመጪነት እና ላኪነት የተገኘው ገቢ በአግባቡ ተጣርቶ ድርሻዬ አልተወሰነልኝም፣ ተሽከርካሪውን በተመለከተ በትዳር ወቅት በጋራ በብድር የተገዛ ሲሆን የብድሩን አከፋፈል በትዳር ዘመናችን ጀምሮ የጋራ ንብረታችን ክፍፍል ሳናደርግ በቆየንባቸው ጊዜዎች ውስጥ ተከፍሎ ያለቀ በመሆኑ መኪናው የጋራ ተብሎ ሊወሰን ሲገባው የሥር ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የተከፈለውን ክፍያ የአሁን አመልካች /የሥር መልስ ሰጭ/ ከግላቸው እንዲከፍሉ ያለአግባብ ግምት በመውሰድ ቀደም ሲል ከተከፈለው ገንዘብ ግማሽ ለአሁን ተጠሪ /ለይግባኝ ባይ/ እንዲተካ በማለት መኪናውን ለአሁን አመልካች /ለመልስ ሰጭ/ እንዲሆን የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የሥር ፍርድ ቤት ቅሬታ በቀረበባቸው ነጥቦች ላይ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ይግባኙ መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ክርክራቸውን የሰማ ሲሆን የአሁን አመልካች /መልስ ሰጭ/ ጋብቻ ከፈጸምንበት ጊዜ ጀምሮ የፍቺ ውሳኔ እስከተሰጠበት ድረስ የአስመጪና ላኪ ንግድ ተሰርቶ የተገኘው የተጣራ ገቢ ብር 197,453.77 /አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከሰባ ሰባት ሳንቲም/ መሆኑን ከገቢዎች ከቀረበው ማስረጃ ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን ለትዳር እና ተያያዥ ወጪዎች ይኸው ገንዘብ ወጥቷል፡፡ በመሆኑም

www.abyssinialaw.com

የአሁን ተጠሪ /ይግባኝ ባይ/ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም። መኪናውን በተመለከተ የአሁን አመልካች /መልስ ሰጭ/ ከፍቺ በኃላ ከፍተኛውን እዳ የከፈልኩና በመኪናው ላይ እዳ የሌለበት ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤት ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት መኪናውን ለአሁን አመልካች/ ለመልስ ሰጭ/ ይገባል ማለቱ በአግባቡ ነው። የአሁን ተጠሪ /ይግባኝ ባይ/ መኪናውን በጋራ ልካፈል ይገባል የሚሉ ካሆነ ከፍቺ በኃላ በግል የከፈልኩትን ብር 237,497.16 / ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም/ ተመላሽ አድርገውልኝ መኪናው ተሸጦ ብንካፈል ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል።

የይግባኝ ሰሚው ክፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙ ያሰሙትን ክርክራቸውን ከመረመረ በኃላ ከአስመጪነትና ላኪነት ጋር የተያያዘውን ክርክር በተመለከተ በአግባቡ ሳይጣራ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ በመልስ ሰጭ /በአሁን አመልካች/ ስም ተመዝግቦ ከሚገኘው የአስመጪና ላኪ ንግድ ተገኘ የተባለውን ገቢ በተመለከተ የተጣራ ገቢው ምን ያህል እንደሆነ ከተጣራው ገቢ ላይ የወጣ ወጪ መኖር አለመኖሩን፣ አለ ከተባለ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነና ግራ ቀኙ ሊከፍሉት የሚችሉት ተራፊ ገንዘብ /ንብረት/ መኖር አለመኖሩን የግራ ቀኙ ቀኙን ክርክር፣ የተሰበሰበውን ማስረጃ እንዲሁም እንደ አግባብነቱ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ በማስቀረብ ጭምር ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲወሰን ጉዳዩን በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት መልሶታል። መኪናውን በተመለከተ ደግሞ መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ ከፍቺ በኃላ የመኪናውን የብድር እዳ የከፈሉ ከመሆኑ ውጭ ይኸው የገንዘብ ምንጭ ከግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ያልተገኘ ይልቁንም መልስ ሰጭ / የአሁን አመልካች/ በግላቸው ከሌላ የገንዘብ ምንጭ በተገኘ ገቢ የተከፈለ መሆኑን በማንሳት ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም። መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ ከግል ገቢያቸው የከፈሉ መሆኑን አላስረዱም ከተባለ ደግሞ ለመኪናው መግዣ ግራ ቀኙ የተበደሩትን ገንዘብ በተመለከተ የተከፈለውንና ከግራ ቀኙ የጋራ ሀብት የተገኘ ነው ተብሎ ግምት የሚወሰድ በመሆኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኪና ግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ተወስኗል በማለት ውሳኔውን ደምድሟል።

ውሳኔውን በመቃወም የአሁን አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ተዘግቶባቸዋል።

www.abyssinialaw.com

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔዎቹን ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው በኩል በውሳኔዎቹ ላይ ተፈጽሞብኛል ያሉዋቸውን ቅሬታ ነጥቦችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ ክርክር የተነሳበት መኪና በብድር ገንዘብ የተገዛ መሆኑ ባልተካደበትና ተጠሪም እዳው የጋራ ሆኖ ንብረቱን በጋራ ለመካፈል እየጠየቁ እያለ እዳው የጋራ ሳይባል ንብረቱ ብቻ የጋራ ነው የመባሉ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጠበቃቸው በኩል በ19/08/2010 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የአመልካች ጠበቃም ግንቦት 10 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን መኪናው የጋራ ነው ተብሎ የተወሰነው እዳው ከባልና ሚስት ገቢ የተከፈለ በመሆኑ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኪና አመልካችና ተጠሪ በትዳር ውስጥ አብረው እያሉ በብድር በተወሰደ ገንዘብ የተገዛ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ከመኪናው እዳ አከፋፈል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የአሁን አመልካች መኪናውን ለመግዛት ከተወሰደው እዳ ከፍተኛው የተከፈለው የአመልካችና ተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኃላ በመሆኑ መኪናው ለአመልካች የግል ሊባል ይገባል፡፡ የግል የማይባል ከሆነ ደግሞ ተጠሪ እዳውን ተጋርተው መኪናው የጋራ ሊሆን ይችላል በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ፍቺ ከተፈጸመ በኃላ የንብረት ክፍፍል ሳይደረግ ባለበት ሁኔታ ከአስመጪነትና ላኪነት ከተገኘው ገቢ እዳው ተከፍሎ ያለቀ በመሆኑ ተጠሪ የሚጋሩት እዳ የለም፣ መኪናው የጋራ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2- 21508 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ በተመለከተ አበዳሪ /አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም/ አመልካችና ተጠሪ ተለያይተው መኖር ከጀመሩበት ከጥር 13 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከጠቅላላ ብድር ምን ያህል እንደተከፈለ ተጠይቆ በቁጥር አ/ብ/ቁ/ተ/አ 091466 ሚያዚያ 25 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ማስረጃ ከ13/05/2006 ዓ/ም በኃላ በጥቅሉ ብር 238,469.29 /ሁለት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ስልሳ ዘጠኝ

ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም/ መከፈሉን የገለጸ መሆኑን ተያይዞ ከቀረበልን የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ይህ የመኪና ብድር ገንዘብ የተከፈለው የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የአመልካችና የተጠሪ የንግድ ሥራ የሚሠራበት የአስመጪነትና ላኪነት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በአሁን አመልካች አማካይነት ሲከናወን የነበረ መሆኑን አመልካች አይክዱም፡፡ ይህ ከሆነ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ እንዳስቀመጠውም እዳው የተከፈለው የባልና ሚስት የጋራ ከሆነው ከንግድ ሥራው ነው ተብሎ ግምት የሚወሰድ ነው፡፡ አመልካች እዳው የተከፈለው ከንግድ ሥራው አይደለም፣ ከግል ንብረቴ ወይም ገንዘብ ነው የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ ከዚህ አንጻር አላስረዱም፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን ስለሚከራከርበት ፍሬ ነገር የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 255 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ጋረ በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎትም በሰበር መዝገብ ቁጥር 44634 ላይበፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህም ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ መሠረት በየትኛውም ደረጃ በሚገኙት ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት እንዳለው በግልጽ ተደንግጎ እንመለከታለን፡፡ ስለሆነም አመልካች የመኪናው የብድር ገነዝብ ከፍቺ በኃላ የተከፈለ በመሆኑ ተጠሪ የተከፈለውን ገንዘብ እስካልተከ ድረስ መኪናው የጋራ ሊሆን አይገባም በማለት የሚከራከሩት ክርክር ከላይ በዝርዝር ከተመለከተው አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የሰበር አጣሪውም እዳው በዚህ መልክ የተከፈለ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ክርክርና ይዘት በአግባቡ ሳይመለከት ከፍቺ በኃላ አመልካች የግል ገንዘብ እንደከፈሉ አድርጎ ተጠሪ እዳውን ሳይከፍሉ መኪናውን እንዲካፈሉ መባሉ ተገቢ እንዳልሆነ አድርጎ የያዘው ጭብጥ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የባልና ሚስት ፍቺ ተፈጽሞ የንብረት ክፍፍል እስከሚደረግ ድረስ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ንብረትም ሆነ ከዚህ ንብረት የሚገኝ ገቢ የጋራ ሆኖ እንደሚቆይ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 89 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በሌላ በኩል አመልካች ከአስመጪነትና ላኪነት ጋር በተያያዘ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ሥር ፍርድ ቤት መመለሱ አግባብ እንዳልሆነ በሰበር ቅሬታቸው ያነሱትን አጣሪው በጭብጥነት ያልያዘ ሲሆን ይህ ችሎት ይህን ቅሬታ እንደተመለከተው ከሆነ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን መመለሱ በአግባቡ ነው በሚል ታልፏል፡፡

ሲጠቃለልም የክፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔም ሆነ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ የሚነቀፍ ሆኖ ስላላገኘነው የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 185503 በቀን 28/10/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 146781 በቀን 30/02/2010 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ክርክር ለተነሳበት መኪና የተወሰደ ብድር ገንዘብ ከአመልካችና ከተጠሪ ገቢ የተከፈለ በመሆኑ መኪናው የጋራ ነው ተብሎ የተወሰነው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
5. ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰበር መ/ቁ 148570

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጃኖ ተሰማ -ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አሊ ሰይድ -ቀረቡ፡፡

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአባትነትና የሞግዚትነት ጥያቄን የሚመለከት ክርክር ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአሁኗ አመልካች ላይ በመ/ቁ 50214269 በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሃብሩ ወረዳ ፍርድ ቤት ጥር 08 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች በሀብሩ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁጥር 427/2000 በ17/03/2000 ዓ/ም በዋለው ችሎት የወራሽነትና የሞግዚነት እንዲሁም የሚስት ማስረጃ ያገኙ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ኢብራሂም መሐመድ በሚል ወራሽነት ያሳወጁለት ከአሁኗ አመልካች ጋር በጸና ጋብቻ ውስጥ ሆነው የወለዱትና እያሳደጉ የነበሩ መሆኑን፣ ይህ ሁኖ እያለ አመልካች ህጻኑ ከመሐመድ ሁሴን እንደተወለደና ወራሽ መሆኑን፣ የሌላ ሰው ሚስት መሆናቸውን የህጻኑ ሞግዚት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ የሚይዙበት አግባብ የሌለ መሆኑንና አመልካች እነዚህን ሁኔታዎችን የሚያሳይ ውሳኔ ያገኙ መሆኑን በሌላ ክርክር ጊዜ ማወቅ የቻሉ መሆኑን ጠቅሰው በመ/ቁጥር 427/2000 በ17/03/2000 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ውድቅ እንዲሆንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ጉዳዩ ቀድሞ ታይቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ

www.abyssinialaw.com

ችሎት ጭምር የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት መሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ ተጠሪ መብትና ጥቅምም የሌላቸው መሆኑንና ሕጻኑ የሐጂ መሀመድ ሐሰን ልጅ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ ከአለፈ በኋላ ክርክሩን መርቶ ተጠሪ ማስረጃዎቻቸውን ያሰሙ ሲሆን የአሁኗ አመልካች ግን በተደጋጋሚ ጊዜ ማስረጃዎቻቸውን እንዲያቀርቡ እድሉ ተሰጥቶአቸው ማስረጃዎቻቸውን በራሳቸው ጉድለት ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው ይህንኑ መብታቸውን በማለፍ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኗ አመልካች ህጻኑን ከሟች አቶ መሐመድ ሀሰን የወለዱት ሳይሆን ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ የወለዱት መሆኑ ተረጋግጦአል፣ በጋብቻ ውስጥ ለተወለደ ህጻን ደግሞ የደም ምርመራ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ አመልካች የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 115219 በሆነ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ መሆኑን፣ የአመልካች የማስረጃ ማሰማት መብት የታለፈውም ያላግባብ መሆኑ የሚዘረዝርና ህፃኑ የሟች ሀጂ መሐመድ ሀሰን ልጅ እንጂ ከተጠሪ የወለዱት ያለመሆኑን ጠቅሰው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ በመ/ቁጥር 427/2000 በ17/03/20000 ዓ/ም የተሠጠው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጉዳይ አመልካች ልጃቸው ኢብራሂም መሀመድ ወይም አቡበከር መሀመድ የሟች ሼህ መሀመድ ሀሰን ልጅ ነው፣ ልጁ የማን እንደሆነ የማውቀው እኔ እናቱ ነኝ ሲሉ ተጠሪ ደግሞ ልጁ የእኔ ነው ፣ ከአመልካች ጋር በነበረን ጋብቻ ውስጥ የተወለደ ነው የሚል ሲሆን ይህንን ለመለየት የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ሳይደረግ በጋብቻ ውስጥ በመወለዱ ብቻ የሕግ ግምት ወስዶ ልጁ የተጠሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ከአመልካች ጋር ሕዳር 10 ቀን 1995 ዓ.ም ተጋብተው በመርሳ ከተማ 01 ቀበሌ ይኖሩ እንደነበር፣ በጋብቻ ወቅት ስሙ አቡበከር አሊ /ኢብራሒም አሊ/ የተባለ ወንድ ልጅ ነሃሴ 25 ቀን 1996 ዓ.ም እንደወለዱ፣ ይህ ሁኖ እያለ አመልካች ህጻኑ የሟች ሼህ መሀመድ ሀሰን ልጅ ነው በማለት የወራሽነትና የሚስትነት ማስረጃ መውሰዳቸው አግባብ ያለመሆኑን ጠቅሰው በዚህ ረገድ በመ/ቁጥር 427/2000 በቀን 17/03/2000 ዓ/ም በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻርላቸው መሆኑን፣ ይህን ክስ ሲያቀርቡና ዳኝነት ሲጠየቁም አለኝ የሚሉትን ማስረጃ ከመቁጠራቸውም በላይ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራም ተደርጎ የልጁ አባትነታቸው እንዲረጋገጥላቸው መከራከራቸውን፣ አመልካች ህፃኑን ከተጠሪ እንዳልወለዱት፣ የሕፃኑ ትክክለኛ አባትም ተጠሪ ሳይሆኑ ሟች መሐመድ ሀሰን መሆናቸውን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 115219 በሆነው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሚያዚያ 11 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ይዘቱም አመልካች ከተጠሪ ጋር የእስልምና ሃይማኖት በሚያዘው አግባብ በኒካ መጋባታችን አልተረጋገጠም በማለት ያቀረቡት ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች በሐይማኖቱ ስርዓት በፍሬ ነገር ደረጃ አጣርተው ውድቅ ያደረጉት በሐይማኖት ስርዓት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በሰበር ችሎቱ ተቀባይነት እንዳላገኘ፣የሕፃን አቡበከር /ኢብራሒም/ አባትነት በተመለከተ የሟች ሃጅ መሐመድ ሀሰን ልጅና ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ አስቀድሞ የተሰጠው ማስረጃ በሕጉ አግባብ መቃወሚያ ቀርቦበት ሳይሰረዝ የተጠሪ ልጅ ነው በማለት መወሰኑ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ በክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በፋ/መ/ቁ 38933 በ21/07/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 47160 ሰኔ 09 ቀን 2007 ዓ.ም የጸናው የውሳኔ ክፍል የተሻረ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መስርተው የቆዩ መሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ/ቁጥር 115219

www.abyssinialaw.com

የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት ጉዳይ ሲሆን አመልካች በዚህ መዝገብ ልጁ የተወለደው ከተጠሪ ሳይሆን ከሟች ሐጅ መሃመድ ሁሴን ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ስነ ስርዓታዊ በሆነ አግባብ በዚህ ሰበር ችሎት ተቀባይነት ያገኘ ከመሆኑ ውጪ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ያገኘ አይደለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 115219 በዚህ ረገድ የሰጠው ውሳኔ ህጻኑ የሟች ሃጅ መሐመድ ሁሴን ልጅና ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ አስቀድሞ የተሰጠው ማስረጃ በሕጉ አግባብ መቃወሚያ ቀርቦበት ሳይሰረዝ የተጠሪ ልጅ ነው በማለት መወሰኑ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ከመሻሩ ውጪ ተጠሪ በሕጉ አግባብ የሚያቀርቡትን መቃወሚያ ወይም ክርክር የገደበ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 115219 የሠጠውን ውሳኔ መሰረታዊ ይዘት፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ሙሉ ይዘትና ተጠሪ በሕጉ አግባብ ሊያቀርቡ የሚችሉትን መቃወሚያ ክርክር ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ነጥብ የማስረጃ የማሰማት መብታቸው ያላግባብ ታልፏል የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሰው ምስክሮች እንዲያሰሙ መብታቸው የተጠበቀላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ መብታቸውን ምስክር እስከመቀየር ድረስ ፍርድ ቤቱ ጠብቆላቸው ምስክሮችን እንዲያቀርቡ በተደጋጋሚ ታዘዘው በራሳቸው ጉድለት የተነሳ ሳያቀርቡ በመቅረታቸው የታለፈ መሆኑን የውሳኔው ግልባጭ የሚሳይ በመሆኑና አመልካችም ሕጋዊ ምክንያት ያላቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ሳይኖር የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ስህተት መፈፀሙን በመጥቀስ የሰበር ቅሬታ ማቅረባቸው ተቀባይነት የሚያገኝበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የማስረጃ ማሰማት መብት በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት የሚከናወንና ይህንኑ በህጉ የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት ተደርጎ የተከራካሪ ወገን መብት በፍርድ ቤት ሲጠበቅ ተከራካሪ ወገኑ ሕጋዊ ምክንያትና ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ በራሱ ጉድለት ማስረጃውን ሳያቀርብ የቀረ ተከራካሪ ወገን ማስረጃ የማሰማት መብት አልተጠበቀልኝም በማለት ቅሬታ የሚያቀርብበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተሰጣቸው በቂ ጊዜ ምስክሮቻቸውን ለማቅረብ ያልቻሉት በራሳቸው ጉድለት ስለመሆኑ ተረጋግጦ የማስረጃ ማሰማት መብታቸው የታለፈ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ ይህ ችሎት ሊቀበል የሚችልበትን የሕግ አግባብ ሳላላገኘ አልፈነዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመጣም አመልካች ከአብራካቸው የወለዱት ህጻን ኢብራሒም/አቡበከር/ የተባለ ከሟች ሐጂ መሐመድ እንጂ ከአሁኑ ተጠሪ የወለድኩት አይደለም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ጋር በፀና ጋብቻ ውስጥ ሁነው ህጻኑን የወለዱ መሆኑን በመጥቀስ በሕጉ ግምት የሕጻኑ አባት እኔ ነኝ በማለት የሚከራከሩ መሆኑን፣ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከሕዳር 10 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 26 ቀን 1996 ዓ/ም ድረስ ጋብቻ የነበራቸው መሆኑን፣ በመ/ቁጥር 104/95 በሆነው አመልካች እስከ ሰኔ 18 ቀን 1995 ዓ/ም ድረስ ከሟች ሐጂ መሐመድ ሁሴን ጋር በጋብቻ ውስጥ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡንና ህጻኑ ከሐጂ መሐመድ ሁሴን ሞት በኋላ አንድ አመት ቆይቶ ነሐሴ 25 ቀን 1996 ዓ/ም የተወለደ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤት ህጻኑ የተጠሪ ልጅ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱትም እነዚህን ፍሬ ነገሮችን መሰረት በማድረግና የደም ምርምራ አባት አለመሆኑን ለማረጋገጥ እንጂ አባትነትን ለማረጋገጥ በሕግ የተፈቀደ መንገድ አይደለም፣ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት ነው ተብሎ የሚገመተው እናትዬውን ያስቀመጠው ባል ነው የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ የአንድ ሰው አባትነት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 በአንቀጽ 136 ስር የተመለከቱ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ማድረግ መሆኑ በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ተመልክቷል፡፡ አባትነትን እንዲታወቅ ለማድረግ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች መካከልም አንዱ በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖር መረጋገጡ እንደሆነ በቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 137 ስር ተመልክቷል፡፡ የወረዳው ፍርድ በሰጠው ውሳኔ ላይ የአመልካቹን አባትነት በፍርድ ለማረጋገጥ መሰረት ያደረገውን የክልሉን የቤተሰብ ሕግ ሲሆን ፍርድ ቤት በተጠሪው ምስክሮች በሰ/መ/ቁጥር 115219 እንዲሁም በሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንጻር የተጠሪ አባትነት በሕግ ግምት የሚወሰድበትና በዲ.ኤን.ኤ ምርመራም የሚስተባበልበት አግባብ የለም በሚል ምክንያት መሆኑን ከወረዳው ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አጥብቀው ከሚከራከሩባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ህጻኑ ከሐጂ መሀመድ ሁሴን የተፀነሰ እና ከመወለዱ ጊዜም ሆነ ከተፀነ በኋላ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በመኖር ላይ ያልነበሩ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ክርክራቸውን በማስረጃ ያላስደገፉ ከመሆኑም በላይ ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን የጋብቻ ግንኙነት ጊዜ ያላገናዘበ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ስለመሆኑ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 137 እና 138 ስር ተመልክቷል፡፡ ህጻኑ የተፀነሰው ወይም የተወለደው አመልካች እንደሚከራከሩት ከሌላ ሰው ጋር በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ጊዜ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ውስጥ የነበሩ መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አባትነትን በሕግ ግምት ወይም በመቀበል መንገዶች ለመወሰን ክርክር ሲነሳ የባህሪ ወሳኝ ቅንጣት (DNA) ውጤት እንደ መከላከያ ማስረጃ እንዲቀርብ በሕጉ በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ዳኝነት ሰጪ የሆነው ፍርድ ቤት በሕጉ የተረዘረጋውን ስርዓት ተከትሎና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆኑን ሲያምንበት ተግባራዊ ሊያደርገው የሚችለው መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀፅ 183(1) እና 155(1(ሀ)) ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የዘር የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ ውጤት በሕጉ በተመለከተው አግባብ በሕጋዊ ምክንያቶች ለማስረጃነት የሚቀርብ እንጂ በሕግ የተቀመጠውን ግምት እናት ስለካደች ብቻ ለማስረጃነት የሚቀርብ ማስረጃ ነው ብሎ ድምዳሜ የሚያዝበት አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የዘር የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ ውጤት ለማስረጃነት እንዲቀርብ በስር ፍርድ ቤት ያልጠየቁ ከመሆኑም በላይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሠበር አቤቱታ ላይም ይህንኑ በቅሬታ ነጥብነት ጠቅሰው የጠየቁት ዳኝነት ካለመኖሩም በላይ ይህ ችሎት ግራ ቀኙን በቃል ሲያነጋግራቸውም ተጠሪ ወጣ ገባ ይል ነበር የሚል ቃል ለችሎቱ በማስታወቅ የምራመራ ሂደቱ እንዲከናወን ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን ተጠሪ ግን ፈቃደኝነታቸውን የገለፁ መሆኑ ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡ በዚህም ምክንያት የዘር የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ ሳይደረግ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመሰጠቱን ጉዳይ በተመለከተ አጣሪው ችሎት በጭብጥነት የያዘው የክርክሩን ሂደት

ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ የህፃኑን በሕግ ግምት የተጠሪ ልጅ መሆኑን መሰረት ያላደረገ፣ በክልሉ የቤተሰብ ህግም በአንቀፅ 181 እና 183(1) ድንጋጌዎች በተመለከተው አግባብ ምርመራው እንዲደረግ የሚያስገድዱ ሕጋዊ ምክንያቶች ስለመኖራቸው ያለመረጋገጡን መሰረት ያላደረገ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሟች ሐጂ መሀመድ ሁሴን ጋር እስከ ሰኔ 18 ቀን 1995 ዓ/ም ድረስ ጋብቻ ውስጥ እንደነበሩ ማስረጃ እንዳላቸው፣ ከተጠሪ ጋርም ከህዳር 10 ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ ሕጋዊ ጋብቻ የነበራቸው መሆኑን የጊዜ መደራረብ መኖሩን ተገንዝቦ ሕጻኑ ከሟች ሐጂ መሀመድ ሁሴን ሊወለድ አይችልም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው በሕጉ የተመለከተውን የእርግዝና ጊዜ መሰረት አድርጎ ስለመሆኑ ከውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ የልጅ አባት ነህ ተብሎ በሕግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ300ኛውና በ180ኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ስጋ ግንኙነት ላለመፈፀሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት እንደሚቻል በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 179 ስር የተመለከተ ሲሆን የተጠቃሹ ቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 139 በአንጻሩ ጋብቻ ከተፈጸመ ከ180 በኋላ ወይም ጋብቻው ከፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል በሚል በንኡስ ቁጥር አንድ ስር ከመንደንገጉም በላይ ለዚህ ተቃራኒ የሆነ የማስረጃ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ጭምር አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ በንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በግልጽ አስፍሯል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ከሟች ሐጂ መሀመድ ሁሴን ጋር የነበራቸው ጋብቻ ሰኔ 18 ቀን 1995 በሞት ከፈረሰ በኋላ ህፃኑን ጋብቻው ከፈረሰ በ300ኛው ቀን ውስጥ የወለዱት ሳይሆን ይህ በሕጉ የተመለከተው ጊዜ ከአለፈ በኋላ ነሐሴ 25 ቀን 1996 ዓ/ም የወለዱ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በተጠቃሹ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 139(2) ድንጋጌ አግባብም ተቃራኒ ማስረጃ ለማቅረብ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ አመልካች የሕጻኑን ከተጠሪ መወለድ ክደው የሚከራከሩ መሆኑ ሲታይም የመካድ ክርክር እያቀረቡ ያሉ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ሁኔታ ልጁ የተጠሪ ልጅ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ተገቢነት የሌለው መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀፅ 185(5) እና 190 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የምንረዳው ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ ህፃን አቡበከር /እብራሒም/ ከአመልካች ወልደዋል ተብሎ የህጻኑ አባት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻልበትን የሕግ አግባብ ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሐብሩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0124269 በ29/07/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2112 በ28/09/2009 ዓ/ም ፤ በአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በሰ/መ/ቁ 03-19077 ሐምሌ 24 ቀን 2009ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡፡
2. የስር ፍርድ ቤቶች ሕፃን አቡበከር /ኢብራሒም/ የተጠሪ ልጅ ነው በማለት በሰጡት ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

www.abyssinialaw.com

የመ/ቁጥር 152719

መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርቱካን ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሺእመቤት ታደሰ ከጠበቃ አበበ ማስረሻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን የሻለቃ ታደሰ በላይነህ ልጅነትን በመቃወም ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኗ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥር 27 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የአመልካች የክስ ይዘት ሲታይም፡- ወላጅ አባታቸው ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህ ከወላጅ እናታቸው ከወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ ጋር በጋብቻ ውስጥ ሁነው በ 1964 ዓ/ም የወለዷቸው መሆኑን፣ የልደት ምስክር ወረቀትም ያላቸው፣ ከቤተሰቦቻቸው አሳድገው፣ አስተምረው የዳሯቸው መሆኑን፣ በሰፈር፣ በቤተዘመድ እና በወረዳም ልጅ ለመሆናቸው የሚታወቁ መሆኑን፣ ወላጆቻቸው ሲሞቱም ወራሽነታቸውን ሲያረጋግጡ የአሁኗ ተጠሪ በመቃወማቸው የወራሽነት ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት አመልካችን ልጅነታቸውን አረጋግጠው እንዲቀርቡ በማዘዙ ምክንያት ክሱን ለማቅረብ የተገደዱ መሆኑን ጠቅሰው

የሁለቱም ሟቾች ልጅ መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ የልጅነት ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪም ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ እንዲፈቀድላቸው በ17/07/2006 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ ጠይቀው ከተፈቀደላቸው በኋላ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መነሻ አሻሽለው ባቀረቡት ክርክር ሟቾች ባልና ሚስት ቢሆኑም መሃን መሆናቸውን፣ አመልካች የሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ የወንድም ልጅ መሆናቸውን፣ ሟቾች ለተጠሪ ኑዛዜ ትተውላቸው ተጠሪ በፍርድ ቤት እንዲፀድቅ ማድረጋቸውንና አመልካች የሟቾች ተወላጅ ባልሆኑበት ሁኔታ ተጠሪ በሟቾች ኑዛዜ ወራሽነት ተጠቃሚ የሆኑበትን የውርስ ንብረት የሚጠይቁበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ለዚህ ክርክራቸው አሉኝ የሚሏቸውን የሠውና የሠነድ ማስረጃ ዘርዝረው ከማቅረባቸውም በተጨማሪ በ26/08/2008 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻም የዲ.ኤን.ኤ ምርምራ እንዲደረግ ትዕዛዝ እንዲሰጣቸው አመልክተው ፍርድ ቤቱም በ25/1/2/2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተጠሪን የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ጥያቄ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎ ብይን ሰጥቷል፡፡

ከዚህም በኋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የሟቾች ልጅ መሆናቸውን በሰውና በሰነድ ማስረጃ ሲያስረዱ ተጠሪ ይህንኑ አላስተባበሉም በሚል ምክንያት አመልካች የሟች ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህና የሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ ልጅ ናቸው በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ የታለፈው ሕጋዊ ባልሆነ ምክንያት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮ የአሁኗ አመልካች ከአቶ ገዛኸኝ በቀለ ጋር የዘረመል /D.N.A/ ምርመራ እንዲያደርጉ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲሰጥና የምርመራ ውጤቱ ሲቀርብለት የመሰለውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም

ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ የዲ.ኤን.ኤ ምርምራ ጥያቄ መጀመሪያ በሕጉ አግባብ ያላቀረቡና ጥያቄውን ከአቀረቡ በኋላም ምራመራው ከማን ጋር እንደሚከናውን የተለያዩ አቋም ይዘው ሲከራከሩ የቆዩ ከመሆናቸውም በላይ ከአመልካች ጋር ምርመራ እንዲያደርግ የታዘዘው ግለሰብም ፍርድ ቤቱ በምስክርነት የሰማውና የአመልካችን ተወላጅነት ያረጋገጠ ሁኖ እያለ ተገቢ ባልሆነ ስነ ስርዓትና ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንዲሚከተለው መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥም ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ የዘረ መል ምርመራ እንዲደረግ ባልጠየቁበት ሁኔታና እንዲሁም አመልካች የዘረ መል ምርመራ አብረው እንዲያደርጉ የተባለው ግለሰብ ከሟች ጋር ያለው የቅርብ ዝምድና ሳይጣራ የዘረመል መርምራ እንዲደረግ የመታዘዙን አግባብነት የሚመለከት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ከሟች ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህና ከወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ በጋብቻ ውስጥ ተወልጄአለሁ በሚል ይኼው በፍርድ እንዲረጋገጥላቸው መሆኑንና የአሁኗ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ተደርጎ ሟቾች ልጅ መውለድ የማይችሉና አመልካችም ከሟቾቹ ያልተወለዱ መሆኑን፣ ተጠሪ ከሟቾቹ የኑዛዜ ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን፣ ግራ ቀኙ አሉን የሚሏቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎቻቸውን ከማቅረባቸውም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ፍሬ ነገሩን ተገቢ ነው ባለው መንገድ ያጣራ መሆኑን፣ የአመልካች የሰው ምስክሮችም ሆኑ በተጠሪ በፍርድ ቤት ማጣሪያነት ቀርቦ እንዲመሰክር የተጠየቀው ምስክርም በማጣሪያ ምስክርነት ቀርቦ አመልካች የሟቾች ልጅ መሆናቸውን እንደሚያውቁ የመሰከሩ ሲሆን አመልካች በሰነድ

www.abyssinialaw.com

ማስረጃነት በ15/04/2006 ዓ/ም የተሰጣቸውን የልደት ምስክር ወረቀት፣ ሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ አባል መሆናቸው ከተረጋገጠው ከምስራቅ በር እድር የቀረበው ሰነድም አመልካችን የእድርተኛ አብራክ ልጅ በሚል ተመዝገበው የሚገኙ መሆኑን እንደሚያሳይ፣ ከክፍሉ ቀበሌ የቀረበው የቤተሰብ ቅጽም አመልካች ልጅ ተብለው የተመዘገቡ መሆኑን እንደሚያሳይ፣ ከኮሪያ ዘማቾች የቀረበው ቅጽም አመልካችና ተጠሪ ልጅ ተብለው የተመዘገቡ መሆኑን እንደሚያሳዩ፣ በአመልካች በኩል የተሰሙት አራት የሰው ምስክሮች አመልካችን ሟቾች ያሳደጓቸው እንጂ ያልወለዷቸው መሆኑን፣ አመልካች አሉኝ የምትላቸው የኑዛዜ ተጠቃሚነት ሰነዶች ሲታይም ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህ በ13/03/94 ዓ/ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ በመ/ቁጥር 300/97 በ6/6/97 ዓ/ም በፍርድ ቤት የጸደቀ መሆኑን፣ ሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ በ13/1/95 ዓ/ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ደግሞ በመ/ቁጥር 38093/05 በ1/12/05 ዓ/ም ፀድቆ የነበረ ቢሆንም በአመልካች ተቃዋሚነት በ17/11/06 ዓ/ም የተሻረ መሆኑን የሚያስገነዝቡ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈሩን ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካችን የሟቾች ልጅነት ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄን ጣልቃ ገብተው ሲቃወሙ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ጥያቄ ያላቀረቡ መሆኑን፣ በ06/11/2007 ዓ/ም በስር ፍርድ ቤት ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታም በሟች ሻለቃ በሻ ታደሰ በላይነህ እና በአመልካች መካከል የዘረ መል ምርመራ እንዲካሄድ የሚል ሲሆን በዚህ የተጠሪ ጥያቄ ላይ አመልካች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ አመልካች በ15/10/2008 ዓ/ም በሰጡት አስተያየት ተጠሪ ጣልቃ ለመግባት በጠየቁበት ማመልከቻ ያልጠየቁትና ስነ ስርዓታዊ ያልሆነ ጥያቄ መሆኑን፣ ሐምሌ 06 ቀን 2007 ዓ/ም አቀረብኩ ላሉት አቤቱታም አቶ ገዛኸኝ በቀለ በምስክርነት እንዲሰሙና ከአመልካች ጋር የዘረመል ምርምራ እንዲያደርጉ በማለት የጠየቁት ጥያቄም ግለሰቡ በማስረጃነት የተሰሙ በመሆኑና ግለሰቡ ከአመልካች ጋር የዘረመል ምርመራ ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለመኖሩን ገልጸው የተከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ከአንድ አባትና እናት መወለዱን በሕግ አግባብ በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚቀርበውን ክስ መቃወም የሚቻለው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ነው፡፡ በአባት በኩል ያለውን መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ ወይም ክርክር በሚቀርብበት አግባብ ስለመሆኑ ከተሸሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992

www.abyssinialaw.com

ከአንቀጽ 167 -179 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የመካድ ክሱ የሚቀርበው አባት ነህ የተባለ ሰው ራሱ መሆኑ የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 174 ያስቀመጠ ሲሆን እርሱ የሞተ ወይም ችሎታ ያጣ ከሆነ ደግሞ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 177 የተጠቀሱት ሰዎች እንደቅደም ተከተላቸው መሆኑን ነው፡፡ በሕጉ ከተመለከቱት ከእነዚህ ሰዎች ውጪ የመካድ ክስ ሌላ ሰው ሊያቀርብ የማይችል መሆኑን፣ በሕጉ የተፈቀደላቸው ሰዎች የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችሉትም የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 171 መሰረት የፍርድ ቤት ፍቃድ ሲያገኙ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ በሕጉ የተመለከተው ፈቃድ የማግኘት ጉዳይ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ህጉ በእናትና በልጁ ያለው ግንኙነት እናትነት ለማረጋገጥ በመወለድ ብቻ እንደሆነ፣ ነገር ግን ይህን ሊሰተባበል አይቻልም ለማለት እንደማይቻል በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 163 ይደንግጋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህን ለማስረዳት ተጨባጭነት ያለው ተግባር መኖሩን ካልረተጋገጠ በቀር ሊፈቅድ እንደማይቻል በተጠቃሹ ሕግ 164/2/ ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሟች ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህ እና ሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተወለዱ መሆኑን አመልካች ገልፀው ተከራክረው በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት ምስክሮቻቸው ይህንኑ የመሰከሩላቸው ከመሆኑም በላይ ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች የቀረቡ ሲሆን ይህንን የሚያስተባብል ማስረጃ ተጠሪ ያለማቅረባቸውን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት ባልየው ስለመሆናቸው የሕግ ግምት መኖሩን ከተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሠብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 126 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በሕግ የልጁ አባት ነው የተባለው ሠው የልጁ አባት ሊሆን እንደማይችል በማያጠራጥር አኳኋን በማስረዳት ለመካድ እንደሚችልና በዚህ መሠረት የሚቀርበው የመካድ ክስ ግን ፍ/ቤት ካልፈቀደና ሊቀርብ እንደማይችል ከተሻሻለው የቤተሠብ ሕግ አንቀጽ 170 እና 171/1/ ድንጋጌ በግልጽ መረዳት ይቻላል፡፡ የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሠብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 176/1/ የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው 180 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት የሚል ይዘት ያለው ሲሆን በድንጋጌው "...በተለይ ማወቅ ከሚገባው...." የሚለው የድንጋጌው አገላለጽ የልጁን መወለድ ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ ተብሎ የሚተረጐም መሆኑን

የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ልጁ በሕጉ ግምት መሰረት አባት የተባለው ሰው ልጅ ያለመሆኑን በማናቸውም ጊዜ ወሬ ከሠማበት ወይም ጥርጣሬ ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ በሚል የተቀመጠ ባለመሆኑ የመካድ ክስ በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ ነው ተብሎ የማይወሰድ መሆኑን ሕጉ ያሳያል፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተወለደን ልጅ ባልየው አባት ነው ብሎ የተወሠደው የሕግ ግምት ጥብቅ ድንጋጌ በመሆኑ አባት አይደለም የሚል ጥያቄ ሲነሣ ይህንን በሚያጠራጥር አኳኋን ማስረዳት እንደሚጠበቅበትና የመካድ ክስ ለማቅረብ እንኳ የፍ/ቤት ፈቃድ እንደሚያስፈልግ መደንገጉ ሲታይ ሕጉ በጋብቻ ውስጥ የተወለደን ልጅ በማናቸውም ጊዜ ማንኛውንም ምክንያት በማቅረቡ መካድ እንዳይኖር ከፍተኛ ጥበቃ ያደረገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ የሕጉ ጥብቅ ድንጋጌ እና ጥበቃ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ልጆች በወላጆቻቸው ተገቢ ባልሆነ ምክንያት ተክደው ወላጅ አልባ ሆነው እንዳይቀሩ፣ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዳይዳረጉ፣ በቤተሠብ መካከል የሚፈጠረውም ያለመተማመን ማህበራዊ ምስቅልቅሎች እንዳይፈጥር በወላጆችና በተወላጆች መካከል ለሚፈጠሩ መብቶችና ግዴታዎችን በአግባቡ ለማስተናገድ ሥርዓት ለማስያዝ ጭምር ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳይ በዕጃችን የተያዘው ጉዳይ ሲታይም የአሁኑ ተጠሪ አመልካች የሻለቃ ታደሰ በላይነህ ልጅ አይደሉም በማለት ተቃውሞአቸውን ለስር ፍርድ ቤት ሲያቀርቡ ከላይ በተጠቀሰው ህግ መሠረት አስቀድሞ የፍርድ ቤት ፍቃድ አላገኙም፤ በተጨማሪም ተጠሪ የኑዛዜ ተጠቃሚ ከመሆናቸው ውጪ በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 174 እና 177(3) ውስጥ ከተዘረዘሩት የመካድ ክስ ለማቅረብ ከተፈቀደላቸው ሰዎች ውስጥ የሚካቱ አይደሉም፡፡

አመልካች የሚች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ ልጅ ነኝ በማለት ያቀረቡትን ክርክር ተጠሪ የሚቃወሙበትን አግባብ ስንመለከተውም እናትነትን ለማስረዳት በተጠቃሹ አዋጅ ውስጥ ከአንቀጽ 163-166 ስር ስርዓቱ ተዘርግቷል፡፡ ይዘታቸውም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡ በእናት በኩል ያለው ተወላጅነት በማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ክርክር ሊደረግበት እንደሚችል ህጉ በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን የተጠቃሹ ህግ አንቀጽ 164 ድንጋጌ በተለይ ሲታይም በተወላጅነት ላይ ስለሚደረገው ክርክር የሚቀርበው

www.abyssinialaw.com

ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ የማይችል መሆኑን በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ስር ሲያስቀምጥ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ በተወላጅነት ላይ ክርክር ለማድረግ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉት ተጨባጭነት ካላቸው የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው በሚል አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጦ ይገኛል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 165 ድንጋጌም ልጁ ተወላጅነቱን የሚያረጋግጥ የልደት ምስክር ወረቀትና ከዚህ ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ በተወላጅነቱ ላይ ለመከራከር ፈቃድ አይሰጥም በሚል በኃይለ ቃል ደንግጓል፡፡ እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 166 ንዑስ ቁጥር አንድ በተወላጅነት ምክንያት የሚቀርበው ክስ በተወላጅነቱ ላይ ክርክር በተነሳበት ሰው ላይ ወይም በወራሾቹ ላይ ሊመሰረት እንደሚችል ያሳያል፡፡

ከእነዚህ ድንጋጌዎች አቀራረፅ፣ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የአንድ ልጅ እናት እገሊት አይደለችም ወይም እኔ ነኝ የሚለው ክርክር የሚነሳው የመወለድ የምስክር ወረቀት ከሌለ ወይም የልጅነት ሁኔታ በሌለ ወይም ይህ ሁኔታ ክርክር የቀረበበት እንደሆነ ስለመሆኑ ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት የሕጉ ድንጋጌዎች ተወላጅነት ላይ የሚነሳን ክርክር የሚገዙ ሲሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 154 እስከ 162 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ስለልጅነት ማስረጃ /Proof of Filiation/ የሚገዙ እና ተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር አግባብነት ካላቸው ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተለዩ ስለመሆኑ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡

በመሠረቱ ስለልጅነት ቀዳሚ ማስረጃ የልደት ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 154 የሚያስገነዝብ ሲሆን የልደት ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ልጅነት እንደሚረጋገጥ በተጠቀሰው አዋጅ በአንቀጽ 155 ስር የተመለከተ ሲሆን የልጅነት ሁኔታ መኖር የሚለው ትርጉም ደግሞ አንድ ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 156 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ አኳኋን የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ልጅ ነው ሲል የሕግ ግምት እንደሚወስድ፣ የሕግ ግምቱ ልጁ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል ሊፈርስ

www.abyssinialaw.com

እንደሚችል በአዋጅ አንቀፅ 157 ንዑስ ቁጥር አንድና ንዑስ ሁለት ስር እንደቅደም ተከተሉ ተመልክቷል፡፡

የደም ምርመራ ( DNA) አንድ ሰው የልጁ አባት ወይም እናት አይደለም ለማለት የሚቀርብ ማስተባባያ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ቢሆንም ይህ የሚከናወነው ደግሞ አባትነትን በሚመለከት የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚያስችሉ ቀዳሚ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፣ እናትነትን በተመለከተም በተጠቃሹ ህግ ከአንቀፅ 153 እስከ 166 ድረስ የተዘረጋው ስርዓት የሚፈቅድ ሁኖ በፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱትን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓቶችን መሰረት በማድረግ ሊቀርብ የሚገባ ነው፡፡

እንግዲህ በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ይዘን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የስር ፍ/ቤት አመልካች ሕግ ጥበቃ በሚያደረገው ጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑንና ሟች ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህና ሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ በጋብቻ ውስጥ ሁነው አመልካችን መወለዳቸውን በአረጋገጠበት ሁኔታና በዚህ ግንኙነት ውስጥ የሚወለድ ልጅ አባት ተብሎ በሕጉ ግምት የሚወሰድበት ከልጁ እናት ጋር የተቀመጠው ወንድ መሆኑ፣ ይህ የህግ ግምት የሚፈርስበት አግባብም የመካድ ክስን በማቅረብ ሁኖ ክሱን ወይም መቃወሚያውን ለማቅረብ የሚችሉ ወገኖች ማንነትና ማቅረቢያ ጊዜውም በህጉ ተለይቶ ከመቀመጡም በላይ የመካድ ክስ እንዲቀርብ የሚፈቀደው በማያጠራጥር ሁኔታ ልጁ ከተወለደበት ወደኂላ ሲቆጠር በ300 እና 180 ቀናት ዉስጥ ከልጁ እናት ጋር ሩካቤ ሥጋ ግኙኝነት ያለመፈጸሙን ሲረጋገጥ ወይም በሌላ ማስረጃ የልጅ አባት መሆን አለመቻሉም ሲያሰረዳ አባት መሆኑ በሕጉ ጥብቅ በሆነ አግባብ ተመልክቶ እያለ፣ እንዲሁም ሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበም በሕጉ ከአንቀፅ 163 እስከ 166 አግባብ ተጠሪ መቃወሚያ ለማቅረብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተገኝተው ፍርድ ቤቱ ፈቃዱን ባልሰጠበት ሁኔታ ከማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ውጪ፣ አመልካች ምርመራ እንዲያደርጉ የታዘዘው ግለሰብም በፍርድ ቤት ቀርቦ የአመልካችን ተወላጅነት ባረጋገጠበትና የዚህ ግለሰብ ዝምድናም ከሁለቱም ሟቾች ጋር ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለምንም መነሻ የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ እንዲደረግ ተጠሪ ጥያቄ በሕጉ አግባብ አቅርበዋል ወደሚል ድምዳሜ ደርሶ የደም ምርመራ እንዲረግ ማዘዙ ከመነሻውም በሕጉ የተመለከተውን ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ በሕጉ ከተዘረጋው

www.abyssinialaw.com

ስርዓት ውጪ እንዲከናወን ተደርጎ የነበረው ምርመራ ታልፎ በጉዳዩ ላይ በቀረቡት የሰውና የሰነድ ማስረጃ የአመልካች የሚኞች መሆናቸው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መወሰኑ ከውጤት አንጻር የሚነቀፍበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት፣ የስር ፍርድ ቤት ግን በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን መዝኖ አመልካች የሚኞች ልጅ ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 182625 ጥቅምት 17 ቀን 2010 ዓ/ም የሠጠው እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 150307 በ9/5/2010 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 21544 በ25/12/2008 ዓ/ም የሠጠው ብይንና ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትእዛዝ

11/07/2010 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.152968

መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች፡-** ሲ/ር ሐምዚያ ሱለይማን -ቀረቡ::

**ተጠሪ፡-** አቶ አያሌው በቀለ-ጠበቃ ኩራባቸው ጎሳ ቀረቡ::

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ አዳማ ልዩ ዞን በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በቀን 14/02/2009 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በ1983 ዓ.ም ጀምሮ በባህል ተጋብተው ሲኖሩ አራት ልጆች ማፍራታቸው በመግለጽ አመልካች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ባህሪያቸው ስለቀየረ በተለያዩ ጊዜያት የሚደበድቧቸው፤የሚሰድቧቸው እንዲሁም የማያከብሯቸው በመሆኑ ጋብቻው ፈርሶ በጋራ አብረው ያፈሩት ንብረት ድርሻቸው እንዲወስነላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ራሷ ባህሪዋን ለውጣ እኔ ያልፈጸምኩት ድርጊት ፈጽመሃል በማለት እኔን መክሰሷ

ትክክል አይደለም በማለት ትዳራችን በአመልካች ጥያቄ እና ፍላጎት በመሆኑ በእርሷ ምክንያት የሚፈርስ መሆኑ ተቆጥሮልኝ የሞራል ካሳ እንድትከፍለኝ በማለት ለአቤቱታው መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ ነገር ግን አመልካች የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት መዝገቡ ለጊዜው እንዲዘጋ በማመልከታቸው ምክንያት የማንቀሳቀስ መብታቸው በመጠበቅ ተዘግቶ የነበረ ሲሆን አመልካች የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስ በቀን 24/08/2009 ዓ.ም በተፃፈ ስለአመለከቱ ፍርድ ቤቱም ተዘግቶ የነበረው መዝገብ እንዲቀሳቀስ በማድረግ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ በቀን 28/09/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ካደረገ ለጋብቻው መፍረስም ተጠሪ ምክንያት በመሆኑ በጋራ አፍርተው ካላቸው ንብረት ውስጥ ከተጠሪ ድርሻ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲያካፍል እንዲሁም የሁለት ልጆች ቀለብ በወር ብር 1,500.00/ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በማሻሻል በተከራካሪዎች መካከል የነበረው ጋብቻ በተጠሪው ጥፋት በመፍረሱ በጋብቻ ውስጥ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲያካፍል በማለት የተሰጠው ወሳኔ ውድቅ በማድረግ የልጆች ቀለብ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 26 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ

www.abyssinialaw.com

ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች ጥያቄ ልጆችን ለማሳደግ ደፋ ቀና ብዬ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት አካል ጉዳተኛ ልጅ በሰው እርዳታ የሚኖር አሸብር አያሌው የሚባለውን ለማሳደግ በጥረት ላይ እያለሁ እና አቅመ አዳም ያልደረሱ አዳን እና ኢለያላ አያሌው የሚባሉትን ለማሳደግ እና ለማስተማር በጥረት ላይ እያለሁ ይህ ተጠሪ በየጊዜው ረብሻ እየፈጠረ አፀያፊ ቃላት እየተናገረ ለዚህ ሁሉ ለትዳር መበተን ዋና ተዋናይ እራሱ ሆኖ እያለ፤እንዲሁም ከእኔ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረን ወይም ተጋብተን እየኖርን እያለን ከትዳር ውጭ ከሌላ ሴት ጋር በፈጸመው የግብረ ስጋ ግንኙነት አንድ ልጅ የወለደ ለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በማያሻማ ተመስክሮበት መከላከል ያልቻለ ስለሆነ በገንዘብ መቀጮ ተቀጥቶ እያለ ምንም አይነት ጥፋት እንዳልፈጸመ ሰው ንብረቱን እኩል እንድንካፈል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት የተካሄደውን ክርክር እና ያቀረብኩትን አቤቱታ መርምሮ ከተጠሪ ድርሻ 20% /ሃያ በመቶ/ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል የተወሰነው የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ መደረጉ ምንም አይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 የፍቺው ምክንያት ለፍቺው አስፈላጊ ባይሆንም ለውጤቱ በተለይም ለጋራ ንብረት ክፍፍሉ ግን ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ለፍቺው የተጠየቀው አንደኛው ወገን በፈፀመው ዝሙት ወይም ድብደባ ምክንያት ከሆነ ፍቺው ተወስኖ በሚደረገው የንብረት ክፍፍል ወቅት ንብረቱ በእኩል መከፋፈሉ ቀርቶ ይህንኑ ጥፋት ግምት ውስጥ ያስገባ ክፍፍል ማድረግ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 111 ከባልና ከሚስት ባንዱ የተፈጸመውና ለፍቺው ምክንያት ሆኖ የተገኘው ጥፋት በሌላው ተጋቢ ላይ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ በዳዩ ላደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ መሰረት ከጋራ ንብረት በካሳ መልክ ያንደኛውን ተጋቢ ድርሻ አብዛኛውን

ወይም ሙሉውን በደል ለተፈጸመበት ወገን እንዲከፈል ሊወሰን ይችላል በማለት ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በርግጥ በፍቺ ወቅት የሚኖረው የጋራ ሀብት ክፍፍል በአንጽ 117 እንደተመለከተው የጋራ ሀብቱ ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አንቀጽ 111 የአንቀጽ 117 ልዩ ሁኔታ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች የፍቺ ውሳኔ እንዲሰጥ አቤቱታ ሲያቀርቡ እንደምክንያት ያቀረቡት ተጠሪ ባህሪያቸው በመቀየር በተለያዩ ጊዜያት የሚደበድቧቸው፤ የሚሰድቧቸው እና የማያከብሯቸው ከመሆናቸውም በላይ ከትዳር ውጭ ከሌላ ሴት ጋር በፈጸሙት የግብረ ስጋ ግንኙነት አንድ ልጅ የወለዱ መሆናቸው በዚህ ተግባራቸውም በአፋር ክልል ሎጊያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.392/2009 በቀን 12/07/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጥፋተኛ በማለት በገንዘብ መቀጮ የቅጣት ውሳኔ የተወሰነባቸው መሆኑን በተጠሪ ከመታመኑም በላይ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶችም ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፍረስ በተጠሪ ጥፋት መሆኑና በአመልካች ጉዳት ስለመድረሱ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ለአመልካች ካሳ የማይከፍሉበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.269768 መጋቢት 7 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና ተጠሪ የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ እና ተጠሪ ለልጆች ቀለብ በወር ብር 1,500.00/አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች ካሳ ሊከፍል አይገባም ሲል የሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.101604 ግንቦት 28 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ውስጥ በተከራካሪዎቹ መካከል የነበረው ጋብቻ በተጠሪ ጥፋት በመፍረሱ በጋብቻ ውስጥ በጋራ ከተፈራው ንብረት ውስጥ ተጠሪ

www.abyssinialaw.com

ከድርሻው ውስጥ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት የተሰጠው ውሳኔ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.26872 ሰኔ 21 ቀን 2009 ዓ.ም በትእዛዝ ያጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. በቀን 17/08/2010 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፣ ይፃፍ፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ ቁጥር 147930

ቀን 28/9/2010 ዓ/ም

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች:- ወ/ሮ ሰብለ ታምራት - ከጠበቃ ቤተልሄም አያሌው - ቀርበዋል

ተጠሪ:- አቶ ግሩም ግዛቸው - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መስከረም 29 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 193012 ሐምሌ 5 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 117619 ህዳር 21 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች በጋብቻ ውስጥ ስለተፈራው መኪና ገቢ በተመለከተ በማስረጃ አረጋግጩ እያለ መታለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተደረገ የብድር ውል ከአሁን አመልካች እውቅና ውጪ

የተደረገ በመሆኑ ውድቅ መደረግ ሲገባው የጋራ እዳ መባሉ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ባቀረበችው ክስ ከተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ጋር ያለን ጋብቻ ፈርሷል፡፡ በጋራ ያፈራነው ንብረት 1. መኪና የሰ/ቁጥር 3-26589 ኦሮ 2. የመኪና ገቢ በቀን 600 በወር 18000 የሾፌር ተቀንሶ ከ17/5/2006 ዓ/ም ጀምሮ ያለው 3. 20/80 የቤቶች ፕሮግራም በንግድ ባንክ የተቆጠበ ገንዘብ 4. ብር 186000 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቆጠበ 5. 61000 የእቁብ ገንዘብ ያካፍለኝ ስትል ጠይቃለች፡፡ ተከሳሽም መኪና የሰ/ቁጥር 3-26589 ኦሮ. የሆነ በብድር ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ ብድሩ የጋራ እዳ ይሁን፡፡ ብር 180000 የተበደርነውን እዳ ያልከፈልን ስለሆነ የጋራ እዳ ነው ይባልልኝ፡፡ የቤት ቁሳቁስ ጠቅሶ የየግላቸው የሆነውን ለይቶ መካፈል እንደሌለበት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 117619 ህዳር 21 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መኪና የሰሌዳ ቁጥር 3-26589 ኦሮ. በትዳር ውስጥ የተገዛና ከእዳም ነጻ መሆኗን በምስክሮች በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው፡፡ የመኪና ገቢ አመልካች ለግል ጥቅሙ ያዋለው መሆኑን ከሳሽ ያላስረዳች በመሆኑ ታልፏል፡፡ ለኮንዶሚንየም ቤት የተጠራቀመ ገንዘብ የጋራ መሆኑን በተማመኑት መሰረት ይካፈሉ፡፡ የእቁብ ብር 40447.37 መኖሩ ተረጋግጧል እኩል ይካፈሉ፡፡ ተከሳሽ ብር 180000 የብድር እዳ የጋራ ይባልልኝ ያለው በተመለከተ በሰው ምስክሮች ብድሩ መኖሩ በመረጋገጡ የጋራ እዳ ነው፡፡ የቤት ቁሳቁስ ተዘርዝሮ የጋራ የሆኑትን የጋራ የግል ናቸው ያለውን የግል ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በመ/ቁጥር 193012 ሐምሌ 5 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የብድር ውሉ በአበዳሪው ብቻ ምስክር አመልካች ስለ ብድሩ ያውቁ ነበር መባሉ የብድሩ ድንጋጌዎች መስፈርት ያሟሉ መሆን አለመሆኑን እና የመኪናው ገቢም ሙሉ በሙሉ መኪናው ካልተሸጠ አይከፈልም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት

www.abyssinialaw.com

ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ታህሳስ 20 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የመኪና ገቢ በተመለከተ መኪናው የተሸጠው በ14/6/2006 ዓ/ም ሲሆን የሽያጭ ውሉ የፈረሰው በ26/2/2007 ዓ/ም መሆኑን አመልካች ገልጻ እያለ ከ17/5/2006 ዓ/ም ጀምሮ የመኪና ገቢ ያካፍለኝ ብላ መጠይቋ ተገቢ አይደለም፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተበደርነው ብድር ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆኑ የቤተሰብ ህጉ ግምት የሚያስቀምጥ ሆኖ እያለ እና አመልካች ለትዳር ጥቅም ያልዋለ መሆኑን ባለማስረዳቷ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ጥር 9 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም 1ኛ. የሰሌዳ ቁጥር 3-26589 ኦሮ. የመኪና ገቢ በተመለከተ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠው መኪናዋ ተሸጣ እንደነበረና የተሸጠችውም በ14/6/2006 ዓ/ም መሆኑን የዚች መኪና የሽያጭ ውሉ ደግሞ በ26/2/2007 ዓ/ም የፈረሰ መሆኑን ነው፡፡ የአሁን አመልካች የዚች መኪና ገቢ ግማሹ እንዲከፈለኝ ሲሉ የጠየቁት ከ17/5/2006 ዓ/ም ጀምሮ ያለውን በቀን 600 ብር ትከራያለች በሚል ሲሆን መኪናውን የተከራየው ራማ ኮንስትራክሽን ከ23/7/2006 ዓ/ም ጀምሮ 600 ብር ከአቶ ዳንኤል ቱፋ ላይ የተከራየ መሆኑን አሳውቋል፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች የመኪናዋ ገቢ ይከፈለኝ ስትል በጠየቀችበት ቀን በፊት በ14/6/2006 ዓ/ም ጀምሮ መኪናዋ የተሸጠችና የሽያጩም ውል በ26/2/2007 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ አመልካችና ተጠሪ መኪናዋን ያስመለሱ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር አለመኖሩና የአሁን ተጠሪ የመኪናዋን ገቢ መሰብሰቡ ባለመረጋገጡ የመኪናዋ ገቸ የነበረው ገቢዋን ሰብስቦ ከሆነም ከውሉ ጋር በተያያዘ የሚታይ ከሚሆን በቀር የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው ማለፉ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ 2ኛ. በስር ፍ/ቤት 180000 ብር የብድር

www.abyssinialaw.com

እዳ የጋራ እዳ ነው የተባለበትን ውሳኔ በተመለከተ ከ500 የኢትዮጵያ ብር በላይ የብድር ውል በጽሁፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም በመሐላ ካልሆነ በስተቀር ማስረዳት እንደማይቻል በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2472 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የአሁን ተጠሪ 180000 ብር ብድር የአሁን አመልካችና ተጠሪ አብረን ተበድረናል ሲል ለማስረዳት ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ በብድሩ ውል ላይ ያለው ፊርማ የአሁን አመልካች ፊርማ እንዳልሆነ በፎረንሲክ ምርመራ ተረጋግጧል፡፡ በብድር ውሉ ላይ ያሉት ሁለት ምስክሮችም ስለመመስከራቸው አያመለክትም፡፡ እንዲሁም የአሁን ተጠሪ መጀመሪያ ባቀረበው ክስ ጋር ያላቀረበውን ማስረጃ ባሻሻለው ክስ ጋር አያይዞ ማቅረቡም የብድር ውል ሰነዱን ህጋዊነት የማያሳይ ነው፡፡ ሌላው የአሁን ተጠሪ ብር 180000 ከአቶ ገናናው ተናገር ተበደርኩ የሚለው በ4/5/2006 ዓ/ም ሲሆን የአሁን አመልካች ከቤት የወጣችው በ17/5/2006 ዓ/ም መሆኑና በ18/11/2006 ዓ/ም በመሀላቸው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን ተበድሬያለሁ ከሚልበት ከ4/5/2006 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች ከ12 ቀን በኋላ በ17/5/2006 ዓ/ም ከቤት ወጥታለች፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን የተበደረው ለመኪና ማስጠገኛ መሆኑን ገልጾ ለመኪናዋ ማስጠገኛ ስለማዋሉ ግን ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪ መሀከል አለመግባባት በተፈጠረበት ጊዜ ውስጥ የአሁን ተጠሪ የተበደረው የ180000 ብር ብድር ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ መረጋገጥ አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት የስር ፍ/ቤት ብድሩ ስለመኖሩ የአሁን ተጠሪን ማስረጃ አበዳሪውን የሰው ምስክር ብቻ ሰምቶ የአሁን አመልካችና ተጠሪ ብድሩን ስለመበደራቸው አረጋግጫለሁ ሲል የጋራ እዳ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ፍሬነገር የማጥራትና ማስረጃን የመመዘን መርህ ባለመከተል የተሰጠው ውሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 193012 ሐምሌ 5 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 117619 ህዳር 21 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የብር 180000 ብድር እዳ የባልና ሚስት የጋራ እዳ መሆኑ ባለመረጋገጡ የአሁን አመልካችን የሚመለከታት አይደለም ብለናል፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ቅ/ሀ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.150408

ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አመለወርቅ ፍቅሬ - ጠበቃ ለገሰ ማሞ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋሁን ታፈሰ -የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የወላይታ ሰዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በወላይታ ሰዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር በቀን 3/6/2006 ዓ.ም በተፈጸመ ጋብቻ በቁጥር 240/270//2006 በቀን 12/06/2006 ዓ.ም በብሔራዊ የጋብቻ ስነስርዓት መሰረት ከሶዶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የጋብቻ ምስክር ወረቀት ወስደው ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ እንደማንኛውም ባለትዳር በአንድ ጣራ ስር መኖር ሳይጀምሩ ወደ አሜሪካን አገር መሄዳቸው በመግለጽ ለአለፉት አራት ዓመታት ከተጠሪው ጋር ምንም

ዓይነት ግንኙነት ሳይኖር በተለያየ ቦታ የሚኖሩ መሆናቸውና ልጆች ሆነ የጋራ ሀብት ያላፈሩ በመሆኑ በመካከላቸው ያለው ጋብቻ ፈርሶ የፍቺ ውሳኔ እንዲወሰንላቸው ተጠሪው ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበው ክስ የሰጡት መልስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በህግ የፀና ጋብቻ ስለመኖሩ ሳይክዱ በጋብቻ ውስጥ መኖራችን ጥያቄ ማንሳት የሚችሉት ተጋቢዎች ወይም አንዳቸው እንጂ ሌላ ሰው የሚያነሳው ሀሳብ የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ስለተጋቢዋ ሆኖ ጠበቃ የፍቺ ጥያቄ ማቅረብ የማይችል ስለሆነ ክሱ ወድቅ እንዲደረግ ይህ መቃወሚያ የሚታለፍ ከሆነ በህጉ መሰረት የሞራል ካሳ ተወስኖ የወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አማራጭ መከላከያ መልሳቸው በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በቀረበው መቃወሚያ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በቀን 4/3/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካች ወንድም አስቀድሞ የተጻፈ ሕጋዊ ውክልና ሰነድ ሳይኖር አመልካችን ወክሎ የአመልካች ጋብቻ እንዲፈርስ ጠበቃን የመወከል መብት በህጉ አልተሰጠውም፤ ስለሆነም በተጠሪ የቀረበው መቃወሚያ ተገቢ ሁኖ ስለአገኘን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33/2/ እና 244/መ/ መሰረት የአመልካች ተወካይ ነኝ ባይ ክሱን ለማቅረብ መብት የለውም ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንን ብይን በመቃወም የአመልካች ተወካይ ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 4 ቀን 2010 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለወንድማቸው የሰጡት ውክልና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ቀርቦ ባለበት የተሟላ ውክልና አልቀረበም በሚል ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው በማለት በአመልካች የቀረበው አቤቱታ ከውክልና አንፃር ለመጣራት ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዙት መሰረት የካቲት 21 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ

www.abyssinialaw.com

መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ጠበቃ በተጠሪ የቀረበው መልስ ላይ የመልስ መልስ መስጠት የማይፈልጉ መሆኑን በመግለጻቸው ምክንያት የቀረበ የመልስ መልስ የለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ በመሰረቱ በመርህ ደረጃ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚገባው ከባልና ሚስቱ አንደኛው ተጋቢ ወይም ሁለቱም ቢሆንም በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው ውክልና ማስረጃ ጋር የሚቀርብ የፍቺ ጥያቄ በህግ የተከለከለ አይደለም፡፡ ከባልና ሚስት አንዳቸው የፍቺ ጥያቄ እስካቀረቡ ድረስ ፍቺው ሊከለከል እንደማይቻልና ፍቺ ሊወሰን አይገባም የሚለውን ነጥብ መሰረት በማድረግ ብቻ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ እንደማይቻል በተሻሻለው ፌዴራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 112 ሆነ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 አንቀጽ 127 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሁኖ ካገኘው ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሲያነጋግር ወይም ጉዳዩን ሲመረምርና ምስክር ሲሰማ በዝግ ችሎት ያስችላል የሚለውን የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌ/አንቀጽ 110/ በመጥቀስ ጋብቻና ጋብቻ ፍቺ በውክልና ሊቀርብ አይችልም በማለት በተጠሪ የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ተጋቢዎችን የሚያነጋግራቸው አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ እንጂ የግድ ማናጋገር እንዳለበት የሚደነግግ ባለመሆኑ፤ጋብቻ በእንደራሴ መፈጸም በመርህ ደረጃ የማይቻል ቢሆንም ከተጋቢዎች አንደኛው ጋብቻው ለመፈጸም ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ በመግለጽ በግንባር ለመገኘት የማያስችለው ከባድ ምክንያት ሲያጋጥመው ጉዳዩ ለፍትህ ሚኒስትሩ ቀርቦ ሲረጋገጥ ጋብቻውን በእንደራሴ አማካኝነት መፈጸም እንደሚቻል በግልጽ በተሻሻለው ፌዴራል ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 12 ተደንግጓል፡፡ ጋብቻ ለመፈጸም በልዩ ሁኔታ በውክልና እንደሚቻል ህጉ እየፈቀደ የፍቺ ጥያቄ በውክልና ሊቀርብ አይችልም በማለት በተጠሪ በኩል የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ እዚህ ሊታይ የሚገባው ነጥብ የውክልናው ማስረጃ ህጋዊነት ነው፡፡ ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት የአመልካቹ ወኪል ሆነው የቀረቡት ሰው በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር በተሟጋችነት ሊቆሙ ስለሚችሉ ሰዎች በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

በመሰረቱ በማናቸውም ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ለመከራከር ባለጉዳዩ ራሱ እንዲቀርብ የሚያስገድድ ሕግ ወይም በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የተለየ ትዕዛዝ የሌለ በሆነ ጊዜ ባለጉዳዩ ራሱ ለመቅረብ የማይችል ወይም የማይፈቅድ ሲሆን ነገሩን ለማስረዳት፣ ለመከራከር፣ለሚጠየቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ ፈጅነት፣በወኪልነት፣በጠበቃነት እንዲከራከር ለማድረግ እንደሚችል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ.57 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ሕግ በቁጥር 60፣61 እና 62 ስር የተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አበል ሳይሰጣቸው ስለሌላ ሰው ሆኖ በወኪልነት ወይም በነገረ ፈጅነት አቤቱታ ለማቅረብ፣ ለመከራከር፣ ለመሚገት እና ነገሩን ለመከታተል የሚችሉት የዋናው ባለጉዳይ ባለቤት፣ወንድም፣እህት፣ልጅ፣አባት ወይም አያት ስለመሆናቸው በቁጥር 58(1) ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ስለአመልካቹ በመሆን ውክልና የተሰጣቸው የአመልካች ወንድም በመሆናቸው ከዋናው ባለጉዳይ ጋር በቁጥር 58(1) ከተመለከተው የዝምድና ግንኙነት መካከል አንዱን የሚያሟሉ ስለመሆኑ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ ነገር ግን የውክልና ሰነድ ከውጭ ሀገር ተዘጋጅቶ የተሰጠ በመሆኑ ከሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንጻር መመርመሩ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭ የተዘጋጁ ሰነዶች ትክክለኝነታቸው በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 1፤6፤23 እና 24 ድንጋጌዎች መሰረት በኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር እና በኢፌዴሪ የፍትህ ሚንስተር የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት መረጋገጥ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ አመልካች ለወንድሚቸው የሰጡት ውክልና ስልጣን በኢፌዴሪ ኢምባሲ ዋሽንግተን በቁጥር 05155/09 በቀን 14/07/2009 ዓ.ም የፊርማና ማህተም ትክክለኛነት ተረጋግጦ የተሰጣቸውን ውክልና የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚንስተር በቁጥር 28456/10 በቀን 22/01/2010 ዓ.ም የፊርማ ማህተሙ ህጋዊነት ከተረጋገጠ በኋላ የኢፌዴሪ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቁጥር ቅጽ/2330/10/2010 በቀን 22/01/2010 ዓ.ም ትክክለኛነቱ የተረጋገጠና የተመዘገበ የውክልና ማስረጃ መሆኑን በተጠሪ በኩል ማስተባበያ ያልቀረበበት መሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ የተሰጠው ውክልና ማስረጃ ይዘትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.58 እና በፍ/ብ/ህ/ቁ.2199 አመልካችን ፍቺን ጨምሮ በማናቸውም ጉዳዮች ወክሎ ለመከራከርም ሆነ ሌላ የህግ ባለሙያ ለመወከል እንደሚችሉ በውክልና ሰነድ ላይ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ የውክልና ማስረጃው ፍትህ ሚንስተርና ውጭ ጉዳይ ሚንስተር ቀርቦ ማህተም ተደርጎ በባለስልጣን ፊርማ ተረጋግጦ የቀረበ ባለመሆኑ ሕጋዊነት የጎደለው ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የቤተሰብ ህጉ የጋብቻ ፍቺ ክስ በወኪል ማቅረብ የማይከልክል ሁኖ እያለ እንዲሁም አመልካች ለወንድሚቸው የሰጡት ውክልና ማስረጃ የህጉን መስፈርት የሚያሟላ ሁኖ ተወካዩ በራሰቸው ወይም ጠበቃ በመወከል ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የሚያስችላቸው ህጋዊ ውክልና በመያዝ ያቀረቡት ክስ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በወላይታ ሶዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 38955 ህዳር 4 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወላይታ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 21387 ህዳር 19 ቀን 2010 ዓ.ም በትእዛዝ ያጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የወላይታ ሶዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

ቅ/ሀ　　　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

# ውርስ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ.ቁ. 152134

ህዳር 24 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትግዕሥት ንጉሴ- የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አሰፋ ንጉሴ

2 አቶ ሞላ ንጉሴ

3 አቶ አዳነ ንጉሴ የቀረበ የለም

4 ወ/ሮ ሂሩት ንጉሴ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የነገሩ አመጣጥ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ከሥር 2ኛ አመልካች ሕፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ ጋር በመሆን ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ የአመልካቾች ወላጅ አባት አቶ ንጉሴ ቱሩፌ አመልካቾችንና ተጠሪዎችን ጨምሮ ስድስት ልጆችን መውለዳቸውን፣ ጥር 26 ቀን 2007 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን፣ አባታቸው ከመሞታቸው በፊት ለረጅም ጊዜ የካንሰር ህመምተኛ እንደነበሩ፣ ራሳቸውን በማያውቁበት ሁኔታ ውስጥ እያሉ 1ኛ ተጠሪ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ከሆኑት

አቶ መኩሪያ አይተንፍሱ ጋር በመሆን መስከረም 6 ቀን 2007 ዓ/ም አስገድደው ኑዛዜ እንዲፈጽሙ ማድረጋቸውን ፣ ኑዛዜውም ትክክል ያልሆነና የሁሉንም ወራሾች መብት ያላከበረ መሆኑን፣ ተናዛዡም በተራ ቁጥር 5 እና 7 ላይ ጠቅሰው የተናዘዙት ንብረት በስማቸው የሌለ መሆኑን፣ እንዲሁም ኑዛዜው አመልካቾችን የመንቀል ውጤት ያለው በመሆኑ ኑዛዜው እንዲፈርስልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 15 ቀን 2008 ዓ/ም በጻፉት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካቾች ኑዛዜው መኖሩን ሟች ከሞተበት ቀን ጀምሮ ያውቃሉ፣ ሟች ከሞተ 40 ቀን ሊሞላው ሳምንት ሲቀረው አመልካቾች በተገኙበት ኑዛዜው ተነቧል፣ በኑዛዜው መቃወሚያ ካላቸው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት ኑዛዜው አይፀናም በማለት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉት እስከ ሶስት ወር ድረስ ነበር ፣ ነገር ግን አመልካቾች መቃወሚያውን ያቀረቡት ኑዛዜው ከተነበበ ከአንድ ዓመት በኃላ ውርስ ሲጣራ ውርስ አጣሪው ጋር ነው፣ መቃወሚያውም ማቅረብ ካለበት የሚቀርበው ህጉ ባስቀመጠው ጊዜ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው፡፡ ስለዚህ መቃወሚያው በይርጋ ይታገዳል፡፡ አመልካቾችም ኑዛዜ ስለመኖሩ ከውርስ አጣሪ መሾም በፊት ያውቃሉ፡፡ በዚሁ ኑዛዜም ወራሽነታቸውን አስመስክረዋል፡፡ ኑዛዜውን የሚቃወሙ ከሆነ ይህንን ማቅረብ የሚችሉት የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ለሰጠው ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንጂ ለዚህ ፍርድ ቤት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች ላቀረቡት መቃወሚያ አመልካቾች በሰጡት መልስ ኑዛዜው መኖሩን ያወቅነው ውርስ አጣሪ ዘንድ ነው፤ ኑዛዜው ተነበበ በተባለበት ቦታ አልነበርንም፡፡ ስለዚህ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ካወቅንበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን በህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ ላይ መቆጠር የሚጀምረው አካለ መጠን ከደረሰችበት ጊዜ አንስቶ ሊሆን ይገባል፤ የአዲስ አባባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾችን የኑዛዜ ወራሽ ያደረገው በወቅቱ ለፍርድ ቤቱ ቀርበው የነበሩት ጠበቃ ከአመልካቾች ባልተሰጣቸው ውክልና ያወጡትን ማስረጃ መሠረት

በማድረግ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች የኑዛዜ ይፍረስልኝ ጥያቄን የማየት ሥልጣን የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እንዲሁም ማስረጃዎችን መርምሮ በመዝገብ ቁጥር 56140 በሆነው በቀን 19/05/2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት ህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ ኑዛዜው ሲነበብ ክስ ለመመስረት የሚያስችል የእድሜ ደረጃ ላይ ባትደርስም ሞግዚትና አስተዳዳሪው የሆኑት ወ/ሮ ትግዕሥት ንጉሴ በቦታው የነበሩ መሆኑን የተጠሪዎች ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ ስላስረዱ የሁለቱም አመልካቾች መብት በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

ይህን ብይን ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች እና የሥር 2ኛ ይግባኝ ባይ ኤልሻዳይ ንጉሴ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከዳመጠ በኃላ በኮ/መ/ቁ. 193480 ጥቅምት 14 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት 1ኛ ይግባኝ ባይ /የአሁን አመልካች/ ያቀረቡት የኑዛዜ ይፍረስልኝ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔን አጽንቷል፡፡ በሌላ በኩል የህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴን ይግባኝ በተመለከተ ክስ ሲመሰረት ዘጠኝ ዓመቷ የነበረ መሆኑ በመልስ ሰጪዎች /በአሁን ተጠሪዎች/ የተካደ አይደለም፡፡ የ2ኛ ይግባኝ ባይ እድሜ ይህ ከነበረ ደግሞ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1846 እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 57114 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው አካለ መጠን ከደረሰች በኃላ ነው፡፡ ህጉ ሞግዚት ካለ መደበኛው የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ይፈጸምባቸዋል በማለት አልደነገገም፡፡ በሞግዚቶች ችልተኝነትና ተገቢ ያልሆነ ሥራ መብታቸው እንዳይጎዳ በሚል እሳቤ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የሁለተኛ ይግባኝ ባይ ጥያቄም በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን ተገቢ ስላልሆነ 2ኛ ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪዎችን ያሉዋቸውን ሌሎች ክርክሮች እና ማስረጃዎች ሰምቶ የመሰለውን

www.abyssinialaw.com

እንዲወስን በማለት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት መልሶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- ኑዛዜው ከሩብ በላይ ጉዳት አድርሶብኛል ሊፈርስ ይገባል በሚል ለቀረበ ክስ የፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት አድርገው የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን እና ውሳኔ ተገቢ አይደለም ፣ የፍትሓብሔር ህግ አንቀጽ 973 ተፈጻሚ የሚሆነው ውርስ ተከፍቶ ውርስ አጣሪ ከተሾመ በኃላ የሚፈጸም ድንጋጌ ሆኖ እያለ ኑዛዜ በማን እና መቼ ተነቧል የሚለውን ነጥብ የሥር ፍርድ ቤቶች በፍትሓብሄር ህግ ቁጥር 946፣ 965 አንጻር ሳይመረምሩ ብይን እና ውሳኔ መስጠታቸው አግባብነት የለውም፣ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በከፊል የተሻሻለው ውሳኔ ከአመልካች ውጪ ክርክሩ እንዲቀጥል ማድረጉ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 40 ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው፣ ከኑዛዜው ተጠቃሚ የሆነ ሰው ኑዛዜው እንዳይፈርስ የተንኮል ሥራ የሰራ መሆኑን፣ ከጠበቃ ጋር ተመሳጥሮ የሌሎች ወራሾች መብት ሲያሳጣ የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በቀረበበት ሁኔታ፣ በዚሁ ተግባሩ በወንጀል ተከሶ እንዲከላከል ብይን በተሰጠበት ሁኔታ እሱ /1ኛ ተጠሪ/ ቀጥሮ የሚያሰራቸው ሠራተኞች እና ባለቤቱ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ብቻ መሠረት ተደርጎ የተሰጠ ፍርድ መሠረታዊ ማስረጃ ምዘና ግደፈት ያለበት ስለሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር እና በኑዛዜ ላይ ተገቢውን ህጋዊ ክርክር እንዲያቀርብ እንዲደረግልኝ እንዲሁም በዚህ የሰበር ቅሬታ ምክንያት ያወጣሁትን ወጪና ኪሳራ እንዲተኩልኝ እንዲወስንልኝ እጠይቃለሁ የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች ተደረገ ስለተባለው ኑዛዜ አላውቅም እያሉ ኑዛዜውን በወቅቱ ስላልተቃወሙ ይርጋ ያግዳቸዋል የመባሉ እና ኑዛዜው አመልካችን ከውርስ የሚነቅል ነው የሚለው አቤቱታም ከፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1123 (1) አንጻር ሳይታይ የመታለፉ አግባብነት

መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 1ኛ ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በጠበቃቸው በኩል በቀን 20/7/2010 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን አመልካችም ሚያዚያ 16 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ መጥሪያ ደርሶዋቸው ቀርበው ለመከራከር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሚያዚያ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በተሰጠው ትዕዛዝ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ወይስ አልተፈጸመበትም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውንና መስከረም 6 ቀን 2007 ዓ/ም ከሟች ተሰጠ የተባለውን ኑዛዜ በተመለከተ አመልካች ያወቁት ውርስ እንዲጣራ ሲደርግ ውርስ አጣሪ ዘንድ እንደሆነ፣ ኑዛዜውን ሟች ያልሰጡትና ሀሰተኛ መሆኑን፣ ከአመልካችና ከህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ ለጠበቃ ውክልና ሳይሰጥ ውክልና እንደተሰጠ በማድረግ ለአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ኑዛዜውን መሠረት በማድረግ ወራሽነትን ተጠሪዎች ማስወሰናቸውን፣ ይህን ሀሰተኛ ተግባር የፈጸሙ ጠበቃም ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቤቱታ ቀርቦባቸው በጉባኤ ከታየ በኃላ በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24/3/ለ/2 መሠረት 2 ዓመት ከ6 ወር ከጥብቅና አገልግሎትና የማማከር ተግባር እንዲታገዱ የተደረገ መሆኑን፣ ጠበቃዋ ያስወሰኑት የወራሽነት ማስረጃን በተመለከተ ውሳኔውን ለሰጠው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች /ህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴን ጨምሮ/ አቤቱታ አቅርበው በአሁን አመልካች እና በህፃን ኤልሻዳይ ላይ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል የከተማው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 2940/07 በቀን 9/2/2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠረዘ መሆኑን፣ እንዲሁም የአሁን 1ኛ ተጠሪ እና ጠበቃዋ

www.abyssinialaw.com

በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ተከሰው እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠ መሆኑን አመልካች አጥብቀው ይከራከራሉ፡፡ ጠበቃዋ በፈጸሙት ድርጊት ጉባኤው ቅጣት የወሰነባቸው መሆኑን እንዲሁም ከአሁን አመልካች እና ከህጻን አልሻዳይ ንጉሴ ውክልና ሳይሰጣቸው እንደተሰጠ በማድረግ ጠበቃዋ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኑዛዜውን መሠረት በማድረግ አቤቱታ አቅርበው ያስወሰኑት ውሳኔ አመልካችን እና ህጻን አልሻዳይ ንጉሴን በሚመለከት የተሠረዘ መሆኑን ይህ ችሎት ተመልክቷል፡፡

በመሠረቱ የአሁን አመልካች እና የሥር 2ኛ አመልካች ህፃን ኤልሻዳይ አቤቱታ ኑዛዜው በማስገደድ የተደረገ እንዲሁም ከውርስ የነቀለ በመሆኑ እንዲፈርስ የሚል ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን የተጠሪዎች ክርክር አመልካቾች ኑዛዜው ሲነበብ በቦታው ላይ ስለነበሩ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በ3 ወር ውስጥ ኑዛዜው እንዲፈርስ ጥያቄ ስላልቀረበ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ከዚህ ክርክር ተነስተን የአሁን አመልካችም ሆነ የህፃን አልሻዳይ አቤቱታ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት የሚታይ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ የፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 ስለ ኑዛዜ መነበብ እንዲሁም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው እንዲፈርስ አቤቱታ የሚያቀርቡበትን ሥርዓት እና ጊዜውን በሚመለከት የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ኑዛዜው ከውርስ ነቅሎኛል /ነቅሎናል/ በማለት ኑዛዜው እንዲፈርስ የሚቀርብን ወይም የቀረበን አቤቱታን የሚመለከት አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካችም ሆኑ ይርጋው አያግድም ተብሎ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጣት ህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ መሠረታዊ አቤቱታ ይዘት ኑዛዜው ከውርስ የመንቀል ውጤት ያለው በመሆኑ እንዲፈርስ የሚል ነው፡፡ ይህ የዳኝነት ጥያቄ ሊታይ የሚገባው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1123 መሠረት ነው እንጂ በተጠቀሰው ህግ አንቀጽ 973 መሠረት አይደለም፡፡ የክርክሩ ይዘት እንደሚያመለክተው የአመልካቾች አባት ኑዛዜ ሠጡ የተባለው በ6/7/2007 ዓ/ም ሲሆን የሞቱት ደግሞ በ26/1/2007 ዓ/ም ነው፡፡ ኑዛዜው እንዲፈርስ ዳኝነት የተጠየቀው ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ/ም ነው፡፡ ይህም በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1123 /3/ መሠረት ጊዜው ያላለፈበት መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በመሆኑም የአመልካች ጥያቄ ይህን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መታየት ሲገባው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 973 ድንጋጌ ተወስዶ አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው ብይንም ሆነ ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 82525 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን ይህም ትርጉም በየትኛውም ደረጃ በሚገኙት ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 494/97 አንቀጽ 2(1) በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ብይንም ሆነ ውሳኔ የአቤቱታውን ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ አመልካችን ኑዛዜው ከውርስ የነቀለ ነው ወይስ አይደለም? የነቀለ ነው የሚባል ከሆነ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚለው ጭብጥ ተይዞ ጉዳይ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤኑ የሰጡት ብይንም ሆነ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 193480 ጥቅምት 14 ቀን 2010 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2.የህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ አቤቱታ በይርጋ አይታገድም ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

3.የአሁን አመልካች አቤቱታ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

4.የአመልካች አቤቱታ በይርጋ ሊታገድ የሚችልበት ህጋዊ መሠረት ስለሌለው አመልካችን ኑዛዜው ከፍ/ህ/ቁ 1123 አንፃር ሲታይ አመልካችን ከ1/4ኛ በላይ የጉዳ ውርስ ነው ወይስ አይደለም? የጉዳ ነው የሚባል ከሆነ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚለውን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አጣርቶ እንዲወስን በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡

5. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

6. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

7. ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ፋ/ዘ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች

ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 153231

መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ እልፌ ደበላ- ቀረቡ

2. ወ/ሮ ደስታ ደበላ - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ሽብሬ ደበላ - ቀረቡ

4. ወ/ሮ ትርንጎ ደበላ - ቀረቡ

5. ወ/ሮ መገርቱ ደበላ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ ንጉሴ ደበላ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው

www.abyssinialaw.com

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ወጫሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የአመልካቾች ክስ ይዘትም ሟች አቶ ደበላ ሄዪ በቀን 13/12/2003 ዓ.ም በሞት ከዚህ አለም የተለዩ መሆናቸው በመግለጽ ተጠሪ ከዚህ በፊት የተወሰነልን መልሶ በመያዝ የባለይዞታነት ማስረጃ ወስዶበት ድርሻችንን ስለከለከለን እንዲሁም የአባታችን ይዞታ ረስተን ውሳኔ ሳይሰጥበት ሳናውቅ የአባታችን የመሬት ይዞታ በእጁ ይዞ ስለሚገኝ ድርሻቸውን ተከፍሎ እንዲሰጠን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ በመጀመሪያ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ የሰጠው ውሳኔ እና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ በኋላ በቀን 28/02/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በሽማግሌዎች አማካኝነት ከዚህ በፊት ተከፋፍሎላቸው የነበረውን ተጠሪ መልሶ ይዞባቸዋል? ወይስ አልያዘም? ተደብቆ ያለው ይዞታ አለ? ወይስ የለም? ይዞታው አመልካቾች ሳያውቁ ከውርስ ክፍፍል የቀረ ነው ? ወይስ እያወቁ ነው የተውት? ይዞታው የሚገኝበት መደበቅ የሚችልበት ቦታ ነው? የሚሉ ነጥቦች በግራ ቀኙ ማስረጃ ከተጣሩ በኋላ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት ለወረዳ ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡

ፍርድ ቤቱም የተዘጋው መዝገብ አንቀሳቅሶ በተመለሱት ነጥቦች ላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪ ያለ አመልካቾች ፈቃድ እነሱ ሳያውቁ በይዞታቸው ላይ በሀይል ቤት የሰራ ስለሆነ በተጠሪ ወጪ በክሱ ተራ ቁጥር 1ኛ ላይ የሚገኝበት ቦታ እና አዋሳኙ በተገለጸው ይዞታ ላይ የተሰራውን ቤት በማፍረስ ለከሳሾች/አመልካቾች/ ይዞታውን እንዲለቅ፤በክሱ ከ2ኛ እስከ 6ኛ  እና 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ይዞታዎች የወላጅ አባታቸው  መሆናቸውና፤ ከሳሾች የይዞታዎቹ  አዋሳኝ የማያውቁ መሆናቸውና እናታቸው ጋር በመሁክ ጡሪ ከተማ ያደጉ ስለሆነ ማወቅ አለመቻላቸውን እና የተደበቀ መሆኑን ስለተረጋገጠ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1103 በመጠቀስ ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታቸው ለሰሜን ሽዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸው አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በማሻሻል በክሱ ተራ ቁጥር 1ኛ እና 7ኛ የተጠቀሱት ይዞታዎች በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ በማጽናት በክሱ ተራ ቁጥር 2-6 እና 8ኛ የተመለከቱት ይዞታዎች ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ለአመልካቾች ሊያካፍል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት የጉዳዩ አከራካሪ የሆነው የውርስ ይዞታ ተረስተው የታለፉና በድጋሚ መጠየቁ አግባብነት ያለው ነው ብለው የወሰነውን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሬት የማይረሳ ነው ልጠይቁ አይገባም ያለበት አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾችና ተጠሪ የሟች ወላጅ አባታቸው አቶ ደበላ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸው፤አመልካቾች በተጠሪ እጅ የሚገኙትን የውርስ ንብረትና ይዞታዎች ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት በመጠየቃቸው ምክንያት ግራ ቀኙ በስምምነት ክፍፍል ማድረጋቸው በመግለጽ ነገር ግን ከውሳኔ በኋላ ለአመልካቾች በደረሳቸው ይዞታ ላይ ተጠሪ በሀይል ቤት በመስራቱ እንዲሁም የተረሱ ይዞታዎች ድርሻቸው እንዲያካፍላቸው ዳኝነት በመጠየቃቸው ምክንያት የግራ ቀኙ ክርክር ከተደረገ በኋላ ተጠሪ በአመልካቾች ድርሻ ላይ ቤት መስራቱን በማረጋገጥ የሰራውን ቤት በራሱ ወጪ አፍርሶ ይዞታው ለአመልካቾች እንዲለቅ መስጠቱን ተገንዝበናል በዚህ ረገድ የቀረበ አቤቱታ የለም፡፡ አከራካሪ የሆነው አመልካቾች በክሳቸው ከ1ኛ እስከ 6ኛ እንዲሁም 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱትን ይዞታዎችን በሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች ከውሳኔ በኋላ ክስ

www.abyssinialaw.com

ለማቅረብ በምክንያትነት የጠቀሱት የውርስ ይዞታዎች የሆኑትን መኖራቸው ባለማወቅቸው መሆኑን የተረሱ የውርስ ሀብት መጠየቅ እንደሚቻል የፍ/ብ/ህ/ቁ.1103፣1104 ስለሚፈቅድ በዚሁ አግባብ የቀረበ ክስ መሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በተጠሪ እጅ የሚገኙትን ክፍፍል ሳይደረግባቸው የቀሩትን እኩል እንዲከፋፈሉ የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ጉዳዩ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ተጠሪ ጉዳዩ ውሳኔ ካገኘ በኋላ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በፍሬ ነገር ዳግም ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት ለስር ፍርድ መልሶታል፡፡ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም የተዘጋው መዝገብ አንቀሳቅሶ የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ለክርክር ምክንያት የሆኑት ይዞታዎች ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ ሲል የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፀና ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 216/3/ አንጻር ተመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በክሱ ከ1ኛ እስከ 6ኛ እና 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ይዞታዎች ተጠሪ ለአመልካቾች ሊያካፍል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ የአመልካች አቤቱታ መሰረት ያደረገው በስር ፍርድ በተጠሪ ያልተነሳ ጉዳይ በማንሳት የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በአግባቡ አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ አንድ ተከራካሪ ወገን ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨ የመብት ጥያቄ ካለው እና በአንድ ክስ የሚጠቃለል የክስ ምክንያት ሆን ብሎ በመቀነስ ያስቀረ ከሆነ በድጋሚ በተመሳሳይ ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 216 /3/ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ የአንድ ክስ ምክንያት መከፋፈል ባለጉዳዮች ጊዜ፣ ወጪና ጉልበት አላስፈላጊ ጫና እና የማጉላላት ውጤት እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ/ዓይነተኛ ዓላማ /main purpose / ጉዳዮችን በህግ አግባብ በመምራት በተቻለ አጭር ጊዜ ውጤታማ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፍትሃዊ ውሳኔ መስጠት ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የህጉ ድንጋጌዎች የምንረዳው ነው፡፡ ከአንድ ጉዳይ የመነጨ የመብት ጥያቄ የሚያቀርቡ ተከራካሪ ወገኖች ክሱን ለመመስረት መነሻ የሆነባቸው ጉዳይ አጠቃልለው

www.abyssinialaw.com

የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ከአንድ የክስ ምክንያት የሚመነጭ ክርክር ከፋፍለው ከቀረቡ /spilting of claim/ በድጋሚ በተመሳሳይ ጉዳይ ሌላ ክስ የማቅረብ መብት የሚሰጣቸው አይደለም፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.216 መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ መመርመሩ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በሁለት ምክንያት ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ አንደኛው ይህ ጉዳይ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው ሁለት ጊዜ መሆኑን ከክርክሩ ሂደትና ከውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ላይ በተጠሪ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 216 መሰረት በማድረግ ያቀረቡት ክርክር ካለመኖሩም በላይ ጉዳዩ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ጉዳዩ እንደገና ወደ ፍሬ ነገር ገብቶ እንዲጣራ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት ሲመልስ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.216 ጥያቄ አልነበረም፡፡ አንድ ተከሳሽ ለቀረበለት ክስ በዝርዝርና በግልፅ መቃወምና መካድ እንደለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 ተመልክቷል፡፡ በይግባኝ ደረጃም ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.329/1/ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳወን ክርክርና ያልቀረበውን አዲስ ነገር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መቀበል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182/2/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎቹ በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልፅ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የክልሉ ሰበር ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፤ በሌላ በኩልም የውርስ ንብረት ክፍያው ከተደረገ በኋላ በክፍያ ውስጥ ያልገቡ በውርሱ ንብረት ውስጥ ገብተው የሚቆጠሩ አዲስ ሀብቶች የተገኙ እንደሆነ አዲስ የክፍያ ስርዓት መፈጠም እንደሚቻል ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1103 እና 1104 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በወጫሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 24658 ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም እና በሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 55692 ግንቦት 24 ቀን 2009 ዓ.ም ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 268679 ህዳር 4 ቀን 2010 ዓ.ም በውሳኔ የተሻሻለው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. በክሱ በ1ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰውን የይዞታ መሬት ተጠሪ ለአመልካቾች እንዲለቅ የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በክሱ ከ2ኛ እስከ 6ኛ እንዲሁም 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ይዞታዎች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክሱ ከ2ኛ እስከ 6ኛ እንዲሁም 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ይዞታዎች አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ በማለት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰበር መ/ቁ/ 159474
ህዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ሙስጠፋ አህመድ
አብርሃ መሰለ
ፈይሳ ወርቁ
ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ እንደገና ተሾመ- የቀረበ የለም፡፡
ተጠሪ፡- አቶ ረታ መልካ - ታልፏል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ሟች እማሆይ ውቢቱ ኃ/ማሪያም በ3/09/2009 ዓ/ም አድርገውት ያለፉት ኑዛዜ መሠረት ተደርጐ የወራሽነት ማስረጃ ይሰጣቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው ሶስት ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ጠይቀው ሟች ወላጅ እናታቸው መሆናቸውን፣ የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን በፍርድ ቤት ያረጋገጡ መሆኑን፣ አመልካች አለኝ የሚሉት ኑዛዜም ሕጋዊ አይደለም የሚሉበትን ምክንያት ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ተጠሪ ጣልቃ ገብተው በአቀረቡት መከራከሪያም የአሁኑ አመልካች አለኝ የሚሉትን መከራከሪያ ነጥብ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በፍትሃ ብሔር ሕጉ መሰረት ኑዛዜ ይመዝገብልኝ፣ ይሻርልኝ፣ እንዲሁም መጠኑ ይቀነስልኝ በማለት ዳኝነት ከሚጠየቅ በስተቀር ይረጋገጥልኝ መባሉ የህግ ድጋፍ የለውም በሚል ምክንያት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ላይ ከአሁኑ አመልካች ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በስር ፍርድ ቤት ብይን ላይ ጉድለት የለውም በማለት በትእዛዝ የአመልካችን ይግባኝ የሰረዘ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎትም በበታች ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የስር ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

አመልካች የኑዛዜ ወራሽነት እንዲረጋገጥላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀብሎ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በተጠሪ ጣልቃ ገብነት መነሻ የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ ተብሎ ዳኝነት አይጠየቅም ሲል መዝገቡን መዝጋቱም ሆነ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳያርሙ መቅረታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸውም በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው እንዲታለፍ ተደርጎአል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ዳኝነት እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ፍርድ ቤት የሚቀርብ አይደለም በማለት የሰጡት ዳኝነት የሕግ መሰረት ያለው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከተው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የታቻለው አመልካች ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት ሟች አደረጉ በተባለው ኑዛዜ መሠረት በማድረግ የወራሽነት ማስረጃ (የምስክር ወረቀት ) ይሰጠኝ (የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 996(1) በማለት መሆኑን፣ ይኼው መነሻ ተደርጎም የአመልካች ምስክሮች ሁሉ ተሰምተው የነበሩ መሆኑን፣ ከዚህ በኋላም የአሁኑ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ሕጋዊ አይደለም የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው የተከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በፍትሐብሔር ሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርበው ክስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ከሚቀርበው ጥያቄ (አቤቱታ) የተለየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ጥያቄዎቹ የተለያዩ በመሆናቸውም የተለያዩ ውጤት ነው ያላቸው፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 996(1) እንደተደነገገው ወራሽ ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው የወራሽነት ምስክር ወረቀት ይሰጠው ዘንድ ለፍ/ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከመቀበሉ በፊት ጠያቂው ማስረጃዎቹን ሁሉ እንዲያቀርብ በማድረግ እና አስፈላጊ መስሎ የታየውን ዋስትና እንዲሰጥ በማስገደድ ጭምር ዋስትናውን ካገኘ በኋላ የተጠየቀውን የምስክር ወረቀት ሊሰጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 996(2) ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቱ የአመልካቹን ጥያቄ

መሠረት በማድረግ ሰጥቶት የነበረው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ሊሰረዝው እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁ.998(1) የተቀመጠው ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ማስረጃው ከተሰጠ በኋላ ማስረጃው የተሰጠው ከህግ ውጪ ነው የሚል ወገን ክርክሩን ከአቀረበ ነው፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ እንደሚቻለው የምስክር ወረቀቱ በጠያቂው አቤቱታ መነሻነት የሚሰጥ ቢሆንም የተሰጠው ያለአግባብ ነው የሚል መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩንና መቃወሚያው ተገቢ ሆኖ ከተገኘም የምስክር ወረቀቱ የሚሰረዝ መሆኑን ነው፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበት ፍ/ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ የምስክር ወረቀቱን ከመስጠቱ በፊት ይኼው ማስረጃ እንዳይሰጥ ተጠሪ ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ በሕግ አግባብ የተደረገ ኑዛዜ በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የፍርድ ቤትን ቡራኬ የማያስፈልገው መሆኑን ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17058 እና በሌሎች መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም መስጠቱን ይታወቃል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም የሚል ተከራካሪ ወገን በቀረበበት አግባብ አይደለም፡፡ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17058 የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የኑዛዜውን ህጋዊነት የሚቃወም ወገን በንብረት ክርክር ጊዜ ክርክሩን ሊያነሳ የሚችል መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህም የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማትና ፍትህ የማግኘት መብትን ሁሉ ያገናዘበ ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡ በመሆኑን ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ጥያቄ በፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ እስከሆነ ድረስ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን ባከበረና የሥነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ አላማ ባገናዘበ መልኩ ሊስተናገድ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የኑዛዜ ወራሽነት እንዲረጋገጥለት አቤቱታ አቅርቦ ማስረጃ ያሰማ ወገን ማስረጃውን ከማግኘቱ በፊት ማስረጃው እንዳይሰጥ የሚል ተከራካሪ ወገን ከቀረበ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በሕጉ አግባብ ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባው እንጂ ከመነሻውም የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ የሚል አቤቱታ መቅረብ አልነበረበትም በማለት መዝገቡን ሊዘጋው የሚገባው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ማስረጃው እንዳይሰጥ የሚል ወገን ቀርቦ ስለኑዛዜው ፎርማሊቲ ሳይሆን ስለኑዛዜው ሕጋዊነት (ኑዛዜው የሚሻርባቸውን ወይም ውድቅ የሚሆንባቸውን ምክንያቶች በሚመለከት) ክርክር ከአነሳ በዚህ ረገድ ጭብጦችን ይዞ ተገቢውን ዳኝነት መስጠትን የሚጠይቅ

www.abyssinialaw.com

ነውና፡፡ ስለሆነም የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ የሚለው ጥያቄ በፍርድ ቤት እንዲቀርብ ሕጉ የግድ አይልም ሲባል ከኑዛዜ ፎርማሊቲ ጋር ተያይዞ የሚታይ እንጂ ስለኑዛዜው ሕጋዊነት ጭምር ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ በሚል አቤቱታ በተከፈተ መዝገብ ላይ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም የሚል ተከራካሪ ወገን ከቀረበ ደግሞ ፍ/ቤቱ ወደ ኑዛዜው ይዘት እና ሕጋዊነት ሁኔታ ገብቶ ውሳኔ መስጠትን የግድ የሚል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን በሕጉ አግባብ በመስማትና በሚገባ በማጣራት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት ስነ ስርዓታዊ እንጂ በንብረት ክርክር ጊዜ የሚታይ ነው ተብሎ የሚታለፍ አይደለም፡፡ ክርክሩ በንብረት ክርክር ጊዜ የሚታይ ነው ብሎ መዝገቡን መዝጋትም ክርክሮች በአነስተኛ ወጪ፣ በተፋጠነ ጊዜና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መሰጠት አለባቸው ከሚለው የስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ ዓላማ ጋርም አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ተገቢነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 07129 በ3/05/2010 ዓ/ም ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28578 በ22/05/2010 ዓ/ም፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 27964 በ25/08/2010 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 07129 ቀጥሎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት እንዲሁም አስፈላጊ ሁኖ ሲያገኘው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማስቀረብና ክርክሩን ስነ ስርዓቱ በሚፈቅደው አግባብ ጭምር በመመራት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

# ውል

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር---146457

ቀን-ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች**:- ወ/ሮ ዘቢባ ሙሳ

**ተጠሪ**፡- አቶ አማን በሪሶ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የከተማ ቦታ ይዞታ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በአዳማ ከተማ 01 ቀበሌ ዉስጥ የሚገኘዉን የካርታ ቁጥሩ 10690/06 የሆነዉ 180 ካ.ሜ የመኖሪያ ቤት ቦታ በአዳማ ከተማ መስተዳድር ተሰጥቶ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘዉን ተጠሪ ምንም መብት ሳይኖረዉ ቦታዉ ላይ ቤት መስራቱን አይቼ ግንባታዉን እንዲያቆም ብጠይቀዉም ፈቃደኛ ስላልሆነ ግንባታዉን በራሱ ወጪ አፍርሶ ይዞታዉን ይልቀቅልኝ የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት አስመልክቶ አመልካች መንግስት አካል ጋር በመቅረብ በዉክልና ቁጥር 052125 በቀን 01/02/2008 ዓ.ም ለአቶ ፋአድ ጀማል ሙሳ ይዞታዉንና ንብረቷን እንዲሸጥ፣ እንዲለዉጥ፣ ለ3ኛ ወገን በማንኛዉም ሁኔታ እንዲያስተላልፍ ዉክልና ሰጥታዉ፤ እሱም ዉክልና አቶ

www.abyssinialaw.com

አህመድ ለሚባል አሳልፎ ሰጥቶ ዉክልናዉ ሕጋዊ መሆኑን አረጋግጬ በቀን 05/07/2008 ዓ.ም በተጻፈ የግዥ እና ሽያጭ ዉል በብር 250,000 ተስማምቼ ገዝቼ ዉሉም ስልጣን ባለዉ አካል ጸድቆ የሊዝ ዉሉ ወደ ስሜ ተዛዉሮ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶኝ ባለይዞታ የሆንኩበትና አመልካች ሳይቃወሙ የገነባሁት ቤት ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ መርምሮ ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ አመልካች ስልጣን ባለዉ አካል ፊት ለመሸጥ ዉክልና ከተሰጠዉ ሰዉ ጋር ተዋዉሎ የገዛና በአመልካች ስም የነበረዉ ወደ ተጠሪ ተዘዋዉሮና ተመዝግቦ የሚታወቅ በመሆኑ እንዲሁም አመልካች ከኢሜግሬሽን እና የዜግነት ጉዳዮች ጽ/ቤት ያቀረቡት ማስረጃም ቢሆን ከአመልካች ጋር ሳይሆን ከአመልካች ተወካይ ጋር ዉሉ የተደረገ በመሆኑና ተጠሪ አመልካች ከአገር መኖር አለመኖሯን የማወቅ ግዴታ የሌለዉ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ይዞታዬን በሕገ-ወጥ መንገድ ይዟል በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ጉዳዩን የተመለከተዉ የአዳማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አቤቱታዉ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ዉሳኔዉን ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ የመኖሪያ ቤት ቦታዬ እንዲሸጥም ሆነ እንዲለወጥ የሰጠሁት ሕጋዊ ዉክልና እንደሌለ እየተከራከርኩ እና ዉክልናዉ ተሰጥቶኛል በተባለበት ወቅትም ሀገር ዉስጥ ያልነበርኩ መሆኔን በመግለጽ የኢሚግሬሽን እና የዜግነት ጉዳዮች ቢሮ በቀን 22/03/09 ዓ.ም ለአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመግለጽ ተጽፎ እያለ ጉዳዩ በሚገባ ሳይጣራ ሀሰተኛ በሆነ ዉክልና ስሙ ከአመልካች ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ ብቻ ተጠሪ በዚህ ዉክልና መሠረት በግዢ ዉል የያዘዉ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ፍትህ ቢሮ በቀን 15/02/2009 ዓ.ም ለወረዳዉ ፍ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ አመልካች በአካል ቀርባ የዉክልና ቁጥሩ 052125 የሆነ በቀን 01/02/2008 ዓ.ም ዉክልና ሰጥታለች በማለት ስለገለጸ ብቻ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ዉክልና ሰጥታለች በተባለበት ቀን በአገር

ያልነበርኩ መሆኔን ስልጣን ከተሰጠዉ አካል በተጻፈ ደብዳቤ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ዉሳኔዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይሻርልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ዉክልናዉ ተሰጠ በተባለበት ጊዜ በሀገር ዉስጥ አልነበርኩም በማለት ከኢሚግሬሽን የተጻፈ መግለጫ ያቀረበችዉና በዉክልናዉ ላይ ያለዉ ፊርማ በፎረንሲክ እንዲመረመር የጠየቀችዉ በስር ፍ/ቤት የታለፈበትና ዉድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ከኢሚግሬሽን የመጣ ደብዳቤ እና የፎረንሲክ ምርመራን ከፍትሕ ቢሮ ከመጣዉ ደብዳቤ ጋር አመዛዝኖ ዉሳኔ መስጠት የስር ፍ/ቤት ማስረጃን የመመዘን ስልጣን እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላልሆነ አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረግልኝ፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በሕገ-ወጥ መንገድ ያለእኔ ፈቃድ የተደረገ የሽያጭ ዉል ይፍረስልኝ የሚል እስካልሆነ ድረስ የሚያዘዉ ጭብጥ ከቀረበዉ ክስ አንጻር ተጠሪ ንብረቱን የያዘዉ በሕገ-ወጥ መንገድ ነዉ ወይስ በሕጋዊ መንገድ የሚለዉ ነዉ፡፡ ለዚህ በማስረጃነት ያቀረብኩት አመልካች እራሷ ለወንድሟ የሰጠችዉን ዉክልና፣ ወንድሟ ለአቶ አህመድ የሰጠዉን ዉክልና፣ በእኔና በ2ኛ ተወካይ መካከል የተደረገ ሕጋዊ የሽያጭ ዉል እንዲሁም የሊዝ ዉል፣ በስሜ የተሰጠኝ ካርታና ፕላን እና የግንባታ ፈቃድ ነዉ፡፡ ዉክልናዉ ሕጋዊ ስለመሆኑ የፍትህ ቢሮ እና ማዘጋጃ ቤቱ ተጠይቆ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህ መሠረት ተደርጎ ማስረጃ ተመዝኖ የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህትት ተፈጽሞበታል የሚባል አይደለም፡፡ ኢሚግሬሽን መስሪያ ቤት በ01/03/2009 ዓ.ም በጻፈዉ ደብዳቤ ላይ በግልጽ እንዳመለከተዉ አመልካች በአካል ቀርባ አገር ዉስጥ ስለመኖሯ አረጋግጦ ሳይሆን ካላቸዉ ዳታ ዉስጥ ባደረገዉ ማጣራት መሆኑን ገልጽዋል፡፡ ይህ ማስረጃ በአካል ቀርባ ከሰጠችዉ ዉክልና ጋር ተመዝኖ የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ፡፡ በ01/03/2009 ዓ.ም በተጻፈዉ ደብዳቤ አመልካች በ5/03/2014 ወደ ሮም መሄዷን የገለጸ ሲሆን በ22/03/2009 ዓ.ም በጻፈዉ ደብዳቤ ላይ ደግሞ አመልካቿ በ09/02/2014 ወደ አገር ዉስጥ ገብታ በ05/06/2014 ከአገር መዉጣቷን ወይም ካናዳ መሄዷንና አገር ዉስጥ ተመልሳ ያልገባች መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይህም እርስ በርሱ የሚጋጭ ነዉ፡፡ በፎረንሲክ ፊርማዉ መጣራት ነበረበት የሚለዉም ቢሆን ዉክልናዉ የመንደር ዉል ሳይሆን

www.abyssinialaw.com

ስልጣን ከተሰጠዉ የመንግስት አካል ተረጋግጦ የቀረበ በመሆኑ ክርክሩ ተገቢነት የለዉም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነዉ በስር ፍ/ቤት አመልካች ክስ ያቀረቡት ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ ይዞታዬን በመያዝ የገነባዉን ግንባታ በራሱ ወጪ እንዲያፈርስ የሚጠይቅ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይዞታዉ አስቀድሞ የአመልካች የነበረ ቢሆንም በሕጋዊ መንገድ የዉክልና ስልጣን ካለዉ ሰዉ ጋር ተዋዉሎ መግዛቱንና ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካች ስልጣን ባለዉ የመንግስት አካል ጋር ቀርባ የዉክልና ቁጥሩ 052125 በሆነ ጥቅምት 01 ቀን 2008 ዓ.ም ለአቶ ፉአድ ጀማል ሙሳ ይዞታዉንና ንብረቱን እንዲሸጥ፣ እንዲለዉጥና ለ3ኛ ወገን በማንኛዉም መንገድ እንዲያስተላልፍ ዉክልና መስጠቷን፤ ተወካይዋ ደግሞ በተሰጠዉ ዉክልና መሠረት ለአቶ አህመድ በሪሶ ቁጥሩ 152845 በቀን 06/03/2008 ዓ.ም ምስራቅ ሸዋ ፍትሕ መምሪያ ቀርቦ ዉክልና መስጠቱን እንዲሁም አቶ አህመድ በሪሶ ደግሞ መጋቢት 05 ቀን 2009 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ባደረገዉ የሽያጭ ዉል ይዞታዉን ለተጠሪ ሸጦለት ቅድመ ሁኔታዎቹ ተሟልቶ የሊዝ ዉሉ ወደ ተጠሪ ስም መዛወሩንና የይዞታ ማረጋገጫና የግንባታ ፈቃድ የተሰጠዉ መሆኑ አረጋግጧል፡፡ ዉክልናዎቹ ትክክለኛ መሆናቸዉ እና በአግባቡ ሽያጭና የስም ዝዉዉር ተደርጎ ይዞታዉ ለተጠሪ መተላለፉን የምስራቅ ሸዋ ፍትሕ መምሪያና በአዳማ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ተጠይቀዉ አረጋግጠዋል፡፡

አመልካች አጥብቃ የምትከራከረዉ ዉክልና ሰጥታለች በተባለችበት ወቅት አገር ዉስጥ ያልነበረች መሆኑን ኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳዮች መስሪያ ቤት አረጋግጦልኛል እንዲሁም በዉክልናዉ ላይ ያለዉ ፊርማ የእኔ አይደለም፤ በፎረንሲክ ይመርመርልኝ በሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ አንድ የዉክልና ሰነድ ሰነዶችን ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት እንዲሰጥና እንዲመዘገብ ያስፈለገበት ዋናዉ ምክንያት ዉክልናዉ

www.abyssinialaw.com

ትክክለኛ እና በወካዩ አማካይነት የተሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ ዉክልናን መሠረት ተደርገዉ የሚፈጸሙ ሕጋዊ ተግባራት የተሳለጡ እንዲሆኑ ለማስቻልና ዉክልናዉ በወካይ አልተሰጠም የሚል አላስፈላጊ ክርክርና ጥርጣሬዎችን ለማስወገድ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ በአዋጅ ቁ/922/08 አንቀጽ 23/1/ ላይ እንደተደነገገዉ በሰነድ መዝጋቢዉ አካል የተረጋገጠዉ ሰነድ ሙሉ እምነት የሚጣልበት ማስረጃ ሆኖ ቅቡልነት ያለዉ ነዉ፡፡ ይህንን ሰነድ ቅቡልነት መቃወም የሚቻለዉም በበቂ ምክንያት ፍርድ ቤት ሲፈቅድ ብቻ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ ሁለት ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ሰነዱን የሚቃወሙበት በቂና ህጋዊ ምክንያት ካላቸዉ ሰነዱ እንዲሰረዝ በህግ አግባብ ከሚጠይቁ በስተቀር በሚመለከተዉ አካል የተረጋገጠ የዉክልና ሰነድ ቅቡልነት ሊኖረዉ አይገባም የሚለዉ ክርክር ስለሰነዶች ምዝገባ የወጣዉን አዋጅ ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ከተወካይ ጋር ዉል የሚገባ ሰዉ ዉክልናዉ በተወካይ የተሰጠና ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን ከማረጋገጥ ባለፈ ወካይ ዉክልናዉ በተሰጠበት ወቅት በአገር ዉስጥ መኖር አለመኖራቸዉንና ፊርማዉ የወካይ መሆን አለመሆኑን የሚያጣራበት አግባብ የለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ይዞታዉ በሽያጭ ዉል ተላልፎልኛል ያለበት ዉክልና በአመልካች ያልተሰጠና የሀሰት ነዉ በማለት የሚከራከሩት የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳዮች መስሪያ ቤት አመልካች ከአገር የወጣችበትና ወደ አገር የገባችበትን ቀን የገለጸ በመሆኑ ዉክልና በተሰጠበት ጊዜ በአገር ያልነበርኩ በመሆኔ ዉክልናዉን ልሰጥ አልችልም ፊርማዉ የእኔ ባለመሆኑ በፎረንሲክ ይመርመርልኝ የሚል ነዉ፡፡ ዉክልናዉ ሰነዶችን ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተሰጥቶ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች ከአገር የወጡበትና ወደ አገር የገቡበትን ጊዜ በማረጋገጥ እንዲሁም በዉክልናዉ ላይ ያለዉ ፊርማ በፎረንሲክ ቢመረመርና ልዩነት አለዉ ቢባል እንኳ ዉክልናዉ በአመልካች አልተሰጠም የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይሆንም፡፡ ስለሆነም አመልካች ከአገር የወጡበትን እና ወደ አገር የገቡበትን ጊዜ በማስረዳት እንዲሁም በዉክልና ሰነዱ ላይ ያለዉ ፊርማ ከአመልካች ከተለመደዉ ፊርማ ጋር ልዩነት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን በማስመርመር ዉክልናዉ በአመልካች አልተሰጠም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻል ባለመሆኑ፤ የስር ፍ/ቤት ዉክልናዉ በአመልካች የተሰጠና ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን ሰነዶችን ለመመዝገብና ለማረጋገጥ

www.abyssinialaw.com

ስልጣን ተሰጥቶት ዉክልናዉን የመዘገበዉን አካል በመጠየቅና በማረጋገጥ እንዲሁም በዉክልናዉ መሠረት የሽያጭ ዉል ተፈጽሞ ይዞታዉ ወደ ተጠሪ ስም በሕግ አግባብ ተላልፎ ተጠሪ ባለይዞታ የሆነበት መሆኑን በማረጋገጥ የአመልካችን ክስ ዉድቅ ማድረጉ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ በሕግ አግባብ ተላልፎለት የባለይዞታነት መብት መፍጠሩን በማረጋገጥ፤ አመልካች ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የያዘብኝን ይዞታ ይልቀቅልኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ ዉድቅ በማድረግ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉም ዉሳኔ ሆነ በየደረጃዉ ጉዳዩን የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዉን ማጽናታቸዉ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ ዉሳኔዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 98982 ታሕሳስ 18 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 25546 የካቲት 16 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 263062 ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 149861

**ቀን** - 30/09/2010ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

አብዬ ካሳሁን

**አመልካች፡-** አቶ ቶዉፊቅ ላሉ - ቀርበዋል ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ስራጅ ጀማል - ቀርበዋል ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በስልጤ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ክስም በአጭሩ በ2004 ዓ.ም ወደ አረብ አገር ስሄድ ዋጋቸዉ በድምሩ ብር 19,000.00 የሚያወጣዉን አንድ በሬ፣ አንዲት ላም ከነጥጃዋ እና አንዲት ሴት አህያ ተከሳሽ እንዲጠብቅልኝ አደራ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም መኖሪያ ቤት እና ንግድ ቤት እንዲገዙልኝ አረብ አገር ሆኜ ብር 320,000.00 የላኩላቸዉ ቢሆንም ተከሳሽ ብር 120,000.00 መልሰዉልኝ ቀሪዉን ገንዘብ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆኑም፤ በመሆኑም ከብቶቹን እንዲሁም ቀሪዉን ገንዘብ ብር 200,000.00 ተከሳሽ እንዲመልሱ ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

ተጠሪ ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ በክሱ የተጠቀሱትን ከብቶች ከከሳሽ በአደራ አልተቀበልኩም፤ ከሳሽ ቤት እንዲገዛላቸዉ ዉጭ አገር ሆነዉ የላኩልኝ ገንዘብ የለም፤ ተከሳሽ ተከፍሎኛል ያሉት ብር 120,000.00 ብድር የሰጠሁት ነዉ በማለት የቀረበባቸዉ ክስ ዉድቅ እንዲሆን በማለት ተከራክረዋል፡፡ በበኩላቸዉ ባቀረቡት የተከሳሽ

ከሳሽነት ክስ በብድር መልክ በባንክ ሂሳባቸዉ ገቢ ያደረግኩትን ገንዘብ ብር 120,000.00 ከሳሽ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ከተጠሪ የተበደርኩት ገንዘብ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ከግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር እንዲሁም ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች ከብቶቹን ለተጠሪ አደራ መስጠቱን ለማስረዳት ቀርበዉ የተሰሙት የሰዉ ምስክሮች ቃል የተለያየ እና እርስ በርሱ የሚጋጭ በመሆኑ በግራ ቀኝ መካከል በህግ አግባብ የተደረገ የአደራ ዉል ስለመኖሩ አለመረጋገጡን፤ እንዲሁም ከብር 500 በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብን በአደራ የመስጠት ዉል ስለመኖሩ ማስረዳት የሚቻለዉ በጽሑፍ በተደረገ ዉል መሆኑን እና አመልካች በዚህ መልኩ ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን (የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2782(1) እና 2472(1) በዋቢነት በመጥቀስ) የአመልካችን ክስ ዉድቅ ያደረገ ሲሆን፤ ተጠሪ ለአመልካች ብር 120000.00 አበድሬያለሁ ያሉትንም በተመለከተ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2472(1) መሠረት ይህን የሚያስረዳ በጽሑፍ የተደረገ የብድር ዉል አለመኖሩን ጠቅሶ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱንም ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናቱ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 20/03/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታ በስር በክልሉ በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ዉሳኔዎች እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ናቸዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ነዉ፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጡትን ዉሳኔ አግባብነት ከግራ ቀኝ ክርክር እና

ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ላቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት ተጠሪ የተለያዩ ከብቶችን ሲጠብቁላቸዉ በአደራ መቀበላቸዉን እንዲሁም ቤት እንዲሰሩላቸዉ አመልካች የላኩትን ገንዘብ ተቀብለዉ አለመመለሳቸዉን ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸዉ ከብቶቹንም ሆነ ገንዘቡን ከአመልካች በአደራ አለመቀበላቸዉን ገልጸዉ የተከራከሩ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካች በክሱ የተመለከቱትን ከብቶችም ሆነ ገንዘቡን ለተጠሪ በአደራ መልክ የሰጣቸዉ ስለመሆኑ በቅድሚያ የማስረዳት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ ከብቶቹን በአደራ መስጠታቸዉን በተመለከተ አመልካች የሰዉ ምስክሮችን አቅርበዉ ያሰሙ ሲሆን፣ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም አመልካች ያቀረቧቸዉን የሰዉ ምስክሮች ቃል በመመዘን፣ የቀረቡት የሰዉ ምስክሮች ቃል የተለያየ እና እርስ በእርሱ የሚጋጭ መሆኑን ጠቅሶ የአደራ ዉል በመካከላቸዉ ስለመደረጉ አላስረዱም በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ተመልክተናል፡፡ በሌላ በኩል በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3-ለ) እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተትን በማረም ላይ የተገደበ በመሆኑ ከፍሬ ነገር ጋር በተያያዘ በስር ፍርድ ቤቶች የቀረቡትን ማስረጃዎች ድጋሚ ሊመዝን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለሆነም አመልካች በክሱ የተመለከቱትን ከብቶች ለተጠሪ በአደራ ስለመስጠቱ አልተረጋገጠም በሚል የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የማይቻል በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

ከዉጭ አገር የተላከ ገንዘብን በተመለከተ አመልካች የሚከራከሩት ተጠሪ የንግድ እና የመኖሪያ ቤት እንዲሰሩላቸዉ ገንዘቡን መላካቸዉን ነዉ፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ የተላከላቸዉ የአደራ ገንዘብ አለመኖሩን ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡ የስር የወረዳዉ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ እንዳመለከተዉም፣ በአደራ የተሰጠ ገንዘብ መኖሩን ለማስረዳት ተቀባይነት የሚኖረዉ ማስረጃ በጽሑፍ የተደረገ የአደራ ዉል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2782 እና 2472(1) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና አመልካች በዚህ መልኩ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በሌላ የሰዉ ወይም የሰነድ ማስረጃ ደግሞ ይህን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

www.abyssinialaw.com

በአጠቃላይ የስልጤ ወረዳ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ሰበር ችሎት የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት፣ በቅደም ተከተል፣ የሰጡት ፍርድ እና ትዕዛዝ በህግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነዉም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉ ሳ ኔ**

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 08453 በቀን 20/12/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የስልጤ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/11642 በቀን 19/06/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/13236 በቀን 25/09/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀን 30/05/2010 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ ዕግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

አ/ጉ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.162776

ታህሳስ 26 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች - ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - አቶ ሰለሞን መርደኪዮስ- ቀረቡ::

ተጠሪ - አቶ ሲሳይ ለበኔ- አልቀረቡም::

በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ከሰ/መ/ቁ 162774 ጋር በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታዎቹ መቅረብ ምክንያት የሆነው ክርክር የተጀመረው ተጠሪ በአመልካች ላይ በደቡብ ክልል አርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት ክስ፡- ከገኔ ዩናይትድ የመኪና አስመጪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር በነበረን ውል መሰረት ቅድመ ክፍያ ብር 160,000.00 (መቶ ስድሳ ሺህ) በመክፈል ሚኒባስ መኪና ለመውሰድ ስጠባበቅ ድርጅቱ የኢኮኖሚ ችግር ገጥሞት ሊፈጽም ባለመቻሉ የአሁኑ አመልካች ለድርጅቱ ከሚከፍለው ብር 254,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ አራት ሺህ) ውስጥ የእኔን ገንዘብ ሊከፍል የዕዳ ማስተላለፍ ውል አድርገናል፡፡ ነገር ግን አመልካች ብር 4,000.00 (አራት ሺህ) ብቻ ከፍሎ ሌላውን ስልላከፈለ ቀሪውን ብር 156,000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ) ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም በውሉ ከተመለከተው ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) መቀጮና ክርክሩ ካስከተለው ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ በውሉ መሰረት የዕዳ መክፈያ ጊዜ ገና ወደፊት ነው፤ በየሳምንቱ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ) ለመክፈል የተስማማን ሲሆን የሁለት ሳምንት ብር 4,000.00 (አራት ሺህ) እንደከፈልኩ ውሉ እንደተቋረጠ አድርጎ መክሰሱ

www.abyssinialaw.com

ያላግባብ ነው፤ ዕዳው በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሳይሆን በ80 ሳምንታት የሚከፈል ነው፤ መኪናዬ ላይ የደረሰው ብልሽት ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት መሆኑን እያወቀ ክስ መመስረቱም ያላግባብ ነው፤ ስለሆነም በየሳምንቱ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ) እየከፈልኩ ዕዳውን እንድጨርስ ይወሰን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ እንደውሉ ግዴታውን ያልተወጣ ተከሳሽ ስለመሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠና ተከሳሽ በመኪናው መበላሸት ምክንያት እንደውሉ አለመፈጸሙን የገለፀ ቢሆንም ስለመኪናው መበላሸት በውሉ ላይ ያልተገለፀ በመሆኑ መከላከያ ሊሆን አይችልም፤ በሌላ በኩል በውሉ አንቀጽ 6 መሰረት መቀጮ ብር 50,000.00 ሊከፍል እንደሚገባ የተመለከተ ቢሆንም ይህ የመቀጮ ገንዘብ የተጋነነ እና ለህግና ለሞራል ተቃራኒ በመሆኑ ሊሻሻል ይገባል በማለት ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ያልከፈሉትን ብር 156,000.00 ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ እንዲሁም ከሳሽ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር እንዲያቀርቡ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን ተጠሪ በውል የተመለከተው የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል አለመወሰኑን በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተከሳሽ የውል ግዴታውን በአግባቡ አለመወጣቱ በማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ በውል የተመለከተው መቀጮ ሊከፈል አይገባም መባሉ አላግባብ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አሻሽሎ በውላቸው የተቀመጠውን ብር 50,000.00 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን ተጠሪ ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የሰበር ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር መርምሮ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች ዋናውን ገንዘብ ብር 156,000.00 እና በውላቸው የተስማሙበትን ብር 50,000.00 ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል፤ መቀጮ እንዲከፍሉ የተወሰነ በመሆኑ ወለድ 9% ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ነሓሴ 18/2010 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ገና ወደፊት ሰማንያ ሳምንት የክፍያ ጊዜ ላለው ዕዳ መቀጮ እንድከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀና ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥቅምት 29/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ውሳኔ የተሰጠው በመካከላችን የተደረገውን ውል እና የቀረበውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በመሆኑ እንዲሁም የሰበር ቅሬታው የተፈጸመውን የህግ ስህተት የሚያሳይ ባለመሆኑ ውድቅ ተደርጎ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል በሰ/መ/ቁ 162774 የተያዘው ጉዳይ የወጪና ኪሳራን የተመለከተ ነው፡፡ ተጠሪ በአርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወጪ ዝርዝር አቅርበው ፍርድ ቤቱ ዝርዝሩን መርምሮ ውሳኔ ባገኘው አጠቃላይ ብር 206,000.00 ላይ የጠበቃ አበል 7% ብር 14,420.00፣ የዳኘነት ብር 4,850.00፣ የምስክር አበል ብር 100.00፣ የቴምብር ብር 52.00 በድምሩ ብር 19,422.00 (አስራ ዘጠኝ ሽህ አራት መቶ ሃያ ሁለት) የአሁን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጠበቃ አበል አሻሽሎ 5% ብር 10,300.00 ሊሆን ይገባል በማለት ሌላውን ዝርዝር ተቀብሎ በአጠቃላይ ብር 15,302.00 (አስራ አምስት ሽህ ሶስት መቶ ሁለት) ወጪ እንዲተካ ወስኗል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎትም ይህን ውሳኔ ተቀብሎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ነሃሴ 12/2010 ዓ.ም ለዚህ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ቅሬታ የሥር ፍርድ ቤቶች የመቀጮውን ብር 50,000.00 አካተው የጠበቃ አበል እንዲታሰብበት ማድረጋቸው ስህተት ስለሆነ የጠበቃ አበል መታሰብ ያለበት ከዋናው ዕዳ ብር 156,000.00 ላይ ብቻ መሆን አለበት ተብሎ እንዲታረም ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ውሳኔው እንዲፀና በመከራከር መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ሲሆን በበኩላችን ቅሬታ በቀረበባቸው ውሳኔዎች የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

እንደመረመርነው የዕዳ ማስተላለፍ ውል መደረጉና ስምምነት ከተደረገበት ገንዘብ ውስጥ አመልካች ብር 4,000.00 (አራት ሺህ) ብቻ ከፍለው ቀሪውን ብር 156,000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ) ያልከፈሉ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ለክሱ በሰጡት መልስ ዕዳው በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሳይሆን በ80 ሳምንታት የሚከፈል መሆኑንና በየሳምንቱ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ) እየከፈልኩ ዕዳውን እንዲያጠናቅቁ እንዲደረግ ተከራክረው የነበረ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ማስረጃውን ተመልክቶ ዕዳውን በአንድ ጊዜ እንዲከፍሉ ሲወስን የበኩላቸውን ይግባኝ ለበላይ ፍርድ ቤቶች አላቀረቡም፡፡ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቅሬታ ያቀረቡት የአሁን ተጠሪ ሲሆኑ ቅሬታቸውም በውል የተመለከተው የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል አለመወሰኑን የተመለከተ ነበር፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች ገና ወደፊት ሰማንያ ሳምንት የክፍያ ጊዜ ያለው ዕዳ ነው በማለት በዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው አይሆንም፡፡

ይልቁንም የዚህን ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚጠይቀው ቀዳሚ ጭብጥ እንደውሉ እንዲፈፀም እንዲሁም የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠው ውሳኔ ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ያልተከፈላቸው ቀሪ ብር 156,000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ) ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም በውሉ ከተመለከተው ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) መቀጮ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሳኔ የሰጡ ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች ዋናውን ገንዘብ ብር 156,000.00 እና በውላቸው የተስማሙበትን ብር 50,000.00 መቀጮ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ነገር ግን መቀጮ እንዲከፍሉ የተወሰነ በመሆኑ ወለድ 9% ሊከፍሉ አይገባም ብሏል፡፡

የገደብ (የመቀጫ) ስምምነት በተደረገ ጊዜ ባለገንዘቡ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ውሉ እንዲፈፀም እንዲሁም የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(1) ሥር የተደነገገ ሲሆን በዚህ ረገድ ባለገንዘቡ ያለው መብት ግን የተገደበ መሆኑን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(2) መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(2) እንደተመለከተው፡-

www.abyssinialaw.com

"ኪሳራው የተወሰነው ለሥራው አፈፃፀም መዘግየት ብቻ ወይም ለተጨማሪ ግዴታዎች አለመፈፀም ካልሆነ በቀር ባለገንዘቡ ውሉ እንዲፈፀምና (ገደቡን) መቀጮውንም እንዲቀበል ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ለመጠየቅ አይችልም" ::

የድንጋጌው የእንግሊዝኛ ቅጅም:--

"He may not require both the enforcement of the contract and the penalty unless the penalty was provided in respect of delay or the non-performance of a collateral obligation" በማለት ይደነግጋል፡፡

ከፍሲል ከተጠቀሰው ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(1) የተመለከተው ድንጋጌ ተጠቃሚ ለመሆን መቀጮ የሚከፈለው የውሉ መዘግየት ወይም ተጨማሪ ግዴታዎች ካሉ የእነዚህ አለመፈፀም የመቀጮውን ክፍያ የሚያስከትል ሲሆን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት የውል ግዴታውን ያልተወጣ ወገን ውሉን ላከበረው ወገን መቀጮ ብር 50,000.00 ለመክፈል የተስማሙ መሆናቸውን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ይህ በመዘግየት የሚከፈል ኪሳራ ስለመሆኑና ከተጨማሪ ግዴታዎች አለመፈፀም ጋር የሚያያዝ ስለመሆኑ በማረጋገጥ የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ዋናው ዕዳ ተከፍሎ እንደውሉ እንዲፈፀም እና መቀጫ (ገደብ) ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) እንዲከፈል መወሰኑ የፍብ/ህ/ቁ 1890(2) ድንጋጌን እና የውሉን ይዘት እንዲሁም የግራቀኙን ክርክር መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መቀጮ እንዲከፈል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤቶች የመቀጮውን ብር 50,000.00 አካተው የጠበቃ አበል እንዲታሰብበት ማድረጋቸው ተገቢ ስለማይሆን የጠበቃ አበል 5% መታሰብ ያለበት በዋናው ዕዳ ብር 156,000.00 ላይ መሆን አለበት ብለናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል መንግስት የአርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 22052 በ29/01/2009 ዓ.ም፣ የጋሞ አካ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 32690 በ27/04/2010 ዓ.ም፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 22190 በ18/07/2010 ዓ.ም እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 26735 በ20/11/2010 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. አመልካች ዋናውን ዕዳ ብር 156000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺ.ህ) የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ከ29/01/2009 ዓ.ም ጀምሮ ዕዳው ተከፍሎ እስካለቀበት ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡
3. ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ በተመለከተ የአርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 22858 በ06/07/2010 ዓ.ም፤ የጋሞ አካ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 33355 በ26/08/2010 ዓ.ም፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 27034 በ30/11/2010 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡ ውሳኔ ባገኘው ብር 156,000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺ.ህ) ላይ የጠበቃ አበል 5% ብር 7800.00፣ የዳኝነት ብር 4,850.00፣ የምስክር አበል ብር 100.00፣ የቴምብር ብር 52.00 በአጠቃላይ የአሁን አመልካች ብር 12,802.00 (አስራ ሁለት ሺ.ህ ስምንት መቶ ሁለት) ወጪ ለተጠሪ እንዲተኩ ወስነናል፡፡
4. ሌላውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ተገልብጦ ከሰ/መ/ቁ 162774 ጋር ይያያዝ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር 133398

ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች :- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች :- አቶ ጉልላት ግዛው - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ :- አቶ ጥላሁን ኃይሉ - አልቀረቡም፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሆኖ በስር ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ ደግሞ አመልካች በመሆን በመኪና ሽያጭ ውል መነሻነት ተከራክረዋል፡፡

በስር ቀርቦ የነበረው ክስ የሚያመለክተው ከሣሽ የሠ.ቁ. 02-99421 አ.አ. የሆነውን የተከሣሽን የጭነት ተሽከርካሪ ምንም ዓይነት ችግር የሌለበት መሆኑን አረጋግጠው ታህሳስ 06 ቀን 2005 ዓ.ም. በተፈረመ የመኪና ሽያጭ ውል መግዛታቸውን እና ከቤት መኪናነት ወደ ግል ተሽከርካሪነት ለማዛወር ለሚመለከተው የትራንስፖርት ጽ/ቤት ሲጠይቁ መኪናው በባለሙያ ተመርምሮ የመኪናው ቁጥርና ሻንሲ የተመታ መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠቀሰው እንደማይሠጣቸው የተገለፀላቸው በመሆኑ መኪናው ጉድለት እንዳለበት እያወቀ ከሣሽ ወደ ስህተት በመምራት ውሉን እንድንፈራረም ያደረጉት ያለአግባብ ስለሆነ ውሉም ሊፈፀም በሚችል አቅም ያልተመሠረተ ስለሆነ የመኪና ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ፣ ተከሣሽ ከሽያጭ ጋር

www.abyssinialaw.com

በተያያዘ ከከሣሽ ላይ የተቀበለውን የሽያጭ ገንዘብ ከሣሽ መኪናውን ከገዛው በኋላ ለማስተካከል ያወጡትን ወጭ በአጠቃላይ ከሕጋዊ ወለድ ከክርክር ወጪና ኪሣራ ጭምር እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው የጠየቁ መሆኑን ተመልክተናል፡፡

ተከሣሽ በሰጡት መልስ መኪናውን መሸጣቸውን ማመናቸውን ነገር ግን ሊብሬ ወደ ገዢ ሳያዛውሩ የተባለው ችግር በመኪናው ላይ ያለ መሆኑን በፍፁም እንደማያውቀ፣ በባለሙያ ተመርምሮ የተላለፈ መሆኑን፣ ከሣሽ ከተረከበው ጀምሮ በእጃቸው ሆኖ ጋራዥ እንደነበረ፣ ጉድለቱ ሲሸጥ ያልነበረ መሆኑን ኃላፊነቱም ለገዢ የተላለፈ መሆኑን፣ በመግለጽ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት አቅርበዋል፡፡ ወደ ነበርንበት ለመመለስም አንችልም ብለዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ውሉ ጉድለት ያለበት ነው ወይንስ አይደለም ? መኪናውን ከሣሽ ከገዛ በኋላ ወጪ አዋ ቷል ወይንስ አላወጣም የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡

አጠቃላይ ክርክሩን ከተመለከተ በኋላም በግራ ቀኙ መሐከል የመኪና ሽያጭ ውል መኖሩ አለማከራከሩን፣ በሽያጭ ውሉ ላይ ጉድለት አለ ወይንስ የለም የሚለው በቅድሚያ መለየት የሚገባ መሆኑን እና የተሸጠው መኪና ሻንሲ እና ቁጥር የተመታ በመሆኑ መሸጥ መለወጥ የማይቻል መሆኑ በመንገድ ትራንስፖርት ፅ/ቤትም ከኮድ 2 ወደ ኮድ 3 መለወጥ እንደማይቻል መከልከሉን በመያዝ የተሰሙ ምስክሮችን ቃል ሲመረመርም መኪናው ከመሸጡ በፊት በባለሙያ/መካኒክ/ የተመረመረ ቢሆንም መካኒክ ሲመረምር ሻንሲው የተመታ መሆኑን መለየት ይችላል ብለው ተከሣሽም ያነሱት ክርክር የሌለ እና የተረጋገጠም ባለመሆኑ ከቀረበው የማስረጃ ክብደት አንፃር የሠ.ቁ. ኮድ 2-99421 አአ የሻንሲ ቁጥር YN 52-009146 የሞተር ቁጥር 3Y-02313681 በማስመሰል የተመታው ከሽያጭ ውሉ በፊት በተከሣሽ እጅ ላይ እያለ የነበረ ጉድለት መሆኑን ፍ/ቤቱ ግንዛቤ መውሰዱን ገልጿል፡፡

ይህ ጉድለት ውል እንዲፈርስ ምክንያት ይሆናል ወይ የሚለውን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2289 ሻጭ ዋቢ ሊሆንባቸው የሚገባቸው ጉድለቶች የሸጠው ነገር ለደንበኛው አገልግሎት ወይም ለንግድ ሥራ ጥራትነት የሌለው ዕቃ ከሆኑ በማለት

www.abyssinialaw.com

የሚደነግግ በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ሻጭ ዋቢ ሊሆንለት የሚችል ጉድለት የተገኘበት ስለሆነ ሊፈርስ የሚገባው ውል ነው በሚል ወስኗል፡፡ ወጪን በተመለከተ ግን ከሣሽ ወጪዎችን ያስረዱልኛል ብለው ያቀረቧቸውን ደረሰኞች እያንዳንዳቸውን በመመልከት የቀረበውን ወጪ ያስረዱም በማለት ውድቅ አድርጐ መኪናው የተሸጠበትን ገንዘብ ብር 110000.00/ አንድ መቶ አስር ሺ ብር/ እና ብር 5798.00/ አምስት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር/ በመጨመር ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲመልስ፣ ከሣሽ ደግሞ የሠ.ቁ. 2-99421 አ.አ. የሆነውን ተሽከርካሪ አሁን ባለበት ሁኔታ ለተከሣሽ እንዲያስረክቡ መሆኑን በመ/ቁ/ 39866 ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም. የሰጠው የውሣኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች ይግባኝ ቢሉም ይግባኝ ቅሬታውን የመረመረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና አከራክሮ በመ/ቁ/ 156835 ህዳር 16 ቀን 2008 በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በሚል ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው የካቲት 11 ቀን 2008 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ክርክር ያስነሳውን ተሽከርካሪ እዳ እና እገዳ የሌለበት መሆኑ ተረጋግጦ ከሣሽ በስማቸው አዛውረዋል፣የባለቤትነት ደብተርም ተጠሪ በስማቸው አውጥተዋል፡፡

ተጠሪ መኪናውን ሲገዙ በተለመደው አሰራር የራሳቸውን ባለሙያ አምጥተው አስመርምረዋል፡፡ ውሉ ከተደረገ ከ5 ወር በኋላ በ9/07/2005 ዓ.ም. የመኪናውን አገልግሎት ከኮድ 2 ወደ ኮድ 3 ለመቀየር ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ የመኪናው ሞተርና ሻንሲ የተመታ መሆኑን የተገለፀላቸው ቢሆንም አመልካች ይህ ጉድለት ስለመኖሩና መቼ እንደተከሰተም የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ ከቅን ልቦና ውጭ ያቀረቡት ጥያቄ ውሉ በመሳሳት የተደረገ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ሽያጩ የተደረገው በታህሳስ 06 ቀን 2005 ዓ.ም. ሲሆን ተጠሪ መኪናውን እስካሁን ድረስ እየተጠቀሙበት የሚገኙ ከመሆኑ አኳያ የመኪና ሽያጭ ውሉ በመፍረስ ወደነበርንበት እንዲመለሱ ቢደረግ

www.abyssinialaw.com

አፈፃፀሙ አዳጋች ነው በሚል የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመው ስህተት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎት ሊጣራ የሚገባውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡ ለችሎቱ እንዲቀርብ በማድረጉ ሊቀርብ ችሏል፡፡ አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪ ደርሶ መልስ እንዲያቀርቡ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው በመሆኑ ጥር 24 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ካቀረቡት በጥቂቱ፡- ውል እንዲፈርስ ክስ ያቀረብኩት ውሉ ከተደረገ እና መኪናውን ከተረከብኩ ከ3 ቀን በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም መኪና ከተረከብኩ ከ3 ዓመት በኋላ ውል እንዲፈርስ ክስ አላቀረብኩም፣ መኪናውን በትራንስፖርት ቅርንጫፍ ባለሙያ አስመርምረው አላስረከቡኝም፣ በመኪናው ላይ ጉድለት ያለበት መሆኑ የታወቀው ተጠሪ መኪናውን ከቤት አገልግሎት ወደ ንግድ ተሽከርካሪነት ለመለወጥ አስቤ መኪናው በትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባለሙያ በተመረመረበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አግባብ በመሆኑ የተፈፀመበት የህግ ስህተት የለውም ተብሎ አቤቱታው ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም አጠቃላይ የቀረበውን ጉዳይ አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ከላይ በስር የቀረበው ክስ ላይ ታህሳስ 06 ቀን 2005 ዓ.ም. ክርክር ያስነሳውን ተሽከርካሪ ሽያጭ ውል ግራ ቀኙ በማድረግ የሽያጭ ገንዘቡንም ብር 110000.00 ሻጭ መቀበላቸውን ገዢም መኪናውን መረከባቸውን የተካደ ባለመሆኑ አለማከራከሩን ተመልክተናል፡፡ ሆኖም መኪናው በተገቢው ርክክብ ከተደረገ በኋላ ስመ ሀብትም ከዞረ በኋላ የመኪናውን አገልግሎት ለመቀየር ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ጥያቄው ቀርቦ ሲፈተሽ ግን የሻንሲው ቁጥር የተመታ መሆኑ በመረጋገጡ በቀይ ሰሌዳ ላይ የተመዘገበ በመሆኑ አገልግሎቱን ማግኘት እንደማይቻል ለተጠሪ የተገለፀላቸው በመሆኑ ውሉ ጉድለት ባለበት ንብረት ላይ የተፈፀመ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ ጠይቀዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

አሁን እያከራከረ ያለው ጭብጥ መኪናው ከሻጭ ወደ ገዢ ከመተላለፉ በፊት በመካኒክ ተፈትሾ የተላለፈ በመሆኑ ኃላፊነት ለገዢ ተላልፏል ሊባል ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለው ነጥብ ላይ ይሆናል፡፡

በስር ፍርድ ቤት መኪናው በአግባቡ ተጠሪ ራሣቸው ባመጡት ሜካኒክ ተፈትሾ እና ተነድቶ ጉድለት የሌለበት መሆኑ ተረጋግጦ ገዢ የተረከቡ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ይህ የመካኒክ ፍተሻ የሻንሲ እና የሞተር ቁጥር ኦርጅናልነት ጨምሮ የሚያረጋግጥ ነው ወይንስ አይደለም የሚለው በአመልካች በስር ክርክር የተደረገበት ባይሆንም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግን ተነስቶ የነበረ በመሆኑ በዚህ መልኩ አመልካች መኪናው ተፈትሾ ለገዢ መተላለፉን ስለማስረዳታቸው የተቀመጠ ነገር የለም፡፡

በኑሮ ልማድ እውቀት እንደሚታወቀው መካኒክ የሚፈትሸው ጉድለት ከመኪናው ጤነኝነት ማለትም አገልግሎት መስጠት እና አለመስጠት ጋር በተያያዘ እንጂ የሻንሲን እና የሞተርን ቁጥር ኦርጅናልነትን የሚጨምር አይደለም፡፡ ይህ ማለት አመልካች መኪናውን ሲሸጡ ይህ ጉድለት መኖሩን ያውቁ ነበር ለማለትም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካችም በአቤቱታቸው እንደገለፁት መኪናው የተላለፈላቸው ከሌላ ሰው መሆኑን የገለፁ በመሆኑ ይህን ምርመራ የመካኒክ ምርመራ የሚያካትት ቢሆን ኑሮ ቀድመው የሚያውቁበት እድል ይኖራቸው ነበር፡፡

ሆኖም አመልካች ጉድለቱ መኖሩን በፍፁም አላውቅም በማለት ይከራከሩ እንጂ ጉድለቱ የለም አላሉም፣ እያነሱ ያሉት ርክክብ ከተፈፀመ በኋላ ከእጄ ወጥቶ በተጠሪ እጅ ገብቷል ስለሆነም ኃላፊነት ተላልፏል የሚል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ኃላፊነት ተላልፏል ጉድለቱ አይመለከተኝም ለማለት ደግሞ ቀድሞ ጉድለቱ ያለመኖሩን በእርግጠኝነት ማረጋገጥ የሚገባው ኃላፊነቱ ከተላለፈ በኋላ ነው ጉድለቱ የደረሰው የሚለው ወገን መሆን ይኖርበታል፡፡

እንዲህ ከሆነ ጉድለቱ መኖሩ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ጉድለት ደግሞ ገዢን አንድ የንብረት ባለቤት ሊያገኝ የሚችለውን መብት የሚቀንስ ወይም ጨርሶ የሚያሳጣ ከሆነ ውሉ የተፈፀመው በመሳሳት በመሆኑ የማይፈርስበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይህን

www.abyssinialaw.com

ተሽከርካሪ ተጠሪ የአገልግሎት ዘርፍ በመቀየር ሥራ ላይ ለማዋል የማይችሉ እና በትራንስፖርት ባለሥልጣን አባባል ቀይ ሰሌዳ ላይ የተመዘገበ በመሆኑ የገዙትን ንብረት ስም ብቻ ማዛወራቸው ንብረቱን ህግ በሚፈቅደው መልክ በመቀየር ሊጠቀሙ የማያስችላቸው አዳጋች ነገር ተፈጥሮባቸዋል፡፡ ስለሆነም የገዙትን ንብረት በፈለጉት መልኩ መጠቀም የማያስችል ሁኔታ መፈጠር ደግሞ ውሉ ከመደረጉ በፊት ችግሩ/ጉድለቱ እንዳለ ቢያውቁ ኑሮ ውሉን አይፈጽሙም ነበር የሚያሰኝ በመሆኑ ጉድለት ያለበት ውሉ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት እንዲፈርስ መወሰኑ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሠረት ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊያስብል የሚችል ምክንያት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማጽናት አቤቱታውን አልተቀበልነውም ስለሆነም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 156835 ህዳር 16 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡት ወጪ ካለ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡
4. መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 153664

**ቀን** - 29/01/2011

**ዳኞች:-**

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዮ ካሳሁን

**አመልካች:-** ወ/ሮ አሻ ፋራህ -ጠበቃ ጣሂር ሼህ አብዱላህ

**ተጠሪዎች:-**

1. አቶ አብዱራህማን ጣሂር
2. ዮሱፍ አሊ ዩሱፍ
3. ሀሰን አሊ ዩሱፍ
4. ሳላህ ኢብራሂም
5. ሮዉዳ አሊ ዩሱፍ
6. ረሺድ አሊ ዩሱፍ
7. ኢስማሃን አሊ ዩሱፍ
8. በድሪያ ኢብራሂም ግራድ
9. ሀሰን ኢብራሂም ኢጋል

} አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል መንግስት በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ተጠሪዎች ከሳሽ፣ አመልካች እና በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነዉ አቶ ሰኢድ አሊ፣ በቅደም ተከተል፣ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪዎች ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ እናቶቻችን ከአያታችን የወረሱት እና በዉርስ ሊተላለፍልን የሚገባ ቦታ 2ኛ ተከሳሽ በህገ ወጥ መንገድ ለ1ኛ ተከሳሽ በሽያጭ በማስተላለፉ ዉሉ ፈርሶ ቦታዉ ይመለስልን የሚል ነዉ፡፡ ተከሳሾች ለፍርድ ቤቱ ቀርበዉ በሰጡት መልስ፤ ቦታዉ ለ2ኛ ተከሳሽ በተለይ ከእናቱ የተሰጠዉ መሆኑን፣

www.abyssinialaw.com

ከሳሾች ከቦታዉ የዉርስ ድርሻ የሌላቸዉ መሆኑን፣ ቦታዉን 2ኛ ተከሳሽ ቆርቆሮ ቤት ሰርቶበት በህጋዊ መንገድ ለ1ኛ ተከሳሽ የሸጠ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ እና ቆርቆሮ የተሰራበት ቦታ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ባደረጉት የሽያጭ ዉል መሠረት በአመልካች እጅ እንደሚገኝ በማስረጃ መረጋገጡን ገልፆ ቤትና ቦታዉ የአመልካች ነዉ በማለት የተጠሪዎችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ ለክስ ምክንያት የሆነዉ ዉል በሚመለከተዉ አካል ዘንድ የተመዘገበ እና የተፈረመም አለመሆኑን፣ ተጠሪዎች ወራሾች መሆናቸዉን እና ለስር 2ኛ ተከሳሽ ለብቻዉ የተሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ ንብረቱ ለተጠሪዎች ሊመለስላቸዉ ይገባል፤ አመልካች በቦታዉ ላይ ቤት ለሰራችዉ ቤት ግምቱን ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ፤ አመልካች በዉሉ ምክንያት ያጣችዉ መብት ካለ በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ ክስ የማቅረብ መብት አላት በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎት የስር 2ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ዉሉ መሠረት የወሰደዉን ገንዘብ ለአመልካች ሊመለስ ይገባል በሚል ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በዚህ ረገድ የሰጠዉን የዉሳኔ ክፍል ብቻ በመሻር ቀሪዉን በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 05/06/2010 ዓ. ም ተዘጋጅቶ በጠበቃዋ አማካይነት በቀረበ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ፤ ተጠሪዎች ወራሾች መሆናቸዉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ፣ እንዲሁም በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ ዉል ተገቢዉን ፎርም ያሟላ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ የቀረበዉ ክርክር በሌለበት ሁኔታ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ በመሻር የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ተከራክራለች፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤት እና ቦታ በአመልካች እጅ ሊገባ የቻለዉ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ባደረጉት የሽያጭ ዉል መሠረት ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት ቤትና ቦታዉ ከአያታቸዉ በዉርስ ሊተላለፍላቸዉ የሚገባ መሆኑን ሲሆን፣ አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ በበኩላቸዉ ቤትና ቦታዉ ለስር 2ኛ ተከሳሽ (ሽያጭ) በግል የተሰጠዉ እንጂ የዉርስ ሀብት አለመሆኑን ገልጸዉ የተከራከሩ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይሁንና ቤትና ቦታዉ ቀደም ሲል የተጠሪዎች አያት የነበረ ሆኖ ለተጠሪዎች በዉርስ የተላለፈላቸዉ እንጂ ለስር 2ኛ ተከሳሽ በግል የተሰጠዉ ያለመሆኑን ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን በተሰጣቸዉ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉ ይህ ከሆነ፣ በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገዉ እና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ህጋዊ ዉጤት የሚያስከትል መሆን ያለመሆኑን ስለ ጉዳዩ ከሚደነግገዉ የፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌ ጋር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንደሚታወቀዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለዉ ልዩ ባህርይ አንፃር፣ ንብረቶቹን ከአንድ ወደ ሌላ ሰዉ ለማስተላለፍ የሚደረጉ አሠራሮች እና ስርዓቶች ጥብቅ መሆን እንዳለባቸዉ ይታወቃል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከአንዱ ወደ ሌላ ሰዉ ማስተላለፍ ስለሚቻልበት ሁኔታ በተመለከተ በፍትሐብሔር ህጋችን የተለያዩ አንቀፆች የተደነገጉ ድንጋጌዎችም ይህኑን የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ከእነዚህም ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ በህጉ አንቀጽ 2878 ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ለሌላ ሰዉ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በሦስተኛ ወገን ላይ ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተም፣ ተጠሪዎች ከቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ያደረገችዉ ዉል ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ የሽያጭ ዉሉ በህግ አግባብ የተመዘገበ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለባት፡፡ ሆኖም ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ዉል በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ያልተመዘገበ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ለክርክሩ ምክንያት

www.abyssinialaw.com

የሆነዉ ዉል የሚጸናበት የህግ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል የሚባል ከሆነ ደግሞ የስር 2ኛ ተከሳሽ (ሻጭ) ሰዒድ አሊ ዩሱፍ በዉሉ ምክንያት የተቀበለዉን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ይህን እንዲያደርግ ሌላ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልግ በዚሁ መዝገብ ላይ መወሰን የሚቻል በመሆኑ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉን የዉሳኔ ክፍል በመሻር የደረሰበት ድምዳሜም በአግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤትና ቦታ የተጠሪዎች የዉርስ ድርሻ ያለበት መሆኑ እስከተረጋገጠ እና አመልካች ቤትና ቦታዉን ለመግዛት ያደረጉት ዉልም በህግ አግባብ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ያልተመዘገበ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የስር 2ኛ ተከሳሽ የሽያጩን ገንዘብ ለአመልካች እንዲመልስ በሚል የተሰጠ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 05-1-101/09 በቀን 04/03/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
3. አመልካች ቦታዉን ከተረከቡ በኋላ ላካሄዱት ተጨማሪ ግንባታ ያወጡትን ወጪ በተመለከተ ወጪዉ እንዲመለስላቸዉ ሊያቀርቡ የሚችሉትን ክስ ይህ ዉሳኔ አይከለክልም፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ 145456

ቀን 24/09/2010 ዓ.ም

**ዳኞች:-**

ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

**አመልካች:** ............... ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማሕበር ነገረ ፈጅ ቤተልሔም ማትዎስ -ቀረቡ::

**ተጠሪዎች:**.............. 1ኛ. አቶ እዮብ ሙሉጌታ ቱሳና

2ኛ. ወ/ሮ መድሃኒት ሙሉጌታ ቱሳና } የቀረበ የለም::

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል::

<u>**ፍ ር ድ**</u>

1. ጉዳዩ ዋስትናን መሰረት ያደረገ ክርክር ሲሆን የጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው:: በስር አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪዎች እና በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነውን አቶ ፈቃዱ ሙሉጌታ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል::
2. አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ፈቃዱ ሙሉጌታ የአመልካች ሠራተኛ በመሆን በወላይታ ቅርንጫፍ ተመድቦ እየሰራ በነበረበት ጊዜ ከባንኩ አሠራር ውጭ የአቶ ጀመሬ መጃ ሎጊሶን ከሆነው ሂሣብ ቁጥር የባለ ሂሣቡን ስምና ፊርማ በማስመሰል ፈርሞ ወደ አመልካች

ባንክ ሻሸመኔ ቅርንጫፍ በማዛወር ብር 50,000 በህገወጥ መንገድ በመውሰዱ ገንዘቡን እንዲከፍል፤ የአሁኑ ተጠሪዎች ዋስ በመሆናቸው ገንዘቡን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

3. የስር ተከሳሾች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ በስር 1ኛ ተከሳሽ ስምና ፊርማ የተደረገ የገንዘብ ዝውውር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

4. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም በክሱ የተጠቀሰው ገንዘብ በስር 1ኛ ተከሳሽ ወጭ ተደርጐ መወሰዱን ተረጋግጦ በወንጀል የተቀጣ መሆኑን፤ የአሁኑ ተጠሪዎችም ዋስ ስለመሆናቸው ያልተካደ መሆኑን በመግለጽ ብር 50,000 በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ከአከራከረ በኃላ የስር 1ኛ ተከሳሽ ድርጊቱ የፈፀመው ለደንበኞች አገልግሎት እየሰጠ ሳይሆን ለራሱ የአመልካች ደንበኛ በመሆን እንደሆነ፤ የሻሸመኔ ቅርንጫፍም ባለመብት ባለማጣራት የከፈለው በመሆኑ ዋሶቹ ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

5. አመልካች ሐምሌ 25 ቀን 2009 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፀመ ያለውን የህግ ስሕተት በዝርዝር ያቀረበ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱ ሲታይም የአሁኑ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያላነሱት ክርክር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለውሳኔ መነሻ ማድረጉ ተገቢ አለመሆኑን፤ የስር 1ኛ ተከሳሽ ገንዘቡ የወሰደው ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ እንዲሻር አመልክቷል፡፡ ጉዳዩን የመረመረው አጣሪ ችሎትም የአሁን ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ የተወነበት አግባብ ባሉበት ማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች 03/05/2010 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

www.abyssinialaw.com

6. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡
7. እንደመረመረነውም የአሁኑ ተጠሪዎች በስር 1ኛ ተከሳሽ ለነበሩት አቶ ፈቃዱ ሙሉጌታ ዋስ ስለመሆናቸው፤ የገንዘብ መጠኑም እስከ ብር 50,000 ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ተጠሪዎች ከባንክ ገንዘብ አልወጣም የሚል ክርክር ሳያቀረቡ ነገር ግን ገንዘቡ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልወጣ በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር የተረጋገጠው የስር 1ኛ ተከሳሽ የአቶ ጀመሬ መጃን ፊርማ ለማስመሰል ብር 50,000 በህገወጥ መንገድ ማውጣቱን ገንዘቡም ከሻሽመኔ ቅርንጫፍ ወጭ አደረጎ መውሰዱን ነው፡፡ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች ተጠያቂ ሊሆኑ አይገባም ለማለት እንደምክንያት የጠቀሰው ድርጊቱ የተፈፀመው አገልግሎት እየሰጠ ሳይሆን እንደደንበኛ ቀርቦ ገንዘብ ሲያወጣ ተገቢ ማጣራት አልተደረገም በሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው የስር 1ኛ ተከሳሽ በአመልካች ባንክ የወላይታ ቅርንጫፍ ሰራተኛ በመሆን ሲሰራ እንደነበር፤ ከዚህ ቅርንጫፍ ባንክ ደንበኛ ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ ወጭ አድርጎ ወደ ሻሽመኔ ቅርንጫፍ በማስተላለፍ ወጭ አድርጎ መወሰዱን ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የስር 1ኛ ተከሳሽ ከሚሰራበት ቅርንጫፍ ባንክ ያለው የደንበኛ ሂሣብ ቁጥር በሕገወጥ መንገድ ገንዘብ በመወሰድ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ በማስተላለፍ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ ማዋሉን ነው፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ ድርጊት ከሻሽመኔ ቅርንጫፍ ገንዘብ ማውጣት ብቻ ተነጥሎ የሚታይ ሳይሆን የወላይታ ቅርንጫፍ ሰራተኛ በመሆን ከህግ ውጭ ከደንበኛ ሂሣብ ገንዘብ ቀንሶ ማስተላለፍንና ወጪ አድርጎ መወሰዱን አብሮ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች የስር 1ኛ ተከሳሽ ዋሶች መሆናቸው አልተካደም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪዎች የስር 1ኛ ተከሳሽ በሥራው አጋጣሚ ያገኘው የደንበኛ ገንዘብ ከህግ ውጭ ቀንሶ በማስተላለፍና በማውጣት መውሰዱ በተረጋገጠበት ሁኔታ ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርጋቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የፌዴራል

www.abyssinialaw.com

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ የስር 1ኛ ተከሳሽ ድርጊት ህጋዊ ውጤት እና የተጠሪዎች የግዴታ አድማስ መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች የስር 1ኛ ተከሳሽ የወሰደው ብር 50,000 በአንድነትና በነጠላ ሊከፍሉ ይገባል፡፡ በመሆኑም የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ እያለባቸው ከኃላፊነት ነፃ ማድረጋቸው የፍ/ሕ/ቁ 1920፣1922 እና 1933 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡ በዚሕም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደቡብ ችሎት በመ/ቁ 238695 03/06/2009 ዓ/ም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 26861 በ23/01/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በመሻር የተሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 140694 በ03/09/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ከስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ፈቃዱ ሙሉጌታ ጋር በአንድነትና በነጠላ በዋስትና ውሉ የተመለከተውን ብር 50,000 የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 26861 በ23/01/2009 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
4. ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ጉ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.145523

ሐምሌ 16 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች:-** ቻን ቹን ያን ኃላፊነቱ የተ/የግ/ማህበር

**ተጠሪ:-** ወ/ሪት ሞሚና ሁሴን -ጠበቃ ፈለቀ ዋነ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመ/ደ/ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት የክስ አቤቱታ በአመልካችና ተጠሪ መከካል የመጋዝን ኪራይ መኖሩን በመግለጽ አመልካች የተከራየውን መጋዝን ከውሉ ጊዜ መጠናቀቅ በኋላ መጋዘኑን ሳይለቅልኝ ማሽኑን በማስቀመጡ መጋዘኑን በወር ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ ላከራየው እችል የነበረ ሲሆን በዚሁ ስሌት እስኪያስረክበኝ ድረስ ታስቦ እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁን አመልካች ለቀረበበት ክስ መልስ የሰጠ ሲሆን በበኩሉ የብር 1,537,322.00/አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ብር/የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪ ከሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 2005 ዓ.ም ድረስ አመልካች ማሽኑን እንዳያወጣ የከለከሉ በመሆኑ የጠየቁት የዚህ ወቅት ኪራይ ሊከፈል አይገባቸውም፤ሆኖም ከመስከረም 2006 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ማውጣት እየቻለ ስላላወጣ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ እስከ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ላለው ጊዜ በወር ብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር/ሒሳብ የሶስት ዓመት ከአምስት ወር ብር 410,000.00/አራት መቶ አስር ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል እንዲሁም ተጠሪ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር እንዲያቀርቡ፤በአመልካች በኩል የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በተመለከተ ተጠሪ የባትሪ ድንጋይ ማምረቻ ማሽኑን ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ቀሪዎቹ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አመልካች በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉው አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች እስከ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም ድረስ ከመጋዘኑ ዕቃውን ሊያወጣ ያልቻለው በተጠሪ ጥፋት ስለመሆኑ በክርክር ሂደት የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑ ከታወቀ የአሁን አመልካች ክስ ከቀረበበትን የኪራይ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም እንዲሁም የአሁን ተጠሪ ከዚሁ መጋዘን ኪራይ ጋር በተያያዘ በአመልካች ላይ የኪራይ ገንዘብ ይከፈለኝ ክስ አቅርበው ብር 240,000.00 በመ/ቁ.196134 ማስወሰናቸውን እራሳቸው በክሳቸው ላይ ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ ከሳሽ በዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነ ክስ ማስቀረት ይቻል ዘንድ ከኪራይ ገንዘቡ ክስ ጋር በመጋዘን ያለውን ዕቃ አውጥቶ መጋዝኑን እንዲያስረክብኝ ይወሰንልኝ በማለት የተጠቃለለ ክስ በማቅረብ ጉዳቱን የመቀነስ ግዴታውን አልተወጣም በማለት አመልካች በቀረበው ክርክር ላይ ዳኝነት ሳይሰጥበት በዝምታ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ህዳር 20

www.abyssinialaw.com

ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች የ3 ዓመት ከ5 ወር የኪራይ ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና ተጠሪ መካከል የመጋዝን ኪራይ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ከሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ለሶስት ዓመት መሆኑ፤ተጠሪ የውሉ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ሰኔ 5 ቀን 2004 ዓ.ም ያልተከፈላቸው የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ክስ መስርተው አመልካች ብር 240,000.00 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነ መሆኑ፤በዚሁ ክስ መጋዝኑን እንዲያስረክባቸው ዳኝነት ያልጠየቁ መሆናቸው፤ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ሚያዚያ 10 ቀን 2005 ዓ.ም ክስ ማቅረባቸው፤ተጠሪ የኪራይ ገንዘብ ካልተከፈለኝ በሚል ምክንያት አመልካች ተከራይቶ ከነበረው መጋዝን ውስጥ ያለውን ዕቃ እንዳያወጣ የከለከሉ ስለመሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ተጠሪ የመጋዝኑ የኪራይ ዋጋ ይታሰብልኛል በሚል ብቻ መጠበቅ ሳይኖርባቸው መጋዘኑ እንዲለቀቅላቸው ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1802 እንደሚደነግገው ተጠሪ የጉዳት ኪሣራ የመቀነስ ግዴታ ነበረባቸው፡፡ አመልካችም ዕቃዎቹ ከመጋዝኑ እንዲያወጣ በህግ አለመጠየቁ ለደረሰው የጉዳት ኪሣራ አስተዋጾ አላቸው፡፡ በመሆኑም ለደረሰው የጉዳት ኪሣራ ሃላፊነት የአመልካች ብቻ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የጉዳት ኪሣራ አመልካች ብቻ እንዲከፍል መወሰኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1799(1) እና 1802 (1) እንዲሁም ተበዳዩ የሚካሰው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሣራ መሆን ስለሚገባው ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት ያለበት ሰው ታውቆ የተጎዳው ወገን ከደረሰበት ጉዳት ጋራ ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ መከፈል ሲለሚገባው ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2090 እና 2091 መሰረት ሲመዘን ህጋዊ ውሳኔ ነው ለማለት የሚቻል

አይደለም፡፡ ለደረሰው የጉዳት ኪሣራ ምክንያቶቹ ከላይ እንደተገለጸው አመልካችም ተጠሪም በመሆናቸው ለደረሰው የጉዳት ኪሣራ ሁለቱም ሃላፊነቱን መሸከም አለባቸው፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤት በተጣራው የኪራይ ዋጋ በብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ታስቦ የስድስት ወር አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት በዚህ መሰረት አመዛዝኖ መወሰን ሲገባው የተጠሪ ጉዳት የመቀነስ ሃላፊነት ግምት ውስጥ ሳይገባ አመልካች ብቻ ሙሉውን የጉዳት ኪሣራ እንዲከፍሉ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.134483 መጋቢት 5 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.140438 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ.ም በትእዛዝ ያፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ከመስከረም 2006 ዓ.ም እስከ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ3 ዓመት ከ5 ወር የኪራይ ሂሳብ በድምሩ ብር 410,000.00 /አራት መቶ አስር ሺህ ብር/ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የስድስት ወር ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. የተቀሩት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች አልተነኩም፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**መ/ይ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.134663

ጥር 21 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች - ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካች - ጅማ ዩኒቨርሲቲ -ነ/ፈጅ ጌታቸው ነጋሽ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ - ቢሊሱማ ሚአ የዕፀዋት ዘር አቅራቢ ድርጅት -አቶ ቢሊሱት ሚአ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ አቶ ካሳሁን መሰለ፤ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ የአሁን አመልካች ነበሩ፡፡

ተጠሪ ያቀረበው ክስ ይዘት፡- የተለያዩ ችግኞችን ለማቅረብ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ውል የፈፀምኩ ሲሆን ስራውን መስራት ስለበዛብኝ 1ኛ ተከሳሽ ይህን ሥራ እንዲሰራልኝ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ እነሱም የችግኝ ዘር መቅረብን አስመልክቶ ጨረታ ላይ እንዲሳተፍ፤ የጨረታ ሰነድ እንዲገዛ እንዲያስገባ፤ ገንዘብ ፈርሞ እንዲወስድ፤ የወሰደውንም ገንዘብ በድርጅቱ ሥም (በቢሊሱማ ሚአ በኢትጵያ ንግድ ባንክ አዳአ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 1000070736679) ገቢ እንዲያደርግ ውክልና ስልጣን ሰጥቸዋለሁ፤ ይሁን እንጂ 1ኛ ተከሳሽ የሰጠሁትን ውክልና ስልጣን በህገወጥነት በመጠቀም ከ2ኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጅማ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 10005222 ከሆነው ብር 420,763.00 (አራት መቶ ሃያ ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ሶስት) በቀን 30/12/2006 ዓ.ም ወጪ በማድረግ ወደራሴ ሂሳብ ገቢ ማድረግ ሲገባቸው 2ኛ ተከሳሽ በቀጥታ ወደ ግሉ ሂሳብ ቁጥር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቢሾፍቱ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 216501041892 አዙሮ ወስዷል፤ 1ኛ ተከሳሽ ባለው ውክልና ስልጣን መሰረት ይህን ገንዘብ ወደራሴ ሂሳብ እንዲመልስ ብጠይቀውም ፍቃደኛ ስላልሆነ

www.abyssinialaw.com

ገንዘቡን ሊከፍለኝ ይገባል፤ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ችግኞች ለማቅረብ ስንስማማ የገንዘብ ክፍያ ሊከፈለኝ የሚገባውን ገንዘብ በሂሳብ ቁጥር 1000070736679 ገቢ እንዲያደርጉ ተስማምተን እያለ ከውሉ ውጪ ሆነ ብለው እኔን ለመጉዳት ገንዘቤን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ በማስገባታቸው የአንድነት ተጠያቂነት አለባቸው፤ ስለሆነም ተከሳሾች ብር 420,763.00 (አራት መቶ ሃያ ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ሶስት) እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር 1ኛ ተከሳሽ በሰጡት መልስ ብዙ ወጪ አውጥቼ ከቢሸፍቱ ከተማ እስከ ጅማ ከተማ ተመላልሼ ጨረታውን አሸንፌ ውል ተዋዉዬ የተለያዩ እፅዋቶችን ከተለያየ ቦታ ገዝቼ አቅርቤያለሁ፤ ከሳሽ ገንዘብ ለመክፈልም ሆነ እፅዋቶችን ለማቅረብ ያደረገው አስተዋፅኦ የለም፤ ከጅማ ዩንቨርሲቲ የተከፈለውን የሽያጭ ዋጋ ከከሳሽ ጋር ተስማምተን ለተለያዩ የግዥ ዋጋዎች ክፍያ ውሏል፤ የጽሁፍ ደብዳቤ እኔ እየፈረምኩ የከሳሽ ባለቤት የድርጅቱን ማህተም መታልኝ 2ኛ ተከሳሽ ገንዘቡን በስሜ ባለው ሂሳብ እንዲያስገባ ጠይቄ ገንዘቡ እንዲገባ ተደርጎ ያለብን እዳ የተከፈለ ሲሆን የቀረው ትርፍ ጥቂት ስለሆነ ከከሳሽ ጋር ሂሳብ እንድንሰራ እና የሚከፈለኝን ክፍያ ከፍሎኝ እንዲያጠናቅቅ ከሳሽን ስጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም፤ ስለሆነም በሂሳብ ባለሙያ ተጣርቶ ያወጣሁት ገንዘብ እንዲቻቻል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ ከከሳሽ ጋር በተደረገው ውል መሰረት ለቀረበው ችግኝ በውሉ የተገለፀውን ብር 420,763.00 ከፍያለሁ፤ ከሳሽ ስራውን የሚሰራው በተወካዩ 1ኛ ተከሳሽ በኩል ነው፤ 1ኛ ተከሳሽ ገንዘቡን መውሰድ እንደሚችል የውክልና ሰነዱ ይገልፃል፤ ይህ በመሆኑ ገንዘቡን ለ1ኛ ተከሳሽ ለመክፈል የህግ መሰረት ያለኝ ሲሆን በተሰጠው ውክልና ላይ የተመሰረተ ነው፤ የሚከፈለው ገንዘብ ወደተወካዩ ሂሳብ እንዳይገባ በሚል በውክልና ሰነዱ አልተገለፀም፤ በፌዴራል ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 6(5) መሰረት ከብር 50,000.00 የሚበልጥ ክፍያ ወደሚከፈለው ሰው ባንክ ሂሳብ ቁጥር በማሳለፍ ክፍያ መፈፀም እንዳለበት ይደነግጋል፤ በዚሁ መሰረት ተወካይ የሂሳብ ቁጥር 216501041892 አቅርበው ገንዘቡ ተላልፏል፤ የከሳሽ ተወካይ ክፍያ እንዲፈፀምለት የጠየቀበት ደብዳቤ በከሳሽ ማህተም ተደግፎ የቀረበ ነው፤ ስለሆነም ከሳሽ እኔን መክሰሱ ተገቢ አይደለም ብሏል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ እንዲሰራ እና እንዲቻቻሉ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ ከሳሽ የሰጠው ውክልና ገንዘብ ወደራሱ ሂሳብ ቁጥር እንዲያስገባ የሚል አይደለም ስለሆነም ወደራሱ ሂሳብ ገንዘቡ እንዲገባ ማዘዙ ከውክልና ስልጣኑ በላይ አልፎ ለራሱ ጥቅም እንደሰራበት የሚያረጋግጥ በመሆኑ የወሰደውን ገንዘብ ሊመልስ ይገባል፤ 2ኛ ተከሳሽን (አመልካችን) በተመለከተም ገንዘቡን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ ያስተላለፈ መሆኑን ያልካደ በመሆኑ፤ ይህን ያደረኩት በተፃፈልኝ ደብዳቤ ተመስርቼ ነው ይበል እንጂ 1ኛ ተከሳሽ በውክልና ስራውን እየሰራ መሆኑን ከውክልናው መረዳት የሚቻል ሲሆን የተሰጠው ውክልና ደግሞ ከችግኝ ሽያጭ የሚገኝ ገንዘብ ወደ ከሳሽ ሂሳብ ቁጥር መግባት እንዳለበት ተገልጾ የሂሳብ ቁጥሩም በውክልናው ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ፤ ውክልናው ገንዘብ መግባት ያለበትን የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1ኛ ተከሳሽ መቀየር የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር ባለመኖሩ፤ 1ኛ ተከሳሽ ገንዘቡን በራሴ ሂሳብ አስገባው በማለት ያቀረበው ደብዳቤ ላይ የተመታው ማህተም መጀመሪያ ከሳሽ ፕሮፎርማ ሲያስገባ በፕሮፎርማው ላይ ካለው ማህተም የተለየ መሆኑን መረዳት ሲችል ገንዘቡን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ማስገባቱ ስህተት ነው ኃላፊነትም አለበት ብሏል፡፡ በአጠቃላይ ሁለቱም ተከሳሾች ከችግኝ ሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ በከሳሽ ባንክ ሂሳብ ማስገባት እያለባቸው ይህን ባለማድረጋቸው የአንድነትና ነጠላ ግዴታ አለባቸው በማለት ብር 420,763.00 ከ 13% የጠበቃ አበል እና ልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩን ሰምቶ የአሁን አመልካች በተወካዩ ደብዳቤ ሲቀርብለት በደብዳቤው መሰል ትዕዛዝ ለመስጠት ሙሉ ስልጣን እንዳለው ማየትና ለተጠሪ ደውሎ ማጣራት ነበረበት የሚል ምክንያት በመጨመር የሥር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ህዳር 28/2009 ዓ.ም ያቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ተጠሪ ለስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ካሳሁን መለሰ ችግኝ እንዲያቀርብ፤ በጨረታ ላይ እንዲሳተፍ፤ የግዢ ትዕዛዝ እንዲቀበል፤ ገንዘብ እንዲቀበል እና የተቀበለውን ገንዘብ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ እንዲያደርግ ውክልና በሰጡበት ሁኔታ ተወካዩ ለአሁን አመልካች ችግኝ አቅርቦ የተከፈለውን ብር

www.abyssinialaw.com

420,763.00 ወደ ተወካዩ የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረጉ አመልካች ከሥር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ለክስ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ በአንድነትና በነጣላ ክፊል የመባሉን አግባብ ከግራ ቀኙ የውል ግንኙነት አንጻር ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙም የሥር ክርክራቸውን በማጠናከር በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት ችግኝ የማቅረብ ስራውን መስራት ስለበዛብኝ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ይህን ሥራ እንዲሰራልኝ የችግኝ ዘር መቅረብን አስመልክቶ ጨረታ ላይ እንዲሳተፍ፤ የጨረታ ሰነድ እንዲገዛ እንዲያስገባ፤ ገንዘብ ፈርሞ እንዲወስድ፤ የወሰደውንም ገንዘብ በድርጅቱ ሥም ገቢ እንዲያደርግ ውክልና ስልጣን ሰጥቸዋለሁ፤ ይሁን እንጂ ከአመልካች ጋር ችግኞች ለማቅረብ ስንስማማ የገንዘብ ክፍያ በሂሳብ ቁጥሬ ገቢ እንዲያደርጉ ተስማምተን እያለ ከውሉ ውጪ ገንዘቤን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ በማስገባታቸው ተጠያቂነት አለባቸው፤ ገንዘቡን ብር 420,763.00 (አራት መቶ ሃያ ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ሶስት) እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ከተጠሪ ጋር በተደረገው ውል መሰረት ለቀረበው ችግኝ በውሉ የተገለፀውን ብር 420,763.00 ከፍያለሁ፤ ተጠሪ ስራውን የሚሰራው በተወካዩ በኩል ነው፤ ተወካዩ ገንዘቡን መውሰድ እንደሚችል በውክልና ሰነዱ ተገልጿል፤ በዚሁ መሰረት ተወካይ የሂሳብ ቁጥር 216501041892 አቅርበው ገንዘቡ ተላልፏል፤ ተወካይ ክፍያ እንዲፈፀም የጠየቁበት ደብዳቤ በተጠሪ ማህተም ተደግፎ የቀረበ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት አመልካች ገንዘቡን ለመክፈል ከተወካዩ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በማለት የወሰኑት የአመልካች መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

ከፍሲል እንደተገለፀው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል መሰረት ለቀረበው ችግኝ በውሉ የተመለከተው የብር 420,763.00 ክፍያ አመልካች ለተጠሪ ተወካይ መክፈሉ ፤ ተጠሪ ስራውን የሚሰራው በተወካዩ በኩል መሆኑ፤ እንዲሁም ተወካዩ ገንዘቡን መውሰድ እንደሚችል በውክልና ሰነዱ ስልጣን የተሰጠው መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ተጠሪ በውሉ ላይ የገንዘብ ክፍያ በሂሳብ ቁጥሬ ገቢ እንዲያደርጉ ተስማምተን እያለ ከውሉ ውጪ አመልካች ገንዘቤን ወደ ተወካይ ሂሳብ በማስገባቱ

www.abyssinialaw.com

ተጠያቂነት አለበት በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ከውሉ በኋላ ነሃሴ 12/2006 ዓ.ም ለተወካዩ በሰጡት ውክልና ገንዘቡን እንዲቀበል እና የተቀበለውን ገንዘብ በድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርግ ውክልና መስጠታቸውን አላስተባበሉም፡፡ የውክልና ሰነዱም ይህን የሚያሳይ ነው፡፡ ይልቁንም የሥር 1ኛ ተከሳሽ (ተወካይ) በተሰጠው ውክልና መሰረት ገንዘቡን መውሰዱን ሳይክድ ከአሁን ተጠሪ ጋር የመቻቻል እና የሂሳብ እናድርግ ጥያቄ ማቅረቡ ለክሱ መነሻ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ለውክልናው 3ኛ ወገን የሆነውን የአሁን አመልካችን ሳይሆን በወካይ እና ተወካይ መካከል የተፈጠረን የጥቅም ግጭት የሚመለከት ነው፡፡

ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2206 ፣ 2187 እና ተያያዥ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ውክልናው በላዩ ተዘርዝረው የተመለከቱትን ጉዳዮችና የነዚሁ ተከታታይ እና ተመሳሳይ የሆነውን እንደ ጉዳዩ አይነትና እንደ ልማድ አሰራር አስፈላጊ የሆነውን ማከናወን የሚያስችል ሲሆን ተወካዩ የፈፀመው ተግባር የወካይና ተወካይ ጥቅሞችን ግጭት የሚያስከትል በሆነ ጊዜ 3ኛው ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀና ሊያውቅ የሚገባ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ኃላፊነት የሚኖርበት አይሆንም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ውል ካደረገ በኋላ ለወኪሉ የሰጠው ውክልና ችግኝ እንዲያቀርብ፤ በጨረታ ላይ እንዲሳተፍና የግዢ ትዕዛዝ እንዲቀበል የሚል ብቻ ሳይሆን ገንዘብ እንዲቀበል እና የተቀበለውን ገንዘብ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ እንዲያደርግ ስልጣን የሚሰጥ ነው፡፡ አመልካች በውል ግዴታው መሰረት ብር 420,763.00 ብር ለተጠሪ ተወካይ ከፍሏል፡፡ ስለሆነም አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ ተወካይ መክፈሉ (በባንክ ሂሳቡ ማስገባቱ) ውሉን እና የውክልና ሰነዱን መሰረት ያደረገ አይደለም የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ በቀር አመልካች ውክልናውን ተከትሎ ክፍያ ለተወካይ የፈፀመው በወካይ እና ተወካይ መካከል ያለውን የጥቅም ተቃርኖ እያወቀ ወይም ማወቅ እየተገባው ነው የሚሰኝ ስለመሆኑ ክርክር እና ማስረጃ አልቀረበም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የውሉን ገንዘብ ለተጠሪ ተወካይ በመክፈሉ ከተወካዩ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በማለት የደረሱበት መደምደሚያ በክርክሩ የተረጋገጠውን ፍሬነገር እና ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የህጉን

www.abyssinialaw.com

ድንጋጌዎች ይዘት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለን በአብላጫ ድምጽ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42179 ሰኔ 28/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 250095 ህዳር 20/2009 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገውን ውል እና ተጠሪ ለተወካያቸው የሰጡትን የውክልና ስልጣን መሰረት በማድረግ የውሉን ገንዘብ ለተወካይ የከፈለ በመሆኑ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የሐሳብ ልዩነት

እኛ ስማችን በአራተኛ እና በአምስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኞች አመልካች በተጠሪ ተወካይ ሂሳብ ቁጥር ገቢ በማድረጉ ከተወካዩ ጋር በአንድነት እና በነጠላ ለተጠሪ ሃላፊነት የለበትም በሚለው በአብላጫው ድምጽ ድምዳሜ ስለማንስማማ በሃሳብ ተለይተናል፡፡

አቶ ካሳሁን መሰለ የተጠሪ ተወካይ በመሆን ከአመልካች ጋር ያደረገው የችግኝ ሽያጭ ውል በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2189/1/ እና 2199 መሰረት አመልካች እና ተጠሪ መካከል እንደተደረገ ስለሚቆጠር፣ አመልካች ችግኙን ስረከብ ተጠሪ ገንዘቡን የማግኘት መብት ያለው ሲሆን አመልካችም ገንዘቡን ለተጠሪ የመክፈል ተነጻጻሪ ግዴታ እንደሚኖርበት ይታወቃል፡፡ ተጠሪ ለተወካዩ በሰጠው የውክልና ስልጣን ተወካዩ ገንዘብ ፈርሞ እንዲወስድ ጭምር ስልጣን የሚሰጥ ቢሆንም፣ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል

በተደረገ የችግኝ አቅርቦት ውል አመልካች ገንዘቡን በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ እንዳለበት ተስማምቶ የተጠሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥር የተሰጠው ሲሆን፣ አመልካች ይህ ስለመሆኑ ክዶ አልተከራከረም፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ መስማማቱን ሳይክድ ገንዘቡን በተወካዩ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ለማድረግ የቻለው ተወካዩ ይህን እንዲያደርግ በደብዳቤ የገለጸለት መሆኑን በመጥቀስ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ገንዘቡ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲሆን ግራቀኝ ሲስማሙ በምክንያት ነው ተብሎ ስለሚታመን አመልካች ይህን ስምምነት የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ ለተወካዩ የሰጠው ውክልና ገንዘብ እንዲቀበል ጭምር የሚያካትት ቢሆንም፣ ገንዘቡ በተወካዩ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግ ግራቀኝ በተለየ ሁኔታ ያደረጉት ግልጽ ስምምነት በውክልና ሰነድ ላይ ከተመለተው የውክልና ስልጣን በልዩ ሁኔታ መታየት ያለበት በመሆኑ የማይፈጽምበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ገንዘቡን በተጠሪ የሂሳብ ቁጥር ገቢ ለማድረግ ከተጠሪ ጋር ባደረገው ስምምነት ግዴታ ገብቶ እያለ ከስምምነቱ ውጪ በሆነ ሁኔታ በተጠሪ ሂሳብ ገቢ ማድረግ ያለበትን ገንዘብ በተወካዩ የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረጉ ገንዘቡን ከተጠሪ ተወካይ ጋር በአንድነት እና በነጣላ ለተጠሪ የማይከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት ከባልደረቦቻችን በሃሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.148158

ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች - ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች - አቶ በትግሉ ከበደ

ተጠሪ - ሽሬ እንዳስላሴ ማረሚያ ቤት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 96204 በ30/10/2009 ዓ.ም ያሳለፈውን ትዕዛዝ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በሽረ እንዳስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በተጠሪ ተቋም ለሚገኙ የህግ ታራሚዎች መንግስት በመደበላቸው በጀት መሰረት ከቀን 15/05/2007 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት ምግብ አብስዬ ለማቅረብ ከተጠሪ ጋር ውል አድርገናል፤ በሂደት ደግሞ በቀን 23/07/2007 ዓ.ም በውሉ መሰረት እየመገብኩ እንደነበር በማረጋገጥ ከቀን 24/07/2007 ዓ.ም ጀምሮ ከሽንኩርት አቅርቦት ተቀንሶ ወደ በርበሬ፣ ስኳር እና ስጋ እንዲሸጋሸግ፤ በዚህ መሰረት የስጋ አቅርቦት ከነበረበት በተጨማሪ አንድ ጊዜ በወር ከተሸጋሸገው ዋጋ ስጋ እንዳቀርብ፤ ውል ከመሻሻሉ በፊት ሳይቀርቡ የቀሩ ውዝፍ አቅርቦት በማጣጣም በቀጣይ በስጋ መልክ እንዳቀርብ ተስማምተናል፤ ነገር ግን ተጠሪ ከተሻሻለው ስምምነት ውጪ ስጋ አላቀረብክም በማለት መክፈል የሚገባውን ብር 230,472.00 አላግባብ የቀነሰብኝ በመሆኑ እንዲሁም በትርፍ ያቀረብኩት የሥጋ ዋጋ ብር 152,712.55 ስላልከፈለኝ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ያላቀረቡት አስቤዛ እና ስጋ በስምምነቱ መሰረት በግራሙ ተለክቶ ባላቀረቡት ልክ ክፍያው የተቀነሰ እንጂ ከውል ውጭ ያስቀረሁት ገንዘብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና የምስክሮቻቸውን ቃል እንዲሁም የሰነድ ማስረጃውን መርምሮ በግራቀኙ መካከል የተደረገው የተሻሻለ ውል በወር አንድ ጊዜ አምስተኛ ሆኖ የሚቀርብ ስጋ ለአንድ ታራሚ 700 ግራም ከሳሽ እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ስለሆነ፤ ውሉ ከመሻሻሉ በፊት የነበሩ ውዝፍ አቅርቦቶች በስጋ መልክ እንዲቀርቡ ተስማምተው ውዝፍ የስጋ አቅርቦት በተሻሻለው ውል መሰረት ማቅረብ የነበረበትን አመልካች ስላላቀረበ፤ እንዲሁም ሌሎች ለክስ ምክንያት የሆኑ አቅርቦቶች አልቀረቡም ተብሎ በተጠሪ የተቆረጠው ገንዘብ ከሳሽ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም አመልካች በውሉ መሰረት መቅረብ የነበረባቸውን ስላላቀረበ ለክስ ምክንያት የሆነው ገንዘብ ተጠሪ ቆርጦ ማስቀረቱ ውሉን መሰረት ያደረገና አግባብነት ያለው ነው በማለት የክሱን ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቅሬታቸውን ለሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 21/2010 ዓ.ም ያቀረቡት ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈፀመው የመጀመሪያ ውል በሌላ ውል ተሻሽሎ እያለ ክፍያው ግን በመጀመሪያው ውል መሰረት እንዲፈፀም በሥር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1826 እና ተከታዮች አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክርና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በስር ፍርድ ቤቶች በተላለፈው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ከተሻሻለው ስምምነት ውጪ ስጋ አላቀረብክም በማለት መክፈል የሚገባውን ገንዘብ አላግባብ የቀነሰብኝ በመሆኑና በትርፍ ላቀረብኩት የሥጋ ዋጋም ስላልከፈለኝ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ያላቀረቡት አስቤዛ እና ስጋ በስምምነቱ መሰረት በግራሙ ተለክቶ ባላቀረቡት ልክ ክፍያው የተቀነሰ እንጂ ከውል ውጭ ያስቀረሁት ገንዘብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ መልኩ የተካካዱበትን ፍሬ ነገር በማስረጃ ያጣራው የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ስምምነት ባደረጉባቸው ውሎች መሰረት ማቅረብ የነበረባቸውን ስላላቀረቡ የክሱን ገንዘብ ተጠሪ ቆርጦ ማስቀረቱ ውሉን መሰረት ያደረገና አግባብነት ያለው ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ የፍሬ ነገር መደምደሚያ ተቀብሎታል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው የመጀመሪያው ውል በሌላ ውል ተሻሽሎ እያለ ክፍያው በመጀመሪያው ውል መሰረት እንዲፈፀም በሥር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1826 እና ተከታዮች አኳያ ለመመርመር በሚል ሲሆን መዝገቡ እንደሚያሳየው የቀደመው ውል መሻሻል የተደረገበት በአቅርቦት እንጂ በዋጋ ጉዳይ አይደለም፡፡ በቀደመው ውል ከነበረው የቀይ ሽንኩርት፣ ቲማቲም እና አትክልት አቅርቦቶች ላይ በመቀነስ በምትኩ ወደ በርበሬ ስኳርና ስጋ አቅርቦት እንዲጨመር መስማማታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠውም አመልካች ማቅረብ የነበረባቸውን እንዳላቀረቡ ተረጋግጧል በሚል እንጂ ጉዳዩ ከክፍያ ልዩነት አንፃር ታይቶ አይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ ጉዳዩ ከውል መተካት አንፃር እንዲታይ ይተካል በተባለው እና ተተክቷል በሚባሉት ውሎች መካከል ያለው የውለታ ጉዳይም ሆነ የውለታው ምክንያት በይዘቱ አዲስ መሆን እንዳለበትና ይህንኑ በውለታውም አይነት ሆነ ከውለታው ምክንያት አንፃር ታይቶ አዲስ የሆነው ውል ከዚህ ቀደም ተደርጎ በነበረው ውል ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በማያጣራጥር አኳኋን ሊያስቀር የሚችል ፈቃድ ከተዋዋይ ወገኖች እንዲኖር አስፈላጊ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1826 እና 1828 የተደነገገ ሲሆን ውልን የማሻሻል ጉዳይ ግን ከዚህ አንፃር ሊታይ እንደማይገባ መገንዘብ ይቻላል፡፡

www.abyssinialaw.com

የሥር ፍርድ ቤት ከፍሲል እንደተገለፀው አመልካች በውሎቹ መሰረት ማቅረብ የነበረባቸውን ስላላቀረቡና ግዴታቸውን አለመፈፀማቸው በማስረጃ ተረጋግጧል ለክስ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት የወሰነው ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ባለው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ካለ ከሚመለከት በቀር መሰል የፍሬ ነገር ክርክርን መርምሮ እና ማስረጃ መዝኖ ውሳኔ የሚሰጥም አይደለም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በገቡት ውል መሰረት አለማቅረባቸውና ባጎደሉት አቅርቦት ልክ ተጠሪ ክፍያ መቀነሱ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ውሉን እና ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የሽረ እንዳስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 13740 ህዳር 15/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 21259 መጋቢት 6/2009 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 96204 በ30/10/2009 ዓ.ም የተላለፈው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ. 156408

ቀን፡- 24/1/2011ዓ.ም

ዳኞች፡..1. ተኽሊት ይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራው

5. አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡.፡- አቶ አክሊሉ ጌታሁን ጠበቃ ክፍለ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፍሬህይወት አሰፋ ጠበቃ ቸርነት ተገኝ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

1. ጉዳዩ የብድር ዉል መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን የጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ ነዉ፡፡ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 226304 ሚያዝያ 12 ቀን 2007ዓ.ም ባቀረቡት ክስ የአሁን ተጠሪ በብድር የወሰዱት ብር 200,000 እንዲመለስላቸዉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በ23/2/2008ዓ.ም በሰጡት መልስ ከአመልካች የወሰዱት ብድር አለመኖሩን፣ ለተጠሪ እናት የተላከዉ ብር 60,000 ፈርመዉ የተቀበሉት ብድር አለመሆኑን በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡
2. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የስር ፍ/ቤትም በተጠሪ ተፈረመ የተባለዉ ሰነድ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ዘርፍ እንዲመረመር የተደረገ ሲሆን በዉሉ ላይ ያለዉን ፊርማ የተጠሪ /ተከሳሽ/ አለመሆኑን መረጋገጡን በመግለጽ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረጉት የብድር ዉል የለም፡፡ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰዉ ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተደረገ የብድር ዉል

www.abyssinialaw.com

የለም፣ ተከፈለ የተባለዉ ብር 60,000 ከብድር ዉሉ ጋር ግንኙነት የለዉም በማለት የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

3. የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔና ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2010ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የብድር ስምምነት መኖሩን የሚያስረዱ ተጨማሪ ምስክሮች እንዳያቀርቡ እንደተከለከሉ፣ የብድር ዉል ለማስረዳት የቀረበዉ ሰነድ ባልተካደበት ለምርመራ መላኩ፣ የምርመራ ዉጤቱም እንደ መጨረሻ ብቸኛ መረጃ ተደርጎ መዉሰዱ በህጉ አግባብ አይደለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የአመልካች አቤቱታ የመረመረዉ አጣሪ ችሎትም የብድር ዉል ሲፈረም የነበሩ ምስክሮች ሳይሰሙ ተጠሪ ሊጠይቁ አይገባም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ከሰ/መ/ቁ. 114553 አንፃር እንዲመረመር በድምጽ ብልጫ ለዚህ ችሎት አስቀርቦታል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 7 ቀን 2010ዓ.ም በሰጡት መልስ በስር ፍ/ቤት የብድር ዉል የሌለ መሆኑን ተረጋግጦ የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡ አመልካች አቤቱታቸዉን የሚደግፍ የመልስ መልስ ሰኔ 22 ቀን 2010ዓ.ም አቅርቧል፡፡

4. ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን እኛም የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ፍርድ ላይ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

5. እንደመረመርነዉም የአመልካች መሰረታዊ የዳኝነት ጥያቄ በብድር የተወሰደዉ ብር 200,000 እንዲመለስላቸዉ የሚያመለክት ነዉ፡፡ ተጠሪ ብድር አለመዉሰዳቸዉን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በህጉ አግባብ የተቋቋመ የብድር ዉል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለዉ ብድር ዉል ነዉ፡፡ አመልካች /ከሳሽ/ የብድር ዉል መኖሩን ለማስረዳት ተጠሪም የተበደሩ መሆኑን ከተረጋገጠ ክፍያ መፈፀማቸዉን ለማስተባበል መቅረብ ያለበት የማስረጃ ዓይነት ምን መሆን እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በብድር የተሰጠዉ ገንዘብ ከብር 500,00 በላይ ከሆነ ብድሩን ለማስረዳት የብድር ዉል መቅረብ ያለበት ሲሆን የብድር ዉሉ ካልቀረበ ደግሞ ተበዳሪዉ

በፍ/ቤት ካላመነ ወይም በቃለ መሀላ ስር ሆኖ ቃሉን ካልሰጠ በስተቀር በሌላ አግባብ ማስረዳት እንደማይቻል ድንጋጌዉ ያመለክታል፡፡ አመላለሱ በተመለከተም ተመሳሳይ የማስረጃ መርህ የሚከተል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472(3) ደንግጓአል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ብር 200,000 ማበደራቸዉ በመግለጽ ክስ ቢያቀርቡም የብድር ዉሉ በተጠሪ አልታመነም፡፡ የብድር ዉል የተባለዉ ሰነድ በፎረንሲክ ምርመራ የተደረገለት ሲሆን በሰነድ ላይ ያረፈዉ ፊርማ የተጠሪ አለመሆኑን ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ ወሰዱት የተባለዉ ብር 60,000 ብድር ክርክሩ የተያያዘ አለመሆኑን የስር ፍ/ቤት ማረጋገጡን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት በሰነድ ላይ የተመለከቱ ምስክሮች ሳይሰሙ ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በሚል ነዉ፡፡ በመሰረቱ ዉሉ በጽሁፍ እንዲሆን በህጉ በተመለከተበት ሁኔታ ሰነድ ራሱ አስረጂ መሆኑን ነገር ግን ሰነድ የተቀደደ፣ የተሰረቀ፣ የጠፋ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ዉሉ በምስክሮች ማስረዳት የሚቻልበት ስርዓት ተመልክቷል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ሰነድ ቀርቧል፡፡ በሰነዱ ላይ ያረፈዉ ፊርማ ግን የተጠሪ አለመሆኑን ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አመልካች በተጠሪ ተክዶ በፎረንዚክ ምርመራ ተጠሪ ፊርማ አለመሆኑን የተረጋገጠዉ ሰነድ ላይ ያለዉ ፊርማ የተጠሪ ስለመሆኑ በሰዉ ምስክሮች ለማስረዳት ያቀረቡት አቤቱታ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2006 እና 2472(1) ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት ያላገናዘበ ነዉ ብለናል፡፡

6. አመልካች ሌላ ያቀረቡት አቤቱታ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ 114553 በሰጠዉ ዉሳኔ የብድር ዉል መኖሩን በሰዉ ምስክሮች ማስረዳት እንደሚቻል የሚያሳየዉ ገዥ ዉሳኔ ታልፏል የሚል ነዉ፡፡ የሰ/መ/ቁ. 114553 አስቀርበን እንደመረመርነዉም በብድር ዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ የኔ አይደለም የሚል ክርክር በመነሳቱ በብድር ዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ ተመርምሮ የተበዳሪ ስለመሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን መነሻ በማድረግ እንዲሁም ተጨማሪ ማጣራት በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱን የሚያሳይ እንጂ የተካደዉ ፊርማ የተበዳሪ ስለመሆኑ ሳይንሳዊ በሆነ የምርመራ ዘዴ ሳይረጋገጥ የሰዉ ምስክሮች ብቻ በማዳመጥ ዉሳኔ አለመስጠቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ መሰረት የሌለዉ መሆኑን ከሚያሳይ በቀር የሰበር

www.abyssinialaw.com

ዉሳኔዉ በጭብጥ ከተያዘዉ ጉዳይ አንድና ተመሳሳይ ነዉ ተብሎ የሚወስድበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ አመልካች በሰበር ቅሬታቸዉ ብር 60,000 መከፈሉን ክርክር ያልቀረበበት ነዉ፡፡ ያሉ ቢሆንም ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት መልስ ብር 60,000 ለተጠሪ እናት የተላከ እንጂ በብድር ወሰዱት የተባለዉ ብር 200,000 ከፊል ክፍያ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ክሱን ለማስረዳት የብድር ዉል የተባለዉን ከማቅረብ ዉጭ በቃለ መሀላ ስር ሆነዉ ተጠሪ እንዲያረጋግጡ ያቀረቡት ክርክር ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡ በዚህ ሁሉም ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል በህጉ አግባብ የተቋቋመ የብድር ዉል የለም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ህግን ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 226304 በ18/2/2010 የሰጠዉ ፍርድ፣ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. በመ/ቁ. 186042 በ 14/6/2010ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለዉ ወጪና ኪሳራ ካለ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉ ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.abyssinialaw.com

የሰበር መ/ቁ/136653

ግንቦት 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሸምሱ ሲርጋጋ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡አቶ ገ/ሚካኤል በርሀ

ተጠሪ፡ አቶ ገ/ዮሃንስ ወ/ጊዮርግስ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የአፈጻጸም ክርክር ላይ ልዩ ልዩ ወጪና ወለድ ክፍያ የሚመለከት ነዉ፡፡ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ አመልካች የፍርድ ባለእዳ ተጠሪና ሌሎች በዚህ መዝገብ ያልተጠሩ ሰዎች የኢት/ልማት ባንክን ጨምሮ ፍርድ ባለመብቶች ሆነዉ የአመልካች ንብረት የሆነዉን በመቀሌ ከተማ የሚገኝ የእንጨትና የብረታ ብረት ስራ ድርጅት ከነቤቱ በሀራጅ ለማሸጥ ሲንቀሳቀሱ ተጠሪ የፍርድ ባለገንዘቦችን ብር ለመክፈል ተስማምቶ ንብረቱን ያለጨረታ ለማስቀረት እንዲችል ፍርድ ቤቱን ጠይቆ የመቐለ ማእከላዊ ፍርድ ቤት ፈቅዶለት ንብረቱን በ27/10/1999 ዓ.ም በተሠጠ ትእዛዝ የተረከበ ሲሆን አመልካች ይህንን በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ችሎት ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ሰበር ችሎቱም በመ/ቁ/45733 በ29/11/02 ዓ.ም በሰጠዉ ፍርድ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳን ተክቶ ለባለመያዣ ባንክ ገንዘቡን ከፍሎ ንብረቱን ካስለቀቀ እና ለሌሎች ባለገንዘቦች ገንዘባቸዉን ከከፈለ በኂላ የፍርድ ባለእዳዉን ንብረት

www.abyssinialaw.com

ያለጨረታ እንዲረከብ ሳይሆን ጨረታ ተከናዉኖ ራሱም ከፈቀደ በጨረታዉ ተካፋይ ሆኖ ሊሆን ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር ጨረታ እንዲከናወን በትእዛዝ መልሷል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የአመልካች ንብረት በጨረታ ከተሸጠ በኋላ ተጠሪ ቀደም ሲል ለፍርድ ባለገንዘቦች የከፈለዉ ገንዘብ እስከነወለዱ ከሽያጭ ገንዘብ ላይ እንዲከፈለዉ በመጠየቁ የመቐሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀችን ካከራከረ በኋላ ዋናዉ ፍርድ ላይ ለባለገንዘቦቹ የተፈረደዉ ዋና ገንዘብ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ወለድ እንደሚታሰብ ስለተወሰነ ተጠሪ በጊዜዉ ገንዘቡን ለባለገንዘቦች ከራሱ ወጪ አድርጎ ስለከፈለ ወለድ ሊያገኝ ይገባል ካላ በኋላ ወለዱ ሊታሰብ የሚገባዉ ከመቼ ጀምሮ ነዉ ለሚለዉ ጥያቄ ላይ በአብላጫ ድምጽ ተጠሪ ድርጅቱን ከተረከበበት ከ27/10/99 ዓ.ም እስከ 13/03/08 ዓ.ም ማለትም አመልካች ዋናዉን ገንዘብ በሞዴል 85 እስከ አስያዘበት ጊዜ ድረስ ያለዉን ወለድ በባንክ ምጣኔ መሰረት ተሰልቶ ለተጠሪ እንዲከፈል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡አናሳዉ ድምጽ ወለድ ለተጠሪ ሊታሰብ እንደሚገባ ተስማምቶ ጊዜዉን በተመለከተ ግን በከፍተኛ ፍርድ ቤት በ27/10/99 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ ተጠሪ ድርጅቱን እንዲረከብ ተደርጎ በእጁ መግባቱ ተረጋግጦ የአፈጻጸም መዝገብ ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጨረታ ሊካሄድ ይገባል በሚል ይህንን ትእዛዝ እስከሻረበት 29/11/02 ዓ.ም ድረስ ላለዉ ጊዜ ተጠሪ ድርጅቱን በእጁ አድርጎ ሲጠቀም ስለነበር ወለድ ሊታሰብ አይገባም ይልቁንም ወለድ ሊታሰብለት የሚገባዉ በ29/11/02 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ገንዘቡን በሞዴል 85 እስከአስያዘበት ጊዜ ድረስ መሆን አለበት የሚል ሀሳብ አስፍሯል፡፡

አመልካች በዚህም ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ የቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በግራቀኙ መካከል በነበረዉ የገንዘብ ክርክር የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/01885 በ17/10/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት አመልካች በባንክ እዳ ዋስትና ተይዞ የነበረዉን አከራካሪ ቤት የተረከቡት በ13/03/08 ዓ.ም ቢሆንም የባንኩን ወለድ ከ27/10/99 እስከ 13/03/08 ዓ.ም ታስቦ ይክፈሉ መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል በሚል ሰበር አጣሪ ጭብጥ ይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ መጥሪያ ደርሶ ተለዋጭ

www.abyssinialaw.com

ቀጠሮም ጠይቀዉ በተሰጠዉ ተለዋጭ ቀጠሮ መልስ ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ተጠሪ ቀደም ሲል በመቐሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01885 በ27/10/99 ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት አከራካሪዉን ቤትና ድርጅት እንዲረከብ የተደረገዉ ከአመልካች የሚፈለግ የኢት/ልማት ባንክ ብድር ብር 740,963.00 ፣የወ/ሮ ስላስ በርሄ እዳ ብር 80,688.00፣የአቶ ስዩም ተሰማ እዳ ብር 125,568.00 እና የተጠሪዉ ገንዘብ ብር 177,561.00 በድምሩ ብር 1,134,780.00 በመክፈሉ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡በዚሁ አግባብ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳን/የአመልካቹን /ንብረት ተረክቦ ስመ ሀብቱም በስሙ ተመዝግቦለት ንብረቱን እየተጠቀመ የቆየ ሲሆን አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ያለጨረታ መረከቡ ተገቢ አይደለም ተብሎ በሰበር መ/ቁ/45733 ዉሳኔ ተሰጥቶ በንብረቱ ላይ ጨረታ እንዲደረግ ወደ ስር ፍርድ ቤት መመለሱም ተረጋግጧል፡፡ይህንን ተከትሎ አመልካች በተጠሪ እጅ ያለዉ ቤትና ድርጅት በጨረታ እንዲሸጥ ትእዛዝ እንዲሰጥ ለከፍተኛዉ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ በክርክር ላይ እያለ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ክርክር የተነሳበትን ቤትና ድርጅት በተጠሪ ስም በመያዣ ይዞ ብር 1,700,000 መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ ዉል ያበደረዉ መሆኑን ገልጾ የቅድሚያ መብት ያለዉ በመሆኑ በጨረታ እንዳይሸጥ በጣልቃ ገብነት ስለመከራከሩና እስከ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ደርሶ ባንኩ ንብረቱ እግድ ያለበትንና ሰበር መ/ቁ/45733 ዉሳኔ የተሰጠበትን በሚጻረር ሁኔታ በመያዣነት መያዙ ከቅን ልቦና ዉጪ ነዉ ተብሎ ስለመወሰኑ ሰበር መ/ቁ/80258 ላይ በ07/09/05 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት ያስረዳል፡፡ ከዚህም ባሻገር ተጠሪና ባለቤቱ የሆነችዉ ወ/ሮ/ ኪሮስ ሲባጋድስ እግድ ያለበትን ንብረት እግድ እንደሌለበት አስመስለዉ ለባንክ መያዣ አስይዘዉ ብድር ወስደዋል ተብለዉ በማታለል ወንጀል ተከሰዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ የተላለፈባቸዉ ስለመሆኑም የፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዟል፡፡ከዚህ በኋላ አመልካች ቤቱ ከተጠሪ እጅ ወጥቶ በጨረታ እንዲሸጥ ሲጠይቁ ተጠሪ ለፍርድ ባለገንዘቦች የከፈለዉን ገንዘብ በሞዴል 85 እንዲያስይዙ የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01885 ላይ ትእዛዝ መስጠቱንና አመልካችም ገንዘቡን በ13/03/08 ዓ.ም በሞዴል 85 ማስያዙ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ፡፡

www.abyssinialaw.com

እንግዲህ አከራካሪዉ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ወለድ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? ወለድ ሊከፍል ይገባል ከተባለስ ከመቼ ጀምሮ ይታሰብለታል? የሚለዉ ነዉ ።በመሰረቱ ባለእዳ ወለድ ሊከፍል የሚገደደዉ በዉል ሲገለጽ ወይም በፍርድ ሲወሰን አሊያም በህግ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን እንደሆነ ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ1803፣1751 እና 2478 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል።በመሆኑም አመልካች የፍርድ ባለእዳ መሆኑና የፍርድ ባለመብቶች ገንዘብ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ወለድ እንዲታሰብ በዋናዉ ክርክር መዝገብ ፍርድ መሰጠቱ እና ተጠሪ አመልካችን ተክቶ ለፍርድ ባለገንዘቦች ገንዘቡን መክፈሉ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ዋናዉ ገንዘብ ተጠቃሎ እስከ ከፈለዉ ድረስ ዋናዉን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ወለዱንም ጭምር ማግኘት እንዳለበት በፍርድ የተላለፈለት መብት ከመሆኑ አኳያ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ። ነገር ግን ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ከ27/10/99 ዓ .ም ጀምሮ በእጁ አድርጎ እስከ 13/03/08 ዓ.ም ድረስ ላለፉት 9 ዓመታት ንብረቱን በእጁ አድርጎ እየተጠቀመበት መሆኑን በመግለጽ ወለድ ሊታሰብ እንደማይገባ አመልካች አጥብቆ መከራከሩን መዝገቡ ያስረዳል።ስለሆነም በእርግጥም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በ27/10/99ዓ.ም በተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት የአመልካችን ንብረት በእጁ አድርጎ ሲጠቀም በቆየበት ጊዜ ከዋና ገንዘብ በተጨማሪ ለገንዘቡ ወለድ እንዲታሰብ ማድረግ ተጠሪ ያለአግባብ እንዲበለጽግ አመልካች ደግሞ ያለአግባብ እንዲጎዳ የሚያደርግ እንደሆነ መረዳት አዳጋች አይደለም።

ስለሆነም ለተጠሪ ወለድ መታሰብ አለበት ቢባል እንኳን ወለድ ከመቼ ጀምሮ ሊታሰብ ይገባል የሚለዉን ለመወሰን ተጠሪ የአመልካችን ንብረት በሰበር ችሎት በመ/ቁ/45733 በተሰጠ ፍርድ መሰረት መልሶ ለአመልካች ያስረከበበት ወይም ከተጠሪ እጅ ወጥቶ በሃራጅ የተሸጠበት ቀን በግልጽ ሊታወቅ ይገባል።በዚህ ረገድ ደግሞ አመልካች ቤቱና ድርጅቱ በሃራጅ እንዲሸጥ ገንዘቡን በሞዴል እንዲያስዝ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ መስጠቱን እና ቤቱና ድርጅቱ ከተጠሪ እጅ ወጥቶ ወደ ሐራጅ ስርዓት እንዲገባ የተደረገዉ በ13/03/08 ዓ.ም ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ መስጠቱን ገልጾ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚያስለዉጥ ክርክርና ማስረጃ በተጠሪ በኩል አልቀረበበትም።ከዚህም ባሻገር ቀደም ሲል ተጠሪ ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቀደም ተከተሉ በመ/ቁ/ 81191 በ05/05/08 እና በመ/ቁ/52053 በ04/06/08 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ የተጠሪ

www.abyssinialaw.com

የወለድ ጥያቄ ዉድቅ ተደርጎ ያደረዉን ንብረቱ በጨረታ ከተሸጠ በኋላ በሂሳብ መተሳሰብ ሰበብ የወለድን ጉዳይ እንደአዲስ በተጠሪ በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በ17/10/08 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ ወለድ ከ27/10/99 ዓ.ም እስከ 13/03/08 ዓ.ም ድረስ ይታሰብለት ማለቱ ፍርድ ቤቱ ራሱ በ05/05/08 ዓ.ም ከሰጠዉ ትእዛዝ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ስነስርዓታዊ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የፍርድ ማስፈጸሚያ ይሆናል የተባለዉን የአመልካችን ንብረት ተጠሪ ከ27/10/1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 13/03/08 ዓ.ም ማለትም ለፍርድ ባለገንዘቦች የከፈለዉ ዋና ገንዘብ በሞዴል እስከተያዘበት እለት ድረስ ንብረቱን በእጁ አድርጎ ሲጠቀምበት የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ በባንክ በመያዣ አስይዞ ገንዘብ ብድር የወሰደበት መሆኑ ጭምር በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በአመልካች ንብረት ሲጠቀም መቆየቱ ተረጋግጦ እያለ ለዚሁ ጊዜ ዉስጥ ከዋናዉ ገንዘብ በተጨማሪ አመልካች ለተጠሪ ወለድ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ የተሰጠዉ ዉሳኔ እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናዉ ፍትሃዊና ምክንያታዊ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1ኛ/የመቐሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01885 ላይ በ17/10/08 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/87641 በ09/03/09 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ተጠሪ በአመልካች ንብረት ሲጠቀም መቆየቱ ስለተረጋገጠ አመልካች ወለድ የመክፈል ሃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መቁ149301

ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ውዴ ደሴ- ጠበቃ አቶ አለማየሁ የኔት ቀረበ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1.አወቀ ደሴ

2 አዲስ ደሴ } የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በአዊ ብሔረሰብ ዞን የባንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ከሳሾች /የአሁን ተጠሪዎች/ በ14/07/2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ወላጅ አባታቸው አቶ ደሴ ካሰ እና እናታቸው ወ/ሮ እምየ በላይ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ገልጸው የውርስ ንብረቶችን 1ኛ/ 56 ዘንግ ቆርቆሮ ቤት ግምቱ ብር 6,000 /ስድስት ሺህ ብር/፣ ሳር ቤት ግምቱ ብር 3,000 /ሶስት ሺህ ብር/፣100 ባህርዛፍ ግምቱ ብር 3,000 /ሶስት ሺህ ብር/ 2ኛ/ አዋሳኙን ጠቅሰው በተለያዩ በአምስት ቦታዎች የሚገኝ የእርሻ መሬት ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ይዘው ያሉትን የውርስ ድርሻ እንዲሰጡዋቸው ፈቃደኛ ሆነው ስላልተገኙ ድርሻቸውን እንዲሰጡ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሁን አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ በቀን 12/09/2009 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ይኸውም የከሳሾች እናት በ1993 ዓ/ም ስለሞቱ የእናታቸውን ድርሻ ለመጠየቅ መብታቸው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000/1/ መሠረት በሶስት ዓመት ይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ለፍሬ ነገሩ በሰጡት መልስ ቆርቆሮ ቤቱን በተመለከተ ከሟች አባታቸው በቀን 18/6/2007 ዓ/ም በተደረገ የሥጦታ ውል መሠረት ተከሳሽ ከባለቤታቸው ጋር የሰሩት በመሆኑ ከሳሾችን አይመለከታቸውም፣ሳር ቤቱን ድርሻቸውን መካፈል ይችላሉ፣ከሳሾች አዋሳኞችን ጠቅሰው ካቀረቡት የእርሻ መሬት መካከል በክሳቸው ተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሱትን አራት ቀዳ መሬት አባታቸው በሥጦታ ውል የሰጡ በመሆኑ ከሳሾችን አይመለከታቸውም የተቀረውን የእርሻ መሬት በተመለከተ የእናታቸው ድርሻ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ የአባታቸውን ድርሻ ከተከሳሽ ጋር መካፈል ይችላሉ፣ባህርዛፉንም በተመለከተ ድርሻቸውን መካፈል እንደሚችሉ ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የባንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት በይርጋ መቃወሚያ ላይ ማስረጃዎችን ሰምቶ ግራ ቀኙ እናት ከሞቱ በኃላ ክርክር የተነሳባቸው ንብረቶች አባታቸው እስከ ሞቱበት 2007 ዓ/ም ድረስ በእጃቸው የቆየ በመሆኑ እና የሥር ከሳሽ ከአባታቸው ጋር አብረው ቢኖሩም ንብረቶቹን የያዙት ከእሳቸው ሞት በኃላ በመሆኑ ይርጋ ሊያገድ አይችልም ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ፍሬ ነገሩንም በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮ፣ ምስክሮችን ቃል ሰምቶና ሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ የቆርቆሮ ቤት አባታቸው በውል በሰጡት ቦታ ላይ ተከሳሽ እና ባለቤታቸው የሰሩበት መሆኑ ስለተረጋገጠ ለከሳሾች አይገባም፣ ተከሳሽ አባቷ በሥጦታ ሰጥቶኛል ያለችውን 4 ቀዳ መሬት በተመለከተ ሟች ሥጦታ ቢሰጥም እንኳ የራሱን ድርሻ እንጂ የሌሎችን ልጆች በሚጎዳ መልኩ መስጠት የለበትም፣ ማለትም የእናታቸውንም ሆነ የራሱን ድርሻ ማለት ነው፡፤ የሳር ኪዳን ቤት፣የባህርዛፍ ተክል የሚቐቹን ተከሳሽ መያዟን እና ያለ መሆኑን ያመነች በመሆኑ ባመነችበት መሠረት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 242 መሠረት በዓይነት ወይንም በግምት ድርሻቸውን ለከሳሾች ልትሰጥ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች /የሥር ከሳሽ/ ውሳኔውን ቅር ተሰኝተው ለአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡የይግባኝ ቅሬታ ይዘትም፡- የእናታቸው ድርሻ በይርጋ

www.abyssinialaw.com

ቀሪ መሆን ሲገባው በብይን መታለፉ አግባብ አይደለም፤ አባቴ በሥጦታ የሰጠኝን አራት ቀዳ መሬት ከሳሾችም እንዲካፈሉ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ በይርጋ አይታገድም መባሉ ተገቢ እንደሆነና ሟች ለአሁን አመልካች በሥጦታ የሰጡትን አራት ቀዳ የእርሻ መሬት አመልካች /ይግባኝ ባይ/ ለመልስ ሰጪዎች /ለአሁን ተጠሪዎች/ ታካፍል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ ለይግባኙ ምክንያት የሆነው አራት ቀዳ መሬት የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ወላጆች መሆኑን፣ እናታቸው በ1993 ዓ/ም መሞታቸውን፣ ወላጅ አባታቸው ደግሞ በ2007 ዓ/ም መሞታቸውን፣ መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ ደግሞ ሁሉንም መሬቶች በሥጦታ አግኝቻለሁ በማለት መከራከሯን ተመልክተናል፡፡ በመርህ ደረጃ ማንም ሊያስተላልፍ የሚችለው ያለውንና የእርሱ የሆነን እንጂ የእርሱ ያልሆነን ለማስተላለፍ አይችልም፡፡ ስለሆነም የአመልካች አባት ከእሳቸው ድርሻ ውጪ ያለውን የባለቤታቸውን ድርሻ በሥጦታ ማስተላለፍ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የአሁን መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ በሥጦታ ሊተላለፍላት የሚገባው የወላጅ አባታቸው ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ መሬት ብቻ እንጂ የወላጅ እናታቸው ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ መሬት ግን ይግባኝ ባዮችና መልስ ሰጭ እንደየ ድርሻቸው መብት ያላቸው ስለሆነ በአዋጁ ከተመለከተው አንጻር መካፈል የሚችል ከሆነ እንዲከፋፈሉት፣ ለመካፈል የማይችል ከሆነ ግን በሚስማሙት መንገድ እንዲጠቀሙ በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሰኔ ለማስለወጥ የአሁን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ተዘግቶባቸዋል፡፡

የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታም ውሳኔውን በመቃወም ሲሆን በጠበቃቸው በኩል የቀረበ የሰበር አቤቱታ ይዘቱም በአጭሩ፡- ሟች ወላጅ እናታችን የሞተችው ነሐሴ 16 ቀን 1993 ዓ/ም ሆኖ እያለ ከ15 ዓመት በላይ ቆይተው ያቀረቡትን ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት እየተቃወምኩ እያለ በብይን መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል፣ሟች ደሴ ካሰ ለአመልካች አራት ቀዳ ይዞታ

መሬት በሥጦታ ሲያስተላልፍ ተጠሪዎች የሚች እናታችን እማሆይ እምየ በላይ ድርሻ ጭምር በሥጦታ ማስተላለፍ ተገቢ ባለመሆኑ የሥጦታ ውል እንዲፈርስ በማለት በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኝነት አልጠየቁም፡፡ አመልካች በቀን 16/03/2005 ዓ/ም የተሰጠ እና በሚመለከተው አካል የፀደቀ የሥጦታ ውል አቅርባ ይህም ውል በፍርድ ፈራሽ ሳይሆን ባልተጠየቀ ዳኝነት ሚች ደሴ ካሰ የሚች ባለቤቱን ድርሻ ጭምር ይዞታ ማስተላለፍ አይችልም በማለት ለአመልካች በሥጦታ የተላለፈልኝን አራት ቀዳ ይዞታ ጭምር ለተጠሪዎች ልታካፍል ይገባል በሚል የተሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ያልጠየቁት ዳኝነት ላይ የተሰጠው ውሳኔ በመሆኑ የህግ ስህተት አለበት እንዲባልልኝ የሚል ነው፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ በተጠሪዎች በኩል በክስ ቁጥር 2 እና 3 ላይ የተጠቀሰው የይዞታ መሬት ለአመልካች በሥጦታ የተላለፈና ሥጦታም መመዝገብ ያለበት አካል ተመዝግቦና ለአመልካች በተላለፈበት ሁኔታ የሥጦታ ውሉ ሳይፈርስ የውርስ ንብረት ነው የተባለበት አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርገላቸው በጠበቃቸው በኩል በ23/4/2010 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አካራካሪውን መሬትና ሀብት ሚች አባታችን እስከሞቱበት 2007 ዓ/ም ድረስ በእሳቸው እጅ የነበረ መሆኑን፣ እሳቸውም የእናታችንን ድርሻ ጭምር በሥጦታ ማስተላለፋቸውን ግራ ቀኙ ሳንካካድ፣ ሥጦታ ውሉም በህግ መሠረት ሲጸና የማይችል በመሆኑ ሊፈጸም አይገባም በሚል በቂ መቃወሚያ ቀርቦበት ይህ ስለመሆኑም ተረጋግጦ የይዞታ መሬቱን ጨምሮ ሌሎች ሀብቶች የውርስ ሀብት ተብሎ በድርሻችን ልክ እንድንከፋፈል መወሰኑ ስህተት የሌለበት ስለሆነ በቂ ወጪና ኪሳራም ታስቦልን በነፃ እንድንሰናበት በማለት ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪዎችን መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን አመልካች ባለመቅረባቸው ከፈለጉ የመልስ መልስ ከምርመራ ቀጠሮ ቀን በፊት እንዲያቀርቡና ለተጠሪዎች እንዲያደርሱ ታህሳስ 25 ቀን 2010 ዓ/ም ታዞ የመልስ መልስ አላቀረቡም፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን ሟች ለአመልካች በሥጦታ ከሰጡት አራት ቀዳ መሬት የግራ ቀኙን የእናታቸውን ድርሻ ሟች አባታቸው ለአሁን አመልካች በሥጦታ ሊሰጡ አይችሉም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ህጋዊ መሠረት አለው ወይስ የለውም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን አራት ቀዳ የእርሻ መሬት በተመለከተ ይዞታው የወላጆቻቸው ስለ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሁን አመልካች ሁለት መከራከሪያዎችን ያነሳሉ፡፡ የመጀመሪያው የአመልካችና የተጠሪዎች እናት በ1993 ዓ/ም ስለሞቱ የአሁን ተጠሪዎች እናታቸው ከሞቱ ከ15 ዓመት በኃላ ያቀረቡ ክስ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ለዚህ መቃወሚያ የአሁን ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ የእናታቸው ድርሻ እስከ አባታቸው ሞት ማለትም እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ በአባታቸው እጅ የቆየ በመሆኑና የሥር ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ እጅ ተይዞ ያልቆየ በመሆኑ በይርጋ አይቋረጥም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት የሟች እናታቸው ድርሻ አባት እስከሞቱበት እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ በአባታቸው እጅ የቆየ እንጂ የአሁን አመልካች ይዘው የቆዩበት ባለመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000/1/ መሠረት በሶስት ዓመት ይርጋ ሊቋረጥ አይችልም በማለት ብይን ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ዋናው ጉዳይ ውሳኔ ሲያገኝ ይህን ብይን የመጀመሪያ የይግባኝ ቅሬታ አድርገው ቢያቀርቡም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአዊ ብሔረሰብ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አጽንቶበታል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ አላቀረቡም፡፡ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዚህ የሰበር ምክንያት የሆነው መሬት ለአሁን አመልካች በሥጦታ የተሰጣቸው በመሆኑ ለተጠሪዎች አይገባም ተብሎ ስለተወሰነ የይርጋውን ክርክር አመልካች ትተውታል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች አራት ቀዳ መሬት ለአሁን አመልካች ይገባል ተብሎ መወሰኑን በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የእናታቸውን ድርሻ አባታቸው ለአሁን አመልካች በሥጦታ ሊሰጡ አይችሉም ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበው ተዘግቶባቸዋል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ አንዱ የቅሬታ ነጥብ ይርጋን የተመለከተ ነው፡፡ ይህ ቅሬታ ነጥብ /ጥያቄ/ ሥነ ሥርዓታዊ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ይኸውም ከላይ

እንደተገለጸው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ ቅሬታን በተመለከተ የወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ተገቢ ነው ብሎ ሲያፀና የአሁን አመልካች ይግባኝ አላሉበትም፡፡ ይልቁንም በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያሉት

የአሁን ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ይርጋን በተመለከተ የአሁን አመልካች ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ባላሉበት ሁኔታ አሁን ለዚህ ችሎት ይህን በተመለከተ በቅሬታነት ማንሳታቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ስለ ይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት የደነገገውን አንቀጽ 320 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችን የተከተለ ባለመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሁለተኛ ቅሬታ ነጥብ አባታቸውም በህግ አግባብ ከሰጡት አራት ቀዳ መሬት ላይ ሁለቱ ቀዳ የእናታቸው ስለሆነ ግራ ቀኙ እኩል ይካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎች የሥጦታ ውል ይፍረስልን ብለው ባልጠየቁት ዳኝነት ላይ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ ለዚህ የቅሬታ ነጥብ የአሁን ተጠሪዎች ለዚህ ችሎት በሰጡት መልስ አካራካሪውን መሬትና ሀብት ሟች አባታችን እስከሞቱበት 2007 ዓ/ም ድረስ በእሳቸው እጅ የነበረ ሲሆን እሳቸውም የእናታችንን ድርሻ ጭምር በሥጦታ ማስተላለፋቸውን ግራ ቀኙ ሳንካካድ፣ ሥጦታ ውሉም በህግ መሠረት ሊጸና የማይችል በመሆኑ ሊፈጸም አይገባም በሚል በቂ መቃወሚያ ቀርቦበት ይህ ስለመሆኑም ተረጋግጦ የይዞታ መሬቱን ጨምሮ ሌሎች ሀብቶች የውርስ ሀብት ተብሎ በድርሻችን ልክ እንድንከፋፈል ተወስኗል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ከተከራከሩባቸው ንብረቶች መካከል የአሁን አራት ቀዳ መሬት አንዱ ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ይህ መሬት የአባታቸው ብቻ ሳይሆን የሟች እናታቸው ድርሻ ጭምር ያለበት ስለሆነ ለአሁን አመልካች በሥጦታ መሰጠቱ ህጋዊ አይደለም በማለት መከራከራቸውን የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ሥጦታው መብታችንን የሚጎዳ ስለሆነ በህግ ይሁንታ ሊሰጠው አይገባም የሚል ክርክር እስከ ቀረበ ድረስ ሥጦታው እንዲፈርስ የተለየ የዳኝነት ጥያቄ ሊቀርብ ይገባል የሚለው የአመልካች ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግራ ቀኙ አባት አራት ቀዳ መሬት ለአሁን አመልካች ሲሰጡ የግራ ቀኙ እናት ድርሻ እንዳለ የአሁን አመልካችም አይክዱም፡፡ ነገር ግን ይህን በተመለከተ አመልካች ይርጋን አንስተው ቢከራከሩም ጥያቄኣቸው ወድቅ ሆኖባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ አባት ከራሳቸው ድርሻ አልፈው ሟች ባላቤታቸውን ድርሻ ጭምር ለአሁን አመልካች ሊሰጡ ይችላሉ ወይ? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ የአመልካች አባት ድርሻቸውን በሥጦታ ለአመልካች መስጠት ይችላሉ እንጂ የባለቤታቸውን ማለትም የግራ ቀኙን እናት ድርሻ ሊሰጡ የሚችሉበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2427 " ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት" በማለት የተደነገገውም ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲሁም የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2451 /1/ የተመለከተው ጽንሰ ሀሳብም አስተላላፊው /ሰጭ/ የራሱ የሆነን ሀብት ብቻ ሊያስተላልፍ እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሟች ደሴ ካሳ ለአሁን አመልካች ሥጦታ ያደረጉት የአሁን ተጠሪዎችን ወላጅ እናት ድርሻ መሬት ነው፡፡ ይህም ደግሞ ከፍ ሲል ከተመለከተው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2451 /1/ አንጻር ሲታይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ፡

በመጨረሻም ለአሁን አመልካች በሥጦታ ሊተላለፍላቸው የሚገባው የወላጅ አባታቸው ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ መሬት ብቻ እንጂ የወላጅ እናታቸው ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ መሬት ሊሆን ስለማይችል ግራ ቀኙ እንደየድርሻቸው ሊካፈሉት ይገባል በማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔም ሆነ ይህ ውሳኔ በአቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ መዝጋቱ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 45274 በቀን 13/11/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ. 70347 በቀን 20/2/2010 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የአመልካች አባት ከድርሻቸው ውጪ ያለውን የእርሻ መሬት ለአሁን አመልካች በሥጦታ ሊሰጡ አይችሉም፤የሟች እናታቸውን ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ የእርሻ መሬት ለግራ ቀኙ ሊሆን ይገባል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ቅ/ሀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 154115

**ቀን** - 25/01/2011

**ዳኞች፡-** ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

**አመልካች፡-** ያዳኒ ራባ -አልቀረቡም ከተባለ ተወካይ ሰመረ ገ/ህይወት ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንዋር መስጊድ ቅርንጫፍ -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በመጋቢት ወር 2007 ዓ.ም የባንክ ደብተራቸዉን ይዘዉ ባደሩበት አልጋ ላይ ረስተዉ መሄዳቸዉን ተከትሎ ተጠሪ በባንክ ደብተራቸዉ ላይ ያለዉን ገንዘብ ማንነቱ ላልታወቀ ሰዉ በመክፈል የገንዘብ እና የሞራል ጉዳት ያደረሰባቸዉ መሆኑን ጠቅሰዉ ተጠሪ ያላግባብ የከፈለዉን ብር 46,900.00 እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 20,000.00 እንዲከፍል ይወሰንላቸዉ ዘንድ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ለክሱ በሰጠዉ መልስ፤ ገንዘቡ የተከፈለዉ አመልካች ከሞሉት ፎርም እና ከፊርማቸዉ ናሙና ጋር በማመሳከር ተገቢዉ ጥንቃቄ ተደርጎ ለአመልካች ለእራሳቸዉ የተከፈለ መሆኑን፣ እንዲሁም ደብተሩ ጠፍቶ አራት ወር ሲቆይ አመልካች ደብተሩ ስለመጥፋቱ ለፖሊስ አመልክተዉ ሂሳቡ እንዲታገድላቸዉ አለማድረጋቸዉን በመጥቀስ ኃላፊነት የለብኝም ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ፤ አመልካች ደብተሩ የጠፋባቸዉ ስለመሆኑ ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታ እያለባቸዉ ይህን ባለማድረግ የሂሳብ ደብተሩ ሦስተኛ ወገን እጅ ገብቶ ገንዘቡን ሌላ ሰዉ እንዲያወጣ ምክንያት በመሆናቸዉ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲከፍል የሚገደድበት ምክንያት የለም በማለት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በቀን 15/06/2010 ተዘጋጅቶ በተወካያቸዉ አማካይነት በቀረበ የሰበር አቤቱታ፤ ተጠሪ ተገቢዉን ማጣራት እና ጥንቃቄ ሳያደርግ ከአመልካች የሂሳብ ደብተር ወጪ አድርጎ ለሌላ ሰዉ ከፍሎ እያለ እና ገንዘቡን የከፈለዉ የባንኩ ሠራተኛም በዚህ ጉዳይ ላይ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ እያለ አመልካች ደብተሩ መጥፋቱን ሪፖርት የማድረግ ግዴታቸዉን አልተወጡም የሚል ምክንያት በመጥቀስ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በሚል በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ ያደረገዉ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሂሳብ ቁጥር 1000065634159 ያስቀመጡትን ገንዘብ የያዘ የባንክ ደብተር መጥፋቱን እና ባንኩ በሂሳብ ደብተሩ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ለ3ኛ ወገን መክፈሉን ሲሆን፤ ተጠሪም የባንክ ደብተር ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ወጪ አድርጎ የከፈለ ስለመሆኑ ክዶ አልተከራከረም፡፡ የተጠሪ ክርክር የነበረዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርጎ ለአመልካች እራሷ

መክፈሉን እና የሂሳብ ደብተሩ ስለመጥፋቱ አመልካች ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታቸዉን አለመወጣታቸዉን ሲሆን፤ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ አመልካች ደብተሩ ስለመጥፋቱ ለተጠሪዉ ባንክ ሪፖርት የማድረግ ግዴታቸዉን አለመወጣታቸዉን ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

በመሠረቱ በግራ ቀኝ መካከል ተደርጎ ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነዉ ግንኙነት መሠረቱ በንግድ ህጉ አንቀጽ 896 እና 897 ስር የተመለከተዉ ገንዘብ በአደራ የማስቀመጥ ዉል (deposit fund) ነዉ፡፡ በዚህ ዉል መሠረትም ተጠሪ አደራ አስቀማጭ እንደመሆኑ የአመልካችን ገንዘብ የመጠበቅ፣ አመልካች ሲጠይቁ ወጪ አድርጎ የመክፈል እና ከአመልካች ዉጪ ለሌላ ሰዉ ያለመክፈል ከዉል የመነጨ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ይህን የማድረግ ግዴታዉን ባለመወጣት በአመልካች ላይ ሊደርስ ለሚችል ጉዳት ከዉል የመነጨ ኃላፊነት እንደሚኖርበትም ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ማንኛዉም ባንክ የሚቀርብለትን የክፍያ ጥያቄ ሲያስተናግድ፣ ገንዘብ እንዲከፈለዉ ጥያቄዉን ያቀረበ ሰዉ በርግጥም አደራ አስቀማጩ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ ተጠሪ በአመልካች የባንክ ሂሳብ ላይ የሚገኘዉን ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ ወጪ አድርጎ ክፍያ የፈጸመ ስለመሆኑ ክዶ እስካልተከራከረ ድረስ፣ ከኃላፊነት ሊድን የሚችለዉ ገንዘቡን የከፈለዉ በባንኩ በተዘረጋዉ ደንብና አሰራር መሠረት አስፈላጊዉን ጥንቃቄ ሁሉ አድርጎ ተከፋዩ አመልካች መሆኑን በማረጋገጥ ክፍያዉን የፈጸመ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ነዉ፡፡ በርግጥ አመልካች ደብተሩ ስለመጥፋቱ ለተጠሪ ባንክ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለባቸዉ ይታወቃል፡፡ ይሁንና፣ ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ በአደራ የመጠበቅ ባለበት ግዴታ መሠረት ተገቢዉን ጥንቃቄ ባለማድረግ ገንዘቡን ለሌላ ሰዉ በመክፈሉ ምክንያት በአመልካች ጉዳት መድረሱ ከተረጋገጠ፣ አመልካች ደብተሩ ስለመጥፋቱ ለተጠሪ አለማሳወቃቸዉ የተጠሪን ኃላፊነት ሊያስቀር የሚችል አይሆንም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት ተይዞ በማስረጃ ተጣርቶ እልባት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ፣ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ የከፈለዉ አስፈላጊዉን ጥንቃቄ

www.abyssinialaw.com

በማድረግ ተከፋዩ አመልካች መሆኑን በማረጋገጥ መሆን አለመሆኑ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ደብተራቸዉ ስለመጥፋቱ ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታቸዉን አልተወጡም በሚል የፍ/ሕጉን አንቀጽ 1752 ድንጋጌ ያለቦታዉ በመጥቀስ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህኑን በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 50523 በቀን 20/04/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 193272 በቀን 25/03/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ገንዘብ ከአመልካች የባንክ ሂሳብ ወጪ አድርጎ ሲከፍል በባንኩ በተዘረጋዉ ደንብና ስርዓት መሠረት ክፍያዉ ለአመልካች የተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ በሚያስችል ደረጃ አስፈላጊዉን ጥንቃቄ በማድረግ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ የግራ ቀኙን ማስረጃ እንዲሁም፣ እንዳስፈላጊነቱ፣ ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎችን ጭምር አስቀርቦ በመመርመር ባንኩ አደራ አስቀማጭ ከመሆኑ አንፃር ክፍያን በመፈጸም ረገድ እንዲያደርግ ከሚጠበቅበት ጥንቃቄ አንፃር በማገናዘብ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ.128086

ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡...1.ተኽሊትይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡-......የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት....ጠበቃ ዶ/ር ዘዉድነህ በየነ እና ነ/ፈጅ አቶ አስራት መኮንን ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡-............ኮንስታ ጆይንት ቬንቸር.....ጠበቃ አቶ ወሰንየለህ ትጉህ ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ይህ ክርክር የተጀመረዉ በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ኔዘርላንድ (ሄግ) የሚገኘዉ ቋሚ የግልግል ዳኝነት ፍ/ቤት የሚያስተዳደረዉ መቀመጫዉ አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ የሆነዉ ሲሆን፣የአሁን አመልካች ተከሰሽ፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በመ.ቁ.2013-32 ሚያዚያ 28 ቀን 2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ግንቦት 6 ቀን 2016) የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

2.የጉዳዩአመጣጥሲታይከሳሽ ኮንስታ ጆይንት ቬንቸር ባቀረበዉ ክስ ከተከሳሽ የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት ጋር የባቡር መስመር ጥገና ዉል ህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም (November 29, 2006) ተስማምተን ነበር፡፡ ከሳሽ በዉሉ መሰረት ስራዉን እየሰራ የነበረ ቢሆንም በተከሳሽ ጥፋት በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 65 መሰረት ዉሉ ተቋርጧል፡፡ በዚህ ዉል መሰረት ከሳሽ ሰርቶ ክፍያ ያልተፈጸመባቸዉ ሥራዎች እና በተከሳሽ ጥፋት ፕሮጀክቱ በመዘግየቱ በከሳሽ ላይ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ፣ ተከሳሽ ካሳ በአጠቃላይ 21,076,081.00 (ሀያ አንድ ሚሊዮን ሰባ ስድስት ሺህ ሰማኒያ አንድ) ዩሮ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈለን እንዲሁም ተከሳሽ ክፍያዉን ላዘገየበት ተጠያቂ ነዉ እንዲባልልን በማለት ከሷል፡፡

3. በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ኮንስታ ከተከሳሽ ጋር ዉሉን ያደረገዉ በተንኮል ወይም በማጭበርበር ተግባር ሲሆን፣ በተጨማሪም ኮንሰታ የእሽሙር ማህበር በዉሉ መሰረት መፈጸም የነበረባቸዉን ግዴታዎች አንድም ያልፈጸሙ በመሆኑ እና በዚህ ምክንያት ተከሳሽ ላይ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ ከሳሽ የጉዳት ካሳ ለተከሳሽ ሊከፍለን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

4. በሌላ በኩል የተከሳሽ ከሳሽ ባቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የከሳሽ ተከሳሽ በግንባታ ዉል መሰረት ባለመፈጸሙ ብር 66,444,384 ዩሮ ከወለድ ጋር እንዲከፍለን በማለት ጠይቋል፤ በአማራጭ የከሳሽ ተከሳሽ ይህን ዉል ያደረገዉ በተንኮል ወይም በማጭበርበር በመሆኑ ዉሉ እንዲሰረዝ (invalidate) ተደርጎ ወደ ነበርንበት እንዲንመለስ፣ በዚህም የከሳሽ ተከሳሽ በባቡር መስመር ጥገና ዉል መሰረት ሥራዉን በአግባቡ ያላጠናቀቀ ስለሆነ ለዚህ ሥራ ተብሎ የተከፈለዉን 27,674,384.00 (ሀያ ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰማኒያ አራት) ዩሮ ከወለድ ጋር እንዲከፍለን፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍለን በማለት ከሷል፡፡ በዚህ ክስ ላይ የከሳሽ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ የተከሳሽ ከሳሽ ያቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

5. ከዚህ በኋላ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር ምስክሮችን በመስማት የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ ዉሉ በማጭበርበር የተደረገ ነዉ ለተባለዉ እና የጂሲኤፍ በኮንስታ ጂቪ የነበረዉ ተሳትፎና ለዉሉ መቋረጥ ተጠያቂነት የለበትም፣ ተከሳሽ ግን ለባቡር መስመር ሥራ ዉል መቋረጥ ተጠያቂነት አለበት፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ ነጥቦች ላይ ዉሳኔ በማስጠት፣ ተከሳሽ 20,664,767 (ሀያ ሚሊዮን ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት) ዩሮ ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከሚከፈልበት ቀን ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍለዉ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ደግሞ ተቀባይነት የለዉም በማለት ዉድቅ በማድረግ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

6. የአሁን አመልካች ግንቦት 18 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አስራ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡ በአዉሮፓ የልማት ፈንድ ሕግ መሰረት የግልግል ዳኝነት ጉባኤ የሰጠዉ ፍርድ በአገሪቱ በሚገኙ ፍ/ቤቶች እንደተሰጠ

www.abyssinialaw.com

የመጨረሻ ፍርድ እንደሚቆጠር ስለሚያመለክት እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.42239 ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ችሎቱ ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን ስላለዉ የሰበር አቤቱታዉ ለዚህ ችሎት ለማቅረብ ችለናል፡፡ የባቡር መስመር ጥገና ዉሉ 114 ኪ.ሜ ለማስጠገን የተስማመን ሲሆን፣ ለፕሮጀክቱ ፋይናንስ የተገኘዉ ከአዉሮፓ ልማት ፈንድ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉል የሚነሱ አለመግባባቶች በአዉሮፓ ልማት ፈንድ የሥነሥርዓት ሕግ የሚመራ ሲሆን፣ የዉል ስምምነቱን የሚገዛዉ የኢትዮጵያ ሕጎች እና የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ መቀመጫ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ስለሆነ አቤቱታዉ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) መሰረት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉን ፍርድ ለማረም ስልጣን ይሰጠዋል፡፡ እንዲሁም በአዉሮፓ ልማት ፈንድ የስነስርዓት ሕግ (EDF Rules)፣ የአዉሮፓ የፍርዶች አፈጻጸም ሰርዓት የኢክሲድ ኮንቬንሽን (ICSID Convention)፣ የኒዉዮርክ ኮንቬንሽን የሚባሉት የዓለም አቀፍ ስምምነቶች በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ ፍርዱ በተሰጠ አገር በሚገኝ አግባብነት ባለዉ ፍ/ቤት ፍርዱን ማስመርመር እንደሚቻል ያስገነዝባሉ፡፡ ስለሆነም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.42239 በሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለዉ፡፡ እነዚህ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደሚያመለክቱት ፍርዱን ከሰጠዉ አንድ ደረጃ ከፍ ባለ አካል ሳይመረመር የሚፈጸመዉ ፍርድ ፍትሓዊና ተቀባይነት ያለዉ የፍትሕ ሥርዓት ስለመኖሩ ዋስትና የማይሰጥ መሆኑን ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ ቅሬታ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በሰጠዉ ዉሳኔ የፈጸመዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ናቸዉ ያላቸዉ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

6.1. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የግንባታ ዉል ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 12.7 መሰረት በኮንስታ ጂቪ የዉስጥ አወቃቀር (የአክስዮን ድርሻ ክፍፍልን ጨምሮ) የሚደረግ ማናቸዉም ለዉጥ አስቀድሞ ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ ይጥላል፡፡ እንዲሁም የግንባታ ዉሉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 64.2 (h) መሰረት ኮንትራክተሩ በዉሉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 12.7 የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ የተንኮል ተግባር መፈጸሙን ማረጋገጥ ሳያስፈልግ አመልካች ዉሉን ማፍረስ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት ለሆነዉ የግንባታ ዉል ባወጣዉ ጨረታ ተጠሪ በጨረታዉ ለመወዳደር ባቀረበዉ የመወዳደሪያ ሰነድ የእሽሙር ማህበሩ ስምምነት ላይ ተጫራቹ

www.abyssinialaw.com

ኮንስታ ጆይንት ቬንቸር የተመሰረተዉ 70% የአክስዮን ድርሻ በያዘዉ ኮንሶርዚዮ ኮንስታ እና 30% የአክስዮን ደርሻ በያዘዉ ጂሲኤፍ በሚባሉት ኩባንያዎች ናቸዉ፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የግንባታ ዉሉን የፈጸመዉ በቅንጂቱ ዉስጥ ሁለቱ ድርጅቶች ያቀናጁትን እዉቀትና ሀብት እንዲሁም በተናጠል ያላቸዉ የግንባታ ግዴታ ደርሻ የዉሉ መሰረታዊ ጉዳይ ነዉ፡፡ አመልካች ይህን የተጠሪ የሁለቱ ድርጅቶች ቅንጂት ባይኖር ኖሮ ተጠሪዉ ከመነሻዉ የጨረታዉን መወዳደሪያ መስፈርትም አያሟላም፣ አመልካችም ከተጠሪ ጋር የግንባታ ዉል ሊፈራረም አይችልም ነበር፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ይህን ቅንጅት በተመለከተ ሶስት ስምምነቶችን በማድረግ ይህን ቅንጅት ወደ ማፍረስ ደረጃ ደርሷል፡፡ በዚህ መሰረት ሐምሌ 27 ቀን 1998 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ኦገስት 3 ቀን 2006) በተፈረመዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 1 መሰረት የጂሲኤፍን የአክስዮን ድርሻ ወደ 0.1% ዝቅ ለማድረግ ተስማምቷል፣ ህዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 24 ቀን 2006) በተደረገዉ የምስጥር ስምምነት ቁጥር 2 የጂሲኤፍ የአክስዮን ድርሻ ወደ 0.2% ዝቅ እንዲል አድርጓል፤ መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ማርች 20 ቀን 2007) በተፈረመዉ የምስጥር ስምምነት ቁጥር 3 መሰረት ጂሲኤፍ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ዩሮ ክፍያን በመቀበል ተሳትፎዉን እስካሁን ድረስ በተፈጸመዉ ብቻ እንዲገደብ አድርጎታል፡፡ ይህም ድርሻ ለይስሙላ የተቀመጠ ነዉ፡፡ ተጠሪ ጨረታዉን ማሸነፉ የተገለጸለት መስከረም 19 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 29 ቀን 2006 ዓ.ም) ሲሆን፣ የባቡር መስመር ግንባታ ዉል የተደረገዉ ህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም ነበር፡፡ አመልካች የተጠሪ የቅንጂት ለዉጥ ያወቃዉ በ2006 ዓ.ም እና በ2007 ዓ.ም ነበር፡፡ ተጠሪ እነዚህን ምስጥራዊ ስምምነቶች ማድረጉን አልካደም፡፡ ተጠሪ በክፉ ልቦና የዉሉ መሰረታዊ የሆነዉን የለዉጥ መረጃ ከአመልካች መደበቁን ያሳያል፣ ይህ ደግሞ ተጠሪ ከጨረታ በፊትና በኋላ ሆነ ተብሎ የማታለል፣ የማጭበርበርና የተንኮል ተግባር መፈጸሙን የሚያረጋግጥ በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1696 እና 1704 የሚጥስ እና ዉሉ እንዲፈርስ የሚያደርግ ምክንያት ነዉ፡፡ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ ተጠሪ የተንኮል ተግባር አልፈጸመም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነዉ፡፡

6.2. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ የናቪጋንት የአማካሪ ድርጅት ባለሙያዎች የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1799-1801 የተመለከተዉን

www.abyssinialaw.com

የጉዳት ካሳ አሰላል ሳያዉቁ ያቀረቡትን ሪፖርት መሰረት በማድረግ፣ በኢትዮጵያ ሕግ የተመለከተዉን የጉዳት ካሳ አሰላል ታሳቢ ሳያደርግ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

6.3. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ ከግራ ቀኛቸዉ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከወገንተኝነት በጸዳ ሁኔታ በእኩልነት በመመዘን መዳኘት ሲገባዉ ቅን ልቦና በጎደለዉ አካሄድ የተጠሪን ማስረጃዎች ሙሉ ለሙሉ በመቀበል፣ የአመልካችን ማስረጃዎች ሳይመዝን መጣሉ የማስረጃ አቀባበል፣ የማስረጃ ምዘና ደንቦችን የሚጥስ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

6.4. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የተሟላ ዲዛይን ሰርቶ ግንባታዉን የማጠናቀቅ ኃላፊነት የተጠሪ መሆኑን በግንባታ ዉሉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 12.1 እና 17.1 የተመለከተዉን በኢትዮጵያ ሕግ ስለዉሎች አተረጓጎም የተደነገገዉን ወደ ጎን በመተዉ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

6.5. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ ወገንተኛነትና የጥቅም ግጭት እያለበት ተጠሪ በዉሉ መሰረት 27 ሚሊዮን ዩሮ ከወሰደ በኋላ አንድ ሜትር እንኳን ተቀባይነት ያለዉ የባቡር መስመር ጥገና ሥራ ሳይሰራ ፕሮጀክቱ ለዘገየበት ተብሎ ተጨማሪ 20 ሚሊዮን ዩሮ ይከፈለዉ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች የሚጠይቀዉ ዳኝነት ከፍ ሲል በተጠቀሱት በእነዚህ ምክንያቶች ሁሉ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን፣ በዚህ ክርክር ምክንያት አመልካች ያወጣዉን ወጪዎች ተጠሪ እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡

7. የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር ፣ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን እንዳለዉ በመግለጽ፣ የተጠሪ ድርጅት የተቋቋመዉ ኮንስታ የ70% ድርሻ እና ጂሲኤፍ የ30% ድርሻ ይዘዉ ሲሆን በመካከላቸዉ የአወቃቀር ለዉጥ መደረጉን ተጠሪ ለአመልካች ሳያሳዉቅ ይህ ደግሞ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ሰነድ አንቀጽ 12.7 እና 64.2 መሰረት ዉል እንዲቋረጥ የሚደርግ ሆኖ ሳለ በግልግል ጉባኤዉ ተቀባይነት ማጣቱ፣ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ይህ የተጠሪ ተግባር በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704 መሰረት የተንኮል ተግባር አይደለም የመባሉን አግባብነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር

www.abyssinialaw.com

አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት አስራ ዘጠኝ ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡

የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡

7.1. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.42239 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡

7.2. በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ይህ ችሎት በመደበኛ ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ዉሳኔ እንጂ የግልግል ዉሳኔዎችን እንደማይመለከት በግልጽ ያስቀመጠ ስለሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ ለማየት አይችልም፡፡

7.3. የአዉሮፓ የልማት ፈንድ የስነስርዓት ሕግ አንቀጽ 33 እና 34 ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠዉ ዉሳኔ በተዋዋይ ወገኖች ላይ አስገዳጅነት ያለዉ እና የመጨረሻ መሆኑን እና በአባል አገሩ የአፈጻጸም ሕግ መሰረት ሊፈጸም የሚገባዉ መሆኑን እንጂ በኢትዮጵያ ዉስጥ እንደተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ በዚህ ሰበር ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ እንዲሁም የኢክሲድ እና የኒዉዮርክ ኮንቬንሽኖች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ እንዲያይ ስልጣን የሚሰጡት አይደለም፡፡ የኢክሲዲ ኮንቬንሽን እና የኢዲኤፍ ስነስርዓት በሽምግልና የተሰጡ ፍርዶች በአገራዊ ፍ/ቤቶች እንዳይከለሱና ሊፈጸም የሚገባ መጨረሻ ፍርድ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በግራ ቀኛቸዉ መካከል በሽምግልና ዳኝነት የተሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ አመልካች ዉሳኔዉ በዚህ ችሎት እንዲታይለት ያቀረበዉ አቤቱታ በሽምግልና ዳኝነት አለምአቀፍ ደረጃ አዉቅና ያገኘ መርህ እና ተሞክሮ የሚጻረር ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች እንደሚለዉ የግልግል ዳኝነት መቀመጫዉ አዲስ አበባ ነዉ በሚለዉ መነሻ ብቻ ፍርዱን እና ይዘቱን ወደ መመርመር ማለፍ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸዉን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነትን ጭምር የሚጥስ ነዉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የሽምግልና ዳኝነት ፍርድ የሕግ ስህተት ያለዉ መሆኑን አመልካች ያላስረዳ ስለሆነ ጥያቄዉ ዉድቅ እንዲደረግልን፡፡

7.4. የግንባታ ዉሉ በተንኮል የተደረገ ነዉ ለተባለዉ የተጠሪ የህብረቱ ጥንክርና አቋም አንጻር የግንባታ ዉሉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 12 (7) እና 64 (2፣ከ) አንጻር ሲታይ ተጠሪ ያደረገዉ የሕግ ሰዉነት ለዉጥ ስለሌለ፣ በተፈጥሮዉም ላይ ሆነ በቁጥጥር ላይ ያደረገዉ ለዉጥ የለዉም፣ የድርሻዉ መጠን ቢለዋወጥም ቁጥጥር የተጠሪ ሆኖ ስለቆየ

የቁጥጥር ለዉጥ አልተደረገም፡፡ አመልካች ለእነዚህ የዉሉ ድንጋጌዎች የሰጠዉ ትርጉም የተሳሳተ ነዉ፡፡ ተጠሪ እነዚህን የዉሉን አንቀጽ ተላልፏል ቢባል እንኳን ግዴታዉን መተላለፉ ብቻ ዉሉን እንደጣሰ ከማስረዳት ባለፈ እነዚህ የዉል ግዴታዎች በመጣስ የማታለልና የማጭበርበር ወይም የተንኮልን ተግባር ፈጽሟል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡ አመልካች ይህ የዉል ድንጋጌ አለመከበሩም ከአምስት አመት በፊት እራሱ ለተጠሪ በጻፈዉ ደብዳቤዎች አዉቆ እና የዉሉ አፈጻጸም እያስቀጠለ ቆይቶ አሁን የዉሉ መጣስ ማጭበርበር ነዉ ዉሉ ይፍረስልን በማለት ያቀረበዉ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፡፡

7.5. በተጠሪ እና በጂሲኤፍ መካከል የተደረገዉ የእሽሙር ማህበር ስምምነት እና የተደረጉት ለዉጦች የአክስዮን ደርሻ መቀነስ ጉዳይ በተጨባጭ ምክንያት እንጂ አመልካችን ለመጉዳት በተንኮል የተደረገ ድርጊት አልነበረም፡፡ በኮንስታ እና በጂሲኤፍ መካከል የተደረገዉ ስለሥራ ተግባራት፣ እና ስለትርፍና ኪሳራ ክፍፍል የሚደረግ የዉስጥ ስምምነት ባለድርሻዎቹ ለአመልካች ባላቸዉ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ላይ ዉጤት የሚኖረዉ አይደለም፡፡ ይህን የዉስጥ ስምምነት ለማድረግ ደግሞ የአመልካችን የቅድሚያ ስምምነት የሚጠይቅ አይደለም፡፡ አመልካች የጂሲኤፍን የተቀነሰ ሚና እያወቀ የተቃወመዉ ነገር በሌለበት አሁን ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ነዉ፡፡ ኮንስታ ፕሮጀክቱን በዉጤታማነት ለማከናወን የሚያስችለዉን ልምድና ያፈጻጸም ሪከርድ ያለዉ ነዉ፡፡

7.6. የኦላፍ ሪፖርት የተዘጋጀዉ ዉሉ ከተቋረጠ ከዓመታት በኋላ እና የግልግል ዳኝነቱ በሂደት ላይ እያለ ሲሆን ሪፖርቱም በመጨረሻ ጸድቆ በደይሬክተር ጄኔራል እንዲዘጋ የተደረገ አይደለም፡፡ ይህ ሪፖርት የዉሉ ድንጋጌ መጣሱን ከማመልከትና በሂደቱ ዉስጥ የተለያዩ ወገኖች የአሰራር ግድፈት መፈጸማቸዉን ከማመልከት ዉጪ የተንኮል ተግባር መኖሩን የሚጠቅስ ነገር የለም፡፡

7.7. ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704 መሰረት የፈጸመዉ የተንኮል ተግባር ስለሌላ አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ ተጠሪ የትርፍና የሥራ ድርሻ ክፍፍልን አስመልክቶ በባለድርሻዎች መካከል የተደረገዉን ስምምነት ሳይገልጽ ቢቀር እንኳን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1705 መሰረት በግራ ቀኛቸዉ መካከል ልዩ ግንኙነት ስለሌለ ዉሉ ፈራሽ የሚሆንበት ሁኔታ የለም፡፡ አመልካች በፕሮጀክቱ ላይ የጂሲኤፍን አለመኖር እያወቀ

www.abyssinialaw.com

ዉሉ እንዲቀጥል አድርጎ እያለ አሁን ያቀረበዉ ክርክር ከክፍያ ግዴታ ለማምለጥ ነዉ፡፡ አመልካች በዚህ ምክንያት የዉል ይፍረስልን ጥያቄ በግልግል ጉባኤዉ ተቀባይነት ማጣቱ በሕጉ አግባብ ስለሆነ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉ የመከራከሪያ ነጥብ የሕግ መሰረት የሌለዉ ስለሆነ ዉድቅ እንዲደረግልን፡፡

7.8. የአሁን አመልካች የግልግል ጉባኤዉ ስለዉሎች አተረጓጎም፣ ስለጉዳት ካሳ ስሌት እና የማስረጃ አቀባበልና ምዘና በተመለከተ የኢትዮጵያ ሕግ ወደ ጎን ትቷል በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ እንዲሁም የግልግል ጉባኤዉ ወገንተኝነትና የጥቅም ግጭት የሚታይበት ነዉ በማለት አመልካት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለዚህ ይህ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም ተብሎ አቤቱታዉ ዉድቅ እንዲደረግልን፣ ይህ ካልሆነ ተጠሪ ያቀረባቸዉን ክርክሮች በመቀበል የሽምግልና ጉባኤዉ አብላጫዉ ድምጽ የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸናልን፣ የጠበቃን አበል ጨምሮ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

9. የአሁን አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የካቲት 21 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ አስራ ስምንት ገጽ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

10. የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት የሚገባቸዉ ጉዳዮች በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የሰጠዉን ዉሳኔ በሰበር የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? በሁለተኛ ደረጃ ግራ ቀኛቸዉ መካከል የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? ዉጤቱስ ምን ይሆናል? የሚሉት ነጥቦች መሆናቸዉን ተገንዝበናል፡፡

11. የመጀመሪያዉን ጭብጥ በተመለከተ ይህ ችሎት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን የሚመለከት ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ይህን ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የፈጸመዉን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አለዉ የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ እና በአባል

አገር የሚፈጸም እንጂ በፍ/ቤት ለክለሳ የሚቀርብ ስላልሆነ ይህ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

12. እንደሚታወቀዉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 ዓ.ም አንቀጽ 80 (3) (ሀ) መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለባቸዉን ማናቸዉንም የመጨረሻ ዉሳኔ በሰበር የማየትና የማረም ስልጣን ይኖረዋል በማለት ደንግጓታል፡፡ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጣቸዉ አካላት ማቅረብና ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ሥር ተመልክቷል፡፡ ይህም ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጣቸዉ አካላት ቀርቦ ታይቶ የመጨረሻ ዉሳኔ የተሰጠባቸዉ ማናቸዉም ጉዳዮች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታረም እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ሥር እንደተመለከተዉ በዚህ ድንጋጌ በተመለከተዉ አግባብ የተሰጠዉን የመጨረሻ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ በሰበር የማየት ስልጣን እንዳለዉ ያሳያል፡፡

13. ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመደበኛ ፍ/ቤት፣ በሕግ ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸዉ አካል እና በሕግ አግባብ በተቋቋመ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ታይቶ የመጨረሻ ዉሳኔ የተሰጠባቸዉን ማናቸዉንም ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ እንደሆነ በሰበር አይቶ የማረም ስልጣን እንዳለዉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ችሎት የፍሬ ነገር ስህተት፣ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እና በዉሳኔዉ ላይ ምንም ተጽህኖ የሌለዉን ቀላል የሕግ ስህተት በሰበር የማየት ስልጣን እንደሌለዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

14. ይህ በእንዲህ እንዳለ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የሰጠዉን ዉሳኔ በፍርድ ቤት የማሳረሙ ጉዳይ ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ከአገሮች ልምድ አንጻር ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ፍርድ እንደተሰጠ ሶስት ዉጤቶችን ያስከትላል፡

1. ተሸናፊዉ ወገን በፈቃደኝነት እንደፍርዱ መፈጸም፡፡

2. አሸናፊዉ ወገን በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት የተሸናፊዉ ወገን ንብረት ባለበት አገር ፍርዱ እንዲጸድቅ፣ እዉቅና እንዲያገኝ ወይም እንዲፈጸምለት ይፈልጋል፡፡

3. በአለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ተሸናፊዉ ወገን ፍርዱ በተሰጠበት አገር ፍርዱ እንዲሰረዝ ማድረግ ናቸዉ፡፡

**15.** በዚህ መሰረት ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንጻር ሲታይ የኒዉዮርክ ስምምነት አንቀጽ 5 (New York Convention Art 5) መሰረት የግልግል ጉባኤ ብይን እዉቅና እና ተፈጻሚነት የሚነፈግበትን ሁኔታዎች ወይም ምክንያቶች ተዘርዝረዉ እናገኛለን፡፡ ኢትዮጵያ ይህን ስምምነት ያልፈረመች ብትሆንም ስምምነቱ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ የሰጠዉን ብይን እዉቅና ሊከለክል እና ለመፈጸም እምቢ የሚባልባቸዉን ምክንያቶች ያስቀምጣል፡፡

**16.** የዩኒስትራል ሞዴል ሕግም (UNCITRAL MODEL LAW) የግልግል ጉባኤ ብይን ወይም ዉሳኔ ሊሰረዝ የሚችልበትን ምክንያቶች ያመለክታል፡፡ ይህን ብይን ወይም ዉሳኔ ለማሰረዝ የሚቀርብ አቤቱታ መቅረብ የሚገባዉ የግልግል ዳኝነት መቀመጫ በሆነዉ ፍርድ ቤት እንደሆነ የዚህ አንቀጽ 34 ይደነግጋል፡፡ የግልግል ዳኝነት ሲታይ በነበረዉ ቦታ ያለዉ ፍርድ ቤት በሂደቱ ላይ የተቆጣጣሪነት ስልጣን ስለሚኖረዉ ሂደቱ ፍትሓዊ እና ከሙስና የጸዳ መሆኑን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህን ሕግ ተከትሎ አገሮች የየራሳቸዉ ሕጎች ያወጡ ሲሆን፣ የግልግል ብይን የሚታረምበት ዓይነት እና ደረጃ ከአገር አገር እንደሚለያይ መገንዘብ ያስፈልግል፡፡ በዚህ መሰረት የዩኒስትራል ሞዴል ሕግ አንቀጽ 34 የግልግል ብይን ዉድቅ የሚደረግበትን ምክንያቶች ያስቀምጣል፡፡

**17.** በአዉሮፓ ልማት ፈንድ ስነስርዓት ሕግ (EDF Rules) የአዉሮፓ የልማት ፈንድ የስነስርዓት ሕግ አንቀጽ 33 (1፣ 3) መሰረት የሽምግልና ዳኝነቱ በጽሑፍ የሚደረግ ሆኖ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የመጨረሻና ገዢ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ የዚህ ሕግ አንቀጽ 34 ማየቱም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ሳይዘገዩ ፍርዱን ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸዉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ እያንዳንዱ የኤሲፒ አገር ወይም አባል አገር አኢዴፍ የስነስርዓት ሕጎች መሰረት የተሰጠ ፍርድን እዉቅና ሰጥቶ ልክ በግዛቱ ዉስጥ የሚገኙ ፍ/ቤቶች ወይም ፍትህ አካላት እንደሰጡት ፍርድ በመቁጠር በግዛቱ ዉስጥ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ አለባቸዉ፡፡

18. የኒፎርም አርብትሬሽን አክት ክፍል 23 (Uniform Arbitration Act section 23) መሰረት የግልግል ብይን በማመልከት ለፍ/ቤት ብይኑን ለማሰረዝ የሚቻልባቸዉን ምክንያቶችን ያሳያል፡፡

19. የፓነማ ስምምነት (Inter-American Convention On International Commercial Arbitration (B-35) (Panama Convention) የሚባለዉ በአንቀጽ 5 እና 6 ሥር እንደተመለከተዉ የግልግል ብይን የታየበት ሕግ አገር፣ ይህን ብይን እዉቅና ለመንፈግና ተፈጻሚነቱን እምቢ ማለት የሚልባቸዉን ምክንያቶች አስቀምጧል፡፡

20. የአሜሪካ የፌዴራል የግልግል ሕግ (The Federal Arbitration Act (USA) ) የግልግል ዳኝነት ብይን የሚታረምበትን በጠባብ ምክንያቶች መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሕጉ ክፍል 10 (ሀ) ሥር የግልግል ብይን የሚሰረዝበትን ምክንያቶች ይዘረዝራል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ሥር የሕግ ስህተት አልተመለከተም፡፡ የአሜሪካ ፍ/ቤቶች እና ተከራካሪ ወገኖች በፌዴራል የግልግል ሕግ ከተመለከተዉ በላይ ሰፋ ያለ የግልግል ብይን የሚታረምበትን ምክንያቶች ያስቀምጣሉ፡፡ እንዲሁም የክልል ሕግ አዉጪዎች የግልግል ብይኑ ሥራ ነገር የሚታረምበትን ማሻሻያዎች እንዲካተቱ አድርጓል፡፡ ሕግ አዉጭዉ ፍ/ቤት በምን ምክንያቶች የግልግል ብይን መሰረዝ እንዳለበት መወሰን እንደሚገባዉ በዚህ ዘርፍ የዳበረው የህግ ልምድ ያስገነዝበናል፡፡(የሕግ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡)

የፌዴራል ፍ/ቤቶች የግልግል ዳኛ በሰጠዉ ብይን ግልጽ የሆነ ሕግ የመተዉ ሁኔታ የሚታይበት እንደሆነ (manifest disregard of the law) ብይኑን የሚሰርዙበትን ምክንያት አግባብ ተግባራዊ አድርጓል፡፡ የግልግል ዳኛዉ ሕግን በግልጽ ወደ ጎን ትቷል የሚባለዉ፡ ሀ) ጉዳዩ ግልጽ በሆነ አግባብነት ባለዉ የህግ መርህ የሚገዛ እንደሆነ እና ለ) የግልግል ዳኛዉ አስቦ/አዉቆ በጥንቃቄ ትኩረት ሳይሰጠዉ የቀረበ እንደሆነ ነዉ፡፡ የግልግል ብይን በሕግ ስህተት ምክንያት የሚታረምበት ምክንያት አንዱ ሕጋዊነት ሲሆን ብይኑ በሕግ ስህተት ምክንያት እንዲታረም በሕግ ስልጣን የተሰጠ ወይም አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም የተሰጠበት እንደሆነ ነዉ፡፡ የአሜሪካ የፌዴራል የግልግል ሕግ አንቀጽ 10 (ሀ) ሥር የተዘረዘሩት ምክንያቶች የሕግ ስህተት የሚያካትት አይደለም፡፡ የኒዉ ጀርሲ የግልግል ሕግ የግልግል ዳኛ ሕግን ተፈጻሚ በሚያደርግበት ጊዜ ጉልህ የሆነ ስህተት የፈጸመ እንደሆነ ፍርድ ቤት ይህን የግልግል ብይን እንደሚሰርዝ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት ፍ/ቤት የግልግል ብይን ግልጽ የሆነ የሕግ

www.abyssinialaw.com

ስህተት ያለበት እንደሆነ በጠባቡም ቢሆን ብይኑን ከማረም የሚከለክለዉ ሕግ እንደሌለ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

21. እ.ኤ.አ. 1996 የወጣዉ የእንግሊዝ የግልግል ሕግ አንቀጽ 69 (England Arbitration Act Of 1996) ተከራካሪ ወገኖች የሕግ ስህተት በማንሳት ለፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብ የግልግል ብይን እንዲታረም መጠየቅ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡

22. በሲዊዘርላንድ ኢንተርካንቶናል የግልግል ሕግ አንቀጽ 36 ደግሞ የግልግል ብይን የተሰጠዉ በተሳሳታ የፍሬ ነገር ድምዳሜ መሰረት በማድረግ የሆነ እንደሆነ ወይም ግልጽ የሆነ የሕግ ወይም ርትዕ ጥሰት የተፈጸመበት እንደሆነ ፍ/ቤት ብይኑን እንዲሰርዝ የሚፈቀድ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

23. ከኢትዮጵያ አንጻር ሲታይ ከክርክር አፈታት ዘዴዎች መካከል አንዱ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንደሆነ የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ የፍትሐ ብሔር ስነስርዓት ሕግ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዎችን ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 3325-3346 እንዲሁም የፍትሐ ብሔር ስነስርዓት ሕግ ቁጥር 315-319 እና አንቀጽ 350-357 ድንጋጌዎችን ያስገነዝባሉ፡፡ የግልግል ዳኝነት የሚታየዉ በኢትዮጵያ ሕግ እስከሆነ ድረስ እነዚህ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸዉ መሆኑ አከራካሪ አይሆንም፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕጉ መሰረታዊ መብት የሚደነግግ ሲሆን የፍትሐ ብሔር ስነስርዓት ሕጉ ደግሞ ይህን መሰረታዊ መብት ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል የስነስርዓት ደንቦችን የሚደነግግ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በሕግ አግባብ ተቋቁሞ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር ሰምተዉ አጣርተዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.318 ሥር በተመለከተዉ መሰረት ብይን ወይም ዉሳኔ መስጠት እንደሚችል ተደግጓል፡፡ ይህ ብይን ወይም ዉሳኔ ልክ በፍርድ ቤት እንደሚሰጥ ብይን ወይም ዉሳኔ ዓይነት መወሰን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በሰጠዉ ብይን ወይም ዉሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት ወይም እንዲሰረዝ አቤቱታ የሚቀርበዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.350-357 ሥር በተመለከተዉ አግባብ እንደሆነ የዚህ ሕግ አንቀጽ 319 (1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በኢትዮጵያ አገር እና በዚህ አገር ሕግ አግባብ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር አይቶ ዉሳኔ የሰጠ እንደሆነ፣ በዚህ ብይን ወይም ዉሳኔ ያልተስማማ ወይም ቅሬታ ያለዉ ወገን ይግባኝ የሚልበት ወይም

www.abyssinialaw.com

ዉሳኔ እንዲሰረዝለት የሚጠይቅበት ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን እና የግልግል ብይን ወይም ዉሳኔ ከሕግ የሚቃረን ወይም ኢ-ፍትሓዊ ቢሆንም እንኳን ዝም ተብሎ የሚፈጸም ነዉ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ከእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለዉ የግልግል ብይን ወይም ዉሳኔ በሕጉ በተመለከተዉ አግባብ እና ምክንያቶች በፍ/ቤት ታይቶ ሊታረም እንደሚችል ነዉ እንጂ በምንም መልኩ ሊታረም የማይችል የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች በናሽናል ሞተርስ ኮርፖሬሽን እና በተጠሪ ጄኔራል ቢዝነስ ዲቨሎፐመንት መካከል በነበረዉ ክርክር በሰ.መ.ቁ.21849 ላይ ህዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተዋዋይ ወገኖች (ተከራካሪ ወገኖች) በግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ታይቶ የተሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ በማለት የተስማሙ በመሆኑ፣ የግልግል ዉሳኔዉ እንደዉሉ በእራሱ የመጨረሻ ዉሳኔ በመሆኑ በሰበር ቀርቦ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት መወሰኑን ማየት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይሄው ችሎት በአመልካች ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የግ/ማህበር እና በተጠሪ ዳኒ ድሪሊንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በነበረዉ ክርክር በሰ.መ.ቁ.42239 ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተከራካሪ ወገኖቹ የግልግል ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ብለዉ ቢስማሙም፣ በግልግል ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ለዚህ ችሎት ቀርቦ የማይታይበት የህግ ምክንያት የለም በማለት በሰ.መ.ቁ.21849 የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመለወጥ ወስኗል፡፡

24. የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብይን ላይ ቅሬታ ያለዉ ተከራከሪ ወገን መቃወሚያዉን የሚያቀርብባቸዉ መንገዶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ.350-357 ሥር ተመልክቷል፡፡ እነዚህም፡

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.351 ሥር በተዘረዘሩት የይግባኝ ምክንያቶች ለመደበኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፣ ነገር ግን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.350 (2) መሰረት ማንኛዉም ተከራካሪ ወገን አዉቆ፣ ገብቶት ወይም ተረድቶ ይህን የይግባኝ መብቱን መተዉ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.355 መሰረት የግልግል ብይን እንዲሻርልኝ በማለት ለፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ ይህ ድንጋጌ ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.356 ሥር የተዘዘሩትን ምክንያቶች የያዘ መሆን እንዳለበት

www.abyssinialaw.com

ያመለክታል። ፍ/ቤቱም በድንጋጌው ስር የተዘረዘሩት ሁኔታዎች መከሰታቸዉን ያረጋገጠ እንደሆነ የግልግል ብይኑን መሰረዝ እንደሚችል ያሳያል።

3. ተከራከሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ ብሎ ቢስማሙም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ከማሳረም እንደማያግዳቸዉ ይህ ችሎት በበርካታ መዛግብት የሰጣቸዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያስገነዝባል።

ከእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ ከግልግል ብይን ላይ ይግባኝ የሚባልበት እና ብይኑ እንዲሻር ወይም እንዲሰረዝ በመጠየቅ መካከል ልዩነት መኖሩን ነዉ። ፍ/ቤት የግልግል ብይን የሚሰረዝበት ወይም የሚያነሳበት አግባብ የሥነሥርዓት እና የስልጣን ትክክለኛነት የሚቆጣጠርበት መንገድ ነዉ። የግልግል ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.356 መሰረት ለመሻር ወይም ለማንሳት ምክንያት የሆኑት ሁኔታዎች ለይግባኝ ምክንያቶች ሊሆኑ እንደማይችሉ መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ።የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የግልግል ብይን ያጸናል ወይም በሶስት ወር ጊዜ ዉስጥ ድጋሚ አይቶ እንዲወስን ለግልግል ዳኝነት ጉባኤ ይመልሳል።

25. ከዚህም በላይ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ለችሎቱ በተሰጠዉ የስልጣን ወሰን ዉስጥ እስከሆነ ድረስ ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጣቸዉ አካላት በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸዉ እንደሆነ ቅሬታቸዉን የሚያሰሙበት መድረክ ነዉ። በዚህ ረገድ በአመልካች ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የግ/ማህበር እና በተጠሪ ዳኒ ድሪሊንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ታይቶ የተሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከግራ ቀኛቸዉ የቀረበዉን ክርክር መሰረት በማድረግ በሰ.መ.ቁ.42239 ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የግልግል ብይን በተመለከተ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ተመሳሳይ የሕግ አፈጻጸም እና ትርጉም እንዲኖር ከማድረግ አንጻር ቅሬታዉ ለዚህ ችሎት መቅረብ የለበትም አይባልም። ይህ ደግሞ ለዚህ ችሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት እና በአዋጅ ቁጥር 454/1997 ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር ማየት ያስፈልጋል። የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በሰጠዉ ዉሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.351 እና 356 ሥር በተመለከቱት ምክንያቶች ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ

ለዚህ ችሎት ቀርቦ የማይታይበት እና የማይታረምበት የሕግ አግባብ የለም፣ ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለዉ በማለት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ደግሞ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (4) መሰረት ሕግ በመሆኑ አስገዳጅነት ያለዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ ብሎ ቢስማሙም፣ ከዉሳኔዉ ቅሬታ ያለዉ ተከራካሪ ወገን ጉዳዩን ለሰበር ከማቅረብ የሚያግደዉ እንዳልሆነ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ከማረም የሚከለክለዉ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

26. እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለዉጭ አገር የግልግል ብይን እዉቅና ለመስጠት እና ተፈጻሚ ለማድረግ የሚቀርበዉን አቤቱታ ለመመርመር ስልጣን እንዳለዉ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11 (2፣ ሐ) ሥር ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.461 ለብይኑ እዉቅና ላለመስጠት እና ተፈጻሚ ላለማድረግ ሥር ስድስት ምክንያቶች መዘርዘሩን ማየት ይቻላል፡፡

27. በመሆኑም ከፍ ሲል በዝርዝር እንደተመለከተነዉ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብይን ወይም ዉሳኔ በሕጉ በተመለከቱት ጠባብ ምክንያቶችም ቢሆንም በፍርድ ቤት ቀርቦ ከመታረም የሚድን እንዳልሆነ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ የአገሮች ልምድ እና የኢትዮጵያ ሕግ የሚያስገነዝበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ አገሮች የየራሳቸዉን ነበራዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የግልግል ብይን ግልጽ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ወይም ጉልህ የሆነ የፍትሕ መጓደል ያስከተለ እንደሆነ እንዲሁም ከሕዝብ ጥቅም (public policy) አንጻር በማየት፣ በየፍርድ ቤቶቻቸዉ ይህን ብይን የሚያሳርሙበት ስርዓት መዘርጋታቸዉን ማየት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ብይን የመጨረሻ ነዉ ብሎ ቢስማሙም እንኳን ፣ፍትሕ የማግኘት መብት እና ፍትሓዊነትን የማስፈን ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ ለተከራካሪ ወገኖች ነጻ ፈቃድ የሚተዉ ባለመሆኑ፣ ብይኑ በፍጹም ለፍ/ቤት ቀርቦ ሊታረም አይችልም ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ ስለሆነም የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብይን ወይም ዉሳኔ በሕጉ በተመለከቱት ምክንያቶች ብቻ ለፍ/ቤት አቅርቦ እንዲታይ እና እንዲታረም ማድረግ እንደሚቻል ነዉ፡፡ ነገር ግን በፍ/ቤት የግልግል ብይን የማሳረም ወይም የማስረዙ ጉዳይ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤን የሚያቋቁሙበት ዓላማ ሙሉ ለሙሉ ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ

www.abyssinialaw.com

መሆን እንደሌለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸዉ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንዲታይላቸዉ ከሚፈልጉባቸዉ ምክንያቶች መካከል የተሰወኑትን ለመጥቀስ በመረጡት ገላጋይ ዳኞች ለመዳኘት ካላቸዉ ፍላጎት፣ የተከራካሪ ወገኖች ነጻነት፣ ጊዜያቸዉን ለመቆጠብ እና ወጪን ለመነቀስ የሚሉት ናቸዉ። ከዚህም በላይ የግልግል ብይን በፍ/ቤት ሊታረም ይገባል ሲባል በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለዉን የንግዱን ማህበረሰብ ዝንባሌ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢንቨስትመንት ከመሳብ አንጻር ያለዉን ተጽኖ ከግምት ያስገባ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነዉ። የግልግል ዳኝነት ጉባኤ በፍ/ቤት ከመታየት የማይድን ቢሆንም እነዚህን ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ በሕጉ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በጠባቡ መሆን እንዳለበት መረዳት ያስፈልጋል።

ሲጠቃለል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ መቀመጫ አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ እስከሆነ ድረስ እና ጉዳዩም ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት በመሆኑ፣ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና የአገሮች ልምድ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕጎች እና ይህ ችሎት በበርካታ መዛግብት ከሰጣቸዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር፣ ተከራካሪ ወገኖቹ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ ብሎ ቢስማሙም ዉሳኔዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ በሰበር ከማየት የሚከለክለዉ የሕግ መሰረት የለም። በመሆኑም ተጠሪ ይህ ችሎት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም ብለናል።

28. ሁለተኛዉን ጭብጥ በተመለከተ ግራ ቀኛቸዉ መካከል የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? ዉጤቱስ ምን ይሆናል? የሚለዉ ነጥብ እንደሚከተለዉ የሚታይ ይሆናል።

29. በአዉሮፓ ልማት ፈንድ ስነስርዓት (EDF Rules) አንቀጽ 14.1 መሰረት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የኢትዮጵያ ሕግን ተግባራዊ ማድረግ እና የኢትዮጵያ ሕግ እስከፈቀደ ድረስ የንግድ ልማድ ከግምት ዉስጥ መግባት እንደሚገባ ተመልክቷል። ስለሆነም ለተያዘዉ ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት በዚህ ጉዳይ የኢትዮጵያ የዉል ሕግን መፈተሽ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

30. እንደሚታወቀዉ በሕግ ፊት የሚጸና ዉል አለ ለማለት ማሟላት ካለባቸዉ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ተዋዋይ ወገኖች ጉደለት የሌለበትን ስምምነት ማድረግ

ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 /ሀ/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች የሚገቧቸዉን ግዴታዎች ፈቅደዉ እና አዉቀዉ መሆን እንዳለበትም የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1679 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ዉሎች ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ሕግ እንደሚሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 /1/ ድንጋጌ የሚያስገነዝበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ዉልን ሲዋዋሉ የፈቃድ ጉድለት መኖር እንደሌለበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1696 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ በዚህ መሰረት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1696 ሥር እንደተመለከተዉ ዉል የሚያፈርሰዉ ከተዋዋዮቹ ወገኖች የአንደኛዉ መፍቀድ በስህተት፣ በድንገተኛ ተንኮል ወይም በኃይል የተገኘ ሲሆን ነዉ በማለት ይደነግጋል፡፡

31. ዉል ሲደረግ የተዋዋይ ወገን የፈቃድ ጉድለት ከሚያስከትሉት ምክንያቶች መካከል የተንኮል ተግባር አንዱ ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704 (1) መሰረት በተንኮል የተደረገ ዉል ፈራሽ የሚሆነዉ ከተዋዋዮቹ አንደኛዉ ወገን ዉሉ እንዲደረግ ያደረገዉ በሁለተኛዉ ተዋዋይ ላይ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ ዉል የማያደርግ እንደነበረ ሲገለጽ ነዉ በማለት ይደነግጋል፡፡

32. በዚህ መሰረት አሁን ወደ የተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በግራ ቀኛቸዉ መካከል የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ተጠሪ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር የተደረገ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ በቅድሚያ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ይህን የባቡር መንገድ ጥገና ሥራ ለመሥራት ጨረታዉን ተወዳድረዉ ያሸፉት የእሽሙር ማህበር የተቋቋመዉ በኮንስታ ኮንሶርዞ እና ጂሲኤፍ (GCF) ሆነዉ የኮንስታ ጄቪ (consta JV) በሚል የእሽሙር ማህበር ነዉ፡፡ በዚህ የእሽሙር ማህበር ኮንሶርዚዮ ኮንስታ 70% የአክስዮን ድርሻ እና ጂሲኤፍ ደግሞ 30% የአክስዮን ደርሻ መያዛቸዉ ተገልጾ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህን ጨረታ ተክትሎ ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ህዳር 29 ቀን 2006) በተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ በአጠቃላይ በብር 40,433,056.70 ዩሮ ተስማምቷል፡፡ በዚህ የዉል ስምምነቱ የሚሰሩ በርካታ ሥራዎች ተዘርዝሮ እናገኛለን፡፡

33. ይህ በእንዲህ እንዳለ ኮንሰታ እና ጂሲኤፍ መካከል ይህን ቅንጅት በተመለከተ ሶስት ምስጥራዊ ስምምነቶች መደረጋቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ሐምሌ 27 ቀን 1998 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ኦገስት 3 ቀን 2006) በተፈረመዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 1 መሰረት የጂሲኤፍን የአክስዮን ድርሻ ወደ 0.1% ዝቅ ለማድረግ ተስማምቷል፣

ህዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 24 ቀን 2006) በተደረገዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 2 የጂሲኤፍ የአክስዮን ድርሻ ወደ 0.2% ዝቅ እንዲል አድርጓል፤ መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ማርች 20 ቀን 2007) በተፈረመዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 3 መሰረት ጂሲኤፍ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ዩሮ ክፍያን በመቀበል ተሳትፎዉን እስካሁን ድረስ በተፈጸመዉ ብቻ እንዲገደብ ማድረጉ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ። የአሁን ተጠሪም ቢሆንም እነዚህ ስምምነቶች መደረጋቸዉን የካደ ነገር የለዉም። ከዚህም በላይ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በሰጠዉ ዉሳኔ እነዚህ ምስጥራዊ ስምምነቶች መደረጋቸዉን በዉሳኔዉ አረጋግጧል። በዚህ ረገድ የአዉሮፓ አንቲ-ፍራዉድ ቢሮ (OLAF) ባዘጋጀዉ የመጨረሻ ሪፖርት ይህ ዉል ከመፈረሙ አምስት ቀን ቀደም ብሎ ጂሲኤፍ በኮንስታ ጂቪ ያለዉን ተሳትፎ ከ30% ወደ 0.2% ዝቅ ማድረጉን እና በዚህም ተጠሪዉ የጠቅላላ ዉል ክፍል አንቀጽ 12.7 መጣሱን አረጋግጧል። የአሁን ተጠሪ እነዚህን ስምምነቶች ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ ቢኖርበትም የአዉሮፓ አንቲ-ፍራዉድ ቢሮ (OLAF) ባደረገዉ ምርመራ ባይደርስበት እና ይፋ ባያደርጋቸዉ ኖሮ ተደብቀዉ እንደሚቀሩ ተረጋግጧል።

34. እንግዲህ የአሁን ተጠሪ ለባቡር መስመር ሥራዉ አመልካች ያወጣዉን ጨረታ ተወዳድሮ እና ጨረታዉን አሸንፎ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ያደረገዉ በኮንሶርዚዮ ኮንስታ 70% የአክስዮን ድርሻ እና ጂሲኤፍ 30% የአክስዮን ደርሻ ባላቸዉ አባላት የተዋቀረ የእሽሙር ማህበር መሆኑን ለአመልካች በመግልጽ እንደሆነ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ የእሽሙር ማህበሩ ዉስጥ የጂሲኤፍ የአክስዮን ድርሻ እና ተሳትፎ 30% ሳይሆን 0.2% መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም የአሁን ተጠሪ አመልካች ባወጣዉ ጨረታ ሲሳተፍ እና ዉል ሲያደርግ የእሽሙር ማህበሩ አባላት የሌላቸዉን የአክስዮን ድርሻ እና የተሳትፎ መጠን እንዳላቸዉ ለአመልካች በመግለጽ ያደረገ መሆኑን ያስገነዝባል። የአሁን ተጠሪ ጨረታዉን ሲወዳደር እና ዉል ሲያደርግ ለአመልካች ትክክል ያልሆነ ወይም ሐሰተኛ ገለጻ ወይም መግለጫ መስጠቱን ያመለክታል። ይህ ደግሞ አመልካች ስለተጠሪ የእሽሙር ማህበር አደረጃጀት እና አወቃቀር ትክክል ያልሆነ ግንዛቤ እንዲወስድ እና የተሻለ ተወዳዳሪ አድርጎ በመዉሰድ ጨረታዉን እንዳሸነፈ በመቁጠር ዉል አብሮ እንዲያደርግ ያደረገዉ መሆኑን ያሳያል። አመልካች ስለእሽሙር ማህበሩ ያልሆነ አቋም እንዲይዝ በማድረግ፣ ተጠሪዉ ለሥራዉ

www.abyssinialaw.com

ብቃት እንዳለዉ በመቁጠር ጨረታዉን አሸንፎ ዉል እንዲያደርግ ያደረገዉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የአሁን ተጠሪ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር አመልካች የባቡር መስመር ሥራ ዉል ከተጠሪ ጋር እንዲያደርግ ያደረገዉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፈጸመዉ የተንኮል ወይም የማጭበርበር ተግባር አመልካች ከተጠሪ ጋር ይህን ዉል ሊያደርግ የቻለ በመሆኑ፣ በአመልካች በኩል ዉሉን ሲያደርግ የፈቃድ ጉድለት መኖሩን የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአሁን ተጠሪ ተግባር የተንኮል ወይም የማጭበርበር ተግባር አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ እና የአሁን ተጠሪ የተንኮል ተግባር የለም በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

35. ሌላዉ መታየት ያለበት ጉዳይ የአሁን ተጠሪ የእሽሙር ማህበሩ ዉስጥ የጂሲኤፍ አክስዮን ድርሻ እና የሥራ ተሳትፎ 0.2% ሆኖ እያለ 30% እንደሆነ የሚገልጽ ሐሰተኛ መግለጫና ማስረጃ በማቅረብ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር አመልካች ወደ ዉሉ እንዲገባ ያደረገዉ ለዉሉ መሰረታዊ የሆነ ነገር (essential or material) ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.7 እና 64.2 (h) ድንጋጌዎች መታየት እንዳለባቸዉ ተገንዝበናል፡፡ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.7 እንደሚያመለክተዉ የሥራ ተቋራጩ የእሽሙር ማህበር ወይም ከሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች ማህበር እንደሆነ፣ እነዚህ ሰዎች ሁሉም በተዋዋይ ባለስልጣን አገር ሕግ መሰረት በዉሉ መሰረት ለመፈጸም የአንድነትና የነጠላ ግዴታ አለባቸዉ እና በተዋዋይ ባለስልጣን ጥያቄ ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዱን እንደማህበሩ መሪ ሆኖ ከባለስልጣኑ ጋር በመስራት የእሽሙር ማህበሩን ወይም ማህበሩን ለማስገደድ ነዉ፡፡ የእሽሙር ማህበሩ ወይም የማህበሩ አወቃቀር ወይም አደረጃጀት ያለ ተዋዋይ ባለስልጣኑ ቅድሚያ ፈቃድ ሊለወጥ አይችልም፡፡ ይህ ድንጋጌ እንደሚያስገነዝበዉ የእሽሙር ማህበር አባላት በማህበሩ ባላቸዉ የአክስዮን ድርሻ መጠን በዉሉ የሚመለከታቸዉን ግዴታዎቻቸዉን መወጣት እንዳለባቸዉ ነዉ፡፡ ከእነዚህ አባላት መካከል አንዱ የሌለዉን ወገን ግዴታ ሸፍኖ ሊወጣ እንደሚችል የሚያመለክት ነገር የለዉም፡፡ የማህበሩ አባላት ድርሻቸዉን እና ተሳትፎአቸዉን ለመቀየር ከፈለጉ መጀመሪያ የአመልካች ፈቃድ ማግኘት እንደሚገባቸዉ ያስገድዳል፡፡ ይህ ማለት የዚህ የእሽሙር ማህበር አባላት የአክስዮን ድርሻ ወይም የስራ ተሳትፎ መጠን ካለ አመልካች

www.abyssinialaw.com

እዉቅና ሊለወጥ እንደማይችል ያመለክታል፡፡ ይህ የሚያመለክተዉ የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር ዉል ሲያድርግ የእሽሙር ማህበር አባላት አደረጃጀታቸዉን እና አወቃቀራቸዉን ኮንስታ 70% የአክስዮን ድርሻ እና ጂሲኤፍ 30% የአክስዮን ድርሻ ጠብቀዉ እያንዳንዳቸዉ በዉሉ የገቡትን ግዴታ እንደሚፈጽሙ በማመን መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ጨረታዉን ሲወዳደር እና አሸንፎም ዉል ከአመልካች ጋር ሲያደርግ በዚህ የድርሻ መጠን እና በዚህ መሰረት በዉሉ የተመለከተዉን ግዴታዎቻቸዉን በሥራዉ ቦታ በመገኘት ለመወጣት እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ አመልካች የዚህ ማህበር አባላት ድርሻ ጨረታዉን ሲወዳደሩና ዉል ሲያደርጉ የተገለጸዉን አለመሆኑን ቢያዉቅ ይህ ዉል ያደርጋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በዚህ ረገድ የአዉሮፓ አንቲ-ፍራዉድ ቢሮ (OLAF) ባዘጋጀዉ የመጨረሻ ሪፖርት በዉሉ የተመለከተዉን ሥራ ለመስራት ኮንስታ ብቻዉን የቴክኒካል ችሎታ ወይም ብቃት ስለሌለዉ ዉሉ እንደማይሰጠዉ እና በፐርሰንት የተመለከተዉ የተሳትፎ መጠን እያንዳንዱ አባል የሚፈጽመዉን ሥራ ድርሻ መሆኑን እና የኮንስታ አባላት የጠቅላላ የዉል ክፍል አንቀጽ 12.7 መጣሳቸዉን አረጋግጧል፡፡ ከዚህም በላይ የጂሲኤፍ ሥራ አስኪያጅ የሆነዉ ሚ/ር ሮሲ የተባለዉ የተጠሪ ምስክር በሰጠዉ የምስክርነት ቃል የጂሲኤፍ ድርሻ ወደ 0.2% መቀነሱን የአሁን አመልካች እና የአዉሮፓ ህብረት ቢያዉቁ ኖሮ ዉሉ ለተጠሪ እንደማይሰጥ መመስከሩን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪ ሆነ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ይህ ድርጊት ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.7 እንደሚጥስ መሆኑን ቢያምኑም የተንኮል ወይም የማጭበርበር ተግባር እንዳልሆነ መግለጻቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡

36. ከዚህ አንጻር ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 64.2 (h) እንደሚደነግገዉ በሌላ አኳን እስካልተጠቀሰ ድረስ ተዋዋይ ባለስልጣን ለሥራ ተቋራጩ የሰባት ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ዉሉን በማቋረጥ እና የስራ ተቋራጩን ከሥራ ቦታ ከሚያባርርባቸዉ ምክንያቶች አንዱ የዉሉ አካል ሆኖ የተመዘገበ ካልሆነ በቀር የስራ ተቋራጩን ሕጋዊ ሰዉነት፣ ተፈጥሮ እና የቁጥጥር ለዉጥ የሚያስከትል ማንኛዉም የማህበሩ አደረጃጀት ወይም መዋቅር ለዉጥ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.7 እና አንቀጽ 64.2 (h) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እንደሚያስገዝበዉ የተጠሪ የእሽሙር ማህበር ዉስጥ የአባላቱ ድርሻ ለዚህ ዉል መደረግ

መሰረታዊ የሆነ ነገር (essential or material) መሆኑን ያስገነዝባል። ስለሆነም የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ጂሲኤፍ በማህበሩ ዉስጥ የነበረዉ ድርሻ መቀነሱ እና የዉሉ አንቀጽ 12.7 የሚጥስ ቢሆንም ለዉሉ መሰረታዊ የሆነ ነገር አይደለም፣ ኮንስታ ብቻዉን ይህን ሥራ ለመስራት ሙሉ አቅም አለዉ በማለት ያቀረበዉ ክርክር እና የግልግል ጉባኤዉ በሰጠዉ ዉሳኔ ይህ ድርጊት የሚያደርሰዉ ጉዳት የለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎችን ድንጋጌዎች የሚጥስ ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል።

**37.** የአሁን ተጠሪ የእሽሙር ማህበሩ ዉስጥ ጂሲኤፍ የነበረዉን ድርሻ በተንኮል ከአመልካች በመደበቅ ዉል ያደረገ በመሆኑ፣ ይህ ደግሞ ለዉሉ መሰረታዊ የሆነ ነገር በመሆኑ፣ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ። የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704 (1) ሥር የተመለከተዉ የተንኮል ተግባር በዉሉ ላይ ተጽኖ የማይፈጥር ተራ ወይም ቀላል ነገር ሳይሆን መሰረታዊ የሆነ ነገር መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። የአሁን ተጠሪ የእሽሙር ማህበሩ ዉስጥ የጂሲኤፍ የሌለዉን ድርሻ እንዳለዉ በመግለጽ አመልካች በማያዉቀው ሁኔታ ወደ ዉሉ እንዲገባ ባያደርገዉ ኖሩ ዉሉን የማያደርግ መሆኑን ያመለክታል። ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን ተጠሪ የፈጸመዉ የተንኮል ተግባር በግራ ቀኛቸዉ መካከል በተንኮል የተደረገዉን ዉል ለማስፈረስ በቂ ምክንያት ይሆናል። አመልካች በዚህ ምክንያት ዉሉ እንዲፈርስለት ለመጠየቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1808 (1) ሥር ተመልክቷል። ፍ/ቤትም በሕጉ አግባብ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ከመስጠት የሚከለክለዉ ነገር እንደሌለ መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር አመልካች የባቡር መስመር ሥራ ዉል እንዲያደርግ ያደረገዉ በመሆኑ፣ ይህ ዉል ፈራሽ ነዉ፣ በግራ ቀኛቸዉ መካከል ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ህዳር 29 ቀን 2006) የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ሊፈርስ ይገባል ብለናል።

**38.** ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠሪ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ከተደረገ በኋላ መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ማርች 20 ቀን 2007) በተፈረመዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 3 መሰረት ጂሲኤፍ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ዩሮ ክፍያን በመቀበል ተሳትፎዉን እስካሁን ድረስ በተፈጸመዉ ብቻ እንዲገደብ ማድረጉን የቀረበዉ ማስረጃ የሚያረጋግጥ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። በዚህ ረገድ የአሁን ተጠሪ

www.abyssinialaw.com

ባቀረበዉ ክርክር ጂሲኤፍ አምስት አመት በኢትዮጵያ በስራ ቦታ እንደሌለ እያወቀ ሥራዉ እንዲቀጥል አድርጓል በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ረገድ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ጂሲኤፍ በሥራ ቦታ መገኘት አለመገኘቱን ለአመልካች ማሳወቅ የሚገባዉ ተጠሪ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ ይህ የሚስጥር ስምምነት መደረጉን እና ጂሲኤፍ በሥራዉ ቦታ ያልነበረ መሆኑን ከአመልካች ሸሽጎ እንደቆየ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ የሚያሳያዉ ተጠሪ ዉሉ ከተደረገ በኋላም የተንኮል ተግባሩን የገፋበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ጉዳይ ነዉ፡፡

39. እንደሚታወቀዉ አንድ ዉል በፍ/ቤት ዉሳኔ የፈረሰ እንደሆነ የዉሉ መፍረስ የሚያስከትለዉ ዉጤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1815 መሰረት መወሰን እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ነገር ግን አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ በግራ ቀኛቸዉ መካከል የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል እንዲፈርስ እስከተወሰነ ድረስ ዉጤቱ ምን ይሆናል? የሚለዉ ነጥብ ሲታይ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ከዚህ አንጻር ጭብጥ በመያዝ የዉሉ መፍረስ የሚያስከትለዉን ዉጤት አጣርቶ ዉሳኔ ያልሰጠበት በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ ይህ ችሎት የዉሉ መፍረስ የሚያስከትለዉ ዉጤት በተመለከተ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉ ነገር ካለመኖሩም በላይ በዚህ አግባብ ተጣርቶ የቀረበ ግልጽ የሆነ ነገር ስለሌለ ጉባኤዉ ድጋሚ አይቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት መመለስም የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የዚህ ዉል መፍረስ የሚያስከትለዉን ዉጤት በተመለከተ መብት አለኝ የሚል ወገን ካለ በሕጉ አግባብ ከሚጠይቅ በስተቀር በዚህ መዝገብ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ አልተገኘም ብለናል፡፡

40. ሲጠቃለል የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ከፍ ሲል በተመለከተዉ ምክንያት በግራ ቀኛቸዉ መካከል የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ፈራሽ ማድረግ ሲገባዉ ይህ ዉል ሊፈርስ አይገባም በማለት አመልካች በዉሳኔዉ የተጠቀሰዉን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍለዉ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ኔዘርላንድ (ሄግ) የሚገኘዉ ቋሚ የግልግል ዳኝነት ፍ/ቤት የሚያስተዳደረዉ መቀመጫዉ አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ የሆነዉ በመ.ቁ.2013-32 ላይ ሚያዚያ 28 ቀን 2008 ዓ.ም

www.abyssinialaw.com

(እ.ኤ.አ. ግንቦት 6 ቀን 2016) የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በግራ ቀኛቸዉ መካከል ህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም (November 29, 2006) የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር የተደረገ ስለሆነ ዉሉ ፈራሽ ነዉ ብለናል፡፡
3. የዉል መፍረስ የሚያስከትለዉን ዉጤት በተመለከተ መብት አለኝ የሚለዉ ወገን በሕግ አግባብ መብቱን ከመጠየቅ ይህ ዉሳኔ አያግደዉም ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. በ22/9/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

# ከውል ውጭ ኃላፊነት

www.abyssinialaw.com

የሰበር መ/ቁ. 152417

ግንቦት 17 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ሚሚ አበበ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ታምራት /ማሙሽ/ ባልቻ - ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ ጉዳይ ክርክሩ በተጀመረበት በምንጃር ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች ሲሆኑ ተከሳሽ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ነበሩ፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በቆንጨራ የቀኝ እጃቸውንና የቀኝ ጭንቅላቸውን በመምታት የቀኝ እጃቸው መዳፍ ማጠፊያ አንጓ እንዲቆረጥ በማድረጋቸው በከባድ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል ተከሰው በፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን፣ በዚህ የወንጀል ድርጊት በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ምክንያትም ስራ ሰርተው ያገኙት የነበረው ገቢ የቀረባቸውና ስራ ስርተው መኖርም ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሰው ብር 300,000.00(ሶስት መቶ ሺህ ብር) ካሳ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪም በሕጉ አግባብ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም ተገቢ ናቸው ያላቸው የአመልካች እድሜና የገቢ መጠን በማስረጃ እንዲጣሩ ለማድረግ ማስረጃዎቹ ከሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡ

www.abyssinialaw.com

በማለት ትዕዛዝ ሲስጥ ቆይቶ የአመልካች ጠበቃ ተገቢውን ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው በዚህ ረገድ ማስረጃዎችን ያልሰማ ሲሆን በኃላፊነት ረገድ ግን በተጠሪው ላይ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረት አድርጎ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ ያደረገ ሲሆን ካሳውን በተመለከተ የአመልካች ጠበቃ በርትዕ እንዲወሰን ያቀረቡትን ጥያቄ ካሳ በርትዕ የሚወሰነው በልዩ ሁኔታ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለውና አመልካችም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 አግባብ የካሳ መጠኑን ለማስረዳት ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሶ ለአካል ጉዳት የተጠየቀውን ካሳ በማለፍ የሞራል ጉዳት ካሳ ብቻ ብር 1000.00(አንድ ሺህ ብር) አመልካች እንዲከፈላቸው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበውም  ተጠሪ በህጉ አግባብ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ ተጠሪ በሌሉበት እንዲታይ ከተደረገ በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የጉዳት ካሳ መጠኑ በርትእ ሊወሰን የሚችል አይደለም በማለት የደረሰበትን ድምዳሜ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ የአካል ጉዳት ካሳውን በርትእ አስልቶ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር) በማድረግ ወስኖአል፡፡ ከዚህም በኂላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡  አመልካች የአሁኑን የሰበር አቤቱታውን ያቀረቡትም በአካል ጉዳት ካሳ መጠን አወሳሰን ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል በማለት ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም የካሳ መጠኑ አወሳሰኑን  ተገቢነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸውም ባለመቅረባቸው መልስ በጽሑፍ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ለክርክሩ በተያዘው ጭብጥ መሰረት ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 14 ሥር “ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር፣የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው” ተብሎ የተቀመጠ ሲሆን አንቀጽ 16 የአካል ደህንነት መብት ምን እንደሆነ ያብራራል፡፡ ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት እንዳለው የሃገሪቱ የበላይ ሕግ ያስገነዝባል፡፡ መንግስትም ሆነ ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው የአካል

ደህንነት የመጠበቅ የሕግ ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ህግ በመተላለፍ በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለደረሰው የአካል ጉዳት ተጉጂው ካሳ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ በህገ-መንግስቱ የተቀመጠው ይህን የሰብአዊ መብት ከሚያረጋግጡ ዝርዝር ሕጐች ውስጥ በፍ/ሕጉ ውስጥ የጉዳት ካሳን አስመልከቶ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ይገኙበቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰው በጥፋቱ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረሰው ጉዳት ኃላፊ ሆኖ ካሳ ሊከፍል እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ. 2028 አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም በመርህ ደረጃ የጉዳት ካሳ ሊከፍል የሚገደደው በጥፋቱ ጉዳት ያደረሰ ሰው ሲሆን በአንዳንድ የተለያዩ ጉዳዮች ደግሞ አንድ ሰው ጥፋት ሳይኖርበትም ኃላፊ እንደሚሆን ከፍ/ሕ/ቁ. 2066 እና ተከታዮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ በራሳቸው አድራጎት በአመልካች አካል ላይ ለአደረሱት ጉዳት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በራሱ ጥፋት በሰው አካል ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊ የሆነ ሰው ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ግዴታ በፍትሐብሔር ሕጉ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ሊታይ የሚገባው የካሳው መጠን ነው፡፡ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነ ሰው የሚከፍለው የካሳ መጠን ከጉዳቱ ጋር ተመዛዛኝ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ሕ/ን/ቁ. 2090 እና 2091 ስር ተመልክቷል፡፡ ወደፊት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ጉዳት የተረጋገጠ ከሆነ እስኪፈፀም መጠበቅ ሳያስፈልግ ካሳው ሊከፈል እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ. 2092 ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን አለበት ሲባል መታየት ያለበት በአጠቃላይ በተጉጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመስራት ኃይል ቅነሳ አንፃር እንጂ ከጉዳቱ በፊት ሲሰራው የነበረውን ስራ ላለመስራት ጉዳቱ ያስከተለው ልዩ ጫናና የቅነሳ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት አለመሆኑን ለዚህም ምክንያት የሚሆነው እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ስራ ለመስራት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አንድ ሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ እንደሆነ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 19338 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣ መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 ፣ 2091 ፣ 2092 ፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው

www.abyssinialaw.com

በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበትና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 ድንጋጌ አግባብም ጉዳት የደረሰበት ሰው የጉዳት ካሳ መጠኑን በትክክል ማስረዳት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በአደጋ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ሰው ለደረሰበት ጉዳት ሊከፈል የሚገባው የካሣ መጠን በትክክል ለመወሰን የሚያስችል ማስረጃ ያልቀረበ ወይም የካሣውን መጠን በማስረጃ አጣርቶ ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ዳኞች ካሣውን በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2102 መሠረት በርትዕ ሊወስኑ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው የርትእ መርህ ፍትሕን ለማስፈን ዳኞች በሕግ ከተደነገገው በመውጣት ወይም ሕጉ ራሱ በአንዳንድ ተለይተው በተገለጹ ጉዳዮች ላይ ርትዕን እንዲከተሉ ሲፈቅድ ከሕግ ይልቅ ህሊናቸው ትክክል ነው የሚለውን እንዲመርጡ እንዲወስኑ የሚፈቅድ ነው፡፡ ስለሆነም ርትዕ የሚያመለክተው የተፈጥሯዊ ሕግጋትን በመጠቀም ፍትሕን መስጠት ሲሆን መሰረታዊ አላማውም በሕግ ያለውን ክፍተትን መሙላት ወይም የሕግን ጥብቅ ደንብ ፍትሐዊ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ርትእ አይነተኛ አላማውና ግቡ ሕግ ትክክለኛ ፍትሕ ላያስገኝ ስለሚችል አከራካሪ ለሆነው ጉዳይ እንደማስረጃዎቹና አከባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታዎች በሕግ ድንጋጌ ስር መታጠር ሳያስፈልግ ፍትሕ ለማስገኘት ነው ተብሎ ይታሳበል፡፡ ስለሆነም አስቀድሞ እርግጠኛ በመሆን ደንብ ማስቀመጥ በማይቻልበት ሁኔታ፣ግልጽና ቁልጭ ያለ መፍትሔ ለመስጠት የሚቻልበት አጋጣሚ ሲኖር፣ጉዳት አድራሹ ድርጊቱን የፈጸመበት ምክንያት ከቁጥጥሩ ውጭ በሆነ ጊዜ ባደረሰው ጉዳት መጠን ካሳ መክፈል ከህሊና ግምት ውጭ በሚሆንበትና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች ሲያጋጥሙ ርትዕ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ረገድ በሕግ የማይተካ ሚና ያለው መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ካሳ በርትእ ሲወሰን በዘፈቀደ ሊሆን የማይገባው ሲሆን በርትዕ የተሰጠ ውሳኔም በበላይ ፍርድ ቤት ሊሻር የሚገባው ይህንኑ የርትእ መሰረታዊ አላማ እግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጸዋል፡፡ ስለሆነም የጉዳት ካሣ መጠን በዝቷል ወይም ያንሣል በሚል ቅሬታ ማቅረብ የሚቻለው በፍትሃ ብሔር ሕግ ቁጥር 2153 ስር የተመለከቱት የተለዩ ሁኔታዎች ማለትም የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያለአግባብ በመያዝ

ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ፣ ያለአግባብ የሆነውን የአገማመት ስርዓት በመከተል የተሰጠ ከሆነ፣ የተወሰነው የካሣ መጠን በግልፅ ከአዕምሮ ግምት ውጪ የሆነና የተወሰነውም በማድላት ወይም በዝንባሌ መሆኑ በእርግጥ ሆኖ የተገኘ ከሆነ እና የተሰጠው የጉዳት ካሣ በሂሳብ መሣሣት የሆነ እንደሆነ በመሆኑና እነዚህ ነጥቦች ባልተረጋገጡበት ሁኔታ ግን በፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 2152 ስር እንደተመለከተው ይግባኝ በሕጉ የተፈቀደ አይደለም፡፡ ስለሆነም የጉዳት ካሳ መጠን ውሳኔ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መወሰን ያለበት ሲሆን ይህም የጉዳት ካሳ ሕግ መሰረታዊ አላማን የሚያሳካ ነው ተብሎ ይታሳበል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ፍርድ ቤቶች የጉዳት ካሳ መጠኑን መወሰን ያለባቸው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ብቻ እንጂ የጉዳት ካሳ መጠኑ ከፍ የማለቱን ወይም ሌላ ግምታዊ የሆነ ምክንያት መሰረት በማድረግ ሊሆን አይገባም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ተጠሪ በወንጀል ድርጊት በአመልካች ላይ የአካል ጉዳት ያደረሱባቸው ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አከራካሪ የሆነው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካሳው በርትእ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን ከአመነ በኃላ መጠኑን ብር 40,000.00 እንዲሆን በርትእ ሲወሰን እግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባቸው የነበሩትን ሁኔታዎች በአግባቡ የያዘ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ችሎቱ የጉዳት ካሳ መጠኑ በርትዕ ሲወሰን ምን ምን ሁኔታዎችን ማገናዘብ አለበት? የሚለውን ነጥብ መመርመር አስፈላጊ መሆኑን ያመነበት ሲሆን ይህንኑ በአግባቡ ለመመለስም አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በአመልካች ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት 40% ስለመሆኑ ተገንዘበናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ላይ 40% የአካል ጉዳት መድረሱን ቢያረጋግጥም አመልካች ከጉልበት ስራ ምን ያህል ገቢ እንደሚያገኙ በማስረጃ አለመረጋገጡን፣በዚህ ስራ የተሰማራ ሰው ገቢ በአመክንዩ በመውሰድ እንዲሁም በአገራችን የአንድ ሰው የእለት ገቢ በአማካኝ ተወስዶ ካሳው መሰላት ያለመበት መሆኑን፣ በዚህ ረገድ ግን ግልጽ የሆነ ማስረጃና የሂሳብ ቀመር ያለመቅረቡን ገልጾ ለእነዲዚህ አይነት ችግር ሕጉ መፍትሄ መዘርጋቱን ጠቅሶ ካሳው በርትዕ መወሰን እንደአለበት ከዘረዘረ በኂላ ይህ በሕጉ የተዘረጋው መፍትሔ ስለጉዳቱ ምን ያህል ኪሳራ እንደሚከፈል በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዳኞቹ የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጎጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሳራውን ልክ እንደሚወስኑ የሚደነግግ መሆኑን፣ ከዚህ አንጻር ሲታይም ተጠሪ የአመልካችን

www.abyssinialaw.com

አንገት ለመምታት ሲሰነዝሩ አመልካች ሲከላከሉ የአካል ጉዳቱ የደረሰባቸው መሆኑ በሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ የካሳውን መጠን የወሰነ መሆኑን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክንያት ጉዳዩ ወንጀል መሆኑንና የወንጀሉ ድርጊት ሲፈፀም አመልካች ሊያደርጉት የሚገባውን ምክንያታዊ ጥንቁቁና በተጠሪ የተሰነዘረው መሳሪያ በአንገታቸው ላይ ቢያርፍ ኖሮ ሊያስከትለው የሚችለውን የከፋ ውጤት ያላገናዘበ ሆኖ ይታያል፡፡ ሕጉ ተጎጂው ያደረገው ጥንቃቄ ማመዛዘን የጉዳት ካሳ መጠኑን በርትዕ ሲወሰን ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ የፈለገው የከፋውን ውጤት ለማስወገድ የሚደረገውን ጥንቃቄ ሳይሆን ጉዳቱን በማስከተል ረገድ በተጎጂ በኩል የተደረገውን ያልተገባ ድርጊትን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ለሕይወታቸው አደገኛ የሆነውን የተጠሪን ድርጊት በእጃቸው ሲከላከሉ በእጃቸውና በጭንቅላቸው ጉዳት መድረሱ በማናቸውም መመዘኛ አመልካች ለጉዳቱ መድረስ ተገቢ ያልሆነ ጥንቃቄ አድርገዋል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክንያት ከፍትሃ ብሔር ሕግ ቁጥር 2153 (ሀ) ድንጋጌ አንጻር ሲታይም ፍርድ ቤቱ የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያለአግባብ በመያዝ ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን የሚያሳይ እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2152 ድንጋጌ አኳያ ሲታይም ለይግባኝና ለሰበር መሰረት የሚሆን የሕግ ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ አንድ የአካል ጉዳት ካሳ መጠኑ በርትዕ እንዲወሰን የግድ የሚል ሆኖ ሲገኝም የጉዳት ካሳ መጠኑ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጠጣኝ እንዲሆን ተደርጎ ሊወሰነው አይችልም ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ጉዳት መድረሱ በተጨባጭ እስከተረጋገጠ ድረስ ለተጐጂው ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ሊከፈለው እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 ስር በመርህ ደረጃ ከመቀመጡም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 (ሀ) ድንጋጌ ስር ዳኞች ሊገምቱ የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያላግባብ በመያዝ ውሳኔ ከሰጡ ወይም ሊገምቱ የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ ትተው ያላግባብ የሆነውን ያገማመት መንገድ ይዘው የተገኙ እንደሆነ በካሳ መጠን ውሳኔው ላይ ይግባኝ የሚፈቀድ መሆኑን መደንገጉ የካሳ መጠን አወሳሰን በዘፈቀደ ሊበዛ ወይም ሊያንስ የማይገባ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

አመልካች ላይ የደረሰው አካል ጉዳት ሙሉ ለሙሉ የመስራትን ችሎታቸውን ያሳጣ ነው ባይባልም በ40% የመስራት ችሎታቸውን የቀነሰ ስለመሆኑ በሕክምና

ተረጋግጧል፡፡ በእርግጥ ለዚህ ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ለመወሰን አስቸጋሪ ቢሆንም የካሳውን መጠን በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ የካሳው መጠን በርትእ ሊወሰን እንደሚችል የፍ/ሕ/ቁ. 2102/1/ ያመለክታል፡፡ የጉዳት ካሳ መጠን ሲወሰን መታየት ያለበት ተጐጂው ከጉዳቱ በፊት ያገኘው ገቢ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት በመስራት ችሎት ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ መሆኑ ደግሞ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የጉዳት ካሳ መጠኑን በርትዕ ለመወሰን እግምት ውስጥ ሊወስዱ ስለሚገባቸው ፍሬ ነገሮች የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2102 በዝርዝር አላመላከተም፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ የቀረቡት ማስረጃዎችና ፍሬ ነገሮች በአግባቡ በማመዛዘን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 ስር የካሳ መጠኑ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ተብሎ የተቀመጠው መርህ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ የካሳው ውሣኔ መሰጠት ያለበት መሆኑን ከውል ውጪ ሃላፊነትን በተመለከተ ከተቀመጡ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም መሰረታዊ ዓላማና መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

በዚሁ መርህ መነሻ አመልካች ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት አስመልክቶ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ስንመለከት ከአመልካች አካላቸው ውስጥ 40% ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በሕክምና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ጉዳቱ ሲደርስ የነበራቸው እድሜና ስራ ሰርተው ሲያገኙት የነበረው የገቢ መጠን ያልተረጋገጠ ቢሆንም አመልካች ወደፊት በተለያዩ አማራጮች የሥራ እድሎች ሊኖሯቸው እንደሚችል ነባራዊ ሐቅ አመላካች ከመሆኑም በላይ የወደፊት ኑሮአቸውን ለማሸነፍም ከፍተኛ ውድድር ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ለዚህ ደግሞ  ባለሙሉ አካል የሆነ ሰውና ከሰውነት ክፍሎች ውስጥ አስፈላጊውን አካል በአደጋ ምክንያት ያጣ ሰው እኩል ተወዳዳሪ ናቸው ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ካሳ በርትዕ ሲወሰን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታዎችንና እነዚህ ነባራዊ ሁኔታዎች በአመልካች የወደፊት ህይወት ላይ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት አሉታዊ ተእጽኖ ግምት ውስጥ ማስገባት የካሳ መጠን አወሳንን ፍትሐዊ ያደርገዋል፣ ሕግ አውጪው ሊያሳካ ያሰበውን ግብም ለማሳካት ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

ስለሆነም አመልካች ለቋሚ የአካል ጉዳት መዳረጋቸው ለካሣ ገንዘብ መጠን አወሳሰን እግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባ ከመሆኑም በላይ ሌላው መሠረታዊ ጉዳይ ዛሬ ያለንበት

የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት እና ተጨባጭ የገንዘብ /ብር/ የመግዛት አቅም በየጊዜው እየቀነሰ መሄዱ ወደፊት ሊታጣ የሚችለው ገቢ ሲወሰን ግንዛቤ ውስጥ የማይገባበት ህጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ ስለሆነም ካሳ በርትዕ ሲወሰን ከእነዚህ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተገናዝቦ መታየት ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡

ባአጠቃላይ አመልካች ላይ የደረሰው ጉዳት ቋሚ የአካል ጉዳት እንደመሆኑ እና የአካል ጉዳት በተፈጥሮ እንደ ንብረት በገበያ ዋጋ ሊተመን የማይችል በመሆኑ የካሣ ገንዘብ ሊሰላ የሚገባው ባጠቃላይ የመስራት አቅሙ ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን መነሻ በማድረግ እና ከላይ በዝርዝር የተመለከትናቸው የሕጉ መንፈስና ዓላማ ግብ ለማድረስ በሚያስችል አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለዚህም አመልካች ላይ የደረሰ ዘላቂ ጉዳት 40% /አርባ በመቶ/ የመስራት ኃይል ማጣታቸውን በዝርዝር ከተመለከቱት የሕጉ ሕሣቤዎች እና የተጎጂዋን ግለሁኔታ በአግባቡ ሳያመዛዝኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153(ሀ) ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ምክንያት በመያዝ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ) ብቻ ለአመልካች ለአካል ጉዳት እንዲከፈል የወሰነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2102 እና 2153(ሀ)) ድንጋጌዎችን በጣሰና ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የተቀመጠውን ሕግ አጠቃላይ ዓላማ ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የተፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡ ከላይ የተመለከቱትን ምክንያቶችን እግምት ውስጥ ስናስገባ በአመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት በርትዕ ሊወሰን የሚገባው የካሳ መጠን ብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺህ ብር) ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሰሜን ሸዋ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፋ/መ/ቁ 0124895 ጥቅምት 17 ቀን 2010 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 030-9010 ታህሳስ 24 ቀን 2010 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት በርትዕ ሊወሰን የሚገባው የካሳ መጠን ብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺህ ብር) ነው በማለት ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ

www.abyssinialaw.com

ይህ ችሎት ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ(9%) ጋር ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**ሠ/አ** **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 131804

መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡-ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- በሰሜን ወሎ ዞን የቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ፕሮግራም-የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አድነው አባተ-የቀረበ የለም፡፡

2 አቶ ወንድወሰን ተፈራ

3 አቶ ተስፋየ ጭቁላ } በሌሉበት የታየ ነው፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ ተጠሪዎች ያለአግባብ እንዲከፈል ያደረጉትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ተብሎ የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በሰሜን ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተጠቀሱ ተከሳሾች ናቸው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪዎችን ጨምሮ በ16 ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረበባቸው ሲሆን 25 ጣልቃ ገቦች ወደ ክርክሩ በመግባት ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች /የሥር ከሳሽ/ በቀን 23/12/2005 ዓ/ም ጽፎ ባቀረው ክስ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ፣ የአሁን 2ኛ ተጠሪ የመስኖ ልማት ዋና የሥራ ሂደት መሪ እና የአሁን 3ኛ ተጠሪ ደግሞ የግዢ፣ ፋይናንስ፣ ንብረት እና የሰው ኃይል አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት መሪ ሆነው ሲሰሩ

www.abyssinialaw.com

ከግዢ መመሪያና ደንብ ውጪ ለ6 ሞተር ሳይክሎች ግዢ ብር 158,850 እንዲከፈል በማድረጋቸው፣ ለባለሙያዎች ለሥልጠናና ለትምህርታዊ መስክ ጉብኝት ለአንድ ሠራተኛ በቀን የሚከፈለው ብር 70 ሆኖ እያለ በቀን ብር 200 የውሎ አበል ለ56 ቀን ብር 47,580 ያለአግባብ እንዲከፈል በማድረጋቸው፣ መልቀቂያ ተሰጥቶ የተሰናበተውን አንድ ሠራተኛ ያለ ምንም ማስታወቂያ በድጋሚ እንዲቀጠር በማድረግ ለሶስት ወር ብር 2,562 እንዲከፈል በማድረጋቸው፣ በ1994 ዓ/ም በወጣው የጽ/ቤቱ የሠራተኞች መተዳደሪያ ማኑዋል መሠረት ጊዜያዊ የቅጥር ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ ግን ለ17 የጽ/ቤቱ ሠራተኞች ከጊዜያዊ ወደ ቋሚ ቅጥር ተሸጋግረው የተሻለ ጥቅም አግኝተው እያለ ከሥራ እንደተሰናበቱ በመቁጥር ለአገልግሎት ካሳ ክፍያ በማለት በድምሩ ብር 17,588.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ ያለአግባብ እንዲከፈል በማድረጋቸው እንዲሁም ሌሎችንም የማይገቡ ክፍያዎችን እንዲከፈሉ በማድረግ ሥልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀምና ተገቢ ያልሆነ አሠራር በመሥራት የመንግሥት ገንዘብ እንዲከፈል በማድረጋቸው በወንጀል ተከሰው መቀጣታቸውን ገልጾ በድምሩ ብር 368,335.97 /ሶስት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከዘጠና ሰባት ሳንቲም/ በነጠላ እና በአንድነት እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪዎችም ለቀረበባቸው ክስ መልሳቸውን በጽሁፍ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ በመ/ቁ. 09881 በሆነው በቀን 8/02/2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪዎችን ኃላፊ በማድረግ ብር 350,777.75 /ሶስት መቶ አምሳ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ሳባት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም/ እንዲከፍሉ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ለ17 ሠራተኞች የተከፈለውን ብር 17,588.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ በተመለከተ ሠራተኞቹ በክርክሩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር በጠየቁት መሠረት ወደ ክርክሩ በመግባት አምነው የተከራከሩ በመሆናቸው ለአሁን 2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች እንዲመልሱ ካለ በኃላ በዚህ ረገድ ከቀረበባቸው ክስ ተጠሪዎችን ከኃላፊነት ነፃ በማድረግ ወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሁን አመልካች ጊዜያዊ የቅጥር ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ብቻ ሆኖ እያለ አስራ ሰባቱ ሰራተኞች ከጊዜያዊ ቅጥር ወደ ቀሚ ተሸጋግረው የተሻለ የኢኮኖሚ ዋስትና አግኝተው እያለ የአገልግሎት ካሳ በሚል ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ ያለአግባብ እንዲከፈል በማድረጋቸው ተጠሪዎች በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተደርገው ተቀጥተው እያለ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ሳይወስን በዝምታ ያለፈው ያለአግባብ ነው በማለት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤት የሥር ጣልቃ ገቦች ያመኑትን የሥራ ስንብት ክፍያ ለ2ኛ እና 3ኛ መልስ ሰጪዎች /ለአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች/ እንዲመልሱ ወስኖ መልስ ሰጪዎችን /ተጠሪዎችን/ ከኃላፊነት ነፃ ማድረጉ ስህተት ቢሆንም ቅሬታ የቀረበበትን ገንዘብ የሥር ጣልቃ ገቦች የወሰዱና የተጠቀሙበት መሆኑ በክርክር ሂደት የተረጋገጠ በመሆኑ ይግባኝ ባይ/አመልካች/ ሊጠይቅ የሚችለው ጥቅም ከመልስ ሰጪዎች /ከአሁን ተጠሪዎች/ ጋር የሚገኝ ባለመሆኑ በውጤት ደረጃ የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ አልተቀበልነውም በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ዘግቶበታል፡፡

አመልካች ውሳኔውንም ሆነ ትዕዛዙን ቅር በመሰኘት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው በቀረበው ጉዳይ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞበታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም፡- ተጠሪዎች ሥልጣናቸውን ያለአግባብ ተጠቅመው በፕሮጀክቱ ላይ ያደረሱትን ኪሳራ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በቀረበው ክስ መሠረት በማስረጃ ተረጋግጦ እያለና በ1994 ዓ/ም በወጣው የፕሮጀክቱ ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 17 (5) መሠረት ጊዜያዊ የቅጥር ሠራተኞች የሥራ ስንብት ክፍያ መፈጸም ያለበት የሥራ ውል ሲቋረጥ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ ተጠሪዎች ግን በ23/03/1999 ዓ/ም በቃለ ጉባዔ የጽ/ቤቱ 17 ሠራተኞች ከጊዜያዊ ቅጥር ወደ ቋሚ ተሸጋግረውና የተሻለ የሥራ ዋስትና አግኝተው እያለ ከስራ እንደተሰናበቱ በመቁጥር የአገልግሎት ከሳ ክፍያ በማለት በድምሩ ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት

መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ እንድከፈል በማድረጋቸው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 407 /2/ መሠረት በሰሜን ወሎ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው ተረጋግጦ ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ ህግን በመተላለፍ በአመልካች ፕሮጀክት ላይ ያለአግባብ ገንዘብ እንድከፈል አዘው ላደረሱት ጉዳት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2035 በጥፋት ላይ የተመሠረተ ውል ሳይኖር ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑና ያለአግባብ የተከፈለ ብር ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 68613 በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈና መሠረታዊ የህግ ጥሰት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመሠረቱት ክስ በ1994 ዓ/ም በወጣው የአመልካች ጽ/ቤት የሠራተኞች መተዳደሪያ ማኑዋል መሠረት ጊዜያዊ የቅጥር ሰራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ ለ17 የጽ/ቤቱ ሠራተኞች ከጊዜያዊ ወደ ቋሚ ቅጥር ተሸጋግረው የተሻለ ጥቅም አግኝተው እያለ ከሥራ እንደተሰናበቱ በመቁጥር የአገልግሎት ካሳ ክፍያ በማለት በድምሩ ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ ያለአግባብ እንዲከፈል በማድረጋቸው በወንጀል ተከሰው ተቀጥተዋል፡፡ ይህን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉን በማለት አመልካች ባቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ሥር ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ ያለአግባብ የካሳ ክፍያ የወሰዱ ጣልቃ ገቦች ይህን አምነዋል፡፡ ያመኑትን ገንዘብ ለአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል በማለት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ የማለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የአሁን 1ኛ ተጠሪ ቀርበው በቀን 26/05/2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ላቀረቡት መልስ የአመልካች ወኪል የሆነው የክልሉ ዐቃቤ ህግ በቀን 11/07/2009 ዓ/ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ሰኔ 7 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት መልስ የመስጠት መብታቸው እንዲታለፍ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ተጠሪዎች ለ17 ሠራተኞች እንዲከፈላቸው ያደረጉትን ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ እንዲመልሱ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ገንዘብ ለአስራ ሰባቱ ሠራተኞች እንዲከፈል ማድረጋቸው መመሪያው የጊዜያዊ ሠራተኛ የቅጥር ውል ሲሰረዝ ተገቢውን ጥቅማ ጥቅም ሠራተኛው ያገኛል ስለሚል በመመሪያው መሠረት የተፈጸመ ነው በማለት የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው በ1994 ዓ/ም የወጣው የፕሮጀክቱ ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 17 (5) መሠረት ጊዜያዊ የቅጥር ሠራተኞች የሥራ ስንብት ክፍያ መፈጸም ያለበት የሥራ ውል ሲቋረጥ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ ተጠሪዎች ግን በ23/03/1999 ዓ/ም በቃለ ጉባዔ የጽ/ቤቱ 17 ሠራተኞች ከጊዜያዊ ቅጥር ወደ ቋሚ ተሸጋግረውና የተሻለ የሥራ ዋስትና አግኝተው እያለ ከስራ እንደተሰናበቱ በመቁጥር የአገልግሎት ከሳ ክፍያ እንዲከፈል ማድረጋቸው ህግን የጣሰ ተግባር ስለሆነ ለሠራተኞቹ ያለአግባብ እንዲከፈላቸው ያደረጉትን ገንዘብ ሊመልሱ ይገባል በማለት ነው፡፡

ይህ የተጠቀሰው መመሪያ ቁጥር 17/5/ ለጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ ስንብት እንዲከፈል የሚፈቅደው ከሥራቸው የተሰናበቱ እንደሆነ ነው፡፡ የዚህ መመሪያ ቁጥር 17/5/ ዓላማም ሠራተኞቹ ከሥራ ከተሰናበቱ በኃላ የሚገጥማቸውን የኢኮኖሚ ችግር ለማቃለል ታስቦ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ሠራተኞቹ ግን በአመልካች ድርጅት ውስጥ በጊዜያዊነት ይሠሩ ከነበረበት በቋሚነት ተቀጥረው እንዲሰሩ ሲደረግ የሥራ ስንብት እንዲከፈላቸው ማድረግ የመመሪያውን ዓላማና መንፈስ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠሪዎቹ በዚህ እና በሌሎችም በፈጸሙዋቸው ድርጊት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተደርገው ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ ይህ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ለፍትሐብሔር ክርክር ደግሞ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ይህም ማስረጃ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 68613 ላይ ከሰጠው

www.abyssinialaw.com

አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶችም የተያዘውን ጉዳይ ከዚህ አንጻር ያለመመልከታቸው ሲታይ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፤

በመጨረሻም የሥር ፍርድ ቤቶች የሥር ጣልቃ ገቦች የሆኑት አስራ ሰባቱ ሰራተኞች ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ገንዘቡ መወሰዳቸውን ባመኑት መሠረት ለአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲመልሱ ሲል የሰጠው ውሳኔ ግልጽ ባይሆንም ተጠሪዎች የአመልካች ድርጅት ገንዘብ ከህግ አግባብ ውጪ እንዲከፈል በማድረጋቸው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2035 መሠረት ተጠያቂነት አለባቸው፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.09881 በቀን 08/02/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 01-03596 በ10/06/2008 ዓ/ም እንዲሁም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 03-14560 ሐምሌ 6 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለአስራ ሰባቱ ሰራተኞች ያለአግባብ የተከፈለውን ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ የአሁን ተጠሪዎች በነጠላና በአንድነት ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ተጠሪዎች ለአመልካች የከፈሉትን ገንዘብ ከአስራ ሰባቱ ሠራተኞች ላይ የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሳኔ አይከለክልም ብለናል፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

የሰበር መዝገብ ቁጥር 142630

ሚያዝያ 11 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡-

1. ሳጅን ግርማ መርጋ
2. ሳጅን ደጀኔ ገሬ
3. ሳጅን ቱፋ ቁፋ

} የፌዴራል ፓሊስ ነ/ፊ መብራቱ በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ደሀቦ መሐመድ-ተወካይ አብዲ ዑመር በV.C. ከሐረር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በ1ኛ አመልካች ከሳሽነት የተነሳ የጉዳት ካሳ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካቾቹ በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48204 በ20/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 244291 በ26/01/2009 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡የአሁኖቹ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የአሁኗ ተጠሪ ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሳቢያ በተጨማሪ ተከሳሽነት ወደ ክርክሩ የገቡ ናቸው፡፡

www.abyssinialaw.com

1ኛ አመልካች በተጠሪዋ ላይ ክስ ያቀረቡት ንብረትነቱ የተጠሪዋ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-32111 ኦሮ የሆነ ተሽከርካሪ በ08/10/2006 ዓ.ም.ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት ላይ ኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ ተገኝቶ ሾፌሩ እንዲቆም ሲጠየቅ ፈቃደኛ ባለመሆን በፍጥነት አልፎ ሲጓዝ የኋላ ጎማ ወልቆበት የ1ኛ አመልካችን አግር ከግራ ጉልበት መገጣጠሚያቸው ላይ መትቶ የ10% ቋሚ የአካል ጉዳት ያደረሰባቸው መሆኑን ገልጸው ለህክምና፣ለምግብ እና ለመጠጥ የወጣ ወጪ ብር 20,000፣ለቀሪ 32 ዓመታት የወር ደመወዛቸው ብር 2,019 በ10% ታስቦ ለተቋረጠባቸው ገቢ ብር 77,529.60 እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 1,000 እና ወጪ ብር 1,000 በድምሩ ብር 99,529.60 /ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከስድሳ ሳንቲም/ ተጠሪዋ እንዲከፍሏቸው በመጠየቅ ሲሆን ተጠሪዋ በበኩላቸው በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጡት መልስ ጉዳቱ የደረሰው በራሳቸው በ1ኛ አመልካች ጥፋት መሆኑን፣መከሰስ የሚገባቸው ሾፌሩ እና አመልካቹን ቀጥሮ የሚያሰራው የመንግስት አካል እንጂ ተጠሪዋ አለመሆናቸውን፣ አመልካቹ ከጉዳቱ በኃላም በስራቸው ላይ ሆነው ደመወዛቸውን እያገኙ በመሆኑ የተቋረጠባቸው ገቢ አለመኖሩን፣ተጠሪ ኃላፊነት አለባቸው ቢባል እንኳ በሽምግልና ድርድር ለ1ኛ አመልካች ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ/ የከፈሉ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ከመከራከራቸውም በላይ በ1ኛ አመልካች ድርጊት ምክንያት ተሽከርካሪያቸው ተገልብጦ ጉዳት በመድረሱ ተሽከርካሪውን ወደ ነበረበት ለመመለስ ያወጡትን ወጪ ብር 40,000 /አርባ ሺህ/ 1ኛ አመልካች እንዲከፍላቸው እና ተጠሪዋ በገቢዎች እና ጉምሩክ አስተዳደራዊ መመሪያ መሰረት ተገቢውን መቀጫ ከፍለው ተሽከርካሪው እንዲለቀቅ ደብዳቤ ከተጻፈ በኃላ አመልካቾቹ ተሽከርካሪውን ይዘው ለ11 ቀናት በስልጣናቸው በማቆማቸው የ11 ቀናት የተቋረጠ ጥቅም በቀን ብር 6,000 ሂሳብ ብር 66,000 /ስድሳ ስድስት ሺህ/ እንዲከፍሏቸው እንዲወሰን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ላይ የአመልካቾቹን መልስ ተቀብሎ ክሱን እና የሁለቱንም ወገኖች ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በ1ኛ አመልካች ላይ ጉዳት ሊደርስ የቻለው ተሽከርካሪው እየተነዳ እያለ 1ኛ አመልካች ተሽከርካሪውን ለማስቆም በማሰብ ወደ ተሽከርካሪው የወረወሩት ጎማ ተፈናጥሮ እግራቸውን በመምታቱ ምክንያት እንደሆነ መረጋገጡን፣ሾፌሩም ተሽከርካሪውን በጎማው ላይ መንዳት በመቀጠላቸው ተሽከርካሪው ተገልብጦ

www.abyssinialaw.com

በተሸርካሪውም ላይ ጉዳት መድረሱ መረጋገጡን፣ተጠሪ በአስተዳደራዊ ውሳኔ የገንዘብ መቀጮ ከፍለው ተሸከርካሪው እንዲለቀቅ በደብዳቤ ከታዘዘ በኃላ አመልካቾቹ ለ11 ቀናት ማስቆማቸው መረጋገጡን፣በ11 ቀናት ውስጥ የተቋረጠው ገቢ ተጠሪ እንደሚሉት ብር 66,000 ሳይሆን ብር 13,200 /አስራ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ/ እንደሆነ መረጋገጡን፣በዚህ ሁኔታ በሁለቱም ወገኖች ላይ ለደረሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2098 ድንጋጌ መሰረት ሁለቱም ወገኖች ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን፣ተጠሪዋ ቀደም ሲል ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ/ ለ1ኛ አመልካች መክፈላቸው በመረጋገጡ ለህክምና፣ለምግብ እና ለመጠጥ የወጣ ወጪ ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ እንዲከፈላቸው 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ለቀሪ 32 ዓመታት የወር ደመወዛቸው ብር 2,019 በ10% ታስቦ የሚገኘው ጉዳት ካሳ ብር 77,529.60 /ሰባ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከስድሳ ሳንቲም/ ተጠሪዋ ለ1ኛ አመልካች መክፈል የሚገባቸው መሆኑን፣በሌላ በኩል በተጠሪዋ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት 1ኛ አመልካች ብር 40,000 /አርባ ሺህ/ ለተጠሪዋ መክፈል የሚገባቸው መሆኑን በዝርዝር ገልጾ ይህንኑ ገንዘብ በማቀናነስ እና ለተቋረጠው ጥቅም ደግሞ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችን ኃላፊ በማድረግ ተጠሪዋ ብር 37,529.60 /ሰላሳ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከስድሳ ሳንቲም/ ለ1ኛ አመልካች እንዲከፍሉ እና 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ ለተጠሪዋ የተቋረጠ ጥቅም ብር 13,200 /አስራ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ/ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በአመልካቾቹ አቅራቢነት ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2098 ድንጋጌን ጠቅሶ ሁለቱም ወገኖች ኃላፊነት አለባቸው እስካለ ድረስ በተጠሪዋ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት አጋማሽ ማለትም ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ ተጠሪዋ እንዲሸከሙ መወሰን ሲገባው ሙሉውን ብር 40,000 /አርባ ሺህ/ 1ኛ አመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በዚህ አግባብ ብቻ በማሻሻል ተጠሪዋ ለ1ኛ አመልካች ሊከፍሉ የሚገባው ብር 59,529.60 /ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከድሳ ሳንቲም/ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡አመልካቾቹ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ 1ኛ አመልካች ኃላፊነታቸውን እየተወጡ በነበረበት ሁኔታ፣ለደረሰባቸው የአካል ጉዳትም ካሳ በተወሰነላቸው ሁኔታ እንዲሁም

www.abyssinialaw.com

ተጠሪዋ ተሽከርካሪውን ያስለቀቁት አስተዳደራዊ ቅጣት ከፍለው መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በተሽከርካሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት 1ኛ አመልካች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾቹ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ሲሆኑ በሰበር አቤቱታቸው ላይ አጥብቀው የሚከራከሩትም መደበኛ ስራችንን በማከናወን ላይ እያለን ተሽከርካሪው በሾፌሩ ጥፋት ተገልብጦ ለደረሰበት ጉዳት ኃላፊነት ሊኖርብን አይገባም በማለት መሆኑን የሰበር አቤቱታቸው ይዘት ያመለክታል፡፡በመሰረቱ አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ባይኖርም በራሱ ጥፋት በሌላው ሰው ላይ ጉዳትን ካደረሰ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ እና ማንም ሰው ከራሱ ጥፋት የተነሳ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረገው ጉዳት ኪሳራ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2027 (1) እና 2028 ስር ተመልክቶል፡፡ አመልካቾቹ በፌዴራል ፖሊስ አባልነታቸው አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት ተሽከርካሪዎችን የማስቆም እና የመፈተሽ ስልጣን እና ኃፊነት ያላቸው ቢሆንም ይህንን ኃላፊነት በሚወጡበት ጊዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2031 (1) ስር እንደተመለከተው የሙያ ስራው የሚመራበትን ደንብ ማክበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ አመልካች ተሽከርካሪውን ለማስቆም የሞከሩበት ቦታ የፍተሻ ጣቢያ አለመሆኑ እና ጊዜውም ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡ተሽከርካሪውን የፍተሻ ጣቢያ ባልሆነ ቦታ አስቁሞ መፈተሹ አስፈላጊ እና ተገቢ ነበር ቢባል እንኳ ማስቆም የነበረባቸው በተሰጣቸው ሙያዊ ስልጠና መሰረት ተገቢውን መንገድ እና ስርዓት በመጠቀም ነው፡፡ይሁን እንጂ 1ኛ አመልካች ተሽከርካሪውን ለማስቆም የሞከሩት ከፊት ለፊቱ ጎማ በመወርመወር መሆኑ እና ተሽከርካሪው ሊገለበጥ የቻለውም ሾፌሩ በተወረወረበት ጎማ ላይ በመንዳቱ መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡1ኛ አመልካች መደበኛ ስራዬን በማከናወን ላይ እያለሁ ተሽከርካሪው በሾፌሩ ጥፋት ተገልብጦ ለደረሰበት ጉዳት

www.abyssinialaw.com

ኃላፊነት ሊኖርብኝ አይገባም ከማለት በቀር ተሽከርካሪውን ለማስቆም የተጠቀሙበት ዘዴ አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት በሙያው የተፈቀደ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡በሰበር አቤቱታቸውም ቢሆን በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ይልቁንም በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ወደ ተሽከርካሪው ጎማ መወርወራቸውን ሳይገልጹ ነገር ግን ጉዳቱ የደረሰባቸው ሾፌሩ እንዲቆም ሲጠየቅ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ ተሽርካሪውን በፍጥነት ሲነዳ የኃላ ጎማ ወልቆበት መሆኑን በክሳቸው ላይ በማስፈር መሆኑን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ያመለክታል፡፡1ኛ አመልካች ተሽከርካረውን ለማስቆም የሞከሩት ከፊት ለፊቱ ጎማ በመወርመወር መሆኑ እና ተሽከርካሪው ሊገለበጥ የቻለውም በዚሁ ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠው ተጠሪዋ ባቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረት 1ኛ አመልካች ለተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ በከፊል ኃላፊ መደረጋቸው የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48204 በ20/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 244291 በ26/01/2009 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ወሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.abyssinialaw.com

# ንግድ

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 143227

**ቀን** - 21/09/2010

**ዳኞች**፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

**አመልካች**፡- ደርሂም ኢንዱስትሪስ ካምፓኒ ሊሚትድ-ጠበቃ አብደላ አሊ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አሁጃን ኢንዱስትሪስ -ጠበቃ ያሬድ ለገሰ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የንግድ ምልክት ፈራሽ ሊሆን ስለሚችልበት ሁኔታን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በኢፌዲሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለጽ/ቤቱ ያቀረበዉ አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- ለፍራፍሬ መጠጦችና ጭማቂዎች ወዘተ የሚያገለግለዉና በስሙ ተመዝግቦ የሚታወቀዉን RANI የሚባለዉን የንግድ ምልክት በንግድ ምልክት እና ምዝገባ ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 36 ስር የተመለከቱትን የምዝገባ መስፈርት ከመሠረቱም ባልተሟላበት ሁኔታ በተከሳሽ ስም መመዝገቡ ተገቢ ባለመሆኑ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ሲል ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ፡፡ አመልካች በበኩሉ የመጀመሪያ መቃወሚያዎች ናቸዉ የሚላቸዉን ክርክሮች በማስቀደም፣ ከፍሬ ነገር ጋር በተያያዘም የንግድ ምልክቱ በከሳሽ ስም ተመዝግቦ የነበረ ቢሆንም በወቅቱ ባለማደሱ ምክንያት መብቱና ማጣቱን፤ በተከሳሽ ስም ሊመዘገብ

የቻለዉም በአዋጅ ቁጥር 501/1998 ተፈቅዶለት መሆኑን ጠቅሶ ሊሰረዝ አይገባዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ጽ/ቤትም በዚህ መልኩ ከግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር መሠረት የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርመር እንዲሁም አስፈላጊዉን የማጣሪያ ጥናት ማድረጉን ጠቅሶ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 7(2) እና 36 መሠረት ለአመልካች ለመጀመሪያ ጊዜ የተመዘገበዉ RANI የንግድ ምልክት ምዝገባ መጀመሪያዉንም ቢሆን በሦስተኛ ወገን የቅድሚያ መብት ምክንያት ሊመዘገብ የማይገባ ስለመሆኑ ፈራሽ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የጽ/ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ሲሆን፣ አመልካች በቀን 08/10/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃዉ አማካይነት በቀረበ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ በአዋጁ መሠረት በስሙ ተመዝግቦ የሚገኘዉ RANI የንግድ ምልክት እንዲሰረዝ በሚል በጽ/ቤቱ ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ነዉ፡፡ እኛም በአመልካች ስም የተመዘገበዉ የንግድ ምልክት እንዲሰረዝ በሚል የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ከግራ ቀኝ ክርክር እንዲሁም ስለጉዳዩ ከሚደነግጉ ህጎች አንፃር መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ ራኒ (RANY) የንግድ ምልክት በአመልካች ስም በ22/01/99 ዓ.ም ከመመዝገቡ በፊት በተጠሪ ስም ከ16/11/80 ዓ.ም እስከ 16/10/86 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ጽ/ቤት ተመዝግቦ የነበረ ስለመሆኑ አመልካች አይክድም፡፡ አመልካች ይህን ሳይክድ የንግድ ምልክቱ በተጠሪ ጥያቄ ምክንያት ሊፈርስ አይገባዉም በማለት አጥብቆ ከሚከራከርባቸዉ ነጥቦች ዉስጥ አንዱ የንግድ ምልክቱ በተጠሪ ስም ቢመዘገብም በወቅቱ ባለመታደሱ ተጠሪ መብቱን አጥቷል በማለት ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩሉ ምዝገባዉ ከመሠረቱም ስለ 3ኛ ወገኖች የቅድሚያ

www.abyssinialaw.com

መብት በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 7(2) ስር የተመለከተዉን ድንጋጌ የማያሟላ መሆኑን በመግለጽ እንዲፈርስ መወሰኑ በአግባቡ ነዉ በማለት ይከራከራል፡፡

በመሠረቱ የኢፌዲሪ አእምሯዊ ጽ/ቤት አንድን የንግድ ምልክት ከመመዝገቡ በፊት ማጣራት የሚገባቸዉን ሁኔታዎች አዋጁ በአንቀጽ 6 እና 7 ስር የሚደነግግ ሲሆን፣ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ከመሠረቱ ሳያሟላ የተደረገ ምዝገባ ፈራሽ ሊደረግ እንደሚገባዉም የአዋጁ አንቀጽ 36(1) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ የአዋጁ ድንጋጌ በአንቀጽ 7(2) ስር የተመለከተዉ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የንግድ ምልክቱ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ የሌላ ዕቃዎችን አገልግሎቶችን በሚመለከት በሚገባ በሚታወቅ ወይም ኢትዮጵያ ዉስጥ ግልጋሎት ላይ ከዋለ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን ከያዘ መመዝገብ የለበትም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በተጠሪ ስም የሚታወቅ ራኒ (RANY) የንግድ ምልክት ምርት ወደ አገር ዉስጥ መግባት ከጀመረ ረጅም ጊዜ እንዳስቆጠረና ምርቶቹም የአመልካች እንደሆኑ ጽ/ቤቱ በአዲስ አበባ የተለያዩ የገበያ ማዕከላት እንዲሁም ድሬዳዋን ጨምሮ በሌሎችም ከተሞች ባደረገዉ ጥናት ያረጋገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የንግድ ምልክት በተጠሪ የሚታወቅ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም ራኒ (RANY) የሚባል የንግድ ምልክት ከመሠረቱም በአመልካች ስም የተመዘገበዉ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 7(2) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ሳያሟላ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 36(1) መሠረት በተጠሪ ጥያቄ መሠረት እንዲፈርስ መደረጉ በአግባቡ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በኢፌዲሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጸንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል የተመለከቱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች የተከተለ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/174339 በቀን 14/07/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ በኢፌዲሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

www.abyssinialaw.com

የሰመ/ቁ. 153890

መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-ወ/ሮ እመቤት ዳኛቸው - ጠበቃ ተፈራ ኢሬንሳ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ይስማው ዘገየ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ ሙሉነሽ ዳኛቸው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተጠሪዎቹ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ክርክር ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ የነበሩት የአሁኗ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 183086 በ13/10/2009 ዓ.ም.የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በአንጻሩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43050 በ04/02/2009 ዓ.ም.የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 145578 በ12/04/2010 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት ነው፡፡

በተጠሪዎቹ መካከል የነበረው ጋብቻ በ07/07/2007 ዓ.ም. በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በወረዳ 4 ክልል ከቅዱስ ሚካኤል መረዳጃ ዕድር በኪራይ በተገኘው ቤት ውስጥ በሚገኙት የመጠጥ ግሮሰሪ ዕቃዎች እና ገቢ የክፍፍል ጉዳይ ላይ ተጠሪዎቹ በክርክር ሂደት ላይ እያሉ የአሁኗ አመልካች የንግድ ፈቃዱን በስማቸው አውጥተው ስራውን እያከናወኑ የሚገኙበትን ግሮሰሪ ተጠሪዎቹ እንደራሳቸው ንብረት በመቁጠር የራሳቸው ባልሆነ ንብረት ላይ የክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸው ተገቢ አለመሆኑን ገልጸው በግሮሰሪው ላይ የቀረበው የክፍፍል ጥያቄ ውድቅ ይደረግልኝ ሲሉ በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል።የአመልካቿ እህት የሆኑት 2ኛ ተጠሪ የጣልቃ ገቧን አቤቱታ ደግፈው የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ተጠሪዎቹ ጣልቃ ገቧን ለመርዳት አምጥተው አብረዋቸው ስላደጉ እንደልጃቸው በመቁጠር የንግድ ፈቃዱን በስማቸው ከማውጣታቸው ውጪ ጣልቃ ገቧ ግሮሰሪውን ለመቋቋም የሚያስችል የፋይናንስ አቅም የሌላቸው መሆኑን፣የግሮሰሪ ዕቃዎቹ የራሳቸው ስለመሆኑም ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን ገልጸው የጣልቃ ገብነት አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ የተከራከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የተጠሪዎቹን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ጣልቃ ገቧ ከተጠሪዎቹ ጋር እንደልጅ ሆነው በጥገኝነት ይኖሩ የነበረ ስለመሆኑ እና ግሮሰሪውን ያቋቋሙት፣ስራውንም ይሰሩ የነበሩት ተጠሪዎቹ ስለመሆናቸው በ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች የተገለጸ መሆኑን፣የግሮሰሪው መገልገያ ቁሳቁሶች ከፊሎቹ በ1ኛ ተጠሪ ስም፣ደግሞ በ2ኛ ተጠሪ ስም የተገዙ መሆኑን የሚያመለክቱ ደረሰኞች በ1ኛ ተጠሪ በኩል በማስረጃነት የቀረቡ መሆኑን፣ጣልቃ ገቧ የግሮሰሪ ድርጅቱን ያቋቋሙት ከቤተሰብ በተሰጣቸው ገንዘብ ስለመሆኑ ገልጸው የመሰከሩት የ2ኛ ተጠሪ ምስክር የ2ኛ ተጠሪ ወንድም ከመሆናቸውም በላይ ብቸኛ ምስክርም በመሆናቸው ገለልተኛ ናቸው ለማለት የማይቻል መሆኑን፣የንግድ ፈቃዱ እና የግብር ደረሰኞቹ በጣልቃ ገቧ ስም መሆኑ ብቻ ግሮሰሪውን በራሳቸው ስም አደራጅተዋል የሚያሰኝ አለመሆኑን ገልጾ የጣልቃ ገቧን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶአል።

www.abyssinialaw.com

ይህንን ውሳኔ በመቃወም ጣልቃ ገቢ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የግሮሰሪው ቁሳቁሶች የተሟሉት ለጣልቃ ገቢ ከቤተሰብ አንድ ጊዜ ብር ሃያ ሺህ፣ሌላ ጊዜ ደግሞ ብር አስራ አምስት ሺህ በተላከ ገንዘብ ስለመሆኑ በጣልቃ ገቢ አንድ ምስክር የተገለጸ መሆኑን፣የዚህን ምስክር ቃል የሚያስተባብል በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር እና በ1ኛ ተጠሪ በኩል የተሰሙት ምስክሮች አንዳቸውም 1ኛ ተጠሪ የግሮሰሪ ዕቃዎቹን ገዝተዋል ወይም ሰጥተዋል የሚል ምስክርነት ባልሰጡበት ሁኔታ የጣልቃ ገብነት ጥያቄው ውድቅ የተደረገው አለአግባብ መሆኑን ገልጾ በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር በንግድ መደብር ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች የንግድ በመደብሩ አካል ተደርገው የሚቆጠሩ ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ በአንቀጽ 128 የተመለከተ መሆኑ ገልጾ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በወረዳ 4 ክልል ከቅዱስ ሚካኤል ዕድር በመከራየት አመልካች የግሮሰሪ ንግድ የሚያከናውኑበት የንግድ መደብር ዕቃዎች የአመልካች ንብረት ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 1ኛ ተጠሪ በተራቸው ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ 2ኛ ተጠሪ በክርክሩ መጀመሪያ ላይ ግረሰሪው የጋራ ንብረት መሆኑን ገልጸው ሲከራከሩ ከቆዩ በኃላ የአመልካቿ ነው በማለት መከራከር የጀመሩት የጣልቃ ገብነት ጥያቄው ከቀረበ በኃላ መሆኑን በማከል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተገለጹትን ፍሬ ነገሮች መሰረት አድርጎ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር በአንጻሩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ክርክር የተነሳበት ግሮሰሪ የንግድ ፈቃድም ሆነ ግብሩ እንዲሁም የቤት ኪራይ ውሉ ጭምር በአመልካች ስም መሆኑ ባልተካደበት ሁኔታ የተደራጀው በተጠሪዎቹ ነው በሚል ብቻ ንብረቱ የተጠሪዎቹ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት

www.abyssinialaw.com

ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ግሮሰሪ የተቋቋመበትን የንግድ ቤት ኪራይ ውል አከራዩ የተዋዋለው ከአመልካቿ ጋር መሆኑ፣የንግድ ፈቃዱ ከጅምሩ የተሰጠው እና ግብሩም የሚከፈለው በአመልካቿ ስም መሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡በንግድ ሕጉ በቁጥር 127 (2) (ሀ) እና (ለ) ስር የተጠቀሰው የንግድ ቤቱ ስም እና የሚነገድበት የተለየ የንግድ ማስታወቂያ ሰሌዳም የሚታወቀው በአመልካቿ ስም ስለመሆኑ በሰበር አቤቱታው የቀረበው የክርክር ነጥብ በ1ኛ ተጠሪ አልተካደም፡፡አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት የንግድ ፈቃድ የሚሰጠውም ፈቃድ ጠያቂው ለንግድ ስራው የሚያስፈልገውን ካፒታል ጨምሮ ተገቢ መስፈርቶችን መሟላቱ ከተረጋገጠ በኃላ እንደሆነ የሚታመን ነው፡፡እነዚህ ሁኔታዎችም አመልካቿ የግሮሰሪ ድርጅቱን እራሳቸውን ችለው ያቋቋቀሙ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችሉ ናቸው፡፡የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔ ላይ እንደገለጸው በንግድ መደብር ውስጥ ግዙፍነት ያለው እንደ መሳሪያዎች፣የቤት ዕቃዎችና ሸቀጥ እንደሚገኙበት በንግድ ሕጉ በቁጥር 128 ተመልክቶአል፡፡እነዚህ የግሮሰሪው መገልገያ ዕቃዎች በሕጉ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡

የዚህ ዓይነቶቹ ንብረቶች ባለሀብትነትም ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኃን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን በእጁ ባደረገው ጊዜ የተላለፈለት እንደሚሆን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1186 (1) ስር ተመልክቶአል፡፡አመልካቿ እነዚህን ንብረቶች በስማቸው በሚታወቀው የግሮሰሪ የንግድ መደብር ውስጥ ይዘው መገኘታቸው ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ የእነዚሁ ንብረቶች ባለሀብት ስለመሆናቸው በሕጉ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡2ኛ ተጠሪ ከስር ጀምሮ የአመልካቿን አቋም ደግፈው የሚከራከሩ መሆኑን የመዝቡ ግልባጭም ሆነ የሰበር ክርክራቸው ያመለክታል፡፡አመልካቿ የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ከማቅረባቸው አቀድሞ 2ኛ አመልካች ግሮሰሪው የጋብቻ ውጤት መሆኑን አምነው የክፍፍል ጥያቄ አቅርበው ነበር መባሉ

www.abyssinialaw.com

ብቻውን የክርክር አቋማቸውን የቀየሩት እህታቸው የሆኑትን አመልካች አለአግባብ ለመጥቀም በማሰብ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡

ከስር ጀምሮ አመልካቿን በመቃወም በመከራከር ላይ የሚገኙት 1ኛ ተጠሪ በተመሳሳይ ስያሜ የሚታወቁ ዕቃዎች የተገዙባቸውን ደረሰኞች በማስረጃነት ከማቅረብ በቀር ዕቃዎቹን በራሳቸው ገንዘብ ገዝተው ወደ ግሮሰሪው ያስገቡት እራሳቸው ስለመሆናቸው ያስረዱ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡በዚህ አግባብ ካላስረዱ ደግሞ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደገለጸው የዕቃዎቹ ባለሀብት አመልካች ስለመሆናቸው በሕጉ የሚወሰደውን ግምት አስተባብለዋል ሊባል አይችልም፡፡በ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች በተነገረው መሰረት በግሮሰሪው ውስጥ ይሰሩ የነበሩት ተጠሪዎች መሆናቸው ብቻውን ግሮሰሪው የእነርሱ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡የንግድ ቤቱ ኪራይ፣የንግድ ፈቃዱ እና ሌሎችም ባለሀብትነትን የሚያመለክቱ መሰረታዊ ጉዳዮች በአመልካቿ ስም እንዲሆን ያደረግነው ባለን ቤተሰባዊ ግንኙነት ነው ከማለት በቀር እንደክርክራቸው ግሮሰሪው የተቋቋመበት የገንዘብ ምንጭ ሙሉ በሙሉ የእነርሱ ከሆነ ግሮሰሪው ከተጋቢዎቹ በአንዳቸው ስም እንዲቋቋም ለማድረግ ያልቻሉበት አሳማኝ እና ሕጋዊ እና ምክንያት ስለመኖሩ 1ኛ ተጠሪ ከስር ጀምሮ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡በመሆኑም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተደረሰበት እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይት ያገኘው ድምዳሜ በክርክሩ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የግሮሰሪ መደብር በተመለከተ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 183086 በ13/10/2009 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በአንጻሩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43050 በ04/02/2009 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 145578 በ12/04/2010 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 183086 በ13/10/2009 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

ቅ/ሀ                                                  የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰበር መዝገብ ቁጥር 158539

ሕዳር 27 ቀን 2011 ዓ/ም

**ዳኞች፡**-1. አልማው ወሌ

2. ሙስጠፋ አህመድ

3. አብርሃ መሰለ

4. ፈይሳ ወርቁ

5. ጻውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ-ነ/ፈጅ ኪዳኔ መካሻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-1. አቶ ምንዳይ ክፍሌ

2. አቶ ጌታቸው መኮንን

3. አቶ ዳንኤል አየለ

(ተጠሪዎች 1–3) በሌሉበት የሚታይ ነው፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባንክ አደራ የተቀመጠ ገንዘብን ለማስመለስ የቀረበን ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በባንኩ የሕግ ባለሞያነት፣ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ የህግ ካውንስሊግ የባንክ ክለርክ/ረዳት/ ሁነው ሲያገለግሉ እንደነበር፣ ተጠሪዎች በስራቸው አጋጣሚ ያገኙትን መረጃ በመጠቀም አቶ ሃይሉ መኮንን ከተባሉ የባንኩ ኢ.ሲ.ኤ ቅርንጫፍ ደንበኛ ሂሳብ ውስጥ ብር 258,764.11 ብር ወጪ በማድረግ ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸውን፣ በዚህ ጉዳይም የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው ቅጣት የተጣለባቸው መሆኑን ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥም 1ኛ ተጠሪ ብር 86,248.70 እንዲሁም መግዛ ክፍሌ የተባሉ ግብረአበር ብር 20,000.00 ገቢ አድርገው ብር 152,497.41(አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት

ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም) የቀረ መሆኑን በመጥቀስ ይህንኑ ገንዘብ ከመጋቢት 12 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ ጥሪ ቢደረግላቸውም ባለመቅባቸው ክርክሩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ሁነው በመገኘታቸው ተገቢው የወንጀል ቅጣት የተወሰነባቸው መሆኑን በመ/ቁጥር 90239 የተሰጠ ውሳኔ የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ በወንጀል ጥፋተኛ መባልን የሚያሳይ ማስረጃም በተመሳሳይ ጉዳይ  የፍትሃ ብሔር ክስ ሲቀርብ ለጉዳዩ አግባብነትና ብቃት ያለው ማስረጃ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ግልባጭ ንባብና በዚህ ረገድ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37184 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለመረዳት የሚቻል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ከአመልካች ደንበኛ ሂሳብ ላይ ያላግባብ ተቀናሽ በማድረግ ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸውን አመልካች በአቀረባቸው ማስረጃዎቸው ያስረዳ መሆኑን ከደመደመ በኋላ አመልካች ተጠሪዎች ከአመልካች ደንበኛ ሂሳብ ላይ ገንዘብ በመውሰድ ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸውን ከመግለፅ እና ይህንን ሊያስረዳ የሚችል ማስረጃ ከማቅረብ ባለፈ አመልካች ገንዘቡን ለደንበኛው መተካቱን ገልፆ ያቀረበው ክስ የለም፣ ገንዘቡ ለደንበኛው ገቢ ተደርጎ ከሆነም ማረጋገጫ እንዲያቀርብ በፍርድ ቤቱ ቢታዘዝም የቀረበ ማስረጃ የለም የሚሉ ምክንያቶችን አስፍሮ አመልካች የደረሰበት ጉዳት አለ፣ ገንዘቡም ሊተካለት የሚገባ ባለመብትም ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር በነበራቸው የስራ ግንኙነት ምክንያት ከአመልካች ደንበኛ ገንዘብ ያላግባብ ወጪ አድርገው ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው ምክንያት በወንጀልም ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን የሚያሳይ የፍርድ ቤት ውሳኔ ለማስረጃነት ቀርቦ እያለ

እና ፍርድ ቤቱም ማስረጃውን ከተቀበለ በኋላ አመልካች የደንበኛውን ገንዘብ ከሚጠብቅበት የጊዜ ገደብ፣ በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገንዘቡን ያስቀመጠ ባለመብት ካልቀረበ ገንዘቡ ወደ ብሄራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ከመሆኑ አንፃር ሳያገናዝብና ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብም ጥያቄ ቀርቦ እያለ ይህንኑ ባላገናዘበ መልኩ አመልካች በተጠሪዎች የጎደለውንና ለግል ጥቅማቸው የዋለውን የደንበኛውን ገንዘብ ስለመክፈሉ ወይም ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች፣ ባንኩ የደንበኛውን ገንዘብ ለመጠበቅ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ እንዲሁም የተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ስርዓትን ያልተከተለ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ለቅሬታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲያስቀርብ ከተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ጋር በተያያዘ ጭብጥ የያዘ ቢሆንም በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች አንጻር ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ነጥብ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት አግባብ የሕግ መሰረት ያለው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ተጠሪዎች የባንኩ ሰራተኛ በመሆን ሲሰሩ በነበረበት ወቅት የተሰጣቸውን ሃላፊነት በማጉደል ከአመልካች ደንበኛ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ በማውጣት ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በሚል ምክንያት ሲሆን ለዚህም ተጠሪዎች በወንጀል የተቀጡ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረቡን፣ የስር ፍርድ ቤትም በተጠሪዎች ላይ የተላለፈ የወንጀል ጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔን የሚያሳይ

ማስረጃ በተመሳሳይ ጉዳይ የፍትሃ ብሄር ክስ ሲቀርብ ለዚሁ ክስ አግባብነት ያለውና ብቃት ያለው ማስረጃ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 እና በዚህ ረገድ ይህ ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መረዳቱን ገልጾ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ለደንበኛው ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፣ ገንዘቡን ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ በፍርድ ቤቱ ሲታዘዝም ሊያቀርብ አልቻለም በሚል ምክንያት አመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት የለም፣ ገንዘቡ ሊተካለት የሚገባ ባለመብትም ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ድምዳሜ ክሱን ውድቅ ያደረገው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር በማስረጃነት አግባብነት እና ብቃት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2149 ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ያስገነዝበናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል የተሰጠ ውሣኔ በፍትሐብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት አግባብነት የሚኖረው በወንጀል ክሱ በወንጀል ፍ/ቤት ተከሣሹ ጥፋተኛ ተብሎ ከተወሰነ ስለመሆኑ እና ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የወንጀል ክስ ማስረጃ አመዛዘን መርህ ከፍትሐብሔር የበለጠ ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚጠይቅ መሆኑ ነው፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎችም በፍትሐብሔሩ ጉዳይም የቀረቡና የተሰሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በወንጀሉና በፍትሐብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍትሐብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁል ጊዜ በፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነትን የማያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና አላማ ያስገነዝበናል፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 46386 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍ/ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ማስረጃ ክብደት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ለፍትሐብሔሩ ክርክር ብቃት ያለው ማስረጃ መሆኑና በፍትሐብሔር ክብደት ሊሰጠው አይገባም የተባለ ማስረጃ ለወንጀሉ ክስ ሲቀርብ ክብደት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ተጠሪዎች ለክርክሩ

ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነትና ብቃት ያለው ማስረጃ መሆኑን አምኖበት ያለፈው መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ከአመልካች ደንበኛ የባንክ ሂሳብ ገንዘብ አውጥተው ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ ከአመልካች ደንበኛ መብት አንጻር ሲታይ ለክሱ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የሥር ፍርድቤትም ይህንኑ የተቀበለው መሆኑን ከውሳኔው ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው የአመልካች ደንበኛ ገንዘብ በተጠሪዎች ያላግባብ መወሰዱንና ለግል ጥቅማቸው የዋለ መሆኑን ተቀብሎ አመልካች ገንዘቡን ለደንበኛ ስለመተካቱ የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም በሚል አቢይ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም የሕጉ ጥያቄ የሚሆነው አመልካች በተጠሪዎች የተወሰደውንና ለግል ጥቅማቸው የዋለውን የደንበኛውን ገንዘብ ለማስመለስ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ለደንበኛው መክፈሉን ወይም ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ በሕጉ የተጣለበት ቅድሚያ ሁኔታ አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ ባንክ በአደራ የተቀበለውን የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ ህጋዊ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በንግድ ህጉ ከቁጥር 896 እስከ 902 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ ባንኩና ደንበኛው የአደራ ስምምነት ውል መግባታቸውን በመግለጽ በውሉ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ባንኩ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ባንኩ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ የደንበኛውን ገንዘብ የባንክ ስራ የሚጠይቀውን አሰራርና ስርዓት በመከተል መጠበቅና ደንበኛው ገንዘቡን ሲጠይቅም መመለስ ነው፡፡ ባንክ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በደንበኛው ገንዘብ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂነት የሚኖርበት መሆኑንም ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎቸው መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ባንኩ የደንበኛውን መብትና ጥቅም

www.abyssinialaw.com

ማስከበር የሚገባው ተገቢውን ጥንቃቄ ወይም የተለመደ አሠራር በመከተል ሲሆን ይህም ባልተገባ መንገድ በደንበኛው ገንዘብ ላይ ጉዳት ያደረሱትን ሰዎች በመከላከል፣ ክስ በማቅረብ ጭምር ስለመሆኑ ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 52(1) ከተጣለበት ግዴታና ከላይ ከተጠቀሱት የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ትክክለኛ አፈፃጸም የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

ባንኩ ከህግ ውጪ የተወሰደውን የደንበኛውን ገንዘብ የወሰደ ሰው በተገቢው ጊዜ ክስ አቅርቦ መብቱን ሊያስከበርለት የሚገባ መሆኑን ሕጉ የጣለበት ግዴታ ሲሆን የደንበኛውን ገንዘብ ደንበኛው በሕጉ አግባብ ባለመጠቀሙ ባንኩ ራሱ የሚጠቀመው ሳይሆን ወይም ለዛለለሙ ባንኩ ይዞ የሚጠብቀው ሳይሆን በሕጉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ማለፉ ከተረጋገጠ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ የሚያደርገው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 592/2000 በግልፅ ያሳያል፡፡ ስለሆነም አመልካች የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ ሕጋዊ ግዴታ ያለበትና ከሕግ ውጪ የደንበኛውን ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ባደረገ ሰው ወይም ደግሞ የአመልካች ሰራተኞች በስራቸው አጋጣሚ ያገኙትን እድል በመጠቀም በባንኩ ገንዘብ ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ከተረጋገጠ ደንበኛው ከባንኩ ገንዘቡን የማግኘት መብት በህግ የተጠበቀለት በመሆኑ ባንኩ ደንበኛውን በመተካት ወይም በራሱ ስም ሁኖ የደንበኛውን ገንዘብ ባልተገባ ወይም በወንጀል ተግባር ወጪ አድርጎ ለግል ጥቅሙ በአዋለው ሰው ክስ ቢያቀርብ ባንኩ በቅድሚያ የደንበኛውን ገንዘብ ስለመክፈሉ ወይም በደንበኛው የባንክ አካውንት ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም ተብሎ ክሱ ውድቅ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም ባንኩ በን/ሕ/ቁጥር 896 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች በሕግ የተጣለበት ግዴታ ያለው ሲሆን ደንበኛው በሕጉ በተመለከተው አግባብ ገንዘቡን የመጠቀም ወይም የማንቀሳቀስ ተግባር ከአቆመም ለብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ስለሆነ ያለግባብ የተወሰደውን የደንበኛውን ገንዘብ አመልካች ባንክ ለራሱ ጥቅም ሊያውል የሚችልበት እድል የለምና፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ባንክ ሰራተኞቹ ሁነው የደንበኛውን ገንዘብ በወንጀል ተግባር በወሰዱት ተጠሪዎች ላይ ገንዘቡን ለማስመለስ ያቀረበውን ክስ ተጠሪዎች ስለመውሰዳቸው የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቦ እያለና የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ

www.abyssinialaw.com

ግዴታና መተካት ደግሞ በሕግ የተጣለበት፣ እንዲሁም ባንኩ የተወሰደውን ገንዘብም ሆነ ቀሪውን የደንበኛውን ገንዘብ ለራሱ ጥቅም ሊያውል የሚችልበት የህግ ማእቀፍ በሌለበት ሁኔታ ባንኩ ለደንበኛው ገንዘቡን ስለመተካቱ የሚያሳይ ማስረጃ እስካላቀረበ ድረስ ጉዳት ደርሶበታል ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባበ የለም ተብሎ ክሱን ውድቅ በማድረግ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33 ድንጋጌን መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ፣ እንዲሁም ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 ድንጋጌን መሰረት ተደርጎ የተሰጠ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሣኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 252399 ሕዳር 13 ቀን 2010 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 211978 ሚያዚያ 11 ቀን 2010 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ በሕጉ አግባብ ያስረዳ በመሆኑ ተጠሪዎች ለክሱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸው፣ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ብር 152,497.41(አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም) ይህ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ(9%) ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ባንኩ የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 149326

**ቀን** - 28/03/2011

**ዳኞች**፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ መብራቱ ጤናዉ - አልቀረቡም፡፡

**ጣ/ገብ ተጠሪ**፡- አረብ ኮንትራክተርስ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአንድ ክስተት ከሁለት በላይ በሆኑ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት መድረሱ መድን ሰጪዉ በመድን ዉሉ ላይ ከተመለከተዉ የኃላፊነት ጣሪያ በላይ እንዲከፍል ምክንያት የሚሆን መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ በቀን 10/04/09 ዓ.ም አዘጋጅተዉ በጣ/ገብ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ቁጥሩ 3-69511 የሆነዉ የተከሳሽ ተሽከርካሪ ወደ ኋላ ተንሸራትቶ በንብረታቸዉ ላይ በብር 150,800.00 የሚገመት ጉዳት ያደረሰ መሆኑን ጠቅሰዉ ተከሳሽ ይህኑን ገንዘብ እንዲከፍላቸዉ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ጣ/ገብ ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ መልስ ጉዳት መድረሱን ሳይክድ፣ የደረሰዉ ጉዳት ግምቱ የተጋነነ ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር የተከራከረ ሲሆን፣ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ

www.abyssinialaw.com

እንዲገባ በማለትም ጠይቋል፡፡ አመልካችም በክርክሩ ጣልቃ በመግባት፣ በከሳሽ የተጠየቀዉ ጉዳት መጠኑ በባለሙያ ተገምቶ ያልቀረበ መሆኑን፣ እንዲሁም በተመሳሳይ ጉዳይ በሌላ መዝገብ በክርክር ላይ ያሉ መሆኑን እና የኃላፊነት መጠኑ ከብር 100,000.00 ስለማይበልጥ ፍርድ ቤቱ ይህኑን ግምት ዉስጥ እንዲያስገባ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በደረሰዉ አደጋ ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰ ጉዳት በብር 130,800.00 ስለመሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ፣ አመልካች በመድን ዉሉ በተመለከተዉ ጣሪያ ልክ ብር 100,000.00 እንዲከፍል፣ ቀሪዉን ለዳኝነት የተከፈለዉን ገንዘብ ጨምሮ የአሁን ጣ/ገብ ተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በቀን 06/03/2010 ዓ.ም በወኪሉ አማካይነት ባቀረበዉ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ የመድን ዉል መሠረት አመልካች በአንድ ክስተት በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰ ጉዳት ለመክፈል የገባዉ ግዴታ እስከ ብር 100,000.00 ብቻ መሆኑን፤ በተመሳሳይ አደጋ ምክንያት ንብረትነቱ የአቶ አርአያ ገ/መድህን የሆነዉ የሰ/ቁጥሩ 1-33616 በሆነዉ ባጃጅ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት መድረሱን ተከትሎ በመ/ቁጥር 00044 ላይ ክስ ቀርቦ አመልካች ብር 54,951.00 እንዲከፍል መወሰኑን፤ ይህም አመልካች በአንድ ክስተት ሊከፍል ከሚገባዉ ጣሪያ በላይ ብር 54,951.00 እንዲከፍል መደረጉን የሚያሳይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ይህኑን ግምት ዉስጥ እንዲያስገባ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ አመልካች መክፈል ከሚገባዉ በላይ እንዲከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮም አመልካች በመድን ዉሉ ከተመለከተዉ ጣሪያ በላይ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡ በዚህ መነሻነት መዝገቡ ከተመረመረ በኋላ፣ በስር ተከሳሽ የነበረዉ በዚህ ችሎት ተጠሪ ሆኖ ጣልቃ እንዲገባ

www.abyssinialaw.com

ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ጣ/ገብ ተጠሪ በቀን 24/01/2011 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ መልስ በዚህ ችሎት በሚደረግ ክርክር ጣልቃ እንዲገባ የተደረገበት አግባብ ኢ-ስነስርዓታዊ መሆኑን፣ እንዲሁም የአመልካችን የኃላፊነት መጠን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አለመሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ፣ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ አጥብቆ የሚከራከረዉ በጣ/ገብ ተጠሪ ተሽከርካሪ ምክንያት በአንድ ጊዜ የሚደርስ አደጋ ከሁለት እና ሁለት በላይ ሠዎች ላይ ጉዳት ቢደርስም የኃላፊነቱ መጠን ከብር 100,000.00 ሊበልጥ እንደማይገባ፣ ይሁንና በተሽከርካሪዉ አማካይነት በተፈጠረ አደጋ ምክንያት ከተጠሪ ሌላ በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰ ጉዳት ተከስሶ ብር 54,591.00 እንዲከፍል መደረጉን እና ይህም ለተጠሪ እንዲከፈል ከተወሰነዉ የገንዘብ መጠን ጋር ሲደመር የአመልካችን ኃላፊነት በመድን ዉሉ ከተመለከተዉ በላይ ብር 154,951.00 የሚያደርስ መሆኑን ነዉ፡፡ ያስቀርባል የተባለዉም ይህኑን ለማጣራት ነዉ፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ ላይ የሚሰጥ ዉሳኔ በጣ/ገብ ተጠሪ መብት ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ዉጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህኑን ግምት ዉስጥ በማስገባት አመልካች ጣ/ገብ ተጠሪን ተጠሪ ማድረግ ሲገባዉ አላደረገም፡፡ ይህ በመሆኑም ጣ/ገብ ተጠሪ በዚህ ችሎት እየተደረገ ባለዉ ክርክር በተጠሪነት እንዲቀርብ መደረጉ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40(5) መሠረት በአግባቡ በመሆኑ ጣ/ገብ ተጠሪ በዚህ ችሎት በተጠሪነት መጠራቱ ከስነ ስርዓት ዉጪ መሆኑን በመግለጽ የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

ወደ ዋናዉ ጉዳይ ስንመለከት ከላይ እንደተገለጸዉ በግራ ቀኝ መካከል በቀን 24/03/2008 ዓ.ም በተደረገ የሦስተኛ ወገን መድን ዉል በፊደል “ሰ“ ለንብረት ጉዳት ካሳ በሚል በተመለከተዉ ርዕስ ስር በአንድ ክስተት በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰ የንብረት ጉዳት ካሳ የአመልካች ኃላፊነት እስከ ብር 100,000.00 ስለመሆኑ በግልጽ

ተመልክቷል፡፡ በጣ/ገብ ተጠሪ ተሽከርካሪ በተፈጠረዉ አደጋ ምክንያት በተጠሪ ንብረት ላይ በብር 130,800.00 የሚገመት ጉዳት የደረሰ ሲሆን፣ በተመሳሳይ አደጋ በአቶ አርአያ ገ/ማርያም የባጃጅ ተሽከርካሪ ላይ መድረሱን ተከትሎ በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00044 ላይ ክርክር ተደርጎ ፍርድ ቤቱ በአደጋዉ ምክንያት በባጃጁ ላይ ለደረሰ ጉዳት ብር 54,951.00 አመልካች እንዲከፍል መወሰኑን እና በዉሳኔዉ መሠረትም የተፈጸመ ስለመሆኑ ከግራ ቀኝ ክርክር ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይሁንና ይህ መሆኑ የአመልካችን የኃላፊነት ጣሪያ ከፍ ሲል በተመለከተዉ አግባብ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገ የመድን ዉል ከተመለከተዉ ከብር 100,000.00 በላይ ሊያደርግ አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባዉን የካሳ መጠን ሲወስን ይህኑን ግምት ዉስጥ ማስገባት ነበረበት፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህን ባለማድረግ በአንድ በኩል አመልካች ለአቶ አርአያ ገ/መድህን 54,951.00 እንዲከፍል ወስኖ እያለ በሌላ በኩል ለተጠሪም ብር 100000.00 እንዲከፍል በማድረግ የአመልካችን የኃላፊነት መጠን እስከ ብር 154,951.00 ሊያደርስ የሚችል ዉሳኔ መስጠቱ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉን የመድን ዉል እንዲሁም የኢንሹራንስ ሰጪዉ ግዴታ የኃላፊነት መጠን በመድን ዉሉ ላይ ከተመለከተዉ መብለጥ እንደሌለበት በንግድ ህጉ አንቀጽ 665(2) ስር የተመለከተዉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00043 በቀን 24/09/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 260035 በቀን 14/02/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንጽ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በሌላ መዝገብ ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ለአቶ አርአያ ገ/መድህን የከፈለዉ ብር 54,951.00 ተቀንሶ፣ አመልካች ለተጠሪ ብር 45,049.00 (አርባ አምስት ሺህ አርባ ዘጠኝ ብር) ሊከፍል ይገባል ተብሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

3. ጣ/ገብ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ በተወሰነዉ ላይ ብር 54,951.00 ተጨምሮ ብር 85,751.00 (ሰማኒያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ አንድ ብር) ለተጠሪ ይክፈል ብለናል፡፡
4. የዳኝነት እና ኪሳራ ክፍያን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
5. በአጣሪ ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
6. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 153981

መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ሚሲስ ሲያዎ ዶንግ - ጠበቃ ሃፍቶም ከሰተ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ሚስተር ዶንግዩ ቸን

2. አቢስንያ ቴክኖሎጂ አዳፕቴሽን ሴንተር ኃ/የተ/የግ/ማህበር } ጠበቃ አብዱራህማን አልአቂብ- ቀረቡ፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪዎች ክስ ይዘትም አመልካች በሁዋ ኢ ስሜንት የተወሰነ የግል ማህበር ውስጥ ስራ አስኪያጅ ሲሆኑ የተሸሙት ለአራት ዓመታት በመሆኑ፤ ምንም ዓይነት የባለአክስዮኖች ስብሰባ ጠርተው የማያውቁ በመሆናቸው፤ ዓመታዊ

የሒሳብ ሪፖርትም ሆነ የትርፍ ክፍፍል ተደርጎ የማያውቅ በመሆኑ፤ ሽያጭ እየደበቁና ግብር እየሰወሩ በገቢ ሰብሳቢ ቢሮ ድርጅቱ እንዲቀጣ ያደረጉ በመሆናቸው ከስራ አስኪያጅነታቸው ይሻርልን፤የድርጅቱ ሒሳብና ሁኔታ ኦዲት እንዲደረግልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

የስር ተከሳሽ የነበሩት አመልካች በሰጡት መልስ የድርጅቱ ባለአክስዮኖች በ03/10/2001፤ 20/07/2002 እና በ23/11/2003 ዓ.ም በተደረጉ ውሳኔዎች ማህበሩ የማቋቋም ውሳኔዎች ተሻሽሏል፤2ኛ ተጠሪ ምንም ገንዘብ አላወጣም፤ስራ አስኪያጅ የማንሳት ጉዳይ በባለአክስዮኖች ስብሰባ ላይ አብላጫ ድምፅ ድጋፍ ሳያገኝ በመቅረቱ ያልተተካ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል አይደለም፤በመመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ስብሰባ የመጥራት ኃላፊነት የሁሉም ባለአክስዮኖች ግዴታ ነው፤አመልካች ስብሰባ ተጠርተው ቀርተው አያቁም፤ስብሰባውም እ.ኤ.አ ዲሴምበር 27 ቀን 2014 እና ጃንዋሪ 20 ቀን ተደርጓል፤የሁሉም በጀት ዓመት ሒሳብ ተደርጓል፤ትርፍ ክፍፍል ተደርጎ ተጠሪዎች ገንዘብ ወስደዋል፤ከስራ አስኪያጅነት ሊያስነሳ የሚችል ጥፋት አልሰራሁም፤የድርጅቱ ሒሳብ በየዓመቱ ኦዲት ተደርጎ ግብር የሚከፈል ሁኖ እያለ በ3ኛ ወገን የሚመረመርበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ካቀረቡ በኋላ ድርጅቱ በስድሳ ሚልዮን ቢቋቋም አመልካችና 1ኛ ተጠሪ እያንዳንዳችን 45% ድርሻ ሲኖረን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ 10% ድርሻ ነበራቸው፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች ባደረግነው ስምምነት ከ14 ሚልዮን በላይ መዋጮ ያዋጣሁ ቢሆንም ተጠሪዎች መዋጮ ያልከፈሉ በመሆናቸው በተለያየ ጊዜ በተደረጉ ስምምነቶች መዋጮው እንዲከፍሉ /ሌላ ግለሰብ እንዲከፍልላቸው ጭምር/ የተስማማ ቢሆንም ምንም ዓይነት መዋጮ አዋጥተው የማያውቁ በመሆናቸው እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 22 ቀን 2015 ከተደረገው ስብሰባ ጀምሮ የሒሳብ ሪፖርት ፀድቆ ትርፍ ክፍፍል እንዲደረግ በተያዘው አጀንዳም ምንም ስምምነት መድረስ አልቻለም በስራ አስኪያጅ ይነሳ ጉዳይ ከፍተኛ አለመግባባት ተፈጥሯል፤ በውጭ ኦዲተር የተሰራውን የማህበሩ ሒሳብ ተጠሪዎች ለማጽደቅ እምቢተኛ ሁኗል፤ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ መነሻነትም የማህበሩ ህልውና አደጋ ላይ ወድቋል፤በአጠቃላይ በመዋጮ፤ስራ አስኪያጅ ሹመት፤ትርፍ ክፍፍል፤በኦዲት ሪፖርትና የማህበሩ አመራር ዙሪያ በአባላት መካከል አለመግባባት እና ብርቱ ጭቅጭቅ የተፈጠረ በመሆኑ ማህበሩ እንዲፈርስ እና ንብረት አጣሪ እንዲሾም የተከሳሽ ከሳሽነት አቅርበው

ተጠሪዎች በበኩላቸው ማህበሩ ሊፍርስ አይገባውም የሚል መልስ ሰጥቷል። ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ማህበሩ ሊፍርስ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በማስቀደም የተፈጠረው ግጭት መሰረታዊ ግጭት አይደለም፤አንዱ ማህበርተኛ በወሰነው ወይም በሰራው ሌላው ደስተኛ ወይም ተጠቃሚ ካለመሆኑ የተነሳ አለመግባባት ነው፤ማፍረስ የመጨረሻ መፍትሔ ነው፤የተጠቀሱ ምክንያቶች አለመግባባት እና ብርቱ ጭቅጭቅ ፈጥሯል የሚባሉ አይደሉም በማለት ማህበሩ ሊፍርስ አይገባውም፤በመቀጠል አመልካች ከተሾሙ አንስቶ 4 ዓመት ያለፈባቸው በመሆኑ፤ድርጅቱ እንዳልተቀጣ ቢገልጹም የተወሰነ ገንዘብ እንደከፈለ ማመናቸው፤በየዓመቱ ስበሰባ እየጠሩ የሒሳብ እና የስራ ሪፖርት ያቀረቡ ስለመሆናቸው ያቀረቡት ክርክር የለም በማለት ክስራ አስኪያጅነታቸው ሊነሱ ይገባል በማለት ወስኖ የድርጅቱ ሁኔታና ሒሳብ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ በኦዲተር እንዲጣራ ሲል የሰጠው ውሳኔ በመቃወም አመልካች ይግባኛቸው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት በትእዛዝ ሰርዞታል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካች የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 25 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካችም አቤቱታቸው በማጠናከር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል። ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አመልካች ከስራ አስኪያጅነት ኃላፊነታቸው እንዲነሱ ያቀረቡት መሰረት በማድረግ የማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 10.4 መሰረት ከአራት ዓመት በኋላ ሌላ ስራ አስኪያጅ እንደሚመረጥ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች

www.abyssinialaw.com

የደረሱበት ድምዳሜ ከመሆኑም በላይ በአጣሪው ችሎትም በጭብጥነት ያልተያዘ ከመሆኑ አንፃር አመልካች ስራ አስኪያጅ እንዲመረጥ የተሰጠ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩበት ጉዳይ በማህበሩ አባላት መካከል ብርቱ ጭቅጭቅ ተፈጥሮ እያለ ማህበሩ ሊፍርስ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው የአመልካችን የማህበሩ ይፍረስ ጥያቄ እና ምክንያት በንግድ ህጉ አንድ ማህበር ስለሚፈርስበት ሁኔታ ከተደነገጉት አንቀጽ 217 እና 218 ጋር በአግባቡ አገናዝበው የሰጡት ውሳኔ እና አተረጓጎም ምንም አይነት የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቿ ምክንያታቸውን በዝርዝር በመግለጽ ሂሳቡ ተጣርቶ ማህበሩ እንዲፈርስ እንዲወሰን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ በቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በግራ ቀኙ መካከል ዝርዝር ክርክር ከተደረገ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችል በቂና ሕጋዊ ምክንያት ያልተገኘ መሆኑን እንዲሁም የንግድ ማህበሮች መቋቋምና በተለያዩ የንግድ፤የኢኮኖሚ ስራዎች ላይ መሰማራት፤ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገትና እንቅስቃሴ ወሳኝ የሆነ ሚና ያላቸው ሲሆን የሀገራት ኢኮኖሚ እድገትም ከንግድ ማህበሮች መቋቋም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በመሆኑም የንግድ ማህበሮች መቋቋም፤መስፋፋት ብሎም መፍረስ ከማህበርተኞች መብትና ጥቅም አልፎ በሶስተኛ ወገኖች /ሰራተኞች፤ከማህበሩ ጋር የውል ግዴታ በሚገቡ ሰዎች በገንዘብ ጠያቂዎች ወዘተ../መብትና ጥቅም ላይ እንዲሁም በአጠቃላይ የሀገር ኢኮኖሚ እድገትና እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ የንግድ ማህበራት ጉዳይ በተለይም የንግድ ማህበራት መፍረስ ጉዳይ በአግባቡ እና በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ገልጾ አመልካቿን ጥያቄ በቀን 15/02/2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በተሰጠ ውሳኔ ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት በቀን 29/05/2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በመሰረቱ የንግድ ማህበሮች ከተቋቋሙ በኋላ እንደየአግባብነቱ በማህበርተኞቹ ስምምነት፣ በሕግ በተመለከተው ምክንያትና በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈርሱ የሚችሉ

www.abyssinialaw.com

ሲሆን የንግድ ሕጉ ለሁሉም ማህበሮች ተፈፃሚነት ያላቸው የማፍረሻ ምክንያት ያስቀመጠ ከመሆኑ በተጨማሪ እያንዳንዱ ንግድ ማህበር ካለው የተለየ ባህሪ አኳያ ለየማህበራቱ ተፈፃሚ የሚሆን ተጨማሪ የማፍረሻ ምክንያቶች አካትቶ ይዟል። በንግድ ሕጉ ስለ ንግድ ማህበሮች በጠቅላላው በሚናገረው ክፍል የሚገኘው ቁጥር 217 ማህበር በሕግ ወይም በስምምነት ሊፈርስ የሚችልበትን ቁጥር 218 ደግሞ በፍርድ ቤት አማካኝነት የሚፈርስበትን ምክንያቶች ያመለክታሉ። ማህበሩ የተቋቋመበትን ጉዳይ ከፈፀመ ወይም ለመፈፀም ባልቻለ ጊዜ፣የንግድ ማህበሩ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ከመድረሱ በፊት ማህበርተኞቹ ማህበሩ እንዲፈርስ ተስማምተው ከወሰኑ፣ማህበርተኞቹ ማህበሩ እንዲቀጥል ካልተስማሙ በቀር ማህበሩ የተቋቋመበት ዘመን ሲያበቃ ማህበሩ ሊፈርስ ይችላል። ማህበሩ የሚቆይበት ዘመን ከመድረሱ በፊት ትክክለኛ ምክንያቶች ኖረውት ከማህበርተኞቹ አንዱ ጥያቄ ሲያቀርብ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈርስ የሚችል ሲሆን ከማህበርተኞቹ አንዱ ተግባሩን (ግዴታዎቹን) ከመፈፀም በብዙ ማስተጓጎል፣በአካል ጉድለት ወይም በማይድን ህመም ምክንያት ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት የማህበሩን ስራ ለመስራት አለመቻሉ፣ በማህበርተኞቹ መካከል ብርቱ ጭቅጭቅና አለመስማማት መፈጠሩ እንደትክክለኛ ምክንያት ሊወሰዱ እንደሚችሉ የንግድ ህግ ቁጥር 218 (2) ድንጋጌ ያመለክታል። ድንጋጌው "ብርቱ ጭቅጭቅና አለመስማማት" የሚለው ሐረግ ምን እንደሚያመላክት የሚያስቀምጠው ግልፅ መመዘኛ የሌለ ቢሆንም ሐረጉ ማህበሩ ከተቋቋመበት መሰረታዊ አላማና ከማህበርተኞቹ አብሮ የመስራት አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር ታይቶ ሊተርጎም የሚችል መሆኑ የሚታመን ነው። ስለሆነም ብርቱ ጭቅጭቅ ሲባል በማህበርተኞቹ መካከል ያለ ማንኛውም አለመግባባት ሳይሆን ማህበርተኞች አብረው ለመስራት የማያስችላቸው ወይም ማህበሩ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት የማያስችለው እና ለስራው አስፈላጊ ከሆነ ጉዳይ ጋር የተገናኘ መሰረታዊ ግጭትና አለመግባባት መኖሩን የሚያመለክት ነው ተብሎ የሚወሰድ መሆኑ ይታመናል። ሐረጉ በዚህ አግባብ መተርጎም ያለበት ካልሆነ ማህበራት ተገቢው የሕግ ጥበቃ ተደርጎላቸው ለአገር ኢኮኖሚ የሚያበረክቱት ሚና የጎላ አይሆንም። በሌላ አገላለፅ ሐረጉ ማህበሩ ተገቢውን ስራ ለማከናወን የሚያስችል ሁኔታ ውስጥ መኖሩን በሚያሳይ መልኩ ካልተተረጎመ ማህበራት ተገቢ ባልሆኑ ምክንያቶች ሁሉ እንዲፈርሱ

www.abyssinialaw.com

የማድረግ አጋጣሚን ሁሉ ሊፈጥር የሚችል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሕጉ መሰረታዊ ዓላማ ያለመሆኑ ይታመናል፡፡

ሌላው በተጠቃሹ ድንጋጌ ስር የተጠቀሱት የማህበር ማፍረሻ ምክንያቶች ተዘርዝረው የተጠቀሱ ሳይሆን አመልካች በመሆናቸው በተለይ “ትክክለኛ ምክንያት” የሚለው የድንጋጌው ሃረግ ሰፊና ትርጉም የሚያሻው በመሆኑ በስራ አስኪያጆቹ ግዙፍ ጥፋት ሲፈፀም፣ስራው የሚጠይቀው ቅን ልቦና ሲጠፋ፣ የማህበሩ ገንዘብ ለግል ጥቅም ሲውል፣ለማህበሩ ገቢ መሆን የሚገባው ገንዘብ አለማድረግን የመሰሉት ምክንያቶች ከተከሰቱና የተፈጠረው ችግርም ማህበሩን ከማፍረስ ውጪ በሌላ ሁኔታ ወይም አግባብ መፍትሔ የማያገኝ መሆኑን ፍርድ ቤቱን የሚያሳምን ከሆነ ማህበሩ ሊፈርስ የሚችልበትን አግባብ የሚያሳዩ ናቸው ተብሎ ሊወሰዱ የሚችሉ ምክንያቶች ናቸው፡፡ የተወሰነ ኣላፊነት ያለው የግል ማህበር የሚፈርስባቸው ምክንያቶችም በንግድ ሕጉ በቁጥር 542 ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ እንደየ ጉዳዮቹ አግባብነት የሚቀርበውን ምክንያት መከሰቱን በማስረጃ ማረጋግጥና ስለመከሰቱ ከተረጋጋጠ ደግሞ የምክንያቱን በቂነት በአግባቡ ሊመረምር የሚገባው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ማህበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት የጠየቁት አባላት የአክስዮን መዋጮ አልከፈሉም፤ለማህበሩ ሊዋጣ የሚገባውን ገንዘብ በተመለከተ በተለያየ ጊዜ ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም አባላቱ በስምምነቱ መሰረት መዋጮ አልከፈሉም፤የከሳሽ ተከሳሽ ማህበሩ ያላቸውን 55% አብላጫ ድምጽ በመጠቀም ከተከሳሽ ከሳሽ የተለየ አቋም ስለሚይዙ ማህበርተኞች መስማማት የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፤ አመልካች ስራ አስኪያጅ እንዲሻር እና በፍርድ ቤት ክስ በማቅረባቸው ምክንያት ድርጅቱ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ በአጠቃላይ በማህበሩ አስተዳደር እና አካሄድ ዙሪያ በአባላት መካከል አለመግባባት እና ብርቱ ጭቅጭቅ ተፈጥሯል የሚሉ ምክንያቶችን መሆናቸው የስር ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ እንደሚታየው እነዚህ ምክንያቶች ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችሉ በቂና ሕጋዊ ምክንያቶች ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ አይደሉም፡፡ በአመልካች የተነሱ ምክንያቶችም ከማህበሩ መፍረስ በመለስ ባሉ እርምጃዎች እልባት ማግኘት የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የማህበሩ ሕልውና እንዲቀጥል መደረግ የሚገባው ከመሆኑ በቀር ማህበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

www.abyssinialaw.com

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.225884 ጥቅምት 15 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.205876 ጥር 29 ቀን 2010 ዓ.ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ካ/የ**

www.abyssinialaw.com

# ንብረት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር ፡-150773

ቀን፡-ግንቦት 27/2010 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች:-** አቶ ሀይሉ ኪዳኑ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ቀጭኑ ዱጉማ ጠበቃ ሙሉቀን ግዛቸው ቀረቡ

2. አቶ ተሰማ አለማየሁ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ አቅርበዉት የነበረዉ ክስ ይዘት፡- ክርክር ያስነሳዉን መሬት በ1989 ዓ.ም በዉሳኔ አግኝቼ እየተጠቀምኩበት የቆየሁ ሲሆን የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ መሬቱን በ2005 ዓ.ም ከሕግ ዉጪ ይዞ ስለሚገኝ ይልቀቅልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በበኩሉ ክርክር ያስነሳዉ መሬት በቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ዉስጥ ይገኝ የነበረ ሲሆን ወደ ኦሮሚያ ከተካለለ በኃላ በጉቶ ጊዳ ወረዳ ግብር እየከፈልኩ ስጠቀምበት የቆየሁት በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ መብት የሌለዉ በመሆኑ ክስ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየዉ የጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት የግራቀችን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን መሬት ለ1ኛ ተጠሪ እንዲለቅ ወስኖ የነበረ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዉን በመሻር አመልካች መሬቱን በኮንትራት ወስጀበታለሁ የሚለዉ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ካደረገ በኃላ የመሬቱ ባለይዞታ ማን እንደሆነና በምን መልኩ በአመልካች እጅ እንደገባ አጣርቶ ተገቢዉን እንዲወስን በነጥብ መልሶለታል፡፡

2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ በሰጠዉ መልስ ክርክር ያስነሳዉን መሬት ከ1ኛ ተጠሪ በኮንትራት ለ5 ዓመት ወስጄ በመሃል ስታመም ለአመልካች ለ10 ዓመት በኮንትራት የሰጡት እንጂ የአመልካች አይደለም በማለት 1ኛ ተጠሪን በመደገፍ ተከራክሯል፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤት ክርክርና ማስረጃዉን መርምሮ 1ኛ ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ በእጁ አድርጎ ሲያዝበት የነበረ ይዞታዉ ለመሆኑ አላስረዳም በማለት ክስ ለማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) መሰረት መብት የለዉም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተዉ የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀችን ካከራከረ በኃላ መርምሮ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን መሬት ከ2ኛ ተጠሪ ለ15 ዓመት በኮንትራት ወስጄ የያዝኩት ነዉ በማለት የተከራከረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ መሬቱን ከ1ኛ ተጠሪ በኮንትራት ወስጄ ለአመልካች በኮንትራት ሰጠሁኝ ያለ በመሆኑ፤ እንዲሁም በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 መሠረት የኪራይ ዉሉ በሚመለከተዉ አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ አመልካች መሬቱን ለ1ኛ ተጠሪ ይልቀቅ በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የአሁኑ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ኮንትራት የሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በሌለበት

www.abyssinialaw.com

እና መሬቱን በ01/09/1998 ዓ.ም በተጻፈ የኮንትራት ዉል ከ2ኛ ተጠሪ ተከራይቼ ስጠቀምበት የቆየሁ ስለሆነ ለመክሰስ መብት የነበረዉ 2ኛ ተጠሪ እንጂ 1ኛ ተጠሪ አይደለም። 1ኛ ተጠሪ ይችላል ቢባል እንኳ ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ አልፈዉ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ። 2ኛ ተጠሪ ይዞታዉ የራሱ መሆኑን ገልጾ አከራየኝ እንጂ ጠያቂ ሲመጣ መሬቱን እንደምለቅ ባልተዋዋልኩበት እንድለቅ መወሰኑ ስህተት ነዉ። ይዞታዉ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት መሬቱን ልቀቅ መባሌ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ።

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል በተነሳዉ የገጠር እርሻ መሬት ጉዳይ የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮንትራት ዉሉ ከ1999 ዓ.ም በፊት መፈጸሙ እየታወቀ የክልሉን የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 በመጥቀስ ዉሉ ባለመመዝገቡ ፈራሽ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ ክርክራቸዉን በጽሁፍ አቅርበዋል።

1ኛ ተጠሪ በሰበር መልሳቸዉ ያቀረቡት ክርክር ይዘት፡- ክርክር ያስነሳዉ መሬት 3 ሄክታር የአርሶ አደር የእርሻ መሬት መሆኑ ተረጋግጦ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 መሠረት ለዚህን ያህል ጊዜ የአርሶ አደር መሬት ማከራየት አይቻልም ተብሎ አመልካች መሬቱን እንዲለቅ መወሰኑ ተገቢ ነዉ። በአካባቢዉ ባለመኖሬ እስክመለስ እንዲጠቀምበት ለ2ኛ ተጠሪ ሰጠሁት እንጂ ለሌላ 3ኛ ወገን እንዲያከራይ ባለመሆኑ የኪራይ ዉሉ አይጸናም። አመልካች መሬቱን በዉል የያዘና የያዘዉም በ1998 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተገቢነት የለዉም በማለት ተከራክሯል። 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ የ1ኛ ተጠሪን ክርክር በመደገፍ መልስ አቅርቧል።

የግራቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል። መርምረን እንደተረዳነዉ ግራቀኙን ያከራከረዉ ይዞታ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ግንቦት 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የኪራይ ዉል ለ15 ዓመት ተከራይቶ የያዘዉ መሆኑን የገለጸ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ መሬቱ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን አረጋግጦ ለ5 ዓመት ተከራይቶ በመታመሙ ምክንያት ለአመልካች ለ15 ዓመት ማከራየቱንና መሬቱ ለ1ኛ ተጠሪ

ሊመለስለት እንደሚገባ ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ክርክር ያስነሳዉን መሬት ለተጠሪ ሊለቅ ይገባል በማለት ሲወስን የሰጠዉ ምክንያት አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ግንቦት 01 ቀን 98 ዓ.ም ያደረጉት የኪራይ ዉሉ፤ የመሬት ኪራይ ዉልን ለመመዝገብ ስልጣን ባለዉ አካል አልተመዘገበም በሚል ነዉ፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉና የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ፤ የኪራይ ዉሉ ከ1999 ዓ.ም በፊት የተደረገ ሆኖ ሳለ አዋጅ ቁጥር 130/99 በመጥቀስ ዉሉ ባለመመዝገቡ ፈራሽ ነዉ መባሉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 10(2 እና 3) መሠረት በባህላዊ መንገድ የሚታረስ መሬትን በዉል ማከራየት የሚችለዉ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ ዉሉም ዋጋ የሚኖረዉ በክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ተመዝግቦ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑ የተመለከተ ሲሆን ይህ አዋጅ ከመደንገጉ በፊት ሥራ ላይ የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 56/94 አንቀጽ 11(2 እና 4) ስር በተመሳሳይ በባህላዊ መንገድ የሚለማን መሬት አርሶ አደሩ ማከራየት የሚችለዉ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ በአካባቢዉ መሬትን ለማስተዳደር ስልጣን ባለዉ አካል ሲረጋገጥ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ አዋጆች ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ አዋጅ ቁጥር 130/99 ከመዉጣቱ በፊትም ሆነ በኃላ አርሶ አደሩ በባህላዊ መንገድ የሚያለማዉን መሬት ማከራየት የሚችለዉ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ ዉሉ ዋጋ እንዲኖረዉ በሚመለከተዉ አካል ተመዝግቦ መረጋገጥ የሚገባዉ መሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን መሬት ለ15 ዓመት ከ2ኛ ተጠሪ ተከራየሁ ከማለቱም በላይ የኪራይ ዉሉ በሚመለከተዉ አካል ያልተመዘገበና ያልተረጋገጠ ነዉ፡፡ ይህ ዉል በአዋጅ ቁጥር 56/94 አንቀጽ 11(2 እና 4) ሆነ አሁን ሥራ ላይ ባለዉ አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 11(2 እና 3) መሠረት ሕጋዊ ዉጤት የሌለዉ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪን ሊያስገድድ የሚችል አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ለ5 ዓመት ተከራየሁት የሚለዉን መሬት በሌለዉ መብት ለ15 ዓመት ሊያከራይ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ከዚህ አንጻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ መሬቱን ይልቀቅ ብሎ መወሰኑም ሆነ በየደረጃዉ ጉዳዩን የተመለከቱት ፍ/ቤቶች ይህንኑ ዉሳኔ ማጽናታቸዉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

ሲጠቃለል አመልካች ክርክር ያስነሳዉን የገጠር መሬት ለ1ኛ ተጠሪ እንዲለቅ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ ዉሳኔዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45979 ጥቅምት 27 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 213383 ሕዳር 13 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 274283 ሕዳር 27 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠዉ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በጉቱ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረዉ አፈጻጸም ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ችሎት የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/134343

ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡1ኛ/አቶ ቴዎድሮስ ዉብሸት

2ኛ/ወ/ሮ ፍሬህይወት ዉብሸት

3ኛ/አቶ ሚካኤል ዉብሸት

ተጠሪዎች፡ 1ኛ/የአዳማ ከተማ ቀበሌ 06 መስተዳድር ጽ/ቤት

2ኛ/አቶ ሙከሚል ከሊል

3ኛ/ወ/ሮ ዓለም ሃጎስ

4ኛ/ወ/ሮ አይሻ ከድር

5ኛ/አቶ ሻምበል ሃይሉ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በዉርስ የተላለፈ የከተማ ይዞታና ቤት ከመንግስት ቤት ጋር ተቀላቅሎ ስለሚገኝ የመንግስት ቤት ፈርሶ ለአጠቃቀም በሚያመች አኳኋን ይዞታዉ ስፋት ተስተካክሎ የይዞታ ማረጋገጫ ለወራሾች እንዲሰጥ የቀረበ የዳኝነት

ጥያቄ የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ ጉዳይ ከሳሾች የአሁኖቹ አመልካቾች ሲሆኑ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ከ2-5 ያሉት ተጠሪዎች ጣልቃ ገብ በመሆኑ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች ክስ ይዘት ባጭሩ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 06 ዉስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 233.06 የሆነ መኖርያ ቤት ይዞታ ስፋቱ 101 ካ.ሜ ከአያታቸዉ ከወ/ሮ ፀሐይ ካሳ በስጦታ የተላለፈላቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ይዞታዉና ቤቱ ከመንግስት ቤት ጋር ተቀላቅሎ ስለሚገኝ ለ1ኛ ተጠሪ ጉዳዩ በአቤቱታ ቀርቦ ቃለ ጉባኤ ተይዞ የመንግስት ቤት ፈርሶ ይዞታዉ ሰፍቶ ከፊሉ ለመንገድ እንዲሆን ሌላዉ ለአመልካቾች ይዞታ ተጨምሮ 260 ካ.ሜ ሆኖ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጥ ስለተወሰነ በዚሁ መሰረት እንዲፈጸም ዉሳኔ እንዲሰጥ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ የከተማ መሬት የማስተዳደርና የመቆጣጠር ስልጣን የአዳማ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ኤጀንሲ እንጂ የተከሳሹ ባለመሆኑ ስልጣን በሌላቸዉ የቀበሌዉ አመራሮች የተሰጠ ዉሳኔ ወይም ቃለጉባኤ ተፈጻሚነት እንደሌለዉ፣አመልካቾች እንዲፈርስ የጠየቁት የመንግስት ቤት የማስተዳደር ስልጣን የመንግስት ቤቶች አስተዳደር አካል በመሆኑና የሌሎችን መብትና ጥቅም የሚመለከት ስለሆነ ተቀባይነት እንደሌለዉ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ከ2-5ኛ ላሉት ተጠሪዎች ከመንግስት ቤቶቹን ተከራይተዉ የሚኖሩበት መሆናቸዉን ገልጸዉ ክርክሩ መብታቸዉን የሚመለከት በመሆኑ ወደ ክርክር በጣልቃ ገብነት ገብተዉ ቤቶቹ እንዲፈርሱ ዉሳኔ ሊሰጥ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካቾች በንብረታቸዉ የመገልገል ህገ መንግስታዊ መብት እንዳላቸዉ እና ይዞታቸዉ ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ ችግሩ እንዲፈታ በቀበሌ አመራር ኮሚቴ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረት የመንግስት ቤቶች እንዲፈርሱና ለአመልካቾች ይዞታ ተጨምሮ በ260 ካ.ሜ ይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ የቀበሌ ቤት ለሚፈርስባቸዉ ሰዎች መስተዳድሩ መፍትሔ እንዲሰጥ የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ለአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ በማቅረባቸዉ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ጉዳዩ የከተማ መሬት ይዞታ ላይ መሬት እንዲሰጥ እና ይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጥ የሚል ከመሆኑ አኳያ ይህም

የከተማዉ እስታንዳርድና ማስተር ፕላን ጋር የሚታይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የመወሰን ስልጣን የለዉም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር ተጠሪዎችን አሰናብቷል፡፡አመልካቾች ለኦሮሚያ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባቀረቡት ይግባኝ ላይ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የአመልካቾች ጥያቄ ፍትህ የማግኘት መብት ጥያቄ ነዉ በሚል አስተዳደሩ ባለዉ መመሪያ መሰረት ይዞታ ተስተካክሎ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ በወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በከፍተኛዉ ፍርድ ቤት መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት የከፍተኛዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡በዚህ ዉሳኔ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ በማቅረባቸዉ ሰበር ችሎቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በቀበሌዉ ኮሚቴ በ15/12/06 ዓ.ም የተያዘዉ ቃለጉባኤ አስተዳደራዊ መፍትኄ የሚያመለክት እንጂ በቀጥታ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚፈጸም ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ተቀብለዉ በቃለ ጉባኤ መሰረት ይፈጸም በማለት የሰጡት ዉሳኔ የህግ መሰረት የለዉም በማለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ በሰበር ችሎቱ ተሽሯል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸዉ ይዘት ባጭሩ ጉዳዩ አዲስ ማስረጃ ጥያቄ ሳይሆን በእጃችን ያለዉ ይዞታ በመመሪያዉ መሰረት ይካፈልልን የሚል የፍትህ ጥያቄ ስለሆነ ፍርድ ቤት ማየት አይችልም መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም የሚል ሲሆን አቤቱታቸዉ ተመርምሮ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ማየት አይችሉም በማለት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሻሩ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በ1ኛ ተጠሪ ወኪል በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በሰበር ችሎቱ የተያዘዉ ጭብጥ ላይ ሰበር ችሎቱ የሚወስነዉ ሆኖ የአመልካቾች ይዞታ ከቀበሌ ቤት ጋር ሳይቀላቀል ማስረጃ ቢሰጣቸዉ ተቃዉም እንደሌለዉ ገልጸዋል፡፡ከ2–5 ያሉትን ተጠሪዎች በጠበቃቸዉ አማካኝነት የሰጡት መልስ የአመልካቾች ጥያቄ የቀበሌ ቤትና ይዞታ ተጨምሮ ይዞታ ተስተካክሎ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ የሚል ስለሆነ በዚህ ጉዳይ የመወሰን ስልጣን የአዳማ ከተማ መስተዳድር ስለመሆኑ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ተከራክረዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የጉዳዩ አመጣጥና ግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ከአያታቸዉ በዉርስ ያገኙት የቤት ቁ/233.06 በ101 ካ.ሜ ላይ ያረፈ ቤት ከመንግስት ቤት ጋር የተቀላቀለ ስለሆነ ካርታና ፕላን ማሰራት እንዳልቻሉ ጠቅሰዉ ተቀላቅሎ የሚገኘዉ የመንግስት ቤት ፈርሶ ይዞታቸዉ ላይ 157 ካ/ሜ ተጨምሮ በ260 ካ.ሜ ይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ ነዉ፡፡ለዚህም መነሻ የደረጉት የ1ኛ ተጠሪ በኮሚቴ ጉዳዩን አይቶ ቃለጉባዔ ይዞ ዉሳኔ ስለመስጠቱ ነዉ፡፡ይህን ቃለጉባኤ አስመልክቶ በአንድ በኩል ቀጥታ ፍርድ ቤት ክስ ለማቅብ የሚያስችል መብት የሚሰጥ ነዉ ወይስ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ሀሳብ ሆኖ በሚመለከታቸዉ የአስተዳደር አካላት ተቀባይነት ሲያገኝ የሚፈጸም ነዉ የሚል ጥያቄ የተነሳበት በሌላ በኩል ደግሞ የቀበሌ ቤት እንዲፈርስ እና ለአመልካቾች ተጨማሪ ይዞታ እንዲሰጥ የቀበሌዉ ኮሚቴ ተፈጻሚነት ያለዉ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉ የህግ መሰረት አለዉ ወይ የሚለዉ መሰረታዊ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ስለሆነም እነዚህ አስተዳደራዊ መዋቀር እና ስልጣን ተከትሎ መፍትሄ ወይም ምላሽ የሚያገኙ ሆኖ አመልካቾች የጠየቁት ዳኝነት በፍርድ ቤት ዉሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ነዉ የሚለዉ መመርመር ተገቢ ነዉ፡፡

በመሰረቱ የዳኝነት ስልጣን ከህግ የሚመነጭ መሆኑ ልብ ይለዋል፡፡በሌላ በኩል ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሰልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለዉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንገስት አንቀጽ 37/1/ በግልጽ ደንግጓል፡፡ከዚህ አንጻር አመልካቾች በፍርድ በዳኝነት አካል ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት በማቅረብ ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት ያላቸዉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም ፡፡በዚህ መዝገብ የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የአመልካቾች ጥያቄ በዉርስ ያገኙት ቤትና ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ የማግኘት መብት ተነፍገዉ ሳይሆን ይዞታቸዉ 101 ካ/ሜ ብቻ በመሆኑ በዚህ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ማሰራት ባለመቻሉና ለአጠቃቀም አመቺ ባለመሆኑ ተቀላቅሎ ያለዉ የቀበሌ ቤት እንዲፈረስና ተጨማሪ ይዞታ ተሰጥቶአቸዉ በ260 ካ.ሜ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ እንዲወሰን የሚል ነዉ፡፡ በዚህ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ከመስጠቱ በፊት መብትና ጥቅም ያላቸዉ ወገኖች እንዲሁም የከተማ መሬት

www.abyssinialaw.com

ይዞታ አጠቃቀም ላይ የመወሰን ስልጣን በህግ ስልጣን የተሰጣቸዉ የአስተዳደር አካላት ዉሳኔ አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል፡፡በተለይም የክልሉ ከተማ መሬት አስተዳደር አካል በአዋጅ ቁ/179/05 አንቀጽ 8 በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት እንዲሁም እንዲፈርሱ እየተባለ ያለዉ የቀበሌ ቤት የሚያስተዳድረዉ አካል እና በቤቱ ዉስጥ የሚኖሩት ሰዎች እጣፈንታ በሚመለከት ስልጣን በተሰጠዉ አካል ባልተወሰነበት ሁኔታ የአመልካቾችን ጥያቄ ብቻ መሰረት በማድረግ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉ የህግ መሰረት የለዉም ፡፡ አመልካቾች በጉዳዩ ላይ አስተዳደራዊ መፍትሄ ከሚመለከታቸዉ አካላት መጠየቅና ማስወሰን እየተገባቸዉ በአስተዳደር አካል ያልተረጋገጠ መብት ይዘዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲሰጣአቸዉ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በማለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1ኛ /የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ/233806 ላይ በ14/02/09 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

ሰበር መ/ቁ159414

ታህሳስ 22 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡አቶ ሚሬሳ ኦብሳ

ተጠሪ፡ አቶ ፍቃዱ ደበሎ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ድንበር ተላልፎ የተሰራ ግንባታ የሚመለከት ነዉ፡፡በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡የተጠሪ ክስ ይዘት ባጭሩ አመልካች ከወሰን 50ሳ.ሜ በመራቅ ቤቱን መገንባት ሲገባዉ 75.ሳ.ሜ ወደ ተጠሪ አስጠግቶ ግድግዳ በማቆሙ የቤቱ ፍሳሽ ወደ ተጠሪ ግድግዳ እየፈሰሰ የተጠሪን ግድግዳ አበላሽቷል በሚል አመልካች ግንባታዉን እንዲያፈርስ እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በራሱ ይዞታ ላይ እንጂ በተጠሪ ይዞታ ላይ ግንባታ እንዳላደረገ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ክርክሩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የጎቡ ሰዮ ወረዳ ፍ/ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶ በተጠሪ በኩል ከቀረቡት ምስክሮች ሁለቱ አመልካች ድንበር አልፎ የሰራዉ ቤት ፍሳሽ የተጠሪ ግድግዳ ላይ የሚፈስ ስለመሆኑ ሲመሰክሩ ሁለት ምስክሮች ማን ድንበር እንዳለፈ እንደማያዉቁ መስክረዋል፡፡በአመልካች በኩል የቀረቡት

ምስክሮች አመልካች ድንበር አላለፈም በመካከላቸዉም 1ሜትር ክፍት ቦታ አለ በማለት በመመስከራቸዉ ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ አወሳሰን እንዲረዳ በባለሙያ ታይቶ ዉጤት እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ የወረዳዉ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ባለሙያ አጣርቶ አመልካች ወደ ተጠሪ ይዞታ 9ሳ.ሜ በ13ሜ በማለፍ የገነባዉ ቆርቆሮ ፍሳሽ በተጠሪ ግድግዳ ላይ እየፈሰሰ ጉዳት ማድረሱን መግለጫ በመስጠቱ አመልካች ወሰን አልፎ የሰራዉን እንዲያፈርስና በባለሙያ ተለክቶ1ሜ.በመራቅ እንዲገነባ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የግራቀኙ ምስክሮች ቃል ሲታይ የአመልካች ምስክሮች አመልካች ድንበር አለማለፉን ስለመመስከራቸዉ እና በባለሙያ ተለክቶ ከቀረበዉ ሪፖርት ይዘት ባላገናዘበ ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት አመልካች1ሜ.ገብቶ እንዲገነባ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በተጠሪ ከተጠየቀዉ ዳኝነት ዉጪ ነዉ በሚል ምክንያት ዉሳኔዉ እንዲታረም ጠይቋል፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ  የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በተጠሪ በኩል በተጠየቀዉ ዳኝነት መሰረት የተወሰነ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በከተማ ፕላን መሰረት በመኖሪያ ቤት መካከል ያለዉ ርቀት 50ሳ.ሜ መሆኑ የሚታወቅ ስለመሆኑና አመልካች 75ሳ.ሜ ወደ ተጠሪ ግድግዳ ተጠግቶ በመስራቱ በድምሩ ከ1ሜ በላይ ስለሚሆን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች በመልስ መልሱ ላይ ክርክር የተነሳበት ይዞታ የገጠር መንደር ስለሆነ በከተማ ፕላን መሰረት ሊታይ አይገባም በማለት የተጠሪ ክርክር ዉድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ይዘት ከላይ ባጭሩ ከላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን እንደመረመርነዉ አመልካችና ተጠሪ በይዞታቸዉ በድንበር የሚዋሰኑ መሆኑ አከራካሪ አይደለም ፡፡ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ ከአመልካች በሚዋሰንበት

በምስራቅ በኩል አመልካች 50ሳ.ሜ ወደ ራሱ ይዞታ ገብቶ ግንባታ ማድረግ እየተገባዉ 75ሳ.ሜ ወደ ተጠሪ ይዞታ ገብቶ በመገንባቱ ከአመልካች ቆርቆሮ ጣሪያ ላይ የሚፈሰዉ ፍሳሽ በተጠሪ ግድግዳ ላይ እየፈሰሰ ጉዳት ስላደረሰ ይህንኑ እንዲያፈርስ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች ወደ ተጠሪ ይዞታ አልገባሁም በማለት የተከራከረ ቢሆንም ከግራቀኙ ምስክሮች ቃል ባሻገር የባለሙያ መግለጫ እንዳረጋገጠዉ አመልካች 9ሳ.ሜ ስፋት በ13ሜትር ቁመት ወደ ተጠሪ ይዞታ ገብቶ የገነባ ስለመሆኑና ከቤቱ ጣሪያ የሚወርደዉ ፍሳሽ  የተጠሪ ግድግዳ ላይ እንደሚፈስና ጉዳት እንዳደረሰ ተገልጧል፡፡

ግራቀኙ የሚከራከሩበት ይዞታ የገጠር መሬት ይዞታ ሆኖ የመኖሪያ መንደር ላይ የተገነባ ቤት ወሰን አጠቃቀም የሚመለከት ስለመሆኑ ከክርክሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ስለሆነም ክርክር የተነሳበት ይዞታና ቤት የሚገኝበት ቦታ በከተማ አስተዳደር የተዋቀረ ባለመሆኑ ጉዳዩ በከተማ አስተዳደር ፕላን መሰረት የሚታይ ባይሆንም በፍ/ብ/ህጉ ስለንብረት አጠቃቀም መብትና ግደታዎች የተደነገገዉን ተመርኩዞ እልባት መስጠት የሚገባ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡በዚሁ አግባብ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1204 እና 1205 ላይ እንደተደነገገዉ ባለሀብቱ ሀብቱን በሚገባ ለመገልገል ሰፊ መብት ያለዉ ቢሆንም በህግ የተጣሉ ገደቦች እንደተጠበቁ ስለመሆኑ ያሥገነዝባል፡፡ከእነዚህ ገደቦች አንዱ በፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 1225/1/ ላይ እንደተመለከተዉ ባለሀብቱ በሀብቱ በሚገለገልበት ጊዜ የጎረቤቱ ርስት ጥቅም የሚቀንስበትን ወይም የሚጎዳበትን ማንኛዉንም ከመጠን ያለፈ ነገር ከመስራት መጠበቅ እንደሚገባ ያስገድዳል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ወሰን በማለፍ ከገነባዉ ቤት ቆርቆሮ /ጣሪያ/ ላይ የሚፈሰዉ ፍሳሽ የተጠሪ ግድግዳ ላይ እየፈሰሰ ጉዳት ማድረሱ በስር ፍርድ ቤት በባለሙያ ታይቶ የተረጋገጠ ስለመሆኑ መዝገቡ ያሥረዳል፡፡ስለሆነም ይህ የአመልካች ድርጊት የተጠሪ ንብረት አጠቃቀም ላይ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የህግ መሰረት ያለዉ ነዉ፡፡ከዚህ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ተጠሪ የጠየቀዉ ዳኝነት እና በማስረጃ የተረጋገጠዉን መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡በመሰረቱ ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባዉ ከሳሽ ወገን በግልጽ ዳኝነት በጠየቀበት አግባብ እና በተከሳሽ እምነት ወይም በማስረጃ  በተረጋገጠ ልክ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ስ/ስ ህግ አንቀጽ 182፣224፣234፣242 እና 273 ድንጋጌዎች

www.abyssinialaw.com

ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ስለሆነም በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ክርክር ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ አመልካች 75 ሳ/ሜ ወደ ተጠሪ ይዞታ ገብቶ የደረገዉን ግንባታ እንዲያፈርስ በሚል ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች ወደ ተጠሪ ይዞታ አልገባሁም በሚል የተከራከረ ሲሆን አመልካች በራሱ ይዞታ ላይ የገነባዉ ቤት ጣሪያ ወደ ተጠሪ ይዞታ ወሰን አልፎ የገባዉ 9ሳ.ሜ ስፋት በ13ሜ.ቁመት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ በዚሁ ልክ ዉሳኔ መስጠት እየተገባ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ቤቱን አፍርሶ አንድ ሜትር ገብቶ እንዲሰራ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ በተጠሪዉ ከተጠየቀዉ ዳኝነት ወጪ በመሆኑና ከፍ/ብ/ስ/ስ ህግ አንቀጽ 182/1/ድንጋጌ የሚጻረር በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/የጎቡ ሳዮ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ11244 ላይ በ26/03/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ ይህንኑ በማጽናት የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተል በመ/ቁ 46059 እና 277027 ላይ የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/አመልካች የተጠሪ ይዞታ ላይ ወሰን አልፎ የሰራዉ ቤት 9ሳ.ሜ.ስፋት በ13ሜ.ቁመት ያለአግባብ ወደ ተጠሪ ይዞታ የገባ ስለመሆኑ በባለሙያ በተረጋገጠዉ መሰረት ባለሙያ ባለበት ተለክቶ በዚሁ ልክ ወሰኑን ያለፈዉን ግንባታ እንዲያፈርስ በማለት ወስነናል፡፡

3ኛ/በዚህ ችሎት ተሻሽሎ በተወሰነዉ መሰረት እንዲያስፈጽም ለጎቡ ሳዮ ወረዳዉ ፍ/ቤት ግልባጭ ይተላለፍ ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

4ኛ/በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 158899

**ቀን** - 26/03/2011

**ዳኞች**:-ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች**:- አቶ ክብሮም አደራ -- ጠበቃ አስቻለው ሽፈራው ቀርበዋል

**ተጠሪ**:- 1. ወ/ሪት ትዕግስት መንገሻ --- ጠበቃ ኑር ሠይድ

2. አቶ አክሊሉ ወልዱ ---- ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በህግ የተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ሳይጠናቀቅ የተደረገ የኮንዶምንየም ቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ በሚል የቀረበን ክስ መነሻ በማድረግ የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በቅደም ተከተል 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 21/10/2008 ዓ.ም አዘጋጅታ ያቀረበችዉ ክስ ይዘትም በአጭሩ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከተማ ሰሚት ሳይት ከመንግስት ያገኘሁትን የኮንዶሚኒየም ቤት 1ኛ ተከሳሽ ወኪሌ ከነበረዉ 2ኛ ተከሳሽ ግንቦት 05 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገ ዉል የገዛሁት ነዉ በማለት ወደ ስሙ እንዲዞር ክስ መስርቶብኛል፤ ይሁንና የአዲስ አበባ ከተማ

www.abyssinialaw.com

ባወጣዉ አዋጅ ቁጥር 19/97 መሠረት አምስት ዓመት ሳይሞላዉ የተደረገ በመሆኑ ምክንያት የሽያጭ ዉሉ የህግ ተቃራኒ ነዉ ተብሎ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ። አመልካች በበኩሉ ዕጣዉ የደረሰዉ ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ሆኖ የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ አምስት ዓመት ካለፈዉ በኋላ ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ ዉሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል። 2ኛ ተጠሪም አመልካች ካቀረበዉ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ክርክር በማቅረብ ተከራክሯል።

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የኮንዶሚኒየም ቤት የደረሰዉ ሰዉ በሽያጭ ማስተላለፍ የሚችለዉ ቤቱን ከገዛ (በዕጣ ካገኘ) በኋላ አምስት ዓመት ሲሞላዉ ስለመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 65140 ላይ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ጊዜዉ መቁጠር የሚጀምረዉ ዕጣዉ ከደረሰ በኋላ መሆኑን፤ በዚህም መሠረት ለ1ኛ ተጠሪ ዕጣዉ የደረሰዉ ሚያዝያ 20/2002 ዓ.ም ሲሆን፣ የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ ደግሞ ግንቦት 25/2007 ዓ.ም በመሆኑ ዉሉ የህግ ተቃራኒ ነዉ ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል። ይግባኙ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዛችዉ ነሐሴ 28 ቀን 2002 ዓ.ም ሲሆን፣ የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ በአ/አበባ ከ/አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 19/97 ዓ.ም መሠረት የአምስት ዓመት ጊዜ ያልተጠናቀቀ መሆኑን፣ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዋቢነት የጠቀሰዉ የሰበር ዉሳኔም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ መሆኑን ጠቅሶ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠን ዉሳኔ በመሻር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የሽያጭ ዉል ፈርሶ ግራ ቀኙ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል። አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም።

አመልካች በቀን 22/09/2010 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበዉ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል። አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል

በመባሉም ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ 1ኛ ተጠሪ ላቀረበችዉ የዉል ይፍረስልኝ ዳኝነት ጥያቄ መሠረት ያደረገችዉ ቤቱን የገዛችዉ ነሀሴ 28/2002 ዓ.ም ሲሆን የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ ግን ግንቦት 25/2007 ዓ.ም በመሆኑ በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 19/97 መሠረት አምስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ የተደረገ መሆኑን ሲሆን፤ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ዉሉ የተደረገዉ አምስት ዓመት ከሞላዉ በኋላ ነዉ በማለት የሚከራከሩት ቀኑ የሚቆጠረዉ ቤቱ በዕጣ ለ1ኛ ተጠሪ ከደረሰበት ከሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ እንጂ ዉሉ ከተደረገበት ከነሐሴ 28/2002 ዓ.ም ጀምሮ አለመሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ዕጣዉ ለ1ኛ ተጠሪ የደረሰዉ ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ሲሆን፣ ከመንግስት ጋር ዉል የተደረገዉ ነሐሴ 28/2002 ዓ.ም በመሆኑ ላይ ግራ ቀኝ ክርክር የላቸዉም፡፡ በመሆኑም ይህ የአምስት ዓመት ጊዜ የሚቆጠረዉ ዕጣዉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ነዉ? ወይስ ዕጣዉ የደረሰዉ ሰዉ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ስምምነት ካደረገበት ቀን ጀምሮ ነዉ? የሚለዉ እልባት የሚያስፈልገዉ ጭብጥ ነዉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 19/97 የኮንዶሚኒየም ቤት የደረሰዉ ሰዉ ለ3ኛ ወገን በሽያጭ ሊያስተላልፍ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት ገዥዉ ጠቅላላ ዋጋዉን ከፍሎ ቢያጠናቅቅም፣ ቤቱን ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለዉ ቤቱን ከገዛ አምስት ዓመት ሲሞላዉ ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 14(2) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ይሁንና የቤት ግዥ ተፈጽሟል ሊባል የሚችለዉ ዕጣዉ ከወጣ በኋላ ነዉ ወይስ ዕጣዉን ተከትሎ ከሚመለከተዉ የአስተዳደሩ አካል ጋር ዉል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ ለሚለዉ ጥያቄ አዋጁ ምላሽ አይሰጥም፡፡ በመሆኑም ቤት ፈላጊዎችን ስለ መመዝገብ እና ቤቶችን ለቤት ፈላጊዎች

ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ በአዋጁ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት መወሰኑ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ቤት ፈላጊዎችን በአዋጁ በተመለከተዉ አግባብ ለይቶ ከመዘገበ በኂላ የከተማዉን አስተዳደር ቤቶች ለቤት ፈላጊዎች ስለሚያስተላልፍበት ሁኔታ አዋጁ በአንቀጽ 6 እና 7 ስር ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የማስተላለፊያ መንገዶች ሁለት ሲሆኑ፣ የመጀመሪያዉ የቅድሚያ መብትን ከማግኘት ጋር በተያያዘ በአዋጁ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ለሚያሟሉት ሰዎች ቅድሚያ በመስጠት ሲሆን፤ ሁለተኛዉ በዕጣ ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 6 እና 7(6-ለ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይም የአዋጁ አንቀጽ 7(6-ለ) "ኤጀንሲዉ ዕጣ አወጥቶ የሚገዛዉን ቤት ከለየ ቤት ፈላጊ ጋር ባዘጋጀዉ ዉል መሠረት እንዲፈራረም ለጽ/ቤቱ ወይም በሚፈረም መሠረታዊ ዉል መሠረት ለሌላ አግባብ ላለዉ አካል ዉክልና ይሰጣል" በማለት ይደነግጋል፡፡ በአጠቃላይ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለዉ፣ ዕጣ ከከተማዉ አስተዳደር ጋር የቤት ግዥ ዉል ለማድረግ መብት የሚሰጥ እንጂ እራሱ የቤት ግዥ ዉል አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም አልፎ የአዋጁ አንቀጽ 7(11) ድንጋጌ፣ ቤት ግዥ ቅድሚያ ክፍያ ፈጽሞ የቤት ሽያጭ ዉል ከተፈራረመ በኂላ ለአበዳሪ ተቋም በዋስትና አስይዞ የቤቱ መግዣ ቀሪ ገንዘብ በተመለከተ ከአበዳሪ ተቋም ጋር ዉል እንደሚያደርግ ሲያመለክት፤ የአዋጁ አንቀጽ 9 የቤት ግዥ ዉል ከመፈረሙ በፊት ቤት ገዥዉ የቅድሚያ ክፍያ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በእነዚህ ሁለቱ ድንጋዎች ስር "የቤት ሽያጭ ዉል ከተፈራረመ" እንዲሁም "የቤት ግዥ ዉል" በሚል ከተገለጹት ሐረጎች መረዳት የሚቻለዉም፣ አንድ ሰዉ የኮንዶሚኒየም ግዥ ፈጽሟል ሊባል የሚችለዉ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ስምምነት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 14(2) ስር ገዥዉ ቤቱን ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለዉ ቤቱን ከገዛ 5 ዓመት ሲሞላዉ ነዉ በሚል የተቀመጠዉ ጊዜ የሚቆጠረዉ ዕጣ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን፣ ገዥዉ የቤት ሽያጭ ዉል ከሚመለከተዉ የመንግስት አካል ጋር ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ ነዉ ማለት ነዉ፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ በአዋጁ የተመለከተዉ የአምስት ዓመት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኂላ ነዉ በሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰዉ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 65140 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ

www.abyssinialaw.com

በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይሁንና ሰበር ሰሚዉ ችሎት በተጠቃሹ መዝገብ ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ "ዉሉ ከተደረገበት ጊዜ" ካለ በኂላ በቅንፍ ዉስጥ "ዕጣ ከደረሰበት ጊዜ" ጀምሮ ያለ ቢሆንም፣ ጊዜዉ የሚቆጠረዉ ዉሉ ከተደረገበት ጊዜ ነዉ ወይስ ዕጣ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ነዉ የሚለዉን ነጥብ በጭብጥነት ይዞ ተገቢዉን ትንታኔ አልሰጠበትም፡፡ በመሆኑም ችሎቱ በአዋጁ አንቀጽ 14(2) ስር የተመለከተዉ የአምስት ጊዜ የሚቆጠረዉ ዕጣዉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 መሠረት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የኮንዶሚኒየም ሽያጭ ዉል የተደረገዉ በአዋጁ አንቀጽ 14(2) ስር የተመለከተዉ የአምስት ዓመት ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ነዉ በሚል ምክንያት ሊፈርስ የሚገባዉ ነዉ በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ፣ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 194652 በቀን 30/06/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 156961 ላይ በቀን 09/09/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰበር መዝገብ ቁጥር 155664

ጥቅምት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ኮ/ቤቶች ልማት ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡-አቶ ሻወል ወልዴ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የመንግስት ቤትን የሚመለከት ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ጉዳይ በማየት ዉሳኔ መስጠታቸዉ ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በስር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 447 የሚገኘውን የመንግስት ቤት ከተከሳሽ ላይ ከ1967 ዓ/ም በፊት የከሳሽ ወላጅ አባት አቶ ወልዴ ብራሮ ተከራይተው እንደነበሩ፤የከሳሽ አባት እና እናት በዚሁ ለክሱ ምክንያት በሆነው ቤት ውስጥ አብረው ሲኖሩ ከሳሽን ጨምሮ 7 ልጆች እንደወለዱና ከሳሽ እዚሁ አከራካሪው ቤት የሚኖር መሆኑ ቤቱን የተከራዩት አባቱ መስከረም 1 ቀን 1982 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል፡፡ከሳሽ ወላጅ አባቴ ወራሽ መሆኔን በፍ/ቤት ተወስኖ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት ከእናቴ ጋር አብሬ የምኖር ስሆን እናቴ ከወንድሞቼና እህቶቼ ጋር 2 ክፍል እኔ ደግሞ 4 ክፍል ይዘን እየኖርንበት እንገኛለን፡፡ወላጅ አባቴ በሞት ከተለየ

በኋላ የኪራይ ውሉን በእናቴ ስም በማድረግ ገንዘብ እየሰጠሁኝ ኪራይ ስከፍል ቆይቻለሁ ቤቱንም እንዳይፈርስ ብዙ ገንዘብ በማውጣት አሳድሸዋለሁ፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ እናቴ ኮንደሚኒየም ቤት ስለደረሳት ተከሳሽ በ3 ቀናት ውስጥ ቤቱን እንድናስረክብ የማናስረክብ ከሆነ ግን ቤቱ እንደሚታሸግ የሚገልፅ ማስጠንቀቅያ የሰጠን በመሆኑ ይህን ተግባር በከሳሽ ላይ ሁከት መፍጠር ስለሆነ የተፈጠሩብኝ ሁከት እንዲወገድልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል ፡፡ ተከሳሽ ለቀረበው ክስ በሰጠው መልስ ከሳሽ አከራካሪ በሆነው ቤት መብት የለውም ፡፡አከራካሪ የሆነው ቤት ህጋዊ ተከራይ ወ/ሮ ፈለቀች ቂጫ ስለሆኑ እሳቸው ኮንደሚኒየም ቤት የደረሳቸው ስለሆነ ቤቱን ለቀዋል ስለሆነም በመመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 3/2007 መሰረት ቤቱ ለመንግስት ማስረከብ ስለሚገባቸው ይህን ለማስፈፀም ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ መስጠታችን የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱንና በግራ ቀኙ የቀረበውን ማስረጃ ተመልክቶ እና አጠቃላይ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ ለከሳሽ አከራካሪው ቤት ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሁከት ተግባር ስለሆነ ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንዲሁም አቤቱታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዘውታል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 14/07/2010 ዓ/ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርቧል የአቤቱታው ይዘት፡- አከራካሪው የሆነው መኖሪያ ቤት ተከራይ የነበሩት የተጠሪ አባት ከሞቱ በኋላ ወደ ተጠሪ እናት ተላልፎ በተጠሪ እናት ስም ኪራይ ሲከፈልበት የቆየ ሲሆን የተጠሪ እናት ኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት ሲደርሳቸው ቤቱን ለአመልካች ማስረከብ ሲገባቸው ልጃቸው ለሆነው ተጠሪ እንዲኖሩበት መደረጉ እና የስር ፍርድ ቤቶችም ውሳኔ መስጠታቸው ከመመሪያው ውጪ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ መሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸውን ተለዋውጠዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ፤ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው አከራካሪው የሆነው በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 447 የሚገኘውን የመንግስት ቤት ተከራይ የነበሩት የተጠሪ ( ከሳሽ) ወላጅ አባት አቶ ወልዴ ብራሮ እንደነበሩ እሳቸው በ1982 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የኪራይ ውሉ የከሳሽ እናት ወደ ሆኑት ወ/ሮ ፈለቀች ጫካ እንደተዛወረ የኪራይ ውሉም በሳቸው ስም እንደሚከፈል ተጠሪ ከነ ቤተሰቦቹ በተጠቀሰው ቤት ውስጥ የሚኖር መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

የመንግስት ቤቶች ለማስተዳደር የወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2007 ስር እንደተመለከተው ማንኛውም የመንግስት ቤት ተከራይ የኮንደሚኒየም ቤት ባለእድል ሲሆን ቤቱን ለቆ ማስረከብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መነሻ ያደረገው ነጥብ ተጠሪ በአባታቸው በኩል የተከራይነት መብት አላቸው በማለት ሲሆን በመመሪያው እንደተጠቀሰው ወላጅ አባት ሲሞት የተከራይ መብት ወደ እናት (ሚስት) እንደሚተላለፍ የሚያሳይ ነው ፡፡ በዚህ መሰረትም የቤቱ ተከራይ የነበሩት አቶ ወልዴ ብራሮ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ባለቤታቸው የሆኑት ወ/ሮ ፈለቀች ጫካ ህጋዊ ተከራይ እና የኪራይ ገንዘቡም በስማቸው የሚከፈል መሆኑ ተጠሪ ግን ቤቱ ውስጥ መኖሩ እንጂ ከአመልካች ጋር ህጋዊ ውል ያለው ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃም ሆነ ክርክር የለም ፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 4/2009 ዓንቀፅ 15(ሐ(መ)) ውሉ ከኔ ጋር እንዲቀጥል ይደግፈኛል በማለት ሲሆን ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደቻልነው በነበረው መመሪያ መሰረት ወላጅ አባት ሲሞት የተከራይ መብት ወደ እናት (ሚስት) እንዲተላለፍ የሚፈቅድ መሆኑ ፣ በዚህ መሰረትም የቤቱ ተከራይ የነበሩት አቶ ወልዴ ብራሮ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ባለቤታቸው የሆኑት ወ/ሮ ፈለቀች ጫካ ህጋዊ ተከራይ እና የኪራይ ገንዘቡም በስማቸው የሚከፈል መሆኑ ተጠሪ ግን ቤቱ ውስጥ መኖሩ እንጂ ከአመልካች ጋር ህጋዊ ውል የሌለው መሆኑ የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 2/2010ም ሆነ ከዚሁ ከተሻሻለው መመሪያ በፊት የነበረው መመሪያ የቤት ተከራይነት መብት ለልጅ የሚተላለፈው ህጋዊ ተከራይ የሆነው ወላጅ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ እንጂ ኮንደሚኒየም ደርሶት ቤቱ ሲለቅ ባለመሆኑ በተያዘው

www.abyssinialaw.com

ጉዳይ ህጋዊ ተከራይ የነበሩት የተጠሪ እናት ወ/ሮ ፈለቀች ጫካ ኮንደሚኒየም ቤት አግኝተው ከተከራዩት ቤት ከለቀቁ ቤቱ በመመሪያው መሰረት አከራይ ለሆነው አመልካች መመለስ አለባቸው፡፡ ስለሆነም አከራካሪ የሆነውን የመንግስት ቤት ህጋዊ ተከራይ የሆኑት የተጠሪ እናት በመሆናቸው እሳቸው የኮንደሚኒየም ቤት ከደረሳቸው ከመንግስት የተከራዩት ቤት ለመንግስት የማስረከብ ግዴታ ያላቸው በመሆኑ እና ተጠሪ አከራካሪው ቤት በተመለከተ መብት ያለው መሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ አመልካች ለከሳሽ አከራካሪውን ቤት ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ህጋዊ ተግባር ነው፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሁከት ተግባር ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**ዉ ሳ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ሰበር ችሎት በመ.ቁጥር 27641 ታህሳስ 16 ቀን 2010 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በማፅናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ የሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር አይደለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/አ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 141625

ሐምሌ 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አድና መላኩ

ተጠሪ፡- የወልዲያ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ከክልሉ ፍትህ ቢሮ ፍሬህይወት አበባ-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0104064 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም ጉዳዩ በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠውን ብይን ፣የሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 19155 በቀን 27/04/2009 ዓ.ም በፍርድ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 03-16739 በ27/06/2009 ዓ/ም በትእዛዝ በማጽናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣንን የሚመለከት ሲሆን በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘትም፡- በወልዲያ ከተማ 06 ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኘውና አዋሳኙ በክሳቸው የተጠቀሰው ቦታ እንዳላቸውና በዚህ ቦታ ላይ ቤት ያላቸው፣ ባህር ዛፍና ሁለት እግር ጽድ ያፈሩ መሆኑን ይዞታውን ለረዥም ጊዜ ይዘው

በሚገኙበት ሁኔታ ተጠሪ ህግና መመሪያን መሰረት ሳያደርግ፣ ለአመልካችም 500 ካ/ሜትር ይዞታ ሳይጠብቅላቸው ቦታውን እየሸነሸነ ለግለሰቦች እየሰጠ እንደሚገኝ፣ በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት ያለምንም ምክንያት በዶዘር መጋቢት ወር 2007 ዓ/ም ያፈረሰባቸውና አቤቱታቸውን ለሚመለከተው አካል አቅርበው የሚመለከታቸው አካላት እንደማንኛውም ባለይዞታ 500 ካ/ሜትር ይዞታ ለአመልካች እንዲጠበቅላቸው አስተዳደራዊ ውሳኔ የሰጡ መሆኑንና በዚህ አግባብ እንዲወሰንላቸው ለተጠሪም ሆነ ለሚመለከተው አካል አመልክተው መፍትሔ ያላገኙ መሆኑን ገልጸው ለክሱ ምክንያት ከሆነው ነባር ይዞታ ላይ 500 ካ/ሜት እንዲጠበቅላቸው፣ ከሕግ ውጪ በዶዘር ለፈረሰባቸው ቤት ግምት ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር)፣ የባህር ዛፉና የፅዱ ግምትም እንዲከፈላቸው እንዲሁም ከ500 ካ/ሜትር በላይ ላለው ይዞታም ካሳ እንዲከፈላው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና በአዋጅ ቁጥር 455/97 መሰረት በፍርድ ቤት በቀጥታ ክስ የሚታይ ያለመሆኑን፣ አመልካች በቦታው ላይ መብት የሌላቸው መሆኑንና ሌሎች የክርክር ነጥቦችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ስልጣንን መሰረት አድርጎ የተነሳውን የተጠሪን መቃወሚያ መርምሮ አመልካች የከተማ ቦታ ይዞታን እንዲለቁ የተደረጉ በመሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በከተማ አስተዳደሩ ስር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አካል ነው እንጂ ለፍርድ ቤት አይደለም የሚል ምክንያት አስፍሮ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ክስ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ሲል በብይን የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ተገቢ ነው በማለት አጽንቶታል፡፡ በመጨረሻም አመልካች የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው በአጣሪው ችሎት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የአመልካች ክስ መሰረታዊ ይዘት ከሕግ ውጪ የተወሰደው ቦታና የወደመው ንብረት በሕጉ አግባብ ታይቶ ባለይዞታነታቸው መብት እንዲጠበቅላቸውና ለወደመው ንብረት ደግሞ ካሳ እንዲከፈል የሚያሳይ ሁኖ እያለ የክሱን መሰረታዊ ይዘት ሳይገነዘቡ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም

www.abyssinialaw.com

በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች በሕገ ወጥ መንገድ ቦታዬ ተወስዶአል፣ ንብረቴም ወድሟል በማለት ያቀረቡት ክስ በአስተዳደራዊ መልኩ ብቻ የሚታይ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና የሊዝ ደንብ ቁጥር 103/2004 በመጥቀስ የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባላመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክር ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ከነባር ይዞታቸው ውስጥ በሕጉ አግባብ ሊጠበቅላቸው የሚገባው ይዞታ መብት ያልተጠበቀላቸው መሆኑንና በይዞታው ላይ የነበሩ ንብረቶችም ኪሳራ ሳይከፈላቸው በዶዘር የወደሙባቸው መሆኑን ጠቅሰው ክስ የመሰረቱ መሆኑን፣ ተጠሪ የሚከራከረው ደግሞ ጉዳዩ ከህግ ውጪ የተያዘውን የከተማ ቦታ የማስለቀቅ ጉዳይ በመሆኑ ለተጠሪ በሕጉ ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ጉዳዩ የከተማ ቦታን ማስለቀቅ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ አካል ከሚቀርብ በስተቀር በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች በህግ የሚቋቋሙ በመሆናቸው የዳኝነት ስልጣናቸው የሚመነጨውም ከህግ ነው፡፡ የማንኛውም ፍርድ ቤት ስልጣን በህግ ተወስኖ የሚሰጥ በመሆኑ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ተቀብሎ ከማስተናገዱ በፊት ጉዳዩን /ክሱን/ ለማየት በህግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ በህግ የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረ የሚሰጥ ውሳኔ  የህግ መሰረት ያለው ነው ለማለት አይቻልም፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት ከነባር ይዞታቸው ውስጥ 500 ካ/ሜትር እንዲጠበቅላቸውና በይዞታው ላይ የነበረው ንብረትም ከሕግ ውጪ በመወደሙ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ተጠሪም ይዞታውን ከሕግ ውጪ በመያዙ መውሰዱንና አመልካች በሕግ አግባብ የያዙት ይዞታ ደግሞ

www.abyssinialaw.com

የተጠበቀላቸው መሆኑን ገልጾ ጉዳዩ የከተማ ቦታን ከማስተዳደር ስልጣኑ ጋር የተያያዘና በከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ አካል ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ ካሳን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና ይግባኝ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 11 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በከተማ አስተዳደር የከተማ መሬት ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ካለ ካሳውን አስመልክቶ የሚቀርበው ቅሬታ ለዚህ አስተዳደራዊ አካል የሚቀርብ ስለመሆኑ ሕጉ የሚደነግግ ሲሆን የከተማው አስተዳደራዊ አካል ካሳውን አስመልክቶ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ እንደሚችልም ሕጉ ደንግጎ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑም ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በአዋጁ መሰረት ይዞታው የተወሰደው ያለአግባብ ነው በሚል መሬት እንዲለቀቅ በተላለፈው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ በአዋጁ ውስጥ አልተካተተም፡፡

የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 በአንቀፅ 26(1) ስር አግባብ ያለው አካል ከቦታው ለሚነሳው ንብረት ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ የከተማ ቦታ ይዞታን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የማስለቀቅና የመረከብ ስልጣን እንደሚኖረው ሲደነግግ በተጠቃሹ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አራት ስር ደግሞ አግባብ ያለው አካል በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታ በአዋጁ አንቀጽ 27 መሰረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ በመስጠትና ካሳ መክፈል ሳያስፈልግ የሰባት ቀናት የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ስልጣን እንደሚኖረው ተመልክቶአል፡፡ የማስለቀቂያ ትዕዛዝን ወይም ማስጠንቀቂያ የሚመለከቱ አቤቱታዎች አቀራረብን በተመለከተም አዋጁ በአንቀጽ 28 ስር ያሰፈረ ሲሆን በአቤቱታዎች ላይ ስለሚኖረው ይግባኝም በአዋጁ አንቀፅ 29 ስር ሰፍሮ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 721/2004 በሕገ ወጥ መንገድ የተያዙ የከተማ ቦታዎችን እንዲለቀቁ የሚደረግበት ስርዓት በግልጽ የተመለከተ ሲሆን አግባብ ያለው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለይግባኝ ሰሚው ጉባኤው ማቅረብ እንደሚችል ሕጉ መደንገጉ ጉዳዩ በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄድበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው አካል ጉዳዩን የሚያስተናግደውም አቤቱታው በቅድሚያ መሬቱን እንዲለቅ ትዕዛዝ

www.abyssinialaw.com

ለሰጠው አካል ቀርቦ መስተናገዱ ሲረጋገጥ መሆኑን በአዋጁ የከተማ ቦታን ማስለቀቅ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ የተዘረጋው ስርዓት ያስገነዝበናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ክሱን የመሰረቱት የነባር ይዞታ ባለመብትነት እንዲጠበቅላቸውና በተጠሪ የወደመ ንብረት ካሳ እንዲከፈላቸው ሲሆን የክሳቸው መሰረታዊ ይዘት የሚያስገነዝበውም የነባር ይዞታ መብትን የሚመለከቱ ህጎች የጠበቁላቸው መብቶች ሳይከበሩላቸው ሕጉቹ ተጥሰው ይዞታው የተወሰደባቸው መሆኑንና ይዞታው ሲወሰድም በላዩ ላይ የሰፈረው ንብረት የወደመባቸው መሆኑን በመሆኑ ነባር ይዞታን የሚመለከቱ ሕጎችንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2035 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ጥያቄአቸውን መመርመርን የግድ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ የከተማ ይዞታን የማስተዳደር ስልጣን በሕጉ አግባብ የተሰጠው ቢሆንም ስልጣንን እና ኃላፊነቱን በሕጉ አግባብ አልተወጣም የሚል ክርክር ያለው ወገን ግን ጉዳዩን በፍርድ ቤት ወስዶ መብቱን ከማስከበር የሚከለክል ያለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37፣ 40(3)(4)፣79(1) እና 78(4) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች ክሳቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርቡ የቻሉትም የሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት የነባር ይዞታ ባለመብትነታቸው እንዲጠበቅላቸው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥተው እያለ ተጠሪ ውሳኔውን ባለማክበሩ ምክንያት መሆኑን ከክሳቸው መግለፃቸው ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 26ከ፣ 27 እና 28 ድንጋጌዎች በተመለከተው አካል በሚመለከተው አካል በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ አላቸው ለማለት የማያስችል በመሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ በተዘረጋው የይግባኝ ጉባኤ መብታቸውን ማስከበር አለባቸው ሊባሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይልቁንም እሚመለከተው አካል መስኖባቸው እያለ በተጠሪ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ሕጎቹ ተጥሰው የይዞታና የንብረት መብታቸው እንደተነካባቸው አመልካች በክሳቸው መጥቀሳቸውና ተጠሪም በሕጉ አግባብ ስልጣኑን በመጠቀም የወሰደው እርምጃ መሆኑን ጠቅሶ መከራከሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247 እና 248 ድንጋጌዎች አግባብ የተጠሪ እርምጃ ሕጉን ተከትሎ የተከናወነ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ማጣራትን የግድ የሚል በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 ወይም አዋጅ ቁጥር 455/97 ድንጋጌዎች አግባብ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በቀጥታ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ስለሆነም ከአመልካች ክስ

www.abyssinialaw.com

መሰረታዊ ይዘት ስንነሳ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንም ሆነ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ብይን በማጽናት የተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0104064 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 19155 በቀን 27/04/2009 ዓ.ም በፍርድ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 03-16739 በ27/06/2009 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0104064 ክርክሩን እንዲቀጥል በማድረግ ከስልጣን ውጪ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ሌሎች የክርክር ነጥቦችን በመመርመርና በማጣራት ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚኅ ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/144901

ሐምሌ 12 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ኢትዮቴሌኮም የሰሜን ምስራቅ ሪጅን

ተጠሪ፡- ወ/ሮ በለጡ ወልደ ተገኝ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ የተከለዉን ኮንቴነር እንዲያነሳ የቀረበዉን ክስ መነሻ በማድረግ የአማራ ክልል ጠ/ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪ ይዞታ ለተጠቀመበት ተገቢዉን ካሳ እንዲከፍል መወሰኑን ተከትሎ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል እንዲታረም የቀረበ አቤቱታ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ክርክሩ የተጀመረዉ በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ያቀረበችዉ ክስ ይዘት ባጭሩ ያለተጠሪ ፈቃድ ለጊዜዉ ነዉ በሚል አመልካች በተጠሪ ይዞታ ዉስጥ ገብቶ የቴሌ ሳጥን/ኮንቴነር/ በመትከሉ ይዞታየን ለመጠቀም አልቻልኩም በሚል ያጣሁትን ጥቅም ግምት ብር 20,700 ከፍሎ ሳጥኑን እንዲያነሳ እንዲወስን በማለት ዳኝነት የጠየቀች ሲሆን አመልካች በበኩሉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለዉም የሚልና ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

www.abyssinialaw.com

የሚላቸዉን መከራከሪያዎች አንስቶ በፍሬነገር ረገድም ሳጥኑ የተተከለዉ በከተማ አስተዳደር ተፈቅዶ ስለመሆኑ ገልጾ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ጉዳን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን ያከራከረዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ መቃወሚያ ዉድቅ ካደረገ በኋላ ስለጉዳዩ ከከተማዉ አስተዳደር መግለጫ ጠይቆ ከተማዉ አስተዳደር አመልካች የተጠሪ ይዞታ ዉስጥ ገብቶ 9.20 ካ.ሜ ተጠቅሞ የቴሌ ሳጥን መትከሉንና በዚህ ይዞታ ላይ እንዲተክል ከተማ አስተዳደሩ እንዳልፈቀደለት ስላላረጋገጠ አመልካች ለተጠቀመዉ ቦታ በአካባቢዉ የሊዝ ዋጋ ለተጠሪ እንዲከፍል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ለተጠሪ በአዋጅ 49/89 እና 455/97 መሰረት ካሳ የመክፈል ግደታ አለበት በሚል ካሳ መጠን ላይ የስር ፍርድ ቤት አጣሪቶ እንዲወስን መልሶለታል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የዳኝነት ስልጣን አስመልከቶ በስር ፍርድ ቤት የቀረበዉ መቃወሚያ መታለፉ ተገቢ አለመሆኑ፣ክሱ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ እና በፍሬነገር ረገድ አመልካች ክስ ያቀረበችበት ይዞታ ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ የተፈቀደ ሆኖ አመልካች ኋላ ላይ በቆርቆሮ አጥር ወደ ይዞታዋ ያስገባች ስለመሆኑ የተተከለዉ ሳጥን በከተማ አስተዳደር ተፈቅዶ በቋሚነት የሚቀመጥ እንጂ በጊዜያዊነት አለመሆኑንና ተጠሪ ኮንቴነሩ እንዲነሳ ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት እንደሌለዉ በመዘርዘር በመጨረሻም ተጠያቂዉ የከተማዉ አስተዳደር መሆን አለበት በሚል የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲታረም ጠይቋል፡፡የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አከራካሪዉ መስመር የተዘረጋዉ ከ5 ዓመት በፊት መሆኑንና ተጠሪ ይዞታዉን ከዚያ በኋላ አስፋፍተዉ የያዙት ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉ ክርክር በስር ፍርድ ቤት መታለፉን አግባብነት ለመመርመር ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲትሰጥ ተደርጓል፡፡ተጠሪ መጥሪያ ተልኮላት መልስ አላቀረበችም፡፡በዚሁ መልስ የማቅረብ መብት ታልፎ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ አመልካች ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ ኮንቴነር መትከሉ አልተካደም፡፡አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ በአዋጅ ቁ/49/89 መሰረት ጉዳዩ መታየት ያለበት በራሱ በአመልካቹ ድርጅት መሆን እንዳለበትና ድርጊቱም የህግ ድጋፍ

ያለዉ ስለመሆኑ ነዉ፡፡ በመሰረቱ ማንኛዉም የቴሌኮሙንኬሽን ድርጅት የቴሌኮሙንኬሽን መስመር ሲዘረጋ የከተማዉን ፕላን ተከትሎ የመዘርጋት ሃላፊነት እንዳለበት የቴሌኮሙንኬሽን አዋጅ ቁ/49/89 አንቀጽ 22/2/ በግልጽ ያስገነዝባል፡፡ከዚህ ባሻገር መስመሩ የባለይዞታን ወይም የሌላ ህንጻ ላይ የሚዘረጋበት አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር አስቀድሞ ለባለይዞታዉ ወይም ለባለህንጻዉ በማስታወቅ የባለይዞታዉ ወይም የባለህንጻዉ ተቃዉሞ እንዳለ ሰምቶ ተገቢዉን የመወሰን ስልጣን ለኤጀንሲዉ የተሰጠ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 18 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ዉስጥ ገብቶ ኮንቴነር መትከሉና ይዞታዉ የተጠሪ ህጋዊ ይዞታ ስለመሆኑ ደግሞ የከተማዉ አስተዳደር ያረጋገጠ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ ፡፡አመልካች ኮንቴነር የተከልኩት በከተማዉ አስተዳደር ፈቃድ ነዉ በማለት የተከራከረ ቢሆንም ከተማዉ አስተዳደር አመልካች ኮንቴነር የተከለበት ይዞታ የተጠሪ የግል ይዞታ እንጂ ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ የተፈቀደ ይዞታ አይደለም በማለት ምላሽ መስጠቱንም በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች ኮንቴነር ከተከለ በኋላ ተጠሪ ቦታዉን አስፋፍተዉ በመያዝ ወደ ይዞታዋ አስገብታለች የሚለዉ ነጥብ የፍሬነገር ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳና በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬነገር በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበዉ ክርክር ተገቢነት ያለዉ ሆኖ አላገኘንም ፡፡ አመልካች በአዋጁ መሰረት ጉዳዩ በኤጀንሲዉ በኩል እንዲታይ ለማድረግም አስቀድሞ ለተጠሪ የሰጠዉ ማስታወቂያ ስለመኖሩ ካለማስረዳቱም በተጨማሪ ጊዜያዊ ነዉ እያለ ተጠሪ እንዲጠባበቁ ያደረገ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ክርክር የተቀረበበት ነዉ፡፡

በመሆኑም አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ የተከለዉ ኮንቴነር በቋሚነት የሚቀጥል እስከሆነ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 20/1/ መሰረት ተገቢዉን ካሳ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ስለዚህም የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠዉን ፍሬነገር መሰረት በማድረግ አመልካች ለተጠቀመበት የተጠሪ ይዞታ ተገቢዉን ካሳ እንዲከፍል ዉሳኔ መስጠቱና የካሳዉ መጠን ተጣርቶ እንዲወሰን ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ በአዋጅ ቁ/49/89 አንቀጽ 20/1/ እና አዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 6 መሰረት ተገቢ ሆኖ ስላገኘን

www.abyssinialaw.com

ዉሳኔዉ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚህ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉ ሳ ኔ፡፡

1ኛ/የአማራ ብ/ክ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/01-0471 በ03/09/09 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በጥር 9 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ እግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

# የፍትሐብሐር ሥነ-ሥርዓት

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ.137704

የካቲት 14 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1.ዳኜመላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ መሀመድ ከማል - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ በቀለ ወልዴ - ከጠበቃ አቶ ምስጋኑ ሙለታ ጋር ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ የሰበር ጉዳይ በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ እንዲነሳልኝ የሚል አቤቱታ መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.06184 በ8/3/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁን አመልካች ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ፣በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ 2ኛ ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ታህሳስ 9 ቀን 2007 ዓ.ም የተደረገዉ የድርጅት ሽያጭ ዉል እንዲፈጸምልኝ በማለት በጠየቀዉ ዳኝነት፣ 1ኛ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጎ፣ 2ኛ ተከሳሽ እንደዉሉ ቢፈጸም አልቃወምም በማለታቸዉ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በመ.ቁ.18073 በ4/7/2007 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በ8000 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈዉ የዱቄት ፋብሪካ ከነመገልገያ ማሽኖቹ ጭምር ታህሳስ 9 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ዉል መሰረት ለከሳሽ እንዲፈጸም በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ዉሳኔ ተከትሎ 1ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ባቀረበዉ አቤቱታ የፍ/ቤቱ መጥሪያ እንዲደርሰኝ ተገቢ ጥረት አልተደረገም፣ መጥሪያ አልደረሰኝም፣ ክርክሩን

ስላልሰማሁት ተከሳሽ በሌለሁበት በጋራ ንብረት ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት እንዲነሳልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ በዚህ አቤቱታ ላይ ከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ተከሳሽ በቀበሌ በኩል መጥሪያ ተልኮለት በቀበሌዉ እንደሌለ አረጋግጦ ጽፏል፤ በአዲስ ዘመን ጋዜጣም ጥሪ ተደርጎለታል፣ የፍ/ቤቱ መጥሪያ ለ1ኛ ተከሳሽ ሚስት ለሆነችዉ ለ2ኛ ተከሳሽ ደርሷት ቀርበ ስለተከራከረች መጥሪያ ለእርሱም እንደደረሰ ይቆጠራል፤ ተከሳሽ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ ላይ ላቀረበዉ ክስ ከመልስ ጋር የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በማያያዝ ግንቦታ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ስለተሰጠ ተከሳሽ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ዉሳኔዉን ያወቀ ስለሆነ አቤቱታ ያቀረበዉ በ23/10/2007 ዓ.ም ስለሆነ ዉሳኔዉን ካወቀ ከ3 ወር በኋላ ስለሆነ አቤቱታዉ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ብይን 1ኛ ተከሳሽ መጥሪያ በቀበሌ በኩል ቢላክለትም በቀበሌዉ እንደማይኖር ቀበሌዉ ደብዳቤ ጽፏል፤ በጋዜጣም ጥሪ ተደርጎለት አልቀረበም፤ በዚህ ጉዳይ የተከሳሽ ባለቤት የሆነችዉ ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ ቀርባ ስለተከራከረች ተከሳሽም ክርክሩን እንደሰማ የሕግ ግምት ያስወስዳል፤ ተከሳሽ ክርክሩን የሰማሁበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከመልስ ጋር በቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ ነዉ የሚባል ከሆነ ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም አዉቋል ስለሚያስብል 1ኛ ተከሳሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት አቤቱታዉን ያቀረበዉ ሰኔ 23 ቀን 2007 ዓ.ም ስለሆነ ይህ ደግሞ ከሁለት ወር በላይ ስለሆነ አቤቱታዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 /1/ መሰረት በአንድ ወር ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበላቸዉን ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች የካቲት 7 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ፡ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.162148 ላይ በነበረን ክርክር በሌለሁበት ዉሳኔ መሰጠቱን ያወቅኩት ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ሳይሆን ግንቦት 22 ቀን 2007 ዓ.ም ትዕዛዙ በደረሰኝ ጊዜ ነዉ፡፡ እኔ በሌለሁበት ዉሳኔ መሰጠቱን እንዳወቅኩኝ ሰኔ 13 ቀን 2007 ዓ.ም በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳልኝ ለሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረብኩኝ ቢሆንም የፍ/ቤቱ ሰራተኞች እስከ ሰኔ 22 ቀን 2007 ዓ.ም

www.abyssinialaw.com

በስብሰባ ላይ የነበሩ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ሊዘገይ መቻሉን እየተከራከርኩኝ የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ሳይቀበሉ መወሰናቸዉ ተገቢ አይደለም፡፡ አመልካች በባለቤቱ በኩል ክርክር እንዳለ ያዉቃል ለተባለዉ ከባለቤቴ ጋር ተጣልቼ የነበረ እና ባለቤቴ ይህን ድርጅት አሳግዳዉ የነበረ ሲሆን ከተጠሪ ጋር በመመሳጠር እግድ እንዲነሳ በማድረግ ስም ዝዉዉር እንዲደረግ አድርጓል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ክርክር እንዳለ ያዉቃል በማለት የጠቀሱት በማስረጃ ባልተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ፣የሥር ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተነስቶ ተገቢ መከራከሪያ አቅርቤ ዉሳኔ እንዲሰጥ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች ከሚስቱ ጋር በጋብቻ ፍቺ ክርክር ጋር ባለበት ሚስቱ መጥሪያዉ ደርሷታል ጉዳዩን ታዉቃለች በመሆኑም አመልካችም ጉዳዩን ያዉቃል ተብሎ ግምት ተወስዶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት የቀረበዉን የአመልካች ጥያቄ ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ16/5/2010 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አመልካች ያቀረበዉ በማስረጃ ያልተረጋገጠ እና አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር ተቀባይነት የሌለዉ ስለሆነ ዉድቅ ሆኖ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች መጥሪያ ሳይደርሰኝ በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገዉ በቀበሌዉ እንደሌለ ተረጋግጧል፣ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት አልቀረበም፣ በሚስቱ ቀርባ ስለተከራከረች ክርክሩን እንደሰማ በሕግ ግምት ይወሰዳል፣ ዉሳኔዉን ካወቀዉ ከአንድ ወር በላይ ስለሆነ አቤቱታዉ ተቀባይነት የለዉም በሚሉት ምክንያቶች መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

እንደሚታወቀዉ ስለመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት በተመለከተ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 94--110 ድንጋጌዎች ሥር ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች

አቀራረጽና ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ የመጥሪያ አደራረስ ሂደት በቅድም ተከተል አራት ደረጃዎች እንዳሉት የሚያሳይ መሆኑን ነዉ፡፡ እነዚህም አንደኛ መጥሪያዉን ለተከሳሹ ለራሱ ማድረስ /የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.95 /3/፣ሁለተኛ መጥሪያዉን ለተከሳሹ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ ለሚገመት ሰዉ ማድረስ /አንቀጽ 99-101/፣ ሶስተኛ በፖስታ በኩል ለተከሳሽ እንዲደርሰዉ በማድረግ /አንቀጽ 106/፣አራተኛ በምትክ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴን በመጠቀም ለተከሳሹ እንዲደርሰዉ ማድረግ እንደሚቻል /አንቀጽ 105/ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የመጥሪያ አደራረስ ዘዴዉ ወይም ሥርዓት በዚህ ቅደም ተከተል ካልተፈጸመ ለተከሳሹ መጥሪያዉ በሕጉ አግባብ ደርሶታል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለአመልካች መጥሪያ እንዲደርሰዉ የወሰደዉን እርምጃ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ቀድም ሲል ሲኖርበት የነበረዉን ቀበሌ ዉስጥ እንደማይኖር የተረጋገጠ በመሆኑ እና ከተጠሪ ጋር በፌዴራል ፍ/ቤት ክርክር ላይ እንደነበሩ የሚታወቅ ስለሆነ፣ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለአመልካች በአድራሻዉ እንዲደርሰዉ ተገቢዉን ጥረት እንዲያደርግ ማድረግ ነበረበት፡፡ ፍ/ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴ በአግባቡ ሳይፈጸም አራተኛ ደረጃ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴ ማለትም ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ማድረጉን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ የሥር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.95 /3/ በሚደነግገዉ መሰረት የአሁን አመልካች ክርክሩን አዉቀዉ ቀርበዉ መከራከሪያዉን እንዲያቀርብ ተጠሪ መጥሪያዉን ለአመልካች ለራሱ እንዲያደርስ ተገቢዉን ጥረት እንዲያደርግ ማድረግ ሲገባዉ ይህ ሳይደረግ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ማድረጉ ከላይ የተመለከቱትን የሥነሥርዓት ሕጎችን የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የፍ/ቤቱ መጥሪያ ለአመልካች እንዲደርሰዉ ተገቢዉ ጥረት ሳይደረግ በጋዜጣ ጥሪ መደረጉ በሕግ የተመለከተዉን የመጥሪያ አደራረስ ዘዴን ያልተከተለ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የፍ/ቤቱ መጥሪያ በሕጉ አግባብ ለአመልካች ደርሶታል ክርክሩን አዉቆታል የሚያስብል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች ሚስት የነበረችዉ የሥር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ በዋናዉ ጉዳይ ቀርባ እስከተከራከረች ድረስ አመልካች

www.abyssinialaw.com

ክርክሩን እንዳወቀ የሕግ ግምት ያስወስዳል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ አደርጓታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ በዚህ ጉዳይ አመልካች እና ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ ሁለቱም ተከሳሾች የነበሩ ስለሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.95/2/ መሰረት ለእያንዳንዳቸዉ መጥሪያ እንዲደርሳቸዉ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በዚህ አግባብ ትዕዛዝ በመስጠት የሥር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ ለአመልካች የተላከዉን መጥሪያ ፈርማ መቀበሏን የሥር ዉሳኔ የሚያመለክተዉ ነገር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ለአሁን አመልካች የተላከዉን መጥሪያ ለወ/ሮ ዘምዘም ስለመሰጠቱ ሳያረጋግጥ ወ/ሮ ዘምዘም ራሳቸዉ ተከሳሽ ስለነበሩ መጥሪያ ደርሷቸዉ ቀርበዉ ስለተከራከሩ አመልካችም ክርክሩን እንደሚያዉቅ የሕግ ግምት እንደሚያስወስድ በመግለጽ መወሰኑ የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.101 ሥር እንደተመለከተዉ የፍ/ቤት መጥሪያ የተላከለትን ተከሳሽ ማግኘት ያልተቻለ ወይም መጥሪያ ተቀባይ የሚሆን ወኪል የሌለዉ እንደሆነ ከተከሳሹ ጋር አብሮት ከሚኖረዉ አካላ መጠን ከደረሰ ቤተሰቡ ላንዱ መስጠት እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ በዚህ ረገድ የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የሥር ፍ/ቤት የሥር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ ለአመልካች የተላከዉን መጥሪያ ፈርሞ ስለመቀበላቸዉ ያረጋገጠዉ ነገር ካለመኖሩም በላይ በወቅቱ የአሁን አመልካች ከሚስቱ ጋር በፍ/ቤት የፍቺ ክርክር እንደነበራቸዉ እና በግንኙነታቸዉ መካከል ችግር እንዳጋጠመዉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በአመልካች እና በሚስቱ መካከል በነበረዉ የፍቺ ክርክር ላይ ዉሳኔ ባይሰጥም፣ የፍቺ ክርክር በመኖሩ በመካከላቸዉ ሰላማዊ ግንኙነት ይኖራቸዋል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለአመልካች በአግባቡ ያደርሳሉ ተብሎ የሕግ ግምት ለመዉሰድ የሚያስደፍር አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህን ሁኔታ በመገንዘብ ተጠሪ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለአመልካች ለማድረስ ተገቢዉን ጥረት እንዲያደርግ ማድረግ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ለሚስቱ መጥሪያ ደርሷት ቀርበ ስለተከራከረች ለአመልካችም መጥሪያ እንደደረሰ ግምት በመዉሰድ አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡

በመጨረሻም የሥር ፍ/ቤት የአመልካች በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገበት ምክንያት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በነበረዉ ክርክር ተጠሪ ከተሰጠዉ መልስ ጋር በቀረበ የሰነድ ማስረጃ ነዉ ያወቅኩኝ

www.abyssinialaw.com

የሚል ከሆነ በዛ ክርክር መልስ የተሰጠዉ ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ስለሆነ አመልካች አቤቱታዉን የቀረበዉ ሰኔ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ የአንድ ወር ጊዜ አልፎበታል በማለት ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም እንዳላወቀ እና ግንቦት 22 ቀን 2007 ዓ.ም በችሎት ጸሐፊ በኩል ትዕዛዝ ሲደርሰዉ እንዳወቀ በዚህ መነሻነትም ለሥር ፍ/ቤት በጊዜ አቤቱታዉን እንዳቀረበ በመግለጽ እየተከራከረ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ በቀረበዉ ክርክር አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ችሎት ቀርበዉ የመከላከያ መልስና የሰነድ ማስረጃ ተቀብሎ ዉሳኔ መሰጠቱን አዉቋል የሚል ሳይሆን አመልካች የዉሳኔ ግልባጭ መጠበቅ ሳያስፈልገዉ ማወቅ ይችል ነበር የሚል ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ያወቀ መሆኑን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ በማስቀረብ ወይም በሌላ አግባብ በማጣራት ያረጋገጠ ነገር መኖሩን የሥር ዉሳኔ አያመለክትም፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ እና ከግራ ቀኛቸዉ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በችሎት ቀርበዉ ተጠሪ ያቀረበዉን የመከላከያ መልስና የሰነድ ማስረጃ በመቀበል፣ እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም አዉቆታል ለማለት የሚያስችል ነገር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በእርግጠኝነት የአሁን አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ማወቁን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባላረጋገጠበት፣ እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን በግምት በዚህ ቀን መሰጠቱን አዉቆታል፣ አመልካች በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አቤቱታዉን ስላላቀረበ ዉድቅ ነዉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 ዓላማ የሚቃረን ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በሕግ አግባብ መጥሪያ የደረሰዉ መሆኑን እና እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን በእርግጠኝነት ያወቀበት ቀን እስካልተረጋገጠ ድረስ የመከላከያ መልስና ክርክር በማቅረብ የመሰማትና ፍትሕ የማግኘት መብት ሕገ መንግስታዊ መብት ስለሆነ አሳማኝና በቂ ባልሆነ ምክንያት ሊነፈግ አይገባም፡፡ በዚህ ረገድ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ፍትሕ የማግኘት መብት ሕገ መንግስታዊ መብት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች በሕግ አግባብ መጥሪያ የደረሰዉ እና እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ማወቁን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባላረጋገጡበት

www.abyssinialaw.com

አመልካች በሌለሁበት የተሰጠዉ ፍርድ ተነስቶ የመከላከያ መልስ እንዳቀርብ በማለት የቀረበዉን አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አልቀረበም በሚል ምክንያት ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.18073 በ10/3/2008ዓ ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.15040 በ17/5/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚችሎት በመ.ቁ.06184 በ8/3/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች በሕግ አግባብ መጥሪያ የደረሰዉ እና እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ያዉቅ እንደነበር ባልተረጋገጠበት፣ በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳልኝ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አልቀረበም በማለት ዉድቅ ማድረጉ በሕግ አግባብ ሆኖ ስላልተገኘ፣የመከላከያ መልስ የመቅረብ የመከራከርና ፍትሕ የማግኘት መብቱ ሊነፈግ ስለማይገባ የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.18073 በ4/7/2007 ዓ.ም አመልካች በሌለበት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 (2) መሰረት ሊነሳ ይገባል ብለናል፡፡
3. የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአሁን ተጠሪ የቀረበዉ ክስና ማስረጃ ለአመልካች እንዲደርሰዉ በማድረግ አመልካች የመከላከያ መልስ እንዲያቀርብ በማድረግ፣ በሕጉ አግባብ ተከራካሪ ወገኖቹን በማከራከርና በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 /1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
5. ግራና ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ፡-139187

ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ**

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

**አመልካች፡-** አቶ መስፍን ዘርዓብሩክ ጠበቃ ዘበነ ፍቅሬ ቀረቡ

ተጠሪ፡-1. ወ/ሮ የወርቅዉሃ አለማየሁ

2. ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ጥላሁን

3. አቶ አሰግድ ጥላሁን

4. ወ/ሮ አደይ አፈወርቅ

5. ወ/ት ሜሮን አፈወርቅ

(ተጠሪዎች 1-5) ጠበቃ ያሬድ ዘርይሁን ቀረቡ

6. አቶ ዳንኤል ተቀባ አልቀረቡም

7. ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ለማ አልቀረቡም

8. አቶ ሩዶለፍ ጆርዳኖ አልቀረቡም

9. ወ/ሮ መዓዛ ዘዉዴ አልቀረቡም

10. የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስትያን ጠበቃ በሬሳ በየነ ቀረቡ

www.abyssinialaw.com

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነበር፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሳሽ፤ከ1ኛ እስከ 9ኛ ተጠሪዎች ተከሳሾች እንዲሁም 10ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ዉል ፈርሶ ቤት ለመረከብ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በአሁኑ አጠራር ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር CKS02/114/2321/227/606/7561/01 ተመዝግቦ የሚገኝ በ986 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የተገነባ ቁጥሩ 169 የሆነ ቤት ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል አቶ ጥላሁን ልዑልሰገድ ከተባሉት አሁን በህይወት ከሌሉት ከ1ኛ ተጠሪ ባለቤት ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ በብር 400,000 (አራት መቶ ሺህ ብር) መግዛታቸውን፤ከገዙም በኋላ ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት ማሻሻያ ማድረጋቸውን፤ስመሃብቱ ወደ ገዥው ሳይዞር አመልካች በኢትዮ-ኤርትራ ግጭት ምክንያት ከአገር ውስጥ መውጣታቸውን፤ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 114/91 ክስ አቅርበው የካቲት 27 ቀን 1992 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ ከአመልካች ጋር አድርገውት የነበረው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ በማስወሰንና ካርታ እንደጠፋባቸው በማስመሰል አዲስ ካርታ አውጥተው ሰኔ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ለ6ኛው ተጠሪ በሽያጭ በብር 450,000 (አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ማስተላለፋቸውን፤ከዚህ በኋላ 6ኛው ተጠሪ ባለቤታቸው ከሆኑት 7ኛ ተጠሪ ጋር ሆነው ነሐሴ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ለ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች በብር 5,100,000 (አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ብር) በሽያጭ ያስተላለፉት መሆኑን ጠቅሰው ከዚህ ሁሉ በኋላ አመልካች ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በመዝገብ ቁጥር 195189 ከሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር በመከራከር ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገው ውል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም የተወሰነ በመሆኑ ሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ሰኔ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ከ6ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲሁም 6ኛው ተጠሪ ከባለቤታቸው 7ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን

www.abyssinialaw.com

ለ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ነሐሴ 26 ቀን 2000 ዓ.ም ያረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ 8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ፣አመልካች ከቤቱ ያገኙ የነበረውን ጥቅም ወደፊት አስልተው የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠበቅላቸውና የክርክሩ ወጭና ኪሳራ እንዲታሰብላቸው ዳኝነት በመጠየቅ ያቀረቡት ክስ ነው።

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ጥር 01 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ቤት ልረከብ በማለት ክስ ያቀረቡ ቢሆንም በአከራካሪው ቤት መብት ያላቸው ለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረቡም፣ህገ ወጥና ለህሊና ተቃራኒ የሆነ ውል ለማስፈረስ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው፣አመልካች አከራካሪውን ቤት ከአገር ውስጥ ሲወጡ በአደራ የሰጡት ሰው ካለ መክሰስ እየተገባቸው ተጠሪዎችን መክሰሳቸው ተገቢ አይደለም በማለት በመቃወሚነት ጠቅሰው በፍሬ ጉዳዩም ላይ ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገው ውል በአዋዋይ ፊት የተደረገ አለመሆኑን፣ አመልካች አቤቱታ አቅርበው ውሉ ሊፈርስ አይገባም ቢባልም ይግባኝ ማቅረባቸውን ገልፀው አመልካች ካሳ ከሚጠይቁ በስተቀር ውሉን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው መልስ አቅርበዋል።

በሌላ በኩል 6ኛ ተጠሪ ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፣7ኛ ተጠሪ ነሐሴ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ መልስ እንዲሁም 8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ጥር 01 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን የሁሉም መልስ በይዘት ደረጃ ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ አከራካሪውን ቤት ህጉን ተከትለው እና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው የገዙ መሆናቸውን ገልፀው ቤቱም ወደ ሌላ ወገን ተላልፎ እንደሚገኝ በመጥቀስ ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ያቀረቡት ነበር። የአሁን 10ኛ ተጠሪ ከ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ቤቱ የተላለፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን አቅርበው ተከራክረዋል።

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ጥቅምት 16 ቀን 2008 ዓ.ም በብይን ውድቅ በማድረግ አልፎ በዋናው ጉዳይ የግራቀኙን ተከራካሪዎች ክርክርና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር በመዝገብ ቁጥር 138454 ሰኔ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች ከሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር ያደረጉት የቤት ግዥ ዉል ሶስተኛዉ

www.abyssinialaw.com

ወገን በሆኑት ከ6ኛ እስከ 9ኛ ባሉት ተጠሪዎች ላይ መቃወሚያ ሊሆን የሚችለዉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2878 መሠረት በመዝገብ ተመዝግቦ ሲገኝ ብቻ ስለመሆኑና በዚሁ ረገድ ሦስተኛ ወገን ገዥዎች ተገቢዉን ማጣራትና ጥንቃቄ አድርገዉ ቤቱን ከባለሀብት የገዙ ስለሆነ በቅን ልቦና የተደረገ ዉል ከመሆኑ አኳያ 6ኛ ተጠሪ ከሟች ጋር ያደረጉት ውልም ሆነ 8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ከ6ኛና 7ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ዉል ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ሲከራካሩ የቆዩ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ ለማስለወጥ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት አልተገኘም ሲል የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የፈፀሙትን መሠረታዊ ህግ ስህተት ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሠረታዊ የህግ ስህተት በመዘርዘር አቤቱታቸው አቅርበዋል፡፡

በሰበር አጣሪው ችሎት ትዕዛዝ መሠረት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብነት ለማጣራት ተጠሪዎች ቀርበው መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ አግባብ ተጠናቋል፡፡ እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች በመሠረታዊነት የሚከራካሩት ከ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እንዲሁም ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች አውራሽ ከሆኑት አቶ ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር ባደረግነው የቤት ሽያጭ ውል የገዛሁትን ቤት ሟች አቶ ጥላሁን ልዑልሰገድ ከ6ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲሁም 6ኛ ተጠሪ ከባለቤታቸው 7ኛ ተጠሪ ጋር ሆነው ከ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ቤቱን እንዲያስክቡኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ከመዝገብ ምርመራው መገንዘብ እንደተቻለው አከራካሪውን ቤት አመልካች ለመግዛት ሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ለመሸጥ ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም ስምምነት አድርገው ነበር፡፡ ከዚህ ስምምነት በኋላ ሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ በመዝገብ ቁጥር 114/91

www.abyssinialaw.com

በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ክስ አቅርበው የካቲት 27 ቀን 1992 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውሉ ስምምነት እንዲፈርስ አስወስነዋል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኋላ አዲስ ካርታ አውጥተው ሰኔ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ለ6ኛው ተጠሪ በሽያጭ በብር 450,000 ማስተላለፋቸውም ተረጋግጧል፡፡ 6ኛው ተጠሪ ባለቤታቸው ከሆኑት 7ኛ ተጠሪ ጋር ሆነው ነሐሴ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ለ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች በብር 5,100,000 በሽያጭ ማስተላለፋቸውም ግልፅ ነው፡፡ አመልካች ይህ ሁሉ ከተከናወነ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በመዝገብ ቁጥር 195189 ከሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር በመከራከር ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም አስወስነዋል፡፡ በመሆኑም ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ አመልካች ከሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ሊፈርስ እንደማይገባ ነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ የሽያጭ ውሉ ፈርሷል የሚል ተፈፃሚነት ያለው ውሳኔ በነበረበት ጊዜ ማለትም በ1997 ዓ.ም እና በ2000 ዓ.ም በቤቱ ላይ የተደረጉ የሽያጭ ውሎች ላይ የሚያስከትለው የህግ ውጤት ምንድን ነው? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በመሠረቱ 6ኛ ተጠሪ ከሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር የአከራካሪውን ቤት ሽያጭ ውል በፈፀሙ ጊዜ ሚቹ ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል ከመፍረሱም በላይ አከራካሪው ቤት አዲስ ካርታ በሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ስም ወጥቶለት በሻጭ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ አመልካችም ቢሆኑ አልካዱም፡፡ አመልካች ከሚች ጋር አድርጌ ነበር የሚሉት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል 6ኛው ተጠሪ ቤቱን ከሚች በገዙ ጊዜ ተመዝግቦ እንዳልነበረም አከራካሪ አይደለም፡፡ በመሆኑም 6ኛው ተጠሪ ቤቱን ሲገዙ ተገቢውን ጥንቃቄ አላደረጉም፤የቅን ልቦና ጉድለት ነበረባቸው ሊባሉ አይችሉም፡፡ በቅን ልቡና ለሆነ ሶስተኛ ወገን የተሰራ ሥራ ውጤት ጠቃሚ ከሆነ እንደረጋ እንደሚቀር በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1816 ሥር ተደንግጎ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 25165 እንዲሁም በሌሎች መዝገቦች ላይ በማይንቀሳቀስ ንብረት ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ግዥ የሚፈፅሙ የቅን ልቦና ገዥዎችን መብት ለመጠበቅ የሚያስችል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ 6ኛው ተጠሪ ቤቱን የገዙት በቅን ልቦና ላይ ተመስርተውና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ከመሆኑም በላይ አመልካች የአከራካሪውን ቤት ሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ

መቃወሚያ በሚሆን አግባብ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2878 መሠረት አስመዝግበው እንዳልተገኙ በሥር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ሟች ለ6ኛ ተጠሪ ያደረጉትም ሆነ ከዚያ በኋላ የተደረገው የሽያጭ ውል ሊፈርስ እንደማይገባ በሥር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ የሚነቀፍበት መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤቶች በአከራካሪው ቤት ላይ ሟች ከ6ኛ ተጠሪ ጋር እንዲሁም 6ኛ ተጠሪ 8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጓቸው ውሎች እንደጸኑ ይቀራሉ ብለው ሲወስኑ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ባልና ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች አውራሽ የከፈሉት ገንዘብና ተያያዥነት ያላቸውን ወጭዎች በተመለከተ በዚሁ መዝገብ ግልፅ ውሳኔ ሳይሰጡ ማለፋቸውን ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ክስ ሲያቀርቡ ሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ከ6ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል እንዲሁም 6ኛ ተጠሪ ከ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ፈርሶ አከራካሪውን ቤት ለመረከብ ቢሆንም ከሟች ጋር በአደረጉት ውል መነሻነት ያወጡት ወጭ እንዳለ በክሳቸው አመልክተዋል፡፡ ክስ ሲያቀርቡም አስፈላጊውን የክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት አሟልተውና የዳኝነት ከፍለው እንዳቀረቡ የሚታመን ነው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ውሉ አይፈርስም ካለ በኋላ አመልካች ለሟች የከፈሉት ገንዘብና እንደጸና እንዲቀር የተወሰነውን ውል መሠረት አድርገው ያወጡት ወጭ ካለ በማጣራት በዚሁ መዝገብ ላይ መወሰን ሲገባው በሌላ መዝገብ በአዲስ ክስ ቀርቦና ተከራክረውበት እንዲወሰን ለተራዘመ የክርክር ሂደት በመጋበዝ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 138454 ሰኔ 01 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 130303 ጥር 26 ቀን 2009 ዓ.ም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ከሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም በአደረጉት ውል መነሻነት ያወጡት ወጭ በተመለከተ በሌላ መዝገብ ክስ አቅርበው እንዲጠይቁ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሮ አመልካች ያወጡት ወጭ

www.abyssinialaw.com

ምን ያህል ነው? የሚለውን ነጥብ አመልካችንና ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎችን በዚሁ መዝገብ በማከራከር ካጣራ በኋላ ተገቢውን እንዲወስን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይመለስለት ብለናል፡፡ ሌላው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3. ሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 142242

ቀን 16/09/2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- ኦይል ሊቢያ ኢትዮጵያ ሊሚትድ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ ገ/ሕይወት የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች የንግድ ድርጅት ለመረከብ ባቀረበው ክስ ላይ የተቋረጠ ጥቅም አጣምሮ መጠየቅ ይችል ነበር ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 እና 33(2) ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡
2. አመልካች ቀደም ሲል በተጠሪ ላይ በመ/ቁ. 76340 ባቀረበው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18 ክልል የሚገኘውንና በቤት ቁጥር 387 የተመዘገበውን የነዳጅ፣ የዘይት ማደያና የመኪና እጥበት ማከናወኛ የንግድ ድርጅት እንዲያስረክቡት ዳኝነት ጠይቆ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገው ክርክር አመልካች ንብረቱን እንዲረከብ ውሳኔ መስጠቱን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

www.abyssinialaw.com

3. አመልካች ንብረቱ እንዲረከብ ከተወሰነ በኋላ ከታህሳስ 4 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ድርጅቱን በፍርድ እስከተረከበበት ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ከነዳጅ ጣብያው አገልግሎት፣ ከነዳጅ፣ ዘይት ሽያጭ ማግኘት የነበረበት ገቢ በድምሩ ብር 971,394.04 ጥቅም የተቋረጠ በመሆኑ ተጠሪ እንዲከፍሉ በኮ/መ/ቁ. 111441 ክስ አቅርቧል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ አመልካች መጀመሪያ ባቀረበው ክስ የተቋረጠ ጥቅምና ኪሳራ መጠየቅ እየቻለ ክሱን ነጣጥሎ ያቀረበ እንደሆነ፤ መጀመሪያ ባቀረበው ክስም የኪሳራ ጥያቄ ወደፊት ለመጠየቅ እንዲፈቀደለት ያቀረበው ጥያቄ በዝምታ የታለፈ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/4/ እና 5(3) መሰረት ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡
4. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለትን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ፍሬ ጉዳዩ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ብር 912,487.43 ከሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታቸውን አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች የተቋረጠ ጥቅም ለወደፊት እንዲጠይቅ መብቱ እንዲጠበቅለት ያቀረበው ጥያቄ በዝምታ የታለፈ በመሆኑ በድጋሚ ክስ ሊያቀርብ የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም በማለት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮአል፡፡
5. አመልካች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ግንቦት 14 ቀን 2009 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ንብረቱ ለማስመለስ ባቀረበው ክስ ላይ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፈለው ግልጽ ዳኝነት ባልጠየቀበት እና የክስ ምክንያት ባልበሰለበትና ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ክስ መቅረብ ነበረበት የሚባልበት የህግ ምክንያት የሌለ መሆኑን እየታወቀ የስር ፍ/ቤት የዳኝነት ጥያቄው በዝምታ ታልፏል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በሕጉ አግባብ አይደለም ተብሎ እንዲሻርለት አመልክቷል፡፡ የአመልካች አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎትም አመልካች ያቀረበው ክስ መብት ሊያቋቁም የሚችል ፍሬ ነገር ባልነበረበት አጠቃለህ ልትከስ ይገባ ነበር ተነጣጥሎ የቀረበ ክስ ነው ተብሎ በድጋሚ ሊቀርብ አይገባውም የመባሉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 እና 33(2) አንጻር ለመመርመር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም ታህሳስ 20 ቀን 2010 ዓ.ም ባቀረበው መልስ

አመልካች የኪሳራውን ጥያቄ ወደፊት ነጥሎ ለማቅረብ በውሳኔ እንዲታወቅለት የመጀመሪያው ክስ ላስተናገደው ፍ/ቤት ያቀረበው ጥያቄ ሳይፈቀደለት የታለፈ በመሆኑ የካሳው ጥያቄ ነጥሎ ማቅረብ አይችልም በማለት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ተብሎ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

6. የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡
7. እንደመረመርነውም አመልካች መጀመሪያ ባቀረበው ክስ የነዳጅ ጣቢያው እንዲረከብ እንዲሁም የገቢና ትርፍ ማጣት ኪሳራ ወደፊት እንደሚጠይቅ በውሳኔ እንዲታወቅለት ማመልከቱን ከቀረበው ክርክር ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው የአመልካች የካሳ ጥያቄ በዝምታ ታልፏል የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ በአንድ ክስ የሚጠቃለሉ ጉዳዮች አጠቃሎ ክስ ማቅረብ የሚገባ ስለመሆኑ፤ በዚህ አግባብ ያልቀረበው ክስ እንደገና የክስ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ያስገነዝበናል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ እንደምንገነዘበው አጠቃሎ ክስ ማቅረብ የሚቻለው በተቋቋመ መብት ላይ ተመስርቶ እንጂ ዳኝነት በተጠቀበት ጊዜ ያልበሰለ ወይም ያልተረጋገጠ መብት ጭምር ማቅረብ እንደማይቻል ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች መጀመሪያ ያቀረበው ክስ መሰረታዊ የዳኝነት ጥያቄው የነዳጅ ማደያው መረከብ ስለመሆኑ አጠቃላይ ካደረጉት ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ የነዳጅ ጣቢያው የባለቤትነት ጥያቄ ባልተመለሰበት ሁኔታ የጥቅም ማጣት ወይም ኪሳራ መጠየቅ ግምታዊ የዳኝነት ጥያቄ ከሚሆን ውጭ የተረጋገጠ መብት/ጥቅም ቀንሶ ማስቀረትን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ነዳጅ ማድያው ለመረከብ ባቀረበው ክስ ለወደፊት የሚጠይቀው መብት መኖሩን ማመለከቱ መጀመሪያ ባቀረበው ክስ ላይ የተቋረጠ ጥቅም እንዲወሰንለት ግልጽ ዳኝነት ጠይቋል ለማለት አይቻልም፡፡ አመልካች ያልበሰለ ወይም ያልተረጋገጠ መብት በመጀመሪያ ክሱ ላይ አጠቃሎ አላቀረበም ተብሎ በስር ፍ/ቤት መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

8. አመልካች መጀመሪያ ባቀረበው ክስ የነዳጅ ጣቢያው የባለቤትነት መብት አከራካሪ የነበረ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የባለቤትነት መብት በሚያከራክርበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች ባልተረጋገጠ መብት ላይ ተመስርቶ የገቢና ትርፍ ማጣት ኪሳራ የሚጠይቅበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ አመልካች መብቱን ወደፊት የሚጠይቅ ስለመሆኑ በክሱ ላይ ማመልከቱ ዳኝነት ጠይቋል የሚያስብል አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበው ክስ ተነጣጥሎ የቀረበ ነው፤ የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘቱ አልተረጋገጠም በማለት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ መሻሩ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ እና 216 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ አመልካች የገቢና ትርፍ ማጣት ኪሳራ ለመጠየቅ ያቀረበው ክስ እንደገና (በድጋሚ) የቀረበ አይደለም ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ. 132137 በ 24/06/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 111441 በ 07/11/2008 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በመሻር የተሰጠ ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው የገቢና ትርፍ ኪሳራ ይከፈለኝ የዳኝነት ጥያቄ እንደገና (በድጋሚ) የቀረበ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 132137 በመክፈት ግራቀኙ በፍሬ ጉዳዩ ያቀረቡትን ክርክር መሰረት በማድረግ ተገቢ ህጋዊ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት መልሰንለታል፡፡ የውሳኔ ግልባጭ ይድረስ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.146503

ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ንጋቷ በየነ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሀረገወይን በየነ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይገባኛል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበሩት አቶ ብርሃኑ በየነ ሲሆኑ አመልካችና ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

አቶ ብርሃኑ በየነ መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ/ም በአመልካችና በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም መስከረም 04 ቀን 1997 ዓ/ም የተውት ኑዛዜው በፍርድ ቤት ቀርቦ መጋቢት 19 ቀን 1997 ዓ/ም መፅደቁን ጠቅሰው ኑዛዜ ያረፈበትን በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 199 የሆነ ቤት በኑዛዜው መሰረት እንዲከፋፈሉ ይወሰነው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችና ተጠሪ በሰጡት መልስም በኑዛዜው መሰረት ክፍፍሉ ቢደረግ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ክፍፍሉን የማይቃወሙ መሆኑን የጠቀሱ ቢሆንም ንብረቱ የእናታቸው ድርሻም ያለበት፣ የአሁኗ

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ለብቻቸው ይዘው እየተጠቀሙ ለማከፋፈል ፈቃደኛ ያልሆኑ መሆኑንና የሟች ሌላ ተተኪ ወራሽ መኖሩንም ጭምር ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የውርስ አጣሪን ሹሞ ጉዳዩ እንዲጣራ ከአደረገ በኋላ ሪፖርቱ በ22/06/2008 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ የቀረበ ሲሆን በዚህ ሪፖርት ላይም አስተያየት እንዲሰጥበት አድርጎ የአሁኗ ተጠሪና የሥር ከሳሽ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ሲገልፁ የአሁኗ አመልካች ግን አለኝ የሚሉትን ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ለክፍፍል ጥያቄው መሰረት የሆነው ኑዛዜ በፍርድ ቤት የፀደቀ መሆኑንና ኑዛዜው ሲፅድቅም አመልካች የነበሩ በመሆኑ በኑዛዜው ህጋዊነት ላይ የሚያቀርቡት ተቃውሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ አንጻር ተቀባይነት የለውም፣ አመልካች ሌላ የሟች ተተኪ ወራሽ አለ በማለት ያቀረቡት አስተያየትም የቀረበ ወራሽ በሌለበትና አመልካች ስለመወከላቸው የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ የአሁኗ አመልካች ያቀረቡትን ተቃውሞ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህም ምክንያት የውርስ አጣሪው ሪፖርት ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በማለት አጽድቆታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም አመልካችንና ተጠሪን ብቻ ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች ክርክር በፍርድ ቤት የጸደቀውን ኑዛዜ ያላገናዘበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ አግባብ ተቀባይነት የለውም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሠጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የበታች ፍርድ ቤቶች ሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም መስከረም 04 ቀን 1997 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ የአመልካችና የተጠሪ ወላጅ እናት የሆኑትንና የሟቹ ሚስት የነበሩትን ሟች ወ/ሮ የሺ ብሩ በሚስትነታቸው ያላቸውን ድርሻ የሚያሳጣ የሕግ አግባብ በሌለበት ሁኔታ ኑዛዜው መፅደቁ አመልካች የእናታቸውን ድርሻ በተመለከተ ቀድመው ተከራክረው የመጨረሻ ፍርድ እንዳገኙ የሚያስገነዝብ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የኑዛዜውን ይዘትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌን ባላገናዘበ መልኩ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ የተደረገ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ቀርቦ ከመያያዙም

www.abyssinialaw.com

በተጨማሪ ስለንብረቱ ክፍፍልና የኑዛዜው ይዘት ግራ ቀኙ በቃል እንዲሰሙ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች ከተሰጡት ውሳኔዎች እና አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረበችው አቤቱታ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ኑዛዜን በተመለከተ ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶአል የሚለው የተጠሪ መቃወሚያ ሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም አከራካሪ ንብረት ላይ ያደረጉት የኑዛዜው ይዘትን የሚመለከት የጉዳዩ ሥረ-ነገር ላይ ክርክር መደረጉን አያመለክትም፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የእናታቸውን ድርሻ በሚመለከተው የውርስ ሃብቱ ክፍፍል ላይ ተከራክረው የኑዛዜውን ይዘት መሰረት ያደረገ ውሳኔ ተሰጥቶአል የሚል አባባልም የለውም፡፡ በአመልካችዋ የሰበር አቤቱታ ጭምር እንደተገለጸው ቀደም ሲል በአቶ ብርሃኑ በየነ በቀረበው የውርስ ሐብት ልካፈል ጥያቄ የግራ ቀኙ ወላጅ አባት ድርሻ የሆነው ቤት ላይ ውሳኔ ተሰጥቶ በዚሁ አውራሽ ድርሻ ላይ ግራ ቀኙ ክፍፍል ያደረጉ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ቢሆንም የሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም ሚስት የነበሩትና የአመልካችና የተጠሪ ወላጅ እናት ሟች ወ/ሮ የሺ ብሩ በቤቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ በተመለከተ ግን ኑዛዜው በፍርድ ቤት ሲፀድቅ በግልፅ ተለይቶ የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ ሟች ወ/ሮ የሺ ብሩ ኑዛዜው ባረፈበት መኖሪያ ቤት ላይ ግማሽ ድርሻ /50%/ ያላቸው መሆኑ በውርስ አጣሪውም የውሳኔ ሃሳብ የቀረበበት ሲሆን የአሁኑ ተከራካሪ ወገኖችም ሆነ በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት ግለሰብ ያቀረቡት የተለዬ ክርክር ስላለመኖሩ ከክርክሩ ሂደት ለመረዳት ችለናል፡፡ ሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም ባደረጉት ኑዛዜም የአሁኗ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሚገኝበት ግቢ ውስጥ ያሉትንና በወር በብር 400.00 (አራት መቶ) የሚከራዩትን ሁለት ክፍሎችን እንዲወስዱ ሲናዘዙ "..........ከኔ ድርሻ የሚታሰብ ሁኖ........" የሚል ሐረግ ያሰፈሩበት መሆኑን የኑዛዜው ሰነድ ይዘት ያሳያል፡፡ ይህ የኑዛዜው ሰነድ ይዘት ኑዛዜው ሲፅድቅ ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ ያረፈበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ነገር የሌለው ከመሆኑም በላይ የሐረጉ ይዘትና መንፈስ ሟች ወ/ሮ የሺ ብሩ በክፍሎቹ ያላቸውን

www.abyssinialaw.com

ድርሻ የሚያሳጣ መሆን ያለመሆኑን፣ ከሌላው የውርሱ ክፍል ላይ በእነዚህ ክፍሎች ላይ ወ/ሮ የሺ ብሩ ያላቸው ድርሻ እንዲካካስ ታስቦ የተቀመጠ መሆን ያለመሆኑን የውርስ ንብረቱ ላይ ሟች ወ/ሮ የሺ ብሩ ግማሽ ድርሻ አላቸው ተብሎ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ አንጻር ታይቶ እልባት ሊያገኝ የሚገባው እንጂ ኑዛዜው በመጽደቁ ብቻ የመጨረሻ ፍርድ አግኝቶአለ ተብሎ የሚታለፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡እንግዲህ የክርክሩ አጠቃላይ ይዘትና ሊታዩ የሚገባቸው ነጥቦች እነዚህ መሆናቸው ከተረጋገጠ በተጠሪ የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የተጠሪ መቃወሚያ የተመሰረተው በኂላ የቀረበው ክስ(ጥያቄ) በቀድሞው የኑዛዜ ይጽደቅልን ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶአል በሚለው ላይ ነው፡፡ ይህን መቃወሚያ ለመወሰን አግባብነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 በመሆኑ ከቀረበው መቃወሚያ ፍሬ ነገር ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡ በተጠቀሰው ድንጋጌ አባባል በኂላ የቀረበው ጉዳይ ቀድሞ በቀረበው ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶአል ሊባል የሚችለው በሁለቱም የተነሳው ክርክር ሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አንድ አይነት ከሆነ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ በያዝነው ጉዳይ የሆነው ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ በቀድሞው ክስ ተነስቶ የነበረው ክርክር የሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም ኑዛዜ ይፀድቅልን የሚል ሲሆን፣ በሁለተኛው ክስ የተነሳው ግን ክስ በተመሰረተበት ንብረት ላይ ሟች ወ/ሮ የሺ ብሩ ድርሻ አላቸው? ወይስ የላቸውም?፣ የሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም የኑዛዜ ይዘት የሟች ወ/ሮ የሺ ብሩን ድርሻ ለሌሎች ወራሾች የሚያስተላልፋበት የሕግ አግባብ አለ? ወይስ የለም? የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ኑዛዜ ፀድቆአል በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ የሕግ ድጋፍ ያለው አይደለም፡፡ በአመልካች የእናት ድርሻ እንካፈል በሚል ለቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በመከሪከሪያነት ያቀረቡት የክርክሩንና የሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም ኑዛዜ የሚተረጎምበትን አግባብ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ አመልካች ከእናታቸው ሊያገኙት የሚገባው የሐብት ድርሻ በተመለከተ የሥረ- ነገር ክርክር ቀድሞ ታይቶአል ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ እንዲሁም አመልካች ኑዛዜው ከፀደቀ በኂላ በቀረበው ክፍፍል ውስጥ ከእናታቸው በውርስ ሊያገኙት ከሚገባው ድርሻ ተገቢውን ያላገኙ መሆኑን ገልጸው የሚከራከሩ በመሆኑ ይህም ፍሬ ነገሩ ተጣርቶ ከሚለይ በስተቀር ኑዛዜው ፀድቆአል በሚል ምክንያት ብቻ ከወዲሁ ውድቅ ሊሆን የሚችልበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ

www.abyssinialaw.com

የለም፡፡ ሲጠቃለልም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ ጋር ሊካፈሉ ስለሚገባው የእናታቸው የውርስ ንብረት ላይ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው የክርክሩን ይዘትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ስር የተመለከቱትን መመዘኛዎችን ያላሟላ በመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወሰነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 232931 በ25/04/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 193316 በ08/10/09 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች የእናታቸውን ድርሻ በተመለከተ ያቀረቡት የክፍፍል ጥያቄ ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የሟች ወ/ሮ የሺ ብሩን የውርስ ሃብት በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር በፍርድ ሐተታው ላይ በተመለከተው አግባብ ተመልክቶና በሚገባ አጣርቶ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር መጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ - 148270

ቀን - 30/09/2010

**ዳኞች፡-** ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ቡልቻ ቱሉ - ቀርበዋል፡፡

2. ወ/ሮ ወርቂ አብዲሳ - ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ተመስገን ሙላቱ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ብ/ክልላዊ መንግስት መስተዳደር በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን 2ኛ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መቃወሚያ ይዘትም በአጭሩ በኡኬ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘዉን እና አዋሳኞቹ በአቤቱታዉ ላይ የተመለከቱትን ቤት እና ይዞታ በተመለከተ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/29375 የሰጠዉ ዉሳኔ መብታቸዉን የሚነካ መሆኑን ጠቅሰዉ ወደ ክርክሩ ገብተዉ ተከራክረዉ እንዲወሰንላቸዉ መጠየቃቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ በቀረበዉ አቤቱታ መነሻነት የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ቀደም ሲል ሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ በመሻር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት እና ይዞታ አመልካቾች በጋራ የሰሩት ነዉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለምሥ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የይግባኝ መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ በወረዳዉ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይህ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ያቀረበ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎት በበኩሉ ተጠሪዎች ባልና ሚስት መሆናቸዉን እና 2ኛ ተጠሪ ጉዳዩ መብቴን ይነካል የሚትል ከሆነ ክርክሩ በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት ጣልቃ ገብታ መከራከር እየቻለች ይህን ሳታደርግ ቀርታ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ያቀረበችዉን የመቃወም አቤቱታ በመቀበል የወረዳዉ እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ሽሯል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቀበል ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 09/02/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት በቀረበ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ 2ኛ አመልካች ለወረዳዉ ፍርድ ቤት ላቀረቡት የመቃወም አቤቱታ መሠረት ያደረገችዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገዉን ክርክር መሠረት በማድረግ በመ/ቁ/29375 በቀን 07/06/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል በማለት ነዉ፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በ1ኛ አመልካች ላይ ያቀረበዉ ክስ ሲሆን፣ተሰጥቶ የነበረዉ ዉሳኔም 1ኛ አመልካች ቤትና ቦታዉን ለተጠሪ ይልቀቅ የሚል ስለመሆኑ ከግራ ቀኝ ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና 1ኛ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለምሥ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝ ተቀባይነት

www.abyssinialaw.com

ባለማግኘቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/209425 በቀን 30/06/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በወረዳዉ እና በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ዉሳኔዎች በመሻር መወሰኑን ተመልክተናል፡፡ አመልካቾች በዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጥብቀዉ ከሚከራከሩባቸዉ ነጥቦች ዉስጥ አንዱ ለመቃወም አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ መሻሩን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበን እያለ ችሎቱ ይህን ሳያጣራ ዉሳኔ መስጠቱን ሲሆን፣ ተጠሪም በጽሑፍ በሰጠዉ መልስ ቀደም ሲል በስር ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉ ዉሳኔ በይግባኝ መሻሩን በተመለከተ ክዶ ካለመከራከሩም በላይ ይህ ችሎትም የዉሳኔዉን ግልባጭ አስቀርቦ ተመልክቶታል፡፡

በሌላ በኩል አንድ ሰዉ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ የመቃወም አቤቱታ መቅረብ የሚችለዉ መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 358 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት የመቃወም አመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቶች ግምት ዉስጥ እንዲያስገቡ ከሚጠበቅባቸዉ ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱ የመቃወም አመልካችን መብት የሚነካ ዉሳኔ መኖር አለመኖሩን ነዉ፡፡ የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ 2ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን የመቃወም አቤቱታ ለወረዳዉ ፍርድ ቤት አቅርባ ጉዳዩ በክርክር ባለበት ወቅት ለመቃወም አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ በ1ኛ አመልካች ይግባኝ ባይነት በዞን እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሂደት ላይ የነበረ መሆኑን ነዉ፡፡ ጉዳዩ በከፍተኛ ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ በሂደት ላይ እያለ በጎን ለወረዳዉ ፍርድ ቤት የቀረበዉ የመቃወም አቤቱታ ከመነሻዉም ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከመቅረቡ በፊት ለመቃወም አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሽሯል፡፡ አመልካቾች ይህን ለሰበር ሰሚዉ ችሎት ገልፀዉ መከራከራቸዉን ከክርክሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የ2ኛ አመልካችን መብት ነክቷል ተብሎ ለመቃወም አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ የተሻረ መሆን አለመሆኑን ማጣራት ነበረበት፡፡

www.abyssinialaw.com

በበኩላችን እንደተመለከትንዉ 2ኛ አመልካች ላቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሽሯል፡፡ በመሆኑም ለመቃወም አቤቱታ ምክንያት የሚሆን ዉሳኔ የለም፡፡ የተሻረን ዉሳኔ መነሻ በማድረግ የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ አይኖርም፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለመቃወም አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ መሻሩን እና የ2ኛ አመልካቸን መብት ሊጎዳ የሚችል ዉሳኔ አለመኖሩን አረጋግጦ የቀረበን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል እንዲሁም ይህኑን መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ዉሳኔዎች በመሻር መወሰን ሲገባዉ ይህን ባለማድረግ የ2ኛ አመልካች የመቃወም አቤቱታ አቀራረብ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል መንፈስ የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/261961 በቀን 29/01/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/29375 በቀን 10/04/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እና የምስ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/42673 በቀን 23/06/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. 2ኛ አመልካች መብቴን ይነካል በሚል የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡበት ዉሳኔ በሌላ አግባብ ስለተሻረ እና መብቷን ሊነካ የሚችል ዉሳኔ ስለሌለ የ2ኛ አመልካች የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም፡፡
3. የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 13/02/2010 ዓ.ም የሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ቅ/ሀ**

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 144470

**ቀን** - 30/11/2010

**ዳኞች:-** ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

**አመልካች:-** ናይል ትራንዚት ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ተጠሪዎች:-** 1. ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባኒያ

2. አጉል ትራንዚት

3. አቶ ኑሩ ኡመር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢንሹራንስ ዉልን መሠረት በማድረግ በመድን ሰጪዉ የተከፈለን የጉዳት ካሳ መድን ሰጪዉ በመድን ገቢዉ ተተክቶ በተጠየቀ የመዳረግ መብት ጋር በተያያዘ የቀረበን ክርክር መሠረት በማድረግ የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ የነበሩት አቶ ኪዳኔ ታረቀኝ እና የአሁን 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ ሊገቡ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ነዉ፡፡

አመልካች በቀን 23/04/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፣ ስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ አመልካች ከፈለገ ከእነርሱ ላይ ክስ መስርቶ ካሳ መጠየቅ ይችላል በሚል ከክሱ እንዲሰናበቱ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች በየበኩላቸዉ በጽሑፍ በሰጡት መልስ፣ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚሉባቸዉንም ምክንያቶች

www.abyssinialaw.com

በመዘርዘር መልስ ሰጥተዋል፤ አመልካች ያቀረበዉ የመልስ መልስም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ እኛም የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉን ብይን አግባብነት እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ፣ አመልካች ከደንበኛዉ ጋር ባደረገዉ የዕቃ አስተላላፊነት ዉል መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ለደንበኛዉ የከፈለዉ የጉዳት ካሳ እንዲተካለት ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ የተለያዩ የመጀመሪያ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን ካቀረበ በኋላ የማጓጓዝ ስራዉ የተከናወነዉ በስር 2ኛ ጣ/ገብ በነበረዉ፣ አቶ ኪዳኔ ታረቀኝ፣ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ የጠየቀ ሲሆን፣ አቶ ኪዳኔ ታረቀኝም በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ በመግባት በሰጠዉ መልስ ያሁን 3ኛ ተጠሪ መኪና በጭነቱ ቦታ የነበረ መሆኑን ጠቅሶ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በማለት መጠየቁን ነዉ፡፡ የስር ፍርድ ቤት የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ፣ አቶ ኪዳኔ ታረቀኝ፣ እንዲሁም የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ በማድረግ ክርክር ከሰማ በኋላ 3ኛ ተጠሪ እና የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ ከክርክሩ እንዲወጡ ብይን መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ በሌሎች ሰዎች መካከል በመካሄድ ላይ ባለዉ ክርክር ጣልቃ መግባት ስለሚቻልበት ሁኔታ የፍ/ሥ/ሥርዓት ህጋችን ከአንቀጽ 40-43 ባሉት ድንጋጌዎች የተመለከቱ ሲሆን፤ ክርክሩን በመስማት ላይ ያለዉ ፍርድ ቤትም ሌላ ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ሊገባ የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ በድንጋጌዎቹ ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ግምት ዉስጥ የማስገባት ግዴታ የሚጠበቅበት ሲሆን፤ ይህን የሚያደርገዉም 3ኛዉ ወገን ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡ ይህ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ 3ኛ ወገን ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ፣ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ክርክሩ በየትኛዉም ደረጃ ላይ ቢሆን ጣልቃ ገቡ ከክርክሩ ዉጪ እንዲሆን ትዕዛዝ ከመስጠት የሚከለክለዉ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ወደ ኋላ ተመልሶ ከክርክሩ ዉጪ እንዲሆኑ ትዕዛዝ መስጠቱ ኢ-

www.abyssinialaw.com

ስነስርዓታዊ ነዉ በማለት አመልካች እያቀረበ ያለዉ ቅሬታ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገዉ 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ እንዳይቀጥል አለመደረጉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ጭብጥ ስንመለከት፤ የስር 2ኛ ጣልቃገብ፣ አቶ ኪዳኔ ታረቀኝ፣ 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሲጠይቅ በምክንያትነት የጠቀሰዉ ጉዳት የደረሰበትን ማሽነሪ የጫነዉ የ3ኛ ተጠሪ መኪና መሆኑን ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ በሌሎች ሰዎች መካከል በመካሄድ ላይ ባለዉ ክርክር ጣልቃ መግባት ስለሚቻልበት ሁኔታ የፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40-43 ይደነግጋል፡፡ የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ ያሁን 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሲጠይቅ፣ በህጉ አንቀጽ 43 መሠረት 3ኛ ተጠሪ ከእርሱ ጋር በድርሻ ካሳዉን ለመክፈል የሚገደድበትን የዉል ወይም የህግ ምክንያት ስለመኖሩ አልገለጸም፡፡ አሲያም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ሲደረግ በነበረዉ ክርክር መሠረት ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ መግባት፣ በፍት/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40 መሠረት፣ የግድ መሆኑን የሚያሳይ የህግ ምክንያት አልቀረበም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪዎችን ከክርክሩ ዉጪ በማድረግ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ብይን በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/111574 በቀን 19/07/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን፤ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/141787 በቀን 29/09/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በቀን 30/05/2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ሠ/አ**

www.abyssinialaw.com

የሰበር መዝገብ ቁጥር 154023

መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ ካሰች በቀለ
2. ወ/ሮ ባንቻየሁ በቀለ } ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-1. ውቢት ዘውዴ- ቀረቡ ፡፡

2. ትግስት ዘውዴ- ወኪል ደሳለኝ ታምራት ቀረቡ ፡፡

3. ልቡ በቀለ-ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች ከወላጅ አባታቸው ከሟች ቄስ በቀለ ሀ/ወልድ በውርስ ሊያገኙ የሚገባውን ይዞታና ግምታቸው ብር 19,000.00 የሚሆኑ ከብቶችን በ25/11/2005 ዓ/ም በተደረገ ኑዛዜ መሰረት የነቀሏቸው መሆኑን ጠቅሰው ኑዛዜው ፈርሶ ድርሻቸውን እንዲያካፍሏቸው ይወሰን ዘንድ የአቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52916 በ20/06/2009 ዓ/ም በይርጋ ውድቅ አድርጎ ብይን ሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28914 በ7/11/2009 ዓ/ም በውሳኔ፣ የኦሮሚያ ብሔረዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 270369 በ14/03/2010ዓ.ም. በትዕዛዝ ማጽናታቸው

www.abyssinialaw.com

መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካቾች በ13/06/2010 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

አመልካቾች በ12/07/2008 ዓ/ም ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘቱ ሲታይም የአመልካቾችና የ3ኛ ተጠሪ ወላጅ አባታቸው ሟች ቄስ በቀለ ሀ/ወለድ መሆናቸውን፣ ሟች በሕይወት እያለ በ25/11/2004 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ አመልካቾችን ከውርስ የነቀሉ መሆኑን ጠቅሰው ኑዛዜው ፈርሶ አመልካቾች ከሟቹ የገጠር መሬት ይዞታና ከብቶች ድርሻቸውን እንዲያገኙ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣ የኑዛዜ ወራሽነታቸውም ቀድሞ በፍርድ ያለቀ በመሆኑ አመልካቾች አዲስ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ ያለመሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ግን የአመልካቾችን ክስ ተገቢ መሆኑን በማመን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች በመስማትና ለጉዳዩ ተያያዥነት አላቸው ያላቸውን የመ/ቁጥር 35076 እና 312903 አስቀርቦ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች ኑዛዜው እንዲፈርስ የጠየቁት ከሶስት አመት በኋላ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካቾች በወላጅ አባታቸው ኑዛዜ ከውርስ የነቀለ መሆኑን ጠቅሰው ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ በተሰጠው የብይን ክፍል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በአባታቸው በ25/11/2004 ዓ/ም የተደረገው ኑዛዜ ከውርስ የነቀላቸው መሆኑን፣ ይዞታውንም በስምምነት ተካፍለው ሲጠቀሙ የነበረ ከመሆኑም በላይ ክርክሩም እኩል ደረጃ ላይ በማይገኙ ወራሾች መካከል ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን መስጠታቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካቾች አከራካሪውን የውርስ ንብረት መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም ተደረገ በተባለ ስምምነት ተካፍለው ሲጠቀሙ የነበረ ከመሆኑ አንጻር ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ

www.abyssinialaw.com

የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች በመቅረባቸውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክርና ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ብይን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎትን ምላሽ የውርስ ንብረት በስምምነት ክፍፍል ተደርጎበት የነበረ መሆን ያለመሆኑና በተለያዩ መዝገቦች በክርክር ላይ የቆዩት ወገኖች በይርጋው አቆጣጠር ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ሳይለይ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ብይን መሰጠቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ወላጅ አባታቸው ከሕግ ውጪ ከውርስ የነቀሉና ከውርስ ንብረቶች መካከል የሟችን ይዞታና ባህርዛፍ ከሟች ቁስ በቀለ ሀ/ወልድ ተወላጆች ልጆችና ወራሾች ጋር በሽማግሌ ለመከፋፈል ስምምነት አድርገው በስምምነቱ መሰረት ክፍፍል ተደርጎ ይዞታዎቹን በመጠቀም ላይ የሚገኙና የገጠር መሬት ባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተርም ያወጡበት ሁኖ እያለ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው መባሉ ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በአመልካቾች የተጠቀሰው ስምምነት የሌለ መሆኑን፣ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ የአመልካቾችን ክርክር ደግፌው የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አመልካቾች አለ የሚሉት ስምምነት የለም ከማለት ውጪ ይህ ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ መሆኑን በዚህ ችሎት ባቀረቡት የመልስ ማመልከቻቸው ገልፀው ያልተከራከሩ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም በአመልካቾች በኩል የተጠቀሰው የክፍፍል ስምምነት መኖር ያለመኖሩን በግልጽ ለይቶ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር የለም፡፡

በመሆኑም የአመልካቾች የወላጅ አባታቸውን የውርስ ንብረት ድርሻ ለመካፈል ያቀረቡት ጥያቄ የይርጋ ጊዜ ያለፈበት መሆን ያለመሆኑን አመልካቾች በክሳቸው እና በቃል ክርክራቸው ጊዜ የገለጿቸው ፍሬ ነገሮች በተለይም መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም ተደረገ የተባለ የክፍፍል ስምምነት መኖር ያለመኖሩና በዚህ ስምምነት መነሻ ድርሻ ድርሻቸውን ይዘው የሚገኙ፣ የይዞታ ማረጋጋጫ ደብተርም ከሚመለከተው አካል በሕግ አግባብ የተሰጣቸው መሆን ያለመሆኑ በማስረጃ ሳይነጥር ሊወሰን ይችል የነበረ አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካቾች ይዞታውን ሲጠቀሙ የነበረ መሆኑን፣ የወራሽነት መብታቸውን ለማስከበርም በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31290 እና 35076 ክርክር የነበረ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች የክርክር ነጥብ ደግሞ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1852 አንጻር ምን አይነት ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል በስር ፍርድ ቤት በጭብጥነት ተይዞ መታየት የነበረበት መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አንድ ተከሳሽ የቀረበበት ክስ በይርጋ የሚቋረጥ መሆኑን ከጠቀሰ ክስ አቅራቢ ወገን ክሱ በሕጉ የተመለከተው ጊዜ ገደብ (ይርጋ) ያላለፈው መሆኑን፣ ጊዜው አልፎ ከሆነም ይርጋውን ሊያቋርጥ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩን በተገቢው ማስረጃ ለማስረዳት የሚችልበት እድል ሳይሰጠው የተከሳሽ መቃወሚያ ብቻ መሰረት ተደርጎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ ብይን የሚሰጥበት አግባብ ስነ ስርዓታዊ ያለመሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 241፣ 244 እና 245(1) ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000፣ 1846፣ 1852 እና 1853 ድንጋጌዎች ጋር አጣምረን በምናነብበት ጊዜ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በተከሳሽ ወገን በቀረበ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ መስጠት ወይም የተቆጠረ ማስረጃ ካለም መስማት የሚችል ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ሕጉ በአንቀጽ 245 (1) ከተመለከተው ድንጋጌም የምንችለው ጉዳይ ሁኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች አለን የሚሉትን ስምምነት ሰነድ ትክክለኛነትና ሕጋዊነት አጣርቶና በሕጉ አግባብ ለአመልካቾች የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ካለም እንዲቀርብ አድርጎ እንዲሁም በመ/ቁጥር 31290 እና 35076 በተደረጉ ክርክሮች ይርጋው ሊቋረጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1852 ድንጋጌ አንጻር በመመርመር ሕጋዊ ውጤቱን ሳይለይ የአመልካቾችን የወላጅ አባታቸውን የውርስ ንብረት ድርሻ እንድንካፈል ይወሰንልን የሚለውን ክስ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 (1) ድንጋጌን ጠቅሶ ውድቅ ማድረጉ ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ሁኖ አልተገኘም፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ብይን ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከአመልካቾች የክርክር ነጥቦች ጋር ያላገናዘበ ሁኖ እያለ ማጽናታቸውም ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. በሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52916 በ20/06/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28914 በ7/11/2009 ዓ/ም በውሳኔ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 270369 በ14/03/2010 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 52916 ቀጥሎ አመልካቾች በወላጅ እናታቸው ድርሻ ላይ ያቀረቡትን ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት በዚህ ችሎት የፍርድ ሐተታ ላይ በተመለከተው አግባብ ይዞታው መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም ተደረገ በተባለ ስምምነት በአመልካቾች ተይዞ ቆይቷል ወይስ አልቆየም፣ አመልካቾች ይዞታውን ከኑዛዜ ተጠቃሚዎች ጋር ክፍፍል አድርገው ከሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ አውጥተውበት ይገኛሉ? ወይስ አይገኙም?፣የይዞታ ማረጋገጫ አግኝተው ከሆነ ሰነዱ የተሰጣቸው የሕግ አግባብ ምንድን ነው?፣ በመ/ቁጥር 31290 እና 35076 ሲካሄዱ በነበሩት ክርክሮች ሲሳተፉ የነበሩ ተከራካሪ ወገኖች እነማን እንደሆኑና በጉዳዮቹ ላይ የተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘቱ ምን እንደሚል፣ እንዲሁም በይርጋው ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ምን እንደሆነ በመመርመርና በግራ ቀኙ እና አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ሁሉ እንዲጣሩ ካደረገ በኃላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ብይን እንዲሰጥ እና ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም የሚባል ከሆነም በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የቀረበለትን ክርክር በአግባቡ አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ 152845

መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- አቶ መሀመድ በሀዲን-አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- ዘምዘም አሊ-አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የይግባኝ ጊዜን የሚመለከት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ያቀረበው ታሕሳስ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ላቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ ማስፈቀጃ ምክንያት ያቀረበ ቢሆንም የይግባኝ ማስፈቀጃ ምክንያቱ በቂ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 326 መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የፌዴራሉ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00079 በቀን 15/02/2010 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አመልካች የይግባኝ ማመልከቻ አቅርቤ ግልባጩ የተሰጠኝ በቀን 13/04/2010 ዓ.ም በእለተ አርብ ነው፤አመልካች ቅዳሜ እና እሁድ የመንግሥት ሥራ ዝግ ስለሆነ ታሕሣሥ 16 ቀን 2010 ዓ.ም የይግባኝ ቅሬታዬን ለፍ/ቤቱ ያቀረብኩ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የይግባኝ ጊዜው አልፏል በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት

www.abyssinialaw.com

የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቱ አመልካች ይግባኙን በቀን 16/04/10 ዓ.ም ማቅረቡን በገለጸበት ሁኔታ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው አልፏል በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ:- ይግባኝ የተጠየቀበት ውሳኔ የተሰጠው በቀን 15/02/10 ዓ.ም ሲሆን አመልካች ይግባኙን ያቀረበው በቀን 16/04/10 ዓ.ም በመሆኑ በራሱ ቸልተኝነት የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፤የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ የሚቆጠረው ቀኖቹን በተከታታይ በመቁጠር እንጂ ቅዳሜ እና እሁድን በመተው አይደለም፤አመልካች በበቂ ምክንያት የተደገፈ የይግባኝ ማስፈቀጃ ያላቀረበ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ይግባኝ የተጠየቀበት ውሳኔ የፌዴራሉ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00079 በቀን 15/02/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሆኑ፤አመልካች ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቀው በቀን 12/04/10 ዓ.ም መሆኑን፤አመልካች የመዝገብ ግልባጭ የተሰጠው በቀን 13/04/2010 ዓ.ም በእለተ አርብ መሆኑ እና ይግባኙን ያቀረበው በቀን 16/04/2010 ዓ.ም መሆኑን የድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በቀን 13/04/10 ዓ.ም የጻፈው መሸኛ ደብዳቤ ያሳያል። ከደብዳቤው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ታሕሣሥ 12 ቀን 2010 ዓ.ም እና ታሕሣሥ 13 ቀን 2010 ዓ.ም የሆኑን ሁለቱ ቀናት በአመልካች ጥፋት ያልባከኑ መሆኑን ነው።

በመሠረቱ የይግባኝ አቤቱታ አቀራረብ የሚመራው በሥነ-ሥርአት ሕጉ በተዘረጋው ሥርአት መሠረት ነው። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323/2 ድንጋጌ የመጀመሪያ ደረጃው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ፤ብይን ወይም ትእዛዝ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን የይግባኙን አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማቅረብ ያለበት ይግባኝ በሚባልበት ጉዳይ ላይ

www.abyssinialaw.com

በተፈረደ በ60 ቀን ውስጥ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ያላቀረበ ተከራካሪ ወገን ይግባኙ እንዲከፈት ይግባኝ ማስፈቀጃ ማቅረብ እንዳለበት የዚሁ ሕግ ቁጥር 324 ያስገነዝበናል፡፡ የይግባኝ ማስፈቀጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም በዚሁ ሕግ ቁጥር 326 መሠረት ይግባኝ ጠያቂው ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለበትን ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑን መርምሮ ይግባኙ እንዲከፈት ሊፈቅድ ወይም ሊከለክል እንደሚችል ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ አመልካች የፌዴራሉ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00079 በቀን 15/02/2010 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ መጠየቅ ይችል ዘንድ ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቀው የ60 ቀኑ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሳያልፍ በቀን 12/04/10 ዓ.ም ሲሆን የመዝገብ ግልባጭ የተሰጠው ደግሞ በቀን 13/04/2010 ዓ.ም በእለተ አርብ በመሆኑ ይግባኙ የሚቀርብበት የመጨረሻው ቀን የመንግስት ሥራ ዝግ በሆነበት ቀን ላይ አርፏል፡፡አመልካችም በቀጣዩ ቀን ታሕሳስ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ይግባኙን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበው ምክንያት በቂ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 326 መሠረት መዝገቡን የዘጋው ቢሆንም የይግባኝ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ከሆኑት ስልሳ ቀናት ውስጥ ሁለቱ ቀናት በአመልካች ችግር የባከኑ ካለመሆናቸው ባሻገር ይግባኝ የማቅረቢያው የመጨረሻ ቀን የመንግስት ስራ ዝግ በሆነበት ቀን ላይ ያረፈ በመሆኑ፤የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1862 ግዴታው የሚፈጸምበት ቀን ከአንድ የበአል ቀን ጋር ከገጠመ በዓል ባልሆነበት በማግስቱ ባለው የሥራ ቀን እንደሚተላለፍ በሚደነግገው አግባብ በተመሣሣይ ሁኔታ አመልካችም ጊዜ ሳያባክን በቀጣዩ የሥራ ቀን ይግባኙን አዘጋጅቶ ያቀረበ ከመሆኑ እና ይግባኝ ሕገ መንግስታዊ ዋስትና ያለው መብት ከመሆኑ አኳያ አመልካች ይግባኙ እንዲከፈት ያቀረበው ምክንያት በቂ ነው ተብሎ ይግባኙ እንዲከፈት መፍቀድ ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት ይግባኙ እንዲከፈት መፍቀድ ሲገባው አመልካች ይግባኙ እንዲከፈት ያቀረበው ምክንያት በቂ አይደለም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 00039 ታሕሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሸሯል፡፡
2. አመልካች ይግባኙ እንዲከፈት ያቀረበው ምክንያት በቂ ምክንያት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 326/1 መሠረት ይግባኙን እንዲያቀርብ ተፈቅዶለታል፡፡
3. አመልካች የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በአሥር ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ያቅርብ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.139313

መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች - ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፀሃይ መንክር

አመልካች - የኢትዮጵያ አየር መንገድ አልቀረቡም

ተጠሪዎች - 1ኛ. ወ/ሮ መሰረት ፍቃዱ ተወካይ አበበች ዘመድኩን ቀረቡ

2ኛ. ገልፍ አየር መንገድ ጠ/ ዮዲት ጉርጂ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፉት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሣሽ ሲሆኑ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞተ ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት በታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም ከሳውዲ አረቢያ ወደ ኢትዮጵያ በአየር መንገዱ ተሳፍሬ ግምታቸው ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) የሚያወጡ ልብሶች እና ቁሳቁሶች በመያዝ የመጣሁ ሲሆን የመጣው ዕቃ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ ሴክሽን ከሌላ ዕቃ ጋር በመለዋወጡ ጠፍቷል፤ እነሱ ደግሞ 2ኛ ተጠሪን ጠይቂ እያሉ እያመላለሱኝ ይገኛሉ፤ በመሆኑም ንብረቴ በመጥፋቱ የንብረቱ ግምት ይከፈለኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
2. አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ዕቃውን ሊረከብ የቻለው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባለው የማመቻቸት ስምምነት መሰረት ነው፤ በዚህ ስምምነት የአመልካች

www.abyssinialaw.com

ኃላፊነት ዕቃው መጥፋቱን ለ2ኛ ተጠሪ ማሳወቅ ብቻ ነው፤ በዚህም መሰረት አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ አሳውቋል፤ ስለሆነም ኃላፊነት የለብኝም፤ በሌላም በኩል የዕቃው ግምት ብር 30,000.00 ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

3. 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ ከአመልካች ጋር ባላቸው ስምምነት መሰረት አመልካች የ2ኛ ተጠሪ የካርጎ ወኪል ነው፤ የ2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት ዕቃውን የማጓጓዝ ብቻ ነው እንጂ ዕቃዎቹ በአግባቡ መጫናቸውን እና መውረዳቸውን በሚመለከት የአመልካች ኃላፊነት ነው፤ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ ስለጉዳዩ ያሳወቀው ነገር የለም፤ ዕቃው የጠፋው በአመልካች ካርጎ ሴክሽን ውስጥ ከሌላ ዕቃ ጋር በመቀያየሩ ነው፤ ስለሆነም ዕቃው የጠፋው በአግባቡ ከተጓጓዘ በኃላ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ምንም ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡
4. ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው ንብረት የጠፋው በ2ኛ ተጠሪ ጥፋት ሳይሆን በአመልካች ካርጎ ክፍል “ዕቃ ተቀያይሮ” መሆኑ የታመነ ፍሬ ነገር በመሆኑ የመካስ ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነው፤ ሊከፍል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተም አመልካች ዕቃው በጠፋ ጊዜ ከሳሽን ያስፈረማቸው ሰነድ ላይ የጠፋው ዕቃ የዋጋ ግምት በማለት ያስፈሩት 4,500 የሳውዲ ሪያል ወይም ብር 26,426.00 (ሃያ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሃያ ስድስት) በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከነወለዱ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡
5. በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የይግባኝ ክርክሩን ከሰማ በኃላ አመልካች ኃላፊ ነው ተብሎ ገንዘቡን እንዲከፍል መወሰኑን የተቀበለው ሲሆን 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ውል የፈፀመ በመሆኑ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ ቢኖርበትም ከሳሽ ባቀረቡት ክስ ላይ ስሙ ከመጠቀሱ ውጪ የዳኝነት ጥያቄ ያልቀረበበት በመሆኑ ከፍ/ብሄር ስነ ስርዓት አንፃር በግልፅ ባልተጠየቀ ዳኝነት የካሳ ገንዘቡን 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍል የሚወሰንበት አግባብ የለም፤ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ሊፀና ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

6. የሰበር ቅሬታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 12/2009 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር ማመልከቻ ዕቃው ከሳውዲ አረቢያ ወደ አዲስ አበባ የመጣው በ1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል ባለው የማጓጓዝ ውል መሰረት በመሆኑ፤ በዋርሶው ስምምነት አንቀጽ 18(2) መሰረት አጓዡ ዕቃውን አጓጉዞ መብት ላለው ሰው እስከሚያስረክብ ድረስ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የሚደነግግ በመሆኑ፤ አመልካች ዕቃውን ሊረከብ የቻለው ዕቃውን ከ2ኛ ተጠሪ ተረክቦ 2ኛ ተጠሪን በመወከል ለ1ኛ ተጠሪ ለማስረከብ በገቡት የማመቻቸት ውል ከመሆኑ ወጪ በ1ኛ ተጠሪ እና በአመልካች መካከል የውልም ሆነ የህግ ግንኙነት ባለመኖሩ አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ አመልካች ኃላፊነት የለበትም በሚል እንዲወሰን ጠይቋል፡፡
7. ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ 2ኛ ተጠሪ የንብረቱ አጓዥ ሆኖ እያለ ከኃላፊነት ውጪ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡
8. 1ኛ ተጠሪ ሚያዚያ 16/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች የ1ኛ ተጠሪን የንብረት ግምት ከፍሎ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባላቸው ግንኑነት መሰረት 2ኛ ተጠሪን ከሶ ከመጠየቅ ውጪ የ1ኛ ተጠሪን ንብረት አልከፍልም በማለት ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡
9. 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ሚያዚያ 25/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ዕቃው የጠፋው በአመልካች አየር መንገድ ካርጎ ሴክሽን ክፍል ውስጥ ከሌላ ዕቃ ጋር ተቀያይሮ መሆኑ በአመልካች በራሱም የታመነ በመሆኑ አመልካች በቸልተኝነት ከሌላ እቃ ጋር በማቀያየር እንዲጠፋ ማድረጉ አመልካችን በኃላፊነት ከሚያስጠይቀው ውጪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ግንኙነት የለውም፤ 2ኛ ተጠሪ ዕቃውን አላጓጓዘም እንጂ አጓጉዟል ቢባል እንኳ ዕቃው የጠፋው በአግባቡ ከተራገፈ በኋላ በአመልካች ካርጎ ሴክሽን ክፍል ውስጥ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ምንም አይነት ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቹም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

www.abyssinialaw.com

10. ከፍሲ.ል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥና በሰበር የተደረገውን ክርክር ሲሆን በበኩላችን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ውል የፈፀመ በመሆኑ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ እንደሚኖርበት ወስኖ ነገር ግን ከሳሽ ባቀረቡት ክስ ላይ ስሙ ከመጠቀሱ ውጪ የዳኝነት ጥያቄ አልቀረበበትም በሚል ገንዘቡን 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍል የሚወሰንበት አግባብ የለም በማለት መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡
11. ይህን ጭብጥ ለመወሰን የሥር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተቀበሉትን እና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የዋርሶ ስምምነት (በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 እንደተሻሻለ) ተገቢ ድንጋጌዎችን ይዘትና ትርጉም እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ መርምረናል፡፡
12. ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው የሥር ሁለቱም ተከሳሾች ዕቃው ስለመጥፋቱ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይልቁንም የየበኩላቸውን ክርክር በማቅረብ ኃላፊነት እንደሌለባቸው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች አከራካሪውን ንብረት መረከቡን እና ከእጁ የጠፋ መሆኑን ሳይክድ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ከከሳሽ ጋር የማጓጓዝ ውል ያደረገው 2ኛ ተጠሪ ሊሆን እንደሚገባና ዕቃውን ሊረከብ የቻለው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባለው የማመቻቸት ስምምነት መሰረት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን አመልካች ንብረቱን የተረከበ መሆኑና የጠፋውም በአመልካች ዕቃ ማስቀመጫ ካርጎ ሴክሽን ውስጥ የመሬት መስተንግዶ ስራ ግዴታውን በሚፈጽምበት ጊዜ ከሌላ ዕቃ ጋር ተቀያይሮ መሆኑ ያልተካደ በመሆኑ በዚህ መልኩ በአመልካች ጥፋት ለጠፋው ንብረት አመልካች ኃላፊ የማይሆንበት የህግ ምክንያት የለም፡፡
13. በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ዕቃውን አላጓጓዝኩም እንጂ አጓጉዘሃል ብባል እንኳ ዕቃው የጠፋው በአመልካች እጅ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ዕቃውን በውል በማጓጓዙ ከውል የመነጨ ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ በ2ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበ ቅሬታ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ካሳውን ሊከፍል አይገባም በማለት የወሰነው በቀረበው ክስ በግልጽ ዳኝነት አልጠየቀበትም፤ ከፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ድንጋጌዎች አንጻር በግልጽ ባልተጠየቀ ዳኝነት 2ኛ ተጠሪ

www.abyssinialaw.com

ካሳውን እንዲከፍል የሚወሰንበት ምክንያት የለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የአሁን አመልካችን እና 2ኛ ተጠሪን በተከሳሽነት በመሰየም ኃላፊነት ያለበት ወገን ተለይቶ እንዲወሰንላቸው ባቀረቡት ክስ ተጓጉዞ የመጣው ዕቃ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ ሴክሽን ከሌላ ዕቃ ጋር በመለዋወጡ የጠፋ በመሆኑና አመልካችም 2ኛ ተጠሪን ጠይቂ እያለ እያመላለሳቸው መሆኑን ጠቅሰው የንብረቱ ግምት እንዲከፈላቸው መጠየቃቸውን ከክሱ መረዳት ይቻላል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 36(5) እንደተደነገገው ከሳሽ መብቱን ማግኘት የሚገባው ከየትኛው ተከሳሽ ላይ እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ የሚያጠራጥር ሁኔታ ያጋጠመው ሲሆን አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሰዎች በህብረት በመክሰስ አላፊነቱ የሚመለከተው የትኛው እንደሆነ ተለይቶ እንዲወሰንለት ለማመልከት ይችላል፡፡ ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ በዚህ አግባብ በሁለቱ ተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረባቸው የሚነቀፍ ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ በክሱ ስሙ ከመጠቀሱ ውጪ የዳኝነት ጥያቄ አልቀረበበትም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ እና ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

14. በአጠቃላይ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ 2ኛ ተጠሪን በተከሳሽነት ስሙን ከማስገባት ውጪ በሱ ላይ ዳኝነት ስላልጠየቁ 2ኛ ተጠሪ ካሳ ሊከፍል አይገባም በማለት የተደረሰበት መደምደሚያ የቀረበውን ክስ እና ከፍሲል የተጠቀሰውን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 102697 ሀምሌ 8 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ፤ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 182461 መጋቢት 1/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በ1ኛ ተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት 2ኛ ተጠሪ ከውል የመነጨ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ተረጋግጦ ከተወሰነ በኋላ የዳኝነት ጥያቄ አልቀረበበትም ገንዘቡን

www.abyssinialaw.com

ሊከፍል አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የዳኝነት ጥያቄውን እና ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ተሽሯል፡፡

3. አመልካች ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ብር 26,426.00 (ሃያ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሃያ ስድስት) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለ1ኛ ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
5. መጋቢት 20/2009 ዓ.ም በዋለ ችሎት በሥር ፍርድ ቤት በመ/ቁ 153294 የተጀመረው አፈፃፀም እንዲታገድ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 153610

መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፊይዛ ከሚል ጠበቃ ልሣነወርቅ ተኪ- ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ አህመድ -ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጠተናል፡፡

**ፍርድ**

የክርክሩ ምክንያት የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክር ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች የካቲት 10 ቀን 2007 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በ23/04/2007 ዓ/ም በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱ፣ በትዳር ውስጥ ከሚያዚያ 1995 ዓ/ም ጀምሮ ከቤት እስከወጡበት የካቲት 2006 ዓ/ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ ን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ ባለአንድ ፎቅ ዘመናዊ ቪላ ቤት፣ የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ A-13872 የሆነና ግምቱ ብር 550,000 የሚያወጣ ያሪስ መኪና፣ በሀሰን ላውንደሪ ንግድ ቤት ውስጥ በአቶ ሰኢድ ሙዘይን ዳኝነትና በአቶ ኤልያ ሰይድ ጸሓፊነት ብር 480,000.00 የእቁብ ገንዘብና የቤት ቁሳቁሶችን ያፈሩ መሆኑን ዘርዝረው ክፍፍሉ እንዲደረግ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ዳኝነት የተጠየቀበት ቤት የተሰራው በ12/01/1994 ዓ/ም ሆኖ አመልካችና ተጠሪ ደግሞ በሸሪዓ ህግ መሰረት የተጋቡት ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም በመሆኑ ንብረቱ የተፈራው ከጋብቻ በፊት

መሆኑን፣ ቤቱን ለመስራት የሚያሥችላቸው ገቢ ስላልነበራቸውም አባታቸውን በላውንደሪ ስራ ስለሚረዱ ቤቱን ከጋብቻ በፊት ወላጅ አባታቸው አቶ አህመድ መሃመድ ሰርተው የሰጧቸው መሆኑን የእቁብ ገንዘብ በጋብቻ እያሉ ታህሳስ 29 ቀን 2004 ዓ/ም ደርሶአቸው ለትዳራቸው ለጋራ ጥቅም ያዋሉት መሆኑን በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ በቤት ቁጥር 069 በአቶ መሃመድ ይማም ዳኘነት፣ በአቶ እንድሪስ አለሙ ጸሐፊነት፣ በአቶ ወንድሜነህ አለሙ ሰብሳቢነት የነበረው እቁብም ለመክፈል ባለመቻላቸውም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38976 ክስ ቀርቦባቸው ገንዘቡን እንዲከፍሉ ታህሳስ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ተወስኖባቸው ከወጪ ኪሳራ ጋር ብር 149,365.95 እንዲከፍሉ በመገደድ መኪናውን ሸጠው እዳውን ከከፈሉ በኂላ ቀሪውን ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ያዋሉ መሆኑን፣ አመልካች ከቤት የወጡት የካቲት 26 ቀን 2006 ዓ/ም ሳይሆን ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ/ም መሆኑን፣ በአቶ ሀሰን ላውንደሪ በአቶ ሰይድ ሙዘይን ዳኘነት በአቶ ኤልያስ ሰይድ ጸሐፊነት በሚሰበሰብ እቁብ ውስጥ የሌሉበት መሆኑን እና የቤት ቁሳቁሶችን ቢካፈሉ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን ሰባት ጭብጦችን በመመስረት የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል ሰምቶና ጉዳዩን መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ ሲፈርስ በሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም የተደረገ ጋብቻ ፈርሷል የተባለ ቢሆንም ተጠሪው የጋብቻ ሰርተፊኬት ጋብቻው በሐይማኖት ስርዓት ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ተፈፅሞ በውልና ክብር መዝገብ ሹም አገልግሎት በ09/09/2003 ዓ/ም ተመዝግቦ ህጋዊ መረጃ እንደተሰጣቸው የሚያሣይ ማስረጃ ያቀረቡና አመልካችም ይህንን ማስረጃ አልካዱም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ እና ቀድሞ በፍቺ ጊዜ ጋብቻው የተፈጸመበት ጊዜ ሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም ነው ተብሎ የተሰጠውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 ስር የሚወድቅ ስህተት ነው በማለት ይህንኑ ስህተት ነው ያለውን ጊዜ አርሞ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻው የተፈጸመው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ነው፣ ቤቱ የተሰራውም ከዚህ በፊት መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠሪ የግል ሃብቱ ነው፣ አመልካች ከቤት የወጣችው ከየካቲት 2006 ዓ/ም በፊት ነው፣ በጋብቻ ጊዜ የጋራ እዳ የነበራቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ኮድ ቁጥር 2 A-13872 መኪና ለጋራ

www.abyssinialaw.com

እዳ የተሸጠ መሆኑ ስላልተረጋገጠ መኪናው የጋራቸው ነው፣ እቁቡን በተመለከተም የወጣላቸው መሆን ያለመሆኑንና የገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ አመልካች ያላስረዱና ተጠሪ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ መሆኑም ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ የቤት ዕቃዎችን በተመለከተ በተጠሪ በታመነው መሰረት እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህ ውሰኔ ውስጥ በጋብቻ ጊዜ፣ በቤቱና በእቁቡ ላይ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኗ አመልካች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለፌዴደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 መሰረት የጋብቻውን ጊዜ ማረሙ ፍፁም የሥነ ስርዓት ህጉንና መሰረታዊ የዳኝነት አሰራር መርህን ያልተከተለ መሆኑን ከገለጸ በኋላ በውጤት ደረጃ ግን ለጋብቻ መኖር መቅረብ ያለበት የጋብቻ ምስክ ወረቀት በመሆኑ ይኼው ሰነድ መቅረቡ ተገቢ እንደሆነ ዘርዝሮ ጋብቻው የተፈፀመው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍልና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በቤቱ ላይ ተሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ጋብቻ እንዲፈርስ ውሳኔ በሰጠበት ጊዜ ጋብቻው በሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም መሆኑን በግልጽ አስፍሮ ውሳኔ በሰጠበት እና በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔም በይግባኝ ባልተለወጠበት ሁኔታ በንብረት ክርክር ጊዜ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ተቀብሎ ጋብቻው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም የተፈጸመ ነው በማለት መወሰኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 ጋር አብሮ በማይሄድ ምክንያት ከመሆኑም በላይ አመልካችና ተጠሪ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ግንኙነት ፈጥረው በ1996 ዓ/ም አመልካች አርግዘው በ1997 ዓ/ም ልጅ የወለዱ መሆኑና ቤቱም ተጠሪ በ1994 ዓ/ም በጨረታ ባገኙት ቦታ ላይ በትዳር ውስጥ መሰራት ተጀምሮ ቤቱ ተሰርቶ የተጠናቀቀው በ2000 ዓ/ም መሆኑ ከሚመለከተው አካል ለስር ፍርድ ቤት በተላከው ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ እያለ ይኼው ማስረጃና በጉዳዩ ላይ የተሰሙት ምስክሮች ቃል በአግባቡ ሳይታይ መታለፉን፣ የእቁብ ገንዘብን በተመለከተ አመልካች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ፈጽመው ምስክሮችን አላቀረቡም የተባለው አመልካችም መጥሪያውን ለእቁቡ ዳኛና ሰብሳቢ ለማድረስ ጥረት አድርገው ምስክሮቹ አውቀው እየተደበቁ ስላስቸገሩኝ በሚኖሩበት ወረዳ

www.abyssinialaw.com

አስተዳደር በኩል እንዲደርሳቸው በማለት በቃለ መሃላ አቤቱታ አመልካች አቅርበው እያሉ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ በማየት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው ምስክሮቹ በአመልካች ጉድለት እንዳልቀረቡ በመቁጠር ውሳኔ መስጠቱ ያላግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም  በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡ እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤትና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መዛግብትም እንዲመጡ ተደርጎ የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት መዝገብ  መጥቶ የሥር ፍ/ቤት የመዝገብ ግልባጭ የያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሥፈልጋቸው አበይት ጭብጦች የሥር ፍርድ ቤት በፍቺ ውሳኔ የለየውን የጋብቻ ጊዜ በንብረት ክርክር ጊዜ በመመልከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 መሰረት ማገረሙ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተጠሪ የግሉ ነው በማለት የወሰነበት አግባብና እቁቡን በተመለከተ የተሰጠው ዳኝነት ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት እያንዳንዳቸውን ነጥቦች በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

የመጀመሪያውን የጋብቻ ጊዜውን በተለመከተ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ሁለት ጊዜ  ውሳኔ የሰጠ መሆኑን የክርክ ሂደት ያስገነዝባል፡፡ ይኼውም አንዱ በፍቺ ውሳኔ ጊዜ ሲሆን በዚህ ጊዜ ጋብቻው በሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም የተፈጸመ መሆኑን ማረጋገጡን አምኖ ጋብቻው እንዲፈርስ መወሰኑን በ23/04/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ያስገነዝባል፡፡ ሁለተኛው ውሳኔ በንብረት ክርክር ጊዜ የተሰጠ ሲሆን በዚህ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው ተጠሪው ጋብቻው የተፈፀመው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ነው በማለት ተከራክረው በዚህ ረገድም የጋብቻ ምስክር ወረቀት ለማስረጃነት አቅርበው ይኼው የሰነድ ማስረጃ ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም የተፈፀመው ጋብቻ ግንቦት 09 ቀን 2003 ዓ/ም በውልና ክብር መዝገብ ስም አገልግሎት መመዝገቡን የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሶና ቀድሞ በፍቺ ውሳኔ ጊዜ ጋብቻው  ሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም የተፈፀመ ነው የተባለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 208 ድንጋጌ መሠረት ሊታረም ይገባዋል በማለት

www.abyssinialaw.com

የሠጠው ውሳኔ ነው ፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው የሥር ፍርድ ቤት በፍቺ ውሳኔ ላይ ጋብቻው የተፈጸመው ሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም መሆኑን በግልጽ ዳኝነት ሰጥቶ ከቆዩ በኃላ በስርዓቱ መሰረት በበላይ ፍ/ቤት ባልተለወጠበት ሁኔታ በንብረት ክርክር ጊዜ ጋብቻዉ የፈፀመዉ ጥር 20 ቀን 1997ዓ.ም ወደሚለዉ ድምዳሜ የደረሰና ለዚህ ዉሳኔ አሰጣጥ ተገቢ ነዉ ብሎ በዋቢነት የጠቀሰው ድንጋጌም የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 208 መሆኑን ነዉ፡፡

የክርክሩ መነሻ ጋብቻን መሰረት ያደረገ ሲሆን የሚመራዉም በተሻሻለዉ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ድንጋጌዎችና በፍታብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ እንዲሁም አግባብ ባላቸው የአዋጅ ቁጥር 25/1988 ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 እንደተመለከተዉ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረ ክርክር ተገቢዉን ዉሳኔ ካገኘ በኃላ በይግባኝ የሚታየዉ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ሲሆን ይህ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ፡፡ በዉሳኔዉ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚለዉ ወገን አቤቱታን ማቅረብ ያለበት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነዉ፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ታይቶ የተሰጠዉን ዉሳኔ ከሻረዉ ግን በዉሳኔዉ ላይ ቅሬታ ያለበት ወገን ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ማቅረብ እንደሚችልም በአዋጁ ተመልክቷል፡፡ ይህ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ ተከራካሪ ወገን ከዚህ በኃላ አቤቱታዉን ሊያቀርብ የሚችለዉ ለሰበር ችሎት ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጪ በሆነ ሁኔታ ዉሳኔዉ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል አይችልም፡፡ ይህ እንግዲህ አጠቃላይ ሂደቱ (ስርአቱ) ሲሆን ዉሳኔዉን በመቃወም ወደ በላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት ወይም አቤቱታ ለማቅረብ የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን ውሳኔውን በሰጠዉ ፍ/ቤት ሊታረም የሚገባ ወይም የሚችል ስህተት አለ ብሎ ካመነ ወደ በላይ ፍ/ቤት አቤት ከማለቱ በፊት ዉሳኔዉን ለሰጠዉ ፍ/ቤት አቤቱታ የሚያቀርብበት ስርአት እንዳለም ይታወቃል፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 208 ጥያቄ የሚነሳዉም እዚህ ላይ ነዉ፡፡

የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 208 ርእሱ እንደሚያመለክተዉ "ስህተት ስለማረም" በሚል የተደነገገ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት (ዉሳኔዉን የሰጠዉ) ሊያርም ወይም ሊያስተካክል የሚችለዉ በሰጠዉ ዉሳኔና ትእዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት

የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት መኖሩን ካረጋገጠ ብቻ ነዉ። ይህ ደግሞ ግልጽ ነዉ። በክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ እና ተያያዥነት ባለዉ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠዉን ዉሳኔ ስህተትን ማረም በሚል ሊያሻሽል ወይም ሊለዉጥ አይችልም።

በያዝነዉ ጉዳይ እንደምናየዉ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ የሰጠበት ክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረዉ ጋብቻ የተፈፀመበት ጊዜን የሚመለከት ይህንንም ፍ/ቤቱ ከመረመረዉ በኃላ በ 23/4/2007ዓ.ም በሰጠዉ የፍቺ ዉሳኔ ጊዜዉ ሚያዝያ 1995ዓ/ም የሚል ግልጽ ዉሳኔ ሰጥቶበታል። ይህ ዉሳኔ በበላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ወይም በሰበር ስርዓት ቀርቦ ስለመለወጡ የሚያሳይ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ተጠሪ አላቀረቡም። በ 23/4/2007ዓ.ም የፍቺ ዉሳኔ ከተሰጠ በኃላም ተጠሪ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 208 የተመለከተዉን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የጋብቻ ጊዜዉ እዲሻሻል አቤቱታ አላቀረቡም። ጉዳዩ በቤተሰብ ሕጉ የሚገዛ እንደመሆኑ መጠን የጋብቻዉን ጊዜ በፍቺ ዉሳኔ ለይቶ መወሰን ጋብቻዉ በንብረት ላይ ስለሚኖረዉ ህጋዊ ዉጤት ለመወሰን እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነዉ። ተጠሪ በፍቺ ጊዜ ጋብቻው የተፈፀመዉ ሚያዝያ ወር 1995ዓ/ም ነዉ ተብሎ በግልጽ የተወሰነዉን የዉሳኔ ክፍል በበላይ ፍ/ቤት ሳያስቀይሩ በንብረት ክፍፍል ላይ ክርክር ሲደረግ የጋብቻዉ ጊዜ 1995ዓ/ም ሳይሆን ጥር 20 ቀን 1997ዓ/ም በማለት ያቀረቡት ክርክር በይዘቱ ሲታይ በፍቺ ዉሳኔ ላይ የተሰጠዉን መሰረታዊ የፍርድ ይዘት የሚቀይር እንጂ በተሰጠዉ ዉሳኔና ትእዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት እንዲታረም የቀረበ ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም። ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤት የተከተለዉ የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ የስነ ስርዓት ሕጉንና መሰረታ የዳኝነት አሰራር መርህን ያልተከተለ መሆኑን እያረጋገጠ ለጋብቻ መኖር መቅረብ ያለበት የጋብቻ ምስክር ወረቀት ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በተጠሪ በኩል በይግባኝ ስርዓት ወይም በመስቀለኛ ይግባኝ አግባብ ጊዜዉን ጠብቆ የቀረበለት አቤቱታ በሌለበት በመሆኑ በህግ አግባብ ያልቀረበለትን ክርክርና ማስጃ በመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መቀበል የሚቻልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ያላገናዘበ በተለይም በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.342 አግባብ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ ምክንያቱን ለዉጦ የሚያጸናዉ በሕግ አግባብ

የቀረበ ክርክርና ማስረጃ መኖሩን በማረጋገጥ ስለመሆኑ የተመለከተዉን ድንጋጌም ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ጥያቄ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የሚስተናገድ ባልሆነበት ሁኔታና የጋብቻውን ጊዜ በፍቺ ውሳኔ ጊዜ ለይቶ መወሰን በንብረት ክፍፍሉ ክርክር ላይ የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎችን በትክክል ለመተግበር የሚያስችል በሆነበት ሁኔታ ይህንኑ በጣሰ መልኩ ጋብቻው የተፈፀመው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ.ም ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይኼው የስር ፍርድ ቤት የፍርድ አሰጣጥ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 ድንጋጌ የወጣ መሆኑ ከተረጋገጠ በኃላ የጋብቻ መኖር በቅድሚያ ለማስረዳት የሚቻለው የጋብቻ ምስክር ወቀት በማቅረብ ነው በሚል ምክንየት ብቻ በስነ ስርዓት ሕጉ ያልቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመቀበል በውጤት ደረጃ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የተቀበለበት አግባብ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻው የተመሰረተው በሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም ነው ወደሚል ድምዳሜ ደርሰናል፡፡

ቀጥለን የተመለከትነው በጋብቻ ውጤቶች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ተገቢነት ሲሆን በአመልካች እስከዚህ ችሎት ከሚከራከሩባቸው ንብረቶች መካከል አንዱ በኢዲስ አበባ ከተማ ን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ባለአንድ ፎቅ ዘመናዊ ቪላ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ይህን ቤት የግል ንብረት ነው በማለት የሚከራከሩት ቤቱ የተሰራው በ12/01/1994 ዓ/ም ነው፣ ጋብቻው ደግሞ ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ነው የተፈፀመው በሚል ነው፡፡ ሆኖም ጋብቻው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ.ም ነው የተፈፀመው የሚለው የተጠሪ ክርክር ከላይ በዝርዝር በተመለከተው ሰነ ስርዓታዊ በሆነ ምክንያት ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ቤቱ የተሰራው በ12/01/1994 ዓ/ም የሚለው ክርክር ግን በስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የተሰሙት ምስክሮች ከሰጡት የምስክርነት ቃልና የክፍሉ የመንግስት አስተዳደር አካል ለስር ፍርድ ቤት ከሰጠው ማስረጃ አንፃር ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ሶስት ምስክሮችን ያሰሙ ሲሆን የሰጡት የምስክርነት ቃልም ሲታይ 1ኛው ምስክር አመልካች ጸንሰው እያለ በ1996 ዓ/ም በን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ አካባቢ ቤት መስራት ጀምረዋል፣ በ1997 ዓ/ም ቤቱ ተሰርቶ ሳይጠናቀቅ ገብተዋል በማለት ሲመሰክሩ 2ኛው ምስክራቸው ደግሞ በ1997 ዓ/ም የአመልካችና የተጠሪ ቤተሰብ ቅልቅል ተደርጎ በዚያ ዝግጅት ቤት

መገኘታቸውን፣ ቤቱ በተወሰነ መልኩ ያለማለቁን፣ ሆኖም መቼ እንደተጀመረ እና እንደአለቀ የማያውቁ መሆኑን ገልፀው ሲመሰክሩ 3ኛ ምስክር ሁነው አመልካች የሰጡት የምስክርነት ቃል ደግሞ ጋብቻቸውን ናዝሬት ከተማ በ1995 ዓ/ም አድርገው ጥር ወር 1996 ዓ/ም ማርገዛቸውን፣ የካቲት ወር 1997 መውለዳቸውን ከጋብቻ በፊት ተጠሪ በ1994 ዓ/ም የቤቱን መሰሪያ ቦታ በጨረታ እንዳገኘ እንደነገሯቸው፣ ከተጋቡ በኃላ በ1995 ዓ/ም ቁፋሮ እንዳዩና በ1997 ዓ/ም ቤቱ ተሰርቶ ጥቂት ነገር ሲቀር የቤተሰብ ቅልቅል ተደርጎ ቤቱ እንደገቡ፣ ቤት ከተገባ በኂላ እንደተሰራ መመስከራቸውን የሚያሳይ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግለባጭ ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሁለት ምስክሮች ያሰሙ ሲሆን 1ኛው ምስክራቸው ወላጅ አባታቸው መሆኑን ገልፀው በሰጡት የምስክርነት ቃል ጋብቻው በ1997 ዓ/ም እንደተፈጸመ፣ አመልካችና ተጠሪ በሚኖሩበት ቤት አቶ ጫላ በተባለው መሃንዲስ በ1994 ዓ/ም ቤቱን ለማሰራት ውል ተዋውለው መሃንዲሱም በ1996 ዓ/ም መግቢያ ላይ አጠናቅቆ ቤቱን ያስረከባቸው መሆኑን፣ ቤቱንም ልጃቸው የሆኑት ተጠሪ በላውንደሪ ስራ ስለሚያገለግሏቸው በራሱ ገንዘብ ያሰሩለት መሆኑን የመሰከሩ ሲሆን የተጠሪ ሁለተኛው ምስክር ደግሞ ቤቱን የሰሩ መሆናቸውን ገልጸው በሰጡት የምስክርነት ቃል ቤቱን ሰኔ 10 ቀን 1994 ዓ/ም በተደረገ በግንባታ ውል ከተጠሪ አባት ጋር እንዳደረጉ፣ ግንባታውን አንድ አመት ከሁለት ወር ፈጅቶባቸው በ1995 ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ ለተጠሪ አባት ማስረከባቸውንና ቤቱንም ያሰሩት የተጠሪ አባት መሆናቸውን፣ ቤቱ ሲጠናቀቅ አከባቢ አመልካች መጥተው ማየታቸውን፣ ቤቱ ሙሉ በሙሉ አልቆ ያስረከቡ መሆኑን ዘርዝረው መስክረዋል፡፡ በ2ኛው የተጠሪ ምስክርና በተጠሪ ወላጅ አባት መካከል ሰኔ 10 ቀን 1994 ዓ/ም የተረገው የግንባታ ውልም ለማስረጃነት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በሌላ በኩል በአዲስ አበባ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በሊዝ ደንብ ቁጥር3/87 መሰረት የቦታ ቁጥር 4073/93 የግንባታ ስራ ፈቃድ ውል ከተጠሪ ጋር የተደረገ የቦታ ካርታ እና የቦታ አቀማመጥን የሚገልፅ በ01/13/93 ዓ/ም የተዘጋጀ፣ የመኖሪያ ቤት ስራ ለመስራት በቀን 23/01/1994 ዓ/ም የተሰጠ ፈቃድ ለስር ፍርድ ቤት የላከ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጄንሲ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በቁጥር የማ/ን/ም/መ/ኤ 590/2008 በቀን 09/05/2008 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የይዞታ ካርታው በቀን 12/01/94 ዓ/ም እንደተሰጠ፣ የግንባታ ፈቃድ ደግሞ

www.abyssinialaw.com

በ23/01/94 ዓ/ም መሰጠቱንና ስለግንባታው መኖር በ12/10/2000 ዓ/ም የተረጋገጠ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ መግለፁን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ካላይ የተመለከቱትን ሲሆኑ ቀጥሎ መነሳት ያለበት የህግ ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት እነዚህን ፍሬ ነገሮችን ከተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ዳኝነት ሰጥቶቷል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ነው፡፡

በመሠረቱ የተጋቢዎችን ንብረትን ሃብት አስመልክቶ የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 የጋራ ንብረት እና የግል ንብረት የሚመራበትን ስርዓት ይደነግጋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62 /1/ ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኙዋቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ በማለት የደነገገ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብታቸው ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስት ከተጋቤ በኂላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ክርክር የተነሳበት ቤት የተሰራበት ቦታ በሊዝ ውል የተገኘው ከሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም በፊት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ግንባታው የተጀመረውና የተጠናቀቀው የግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ አብረው ባሉበት ወቅት ስለመሆኑ የአመልካች የሰው ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጄንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁጥር የማ/ን/ም/መ/ኤ 590/2008 በቀን 09/05/2008 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳበቤ ከሰጠው መግለጫ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ቃል ሲታይ ግን የሚመለከተው አካል ከሰጠው መግለጫ ጋር አብሮ የማይሄድ በመሆኑ የማስረጃነት ዋጋ ሊሰጠው የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪና አመልካች ከሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም በፊት በፍቅር ግንኙነት ውስጥ የነበሩ መሆኑና አመልካች በግልጽ ጠቅሰው ያቀረቡትን ክርክርም ተጠሪ ማስተባበያ ክርክር ያላቀረቡበት መሆኑን የተገነዘብን በመሆኑ ተጠሪ የመንግስትና የህዝብ ንብረት የሆነውን ይዞታ በሊዝ ውል በስማቸው ወስደው ቆይተው በቦታው ላይ ንብረቱን ያሰፈሩት ከአመልካች ጋር ሕጉ ጥበቃ በሚያደርገው ግንኙት ውስጥ መሆኑ ተረጋግጧል፡፧ ስለሆነም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57፣62 እና

www.abyssinialaw.com

63 ድንጋጌዎች አግባብ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ሊባል የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመጨረሻ የተመለከትነው በእቁቡ ላይ የተሰጠውን ውሳኔን ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲያቀርቡ ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት የጠየቁት በሀሰን ላውንደሪ የንግድ ቤት ውስጥ በአቶ ሰይድ ሙዘይን ዳኝነት በአቶ ኤልያስ ሰይድ ፀሓፊነት የሚጣለውን የእቁብ ገንዘብ ብር 480,000.00 ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ረገድ በቀረበው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ላይ መልስ ሲሰጡ እቁቡ ታህሳስ 29 ቀን 2004 ዓ/ም ደርሶአቸው ለጋራ ትዳር ጥቅም ያዋሉ መሆኑን ከዚህ ውጪ በእቁቡ የሌሉበትና ክሱ ሐሰት መሆኑን ገልፀዋል፡፤ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አመልካች ራሳቸው በሰጡት የምስክርነት ቃል የእቁቡ ገንዘብ ስንት እንደሆነና መቼ እንደወጣላቸው በእርግጠኝነት ያልገለጹ መሆኑንና የእቁቡ ዳኛ እና ፀሐፊዎች ቀርበው እንዲያስረዱ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶላቸውም ትዕዛዙም አድርሰው ምስክሮቹ ቀርበው እንዲያስረዱ ያላደረጉ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ አጥብቀው የሚከረከሩት የእቁቡ ዳኛ እና ፀሓፊ ለምስክርነት እንዲቀርቡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ለማድረስ ጥረት ቢያደርጉም ምስክሮቹ አውቀው እየተደበቁ ስለአስቸገሯቸው ይህንኑ ለስር ፍርድ ቤት በቃለ መሃላ አሳውቀው ምስክሮቹ በሚኖሩበት ወረዳ አስተዳደር በኩል መጥሪያው እዲደርሳቸው ተደርጎ እንዲቀርቡ እንዲደረግላቸው ጠይቀው እያለ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ትዕዛዝ ሳይኖር ምስክሮቹን አመልካች አላስቀረቡም ማለቱ ስህተት ነው በሚል መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ቀርቦም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ማመልከቻ መኖር ያለመኖሩንና የስር ፍርድ ቤት ተገቢው ብይን የሰጠበት ጉዳይ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከትም አመልካች ለምስክሮቹ መጥሪያው በክፍሉ የወረዳው አስረዳደር በኩል እንዲደርሳቸው እንዲታዘዝላቸው መጠየቃቸውንና የሥር ፍ/ቤት በዚህ ጥያቄ ላይ ተገቢውን ትዕዛዝ ሳይሰጥ አልፎ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ ምስክር ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን የሚቀርበው በፍርድ ቤት መጥሪያ ተደርጎለትና ይኼው መጥሪያም ምስክሩን ማስረጃዬ ነው ብሎ የቆጠረው ሰው በስነ

www.abyssinialaw.com

ስርዓት ህጉ ከቁጥር 96 እስከ 102 ድረስ ስለመጥሪያ አደራረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በመከተል መጥሪያውን ለምስክሩ እንዲያደርሰው በማድረግ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 116 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ለአንድ ጉዳይ ለምስክርነት የተቆጠረ ሰው ደግሞ በፍርድ ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ የመመስከር ግዴታ ያለበት ሲሆን ምስክ ሊቀርብ ካልቻለም በሕግ አግባብ ተገዶ የሚቀርብ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከቁጥር 116 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ምስክሩ በጥሪው መሠረት ላለመቅረብ ሆነ ብሎ እየተሰወረ ያስቸገረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ በታየው መንገድ ትዕዛዝ በመስጠት ተጠሪው ምስክር ተገዶ ወይም ታስሮ እንዲቀርብ ማዘዝ እንደሚገባው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 118(2)(ለ) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናይ የሥር ፍርድ ቤት ምስክሮችን ያላስቀረበው በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች እንዲቀርቡ የጠየቋቸው የዕቁብ ዳኛ እና ፀሐፊ ቀርበው መሰማታቸው ክርክሩ ከሚመራበት የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111፣ 249 እና 257 አኳያ እንደዚሁም ከማስረጃ አቀራረብና አቀባበል አኳያ ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ የሥር ፍር ቤት እነዚህን ምስክሮች ሳይሰማ ለዚህ የሠበር አቤቱታ ምክንያት በሆነው የእቁብ ጉዳይ ውሳኔ መስጠቱም ሆነ የፌፌራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ የፍርድ አመራር ጉድለት በይግባኝ ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ /ሣያነጥሩ/ መወሰን ደግሞ የፍርድ አካሄዱን ያልተሟላ የሚያደርግና የተከራካሪ ወገንን የመከራከር መብት የሚያጣብብ፣ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግንተናል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ ከተመለከቱት መረታዊና ህጋዊ ምክንያቶች አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤቶች ክርክር የተነሳበት ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው፣ እቁቡም በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 88409 ሚያዚያ 17 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 182989 መስከረም 13 ቀን 2010 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻው የተመሰረተው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ነው ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር በፍቺው ወሳኔ መሰረት ጋብቻው ሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም ጀምሮ ያለ ነው ብለናል፡፡
3. በን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ የሚገኘውና የቤት ቁጥር አዲስ የሆነው ክርክር የተነሳበት ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ክፍፍሉም በቤተሰብ ሕጉ በተመለከተው አግባብ ሊከናወን ይገባል ብለናል፡፡
4. የእቁብ ገንዘቡን በተመለከተ የተሰጠውን የውሰኔ ክፍል በመሻር የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ክርክሩን በመ/ቁጥር 188409 እንዲቀጥል አድርጎ የእቁቡን ዳኛ እና ጸሃፊ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 118(2)(ለ) አግባብ እንዲቀርቡ አድርጎ ምስክርነታቸውን በመስማትና ተገቢ ነው ካለም በሌላ ማስረጃም ጭምር ከአጣራ በኂላ አግባብነት ካለው የቤተሰብ ህግ ድንጋዎች አንፃር በመመልከት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. በሌሎች የንብረት ክርክሮች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
6. በዚህ ችሎተ ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

### ትእዛዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 12 ቀን 2010ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይፃፍ

**መዝገቡ ተዘግቶአል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ.154727

ህዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡.....1. ተኽሊት ይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡......አቶ ተኽላይ ፍሰሃ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡............ወ/ሮ ለታይ ለገሠ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የጀመረዉ በትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሽሬ እ/ስላሴ ምድብ ችሎት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.98593 በ14/6/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ በሽሬ እ/ስላሴ ከተማ 04 ቀበሌ ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን በ140 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያለዉን ቤት በብር 250 ሺህ ሽጠዉልኝ ገንዘቡን ተቀብለዉ ስመ ሀብቱን ሊያዛዉሩልኝ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ቤትና ቦታዉን ስመ ሀብት እንዲያዛዉሩልኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ቢሰጥም ተከሳሽ መጥሪያ ተቀብለዉ ያለ በቂ ምክንያት መልስ ይዘዉ ሳይቀርቡ በመቅረታቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡ ነገር ግን ተከሳሽ ክስ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ በቃል ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የከፍተኛዉ ፍ/ቤት የከሳሽ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት እና በመሐንዲሶች ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ሁለት ክፍል ማሻሻያ እና ሽንት ቤት ያለበትን ቦታ ለከሳሽ ሸጠዉ ከሳሽ ደግሞ በቦታዉ ላይ ሕንጻ ገንብተዉ ስለሚገኙ የሕንጻዉ ባለቤት ከሳሽ በመሆኑ፣ ቤትና ቦታዉ የከሳሽ በመሆኑ ተከሳሽ ስመ ሀብቱን

www.abyssinialaw.com

ወደ ከሳሽ እንዲያዛዉር በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ጉዳይ በይግባኝ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ26/6/2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበብኝ ክስ ላይ በ15/9/2010 ዓ.ም መልስ እንዲቀርብ ያዘዘ ሲሆን አመልካች በዚህ ቀን በችሎት ፊት ቀርቤ መልሴን በጽሑፍ አዘጋጅቼ ለማቅረብ ጊዜ ስላጠረብኝና ከጠበቃ ጋር ተማክሬ በቀጣይ ቀጠሮ መልስ እንዳቀርብ እንዲታዘዝልኝ የጠየቀኩኝ ሲሆን ፍ/ቤቱ መልሴን እንዳቀርብ ማዘዝ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ የሰጠዉ ዉሳኔ እና የሥር የጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በማጽናት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ተሽሮ የጠየቅኩት ዳኝነት እንዲወሰንልኝ በማለት በዋናዉ ክርክርም በዝርዝር ቅሬታቸዉን አቅርቧል፡፡

ይህ ችሎት ጉዳዩን በማየት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ23/9/2010 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የአሁን ተጠሪ በዋናዉ ጉዳይ ላይ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነዉ የሚሉበትን ምክንያቶች በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ስላላቀረበ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት የአሁን አመልካች በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ መታለፉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ መሰረት የስር የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ሲታይ የአሁን አመልካች የፍ/ቤቱ መጥሪያ ደርሶት ያለ በቂ ምክንያት መልሱን ይዞ እንዳልቀረበ በመግለጽ መልስ የመስጠት መብቱን ማለፉን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ከስር የጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር በፖሊስ በኩል የፍ/ቤትን መጥሪያ ለአመልካች በ8/9/2009 ዓ.ም የሰጠሁት ስለሆነ ለ15/9/2009 ዓ'ም

መልሱን ይዞ ለመቅረብ በቂ ጊዜ እንደነበረዉ ገለጾ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በ10/9/2009 ዓ'ም መጥሪያ ቢመጣለትም አንብቡልኝ ብላቸዉ ሊያነቡልኝ ፈቃደኛ አልሆኑም፤ አመልካች በ13/9/2009 ዓ'ም ፍ/ቤት ቀርቦ በመታመሜ ምክንያት መልስ ለማዘጋጀት አልቻልኩም ስለዚህ ከባለሙያ ተማክሬ መልሴን እንዳቀርብ ብሎ እንዳመለከቱ፤ አመልካች መጥሪያዉን ቢቀበል ኖሮ ለ15/9/2009 ዓ'ም መልስ አዘጋጅቶ ለመቅረብ እንደሚችል በመግለጽ መታለፉ ተገቢ መሆኑን በመግለጽ የስር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ስለዚህ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር እንኳን ቢሆን አመልካች መልሱን ይዞ እንዲቀርብ እየተደረገ ያለዉ በስምንት ቀናት ዉስጥ እንደሆነ እና አመልካች ከባለሙያ ተማክሮ መልሱን ለማቅረብ ጊዜ እንዳልበቃዉ በመግለጽ ፍ/ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጠዉ እንዳመለከተ ማየት ይቻላል፡፡ አመልካች የቀረበበትን ክስና ማስረጃ በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለዉን መልስ ለማቅረብ ከተሰጠዉ ቀጠሮ ከ10 ቀን በፊት ሊደርሰዉ እንደሚገባዉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.240 [2] ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካች መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘዉ እና ቀጠሮ የተሰጠዉ ከ10 ቀን ባነሰ ጊዜ ዉስጥ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ አመልካች በሕግ በተመለከተ ጊዜ ዉስጥ ተገቢዉን ዝግጅት በማድረግ መልሱን አዘጋጅቶ እንዲቀርብ የሚያስችለዉ ጊዜ ሆኖ አይገኝም፡፡ ይህ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት የተጠበቀዉን መብት የሚነፍግ ነዉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች በሕጉ አግባብ ተገቢዉን የመከላከያ መልሱን እንዲያቀርብና ሙሉ ክርክሩን እንዲያቀርብ ማድረግ ሲገባቸዉ የመከላከልና የመከራከር መብቱን በመንፈግ ዉሳኔ መስጠታቸዉን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች የመከላከያ መልሱን ሳያቀርብ እና ክርክሩን አቅርቦ ሳይሰማ የሰጡት ዉሳኔ የመከላከልና የመከራከር የመሰማት መብቱን የነፈገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ምክንያት የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. በትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.24388 በ11/12/2009 ዓ'ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የትግራይ

www.abyssinialaw.com

ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ.98593 በ14/6/2010 ዓ'ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ መሰረት የአሁን አመልካች የመከላከያ መልሱን እና ክርክሩን እንዲያቀርብ በማድረግ፤ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር፤ ጉዳዩን በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ' 343 [1] መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. ይህ ዉሳኔ ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ'ም ተነብቧል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጕ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.119851

መጋቢት 26 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካቾች - 1ኛ. ወ/ሮ ሶፊያ መሐመድ

2ኛ. አቶ አህመድ መሐመድ

3ኛ. ወ/ሮ ዘብይዳ መሐመድ

ተጠሪ - አቶ እንድሪስ ጋሹ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

1. ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ከሟቾች ሐጂ መሐመድ ሰይድ እና ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ (የአሁን አመልካቾች ወላጆች) ጋር ሚያዚያ 21 ቀን 1974 ዓ.ም በተፃፈ የቤት ሽያጭ ውል በቀድሞው ወረዳ 24 ቀበሌ 09 የቤ/ቁጥር 312 የሆነ ቤት በብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) ገዝተው በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ምክንያት ስም እንዲዛወርላቸው በተዋዋዩቹ ላይ ነሃሴ 23/1983 ዓ.ም ክስ መስርተው በክልል 14 መስተዳደር ወረዳ 24 ፍርድ ቤት በትዕዛዝ መ/ቁ 742/83 ታህሳስ 25/1986 ዓ.ም ስም እንዲዛወር ውሳኔ ተሰጥቷል፤ ይህን ውሳኔ ለማስፈፀም በቀድሞ ተከሳሾች ወራሾች (የአሁን አመልካቾች) ላይ አቤቱታ አቅርበው በፍ/ብ/መ/ቁ 1422 በ15/03/97 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ሊፈጸም የማይችል ውሳኔ ነው ተብሎ መዝገቡ መዘጋቷል፤ ስለሆነም ተከሳሾች የሻጮች ወራሾች ስለሆኑ ቤቱን እና ለስም ማዛወር የሚጠቅሙ የቤቱን ሰነዶች እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
2. አመልካቾች ለክሱ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 መሰረት

ውድቅ እንዲደረግ፣ ውሉን መሰረት በማድረግ በሚቾች ላይ መስርተውት በነበረው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 217(3) እና 218 ሁሉንም ጥያቄ አጣምረው ሊያቀርቡ ይገባ ነበር፣ እንዲሁም ጉዳዩ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ እና በፍ/ብ/ህ/ቁ 2892(3) መሰረት በአንድ ዓመት ይርጋ የታገደ ነው እንዲባል ጠይቀዋል፡፡ በፍሬ ጉዳዩም በሰጡት መልስ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 12(1) ላይ በግልጽ እንደሰፈረው የከተማ ቤት በሽያጭ የሚተላለፍ ከሆነ መንግስት የግዥ ቀዳሚነት መብት አለው፣ ይህም በመሆኑ በ1974 ዓ.ም የሚደረግ የቤት ሽያጭ ፍጹም አልነበረም፣ ከሳሽ ውልን አደረኩ ባሉበት ጊዜ አውራሻችን በሚኒስቴሩ የፀደቀ ንብረት የላቸውም፣ በዚህም መሰረት የተከሳሾች አውራሽ ንብረቱን ለማስተላለፍ መብት አልነበራቸውም፣ ስለሆነም ውሉ ሐሰተኛ ወይም ህገወጥ ነው፣ በአጠቃላይ የቀረበው ክስ በህጉ አግባብ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ይሁንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

3. ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት በአመልካቾች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ዝርዝር ክርክር ውድቅ በማድረግ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እና ሰነዶችን እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡ አመልካቾች መቃወሚያዎቹ መታለፋቸውን እና በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ጉዳዩን በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ ተገቢ መሆኑን፣ ነገር ግን ፍሬ ጉዳዩ ባግባቡ ተጣርቶ አለመወሰኑን በመጥቀስ በድጋሚ አጣርቶ እንዲወስን ወደ ስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መልሷል፡፡
4. በዚህ መልኩ የተመለሰለት የሥር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን ተመልክቶ የቀደመ ውሳኔውን በድጋሚ አሳልፏል፡፡
5. ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካቾች መቃወሚያዎቹ የታለፉት አላግባብ መሆኑን እና በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም መቃወሚያዎችን በተመለከተ አስቀድሞ ውሳኔ የሰጠባቸው በመሆኑ በጊዜው ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊጠይቁባቸው ይገባ እንደነበር፣ በፍሬ ጉዳዩ ተጣርቶ የተሰጠው ውሳኔም ግድፈት እንደሌለበት ወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

6. የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ህዳር 8/2008 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ መቃወሚያዎቹ በመታለፋቸውም ሆነ በፍሬ ጉዳዩ ተፈፀሙ የሚሏቸውን የህግ ስህተቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡
7. አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አከራካሪው ቤት በአመልካቾች እጅ ስለመኖሩ ባልተካደበት የቤት ሽያጭ ገንዘቡም አልተከፈለም ተብሎ ቀደም ሲል በመ/ቁ 742/83 በተሰጠ ፍርድ ላይ በተመለከተበት እና በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 1422 ስመሃብት ይዛወር ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሊፈፀም የማይችል ነው ተብሎ አፈፃፀሙ በተዘጋበት የስር ፍርድ ቤቶች ክሱን ዳግም በ2004 ዓ.ም በተከፈተ መዝገብ አስተናግደው የቤት ሽያጭ ውሉ ህጋዊ ስለሆነ አመልካቾች ቤቱን እና ኦሪጅናል ካርታውን ለተጠሪ ያስረክቡ በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡
8. ተጠሪ በሰጡት መልስ በቅድሚያ የሰበር አቤቱታውን አቀራረብ በተመለከተ መቃወሚያዎችን አቅርበዋል፡፡ የመቃወሚያው ይዘት አመልካቾች ለሰበር አቤቱታ መነሻ ያደረጉት ቀደም ሲል የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ 126113 በ26/06/2005 ዓ.ም ክርክር አድርጎ ውሳኔ የሰጠባቸው ነጥቦች ላይ ማለትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 መሰረት የቀረበውን መቃወሚያ፤ የይርጋ ክርክሩን፤ የሽያጩን ገንዘብ ክፍያ እንዲሁም በህግ የታወቀ መብት እና የሥም ዝውውር ጥያቄን በተመለከተ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አግባብ በወቅቱ ይግባኝ አልተባለበትም (የሰበር አቤቱታ አልቀረበበትም) ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ይህ ከታለፈም በጉዳዩ ላይ ፍርድ የተሰጠው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 23018 በ22/09/04 ዓ.ም እና በከፍተኛው ፍርድ ቤት በ26/06/2005 ስለሆነ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት ነው ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ ብለዋል፡፡ በፍሬ ጉዳዩም ዝርዝር መልሳቸውንም አቅርበዋል፡፡
9. አመልካቾች ባቀረቡት የመልስ መልስ ቅሬታቸውን በማጠናከር ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ስልጣን አንፃር በተለይም የህግ ድንጋጌዎችን ወጥነት ባለው መልኩ እንዲተረጎሙ ከማድረግ አኳያ የህግ ጥያቄዎች ለችሎቱ መቅረባቸው የሚነቀፍበት ምክንያት ሊኖር እንደማይገባ በመግለፅ በሰበር አቤቱታው አቀራረብ ላይ የተነሳው

መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም እንዲባል ጠይቀዋል፡፡ በሌሎች ነጥቦች ላይም የሥር ክርክራቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

10. የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ተጠሪ የሰበር አቤቱታው አቀራረብ በተመለከተ ያነሱት መቃወሚያ ይህ ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የሰጣቸውን አስገዳጅ ትርጉሞች መሰረት በማድረግ የቀረበ በመሆኑ ከዚህ አንፃር ሰበር ችሎቱ አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳዮች ያሳለፋቸው ገዥ ትርጉሞች በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት በድጋሚ ሊታዩ የሚገባ መሆን አለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

11. ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካቾች ለሰበር አቤቱታ መነሻ ያደረጉት ቀደም ሲል የከፍተኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ ፍሬ ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደስር ፍርድ ቤት ሲመልስ በመቃወሚያዎቹ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቶበት የነበረ በመሆኑ በመቃወሚያዎቹ ላይ በዚህ መልኩ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በወቅቱ የሰበር አቤቱታ አልቀረበበትም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ስልጣን አንፃር የህግ ጥያቄዎች ለችሎቱ መቅረባቸው የሚነቀፍበት ምክንያት ሊኖር እንደማይገባ በመግለፅ መከራከሪያው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

12. ስለሆነም ውሳኔ የሚሻው ጉዳይ በእንዲህ አይነቱ ክርክር በመቃወሚያው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ መነሻ ያደረገ የሰበር ቅሬታ መቅረብ ያለበት መቼ ነው? የሚለው ነው፡፡ ይህም ማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመቃወሚያው ላይ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ/የሰበር አቤቱታ ለበላይ ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ ወደታች ፍርድ ቤት የተመለሰውንና በፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት የተመለሰውን ክርክር ውጤት መጠበቅና የተጠቃለለ ቅሬታ ማቅረብ ይገባል? ወይስ ወደስር ፍርድ ቤት የተመለሰው ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚሰጠውን ውሳኔ መጠበቅ ሳያስፈልግ በመቃወሚያው ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ያለውን ቅሬታ ወዲያውኑ/በቀጥታ ማቅረብ ይገባል? የሚለው ነው፡፡

13. ይህንኑ ነጥብ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስቀድሞ ከተያዘው አቋም እና ከተሰጠው ትርጉም፣ ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ አላማና ከሰበር ችሎት

www.abyssinialaw.com

ኃላፊነት፣ እንዲሁም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ የክርክር አመራር እና የቅሬታ አቀራረብ መሰረታዊ መርሆዎች አንፃር መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

14. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ አስቀድሞ በሰጠው ትርጉም ለክሱ በሚቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ በይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔን በመቃወም የሰበር አቤቱታ መቅረብ የሚገባው ወዲያውኑ ማለትም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በህግ በተደነገገው የሰበር ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ ከሚሆን በቀር በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ሥር ፍርድ ቤት በመለሰው ክርክር ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ውጤት ጠብቆ የሚቀርብበት ህጋዊ ምክንያት እንደሌለ፣ ስርዓቱን ጠብቆ በጊዜው የይግባኝ (ሰበር) ክርክሩን መቀጠል ሲገባ በዚህ መልኩ አቤቱታ የማቅረብ መብታቸውን በራሳቸው ጊዜ በመተው ወደስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተመልሶ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያው ላይ አስቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ ላይ አጠቃለው የሚያቀርቡት አቤቱታ የህግ መሰረት እንደሌለው በሰ/መ/ቁ 90810 ፣ 76963፣ 125165 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

15. ለዚህ መደምደሚያ እና ትርጉም መሰረት የተደረገው ከመቃወሚያው ጋር በተያያዘ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 320(3) መሰረት ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ብይን/ትዕዛዝ ነው የሚባል አይደለም፣ እንዲሁም በዚህ መልኩ በበላይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጠው ውሳኔ በህግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በበላይ ፍርድ ቤት እስካልተለወጠ ድረስ በግራቀኙ ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ በአጠቃላይ የሰበር ችሎቱ የቀደመ አቋም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ወደ ስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገሩ ረገድ ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት የተላከውን ጉዳይ ውጤት ሳይጠብቅ በመቃወሚያው ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሰበር ቅሬታውን/ይግባኙን ማቅረብ ይኖርበታል፣ ይህን ሳያደርግ ከቀረ የፍሬ ነገር ክርክሩን ውጤት ጠብቆ መጀመሪያ ያልተጠቀመበትን የሰበር አቤቱታ/ይግባኝ የማቅረብ መብት እንደገና በማንሳት ሊጠቀምበት አይችልም የሚል ነው፡፡ ይህ ትርጉም የሰበርን አላማ ከግንዛቤ ባስገባ መልኩ በጥንቃቄ ሊታይ ይገባል፡፡

www.abyssinialaw.com

16. በመሰረቱ የሰበር ስርዓት የመዘርጋት አላማ በአንድ ሀገር ውስጥ ወጥ የሆነ የህግ አተረጎጎም እና አፈጻጸም መኖሩን በማረጋገጥ የህግ የበላይነትን ማስፈን ነው፡፡ ይህን ማድረግ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ ሊቆይ የማይችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ጸንቶ እንዲቆይ ማድረግ ህብረተሰቡ በዳኝነት አካሉ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ በመሆኑ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዲቆይ መፍቀድ በዳኝነት አካሉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡ በመሆኑም የሰበር ሥርአቱ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዳይቆይ በማድረግ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ እና የዳኝነት አካሉ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚታመን እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
17. በዚህ መሰረታዊ ምክንያት ህገ-መንግስቱ የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሆኑንና ፍርድ ቤቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም "የመጨረሻ ውሳኔ" ለማረም የሰበር ችሎቱ ስልጣን ያለው መሆኑን በአንቀጽ 80(3(ሀ)) ስር ደንግጓል፡፡ በተለይ አዋጅ ቁጥር 454/1997 ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጥ የህግ ትርጉም ይኸው ችሎት ራሱ በሌላ ጊዜ እስካልለወጠው ድረስ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅ ስለመሆኑ በአንቀፅ 2(4) ስር ደንግጓል፡፡ ይህም የሰበር ስርዓት በዳኝነት ስልጣን ተዋረድ በመጨረሻ እርከን ላይ ሆኖ ህጎች በትክክልና በወጥነት መተርጎማቸውንና መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሲሆን በውጤቱም ሰበር ህጋዊ ያልሆኑ ውሳኔዎች ጸንተው እንዳይቆዩ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡
18. ከዚህም ሌላ ሰበር መደበኛ የይግባኝ ማቅረቢያ አሰራር ሳይሆን ፍርድ ቤቶች በመጨረሻ ውሳኔዎቻቸው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈጽመዋል በሚባልበት ልዩ ሁኔታ ብቻ የህጉ አተረጓጎም ወይም አተገባበር የሚቃናበት ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በተሳሳተ መልኩ የሰጧቸውን ውሳኔዎች ሰበር ችሎቱ ሊያስተካክል የሚችልበት ወይም በማናቸውም ሁኔታ ስህተት የተፈፀመባቸው ውሳኔዎች ቀሪ ሊሆኑ የሚችሉበት መንገድ እንዲጠብ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡
19. በሌላም በኩል ከፍሲል እንደተገለፀው የሰበር ችሎቱ የተቋቋመው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም "የመጨረሻ ውሳኔ" ለማረም ነው፡፡ በእኛችን

ካለው ጉዳይ ጋር በተያያዘ በክርክሩ ላይ “የመጨረሻ ውሳኔ” ተሰጥቷል ሊባል የሚችለው መቼ ነው? የሚለው በአግባቡ ሊታይ ይገባል፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 ንዑስ ቁጥር (1) እና (2) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የወሰነው የበታች ፍርድ ቤት ጠቃሚ የሆነውን ጭብጥ ሳይዝ ወይም ጉዳዩን ሳይመረምርና ሳይረዳ ያለፈው መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካረጋገጠ የተዘለሉለትን ጭብጦችና ፍሬ ነገሮች ለይቶ እንደገና እንዲመረምርና እንዲያጣራው ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሶ ይልክለታል፤ በዚህ መልኩ እንደገና እንዲያይ የተላከለት ፍርድ ቤትም በትዕዛዙ መሰረት ዳኝነቱን ካየ በኃላ ያጣራውን ነገር ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መልሶ ይልካል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከድንጋጌው መገንዘብ እንደሚቻለው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 መሰረት ጉዳዩ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ የሚላከው ተጣርቶ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንዲመለስ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተዘለሉለትን ጭብጦችና ፍሬ ነገሮች ለይቶ እንደገና እንዲመረምርና እንዲያጣራው ሲመልስ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል የሚባልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ የመጨረሻ ውሳኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ ደግሞ የሰበር አቤቱታ እንዲቀርብ ማድረግ ከፍሲል የጠቀስናቸውን የህጉን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

20. ከዚህም ሌላ መቃወሚያውን መሰረት ያደረገ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የሚኖረው ቅሬታ ተከራካሪው ወገን ወደስር ፍርድ ቤት በተመለሰው ክርክር አሸናፊ ከሆነ ቀሪ ሊሆን የሚችልበት እድል በመኖሩ ስህተቱ ሊታረም የሚገባው ወዲያውኑ በሚቀርብ የሰበር አቤቱታ ብቻ ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡

21. በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት በመቃወሚያው ላይ የሰጠውን ብይን በማጽናት ነገር ግን በፍሬ ነገሩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ሲመልስ በመቃወሚያው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት የሰበር/ይግባኝ ቅሬታ ወዲያውኑ ካልቀረበ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የተባለበት አግባብ በአንድ በኩል በስረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሰበር ችሎቱ ተያያዥነት ያላቸውንና ተጠቃለው ቢቀርቡ

በአንድ መዝገብ ውሳኔ ሊያገኙ የሚችሉ ጉዳዮችን በተነጣጠለ መልኩ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ያደርጋል፡፡ ይህም በተከራካሪዎች ላይ ተጨማሪ እንግልትና ወጪን እንዲሁም በችሎቱ ላይ አላስፈላጊ የሥራ ጫናን የሚፈጥር ነው፡፡ በተለይ እንዲህ አይነት ክርክሮች ከክልል ፍርድ ቤቶች የሚነሱ ሲሆን ተከራካሪዎች በአንድ መዝገብ በተነሱ ክርክሮች ሁለት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት መመላለስ እንዲኖርባቸው የሚያድርግ ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን ወደስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መመለሱን ተቀብለው የጉዳዩን መጠናቀቅ በቅን ልቦና ሲጠባበቁ በመቃወሚያው ላይ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተትን ወዲያውኑ አላቀረባችሁም በሚል በሰበር ለማሳረም እንዳይችሉ የተደረጉት ባለጉዳዩች በርካቶች መሆናቸውንና በዚህ ምክንያት ፍትህ መጓደሉን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አስቀድሞ በሰበር ችሎቱ የተያዘው አቋም የሥነ ሥርዓት ህጉን መንፈስ በተለይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 እና 320 ድንጋጌዎችን ይዘት እና የሰበር ስርዓቱን አላማ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

22. በእነዚህ ምክንያቶች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ሥር ፍርድ ቤት በመለሰው ክርክር ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ውጤት ጠብቆ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያውም ሆነ በፍሬ ነገሩ ላይ የተጠቃለለ የሰበር አቤቱታ መቅረቡ ህጉን የተከተለ ከመሆኑም በላይ በአንድ ጉዳይ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በተበታተነ ሁኔታ ክርክር እንዳይካሄድ የሚያደርግ፤ የተከራካሪዎችን መብት በተሻለ የሚያስከብር እና የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ፀንቶ እንዳይቀር የሚያደርግ በመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው ትርጉም ሊለወጥ ይገባል ብለናል፡፡

23. ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት ቀደም ሲል በዚህ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 90810 ፣ 76963፣ 125165 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት ተሰጥቶ የነበረውን ትርጉም ለውጠናል፡፡ ይኸውም ፡- ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 መሰረት ወደስር ፍርድ ቤት በተመለሰበት ሁኔታ ለክሱ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔን በመቃወም የሰበር አቤቱታ መቅረብ የሚገባው ወዲያውኑ ማለትም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በህግ በተደነገገው የሰበር

ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ ከሚሆን በቀር በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ሥር ፍርድ ቤት በመለሰው ክርክር ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ውጤት ጠብቆ ተጠቃሎ የሚቀርብበት ምክንያት የለም ተብሎ የተሰጠው ትርጉም ተለውጧል። ወደስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተመልሶ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ በመቃወሚያው ላይ አስቀድሞ በተሰጠው ብይን ላይ ተጠቃሎ የሚያቀርበው አቤቱታ ህጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሊባል አይገባም ብለናል።

24. በተያዘውም ጉዳይ አመልካቾች ለክሱ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ በመደረጉ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ በወቅቱ የሰበር አቤቱታ አልቀረበበትም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ በተጠሪ በኩል የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም ብለናል።

25. ከፍሲል እንደተገለፀው ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ከአመልካቾች ወላጆች ጋር ሚያዚያ 21 ቀን 1974 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል አከራካሪውን ቤት ገዝተው በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ምክንያት ስም እንዲዛወርላቸው ክስ መስርተው በትዕዛዝ መ/ቁ 742/83 ታህሳስ 25/1986 ዓ.ም ስም እንዲዛወር ውሳኔ አሰጥተው እንደነበር፤ ይህን ውሳኔ ለማስፈፀም አቤቱታ አቅርበው በፍ/ብ/መ/ቁ 1422 በ15/03/97 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ሊፈጸም የማይችል ውሳኔ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉን በመጥቀስ አመልካቾች የተዋዋዮች (የሻጮች) ወራሾች ስለሆኑ ቤቱን እና ለስም ማዛወር የሚጠቅሙ የቤቱን ሰነዶች እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል። አመልካቾች በበኩላቸው ለክሱ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ፤ ውሉን መሰረት በማድረግ በሟቾች ላይ መስርተውት በነበረው ክስ ሁሉንም ጥያቄ አጣምረው ሊያቀርቡ ይገባ ነበር፤ እንዲሁም ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው እንዲባል የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም በህጉ አግባብ የተደረገ ውል ባለመኖሩ ቤቱንም ሆነ ሰነዶችን ልናስረክብ አይገባም የሚሉበትን መከራከሪያ በማንሳት ተከራክረዋል።

26. በበኩላችን አመልካቾች ካቀረቧቸው መቃወሚያዎች መካከል ለክሱ መቅረብ ምክንያት የሆኑት ነገሮች ላይ ሁሉ በሙሉ ተጠቃሎ መቅረብ ይገባው ነበር በሚል የቀረበውን ክርክር መርምረናል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216(2) እንደተደነገገው ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በሙሉ በክሱ ማመልከቻ ላይ

www.abyssinialaw.com

አጠቃሎ ማቅረብ እንደሚገባው የሚደነግግ ሲሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216(3) ደግሞ ከሳሹ ሊከስበት ሲችል ሆነብሎ በመቀነስ ባስቀረው ነገር እንደገና ሌላ ክስ ለማቅረብ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ተጣምረው ስለሚቀርቡ ክሶችም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 218 ሥር ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑት ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ማቅረብ ሲችል ቀንሶ ባስቀረው ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል ከድንጋጌዎቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡

27. በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ የሽያጭ ውል ነው ያሉትን መሰረት በማድረግ የቤቱ ስም እንዲዛወርላቸው ክስ መስርተው በትዕዛዝ መ/ቁ 742/83 ታህሳስ 25/1986 ዓ.ም ስም እንዲዛወር ውሳኔ አሰጥተው ነበር፡፡ በሌላ በኩል ለአሁኑ ክርክር ምክንያት የሆነውን ክስ በማቅረብ አመልካቾች የተዋዋዮች (የሻጮች) ወራሾች ስለሆኑ ቤቱን እና ለስም ማዛወር የሚጠቅሙ የቤቱን ሰነዶች እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት መጠየቃቸውን ተገንዝበናል፡፡ በሁለቱም ክስ የዳኝነት ጥያቄ የቀረበው ውሉን መሰረት በማድረግ እንደውሉ ተፈጽሞ ስመሃብቱ እንዲዞርና ቤቱንና የቤቱን ሰነዶች ለመረከብ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የቀደመው ውሳኔ በአፈጻፀም ውድቅ ሲደረግባቸው እንደገና በሁለተኛው ክስ ያቀረቡት ጥያቄ በመጀመሪያው ክስ ተጠቃሎ ሊጠየቅ የሚገባው ነበር፡፡ በመጀመሪያው ክስ አጠቃለው ሊያቀርቡት ሲገባ ሁለተኛ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 አንጻር የማይቻል በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የክስ መቃወሚያ ተቀብለው ክሱን ውድቅ ሊያደርጉት ሲገባ ይህን አልፈው ፍሬ ጉዳዩን በመመልከት አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እና ሰነዶችን እንዲያስረክቡ በማለት ያሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በዚህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 90810 ፣ 76963፣ 125165 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ስር ፍርድ ቤት የተመለሰው ፍሬ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት በመቃወሚያዎቹ ላይ በተሰጠ ውሳኔ የሰበር አቤቱታ ወዲያውኑ ካልቀረበ የፍሬ ጉዳዩን የመጨረሻ ውሳኔ ጠብቆ የሚቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም ተብሎ የተሰጠው አስገዳጅ ትርጉም የሰበር ችሎቱ

www.abyssinialaw.com

የተቋቋመበትን ዓላማ ዳር የሚያደርስ ሆኖ ስላላገኘነውና ህጉንም መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው ይህ ትርጉም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(4) መሰረት ተለውጧል፡፡ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ገዥ ይሆናል ብለናል፡፡

2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 መሰረት ጉዳዩ ወደስር ፍርድ ቤት ተመልሶ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያው ላይ አስቀድሞ በተሰጠው ብይን ላይ ተጠቃሎ የሚያቀርበው የሰበር አቤቱታ ህጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሊባል አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በመጀመሪያው ክስ አጠቃለው ሊያቀርቡት ሲገባ ሁለተኛ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 አንጻር የማይቻል በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የክስ መቃወሚያ ተቀብለው ክሱን ውድቅ ሊያደርጉት ሲገባ ይህን አልፈው ፍሬ ጉዳዩን በመመልከት አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እና ሰነዶችን እንዲያስረክቡ ያሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 23018 ሚያዚያ 29/2006 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 153710 ጥቅምት 15 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡
4. ከሥር ፍርድ ቤቶች የተላኩት መዛግብት በመጡበት አግባብ ይመለሱ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ግራቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠ የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የስድስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

## <u>የልዩነት ሀሳብ</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር አምስት ላይ የተጠቀሰዉ ዳኛ የአብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በሚከተሉት ምክንያቶች በመለየት የልዩነት ሀሳብ አስቀምጫለሁ፡፡

www.abyssinialaw.com

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በክልል 14 መስተዳደር ወረዳ 24 ፍርድ ቤት በመ.ቁ.742/83 ታህሳስ 25 ቀን 1986 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በአሁን ተጠሪ (ከሳሽ) እና በሟቾች ሐጂ መሐመድ ሰይድ እና ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ (ተከሳሾች) መካከል ሚያዚያ 21 ቀን 1974 ዓ.ም በተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 09 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 312 ሆነዉ ስመ ሀብቱ ወደ ከሳሽ እንዲዛወር በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ ይህ ዉሳኔ እንዲፈጸምላቸዉ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡት ቢሆንም በመ.ቁ.1422 በ15/3/1997 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ ዉሳኔዉ ሊፈጸም አይችልም ተብሎ ተወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን ተጠሪ (የሥር ከሳሽ) በአሁን አመልካቾች (በሥር ተከሳሾች) ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ተከሳሾች በቤት ሽያጭ ዉሉ መሰረት ቤቱን እና ቤቱን የሚመለከቱትን ሰነዶች እንዲያስረክቡኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካቾች (የሥር ተከሳሾች) በዚህ ክስ ላይ በሰጡት መልስ ይህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ታይቶ ዉሳኔ ያገኘ በመሆኑ አሁን የቀረበዉ ክስ ድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፤ ከሳሽ ከዚህ ቀደም ክስ ሲያቀርቡ ጉዳያቸዉን በአንድ ላይ አጠቃልሎ ማቅረብ ሲገባቸዉ በመከፋፈል አሁን ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም፤ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በማንሳት የተከራከሩ ሲሆን፤ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ክርክራቸዉን አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካቾች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ዉድቅ በማደረግ፤ በፍሬ ጉዳይ አመልካቾቹ ቤቱን እና ቤቱን የሚመለከቱትን ሰነዶች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ዉድቅ በማድረግ የሰጠ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ በማለት በማጽናት፤ ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ ግን በአግባቡ ተጣርቶ ዉሳኔ የተሰጠበት ባለመሆኑ ጉዳዩን ድጋሚ ተጣርቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ለሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ ዉሳኔ መሰረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ የግራ ቀኛቸዉን በማከራከርና በማጣራት የቀደመዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መታለፋቸዉ ተገቢ እንዳልሆነ በመግለጽ እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ የተሰጠዉንም ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን፤ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ስለመታለፋቸዉ የቀረበዉን ቅሬታ በተመለከተ ይህ ፍ/ቤት አስቀድሞ ዉሳኔ የሰጠባቸዉ በመሆኑ በጊዜዉ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሊጠይቁባቸዉ ሲገባቸዉ አሁን ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፤ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ ሲታይ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ ግድፈት የለዉም በማለት በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ያነሷቸዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ማለፋቸዉ ተገቢ አይደለም እና በዋናዉ ጉዳይ ዝርዝር ቅሬታቸዉን በማቅረብ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡ ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ የአሁን አመልካቾች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በተመለከተ የተሰጠዉን ዉሳኔ አሁን ለዚህ ችሎት ቅሬታ ሊያቀርቡ እንደማይችሉ እና በዋናዉ ጉዳይም የሥር ፍ/ቤት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ እኔ ይህ ጉዳይ በሚከተለዉ አግባብ መታየት አለበት ብዬ የልዩነት ሀሳቤን አስቀምጣለሁ፡፡

**ሀ. አስገዳጅ ሕግ ትርጉም የሚለወጥበት አግባብ በተመለከተ፡**

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ የሆኑትን ጉዳዮች በተመለከተ በሰ.መ.ቁ.90810፣ 76963፣ 125165 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ አስቀድሞ በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ተከትሎ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ በመሆኑ ዉሳኔዉን በመቃወም የሰበር አቤቱታ መቅረብ የሚገባዉ ዉሳኔዉ ከተሰጠ ቀን ጀምሮ

www.abyssinialaw.com

በሕጉ በተቀመጠ የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ ገደብ ዉስጥ መሆን አለበት እንጂ በፍሬ ጉዳይ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰዉን ዉሳኔ ዉጤት ጠብቆ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንደማይቻል ዉሳኔ ሰጥቶበታል። በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥራቸዉን ሲያከናዉኑ መቆየታቸዉ ግልጽ ነዉ። በመሆኑም በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በርካታ ባለጉዳዮች ባለመብት ሆነዉ ሌሎች ደግሞ በክርክሩ መሸነፋቸዉ የማይካድ ሀቅ ነዉ። እንግዲህ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ ይህ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መለወጥ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ።

እንደሚታወቀዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (4) መሰረት ፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠዉ የህግ ትርጉም በየትኛዉም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል። ሆኖም የሰበር ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፣ በማለት ደንግጎታል። ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት አምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ የሚሰጡት የህግ ትርጉም በማናቸዉም ፍ/ቤት ላይ የአስገዳጅነት ዉጤት እንዳለዉ፣ ሕግ እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን፣ ችሎቱ ግን በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ የቀደመዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መለወጥ እንደሚችል ነዉ። ችሎቱ በዚህ ድንጋጌ አግባብ የዳኝነት ሥራዉን እያከናወነ የሚገኝ ቢሆንም አስገዳጅ የህግ ትርጉም ማለት ምን ማለት እንደሆነ? እና ይህ ትርጉም ደግሞ የሚለወጥበት አግባብ ግልጽ የሚያደርግ ዝርዝር መመሪያ ቢዘጋጅለት ተገቢ መስሎ ይታየኛል። ምክንያቱም ችሎቱ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ከሰጠ በኋላ እና ፍ/ቤቶች በዚህ አግባብ የዳኝነት ሥራቸዉን እያከናወኑ እና ባለጉዳዮች ደግሞ ክርክራቸዉን እያቀረቡ ባሉበት ሁኔታ በቀላሉ ተነስቶ ይህን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚለዉጥ ከሆነ ወጥነት ያለዉ የህግ ትርጉም ከመስጠት አንጻር አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረዉ መገመት አያዳግትም። ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የህግ ድንጋጌ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚለወጥበት አግባብ በግልጽ ባይመለከትም በወቅቱ የነበሩት የማህበራዊ ሁኔታዎች መለወጥ፣ ወይም የሕጉ አካባቢያዊ ሁኔታ ሲለወጥ፣ የቀደመዉ ዉሳኔ ከወቅታዊ ፖሊሲዎች ጋር የሚጣጠሙትን ዉሳኔዎች ማመንጨት ሲያቅተዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መለወጥ

www.abyssinialaw.com

አስፈላጊ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ይህ ችሎት የቀደመዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ባጠቃላይ ካለዉ ነበራዊ ሁኔታ ወይም እዉነታ ጋር የማይሄድ መሆኑን የተገነዘበ እንደሆነ ይህን የህግ ትርጉም መለወጥ ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የቀረበለትን ቅሬታ ተከትሎ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ የሰጠ እና ዋናዉን ጉዳይ ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰ እንደሆነ፣ ፍ/ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ተከራካሪ ወገን ዉሳኔዉ እንደተሰጠ የሰበር አቤቱታ በሕጉ በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ማቅረብ እንዳለበት አስዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ፣ አሁን ባለዉ ሁኔታ ይህን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመለወጥ የሚያስችል የተለወጠ ማህበራዊ ሁኔታ፣ የሕጉ አካባቢያዊ ሁኔታ መለወጥ ወይም ወቅታዊ የፖሊሲ ሁኔታ መለወጥ፣ እንዲሁም ባጠቃላይ ያለዉ ነበራዊ ሁኔታ መለወጥን የሚያሳይ ነገር የለም፡፡ ስለሆነም ይህ ችሎት በዚህ ጉዳይ አስቀድመዉ የተሰጡትን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመለወጥ የሚያስችለዉ በቂ ምክንያት የለም፡፡

**ለ. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ስለመሆኑ፡**

እንደሚታወቀዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ.244 (2) ሥር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ተዘርዝረዉ እናገኛለን፡፡ ፍ/ቤት ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት ከተከራካሪ ወገን የቀረበለትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ መስጠት እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 (1) ሥር ተመልክቷል፡፡ አንድን ክርክር ተቀብሎ እያየ ያለዉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ አግባብ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ፣ ተከራካሪ ወገኖችን በዋናዉ ጉዳይ ማከራከርና ማጣራት የቀጠለ እንደሆነ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 (3) መሰረት በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማቅረብ እንደማይቻል እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጥ አንድ ላይ አጠቃልሎ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በተሰጠዉን ዉሳኔ ላይ ቅሬታዉን ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

ነገር ግን አንድን ጉዳይ መጀመሪያ ያየዉ ፍ/ቤት የቀረበለትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ያደረገ እና ከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበ እንደሆነ፣ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር

www.abyssinialaw.com

የቀረበዉ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ መሆን የለበትም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ እና በሥረ ነገር ላይ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት የሚመልስበት አግባበ እንዳለ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ጉዳይ መጀመሪያ የቀረበለት ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉን ባለመቀበል ዉድቅ በማድረግ፤ በዋናዉ ጉዳይ ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ የሰጠ እንደሆነ፣ ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበ እንደሆነ እና ፍ/ቤቱም ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመቀበል በማጽናት እና የሥር ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ላይ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከርና በማጣራት ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ሊመልስለት እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህ ሁለት ዉሳኔዎች መገንዘብ የሚቻለዉ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ መሆኑን ነዉ፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ተከራካሪ ወገን ይግባኙን ወይም የሰበር አቤቱታዉን በሕግ በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወይም ለሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ እንደሚገባዉ ነዉ፡፡

**ሐ.** ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ለዛ ፍ/ቤት በዛ ጉዳይ ላይ ዉሳኔዉ የመጨረሻ ዉሳኔ እስከሆነ ድረስ እንደአግባብነቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 ወይም 358 ዉሳኔዉን ለሰጠ ፍ/ቤት በሚቀርብ አቤቱታ ወይም ፣ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ካልቀረበ፣ ዉሳኔዉ እንደጸና የሚቆይ እና በተከራካሪ ወገኖች ላይ አስገዳጅነቱ እንደሚቀጥል ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ዉሳኔ በሕግ አግባብ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት እስካልተሻረ ድረስ በተከራካሪ ወኖቹ ላይ አስገዳጅነቱን የሚያስቀር ነገር አይኖርም፡፡

**መ.** ከፍ ሲል በፊደል ‹‹ለ›› ላይ በተመለከቱት ሁለት ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ላይ ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለሥር ፍ/ቤት መልሶለት እንደሆነ፣ የሥር ፍ/ቤት የሚያየዉ ጭብጥ ተይዞ የተመለሰለትን የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጂ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን የሚያይበት አግባብ አይኖርም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ ድጋሚ አይቶ ዉሳኔ

www.abyssinialaw.com

የሚሰጥበት አግባብ ስለማይኖር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.328 መሰረት የይግባኝ ምክንያት ተደርጎ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታ የሚቀርብበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ የሥር ፍ/ቤት እንደጭብጥ በመያዝ ዉሳኔ ያልሰጠበትን ጉዳይ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደግሞ የሚያይበት አግባብ እንደማይኖር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329(1) ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም ይግባኝ ባይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 327 መሰረት በዚህ ጉዳይ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ሊያቀርብበት አይችልም ማለት ነዉ፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከዚህ ቀደም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ በመስጠቱ ድጋሚ የሚያይበት አግባብ ስለማይኖር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ምንም ዓይነት ዉሳኔ ስለማይሰጥ ቅሬታዉ ለሚቀጥለዉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወይም ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡

**ሠ.** በዚህ አግባብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በተመለከተ ድጋሚ አይቶ ዉሳኔ ባልሰጠበት እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም በዚህ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የሚቀርበዉን ቅሬታ ተቀብሎ የሚያይበት አግባብ የለም፡፡ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ እና የሥር ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥ አስቀድሞ ከሰጠዉ ዉሳኔ ላይ በወቅቱ በሕግ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወይም የሰበር አቤቱታ ለሰበር አቤቱታ ያልቀረበ እንደሆነ፣ ዋናዉ ጉዳይ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ዉሳኔ ካገኘ በኋላ፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት አስቀድሞ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ለማቅረብ፣ በማስፈቀጃ እስካልሆነ ድረስ፣ የይግባኝ ማመልከቻ ወይም የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ ስለሚያልፍበት ተቀባይነት ሊኖረዉ አይችልም ማለት ነዉ፡፡

**ረ.** ተከራካሪ ወገኖች ላይ ከሚደርሰዉ እንግልት እና ክርክሩ ከሚያስከትለዉ ወጪ አንጻር ሲታይ እንደሚታወቀዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ የሚሰጠዉ ፍ/ቤቱ ወደ በፍሬ ነገር ላይ ማስረጃ ከመቀበሉ ወይም የሰዉ ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት ወይም ወደ ዋናዉ ክርክር ሳይገባ ከጅምሩ ለመቋጨት የሚያስችል በመሆኑ የተከራካሪ ወገኖችን እንግልት እና ለወጪ የመጋለጥ ሁኔታን የሚቀንስ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 (3) ሥር የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት

የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ በመስጠት በዋናዉ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን አጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥ የመለሰ እንደሆነ፣ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ሙሉ ክርክር በማካሄድ ማስረጃ በማቅረብ፣ ምስክሮች በመስማት፣ ጉዳዩን ለማጣራት ከሚፈጀዉ ወጪ እና ጊዜ ከመቀነስ አንጻር ወደ ሥር ፍ/ቤት ሄዶ ከመከራከር ይልቅ አንድ ጊዜ እስከተጀመረ ድረስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት አቅርቦ ጉዳዩ መቋጫ እንዲያገኝ ማድረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከራካሪ ወገኖች በዋናዉ ጉዳይ በመከራከር ጊዜያቸዉንና ገንዘባቸዉን ከመጨረስ ይልቅ ክርክሩ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚያልቅ ከሆነ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት በማቅረብ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ማድረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻርም ሲታይ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ማቅረቡ ተገቢ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

**ሰ.** ሌላዉ መታየት ያለበት ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) ድንጋጌ መሰረት ዋናዉ ጉዳይ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ተጣርቶ እንዲወሰን ተብሎ የተሰጠ ዉሳኔ፣ የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት አይገባም ወይ? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ በእርግጥ በዚህ ድንጋጌ አግባብ ዉሳኔ የተሰጠ እንደሆነ ግራ ቀኛቸዉ ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ጉዳዩ ተጣርቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ ነገር ግን አንድ ጉዳይ በዚህ ድንጋጌ አግባብ ወደ ሥር ፍ/ቤት ሲመለስ ከናካቴዉም ሙሉ በሙሉ የሰበር አቤቱታ ሊቀርበብት የሚችል አይደለም ብሎ መደምደም ተገቢ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ግልጽ ሕግን በመጣስ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ድጋሚ ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በመለሰዉ ጉዳይ ላይ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ከመከራከር ይልቅ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ማቅረቡ ተገቢ ነዉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ ሁሉ ላይ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ማቅረብ አይችልም ብሎ መደምደም ተገቢ ሆኖ አይታየኝም፡፡

**ሸ.** ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አሁን ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ የሆኑትን ጉዳዮች በተመለከተ በሰ.መ.ቁ.90810፣ 76963፣ 125165 እና

www.abyssinialaw.com

በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም አሁን ባለዉ ሁኔታ መለወጡ ተገቢ መስሎ አላገኘሁኝም፡፡

ቀ. የአሁን አመልካቾች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት እያለ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ እንደሰጠ በሕግ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ዉስጥ የሰበር አቤቱታቸዉን ለሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ እየቻሉ፣ በዚህ ረገድ ግልጽ የሆነ የሰበር ዉሳኔ እያለ ቅሬታቸዉን በወቅቱ አለማቅረባቸዉ ወይም የተዉት በቅን ልቡና ነዉ የሚያስብል ምንም ነገር ስለሌለ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡

በ. በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት አስቀድሞ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም በሕግ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ የሰበር አቤቱታ ባላቀረቡበት፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አሁን ዋናዉን ጉዳይ አከራክሮ ዉሳኔ ከመስጠት በስተቀር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ድጋሚ አይቶ ዉሳኔ ባልሰጠበት፣ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያቀርቡበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካቾች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፣ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መነሻ በማድረግ የሚሻርበት አግባብ አይኖርም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔዎች በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ በመሆኑ ሊጸኑ ይገባል ብዬ የአብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በመለየት የልዩነት ሀሳቤን አስቀምጣለሁ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

ፋ/ዘ **የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡**

www.abyssinialaw.com

# የዳኝነት ሥልጣን

www.abyssinialaw.com

የሰበር መዝገብ ቁጥር 152590

ጥቅምት 13 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች-፡-ፀጋይ አስማማው

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ እየሩሳሌም አስገዶም -ጠበቃ መስፍን አሰፋ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ተወልደ ኃ/ማርያም -ጠበቃ ጋሻው አሰፋ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ተጠሪው በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የክፍፍል ጥያቄ ያቀረቡባቸው ንብረቶች በአሜሪካን አገር የሚገኙ በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሳ መሆኑን፣የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) ድንጋጌ የተሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን ገልጾ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በሚል መዝገቡን ዘግቶ በመመለስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 44434 በ20/04/2010ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206713 በ09/05/2010 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ አመልካቿ በ24/08/2009 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ክስ ያቀረቡት የጋራ ንብረት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግላቸው በመጠየቅ ሲሆን አመልካቹ በበኩላቸው ለክሱ በ02/10/2009 ዓ.ም. መልስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ በአመልካቿ ስም በአሜሪካን አገር የተቀመጠ ነው የተባለ የጋራ ገንዘብ እና ንብረት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግላቸው በመጠየቅ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ላይ የአመልካቿን መልስ ከተቀበለ በኃላ የሥረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ ከግራ ቀኙ የቀረበ መቃወሚያ ባይኖርም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት መርምሮ ተገቢውን ብይን ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን፣የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በቀረበ ጊዜ የፍርድ ቤቱ የሥረ ነገር ስልጣን የሚወሰነው አንደኛው ወገን ያቀረበውን ከፍተኛ የሀብት ግምት መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ዋናውን ክስ ከተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ነጥሎ ለማስተናገድ የሚቻልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አለመኖሩን፣የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የቀረበበት ገንዘብ እና ንብረት በአሜሪካን አገር እንደሚገኝ የተገለጸ በመሆኑ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግ ጉዳይን የሚያስነሳ መሆኑን፣የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) ድንጋጌ የተሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን በመገለጽ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 9 (1) እና (2)፣231 (1) (ለ)፣245 (2)፣17 (3) እና 30 (1) ድንጋጌዎችን፣እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 83169 እና 37339 የተሰጡ የሰበር ገዥ ውሳኔዎችን በአስረጂነት ጠቅሶ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን በብይን ዘግቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ ያሰናበተው ሲሆን አመልካቿ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈራውን ንብረት በመጥቀስ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲያቀርቡ ተጠሪ ደግሞ በአሜሪካን አገር የተፈራው ንብረት ጭምር ተካቶ ክፍፍል እንዲፈጸም የተከሳሽ ከሻስነት ክስ ማቅረባቸውን ተከትሎ ሁለቱም ክሶች የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ እንደሆነ በመቁጠር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በሚል የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት

www.abyssinialaw.com

ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታው የቀረበበት ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በስረ ነገሩ ለመዳኘት ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻ የቀረበለት እንደሆነ ተከሳሽ ወገን መቃወሚያ ባያቀርብ እንኳ በቁጥር 231 በተነገረው ድንጋጌ መሰረት ማመልከቻው ተቀባይነት የለውም በማለት መመለስ የሚገባው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 9 ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ ለሥረ ነገር ሥልጣን ጉዳይ መነሻ የሆነው ዋናው ክስ ሳይሆን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በሆነ ጊዜም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 9 ድንጋጌ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚነት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 17 (3) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡የግል አለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው አንዱ ነጥብ ሁለቱም ክሶች ማለትም ዋናው እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የግል ዓለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ እንደሆነ በመቁጠር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በሚል የመወሰኑን አግባብነት ማጣራት ነው፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዋናው ክስ የቀረበባቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ጉዳይ ከተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም ከማለት በቀር ዋናው ክስ ጭምር የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሳ ነው የሚል አቋም አልያዘም፡፡ሁለቱ ክሶች ተጠቃለው በአንድ ፍርድ ቤት ሊታዩ ይገባል ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰውም የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 17 (3) ድንጋጌን በመዝገብ ቁጥር 83169 የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ በአስረጂነት በመጥቀስ ነው፡፡በመሆኑም እነዚህን ፍሬ ነገሮች አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተያዘው አቋም በራሱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ይሁን እንጂ በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በርግጥ የግል አለም አቀፍ ሕግ የተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ በአግባቡ ሊጤን የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩ የግል አለም አቀፍ ሕግ የተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው ተጠሪው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ያቀረቡበት ገንዘብ እና ንብረት የሚገኘው በአሜሪካን አገር ነው መባሉን ብቻ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የብይኑ ይዘት ያመለክታል፡፡ተጠሪውም በሰበር መልሳቸው ላይ ገንዘቡ እና ንብረቱ በአሜሪካን አገር የሚገኝ ነው ከመባሉ በተጨማሪ ተጠሪው የአሜሪካን አገር ዜግነት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው ጉዳዩ “Foreign element” ያለው በመሆኑ የሕግ ግጭት አያስነሳም ለማለት አይቻልም ከማለት በቀር የተለየ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡እንደሚታወቀው አንድ ጉዳይ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን /conflict of laws/ የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችለው አንድን ጉዳይ የሚገዙት ለክርክሩ አወሳሰን አግባብነት ያላቸው የተለያዩ አገሮች ሕጎች ክርክሩ በተለያየ አግባብ እንዲፈታ የሚደነግጉ መሆኑ ሲረጋገጥ፣በዚህም ምክንያት የተለያዩ አገሮች ሕጎች ግጭት ወይም ተቃርኖ /conflict of laws/ መኖሩ ሲረጋገጥ እና ከእነዚህ የተለያዩ አገሮች ሕጎች መካከል ክርክሩ ሊወሰን የሚገባው በየትኛው አገር ሕግ መሰረት ነው? የሚል ጥያቄ አከራካሪ ሆኖ ሲቀርብ መሆኑን የግል ዓለም አቀፍ ሕግ አጠቃላይ መርሆዎች ያመለክታሉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ የግራ ቀኙ ጋብቻ የተፈጸመው በኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም በሚል በተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭም ሆነ የሰበር መልሳቸው የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡የፍቺ ውሳኔም የተሰጠው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡በፍቺ ክርክር ጊዜ ስለሕጎች ግጭት ወይም ተቃርኖ በተከራካሪ ወገኖችም ሆነ በፍርድ ቤቱ የተነሳ ጉዳይ የለም፡፡በመሰረቱ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኃላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ፣በአንፃሩ ግን ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው እንደሚሆኑ፣እንዲሁም የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስት ከተጋቡ በኃላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት የጋራ ሀብታቸው እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 213/1992 በወጣው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 57 እና 62 (1) እና (2) ስር ተመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ አመልካቿ ክስ ያቀረቡትም ከላይ በተመለከቱት የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት የጋራ ናቸው የተባሉት ንብረቶች ክፍፍል እንዲደደረግላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ተጠሪው ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የጠየቁትም በአመልካቿ ስም በአሜሪካን አገር የተቀመጠ ነው የተባለ የጋራ ገንዘብ እና ሀብት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ጋብቻ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ተጋቢዎቹ በጋራ ያፈሩትን ንብረት የባለሀብትነት መብት በተመለከተ የአሜሪካን አገር ሕግ ጉዳዩን የሚገዛው ከኢትዮጵያ ሕግ በተለየ ሁኔታ ነው በሚል በተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክር የለም፡፡የስር ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ የለም፡፡ጉዳዩን በሚገዙት የሁለቱ አገሮች ሕጎች መካከል ግጭት ወይም ተቃርኖ አለ ካልተባለ ደግሞ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የቀረበበት ገንዘብ እና ንብረት የሚገኘው በአሜሪካን አገር ነው መባሉ እና ተጠሪው የአሜሪካን አገር ዜግነት ያላቸው መሆኑ ብቻውን ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩትን በአሜሪካን አገር የሚገኝ ነው የተባለ ገንዘብ እና ንብረትን በተመለከተ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ውሳኔ በአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች ሊፈጸም ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ጥያቄ ደግሞ ራሱን የቻለ የፍርድ አፈጻጸም ጥያቄ እንጂ ተመሳሳይ ጉዳይን ከሚገዙ የተለያዩ አገሮች ሕጎች ግጭት ወይም ተቃርኖ ጋር በቀጥታ የሚያያዝ ጉዳይ አይደለም፡፡እንደ ስር ፍርድ ቤቶች አቋም ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ተስተናግዶ ውሳኔ ቢሰጥ እንኳ በአሜሪካን አገር ይገኛሉ የተባሉትን ገንዘብ እና ንብረት አስመልክቶ የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ራሱን ችሎ የሚነሳ ጥያቄ መሆኑን ማስቀረት የሚችል አይደለም፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ መዝገቡን በብይን የዘጋው በመዝገብ ቁጥር 37339 የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ በአስረጂነት በመጥቀስ ነው፡፡በመሰረቱ አስቀድሞ በቀረበለት ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ቀጥለው በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው በሁለቱ ጉዳዮች ለክርክር የቀረቡት የሕግ እና የፍሬ

www.abyssinialaw.com

ነገር ነጥቦች ተመሳሳይነት ያላቸው በሆነ ጊዜ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡በመዝገብ ቁጥር 37339 የተሰጠው ገዥ ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩ ቀድሞውኑ በአንድ መዝገብ ተስተናግዶ ውሳኔ ማግኘት የነበረበት ነው በሚል ክሱን አልቀበልም ማለቱ ተገቢ አለመሆኑ ተገልጾ ጉዳዩ እንዲታይ የተመለሰበት እንጂ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ነው የተባለ ንብረት ከፊሉ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኝ መሆኑ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ተብሎ ትርጉም የተሰጠበት አይደለም፡፡በውሳኔው የመጨረሻ ፓራግራፍ የሰፈረው የውሳኔው ክፍልም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተያዘውን አቋም ለማመላከት ታስቦ የሰፈረ ነው የሚባል እንጂ ሰበር ችሎቱ እራሱ ጉዳዩን በጭብጥነት ይዞ ገዥ ውሳኔ ያሳረፈበት አይደለም፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠቃሹን የሰበር ችሎት ውሳኔ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ነው የተባለ ንብረት ከፊሉ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኝ መሆኑ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ተብሎ ትርጉም እንደተሰጠበት አድርገው በመውሰድ የያዙት አቋም የውሳኔ ትክክለኛ ዓላማ እና ይዘት መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. ጉዳዩን የማየት የስነ ነገር ስልጣን የለኝም በሚል መዘገቡን ዘግቶ በመመለስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 44434 በ20/04/2010 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206713 በ09/05/2010 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ በጋብቻቸው ጊዜ ካፈሩት ገንዘብና ንብረት ከፊሉ በአሜሪካን አገር ይገኛል መባሉ ብቻውን የግል ዓለም አቀፍ ሕግን ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ጭምር የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው በማለት ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

4. መዝገቡን አንቀሳቅሶ ክርክሩን ቀጥሎ በማየት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) መሰረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
5. የውሳኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.144242

ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

አብዬ ካሳሁን

አመልካች - አቶ ገዛህኝ አየለ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች - 1ኛ. አቶ ኑረዲን ዓሊ - ቀረቡ

2ኛ. አቶ አይደር ከድር - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት የአሁን 1ኛ ተጠሪ አላግባብ ተይዞብኛል የሚሉት በከተማው ቀበሌ 04 አስተዳደር ክልል የሚገኘውን ቁጥሩ 027 የሆነ የቀበሌ የንግድ ሱቅ እንዲመለስላቸው ያቀረቡትን ክስ ተመልክቶ የአሁን አመልካች ሱቁን ለከሳሽ (1ኛ ተጠሪ) እንዲያስረክቡ ያሳለፈውን ውሳኔ እና ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔው ግድፈት አልተገኘበትም በማለት የቀረበለትን አቤቱታ ባለመቀበል ትዕዛዝ በመስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 29/2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አከራካሪው ጉዳይ የቀበሌ ቤት ሆኖ ዕያለ የስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው በማለት ክርክሩን አይቶ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

በበኩላችን አመልካች በዳኝነት ስልጣን ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ክሱ የቀረበው የድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 04 አስተዳደር በሚያስተዳድረው በቀበሌው ክልል የሚገኘውን ቁጥሩ 027 የሆነ የንግድ ሱቅ

www.abyssinialaw.com

ለማስመለስ ሲሆን ከክሱ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው ዳኝነት የተጠየቀው የሥር 1ኛ ተከሳሽ (የአሁን 2ኛ ተጠሪ) በከሳሽ ከተሰጠው የውክልና ስልጣን ውጪ በቤቱ በራሱ ሥም የንግድ ፍቃድ ከማውጣቱም በላይ ለ2ኛ ተከሳሽ (አሁን አመልካች) በአደራ ሰጥቶት የሚገኝ በመሆኑ እንዲመልስልኝ ብጠይቀውም ለመመለስ ፈቃደኛ ስላልሆነ ከመንግስት የተከራየሁትን የንግድ ሱቅ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ በመግባት የውሉን ይዘት መርምሮ ቤቱ ለከሳሽ እንዲመለስ ወስኗል፡፡

በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1)(ረ) እንደተደነገገው የከተማው አስተዳደር የሚያስተዳድራቸው ሆኖ ለንግድ፣ ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክሶችን ተመልክቶ ለመወሰን የድሬደዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ለክሱ ምክንያት የሆነው በግለሰቦች መካከል የተደረገ ውል ሲሆን ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ የተሰጠውም ከውሉ ጋር በተያያዘ በቀረበው ክርክር ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ የሚሸፈን አይሆንም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 4 ሥር እንደተመለከተውም በቀጥታ ወይም በግልፅ ካልታገዱ በቀር መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሁሉ የፍትሐ ብሔርን ክስ ተቀብለው ለማከራከር ሥልጣን አላቸው፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሊታይ ይገባል በሚል በአመልካች የቀረበው መከራከሪያ ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ እና ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ህጎች ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 60477 ሚያዚያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12730 ሰኔ 20 ቀን 2009 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 6/2010 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

አ/ጐ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 145733

ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ ኤበሳ አመንቴ ጃለታ -

ተጠሪዎች፡- 1. የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት

2. የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አካባቢ ንግድና እንዲስቱሪ ፅ/ቤት

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 26794 ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡

ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች እንደነበሩ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት፡- በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 108 ከግለሰብ ላይ በመከራየት ከ2ኛ ተከሳሽ መ/ቤት በተሰጠኝ የዋና ምዝገባ ምስክር ወረቀት የንግድ ስራ ፍቃድ የሆቴል ድርጅት በማቋቋም አገልግሎት ላይ እያለሁ ከሳሽ ለ2009 ዓ/ም የግብር ዘመን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሊከፈል

www.abyssinialaw.com

የሚገባውን የመንግስት ግብር በመክፈል እና ለ2009 ዓ/ም የግብር ዘመን የንግድ ስራ ፍቃድ እንዲታደስ የሚፈቅድ ክሊራንስ በመቀበል 2ኛ ተከሳሽ ጥያቄ በቀረበለት በአጭር ጊዜ ውስጥ የከሳሽን ንግድ ስራ ፍቃድ ማደስ ሲገባው አላግባብ ለረጅም ጊዜያት ሲያጉላላኝ ከቆየ በኋላ በቀን 28/04/2009 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ የአካባቢ ፅ/ቤት የንግድ ስራ ፍቃድህ እንዲታገድ ስላሳወቀኝ የንግድ ስራ ፍቃድህ አናድስም በማለት ክልከላ ከማድረጉ በላይ የንግድ ስራ ፍቃድህ ታግዷል በማለት በቀን 28/04/2009 ዓ/ም የተፃፈ የማሳወቂያ ደብዳቤ ሰጥቶኛል፡፡ ስለሆነም የንግድ ስራ ፍቃዴን ያገዱኝ እና እንዳይታደስ የከለከሉኝ ያለአግባብ ስለሆነ ክልከላው ተነስቶ የንግድ ስራ ፍቃዳቸው እንዲታደስ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቋን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በበኩላቸው በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች በመሆን በሰጡት መልስ በከሳሽ የንግድ ድርጅት ላይ በተደጋጋሚ በተደረገ የድምፅ ልኬት ከሳሽ የሚለቀቀው የድምፅ ማጉያው ድምፅ ከሚፈቀደው ድምፅ ልኬት በላይ በመሆኑ በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ የድምፅ ብክለት እያደረሰ ስለመሆኑ በባለሞያ የተረጋገጠ በመሆኑ የተወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ በአግባቡ መሆኑ በመግለፅ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች የንግድ ስራ ፍቃድ የታገደውና እንዳይታደስ የተከለከለው ከህግ ውጪ ነው በማለት የስር 2ኛ ተከሳሽ የነበረው አዲስ ከተማ ክ/ከተማ የንግድ ፅ/ቤት ተጠሪን የንግድ ስራ ፍቃድ ያገደውና እንዳይታደስ የከለከለው ከህግ ውጪ ነው ፡፡ የአመልካች የንግድ ስራ ፍቃድ ሊታደስ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመቀጠል ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 46 መሠረት አግባብ ባለው አካል አስተዳደራዊ እርምጃዎች የተወሰደበት ማናቸውም ሰው በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 47 ንኡስ አንቀፅ 3

www.abyssinialaw.com

መሠረት በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ቅሬታ ካለው ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበት ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንጂ በቀጥታ ክስ ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አሁን በአመልካች የቀረበው አቤቱታ ይህ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የአመልካች ቅሬታ ይዘት ባጭሩ ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀፅ 46 እና 47 መሰረት በአስተዳደር አካል የተወሰዱት ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በህግ ጉዳይ ላይ ስልጣን ላለው ፍርድቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይገባል ሲባል ጉዳዩ መቅረብ ያለበት ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንጂ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አይደለም በማለት ውሳኔ መስጠቱ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 79 መሰረት የተቀመጠውን መብት የጣሰና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት እንዲታይ በመደረጉ 1ኛ ተጠሪ መልስ በፅሁፍ የሰጠ ሲሆን ለ2ኛ ተጠሪ አመልካች መጥሪያ ባለመውሰዳቸው አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ቅሬታ እንዳልፈለገው ተቆጥሮ የታለፈ ስለመሆኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም በሰበር አጣሪው ችሎት እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል ፡፡ እንደመረመርነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ በመሆን ያቀረበው ክስ ከ2ኛ ተከሳሽ መ/ቤት በተሰጠኝ የዋና ምዝገባ ምስክር ወረቀት የንግድ ስራ ፍቃድ የሆቴል ድርጅት በማቋቋም አገልግሎት ላይ እያለሁ ከሳሽ ለ2009 ዓ/ም የግብር ዘመን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሊከፈል የሚገባውን የመንግስት ግብር በመክፈል እና ለ2009 ዓ/ም የግብር ዘመን የንግድ ስራ ፍቃድ እንዲታደስ የሚፈቅድ ክሊራንስ መነሻነት 2ኛ ተከሳሽ የከሳሽን ንግድ ስራ ፍቃድ ማደስ ሲገባው የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ የአካባቢ ፅ/ቤት የንግድ ስራ ፍቃድህ እንዲታገድ ስላሳወቀን የንግድ ስራ ፍቃድህ አናድስም በማለት ክልከላ ከማድረጉ በላይ የንግድ ስራ ፍቃድህ ታግዷል በማለት በቀን 28/04/2009 ዓ/ም የተፃፈ የማሳወቂያ ደብዳቤ እንደደረሰው በመግለፅ እና የንግድ ስራ ፍቃዳቸውን

እንዳይታደስ የከለከለው ያለአግባብ መሆኑ ጠቅሰው የንግድ ስራ ፍቃዳቸው እንዲታደስ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 46 መሠረት አግባብ ባለው አካል አስተዳደራዊ እርምጃዎች የተወሰደበት ማናቸውም ሰው በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 47 ንኡስ አንቀፅ 3 መሠረት በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ቅሬታ ካለው ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበት ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንጂ በቀጥታ ክስ ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑ ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለመረዳ እንደተቻለው ተጠሪዎች የአመልካችን የንግድ ስራ ፍቃድ እንዳይታደስ በመከልከል የወሰዱት እስተዳደራዊ እርምጃ በተመለከተ አመልካች በቀጥታ ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኝነት መጠየቃቸው አግባብነት ነው ?ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መመርመሩ አስፈለጊ መሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 46 እንደተመለከተው አዋጅ፣አዋጅን ተከትለው የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ተላልፎ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ አግባብ ያለው አካል በአዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ በተመለከተው መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወስድ የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አግባብ ያለው ባለስልጣን የበላይ ሃላፊ የቀረበውን አቤቱታ ሰምቶ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ እንዳለበት በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ የበላይ ሃላፊው ውሳኔውን ያላሳወቀው እንደሆነ ቅሬታ አቅራቢው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ እንደሚችል በዚሁ አዋጅ ዓንቀፅ 47(2) የተመለከተ ሲሆን ፤አግባብ ያለው ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም ምላሽ ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው ውሳኔ በተሰጠ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል በዚሁ አዋጅ ዓንቀፅ 47(3) ስር ተደንጓል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት የሚቻለው አግባብ ያለው ባለስልጣን ውሳኔ ያገኘ እና በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን በህግ ጉዳይ ላይ ብቻ ይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በተያዘው ጉዳይ በቀን 28/04/2009 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የንግድ ስራ ፍቃድህ አናድስም፤ የንግድ ስራ ፍቃድህ ታግዷል በማለት ተጠሪ በቀን 28/04/2009 ዓ/ም የተፃፈ ደብዳቤ ለአመልካች የደረሰው በመሆኑ አመልከች በዚሁ አስተዳደራዊ እርምጃ ቅር የተሰኘ ከሆነ በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 47(3) መሰረት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንጂ በቀጥታ ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ስለማይችሉ የስር ፍርድቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

## ው ሳ ኔ

1.በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 26794 ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል።

2 . በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ብ/ግ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር---153617

ቀን-መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** አቶ ደሱ ታምሩ

**ተጠሪ፡-** ፌያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የተጠሪ አባላት እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ስራ ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር በሚል ተደራጅተን ስንሠራ ቆይተን ወደ ፌያ ጠቅላላ ስራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በሚል ወደ ንግድ ማህበር ቀይረናል፡፡ አመልካች የዚህ ማህበር ስራ አስኪያጅ በመሆን ከሰኔ ወር 2003 ዓ.ም እስከ መጋቢት 26 ቀን 2006 ዓ.ም ሲሠራ በቆየበት ወቅት በተለያየ ምክንያት የወሰደዉና ማህበሩ ላይ ጉዳት ያደረሰዉን በጠቅላላዉ ብር 83,517.18 ይክፈለን የሚል ነዉ፡፡

አመልካች በሰጠዉ መልስ በስራ አስኪያጅነት የሠራሁት ማሕበሩ የሕብረት ሥራ ማህበር በነበረበት ወቅት እንጂ የንግድ ማህበር ከሆነ በኃላ ሥራ አስኪያጅ አቶ አለማየሁ አዱኛ ነበር፡፡ ዳኝነት የተጠየቀባቸዉን ገንዘቦች ለመክፈል በወቅቱ የሂሳብ ሠራተኛ ወይም ገንዘብ ያዥ ስላልነበርኩ ለመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ መርምሮ አመልካች ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀዉን

www.abyssinialaw.com

ገንዘብ ለመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ብር 83,517.18 ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል። በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካቾች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ አመልካች ኃላፊነት አስከትሏል የተባለዉን ድርጊት የፈጸመዉ የተጠሪ ማህበር ወደ ንግድ ማህበር ከመቀየሩ በፊት እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ስራ ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር በነበረበት ወቅት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 47 እና 49 መሠረት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ የሽምግልና ዳኝነት አካል እንጂ ለመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖረዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል። በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ክስ በተመሠረተበት ወቅት ተጠሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሕብረት ሥራ ማሕበር መሆኑ ቀርቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 147/91 የሚተዳደር ሳይሆን በንግድ ሕጉ የሚገዛ በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ የሚታየዉ በሽምግልና ዳኝነት ነዉ በማለት መደበኛ ፍ/ቤት የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለዉም ሲል የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ መሻሩ ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ ዉሳኔዉን ሽሮ የፍሬ ጉዳይ ይግባኙን ተመልክቶ ተገቢዉን ይወስን ዘንድ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመለስ ወስኗል። ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ዉሳኔዉን ለማስለወጥ ነው።

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፦ በእናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ስራ ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር እና በፈያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በዉልም ሆነ በሕግ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ሳይኖር እንዲሁም ግንኙነት እንዳላቸዉም ክርክርም ሆነ ማስረጃ ቀርቦ ባልተረጋገጠበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ከመጀመሪያዉ ክሱን ለማቅረብ የቻለዉ የቀድሞ የሕብረት ሥራ ማህበሩ መብትና ግዴታዎች በሙሉ ወደ አሁኑ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመለወጡ ምክንያት መሆኑን በግራ ቀኙ ከቀረበዉ ክርክር እና ማስረጃ መገንዘብ ይቻላል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የተሳሳተ ነዉ። የሕብረት ሥራ ማህበሩ ከፈረሰ ከዓመታት በኋላ ክስ የቀረበዉ በሌላ ማህበር ስም ነዉ። በሌላ በኩል ተጠሪ ኃ/የተ/የግል ማህበሩን የሚመለከቱትን ብቻ በመለየት ክስ አልመሠረተም። ስለሆነም የፌዴራል

መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት በሕብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49(3) እና የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 91745 የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሚቃረን መልኩ የሰጡት ዉሳኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የተጠሪ ድርጅት ቀደም ብሎ እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ሥራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሕብረት ሥራ ማህበር ነበር በማለት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሲወሰን ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳይቀርብና በሕብረት ሥራ ማህበርና ኃ/የተ/የግ ማህበር መካከል ያለዉ ልዩነት ከግንዛቤ ዉስጥ ሳይገባ ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉን ቅሬታ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የሰጠዉ መልስ ይዘት፡- እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ስራ ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር በጥቃቅንና አነስተኛ ሲደራጅ የነበረዉ ስያሜ ሲሆን በ2004 ዓ.ም ወደ ፊያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር በሚል የስያሜ ለዉጥ አድርጓል፡፡ በሁለቱ መካከል የስም ለዉጥ እንጂ የአባላትም ሆነ የንብረት ልዩነት በሌለበት ሁኔታ ምንም የሕግ ግንኙነት የላቸዉም የሚለዉ ቅሬታ ተገቢነት የለዉም፡፡ የቀድሞ ማህበር አባላቱንና ንብረቱን በመያዝ የተጠሪን ንግድ ማህበር መስከረም ወር 2006 ዓ.ም ሲቀየር አመልካች እስከ መጋቢት 2006 ዓ.ም በሥራ አስኪያጅነት አገልግለዉ ከማህበር አባልነት ተሰናብተዋል፡፡ አመልካች ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ ላደረሱት ጉድለት በአንድ ላይ ከሚጠየቁ በቀር ተጠሪ ክስ ማቅረብ ያለበት ለይቶ ነዉ የሚለዉ ክርክር ተገቢነት የለዉም፡፡ ስለሆነም አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ ዉድቅ ይደረግልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተገነዘብነዉ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሲያቀርብ የጠየቀዉ ዳኝነት ፊያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ተብሎ ከመመዝገቡ በፊት እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ሥራ ኃ/የተ/የህብረት ሥራ ማህበር በሚል

በሚታወቅበት ወቅት አመልካች የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሠራ ለግል ጥቅሙ ያዋለዉንና በሌላ መንገድ በድርጅቱ ላይ ያደረሰዉን ጉዳት በድምሩ ብር 83,517.18 እንዲከፍለዉ ሲሆን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ሙሉን ገንዘብ እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ሳይገባ ለክሱ መነሻ የሆነዉ ነገር ማሕበሩ የሕብረት ሥራ ማሕበር በነበረበት ወቅት የተፈጸመ ተግባርን መነሻ ያደረገ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 149/91 አንቀጽ 49 እና 47 መሰረት ስልጣን የተሰጠዉ ለሽምግልና ዳኝነት አካል በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ዓይቶ ለመወሰን ስልጣን የለዉም በማለት ዉሳኔዉን ሽሮታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ክርክሩ እየተደረገ ያለዉ ከሕብረት ሥራ ማሕበር ጋር ሳይሆን ኃላፊነቱ ከተወሰነ የግል ማሕበር ጋር በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ዓይቶ የመወሰን ስልጣን አለዉ በማለት የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ተመልክቶ እንዲወስን መልሶለታል፡፡

በመሠረቱ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 47 እና 49 መሠረት ጉዳዩ በቅድሚያ በእርቅ ካላለቀ በሽምግልና ዳኝነት የሚታየዉ በአንድ ማሕበር እና በአባላቱ ወይም በቀድሞ አባሉ ወይም በአመራሩ ወይም በቀድሞ አመራሩ ወይም ከሌላ ማሕበር ጋር ክርክር ሲኖር ነዉ፡፡ አንድ ማሕበር ሕልዉናዉ ካበቃ በኃላ ወይም መብትና ግዴታዉ የሕብረት ሥራ ማሕበር ወደ አልሆነ የንግድ ማሕበር ተላልፎ በሚገኝበት ወቅት ክርክሩ በሽምግልና ዳኝነት ይታያል የሚል የሕግ ድንጋጌ ባለመኖሩ መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የሆነዉ የአሁኑ ተጠሪ ከሕብረት ሥራ ማሕበር የተላለፈልኝ መብትና ግዴታ አለኝ አለ እንጂ ራሱ ኃ/የተወሰነ የግል ማሕበር በመሆኑ ጉዳዩን ለሽምግልና ዳኝነት ለመወሰድ የሚገደድበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሕብረት ሥራ ማሕበሩ የቀድሞ አባል በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 47 እና 49 መሠረት በሽምግልኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተገቢነት የለዉም፡፡

ሌላዉ ግራ ቀኙን ያከራከረዉና የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ተጠሪ የቀድሞዉ እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ሥራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሕብረት ሥራ ማሕበር መብትና ግዴታ የተላለፈለት ድርጅት ስለመሆኑ

www.abyssinialaw.com

ማስረጃ ሳይቀርብና በሁለቱ ማሕበራት መካከል ያለዉ ልዩነት ከግንዛቤ ዉስጥ ሳይገባ ዉሳኔ መሠጠቱ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ጭብጥ በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ዓይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አለዉ ሲል ወሰነ እንጂ በሁለቱ ማሕበራት መካከል የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ መኖሩን አስመልክቶ በማስረጃ የተደገፈ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን የፍሬ ጉዳይ ክርክር ዓይቶ አልወሰነም፡፡ ይልቁንም ይግባኝ ሰሚዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ተመልክቶ እንዲወሰን መልሶለታል፡፡

በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሰረት ለዚህ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን አይደለም፡፡ አመልካች ያነሳውን የፍሬ ጉዳይ ክርክርን በተመለከተ ገና የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበትና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ታይቶ እንዲወሰን የተመለሰ በመሆኑ በዚህ ረገድ የመጨረሻ ውሳኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ በሰበር የሚታይ አይሆንም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሕብረት ስራ ማህበር አለመሆኑን በማረጋገጥ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን አለው በማለት የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ተመልክቶ እንዲወስን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መመለሱ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉ ሳ ኔ**

1. በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 149468 ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ 142594

ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- የደሴ ከተማ ዓይነ ሥውራን ማሕበር

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ዓይነ ሥውራን ብሔራዊ ማሕበር

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የመ.ቁ 142594 እና 156658 የሆኑ መዝገቦች ተጣምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የተሰረዘን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታን በሚመለከት የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ አመልካች፤በዚህ የሰበር ክርክር የሌለ የደሴ ከተማ አሥተዳደር ኢ/ከ/ል/አገ/መምሪያ ተጠሪ የአሁን አመልካች ደግሞ ጣልቃገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪው በ1952 ዓ.ም የተቋቋመ እና በበጎ አድራጎት ድርጅት እና ማሕበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ ማሕበር መሆኑ፤ማሕበሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ቅርንጫፍ ማሕበራት ያሉት እና በደሴ ከተማ ውስጥም የኢትዮጵያ ዓይነሥውራን ብሔራዊ ማሕበር የደቡብ ወሎ ዞን ዓይነሥውራን ቅርንጫፍ ማሕበር ያቋቋመ መሆኑን፤ማሕበሩ በደሴ ከተማ ቧንቧ ውሃ ክፍለ ከተማ ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ የያዘውን ይዞታ ካርታ አውጥቶ እና ግንባታ ገንብቶ አትክልት በመትከል ከሠላሣ ሥድሥት ዓመታት በላይ የሚጠቀምበት መሆኑን፤የሥር ተጠሪው ምንም ዓይነት

ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረው የተጠሪን ካርታ በመሠረዝ በአሁን ወቅት በሌላ ባልተቋቋመ እና ሕጋዊ ሰውነት በሌለው በደሴ ከተማ አሥተዳደር በደቡብ ወሎ ዞን ዓይነሥውራን ማሕበር ሥም ካርታ እንዲሰራ ያደረገ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ካርታ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር ተጠሪ በሰጠው መልስ ተጠሪው ማሕበር ቅርንጫፍ ለመክፈት የተፈቀደለት ስለመሆኑ ማሥረጃ ያላቀረበ መሆኑን፤ቦታው በቅድሚያ ለደሴ ዓይነሥውራን ማሕበር ት/ቤት መሥሪያ መሆኑን እና ለደሴ ከተማ እና አካባቢዋ ዓይነሥውራን ማሕበር በ1972 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የተወሰኑ ግለሰቦች በቂ ባልሆነ ምክንያት ሥያሜውን በተጠሪ ሥም በመቀየር ከታለመለት ዓላማ ውጪ ቤቱን በማከራየት ተጠሪው ሲጠቀምበት የነበረ መሆኑን፤የከተማው ከንቲባ ጽ/ቤት ባቋቋመው አጣሪ ቡድን አማካኝነት ተጣርቶ በቀረበው አሥተያየት ጉዳዩ ተመርምሮ ተጠሪ ከተመለከተው ዓላማ ውጪ በማከራየት የሚጠቀምበት በመረጋገጡ ካርታው መሰረዙ የአካባቢውን ዓይነሥውራን ተጠቃሚ የሚያደርግ እና ሕጋዊ ተግባር መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የአሁን አመልካችም ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር አመልክቶ ተፈቅዶለት ባቀረበው ክርክር ተጠሪ ክስ ያቀረበበት ጉዳይ አሥተዳደራዊ ጉዳይ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን፤ሥረዛ የተደረገበት ካርታ የኢትዮጵያ ዓይነሥውራን ብሔራዊ ማሕበር የደቡብ ወሎ ዞን ዓይነሥውራን ቅርንጫፍ የሚል እና በአዋጁ መሠረት ቅርንጫፍ ስለመሆኑ ማሥረጃ ያልቀረበበት በመሆኑ ተጠሪው ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የሌለው መሆኑን፤አከራካሪው ይዞታ የተሰጠው ለወሎ ክፍለ ሐገር ዓይነሥውራን ት/ቤት መሆኑን፤ የተጠሪ ማሕበር ሥያሜውን ወደ ደሴ ከተማ ዓይነሥውራን ማሕበር በሚል በ1999 ዓ.ም ካርታ ተሰርቶ እየተጠቀመ የተወሰኑ ግለሰቦች በቂ ባልሆነ ምክንያት ካርታ ሰጪውን በማሣሣት የተቀየረ መሆኑ በመረጋገጡ ወደ ቀድሞው እንዲመለስ ውሳኔ ማሳለፉ ሕጋዊ ተግባር መሆኑን፤ተጠሪ ይዞታውን ለሌላ 3ኛ ወገን በማከራየት ገንዘቡን ለተወሰኑ ግለሰቦች መጠቀሚያ ማድረጉ ስለተረጋገጠ ካርታው እንዲሰረዝ የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሆኑን እና አመልካች በክልሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማሕበራት አዋጅ መሠረት ተመዝግቦ ሕጋዊ

www.abyssinialaw.com

ሠውነት የተሰጠው መሆኑን በመግለጽ የተጠሪው ክስ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል። ተጠሪም አመልካች ላቀረበው የጣልቃገብነት መከራከሪያ መልስ ሰጥቷል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ የተመለከተው በደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ምሥክሮችን ከሰማ እና ጉዳዩን የሚመለከት የተለያየ የሰነድ ማሥረጃ በትዕዛዝ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ የግራቀኙን ክርክር እና ማሥረጃ መርምሮ የቀረቡት ማሥረጃዎች የሚያሳዩት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቦታ ለዓይነስውራን ት/ቤት በሚል ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ በጊዜው እውራን ተራድኦ ድርጅት በአሁኑ ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማሕበር ለተባለው ለአሁን ተጠሪ ማሕበር የተሰጠው መሆኑን፤ተጠሪ በቀድሞው የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማሕበር የወሎ ክ/ሐገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአሁኑ ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ዓይነስውራን ብሔራዊ ማህበር የደቡብ ወሎ ዞን አይነስውራን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያለው መሆኑን እና ይኸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከብሔራዊ ማሕበሩ ጋር በመሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቦታ እንዲሰጠው፤ካርታ እንዲሰራለት እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀ መሆኑን፤ቦታው ከተሰጠው በኋላም በብሔራዊ ማሕበሩ ስም የሊዝ ውል በመግባት እና የግንባታ ፈቃድ በማውጣት በቦታው ላይ ግንባታ ያከናወነ እና ቦታው ለአመልካቹ የተሰጠ ስለመሆኑም የሥር ተከሳሹም ሆነ የከንቲባው ጽ/ቤት የሚያውቁ እና የፈቀዱ መሆኑን በመሆኑ ቦታው ለተጠሪ የተሰጠ ነው፤የሥር ተከሳሽ ካርታው የተሰረዘው ቦታው የአመልካቹ ነው በሚል ቢሆንም ቦታው ሲሰጥም ሆነ ካርታው ሲሰራ አመልካች ቦታው እንዲሰጠው ያመለከተ እንዲሁም ቦታውን የተረከበ ስለመሆኑ ያላስረዳ በመሆኑ የሥር ተከሳሹ ካርታውን ያመከነው ከሕግ ውጪ ነው፤አመልካች ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው እና ቦታው ይገባኛል በማለት አቤቱታ ያቀረበው ከጥር ወር 2006 ዓ.ም ወዲህ በመሆኑ አመልካች ባልነበረበት ወቅት ለተገኘ መብት ባለመብት አያደርገውም፤የተጠሪ ካርታ መክኖ በደሴ ከተማ አሥተዳደር እና የደቡብ ወሎ ዞን ዓይነስውራን ማሕበር በሚል የተሰራ ቢሆንም በዚህ ስም የሚጠራ እና የተመዘገበ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ማሕበር የሌለ ስለመሆኑ በሚመለከታቸው አካላት የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ክስ በቀረበበት ቦታ ላይ መብት እና ጥቅም የለውም ሲል ወስኗል።

www.abyssinialaw.com

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪው በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ ማሕበር በመሆኑ እና ዋና መሥሪያ ቤቱም አዲስአበባ በመሆኑ ተጠሪ የመሰረተው ክስ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6 መሠረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚታይ ነው፤በሕገመንግሥቱ በተሠጠው ውክልና መሠረት የተጠሪ ክስ በክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚታይ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተጠሪ ሥልጣን የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ክልሎች በሥራቸው ያሉትን ከተሞች ለማቋቋም፤ለማደራጀት፤ሥልጣን እና ተግባራቸውን ለመወሰን እንዲችሉ የወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች የመዳኘት ፍትሐብሔራዊ ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት መሆኑን ይደነግጋል፤ አከራካሪው ጉዳይ በደሴ ከተማ ቧንቧ ውሃ ክፍለከተማ የሚገኘውን ይዞታ ካርታ እና ፕላን ሊሰረዝብን አይገባም የሚል በመሆኑ በከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት የሚታይ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በፍሬነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን በማለት ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልሶለታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የመ.ቁ 142594 በሆነው መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በፌዴራል መንግሥት የተቋቋሙ እና የተመዘገቡ የንግድ ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የሥረ ነገር ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፤ክርክሩ ከማንኛውም የክስ ምክንያት የመነጨ ቢሆንም የክርክሩ ተሳታፊ በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ ከሆነ ወይም መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያየ ክልል በሆነ ተከራካሪዎች መካከል የተነሳ ክርክር የማየት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፤ተጠሪ የፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ

www.abyssinialaw.com

ማሕበር በሆኑ እና መደበኛ መቀመጫውም አዲስ አበባ በመሆኑ፤አመልካች ደግሞ በአማራ ክልል የተመዘገበ ማሕበር በመሆኑ ክርክሩን የማየት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሆነው ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማው ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አላቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ ማሕበር ሆኖ ሳለ የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማው ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አላቸው በማለት የሥር ይግባኝ ሰሚው የከተማው ፍ/ቤት በፍሬነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን በማለት ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመለሰው መሠረት ጉዳዩ የተመለሰለት የሥር ይግባኝ ሰሚው የከተማው ፍ/ቤት ዋናውን ጉዳይ አይቶ የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በዋናው ጉዳይ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የመ.ቁ 151771 በሆነው መዝገብ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች በመ.ቁ 151771 ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘት ተጠሪ በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ ማሕበር ስለመሆኑ እና መደበኛ መቀመጫውም አዲስ አበባ ከተማ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች በቀረበው የምዝገባ የምሥክር ወረቀት ተረጋግጧል፤አመልካች ደግሞ በአማራ ክልል በደሴ ከተማ አሥተዳደር የተመዘገበ በመሆኑ ክርክሩን የማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ነው፤የከተማው ፍ/ቤቶች የይዞታ መብት አጠባበቅን የሚመለከት ክርክር የማየት ሥልጣን ያላቸው ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 25/88 ን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች በማይቃረን ሁኔታ እንጂ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ሊሆን አይገባውም፤በመሆኑም አመልካች በመ.ቁ 142594 ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ምላሽ ሳያገኝ በፍሬጉዳዩ ላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው

www.abyssinialaw.com

ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ፤ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ፡-

1. የደሴ ከተማ አሥተዳደር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበውን ክስ ተቀብሎ ለመወሰን የሚያስችል የሥረ-ነገር ሥልጣን አላቸው? ወይስ የላቸውም?
2. የሥር ፍ/ቤቶች በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 (2)እና(6) መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን፤በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እና ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን ተቀብለው የማስተናገድ ሥልጣን እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች የመዳኘት ፍትሐብሔራዊ ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ሁለቱም አዋጆች የየራሣቸውን ዓላማ ይዘው የወጡ ከመሆናቸው አኳያ በመዝገቡ የተያዘው ጉዳይ በየትኛው ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን ሥር ሊታይ እንደሚገባ መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 (2)እና(6) መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን፤በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ

www.abyssinialaw.com

ድርጅቶች እና ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች በማለት የተገለጸው ሀሳብ የጉዳዮች ዓይነት ምንም ይሁን ምን ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ ክርክርን፤በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበን ማሕበር የሚመለከት ክርክርን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች የመዳኘት ፍትሐብሔራዊ ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት መሆኑን በመግለጽ የሚደነግግ ሲሆን ለጉዳዩ ዓይነት ትኩረት በመስጠት በድንጋጌው ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮች በከተማው አሥተዳደር ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር እንዲታዩ ታሳቢ በማድረግ የተደነገገ ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 (2)እና(6) መሠረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቀው መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ ወይም በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እና ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ማናቸውም ዓይነት ክርክሮችን ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያሻው መሠረታዊ ነጥብ በመሆኑ አዋጆቹ ከወጡለት ዓላማ አንጻር በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል እንዲሁም በፌዴራል መንግሥቱ ተመዝጋቢ የሆነ ማሕበር ተከራካሪ የሆነበት ነው ተብሎ አካላት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በደሴ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ይዞታን በሚመለከት የተሰጠን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አላግባብ ተሰርዞብናል በማለት የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ከመሬት ይዞታ ባለመብትነት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ይህንኑ በሚመለከት የሚቀርብ ክስ በከተማው ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚታይ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ ወይም በፌዴራል መንግሥቱ

አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እና ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች በፌዴራል ፍ/ቤቶች የሥረነገር የዳኝነት ሥልጣን የሚታዩ መሆናቸው የሚደነግግ ቢሆንም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 52/2/ለ ለክልሎች በተሰጠው ሕግ የማውጣት ሥልጣን መሠረት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 ደግሞ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤ የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች በከተማው ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚታዩ መሆናቸውን የሚደነግግ በመሆኑ በመዝገቡ የተያዘው ጉዳይ በየትኛው ፍ/ቤት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ሊታይ ይገባል የሚለውን ለመለየት የክርክሩን ልዩ ባህርይ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አከራካሪ የሆነው ጉዳይ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተሰጠን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስረዛን የሚመለከት ሲሆን አከራካሪ የሆነው ይዞታ የሚገኘውም በደሴ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 25 የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚቀርበው ክስ ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ ላስቻለው ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ክልሎች በሕገመንግሥቱ በተሰጣቸው ሕግ የማውጣት ሥልጣን መሠረት የወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 ደግሞ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች በከተማው ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚታዩ መሆናቸውን የሚደነግግ በመሆኑ፤ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት በመሆኑ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 25 የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚቀርበው ክስ ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ ላስቻለው ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት የሚደነግግ በመሆኑ አከራካሪ ከሆነው ጉዳይ አንጻር የተከራካሪ ወገኖች መደበኛ ነዋሪነት ወይም የተከራካሪው ወገን የፌዴራል መንግሥቱ ተመዝጋቢ መሆን ግምት ውስጥ ሳይገባ የጉዳዩን ዓይነት መሠረት በማድረግ አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 መሠረት የከተማው አሥተዳደር

www.abyssinialaw.com

ፍ/ቤቶች ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ተቀብለው የመወሰን የሥረነገር ሥልጣን አላቸው ብለናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማሥረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች አከራካሪው ቦታ ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ በጊዜው እውራን ተራድኦ ድርጅት በአሁኑ ወቅት ደግሞ ለአሁን ተጠሪ የተሰጠው መሆኑን፤ተጠሪ በቀድሞው የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማሕበር የወሎ ክ/ሐገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአሁኑ ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ዓይነስውራን ብሔራዊ ማህበር የደቡብ ወሎ ዞን አይነስውራን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያለው መሆኑን እና ይኸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከብሔራዊ ማሕበሩ ጋር በመሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቦታ እንዲሰጠው፤ካርታ እንዲሰራለት እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀ መሆኑን፤ቦታው ከተሰጠው በኋላም በብሔራዊ ማሕበሩ ስም የሊዝ ውል በመግባት እና የግንባታ ፈቃድ በማውጣት በቦታው ላይ ግንባታ ያከናወነ እና ቦታው ለተጠሪ የተሰጠ መሆኑን፤ቦታው ለተጠሪ ሲሰጥም ሆነ ካርታው ሲሰራ አመልካች ቦታው እንዲሰጠው ያመለከተ እንዲሁም ቦታውን የተረከበ ስለመሆኑ ያላስረዳ መሆኑን፤የሥር ተከሳሽ ካርታውን ያመከነው ከሕግ ውጪ መሆኑን፤አመልካች ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው እና ቦታው ይገባኛል በማለት አቤቱታ ያቀረበው ከጥር ወር 2006 ዓ.ም ወዲህ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ክስ በቀረበበት ቦታ ላይ መብት እና ጥቅም የለውም ሲሉ ወስነዋል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት ለዚህ ችሎት የተሰጠው ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ አከራካሪ የሆነው ይዞታ የተጠሪ መሆኑ እና ለተጠሪ ተሰጥቶ የነበረው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አላግባብ የተሰረዘ መሆኑን፤አመልካች ክስ በቀረበበት ቦታ ላይ መብት እና ጥቅም የሌለው መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ እና ይህ ችሎትም ፍሬነገርን የማጣራት እና ማሥረጃን የመመዘን ሥልጣን የሌለው በመሆኑ በየደረጃው ያሉ የክልሉ

www.abyssinialaw.com

ፍ/ቤቶች ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0316061 መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የከተማው ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 16958/07 ግንቦት 29 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁ 1150/09 ሚያዝያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-18027 መጋቢት 21 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ሚያዝያ 08 ቀን 2010 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

**-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.145128

ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች:-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች:-

1. ወ/ሮ ኬሚያት ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር ቀረበ በ v.c ከሐረር
2. ወ/ሮ ፍርደውሳ ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር የቀረበ የለም

ተጠሪዎች:-

1. አቶ አንዋር ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር } የቀረበ የለም
2. ወ/ሪት መሊካ ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከልጅነት ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን አመልካቾቹ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 72/09 በ19/04/2009 ዓ.ም.የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17/2009 በ30/08/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው።

www.abyssinialaw.com

የአሁኖቹ ተጠሪዎች ከሌሎች ሶስት ተወላጆች ጋር በመሆን የሟች ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር ልጆች እና ወራሾች መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው በክርክር ላይ እያሉ ተጠሪዎቹ ልጆች መሆናቸውን አናውቅም በማለት የአሁኖቹ አመልካቾች በተቃዋሚነት መቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በማስረጃ ካጣራ በኃላ የሌሎቹን ተወላጆች ጥያቄ ተቀብሎ ውሳኔ ሲሰጥ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ግን ልጅነታቸው አልተረጋገጠም በሚል ጥያቄአቸውን ውድቅ ያደረገው መሆኑን፣በተጠሪዎቹ አቅርራቢነት ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር እንዲሁም የሟቹ ወንድሞች ናቸው የተባሉትን ሶስት ግለሰቦች አስቀርቦ በማጣሪያ ምስክርነት ከሰማ በኃላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ተጠሪዎቹ ከተለያዩ እናቶች በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ለጉዳዩ አግባብነት አለው ያለውን ሃይማኖታዊ ሕግ እና ድንጋጌ ጠቅሶ ተጠሪዎቹ የሟች ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር ልጆች እና መጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፣ይህንን ውሳኔ በመቃወም አመልካቾቹ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾቹ ያቀረቡት የዲ.ኤን.ኤ. ምርመራ ይደረግልን ጥያቄ በስር ሸሪዓ ፍርድ ቤት የመታለፉን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪዎቹ የሟች ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር ልጆች መሆናቸውን አናውቅም በማለት የአሁኖቹ አመልካቾች ከስር ጀምሮ የሚከራከሩ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ተጠሪዎቹ የሟቹ ልጆች እና ወራሾች ናቸው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የሟቹን ሶስት ወንደሞች በማጣሪያ ምስክርነት ከሰማ በኃላ 1ኛ ተጠሪ በሟች እና ወ/ሮ አሊያ ኑሬ በሚባሉ ሴት መካከል በነበረ ጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑ እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በሟች እና ወ/ሮ አሻ አብዶ በሚባሉ ሴት መካከል በነበረ ጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑ መረጋገጡን ገልጾ እና ለጉዳዩ አግባብነት አለው ያለውን ሃይማኖታዊ ሕግ በአስረጂነት በመጥቀስ

www.abyssinialaw.com

ነው፡፡እንደሚታወቀው የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስራቸውን የሚያከናውኑት በሸሪዓ ሕግ እና በሐገሪቱ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ መሰረት ስለመሆኑ የክልሉን ፍርድ ቤቶች እና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 3/1988 /እንደተሻሻለ/ በአንቀጽ 28 ስር ተመልክቷል፡፡ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን መርምሮ የማረም ስልጣን የሚኖረው በክርክር አመራር ረገድ ፍርድ ቤቶቹ የጣሱት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ መኖሩ ሲረጋገጥ እና ጥሰቱም መሰረታዊ የሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት አለው ያለውን የማጣሪያ ማስረጃ በመስማት እንዲሁም ለጉዳዩ አወሳሰን የሚረዱ የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር እና የአመልካቾቹን ተጨማሪ የመከላከያ ምስክሮች ጭምር ሰምቶ ሃይማኖታዊ ሕጉን መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በክርክር አመራር ስነ ስርዓታዊ ጉዳዮች ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ሃይማኖታዊ ሕጉን መሰረት በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ አስመልክቶ ደግሞ ይህ ችሎት ጉዳዩን ሊመረምር የሚችልበት አግባብ አይኖርም፡፡በአመልካቾቹ የቀረበውን የዲ.ኤን.ኤ. ምርመራ ይደረግልን ጥያቄ በማለፍ ተጠሪዎቹ በጋብቻ የተወለዱ መሆናቸውን በማስረጃ አጣርቶ በሃይማኖቱ ሕግ መሰረት የልጅነት እና የወራሽነት ውሳኔ መስጠቱም ፍርድ ቤቱ በክርክር አመራር ረገድ ጥሰት ፈጽሞአል የሚያሰኝ አይደለም፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 72/09 በ19/04/2009 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17/2009 በ30/08/2009 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ በመዝገብ ቁጥር 16506 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ21/11/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ቤ/ፍ

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ. 145053

ቀን፡- 24/9/2010ዓ.ም

ዳኞች፡- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዩ ካሳሁን

አመልካቾች፡- 1ኛ ወ/ሮ ስኳሬ ለገሰ

2ኛ ወ/ሮ ፋንቱ ተዘራ

3ኛ አቶ ፀጋዬ ወ/ተንሳይ — ቀረቡ፡፡

4ኛ ወ/ሮ ጥሩወርቅ አሰፋ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ዉሃና ፍሳሽ ባለስልጣን- የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

1. ጉዳዩ ዉዝፍ የዉሀ ፍጆታ ሂሳብ ለማስከፈል የቀረበ ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች እና በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑትን 1ኛ የአ/ከ/ክ/ከተማ ወረዳ 7 አስተዳደር ጽ/ቤት 2ኛ ወ/ሮ ሽቶ መሀመድ 3ኛ አቶ ጳዉሎስ አለማየሁ ተከሳሾች ነበሩ፡፡
2. የአሁኑ ተጠሪ ከቀረበዉ ክስ መረዳት የተቻለዉ የአሁኑ አመልካቾች እና በስር 6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች የነበሩትን ጨምሮ ከጥቅምት 2006 እስከ ጥር

2008ዓ/ም ድረስ የተጠቀሙበት ዉሀ ፍጆታ ብር 5895.55 ያልከፈሉ በመሆኑ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

3. አመልካቾች መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ጉዳይ የበኩላቸዉን የመከላከያ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍ/ቤቱ የሥረ ነገር ስልጣን የለዉም ያሉ ሲሆን በፍሬ ገዳዩም በተጠሪ ክስ የተጠቀሰዉ ሂሳብ የቤት ቁጥር 1180 ሳይሆን የቤት ቁጥር 797 ነዉ የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

4. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የሥር ፍ/ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉ በብይን ካለፈ በኃላ አመልካቾች አገልግሎት ያገኙ መሆኑ በማረጋገጡ ተጠሪ በክሱ የጠቀሰዉ ብር 5895.55 ይክፈሉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ይህ ዉሳኔ በመቃወም ለከተማዉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ አቤቱታ አቅርበዉ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ የክርክሩ መሰረታዊ ይዘት ዉል መነሻ ያደረገ በመሆኑ የከተማዉ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን የላቸዉም በማለት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሽሯል፡፡ በመቀጠል በሰበር ስልጣኑ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአዲስ አበባ ፍ/ቤቶች ስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ መሆኑን በመግለጽ የይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በድምጽ ብልጫ በመሻር የመ/ደ/ፍ/ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነዉ፡፡

5. አመልካቾች ሐምሌ 17 ቀን 2009ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ሥልጣን የሌላቸዉ መሆኑን ያሳያል ያሉትን ምክንያት በመዘርዘር ዉሳኔዉ እንዲሻር ጠይቋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት አጣሪ ችሎትም አመልካቾች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ የተደረገበት አግባብ ተጠሪ ባለበት ማጣራት ይቻል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀረበዉ ሲሆን ተጠሪም ጥቅምት 09 ቀን 2010ዓ.ም ባቀረበዉ መልስ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

6. የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ይዘት ያለዉ ሲሆን እኛም በስር የከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡
7. እንደመረመርነዉም በስር ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ከቀረበዉ ክስ መገንዘብ የተቻለዉ የአሁኑ አመልካቾች የተጠቀሙበትን የዉሃ ፍጆታ እንዲከፍሉ የሚጠይቅ ነዉ፡፡ የክሱ መሰረታዊ ይዘት ዉል መነሻ ያደረገ ክርክር ነዉ፡፡ የከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ለመሻር መነሻ ያደረገዉ ክርክሩ በሁለት የከተማዉ አስተዳደራዊ ተቋማት የተነሳ ከሚል እሳቤ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነዉ የአሁኑ አመልካቾች በስር 1ኛ ተከሳሽ ከነበረዉ ቤት የተከራዩ መሆኑ እንዲሁም ከአሁኑ ተጠሪ የዉሃ አገልግሎት የሚያገኙ ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ በዉሉ መሰረት የዉሃ ፍጆታ ሂሳብ እንዲከፈለዉ ነዉ፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የዉሃ አገልግሎት መስጠቱ አመልካቾች ደግሞ ተጠቃሚዎች ከመሆናቸዉ አንፃር የተገለገሉበት ሂሳብ የመክፈል ግዴታ ያላቸዉ መሆኑን ተጠቅሶ የቀረበዉ ክርክር መነሻዉ ዉል እንጂ የሁለት ተቋማት ክርክር ስለመሆኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዉሳኔዉ እንደገለፀዉ ክርክሩ ዉል መነሻ ያደረገ ያልተከፈለ ገንዘብ ለማስከፈል የቀረበ ክስ ከመሆኑ አንፃር የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ያላቸዉ ስለመሆኑ የሚሳይ አንዳችም የህግ መሰረት ያለዉ ክርክር አልቀረበም፡፡ በሌላ በኩል የከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሠ) የተረጎመበት አግባብ የድንጋጌዉ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያልተከተለ ነዉ፡፡ የስረ ነገር ስልጣን ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በራሱ ጊዜ የሚያነሳ ስለመሆኑም የፍ/ሕ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 9(2) እና 231 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡ በመሆኑም የከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ ዉል መነሻ ያደረገ መሆኑን መገንዘብ እየተገባዉ ጉዳዩ በከተማዉ ፍ/ቤቶች የሚታይ ነዉ በማለት የደረሰበት መደምደሚያ አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 ያላገናዘበ ነዉ ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 26796 ሰኔ 29 ቀን 2009ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 26581 በ 12/08/2009ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የዉል ጉዳይ የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የላቸዉም በማለት ወስነናል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 26581 በ 12/08/2009ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 144613

**ቀን** - 30/09/2010

**ዳኞች**፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

**አመልካቾች**፡-1.አቶ ያሲን ኢብራሂም ቀርበዋል

2.አቶ ጌቱ እሸቱ ቀርበዋል

**ተጠሪ**፡- አቶ ኃይሉ ታዬ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት መስተዳደር በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልክቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአጭሩ በጉንዶ መስቀል ከተማ ቀበሌ 02 ዉስጥ ያለኝን 200 ካ/ሜትር መሬት ተከሳሾች ያላግባብ የያዙብኝ በመሆኑ ይህኑን መሬት እንዲለቁ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካቾች በበኩላቸዉ ከሳሽ በቦታዉ ላይ የነበራቸዉን መብት በ1995 ዓ.ም ለእህቱ አሰገደች ታዬ መስጠቱን እና አሰገደች ይዞታዉን ለሌላ ሰዉ በሽያጭ ዉል ካስተላለፉላቸዉ ሰዉ ገዝተዉ የያዙት እንጂ የከሳሽ አለመሆኑን ገልፀዉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ከግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ፣ አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን

ቦታ በህገ ወጥ መንገድ የያዙ መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ በላዩ ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰዉ ይዞታዉን ለተጠሪ እንዲለቁ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎት መዝገቡን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በሚል ተጠሪ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የፍሬ ነገር ክርክሩን በተመለከተ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በትዕዛዝ የፀናዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 04/11/09 ዓ.ም በጠበቃቸዉ አማካይነት ተዘጋጅቶ በቀረበ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ነዉ፡፡ ይህ ችሎትም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ ተቀብሎ የማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ስልጣን ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 25/88፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን በሚደነግገዉ አንቀጽ 5(2) ስር፣ መደበኛ ነዋሪነታቸዉ በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰበር ስልጣን የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ የክልል ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3-ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶችን ስልጣን ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 141/2000 ሲሆን፣ የዚህ አዋጅ

አንቀጽ 26(1-ሠ) የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የዳኝነት ስልጣን የክልል ጉዳዮችን በተመለከተ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ የተገደበ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ባላቸዉ የዉክልና ስልጣን መሠረት የፌዴራል ጉዳዮችን አይተዉ የሚሰጧቸዉ የመጨረሻ ዉሳኔዎችን ተቀብሎ ለማየት ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት የአመልካቾች አድራሻ በኦሮሚያ ክልል ደራ ወረዳ ጉንዶ መስቀል ከተማ ቀበሌ 02 ሲሆን፣ የተጠሪ አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 06 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ መሆኑን ነዉ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለዉ ለማለት ሁለት ምክንያቶችን የጠቀሰ ሲሆን፣ የመጀመሪያዉ ምክንያት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 መሠረት አዲስ አበባ ክልል አይደለም የሚል ነዉ፡፡ በእኛ በኩል እንደተመለከትንዉ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 የፌዴሬሽኑ አባላት የሆኑትን ዘጠኙን ክልሎች በመዘርዘር በአንቀጽ 50(4) ሁሉም ክልሎች የራሳቸዉ አስተዳደር እንደሚኖራቸዉ ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በአንቀጽ 49 (2) ስር አዲስ አበባ ከተማ ራሱን በእራሱ የማስተዳደር ሙሉ ስልጣን እንዳለዉ እና ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 87/89 እንዲሁም ይህን አዋጅ አሻሽሎ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 361/95 መሠረት አዲስ አበባ ከተማ ራሱን በእራሱ በማስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ ኦሮሚያ እና አዲስ አበባ የየራሳቸዉ የሆነ የአስተዳደር ስልጣን ክልል ያላቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2) ስር "በተለያዩ ክልሎች" በሚል የተመለከተዉም በተለያዩ የአስተዳደር ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ለማለት እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ በመሆኑም የዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስልጣን ክልል ዉስጥ የሚኖሩትን አያጠቃልልም ሊባል የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የጠቀሰዉ ሁለተኛዉ ምክንያት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ንብረት የሚገኘዉ በኦሮሚያ ክልል ዉስጥ እና ዉሉም የተደረገዉ በኦሮሚያ ክልል

www.abyssinialaw.com

ዉስጥ መሆኑን ነዉ፡፡ በመሠረቱ ንብረቱ የሚገኝበትን ወይም ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታ ግምት ዉስጥ በማስገባት የሚወሰነዉ የአካባቢ ስልጣን እንጂ የስረ ነገር ስልጣን አለመሆኑን ከፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 24 እና 25 ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ መሆናቸዉ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ዉል ወይም ንብረቱ የሚገኘዉ በክልሉ ዉስጥ መሆኑ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑን አያስቀርም፡፡ ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሆኖ ግን የአካባቢ ስልጣኑ በክልሎች ስር የሚወድቅ ሲሆን፣ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2) እና 80(4) መሠረት፣ እንደነገሩ ሁኔታ፣ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉክልና ጉዳዩን የማየት ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ንብረት እንዲሁም ዉሉ የተደረገዉ በኦሮሚያ ደራ ወረዳ ጉንዶ መስቀል ከተማ 02 ቀበሌ መሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በዉክልና ለማየት ስልጣን ባለዉ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ የማድረግ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል ቢሆንም የስረ ነገር ስልጣኑን የፌዴራል ከመሆን አያስቀርም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የጠቀሰዉ ምክንያት የህግ መሠረት ያለዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ የአስተዳደር ክልል ዉስጥ የሚኖሩ መሆናቸዉ ተረጋግጦ እያለ እና በዚህም ምክንያት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሆኖ እያለ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በህግ ተቀባይነት የሌላቸዉን ምክንያቶች በመጥቀስ ጉዳዩን ተቀብሎ በማከራከር የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/263017 በቀን 19/10/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ ተቀብሎ ለማየት ስልጣን የለዉም ብለናል፡፡
3. አመልካቾች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸዉ በህግ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ለማቅረብ ያላቸዉን መብት ይህ ዉሳኔ አያስቀርም፡፡
4. ይህ ችሎት በቀን 26/01/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዕግድ ተነስቷል፡፡
5. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/አ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.157560

መጋቢት 23 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች:- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካቾች: - 1ኛ. ወ/ሮ አለምሸዋ አባተ አበበ

2ኛ. ወ/ሮ ስንታየሁ አበራ መኮንን | ጠበቃ መታሰቢያ ሐይልዬ ቀረቡ

3ኛ. አቶ አንተነህ አበራ መኮንን

4ኛ. አቶ በሐይሉ አበራ መኮንን

ተጠሪዎች: - 1ኛ. አቶ ሚሊዮን አባተ አበበ | 1ኛ ተጠሪ በራሳቸውና ስለ 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ፍሬህይወት ፀጋ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15897 ህዳር 15 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 04236 መጋቢት 11 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት በመሻር ባሳለፈው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ በመሆኑ ጉዳዩ በዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታይቶ በክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ የተፈፀመው ስህተት ይታረምልን በማለት አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በሐረር ከተማ ቀበሌ 09 ውስጥ የሚገኘውንና በይዞታችን

ባቆየነው ቦታ ላይ የሰራነውን ግምቱ ብር 60000.00 (ስድሳ ሽህ) የሆነ ሶስት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ተጠሪዎችን አስጠግተናቸው እንደ ኪራይ የሚታሰብ ብር 500.00 (አምስት መቶ) እየከፈሉ ይኖሩበት ነበር፤ ይሁን እንጂ በይዞታችን ላይ በገንዘባችን የሰራነውን ይህን ሶስት ክፍል ቤት ስመ ሃብት ወደራሳቸው ለማዞር እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆኑን ስለደረስንባቸው ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የበኩላቸውን መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አከራካሪውን ቤት አመልካቾች በራሳቸው ይዞታ በህጋዊ የግንባታ ፈቃድ መሰረት የሰሩት ስለመሆኑ በሰውና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች በቤቱና ቤቱ በተሰራበት ይዞታ ላይ ምንም ዓይነት መብት የላቸውም በማለት ተጠሪዎች ቤቱን ለቀው ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ባለስልጣን ተጣርቶ እንዲቀርብ ካደረገና የግራቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ክርክር ያስነሳው ቤትና ቦታ ከአሁን አመልካቾች ህጋዊ ይዞታ ውጪ በመሆኑና ይኸው ቦታም በመንግስት ይዞታነት ሥር ያለ በመሆኑ አመልካቾች በህጋዊ መንገድ ካርታ ተሰጥተውበት ካለው ይዞታ ውጪ በሆነ የመንግስት ይዞታ ላይ በጨረቃ ቤትነት ተገንብቶ ባለው ሰነድ አልባ ቤት ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታው በቀጥታ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ሚያዚያ 26 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ማመልከቻ የሐረሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ሰኔ 21/2010 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ውሳኔው በህጉ አግባብ የተሰጠ ነው

www.abyssinialaw.com

ተብሎ እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡አመልካቾችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡም ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ እንደመረመርነው ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ነው የሚባልበት ምክንያት የሌለ ሲሆን የክልል ጉዳይ መሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ያለው መሆኑም ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የተያዘው ጉዳይ በክልሉ ሰበር ችሎት ሳይታይ በቀጥታ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳዮች በሰጠው ትርጉም ምክንያት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስቀድሞ ያሳለፋቸው ገዥ ትርጉሞች በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት በድጋሚ ሊታዩ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 111887 ሚያዚያ 25/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የሰበር ችሎት በህግ አግባብ ሳይቋቋም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በሰበር አቤቱታ ስርዓት ሊያስተናግዱ የሚችሉበት አግባብ ሊኖር እንደማይችል፤ በሐረሪ ክልል የሰበር ስርዓት በዝርዝር ህጎች በግልጽ ያልተቀመጠና ያለው አሰራርም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያለመኖሩን የሚያስገነዝብ በመሆኑ፤ በውስን ጉዳዮች ላይ ብቻ በክልሉ ሰበር ችሎት ተቋቁሟል እየተባለ የሰበር ስርዓት ተግባራዊ የሚሆንበት አግባብ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ በመሻር የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ወገን አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚገባው በቀጥታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው በማለት ወስኗል፡፡ በተመሳሳይም በሰ/መ/ቁ 120858 ህዳር 8/2009 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ በሐረሪ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያልተቋቋመ መሆኑን፤ በሐረሪ ክልል የሰበር ስርዓት በዝርዝር ህጎች ያልተቀመጠና ያለው አሰራርም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያለመኖሩን የሚያስገነዝብ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ መወሰኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ጉዳዩ ሊቀርብ የሚገባው በቀጥታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስለመሆኑ ተወስኗል፡፡ በነዚህና በመሰል መዛግብት በተሰጠው

www.abyssinialaw.com

አስገዳጅ ትርጉም ምክንያት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዮችን በሰበር ማየቱን እንዳቆመ ተገንዝበናል፡፡ በተያዘው ጉዳይም የሰበር አቤቱታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሳይቀርብ በቀጥታ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ስለ ፍርድ ቤቶች ጣምራነት እና ስልጣን በሚደነግገው የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ሥር እንደተመለከተው የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንደሚኖረውና ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ የሐረሪ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 70(2)(ሀ) በማንኛውም የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የማየት ሥልጣን እንዳለውና ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡

በዚህ መልኩ በህገመንግስታቱ የተቋቋመው እና ሥልጣኑ የተለየውን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተመለከቱ ዝርዝር ህጎች መውጣታቸውን ከክልሉ ፍርድ ቤቶች የማቋቋሚያ አዋጆችና ማሻሻያቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 ምዕራፍ ሁለት ስለመደበኛ ፍርድ ቤቶች መቋቋምና ስለዳኝነት ስልጣናቸው የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 3(1) ሥር የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቋቋሙ ተመልክቷል፡፡ የችሎቶቹን አሰራር በሚደነግገው አንቀጽ 7(1) ሥር ደግሞ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ችሎቶች እንደሚኖራቸው ተመልክቷል፡፡ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የሚዘረዝረው የአዋጁ አንቀጽ 15 በንዑስ ቁጥር 3 ስር ደግሞ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠን የመጨረሻ ፍርድ ወይም ውሳኔ በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ከዚህም በቀር የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 እና ማሻሻያ አዋጆች ቁጥር 8/1991 እና 17/1991 እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1999 ማሻሻያ ካደረገባቸው ጉዳዮች አንዱ የክልሉን ሰበር ችሎት የተመለከተ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በቀዳሚው አዋጅ ቁጥር 3/1988 አንቀጽ 15(3) የተመለከተው ተሰርዞ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

"መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠን የመጨረሻ ፍርድ ወይም ውሳኔ በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡ የሰበር አቤቱታ አቀራረብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት እና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነስርዓት ስለ ይግባኝ አቀራረብ በተደነገጉት መሰረት ነው" በሚል ተተክቷል፡፡

ከፍሲል የተጠቀሱት የፌዴራሉም ሆነ የክልሉ ህገመንግስቶች እንዲሁም የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ እና ማሻሻዎች ሁሉ የክልሉ ሰበር ችሎት መቋቋሙን፤ የሰበር ችሎቱን ሥልጣን እና ለሰበር ችሎቱ አቤቱታ የሚቀርብበትን ስርዓት ሁሉ በህግ መደንገጉን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ የሰበር ችሎቱን ዝርዝር አደረጃጀትና አሰራር ሥርዓት መደንገጉ ለክልሉ ህግ አውጭ አካል የተተወ በመሆኑ በዚህ መልኩ ዝርዝር ህጎች እንዲወጡ ማድረግ ተገቢ ሲሆን እስካሁን በክልሉ ህግ አውጭ አካል በወጡት አዋጆ መሰረት የክልሉ ሰበር ችሎት በአግባቡ ተደራጅቶ አገልግሎት የማይሰጥበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ሥራ ላይ ባሉት ህጎች አግባብ ችሎቱ እንዲደራጅና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግም ከፍርድ ቤቱ ኃላፊዎች የሚጠበቅ ነው፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ ሥራ ላይ ባሉት ህጎች መሰረት በክልሉ ሰበር ችሎት ታይተው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ሲቀርብ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አልተቋቋመም፤ እንዲሁም በክልሉ የሰበር ስርዓት በዝርዝር ህጎች አልተቀመጠም በማለት ውድቅ መደረጉና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ እንዳይወሰን መደረጉ፤ እንዲሁም ጉዳዩች ሊቀርቡ የሚገባው በቀጥታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስለመሆኑ የተሰጠው ትርጉም ከፍሲል የተጠቀሰውን የህገመንግስቱንና የፍርድ ቤቱን ማቋቋሚያ አዋጆች የተከተለ ባለመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው ትርጉም ሊለወጥ ይገባል ብለናል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት ቀደም ሲል በዚህ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 111887 ሚያዚያ 25/2008 ዓ.ም፤ በሰ/መ/ቁ 120858 ህዳር 8/2009 ዓ.ም እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ መዛግብት ሰጥቶት የነበረውን ትርጉም ለውጠናል፡፡ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ገዥ ይሆናል ብለናል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ ምክንያት አመልካቾች የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ባሳለፈው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ በመሆኑ በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ በቅድሚያ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊያቀርቡ ይገባል በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በዚህ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 111887 ሚያዚያ 25/2008 ዓ.ም፤ በሰ/መ/ቁ 120858 ህዳር 8/2009 ዓ.ም እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ መዛግብት ሰጥቶት የነበረው ትርጉም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት ከላይ በፍርዱ በተመለከተው መሰረት ለውጠናል፡፡
2. አመልካቾች የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ባሳለፈው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ በመሆኑ በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊስተናገድና ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ነው ብለናል፡፡
3. መስከረም 7/2011 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ብ/ግ

www.abyssinialaw.com

# አፈፃፀም

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር--156758
ቀን-ሕዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** የአብክመ ገቢዎች ባለስልጣን ዐ/ሕግ

**ተጠሪ፡-** አቶ መስፍን ጥላሁን

ይህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ አቶ በላይ አካለ ከሚከራከሩበት የሰ/መ/ቁ 156757 ጋር ከአንድ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ የተነሱ ጉዳዮች በመሆናቸዉ መዝገቦቹ ተጣምረዉ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአፈጻጸም ጉዳይ ሆኖ የተጀመረዉ በአማራ ክልል በባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፤ አቶ ነጋሹ ዉዱ እና ሻ/ል ክ/ጎርጊስ ዘነበ የፍርድ ባለዕዳዎች፤ አቶ በላይ አካለ የጨረታ አሸናፊ ሲሆኑ የአሁኑ አመልካች ደግሞ የመቃወም አመልካች ነበር፡፡ አመልካች ያቀረበዉ መቃወሚያ ይዘት፡- በፍርድ ባለዕዳዎች ስም የሚገኘዉ የድንጋይ ወፍጮ ወይም ክሬሸር የፍርድ ባለዕዳዎች ባልከፈሉት የግብር ዕዳ ብር 2,324,972.07 ምክንያት በደብዳቤ ቁጥር ገቢ 1214/01/06 መጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም እና በቁጥር ዘል/ቀመ/2801/06 በቀን 23/07/06 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 78(2) ለአመልካች በተሰጠዉ ስልጣን ዕግድ ተሰጥቶበት እያለ ወፍጮዉ የሚገኝበት ዘንዘልማ ቀበሌ ሆኖ ሳለ ተጠሪ ፍ/ቤቱን በማሳሳት ንብረቱ ለማይገኝበት ለሕዳር 11 ቀበሌ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ መደረጉ ሆን ተብሎ በመሆኑ ጨረታዉ ተሰርዞ ንብረቱን እንድንረከብ፤ ንብረቱ የድንጋይ ወፍጮ

www.abyssinialaw.com

እንደመሆኑ የሽያጭ ጨረታዉም ሆነ የዕግድ ትዕዛዙ በግልጽ ማስታወቂያ ለሕዝብ ይፋ ያልተደረገና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 414(2) እና 425(2) ድንጋጌዎችን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ጨረታዉ ተሠርዞ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 81(1) መሰረት አመልካች የቀደምትነት መብት ያለዉ በመሆኑ ንብረቱን እንድንረከብ ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 መሰረት ጨረታ እንዲፈርስ ጥያቄ መቅረብ የሚችለዉ በአሻሻጡ ስርዓት ላይ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ ሲሆን ይህ ባልሆነበት የቀረበዉ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፡፡ አቤቱታዉ መቅረብ የነበረበት ንብረቱ በጨረታ ከመሸጡና ለሦስተኛ ወገን ከመተላለፉ በፊት ሆኖ ሳለ ከተሸጠ በኃላ የቀረበዉ አቤቱታ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 ድንጋጌ አንጻር ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የጨረታዉ አሸናፊ በበኩሉ ጨረታዉን በሕጋዊ መንገድ ተወዳድሬ አሸንፌ የጨረታዉ ዉጤት ቀርቦ በችሎት ጨረታዉ ጸድቆ ገንዘቡን በሙሉ ለፍርድ ባለመብት ከፍዬ የድንጋይ ወፍጮዉን እንድረከብ ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡ ይህ በሆነበት ጨረታዉ እንዲሰረዝ የቀረበዉ አቤቱታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 እና 445 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ ዉድቅ ይደረግልኝ የሚል ነዉ፡፡

የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር መርምሮ የድንጋይ ወፍጮ ወይም ክረሸሩ ከአለበት ቦታ ተነቅሎ ገቹዉ አካል ወደ ፈለገበት ቦታ ሊወሰድ የሚችል በመሆኑ የሚንቀሳቀስ ንብረት ነዉ፤ አመልካች አቤቱታዉን ያቀረቡት ንብረቱ በጨረታ ከተሸጠ በኃላ በመሆኑና ንብረቱ የሚገኝበትን የዘንዘልማ ቀበሌን በበላይነት የሚያስተዳድረዉ የሕዳር 11 ክፍለ ከተማ በመሆኑ የጨረታዉ አካሄድ ተገቢ በመሆኑ ጨረታዉ ሊፈርስ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ክረሸሩ በመሬት ላይ የተተከለ በመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት መሆኑን፤ ይህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 424(2) እና 454(2) መሰረት የጨረታዉ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከ30 ቀን ባላነሰ ጊዜ ሊነገር የሚገባዉ መሆኑን በመግለጽ ጨረታዉ

www.abyssinialaw.com

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 መሰረት ጉድለት ያለበት በመሆኑ ጨረታዉ ፈራሽ ነዉ፤ ክሬሸሩ የድንጋይ ወፍጮ መቼና በማን እንደተከበረ፣ ማን ምን ያህል ባለገንዘብ ነዉ የሚሉትን አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሠኘት ተጠሪ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የተመለከተዉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ክሬሽር የድንጋይ ወፍጮ የመኪና ዓይነት በመሆኑ ተንቀሳቃሽ ንብረት እንጂ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለመሆኑ ለ15 ቀናት የጨረታ ማስታወቂያ አየር ላይ እንዲቆይ ተደርጎ የተሸጠና የፍ/ብ/ስ/ሥ/ሕ/ቁ 426 ድንጋጌን ያሟላ በመሆኑ ጨረታዉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ በመሻር እና የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የድንጋይ ወፍጮዉ ተተክሎ የሚሠራዉና የሚገኘዉ በዘንዘልማ ቀበሌ ሆኖ እያለ እና ይህ ንብረትም አስቀድሞ በግብር ዕዳ ተከብሮ እያለ ተጠሪ ፍ/ቤቱን በማሳሳት ንብረት የማይገኝበትና ገቢ ተቋሙ ሊያዉቅ በማይችልበት ሕዳር 11 ቀበሌ ጨረታ እንዲወጣ በማድረግ ጨረታዉን እንዲከናወን ያደረጉ መሆኑ እየታወቀ ሁለቱ ቀበሌዎች ራሳቸዉን የቻሉ ቀበሌዎች ሆነዉ እያለ በአንድ ቀበሌ ሥር እንዳሉ ተደርጎ ጨረታዉ ሊፈርስ አይገባም ያለበት አግባብ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም፡፡ ክሬሸሩ ከመሬት ተተክሎ የሚሠራ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሆኖ እያለ እንደሚንቀሳቀስ ንብረት ይቆጠራል ተብሎ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ጨረታዉ ሕግን ያልተከተለ በመሆኑ ጨረታዉ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት አከራካሪዉን ክሬሽር ወፍጮ አስመልክቶ የቅድሚያ መብት አለኝ ሲል ያቀረበዉ መቃወሚያ ጉዳዩ በጨረታ ተሸጦ የተፈጸመ ነዉ ተብሎ ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት የአፈጻጸም ንብረት የመሸጥ ስነ ስርዓት መጠበቁንና የተሸጠዉ ንብረትስ የሚንቀሳቀስ ነዉ ወይስ የማይንቀሳቀስ ነዉ የሚለዉን ነጥብ በመለየት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 424-426 እና 445 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልሰ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ የሰጡት መልስ ይዘት፡- ክሬሸር የድንጋይ ወፍጮ ድንጋይ በሚገኝበት ቦታ እየተዘዋወረ የሚሠራ ነዉ፡፡ ወፍጮዉም ለሥራዉ ሲባል ከመሬቱ ጋር የተያያዘ ቢሆንም ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር ወፍጮዉ ሳይጠፋ እና አጉል ሳይሆን ምንም ብልሽት ሳይደርስበት ከመሬት ለመለያየት የሚችል ማሽን በመሆኑ ተንቀሳቃሽ ንብረት እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1132(2) መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ የሚባል አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል የድንጋይ ወፍጮዉ በሞተር የሚሠራ በመሆኑ እንደመኪና እና የኮንስትራክሽን ማሽኖች ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ምዝገባ የሚያስፈልገዉ ቢሆንም ጨረታዉ ሲሸጥ በተንቀሳቃሽ ንብረት ጨረታ ስርዓት የሚከናወን ነዉ፡፡ ወፍጮዉ የሚገኘዉ ባሕርዳር ከተማ ሕዳር 11 ክ/ከተማ በመሆኑ ለሕዳር 11 ቀበሌ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ታዛቢ ፖሊስ ባለበት ጨረታዉ የተካሄደ በመሆኑ ስህተት የለዉም፡፡ ቀበሌዉ ትዕዛዙ ሲደርሰዉ ንብረቱ በክልል ስር አይገኝም በማለት አላስፈጽምም አለማለቱ ንብረቱ በክልሉ ስር የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም በጨረታዉ የተሸጠዉ ንብረት የሚገኝበትን ቦታ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚለዉ ጉልህ የሆነ የማታለል ወይም የማታለል ተግባር መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 መሰረት ጨረታዉን ሊፈርስ የሚያስችል ምክንያት አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

በመዝገብ ቁጥር 156757 አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታም ሆነ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ለማጣራት የተያዘዉ ነጥብ ተመሳሳይ ሲሆን የጨረታዉ አሸናፊ ነዉ የተባሉትና በዚህ መዝገብ ተጠሪ የሆኑት አቶ በላይ አካል የሰጡት መልስ የድንጋይ ወፍጮዉ ራሱን ችሎ ከመሬቱ ጋር ተለያይቶ አገልግሎት መስጠት የሚችልና ከመሬቱ ጋርም ሲለያይ አጉል የማይሆንና የማይጠፋ መሆኑን አረጋግጦ የክልሉ ሰበር ሰሚ የሰጠዉ ዉሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1132(2) ድንጋጌን ያገናዘበ ነዉ፡፡ አመልካች በቅድሚያ መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለዉ ከሚሸጠዉ ንብረት ላይ ገንዘቡን በማግኘት ወይም ንብረቱን ቀድሞ በመሸጥ እንጂ ንብረቱ ተሸጦ ለሌሎች ባለመብቶች ከተሰጠ በኃላ የቅድሚያ መብቱን የጨረታ ማፍረሻ ምክንያት ሊያደርገዉ አይችልም፡፡ ዘንዘልማ ቀበሌ በሕዳር 11 ክፍለ ከተማ ዉስጥ ያለ በመሆኑ አመልካች እንደሚሉት በማጭበርበር የተሠራ ሳይሆን አመልካች ራሳቸዉ ዕግዱን ለሚመለከተዉ አካል አለማድረሳቸዉን

www.abyssinialaw.com

የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነዉ ክርክር ያስነሳዉ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሆነዉ የድንጋይ ወፍጮ ወይም ክረሸር የፍርድ ባለመብትን ገንዘብ ለማስከፈል ተብሎ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊዉ ከተለየና ገንዘቡን ከከፈለ በኃላ ገንዘቡ ለፍርድ ባለመብቶች ተከፍሎ ገዥዉ ንብረቱን እንዲረከብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ርክክቡ ከመፈጸሙ በፊት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረበዉ አቤቱታ የቅድሚያ መብት ያለዉና ንብረቱን ከዚህ በፊት ያሳገደዉ መሆኑን እንዲሁም የጨረታ ሽያጩ አፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ ማስታወቂያ ያልተነገረና ጉድለት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ጨረታዉ ይፍረስ የሚል ነዉ፡፡ በተለይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጨረታዉ ጉድለት የለበትም ለማለት የሰጠዉ ምክንያት ክርክር ያስነሳዉ ንብረት ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑና የሀራጅ ጨረታ ማስታወቂያዉ ተለጥፎ 15 ቀናት የቆየ በመሆኑ ጨረታዉ ጉድለት የሌለበት በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ከዚህ አንጻር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ያስነሳዉ ክሬሸር ወይም የድንጋይ ወፍጮ የሚንቀሳቀስ ንብረት ነዉ በሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ የጨረታ ሽያጩ ጉድለት የለዉም ማለቱ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? እንዲሁም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ንብረቱን አስቀድሞ ማሳገዱንና በሕግ የቅድሚያ መብት ያለዉ መሆኑን በመግለጽ ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚሉ ነጥቦች የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ አብይ ጭብጦች ናቸዉ፡፡

ክርክር ያስነሳዉ የድንጋይ ወፍጮ ወይም ክሬሸር የተሸጠበት የጨረታ ሂደት ጉድለት አለበት ወይስ የለበትም የሚለዉን ለመመለስ በቅድሚያ ንብረቱ የሚንቀሳቀስ ንብረት ነዉ ወይስ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ የሚለዉ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባዉ ነዉ፡፡ በመሠረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1130 እና 1132 መሠረት የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የሚባሉት መሬትና ቤት ወይም ከእነዚህ ነገሮች ጋር በግዙፍነት የተያያዘ ሆኖ የተባለዉ ነገር

www.abyssinialaw.com

ሳይጠፋና አጉል ሳይሆን ለመለያየት የማይቻል ሲሆን መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህና በሌሎች ድንጋጌዎች ከተቀመጡት ዉጭ ያሉ ንብረቶች ተንቀሳቃሽ ንብረቶች መሆናቸዉ አሻሚ አይደለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ክርክር ያስነሳዉ ክሬሸር ወይም የድንጋይ ወፍጮ ግብዓት ባለበት ቦታ እየተንቀሳቀሰና እየተተከለ ድንጋይ የሚፈጭ ሲሆን ከሚፈጨዉ የድንጋይ ቦታ ጋር ሳይነጣጠል ተተክሎ ካለበት ቦታ ወይም ጥሬ ዕቃ የመጠቀም መብት ጋር ካልተሸጠ በቀር ራሱን ችሎ እስከተሸጠ ድረስ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም ክሬሸሩ ከተተከለበት የድንጋይ ማዉጫ ቦታ የመጠቀም መብት ጋር የተሸጠ መሆኑን የሚገልጽ ነገር በሌለበት ሁኔታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ ሊባል የሚችል ባለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ተንቀሳቃሽ ንብረት ነዉ መባሉ ስህተት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ስለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር በወጣ አዋጅ ቁጥር 177/91 እና በአዋጁ መሠረት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ቁጥጥርና ምዝገባ እንዲሁም የባለቤትነት ደብተር አሰጣጥ አስመልክቶ በወጣዉ መመሪያ አንቀጽ 3(1/ለ) መሰረት ክሬሸር እንደአስፓልት ሚክሲንግ ፕላንትና ክሬን ሁሉ ከቦታ ወደ ቦታ እየተወሰደና እየተተከለ የሚሠራ ምዝገባና የባለቤትነት ደብተር የሚሰጠዉ ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት መሆኑ ተመላክቷል፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 3(2) መሰረት ከምዝገባና ቁጥጥሩ ዓላማዎች ዉስጥ አንዱ መሳሪያዎቹ ለዋስትናና መያዣና ለተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚዉልበትን ሁኔታ ማመቻቸት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከተጠቀሱት የአዋጁና የመመሪያዉ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ክሬሸር ወደ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ ወይም እንዳይሸጥ የሚታገደዉ ክሬሸሩ ለሚገኝበት ቀበሌ ወይም የአስተዳደር አካል ደብዳቤ በመጻፍ ሳይሆን ክሬሸሩን ለሚመዘግበዉና የስም ዝዉዉር በማድረግ የባለቤትነት ደብተር ከሚሰጠዉ አካል ዘንድ ዕገዳዉ እንዲመዘገብ በማድረግ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ክሬሸሩ ለሚገኝበት ቀበሌ ደብዳቤ በመጻፉ ብቻ ንብረቱ በሕግ ፊት የጸናና ንብረቱ ወደ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የሚያግድ ዕግድ ነበረበት ለማለት አይቻልም፡፡

www.abyssinialaw.com

ከላይ ከተገለጸዉ አንጻር የድንጋይ ወፍጮዉ ወይም ክሬሸሩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሳይሆን ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት ነዉ የተባለ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 426 መሠረት የጨረታዉ ማስታወቂያዉ ተለጥፎ ለ15 ቀናት የቆየ መሆኑ በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ የጨረታዉ ሂደት ጉድለት አለበት ሊባል የሚችል አልሆነም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ያቀረበዉ ንብረቱ በሀራጅ ጨረታ ከተሸጠና ገንዘቡም ለፍርድ ባለገንዘቦች ከተከፈለ በኋላ የቀረበ በመሆኑ አመልካች በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 78(2) መሠረት ያለዉን የቀዳሚነት መብት ሊጠቀም አይችልም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ መወሰኑ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በተገለጸዉ አግባብ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት የመቃወም አቤቱታዉን ያቀረበዉ ክርክር ያስነሳዉ ክሬሸር በጨረታ ከተሸጠና ገንዘቡም ለፍርድ ባለገንዘብ ከተከፈለ በኋላ በመሆኑ፤ በጨረታዉ ሂደትም ጨረታዉን ሊያስፈርስ የሚችል ጉድለት ባለመገኘቱ እንዲሁም ንብረቱ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የተሰጠ ዕግድ በሕግ አግባብ ያልተመዘገበ በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 03-61518 ጥር 28 ቀን 2010 ዓ.ም እና 03-61481 የካቲት 02 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጣቸዉ ዉሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ከተወሰነዉ የሰ/መ/ቁ 156757 ጋር ይያያዝ ተብሏል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር---152339

መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ እድገት ፎጊ - ጠበቃ መሐመድ ሲራጅ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ም/ኢ/ር አሻግሬ ወ/ማሪያም - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው አፈጻጸምን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል በየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል የነበረዉ ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ የነበራቸዉ ቤት ግምቱ ብር 53,000 ሆኖ ከቀረበ በኃላ ተጠሪ ብር 2000 ጨምሮ በብር 55,000 ለማስቀረት የጠየቀ ሲሆን አመልካች በበኩላቸዉ በብር 60,000 ለማስቀረት ጠይቀዉ ሁለቱም ገንዘብ ለማምጣት በሚል ሄደዉ ተጠሪ ገንዘብ ይዞ ቢመለስም አመልካች ሳይቀርቡ ቀርተዋል፡፡ ሀራጅ ጨረታ ወጥቶ በሁለተኛዉ ጨረታ መ/ር አብነት ወልዴ በብር 54,184 ብር ያሸነፈ ሲሆን ተጠሪ አመልካች ከፍዬ አስቀራለሁ ባሉት መሠረት ድርሻዉን ብር 30,000 በአንድ ጊዜ ከፍለዉ የሚያስቀሩ ቢሆን የማይቃወም መሆኑን የገለጸ ሲሆን አመልካች

ብር 12,000 ይዘዉ መቅረባቸዉንና ልጆች ስላሏቸዉ ቀሪዉን ለመክፈል ጊዜ እንዲሰጣቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙ ያቀረቡት የቅድሚያ ግዥ መብት የሕግ ድጋፍ የለዉም በማለት የጨረታ አሸናፊ የሆነዉ መ/ር አብነት ወልዴ ብር 54,184 ከፍሎ ቤቱን እንዲረከብ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ቅር ተሰኝተዉ ቅሬታ በየደረጃዉ ላሉ ፍ/ቤቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ዉሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ነው፡፡
አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በወረዳዉ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ማዘጋጃ ቤት መጋቢት 04 ቀን 2006 ዓ.ም በባለሙያ ገምቶ ያቀረበዉ ግምት 38,000 ሲሆን በቀጠሮ ከተጠሪ ድርሻ ዉስጥ 12,000 ይዤ ብቀርብም ተጠሪ ሳይቀርብና እንደፍርዱ እንዲፈጸምለት ሳይጠይቅ ከሰባት ዓመት በኃላ እንሰትና የጓሮ አትክልት አልምቼበት እያለሁ በ2010 ዓ.ም እኔ ባላወቅኩበት ሁኔታ ብር 53,000 ነዉ ተብሎ ተገምቶ በላዩ ላይ መሸጡ ተገቢ ባለመሆኑ የአፈጻጸም ትዕዛዙ ይሻርልኝ፡፡ አንድ መኖሪያ ቤት ያለአግባብ ሦስት ዙር መገመቱ ስህተት ነዉ፡፡ ከፍቺ በኃላ ያለማሁትን የጓሮ አትክልት በብር 816 የተገመተ ቢሆንም ሳይታሰብልኝ ቀርቷል፡፡ በአጠቃላይ በቤቴ የመኖር መብቴ እንዲከበርልኝ በቀደምትነት የመግዛት መብቴ ይጠበቅልኝ የሚል ነዉ፡፡
የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የጨረታ መነሻ ዋጋ ከታወቀ በኃላ ግራቀኙ ይሸጥ የተባለዉን ንብረት ይህንኑ ዋጋ በማጣቀስ ያስቀሩት እንደሆነ የቅድሚያ መብት መብታቸዉን በማረጋገጥ ረገድ ስርዓቱን ከተከተለ በኃላ የቅድሚያ መብት ሊሰጥ አይገባም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ አግባብነት ከሁሉም በላይ ንብረቱ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ከመሆኑ እና አመልካች ከሐራጅ መሸጫ ዋጋ የተሻለ ዋጋ ላቅርብ እያሉ ጥያቄያቸዉ የመታለፉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 430 ድንጋጌ አፈጻጸም አንጻር ለማየት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡
የተጠሪ መልስ ይዘት፡- በሕጋዊ መንገድ በማዘጋጃ ባለሙያ ተገምቶ፤ የጓሮ አትክልት ግምት ብር 816 መሆኑንን የአመልካችም መብት በቅድሚያ ተጠብቆላት እኔን ድርሻ ሰጥታ እንድትጠቀም ቢፈቀድላትም በቀጠሮ ሳትቀርብ ቀርታለች፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች የእኔን መብት በመጋፋቷና በተደጋጋሚ መሰናክል በመፍጠሯ በሀራጅ

www.abyssinialaw.com

ጨረታ ቤቱ ተሸጦ ድርሻዬ ብር 26,500.0 ተረክቤ የእሷን ድርሻ በሥር ፍ/ቤት ተቀምጦላት እያለ ባለቀ ጉዳይ ያቀረበችዉ ቅሬታ ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ የሰበር አቤቱታዋ ዉድቅ ይደረግልኝ የሚል ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነዉ ግራ ቀኙ በጋራ በጋብቻ ዉስጥ ያፈሩትን ቤት ፍቺን ተከትሎ እንዲከፋፈሉ ዉሳኔ የተሰጠ ሲሆን በአፈጻጸም ሂደት ቤቱ በማዘጋጃ ቤት ብር 51,8161 ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ተጠሪ ብር 2,000 ጨምሮ ለመግዛትና የአመልካችን ድርሻ ከፍሎ ለማስቀረት የጠየቀና ገንዘብ ይዞ የቀረበ ሲሆን አመልካች በብር 60,000 ለማስቀረት ጠይቃ ተጠሪም ፈቃደኛ ቢሆንም አመልካች ብር 12,000 ይዛ በመቅረብ ቀሪዉን ለመክፈል ጊዜ ከመጠየቅ በቀር ግዥዉን ለመፈጸምና የቅድሚያ ግዥ መብት ልትጠቀም አልቻለችም፡፡ ከዚህም በኃላ የስር ፍ/ቤት ቤቱን ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ጨረታዉን በብር 53,000 ያሸነፈዉ መ/ር አብነት ወልዴ ገንዘቡን ከፍሎ ቤቱን በአፈጻጸም እንዲረከብ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ከሽያጭ ገንዘቡ ድርሻዉን የወሰደ ሲሆን አመልካች ድርሻዋን ባለመዉሰዷ በአደራ በመስሪያ ቤቱ ግዥና ፋይናንስ ክፍል እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ አመልካች አጥብቃ የምትከራከረዉ በ2003 ዓ.ም በማዘጋጃ ቤት ተገምቶ በቀረበዉ ግምት መሠረት ብር 12,000 ለመክፈል ይዤ ቀርቤና ሌላዉን በሂደት ለመክፈል ጠይቄ ባለሁበት ከቤቱ ተፈናቅዬ ቤቱን ገዥዉ እንዲረከብ ትዕዛዝ መሠጠቱ ስህተት ነዉ በሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ቤት የቅድሚያ ግዥ መብት ጠይቃ አልተከለከለችም፡፡ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 430(1) መሠረት በሀራጅ ጨረታዉ ለመሳተፍ ጠይቃ አልተከለከለችም፡፡ አመልካች ለመግዛት በጠየቀችዉ ብር 60,000 እንድታስቀር ተጠሪ ስምምነቱን ገልጾ የነበረ ሲሆን አመልካች የተጠሪን ድርሻ ለመክፈል ይዛ የቀረበችዉ ገንዘብ ብር 12,000 ብቻ በመሆኑ ቤቱን ልታስቀር አልቻለችም፡፡ ጊዜ ተሰጥቶኝ በሂደት ልክፈል የሚለዉ ክርክርም ቢሆን ባለገንዘብ በሆነዉ በተጠሪ ፈቃድ ላይ የሚመሠረት በመሆኑ ጊዜ እንዲሰጥ ሊገደድ አይችልም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ግምት መክፈል የነበረብኝ በ2003 ዓ.ም በነበረዉ ግምት ነዉ የሚለዉ ክርክሯም የሕግ መሠረት የለዉም፡፡ ምክንያቱም ፍርዱ እስካልተፈጸመ ድረስ ቤቱ በአመልካች እጅ

www.abyssinialaw.com

ቢቆይም የጋራ ሀብት በመሆኑ በቆይታ የሚመጣዉ የግምት ጭማሪ ሁለቱንም የሚጠቅም በመሆኑ ነዉ፡፡

ሌላዉ አመልካች ከቤቱ ልፈናቀል አይገባም በማለት ብትከራከርም ቤቱን በሀራጅ ጨረታ ተሳትፎ ግዥ የፈጸመዉ ተጠሪ ሳይሆን መ/ር አብነት ወልዴ በመሆኑ ገዥዉ ተከራካሪ ባልሆነበትና በተጠሪነት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ባልተደረገበት ሁኔታ የሀራጅ ሽያጩ ሊሠረዝ ወይም የአመልካች የቅድሚያ ግዥ መብት ሊጠበቅ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች አቤቱታ ተገቢነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ካቀረቡት የሰበር አቤቱታ አንጻር የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1ኛ. በየም ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06376 መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03196 ጥቅምት 08 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 09299 ታሕሳስ 24 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በስር ፍ/ቤት የተጀመረዉ አፈጻጸም ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ ጥር 10 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3ኛ. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ 152185

መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- አቶ ደገፉ ምሰኔ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ፍርድ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 105067 አመልካች ለተጠሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ይህን ውሳኔ መነሻ በማድረግ ለከፈቱት የአፈጻጸም ክስ አመልካች በሰጠው መልስ ካርታው ሊሰጣቸው የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 መሠረት ወደ ሊዝ ስሪት በማስገባት በመሆኑ ተጠሪ ሊከፍሉት የሚገባ ክፍያ አለ በማለት ገልጿል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ጉዳዩ ሳይፈጸም የቆየው በአመልካች ችግር መሆኑን እና ከአዋጁ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በቀድሞ ሕግ መሠረት ሊስተናገዱ የሚገባ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

አፈጻጸሙን የመራው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራቀኙ መካከል ያለውን የአፈጻጸም ክርክር መርምሮ ተጠሪ በተለያየ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ከመውጣቱ በፊት አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የጠየቁ መሆኑን እና ሊፈጸምላቸው እንዳልቻለ በመ.ቁ 105067 ከተሰጠው ውሳኔ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው ሊሰጣቸው የሚገባው በአዋጁ አንቀጽ 6 መሠረት ሳይሆን በአንቀጽ 37/1/ መሠረት ነው ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ ካርታ የወሰዱበት ጊዜ እንጂ የጠየቁበት ጊዜ ወደ ሊዝ ስሪት ገብተው የሚስተናገዱበትን ጊዜ የማይወስን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የካርታ መስተንግዶ ጠየቅኩ ያሉበት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 2001 ጊዜ ሲሆን በዚህ ወቅት አዋጅ ቁጥር 272/94 እና የከተማ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1/94 በሰነድ አልባ የሚስተናገዱ አካላት ወደ ሊዝ ስሪት ስለሚገቡበት ሁኔታ እና የካርታ መስተንግዶ ስለሚያገኙበት አግባብ የተደነገገ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ይህን አልፈው ተጠሪ ያለ ሊዝ ክፍያ እና ስሪት ካርታ እንዲሰጣቸው የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 721/2004 አተገባበር አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የገዛሁት እና ውሉ ተመዝግቦ ማስረጃ እንዲሰጠኝ የጠየቅኩት ንብረት ሰነድ አልባ አይደለም፤ቤቱ በፍቃድ እና በፕላን የተሰራ እና በሻጭ ስም የተመዘገበ ነው፤አመልካች መስሪያ ቤት ጉዳዩ እንዳይፈጸም በማድረግ ሊዝ እስኪታወጅ አቆይቶታል፤ጊዜው የተራዘመው በአመልካች ጥፋት እንጂ በተጠሪ ጥፋት አይደለም፤አመልካች ውሉን ያስገባሁት እና እንዲመዘገብልኝ የጠየቅኩት ከአዋጁ በፊት ስለሆነ ሊፈጸምልኝ የሚገባው ውሉን ባስገባሁበት ወቅት በነበረው ሕግ መሠረት

www.abyssinialaw.com

ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ  በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ተጠሪ ንብረቱ በስማቸው ተመዝግቦ የባለቤትነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው በማለት በአመልካች ላይ ክስ ያቀረቡት በመስከረም ወር 2008 ዓ.ም መሆኑን፤ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 105067 በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ይፈጸምልኝ በማለት ሲመላለሱ የቆዩ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ተጠሪ በየትኛው ሕግ መሠረት ሊስተናገዱ እንደሚገባ  በውሳኔው ላይ ለይቶ ያላስቀመጠ መሆኑን፤ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ መሠረት በማድረግ የአፈጻጸም ክስ የከፈቱ መሆኑን እና የስር ፍ/ቤቶችም ተጠሪ ሊስተናገዱ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 37/1/ መሠረት ነው በማለት የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሰጡ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 6/3 በነባር ይዞታ ላይ የሰፈረ ንብረት ባለቤትነት ከውርስ በስተቀር በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ከተላለፈ ንብረቱ የተላለፈለት ሰው የቦታው ባለይዞታ መሆን የሚችለው በሊዝ ስሪት መሰረት ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 37/1 ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ቀደም ሲል ቀርበው በእንጥልጥል ላይ ያሉ የከተማ ቦታ ጥያቄዎችን በሚመለከት አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ  ውስጥ በቀድሞ ሕግ መሠረት ውሳኔ መስጠት አለባቸው በማለት ይደነግጋል፡፡

የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ከመውጣቱ በፊት አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የጠየቁ በመሆኑ እና ሊፈጸምላቸው ያልቻለ በመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው ሊሰጣቸው የሚገባው በአዋጁ  አንቀጽ 6 መሠረት ሳይሆን በአንቀጽ 37/1 መሠረት ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ ቢሆንም ተጠሪ አስተዳደሩ

ጥያቄዎን አልተፈጸመልኝም በማለት በመደበኛው ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡ በመሆኑ የተጠሪ ጉዳይ ከአስተዳደሩ እጅ መውጣቱን የሚያሳይ እንጂ በአዋጁ አንቀጽ 37/1 በተገለጸው አግባብ ቀደም ሲል ቀርቦ በእንጥልጥል ላይ እንደነበረ ሊወሰድ የሚገባ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ክስ ያቀረቡት አዋጅ ቁጥር 721/2004 ከወጣ በኋላ በ2008 ዓ.ም ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠውም ተጠቃሹ አዋጅ በስራ ላይ እያለ በመሆኑ የተጠሪ ጉዳይ ሊስተናገድ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 37/1 መሠረት ሳይሆን በአዋጁ አንቀጽ 6/3 በሊዝ ስሪት መሠረት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባቸው ተጠሪ ሊስተናገዱ የሚገባው በአዋጁ አንቀጽ 37/1 መሠረት ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 119226 መጋቢት 11 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 188394 ጥቅምት 16 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አፈጻጸሙ ሊቀጥል የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 37/1 መሠረት ሳይሆን በአዋጁ አንቀጽ 6/3 በሊዝ ስሪት መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

**መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ካ/የ**

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ 152172

ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም ሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር የሕብረት ሥራ ማሕበር

ተጠሪዎች፡- እነ ሰለሞን እሸቴ (191 ሰዎች)

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ውሳኔ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በሕብረት ሥራ ማሕበራት ማደራጃ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ታሕሣስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ ይህንኑ ውሳኔ መነሻ በማድረግ አፈጻጸሙን የመራው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ፍርዱን ላለመፈጸም የተጠሪዎች ድርሻ ተለይቶ አልቀረበም በማለት የሰጠው ምክንያት ተጠሪዎች ለግልግል ዳኞች አቤቱታ ሲያቀርቡ 191 ሰዎች አንድ ላይ ሆነው ሲሆን ውሳኔም ያገኙት በጠቅላላው ለ191 ሰዎች በመሆኑ ድርሻቸውን ስለሚያውቁት እና ሊከፋፈሉት ስለሚችሉ የተሰጠው ምክንያት ተቀባይነት የለውም በማለት የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ አድርጎ ይክፈላቸው፤አመልካች ከአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ ለተገባው አክሲዮን ባለድርሻ

www.abyssinialaw.com

በመሆናቸው ባለመብቶቹ የደረሰበት የገንዘብ መጠን የሚገባቸውን ሠርተፍኬት በየስማቸው አዘጋጅቶ ይስጣቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ማሕበሩ 7200 አባላት ያሉት ሲሆን የትርፍ ክፍፍል ለአባላቱ የሚከፋፈለው በሕብረት ስራ ማሕበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 45 እና በማሕበሩ ደንብ አንቀጽ 46 መሠረት አባሉ በማሕበሩ ካፒታል ውስጥ ያለውን የእጣ እና ቁጠባ መጠን መሠረት በማድረገ በመሆኑ የሽምግልና ዳኞችም ይህንኑ መሠረት አድርገው በውሳኔአቸው ተ.ቁ 2 እና 7 ላይ ተጠሪዎች ከማሕበሩ በወጡበት 2003 ዓ.ም ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር 2,179,133.05 ድርሻቸው ተሰልቶ እንዲከፈላቸው የሚለው ውሳኔ በመለወጥ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠጠቱ ተገቢ አይደለም፤እንዲሁም የማሕበሩ አባል ሲሞት ቤተሰቦቹ በዕዳ እንዳይጠየቁ ያዋጡትን ብር 3,155,216.56 የአጠቃላይ የማሕበሩ አባላት ገንዘብ ታስቦ ይከፈል በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ እና ከሳሾች የማህበር አባል በነበሩበት ጊዜ ለተገዛው የአክሲዮን ድርሻ በደረሰበት ካፒታል መጠን ሰርተፍኬት አዘጋጅቶ ይስጣቸው ተብሎ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ከዋናው ውሳኔ ውጪ የተሰጠ በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የሽምግልና ዳኞች በቀን 28/04/09 በሰጡት ውሳኔ ተጠሪዎች ከብር 5,361,749.61 ውስጥ ድርሻቸው ተለይቶ ሊከፈላቸው እንደሚገባ ተወስኖ እያለ የአፈጻጸም ችሎቱ ይኸው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ የተጠሪዎች ድርሻ እንደሆነ ተቆጥሮ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ማዘዙ ፍርዱን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪዎች በሽምግልና ዳኞቹ ውሳኔ መሠረት የሚገባን ድርሻ ተለይቶ ከነወለዱ እንዲከፈለን እና በአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ ከተገዛው የብር 7,500,000 አሁን የተደረሰበትን ካፒታል ጨምሮ የአክሲዮን ድርሻችንን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ እንዲሰጠን እንጂ የማይገባንን እና ውሳኔ ያልተሰጠበትን ክፍያ እንዲሰጠን ስላልጠየቅን በሽምግልና ዳኞቹ ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸምልን የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጠው የመልስ መልስ ተጠሪዎቹ ከአዲስ አንተርናሽናል ባንክ ከተገዛው ሼር በስተቀር የ 2003 ዓ.ም የትርፍ ክፍፍል ብር 2,179,133.05 እና የማሕበሩ አባል ብድሩን ሳይከፍል ቢሞት ለዕዳ መሸፈኛ የተዋጣው ብር 3,155,216.56 የጠቅላላ የማሕበሩ ገንዘብ መሆኑን አምነው በሽምግልና ዳኞች ውሳኔ መሠረት እንዲከፈላቸው መልስ መስጠታቸው የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎች ያልጠየቁትን ከሽምግልና ዳኞች ውሳኔ ውጪ ክፍያ እንዲከፈላቸው ትዕዛዝ መስጠታቸውን የሚያሳይ ነው፤ተጠሪዎች ከአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ ማሕበሩ የገዛውን አክሲዮን በተመለከተ አሁን በደረሰበትን ካፒታል ተዘጋጅቶ ሰርተፍኬት እንዲሰጠን በማለት የሰጡት ምላሽ ግን ከሽምግልና ዳኞኞች ውሳኔ ውጪ ስለሆነ በዚህ አግባብ ያቀረቡት መከራከሪያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል በማለት የተያዘውን የብር 5,361,749.61 የአፈጻጸም ትዕዛዝ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የአፈጻጸም ትዕዛዝ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ውሳኔ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በሕብረት ሥራ ማሕበራት ማደራጃ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ታሕሣስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሆኑን፤ተጠሪዎች የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡት በውሳኔው መሠረት ይፈጸምልን በሚል መሆኑን፤አፈጻጸሙን የመራው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች የተጠሪዎች ድርሻ ተለይቶ ባለመቅረቡ ፍርዱን ለመፈጸም አለመቻሉን በመግለጽ ያቀረበውን ምክንያት ለግልግል ዳኞች አቤቱታ ያቀረቡት አንድ መቶ ዘጠና አንዱ ተጠሪዎች በመሆናቸው እና ድርሻቸውን የሚያውቁት በመሆኑ ፍርዱን ላለመፈጸም የተሰጠው ምክንያት ተቀባይነት የለውም በማለት የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል

www.abyssinialaw.com

ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ አድርጎ እንዲከፍላቸው በማለት የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካች ገንዘቡን በሚመለከት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከረው ማሕበሩ 7200 አባላት ያሉት ሲሆን የትርፍ ክፍፍል ለአባላቱ የሚከፋፈለው አባሉ በማሕበሩ ካፒታል ውስጥ ያለውን የእጣ እና ቁጠባ መጠን መሠረት በማድረግ ሲሆን የሽምግልና ዳኞችም ውሳኔ የሰጡት ተጠሪዎች ከማሕበሩ በወጡበት 2003 ዓ.ም ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር 2,179,133.05 ድርሻቸው ተሰልቶ እንዲከፈላቸው፤የማሕበሩ አባል ሲሞት ቤተሰቦቹ በዕዳ እንዳይጠየቁ ያዋጡትን ብር 3,155,216.56 የአጠቃላይ የማሕበሩ አባላት ገንዘብ ታስቦ ይከፈላቸው የሚል ሆኖ ሳለ ከኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ ተደርጎ እንዲከፈላቸው በማለት የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ከውሳኔው ይዘት ውጪ ነው በሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ለዚህ ችሎት በሰጡት መልስም የአፈጻጸም ክስ ያቀረብነው በሽምግልና ዳኞቹ ውሳኔ መሠረት የሚገባን ድርሻ ተለይቶ ከነወለዱ እንዲከፈለን አልጠየቅንም በማለት የአመልካችን አቤቱታ በመደገፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በመሰረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ፤አፈጻጸሙን የሚመራው ፍ/ቤትም በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት እንደፍርዱ ይዘት እና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ ፍርዱን የሚያስፈጽም በቀር የፍርዱን ይዘት በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆኖ በማስፋት ፍርድን የመተርጎም ስልጣን እንደሌለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 372፤378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የስር ፍ/ቤት የሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ከዋናው ውሳኔ ይዘት ውጪ ነው በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤት የአፈጻጸም ትዕዛዝ በዋናው ፍርድ መሠረት የተሰጠ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተው መርምረናል፡፡

ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ውሳኔ በቂርቆስ ክፍለከተማ አስተዳደር በሕብረት ሥራ ማሕበራት ማደራጃ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ታሕሣስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ሲሆን በውሳኔው ገጽ 9 ተ.ቁ 2 ላይ ተጠሪዎች ከማሕበሩ በወጡበት የ2003

www.abyssinialaw.com

ዓ.ም በጀት ዓመት ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር 2,179,133.05 መሆኑ የሚያሳይ የኦዲት ሪፖርት የቀረበ በመሆኑ በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ውጤት መሠረት ተጠሪዎች ድርሻቸው ተሰልቶ የትርፍ ክፍፍሉ በየድርሻቸው መሠረት ከነወለዱ እንዲሰጣቸው የሚል ሲሆን፣በዚሁ ገጽ ተ.ቁ 3 ላይ በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ገንዘብ በመንግስት ኦዲተሮች ተመርምሮ የተገኘው ገንዘብ ብር 3,155,216.56 የተሰበሰበው ተጠሪዎች ለማሕበሩ እያንዳንዳቸው እየከፈሉ ያጠራቀሙት ብር 5 እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ከማሕበሩ ከቆጠቡት ገንዘብ ሲበደሩ ከጠቅላላው ብድር ላይ 1% እና 5 ብር ከነወለዱ ታስቦ ተጠሪዎች ከማሕበሩ እስከወጡበት 2003 ዓ.ም ድረስ ያላቸው ሂሳብ በነፍስወከፍ እንዲከፈላቸው የሚል ነው፡፡ ከውሳኔው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ካልተከፋፈለው የማሕበሩ የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ትርፍ ብር 2,179,133.05 እና በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ብር 3,155,216.56 ውስጥ የተጠሪዎች ድርሻ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው በማለት ውሳኔ መስጠቱን እንጂ በኦዲት ሪፖርተ መሠረት የተገለጸው የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ትርፍ ብር 2,179,133.05 እና በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ብር 3,155,216.56 የተጠሪዎች ድርሻ ስለሆነ ይከፈላቸው በማለት የተሰጠ ውሳኔ አለመሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም የማሕበሩ የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ትርፍ ብር 2,179,133.05 እና በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ብር 3,155,216.56 በተመለከተ አፈጻጸሙ ሊቀጥል የሚገባው ተጠሪዎች ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ያላቸው ድርሻ በቅድሚያ በሂሳብ ባለሙያ ተሰልቶ እና ተለይቶ እንዲቀርብ ከተደረገ በኂላ ተገቢ የሆነ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝተናዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት ፍርዱን በውሳኔ መሠረት ማስፈጸም ሲገባው ውሳኔ ያረፈበት ጠቅላላ ገንዘብ የተጠሪዎች ድርሻ እንደሆነ በመቁጠር የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ አድርጎ እንዲከፍላቸው በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ፣ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ ስለፍርድ አፈጻጸም የተደነገጉትን የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 40148 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ፤ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 193484 ጥቅምት 09 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ አድርጎ እንዲከፍላቸው በማለት የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ከዚህ ውጪ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ አልተነካም፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቂርቆስ ክፍለከተማ አስተዳደር በሕብረት ሥራ ማሕበራት ማደራጃ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ታሕሣስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የማሕበሩ የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ትርፍ ብር 2,179,133.05 እና በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ብር 3,155,216.56 አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ መሠረት ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ ተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባ ድርሻ ተለይቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ፍርዱን እንዲያስፈጽም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ/** - 144272

**ቀን** - 24/11/2010

**ዳኞች፡-**

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

**አመልካች፡-** የሻለቃ አሰፋ መንገሻ ህጋዊ ወራሾች - ወኪል ወ/ሮ ክብሬ አሰፋ -ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** አቶ ዮናስ ዳኜ -በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ክርክሩ የተጀመረዉ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት አርባ ምንጭ ከተማ ማዘጋጃ ቤት፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ በላይ አስራቴ በቅደም ተከተል ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡

ተጠሪ በቀን 06/08/2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ክስ ይዘት በአጭሩ በአርባ ምንጭ ከተማ ስፋቱ 3,200.00 ካ/ሜትር የሆነዉ ቦታ በህጋዊ መንገድ በ1976 ዓ.ም ተሰጥቶት በቦታዉ ላይ የተሻለ ድርጅት ለመገንባት በዝግጅት ላይ እያለ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ንብረቱን የሚመለከቱ የተለያዩ ሰነዶችን በቤት ዉስጥ ትቶ ወደ ኤርትራ መሄዱን፤ አባቱ አቶ ዳኜ መክበብ በተሻረ ዉክልና ድርጅቱን እና ቤቱን በባንክ በማስያዝ ከ3ኛ ተከሳሽ ባንክ ገንዘብ ከተበደረ በኋላ ገንዘቡ ሙሉ

www.abyssinialaw.com

በሙሉ ተከፍሏል በሚል የስር 3ኛ ተከሳሽ ለ1ኛ ተከሳሽ ማስረከቡን፣ 2ኛ ተከሳሽ ያላግባብ ካርታ በመስጠት እንዲሁም 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን በሽያጭ ለ4ኛ ተከሳሽ ያስተላለፉ መሆኑን በመጥቀስ ዉሉ ፈርሶ የቤቱ ካርታ ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ እና ይዞታዉን ከእነ ጋራዡ ድርጅቱ እንዲያስረክቡት ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ።

የአሁን አመልካች ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ የከሳሽ አባት፣ አቶ ዳኜ መክበብ፣ ከከሳሽ በተሰጣቸዉ ዉክልና መሠረት ቤቱን አስይዞ ከ3ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ሲበደሩ አባታቸዉ የዋስትና ግዴታ ገብተዉ የነበረ መሆኑን፤ አቶ ዳኜ መክበብ የብድር ገንዘቡን ባለመክፈላቸዉ ገንዘቡን እንዲከፍሉ የተሰጠዉን ዉሳኔ ተከትሎ ቤቱ በአፈፃፀም በጨረታ እንዲሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ የነበረ ቢሆንም ቤቱ ሊሸጥ ባለመቻሉ አበዳሪዉ 3ኛ ተከሳሽ ባንክ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በጨረታዉ መነሻ ዋጋ ቤቱን ተረክቦ ለብዙ ዓመታት ሲያስተዳድረዉ ከቆዬ በኋላ አመልካቾች በዋስትና ግዴታዉ ምክንያት ሊሸጥ ይችል የነበረዉን የአባታቸዉን ንብረት ለማስቀረት ሲባል የባንኩን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ በመሸፈናቸዉ 3ኛ ተከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት እንዳስረከባቸዉ እና ቤቱም በስማቸዉ እንዲሆን መደረጉን፤ አመልካቾች በዚህ መልኩ የተረከቡትን ቤት በህግ አግባብ ለስር 4ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን ጠቅሰዉ ተከራክረዋል። ሌሎች ተከሳሾችም በክሱ ኃላፊነት የለብንም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር መልስ ሰጥተዋል።

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪ አባት፣ አቶ ዳኜ መክበብ፣ ቤቱ ከ3ኛ ተከሳሽ ባንክ ለተበደሩት የገንዘብ ዕዳ መክፈያ እንዲሆን የጠየቁት ቤቱ የእራሴ ነዉ በሚል እንጂ ከተጠሪ ባገኙት ዉክልና መሰረት ባለመሆኑ አባቴ የእኔን ቤት በመያዣ አስይዞታል በሚል ተጠሪ ያቀረበዉን ክርክር አለመቀበሉን፤ አመልካቾች ለቤቱ መያዝ ምክንያት የሆነዉን እዳ በመክፈላቸዉ 3ኛ ተከሳሽን ተክተዉ የቤቱ ባለቤት ሊሆኑ የሚችሉበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን፤ ይሁንና የስር 4ኛ ተከሳሽ ቤቱን የገዛዉ በቅን ልቦና በመሆኑ የሽያጭ ዉል ይፍረስ በሚል ከሳሽ ያቀረበዉ ዳኝነት ተቀባይነት እንደሌለዉ፤ አመልካቾች ዕዳዉን ሙሉ በሙሉ በመክፈላቸዉ ቤቱ

www.abyssinialaw.com

ከተሸጠበት ብር 600,000.00 ዉስጥ ብር 412,309.42 ተመላሽ ተደርጎላቸዉ ቀሪዉ ብር 187,690.58 አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል። አመልካቾች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 27/10/2009 ዓ.ም አዘጋጅተዉ በጠበቃቸዉ አማካይነት ባቀረቡት 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል። አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርብ ጥሪ የተደረገለት ቢሆንም ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ንብረትነቱ የራሱ የሆነዉን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት አባቱ፣ አቶ ዳኜ መክበብ፣ ህጋዊ የሆነ የዉክልና ስልጣን ሳይኖራቸዉ ለባንክ መያዣ አድርገዉ ገንዘብ መበደራቸዉን የስር 3ኛ ተከሳሽ ባንክም በዚህ አግባብ በእጁ የገባዉን ቤት ያላግባብ ለአመልካቾች ማስተላለፉ እና አመልካቾችም መብት ሳይኖራቸዉ ቤቱን ለስር 4ኛ ተከሳሽ በመሸጥ ያደረጉት ዉል መብቱን የሚነካ መሆኑን ሲሆን፤ አመልካቾች በበኩላቸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የአባቱ፣ የአቶ ዳኜ መክበብ፣ እንጂ የተጠሪ አለመሆኑን እና ቤቱ ለአመልካቾች እንዲተላለፍ የተደረገዉም የብድር ዕዳዉ ባለመከፈሉ ምክንያት ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ በፍርድ ቤት በተሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት ገዥ ባለመገኘቱ አበዳሪዉ ባንክ (የስር 3ኛ ተከሳሽ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቤቱን ሲያስተዳድረዉ ከቆዩ በኋላ አመልካቾች የባንክ ዕዳዉን በመሸፈናቸዉ በስማቸዉ እንዲሆን አድርጎ በዚህም መሠረት የቤቱ ባለ ሀብት በመሆን ለስር 4ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን ገልጸዉ የተከራከሩ መሆኑን ተገንዝቧል።

www.abyssinialaw.com

በስር 3ኛ ተከሳሽ የነበረዉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በመያዣነት ይዞ ለተጠሪ አባት ገንዘብ አበድሮ የብድር ገንዘቡ ባለመመለሱ ክስ ቀርቦበት በመ/ቁ/614/82 መጋቢት 8 ቀን 1984 ዓ.ም በተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጸምለት አበዳሪዉ ባንክ ባቀረበዉ የአፈፃፀም ክስ መነሻነት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/176/85 ላይ ጥቅምት 1 ቀን 1988 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤቱን በሐራጅ ሸጦ ለፍርድ ባለ መብት ዕዳዉን በማስከፈል እንዲያስፈጽም ዉክልና መስጠቱ፤ በዚህም መሠረት ቤቱ እንዲሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ቢወጣም ገዥ ባለመገኘቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን እንዲረከብ እና የስም ዝዉዉርም እንዲደረግ ፍርዱን እንዲያስፈጽም ዉክልና የተሰጠዉ የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መስጠቱ፤ በዚህም ንግድ ባንክ ቤቱን ተረክቦ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ሲያስተዳድረዉ የነበረ መሆኑ፤ ይህ ከሆነ በኋላ የተጠሪ አባት ለተበደረዉ ገንዘብ የአመልካቾች አባት ሻለቃ አሰፋ መንገሻ ዋስ በመሆን በአዲስ አበባ የሚገኘዉን ቤታቸዉን ለባንክ መያዣ ሰጥተዉ የነበረ በመሆኑ እና ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ቤት የብድር ዕዳዉን መክፈል ባለመቻሉ የአመልካቾች አባት ቤት በዕዳ ምክንያት መሸጥ የለበትም በሚል ምክንያት አመልካቾች የባንኩን ዕዳ ሙሉ በሙሉ በመክፈላቸዉ ባንኩ ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነዉን ቤት እንዲረከቡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/176/85 መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት አመልካቾች ቤቱን ሰኔ 23 ቀን 1998 ዓ.ም የተረከቡ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ተጠሪም ይህ ስለመሆኑ ክዶ አልተከራከረም፡፡ በመሠረቱ በአፈፃፀም ምክንያት በሐራጅ እንዲሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዥ ካልተገኘ ባለ ገንዘቡ ንብረቱን የመረከብ መብት እንዳለዉ እና የአፈፃፀም መዝገቡን የያዘዉ ፍርድ ቤትም ይህ እንዲሆን የማዘዝ ስልጣን እንዳለዉ በፍ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 428(2) ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህም መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ባንክ እንዲሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዥ ባለመገኘቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የስር 3ኛ ተከሳሽ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ) መረከቡ ከተረጋገጠ የቤቱ ባለ መብት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነዉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ይህን ግምት ማስተባበል የሚቻለዉ ባንኩ ቤቱን እንዲረከብ በሚል ተሰጥቶ የነበረዉ ትዕዛዝ ስነ-ስርዓት ህጉ በሚፈቅደዉ አግባብ በሌላ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሻሩ ሲረጋገጥ እንደሆነ ይታመናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህ ጋር በተያያዘ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክርክር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀን 25/01/98 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሻለቃ አሰፋ መንገሻ ወራሾች ዕዳዉን አጠቃለዉ መክፈላቸዉን ባንኩ ማረጋገጡን ጠቅሶ ቤቱ ለተጠሪ እንዲመለስለት ሲል ትዕዛዝ መስጠቱን ሲሆን፤ አመልካቾች በበኩላቸዉ ተሰጠ የተባለዉ ትዕዛዝ በሦስት ዳኛ መሆን ሲገባዉ በአንድ ዳኛ የተሰጠ ከመሆኑም በላይ ከ 6 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን ተረክቦ እንዲያስተዳድረዉ ተሰጥቶ የነበረዉን ትዕዛዝ በመሻር በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በበኩሉ በዚህ መልኩ የተሰጠዉን ትዕዛዝ የተቀበለ መሆኑን በዉሳኔዉ የገለጸ ቢሆንም፣ የዚህን ትዕዛዝ ህጋዊነት ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ የፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች እንዲሁም አመልካቾች በዚህ ረገድ ካቀረቡት ክርክር አንፃር በማገናዘብ ተገቢዉን ማጣሪያ በማድረግ አለመሆኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ ይህ በአጠቃላይ የሚያሳየዉ የስር 3ኛ ተከሳሽ፣ ማለትም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤት በዕዳ ምክንያት መረከቡ በተረጋገጠበት እና ይህ መሆኑ ባንኩን በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት የሚሰጠዉ ሆኖ፣ ባንኩ የቤቱ ባለቤት እንዲሆን የተደረገበት ትዕዛዝ በሌላ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በህግ አግባብ የተሻረ መሆኑ ሳይረጋገጥ፣ የስር ፍርድ ቤት ባንኩ በቤቱ ላይ መብት አለኝ በሚል ምክንያት ለአመልካቾች ያስተላለፈበት አግባብ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ነዉ፡፡

በሌላ በኩል፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሱን ሲያቀርብ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የእኔ ነዉ በሚል ነዉ፡፡ ይሁንና አመልካቾች ቤቱ ለእርሱ ሳይሆን የአባቱ የአቶ ዳኜ መክበብ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ በጠየቀዉ ዳኝነት መሰረት ሊወሰንለት የሚችለዉ የቤቱ ባለቤት እርሱ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ምንም እንኳ ቤቱ በስሙ (በተጠሪ) ተመዝግቦ የሚታወቅ ቢሆንም፣ የተጠሪ አባት፣ አቶ ዳኜ መክበብ ቀደም ሲል በአፈፃፀም መዝገብ ላይ ባቀረቡት አቤቱታ፣ ቤቱ ሊመዘገብ የቻለዉ በወቅቱ ከአንድ ቤት በላይ ስለማይፈቀድ በተጠሪ ስም እንዲሆን ተደረገ እንጂ ቤቱ የተጠሪ ሳይሆን የእራሳቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ መስጠቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የቤቱ ባለ ሀብት የተጠሪ አባት እንጂ ተጠሪ አለመሆኑን የተቀበለ ስለመሆኑ ከዉሳኔዉ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ፍርድ ቤቱ በአንድ በኩል ቤቱ የአባቱ እንጂ

www.abyssinialaw.com

የተጠሪ አይደለም እያለ፣ በሌላ በኩል ግን ቤቱ ከተሸጠበት ገንዘብ በዉሳኔዉ የተመለከተዉ የገንዘብ መጠን ለተጠሪ እንዲከፈል ያለበት ምክንያትም ግልጽ አይደለም፡፡ የቤቱ ስመ ሀብት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ፣ የስር ፍርድ ቤት ቤቱ የተጠሪ ሳይሆን የተጠሪ አባት ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉም በግራ ቀኝ ከቀረበዉ ክርክር እና ማስረጃ አንፃር በአግባቡ በማጣራት ነዉ ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት የስር 3ኛ ተከሳሽ ባንክ በዕዳ ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተረክቦ በስሙ አድርጎ የነበረዉ እና ይህ በሌላ ትዕዛዝ መሻሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ባንኩ ቤቱን ለአመልካቾች ለማስተላለፍ መብት የለዉም በሚል የደረሰበት ድምዳሜ፤ እንዲሁም ተጠሪ የቤቱ ባለ ሀብት መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በዉሳኔዉ የተመለከተዉ ገንዘብ እንዲከፈለዉ በሚል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19212 በቀን 12/08/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23541 በቀን 04/05/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የተጠሪ ነዉ? ወይስ የአባቱ የአቶ ዳኜ መክበብ? የአቶ ዳኜ መክበብ ነዉ የሚባል ከሆነ ተጠሪ ከጠየቀዉ ዳኝነት አንፃር የሚያስከትለዉ ህጋዊ ዉጤት ምንድን ነዉ? ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት የስር 3ኛ ተከሳሽ ባንክ እንዲረከብ በሚል ቀደም ሲል ፍርዱን በሚያስፈጽም ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉን ትዕዛዝ ተከትሎ ባንኩ ቤቱን ተረክቦ ሲያስተዳድር ከቆዬ በኋላ ቤቱ ለተጠሪ ይመለስ በሚል የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 33/88 በቀን 27/10/98 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ አንድ ትዕዛዝ ሊሻር ወይም ሊሻሻል የሚችልበትን ስርዓት የተከተለ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች አንፃር

www.abyssinialaw.com

በማገናዘብ አጣርቶ ተገቢዉን ዉሳኔ ይሰጥበት ዘንድ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

**የሰ/መ/ቁ** - 146955

**ቀን** - 30/09/2010

**ዳኞች፡-**

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዩ ካሳሁን

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ብሩክ ኃ/መስቀል
2. አቶ ኤሊያስ ኃ/መስቀል — አልቀረቡም
3. አቶ ኢዩብ ኃ/መስቀል

**ተጠሪ፡-** አቶ ነብዩ ኃ/መስቀል -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የእርቅ ስምምነት ይፈጸምልኝ በሚል በቀረበዉ ክስ መነሻነት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በአጭሩ በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 09 ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ እና ቁጥሩ 7251 የሆነዉ ቤት ግራ ቀኝ በዉርስ አግኝተን የጋራችን የሆነዉን ቤት በተመለከተ በ19/10/07 ዓ.ም በመካከላችን የተደረገ የእርቅ

ስምምነት ዉል ይፈጸምልን የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የእርቅ ስምምነቱ እንዲፀድቅ ቀደም ሲል ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን፣ ከሳሾች የእርቅ ስምምነት ነዉ በማለት ያቀረቡትም የቤቱን ካርታ የማይገልጽ በመሆኑ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ካርታ የሌለዉ እና ብረትነቱም የመንግስት ሆኖ ቀበሌ የሚያስተዳድረዉ መሆኑ መረጋገጡን ገልፆ አመልካቾች ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት አመልካቾች ለክሳቸዉ መሠረት ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በየትኛዉ ላይ እንደሚፈጸም የማያመለክት መሆኑን ጠቅሶ የቀረበዉን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 23/12/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት በቀረበዉ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት በግራ ቀኝ መካከል በ19/10/2007 ዓ.ም ተደረገ የተባለዉን የእርቅ ስምምነት ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ስምምነቱ ለአፈፃፀም ቀርቦ ተቀባይነት ማጣቱን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ መልኩ ካቀረቡት ክርክር አኳያ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት ተይዞ እልባት ማግኘት የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ በፍርድ ቤት ሊፈጸም የሚችል በግራ ቀኝ መካከል የተደረገ የእርቅ ስምምነት መኖር አለመኖሩ ነዉ፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክስ ዉድቅ ያደረገዉ

www.abyssinialaw.com

ለክርክሩ ምክንያት ለሆነዉ የእርቅ ስምምነት መነሻ የሆነዉ ቤት ካርታ የሌለዉ እና የመንግሰት መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከቤቱ ባለቤትነት ጋር በተያያዘ በግራ ቀኝ የተነሳ ክርክር ሳይኖር ከፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 182 በሚዒረር መልኩ ከክርክሩ ጭብጥ ዉጪ በመዉጣት ዉሳኔ መስጠቱን በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ ብለናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች ለክሳቸዉ መሠረት ያደረጉት የእርቅ ስምምነት ተገቢዉን የፍሬ ነገር መግለጫ ያልያዘ እና ስምምነቱ በየትኛዉ ቤት ላይ እንደሚፈጸም የማያመለክት ስለመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋግጦ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉን ትዕዛዝ መስጠቱን ተመልክተናል፡፡ አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት አቤቱታም ተጠሪ ስምምነቱ ሊፈጸም የሚችል ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ሳይከራከር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህን ዉሳኔ መስጠቱ አግባብ አለመሆኑን የተከራከረ ቢሆንም፣ ስምምነቱ ግልጽና ሊፈጸም የሚችል ስለመሆኑ ገልጸዉ አልተከራከሩም፡፡ እኛም ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን የእርቅ ስምምነት አስቀርበን እንዳየነዉ እርቅ ስምምነቱ ስለየትኛዉ ቤት፣ እንዲሁም ተጠሪ በእርቅ ስምምነቱ መሠረት እንዲፈጽም የሚጠበቅበት ግዴታ ምን እንደሆነ በተብራራ መልኩ አያስቀምጥም፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3312(1) መሠረት እንደዉሳኔ ተቆጥሮ በፍርድ ቤት ለአፈፃፀም አቅርቦ ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ስምምነቱ ግልጽና የፈፃሚዉን አካል ግዴታ በማያሻማ ሁኔታ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ዓይነት ግልጽ ያልሆነ የእርቅ ስምምነት ሲቀርብ፣ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሌላ ተከራካሪ ወገን ክርክር እንኳን መስማት ሳያስፈልገዉ ይህኑን ጠቅሶ ክሱን ዉድቅ ማድረግ ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ቤቱ የመንግስት ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤት የደረሰበትን ድምዳሜ ማረም ሲገባዉ ይህን አለማረሙ ስህተት ቢሆንም፣ አመልካቾች ለክሳቸዉ መሠረት ያደረጉት ስምምነት ግልጽ እና የተብራራ አይደለም በሚል ምክንያት የቀረበለትን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ትዕዛዝ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/189984 በቀን 20/10/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/101014 በቀን 03/02/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ቤቱ የመንግስት ነዉ በማለት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
2. ይህ ችሎት በቀን 13/03/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር. 156389

ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ነ/ፈጅ ፈየራ ኦልጅራ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሺወርቅ ሲባኒ ጠበቃ ሲሳይ ወ/ዮሐንስ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአፈጻጸም ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ፍርድ ባለመብት፣ አቶ ደርቤ መኮንን የፍርድ ባለዕዳ ሲሆኑ የአሁን ተጠሪ ደግሞ የመቃወም አመልካች ነበሩ፡፡ አመልካች የፍርድ ባለዕዳዉ ንብረት ነዉ ባለዉ የቡና ማሽን ላይ አፈጻጸሙ እንዲቀጥልለት የጠየቀ ሲሆን የአሁን ተጠሪ የቡና ማሽኑ የፍርድ ባለዕዳዉ ንብረት ሳይሆን የራሳቸዉ ንብረት እንደሆነና እንዲለቀቅላቸዉ በመጠየቅ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸዉ ለአቤቱታዉ በሰጡት መልስ የፍርድ ባለዕዳዉ ይህንን ንብረት ከአመልካች በተከራየዉ ቤት ዉስጥ የሚጠቀምበት ስለሆነና የፍርድ ባለዕዳ የቤት ኪራይ ስላልከፈለና አመልካች ንብረቱ የሌላ ሰዉ መሆኑን አስቀድሞ ስለማያዉቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 መሠረት ዉሳኔዉ ሊፈጸምበት ስለሚገባ አቤቱታዉ ተገቢነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶ ክርክር ያስነሳዉ የቡና ማሽን የፍርድ ባለዕዳዉ ሳይሆን የተጠሪ መሆኑ ስለተረጋገጠ ንብረቱ ላይ ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቶ ለተጠሪ ይልቀቅ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ አመልካች ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ዉሳኔዉን በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2925 መሰረት አመልካች የቡና ማሽኑን ለኪራይ ዕዳ አከፋፈል ዋስትና እንዳይዝ የሚከለክሉ ነገሮች ስለመኖራቸዉ በጭብጥነት ይዞ ማጣራት ሲገባዉ ንብረቱ የተጠሪ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል እና አመልካች ማሽኑ የተጠሪ አለመሆኑን አላስተባበለም በሚል ብቻ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት በበኩሉ አመልካች የቡና ማሽኑ የተጠሪ ስለመሆኑ የሚያዉቅ መሆኑ በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን ከደመደመ በኃላ ተጠሪ ማሽኑን በፍርድ ባለዕዳ ማከራየቷን ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ የለባትም፤ የግል ንብረቷ መሆኑን አስረድታለች በሚል የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ማጽናቱ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሌለዉን የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1193(2)ን በመጥቀስ አመልካች የቡና ማሽኑን ለፍ/ባለዕድዉ ዕዳ መክፈያነት መያዝ አይቻልም ብሎ የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይሻርልን የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከስር የፍርድ ባለዕዳ ጋር ተከራክሮ ለማስፈጸሚያነት ያስያዙት የቡና ማሽን የአሁኑ ተጠሪ ንብረቱ የግሌ ነዉ በማለት የኪራይ ዉል በማቅረባቸዉ ብቻ ለአፈጻጸም ሊዉል አይገባም መባሉን ከፍ/ሕ/ቁ 1193(1) እና 2924 አንጻር ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለአቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት፡- አንድ ንብረት ላይ ፍርድ ሊፈጸም የሚችለዉ የባለዕዳዉ ንብረት መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን ክርክር ያስነሳዉ የቡና ማሽን የፍርድ ባለዕዳዉ ሳይሆን የግሌ መሆኑ ተረጋግጦ እንዲለቀቅልኝ በስር ፍ/ቤት መወሰኑ

www.abyssinialaw.com

ተገቢ ነዉ፡፡ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1193(1) መሰረት ክርክር ያስነሳዉ ንብረት የፍርድ ባለዕዳዉ መሆኑን ግምት በመዉሰድ ለአፈጻጸም እንዲዉል የጠየቀ ቢሆንም ተጠሪ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1193(2) መሰረት አመልካች የያዘዉ ግምት ልክ አለመሆኑን በበቂ ማስረጃ በማስረዳት ያስተባበልን በመሆኑ ንብረቱ እንዲለቀቅ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ባቀረበዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች የንግድ ቤቱን ለፍርድ ባለዕዳ አከራይቶ የነበረ ሲሆን የፍርድ ባለዕዳ ያልከፈለዉ ዉዝፍ ኪራይ በመኖሩ ክስ አቅርቦበት አስወስኗል፡፡ አመልካች የተወሰነለት ገንዘብ አፈጻጸም የፍርድ ባለዕዳዉ በተከራየዉ ቤት ዉስጥ ይሠራበት በነበረዉ የቡና ማሽን ተሸጦ እንዲፈጸምለት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸዉ የቡና ማሽኑ የፍርድ ባለዕዳዉ ንብረት ሳይሆን የራሳቸዉ ንብረት በመሆኑ ለአፈጻጸም ሊዉል እንደማይገባና ሊለቀቅላቸዉ እንደሚገባ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ማስረጃ ከሰማ በኃላ የቡና ማሽኑ የፍርድ ባለዕዳዉ ሳይሆን የተጠሪ መሆኑን ካረጋገጠ በኃላ ለአፈጻጸም ሊዉል ስለማይገባ ለተጠሪ ይለቀቅላቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳዉ ባይሆንም አመልካች ይኸዉ ንብረት የሌላ ሰዉ መሆኑን አውቆ የነበረ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስና በተከራየዉ ቤት ዉስጥ የሚጠቀምበት እስከሆነ ድረስ ላልተከፈለ የቤት ኪራይ አከፋፈል ሊውል ይገባል በማለት ነዉ፡፡

በመሠረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 ተከታዮች ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በመርህ ደረጃ አንድ ፍርድ በአንድ ንብረት ላይ ሊፈጸም የሚችለዉ ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳዉ ንብረት መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 ያንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ የሆነ ሰዉ ባለፈዉ ዓመት ላልተከፈለዉ ኪራይና ላለበትም ዓመት ስድስት ወር ሊከፈለዉ ለሚገባዉ ኪራይ ዋስትና ለቤቱ ማጌጫ ከሚያገለግሉት ዕቃዎችም ሆነ ለስፍራዉ ማልሚያ ከሚጠቀሙት መሳሪያዎች ላይ የመያዣ መብት ያለዉ መሆኑን ሲደነግግ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2926(2) ደግሞ በስዉር

www.abyssinialaw.com

ወይም በኃይል የተወሰዱትን ዕቃዎች ሳይቀሩ አከራይ በአስር ቀን ዉስጥ በፍርድ በማስያዝ የአከራዩን መብቶች በቀደምትነት መክፍያ እንዲሆኑ ማድረግ የሚችል መሆኑን፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2925 አከራዩ የዕቃዎቹ ባለሀብትነት የተከራዩ አለመሆኑን አዉቆ እንደሆነ ወይም ማወቅ ይገባዉ ኑሮ እንደሆነ በዕቃዎቹ ላይ የመያዣ መብቱ ሊፈጸም እንደማይችልና የራሱ አለመሆናቸዉን ያወቀዉ ዉሉ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ የሆነ እንደ ሆነ ዉሉ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ እንዲፈርስ ካላመለከተ በቀር በእነዚህ ዕቃዎች ላይ ይዞ የማቆየት መብቱ ይቀርበታል ተብሎ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከነዚህ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻለዉ የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ የሆነ ሰዉ ከላይ ለተገለጸዉ ጊዜ ላልተከፈለዉ የዉዝፍ ኪራይ ክፍያ አከፋፈል ሲባል ተከራዩ ለቤቱ ማጌጫነት ወይም ለስፍራ ማልሚያነት ከሚጠቀምባቸዉ ዕቃዎች ላይ ዕቃዎቹ የራሱ ባይሆኑም ይህንኑ አከራዩ እስካላወቀ ወይም ማወቅ ነበረበት እስካልተባለ ድረስ በሕግ የተቋቋመ የመያዣ መብት ያለዉ መሆኑና በልዩ ሁኔታ ለአፈጻጸም ሊያዉላቸዉ የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ክርክር ያስነሳዉ የቡና ማሽን የፍርድ ባለዕዳዉ ንብረት ሳይሆን የተጠሪ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም የፍርድ ባለዕዳዉ ለተከራየዉ ቤት ማልሚያነት ይጠቀምበት የነበረ መሆኑ እስካልተካደና እስከተረጋገጠ ድረስ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንጻር ለአፈጻጸም ሊዉል የሚገባዉ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ሳይጣራና ሳይረጋገጥ ንብረቱ የባለዕዳዉ ሳይሆን የተጠሪ ነዉ ስለተባለ ብቻ ለአፈጻጸም ሊዉል አይገባም ተብሎ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም የቡና ማሽኑ የተጠሪ መሆኑ ቢረጋገጥም የፍርድ ባለዕዳዉ ለተከራየዉ ቤት ማልሚያ የሚጠቀምበት መሣሪያ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት፡-

1. አመልካች በቡና ማሽኑ ላይ የመያዣ መብት ያለዉ መሆን ያለመሆኑ?
2. አመልካች የተወሰነለት የኪራይ ገንዘብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 መሠረት የመያዣ መብት የሚያሰጠዉ መሆን አለመሆኑ?
3. እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2925 ድንጋጌ አንጻር አመልካች ቤቱን ሲያከራይ የቡና ማሽኑ የፍርድ ባለዕዳዉ ወይም የተከራዩ አለመሆኑን ያዉቅ የነበረ መሆኑ ወይም ማወቅ ይገባዉ የነበረ ወይም ዉሉ ጸንቶ በቆየበት ወቅት

www.abyssinialaw.com

ይህንኑ አዉቆ የነበረ መሆን ያለመሆኑ? በቅድሚያ በማስረጃ ሊጣራና ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት ክርክር ያስነሳዉ የቡና ማሽን የፍርድ ባለዕዳዉ ሳይሆን የተጠሪ መሆኑን ቢያርጋግጥም ከአመልካች ክርክርና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንጻር ንብረቱ ለአፈጻጸም መዋል መቻል አለመቻሉ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ሳይጣራና ሳይረጋገጥ ንብረቱ ለአፈጻጸም ሊዉል አይገባም ተብሎ መወሰኑ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በለመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ አጣርቶ እንዲወስን ለስር ፍ/ቤት መመለሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 23545 ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 264744 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሀተታዉ በተገለጸዉ አግባብ ግራ ቀኙን አከራክሮና በማስረጃ አጣርቶ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት ጉዳዩ ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይመለስለት ተብሏል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. ሚያዚያ 02 ቀን 2010 ዓ.ም አፈጻጸሙ ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

ሰበር መ/ቁ154222

ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-አቶ ረሽድ አደም

ተጠሪ፡-አቶ ታሪኩ አማረ

መዝገቡ ለምርምራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ፡፡**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በመጀመሪያ ጨረታ ሽያጭ ላይ ተወዳድሮ አሸናፊ የተባለዉ ገዥ ዋጋ ከፍሎ ግዥዉን ባለመፈጸሙ ድጋሚ ጨረታ ሲደረግ የሽያጭ ዋጋ ቢቀንስ ልዩነት የመክፈል ሃላፊነት የሚመለከት ክርክር መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የፍርድ ባለእዳ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የፍርድ ባለመብት ወ/ሮ ብሻሺ አዲሱ መካከል በነበረዉ የአፈጻጸም ክርክር የፍርድ ባለእዳ ንብረት የሆነ ቤት በጨረታ እንዲሸጥ በተሰጠ ትእዛዝ መሰረት በመጀመሪያ ጨረታ ላይ የአሁኑ አመልካች ወንድም የሆነዉ አቶ ከሊል አደም በጨረታዉ ተወዳድሮ ቤቱን በብር 200,000 አሸናፊ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ ባለመቻሉ ሁለተኛ ጨረታ እንዲወጣ ሲደረግ የአሁኑ አመልካች ተወዳድሮ በብር 137,000 አሸናፊ ሆኖ ሽያጩ እንዲከናወን በመደረጉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/ 429/2/ መሰረት ተጫራቹ በመጀመሪያ ጨረታ እና በሁለተኛ ጨረታ መካከል ያለዉን የዋጋ ልዩነት ብር 63,200 አመልካች እንዲከፍል ተጠሪ አቤቱታ አቀረበ፡፡ የአፈጻጸም መዝገቡን የያዘዉ የመቱ

ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን አስተያየት ከተቀበለ በኂላ የአመልካች ወንድም በመጀመሪያዉ ጨረታ የተወዳደረዉ ለአመልካች ስለመሆኑ በመግለጹና አመልካችም ይህንኑ አምኗል በሚል በሁለቱም ጨረታ የተወዳደረዉ አመልካች ነዉ በሚል የዋጋ ልዩነቱን ብር 63,200 የአሁኑ አመልካች እንዲከፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/429/2/ መሰረት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለኢሉባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የአመልካች ወንድም በአመልካች ስም ጨረታ እንዲወዳደር ግልጽ ዉክልና መስጠቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ልዩነቱን የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2205 ዋቢ በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሽሯል፡፡በሌላ በኩል በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ ከደመወዙ ተቆርጦ ይከፈል በማለት ቃሉን የሰጠዉን በመጀመሪያ ጨረታ አሸናፊ ተብሎ ግደታዉን ያልተወጣዉ ሰዉ ላይ የመጠየቅ መብት ጠብቆለታል፡፡የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ በማቅረቡ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ አመልካች በህግ አግባብ ለወንድሙ የሰጠዉ ዉክልና ባይኖርም ወንድሙ የሆነዉ ከሊል አደም በሰጠዉ ሀሳብና አመልካች በሰጠዉ ሀሳብ መሰረት የዋጋ ልዩነቱን የመክፈል ሃላፊነት የአመልካች ነዉ በማለት የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡አመልካች በዚህ ቅር ተሰኝቶ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ሰበር ችሎቱ ግራቀኙን አከራክሮ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ አመልካች በህግ አግባብ ለወንድሙ አቶ ከሊል አደም የሰጠዉ ዉክልና ሳይኖር አቶ ከሊል አደም በመጀመሪያዉ ጨረታ በራሱ ስም ተወዳድሮ አሸናፊ ነዉ ለተባለበት አመልካች ሃላፊነት ሊወስድ እንደማይገባ ፣አቶ ከሊል አደም በመጀመሪያ ጨረታ አሸናፊ ተብሎ ግዴታዉን ባለመወጣቱ ካስያዘዉ ገንዘብ ላይ ተቀንሶ ገቢ መደረጉን በሁለተኛ ጨረታ እንዳይወዳደር መደረጉ እና አቶ ከሊል አደም የዋጋ ልዩነት ከደመወዙ ተቀንሶ ገቢ ይደረግ እያለ ባለበት ሁኔታ አመልካች እንዲከፍል መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ እንዲታረም ጠይቋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በመጀመሪያ ጨረታ ተወዳድሮ ካሸነፈ በኋላ ክፍያዉን ሳይፈጽም የቀረዉ የአመልካች ወንድም ሆኖ ሳለ በዚሁ ምክንያት ድጋሚ ጨረታ ወጥቶ አመልካች ተወዳድሮ ባነሰ ዋጋ በማሸነፉ አመልካች ልዩነት እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/429 አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በመጀመሪያዉ ጨረታ ላይ አመልካችና ቤተሰቦቹ እንደተወዳደሩ፣ አቶ ከሊል አደም ለአመልካች በሚል እንደተወዳደረ በስር ፍርድ ቤት ላይ መግለጹና አመልካችም ይህንኑ በፍርድ ቤት ስለማረጋገጡ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡የአመልካች ጠበቃ ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ ክርክር ይዘት ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ከመዝገቡ እንደተገነዘብነዉ አከራካሪዉ ጉዳይ በመጀመሪያ ጨረታ እና በሁለተኛ ጨረታ መካከል የንብረቱ ዋጋ ልዩነት ሲፈጠር ሃላፊነት የሚከተለዉን ወገን የመለየት ጉዳይ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ህግ አንቀጽ 429 ላይ በጨረታ ለገዛዉ ንብረት ዋጋዉን ሳይከፍል ወይም ግዴታዉን ሳይፈጽም የቀረ ገዢ ንብረቱ በሁለተኛ ጨረታ ሲሸጥ ለጎደለዉ ገንዘብ በሃላፊነት የሚጠየቅበት ሁኔታ ተደንግጓል፡፡በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሁለት ላይ እንደተደነገገዉ ንብረቱ እንደገና በሚሸጥበት ጊዜ ዋጋ የቀነሰ እንደሆነ በመጀመሪያ ጨረታ ንብረቱን የገዛዉና ዋጋዉን ያልከፈለዉ ተጫራች የፍርድ አፈጻጸም እዳ በሚከፈልበት ዓይነትና ሁኔታ ልዩነቱንና ኪሳራዉን እንዲከፍል እንደሚገደድ ተመልክቷል፡፡ስለዚህም የዋጋ ልዩነቱንና ኪሳራዉን የመክፈል ግደታ የተጣለዉ በመጀመሪያ ጨረታ ተወዳድሮ የጨረታዉ አሸናፊ ነዉ የተባለዉ ሰዉ ላይ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ክርክር በመጀመሪያ ጨረታ ተወዳድሮ የጨረታዉ አሸናፊ ነዉ የተባለዉ እና በዚሁ አግባብ ግዴታዉን ያልተወጣዉ የአመልካች ወንድም የሆነዉ አቶ ከሊል አደም ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ሂደት የተገለጸ ጉዳይ ነዉ፡፡አከራካሪ የሆነዉ ጉዳይ የአመልካች ወንድም በመጀመሪያ ጨረታ የተወዳደረዉ ለአመልካች ወይስ ለራሱ ጥቅም ነዉ የሚለዉ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የአመልካች ወንድም በስር ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

ቀርቦ የተጫረተዉ በራሱ ስም ቢሆንም ለአሁኑ አመልካች ጥቅም ስለመሆኑ ገልጾ ገንዘቡን በወቅቱ ገቢ ማድረግ ባለመቻሉ ለሚፈጠረዉ የዋጋ ልዩነት ከራሱ ደመወዝ ተቀንሶ ገቢ እንዲደረግ የጠየቀ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት የዚህ ሰዉ ጥያቄ ያለፈበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበዉ ክርክር የመጀመሪያ ጨረታ ላይ እንዳልተወዳደረ፣ ወንድሙ አቶ ከሊል አደም በጨረታዉ በአመልካች ስም እንዲወዳደር ዉክልና ያልሰጠ ስለመሆኑ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ላይ ቀርቦ ወንድሙ ለእሱ እንደተወዳደረ አምኗል በማለት በመዝገብ ላይ ያሰፈረዉ ትክክል እንዳልሆነ አጥብቆ ተከራክሯል፡፡ስለሆነም የአመልካች ወንድም በመጀመሪያዉ ጨረታ የተወዳደረዉና አሸናፊ የተባለዉ ለራሱ ጥቅም ወይስ ለአሁኑ አመልካች ጥቅም ነዉ የሚለዉን ጥያቄ ለይቶ በመወሰን ረገድ በየደረጃዉ ክርክሩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የተለያየ መነሻ በመያዝ የተለያየ ዉሳኔ ማስጠታቸዉን ከላይ ተመልክተናል፡፡ይሕም አንዱ ፍርድ ቤት ግራቀኙ በችሎት በሰጡት ሀሳብ ለአመልካች ጥቅም ስለመሆኑ ታምኗል የሚል መነሻ የያዘ ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ በመጀመሪያ ጨረታ አመልካች ግልጽ ዉክልና መስጠቱ አልተረጋገጠም በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ ባንድ ጉዳይ ላይ ሃላፊነት የሚመነጨዉ ከህግ ወይም ከዉል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ከዚህ መዝገብ ክርክር እንደተገነዘብነዉ የአመልካች ሃላፊነት ምንጩ በአመልካችና በወንድሙ መካከል በነበረዉ ግንኙነት ወንድሙ ለፈጸመዉ ተግባር እንደወኪል ታይቶ ሃላፊነት እንዲወስድ የሚል ክርክር ነዉ፡፡በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2079 እንደተደነገገዉ የሌላ ሰዉ እንደራሴ በመሆን ስራዎችን የመፈጸም ስልጣን የሚገኘዉ ከህግ ወይም ከዉል ነዉ፡፡ዉክልናዉ በዉል የተሰጠ እንደሆነ ተወካዩ በወካዩ ስም ህጋዊ ስራዎችን እንዲሰራ የሚደረግበት ዉል መኖሩን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2099 ይገልጻል፡፡ በዉል የሚሰጥ ዉክልና ጠቅላላ ዉክልና ወይም ልዩ ዉክልና ተብሎ በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2002 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ከማስተዳደር ስልጣን ያለፈ ተግባር ማከናወን የሚቻለዉ በልዩ ዉክልና ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2005/2/ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ክርክር አከራካሪዉ ጉዳይ የአመልካች ወንድም የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመግዛት በመጀመሪያ ጨረታ ላይ የተወዳደረዉ በራሱ ስም ቢሆንም

ለአመልካች ጥቅም ነዉ በሚል የአመልካች ወኪል ሆኖ እንደተወዳደረ ተወስዶ ሃላፊነቱ የአመልካች መሆን አለበት ወይስ አይደለም የሚል ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የአመልካች ወንድም አቶ ከሊል አደም በመጀመሪያ ጨረታ የተወዳደረዉ በራሱ ስም ከመሆኑም በተጨማሪ ከአመልካች የተሰጠዉ ግልጽ ዉክልና ስለመኖሩ የቀረበ ማረጋገጫ የለም፡፡በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ አቶ ከሊል አደም በአንድ በኩል በራሱ ስም መጫረቱን እየገለጸ ፤ በሌላ በኩል ለወንድሜ ነዉ የተጫረትኩት ገንዘቡን መክፈል አልችልም ከደመወዝ ይቆረጥ በማለቱና አመልካች ስር ፍርድ ቤት ቀርቦ ይህንኑ አምኗል በሚል ምክንያት ነዉ፡፡እዚህ ላይ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ አመልካች በግልጽ ለወንድሙ አቶ ከሊል አደም በዚህ በግልጽ ዉክልና መስጠቱ ባልተረጋገጠበትና ስር ፍርድ ቤት ላይ የተመዘገበዉ ቃል አመልካች በግልጽ የመጀመሪያዉ ጨረታ ላይ ሃላፊነት የወሰደበት ሁኔታ በሌለበት ፍርድ ቤቱ አመልካች አምኗል የሚል በመመዝገብ አመልካችን ሃላፊ ማድረግ ተገቢ አይደለም የሚል ነዉ፡፡በዚህም ላይ ጉዳዩን በተለያየ ደረጃ የተመለከቱት የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በፍርድ ቤት ቀርቦ በችሎት ላይ የተመዘገበ ቃል እምነት የሚጣልበት ነዉ ወይስ አይደለም በሚለዉ ነጥብ ዙሪያ የተለያየ አቋም መዉሰዳቸዉ ከመዝገቡ ላይ ይታያል፡፡ከላይ እንደተመለከትነዉ ይህ ጉዳይ የፍትሓብሔር ክርክርም ቢሆን ሃላፊነትን የሚያሥከትል ከመሆኑ አኳያ አመልካች በዚህ ጉዳዩ ላይ የሰጠዉ ቃል አሻሚና አከራካሪ ከሆነ እሱን ሃላፊነት ዉስጥ የሚያስገባ ሊሆን አይገባም፡፡በሌላ በኩል የአመልካች ወንድም የሰጠዉ ቃል ቢሆን ራሱ ሃላፊነት የሚወስድበት ከሚሆን በስተቀር በራሱ ስም ጨረታዉን መወዳደሩን ግልጾ እርስ በርሱ የሚጣረስ ሃሳብ ማቅረቡ በግልጽ እየታየ ወንድሙ ለፈጸመዉ ተግባር አመልካች ሃላፊነት እንዲወስድ ለመወሰን የሚያስችል የህግ መሰረት የለዉም፡፡ሲጠቃለል በዚህ ጉዳይ አመልካች በመጀመሪያ ጨረታ በራሱ ወይም በህጋዊ ወኪል አማካይነት ስለመወዳደሩና ስለማሸነፉ በበቂ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ወይም ሃላፊነት ስለመዉሰዱ አጣራጣሪና አከራካሪ በሆነበት ሁኔታ ዉስጥ በሁለተኛዉ እና በአንደኛዉ ጨረታ መካከል ለተፈጠረዉ የዋጋ ልዩነት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ /429/2/ መሰረት ሊከፍል የሚገደድበት የህግም ሆነ የዉል ግንኙነት ምክንያት ባለመኖሩ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች አመልካች ሃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም

www.abyssinialaw.com

ይገባል ብለናል፡፡በሌላ በኩል የኢሉባቦር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ ላይ እንዳመላከተዉ ተጠሪ ከአቶ ከሊል አደም ላይ የሚጠይቀዉ መብት በዚህ ዉሳኔ የተገደበ አይሆንም ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/210226 ላይ በ28/06/09ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/268042 ላይ በ09/04/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 348/1/መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/የኢሉባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/29822 ላይ በ19/03/09 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡ይጻፍ፡፡

3ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

www.abyssinialaw.com

# የወንጀል ሕግ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/153228

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፤የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ

ተጠሪዎች፡1ኛ/ፈንቴ ንጉስ

2ኛ/ታድሎ ጥላሁን

3ኛ/ምናለ ዳኛዉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ተጠሪዎች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ ተላልፈዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል ተብሎ ከቀረበባቸዉ ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ፍርድ አግባብነት ለመመርመር የቀረበ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ እነ ቄስ ወርቁ ገላዬ /9 ሰዎች/በተጠረጠሩበት የደን እንጨት መቁረጥ ወንጀል የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፎገራ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ላይ በምስክርነት ቀርበዉ ተጠርጣሪዎቹ ጥር 24 ቀን 2008 ዓ.ም ከቀኑ 6:30 ላይ ፎገራ ወረዳ ምንጡራ ቀበሌ ሸንበቆ ጎጥ ከተባለዉ ቦታ የማህበራት የተፈጥሮ ደን የሆነዉን ሁሉም ተከሳሾች መጥረቢያ በመያዝ ደኑን ሲጨፈጭፉ አይተናል በማለት ቃል ከሰጡ በኋላ የአቃቤ ህግ ምስክር ሆነዉ በፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃላቸዉን በ07/10/08 ዓ.ም

www.abyssinialaw.com

ሲሰጡ ሁሉም ተከሳሾች መጥሪቢያ ይዘዉ ሲቀርጡ አላየንም በማለታቸዉ ደን ቆርጠዋል ተብለዉ ክስ የቀረበባቸዉ ተከሳሾቹ በ21/10/08 ዓ.ም በተሰጠ ፍርድ በነጻ እንዲሰናበቱ ስለተወሰነ ተጠሪዎች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 453/2/ ተላልፈዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ሰጥተዋል በሚል ክስ የቀረበባቸዉ ሲሆን ተጠሪዎች ክሱን ክደዉ ስለተከራከሩ ክሱን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀችን ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ ተጠሪዎች የተመሰከረባቸዉን በመከላከያ ማስረጃ አላስተባበሉም በማለት በተከሰሱበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት እያንዳንዳቸዉ በ6ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸዉ ፍርድ ቤቱ ግራቀችን አከራክሮ የተጠሪዎች ድርጊት ጥፋት መሆኑን ለማስረዳት በአቃቤ ህግ በኩል የቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡት የምስክርነት ቃል እና ከዚህ ጋር ማነጻጸሪያ ሆኖ የቀረበዉ ተጠሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበዉ ቃለ መሃላ ፈጽመዉ የሰጡት ምስክርነት ቃል ብቻ ስለመሆኑ ገልጾ በፖሊስ የምርመራ ወቅት የሚሰጠዉ ምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት ከተሰጠ ምስክርነት ቃል ጋር ተነጻጽሮ የትኛዉ ትክክለኛ ነዉ የሚለዉን ለመለየት ተጨማሪ ማስረጃ እንደሚያስፈልግ ከዚህም ባሻገር ከጅምሩም ቢሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 453 የሚሸፍነዉ ዳኝነት ወይም ዳኝነት ነክነት ባለዉ ሂደት ላይ የሚሰጥ ምስክርነትን ቃል የሚመለከት ስለመሆኑና ፖሊስ ስልጣንና ተግባር እንዲሁም የወንጀል ምርመራ ሂደት ዳኝነት ነክነት ያለዉ ተግባር ነዉ ተብሎ በዚህ አንቀጽ ስር ሊሸፈን እንደማይገባ በማተት የስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ያስተላለፈዉን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በመሻር ተጠሪዎች በነጻ እንዲሰናበቱ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የፖሊስ ተቋም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ተቋም አይደለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ትርጉም የፖሊስ ተቋም በወንጀል ጉዳይ የመጀመሪያ የምስክርነት ቃል የሚሰጥበትና አቃቤ ህግም ይህንኑ መሰረት አድረጎ ክስ የማቅረብ ወይም ያለማቅረብ ጉዳይ ዉሳኔ የሚሰጥበት ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት የፖሊስ ተቋም የዳኝነት ነክነት ተግባር የሚፈጸሚበት አይደለም ተብሎ የተሰጠዉ ትርጉም መሰረታዊ የህግ ስህተት

የተፈጸመበት ነዉ በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡የአመልካች ሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪዎች እነ ቄስ ወርቁ ገላየ 9 ሰዎች በተከሰሱበት የደን መቁረጥ ወንጀል ምርመራ በፎገራ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ቀርበዉ ወንጀሉ ሲፈጸም የተመለከቱ መሆኑን መስክረዉ በፍ/ቤት ደግሞ የአቃቤ ህግ ምስክር ሆነዉ ቀርበዉ በፖሊስ የሰጡትን ቃል በመለወጣቸዉ ከቀረበባቸዉ ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ የተሰጠዉ ዉሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 453/2/ አያሟላም ተብሎ ዉድቅ መደረጉ አግባብነት ከመሰረታዊ ማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በቀበሌዉ ዉስጥ በህዝብ ተመራጭነት በተሰጣቸዉ ሃላፊነት ድርጊቱ በፖሊስ እንዲጣራ ከመጠየቅ ዉጪ የድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት እንደማያዉቁ ለፖሊስ ገልጸዉ እያለ ፖሊስ በማስፈራራትና በማንገራገር እነሱ ያላሉትን ቃል በመመዝገብ ሳያነብላቸዉ እንዳስፈረማቸዉ ጠቅሰዉ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ትክክለኛዉን እዉነታ የምስክርነት ቃል የሰጡ ስለሆነ‌ሙና የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መሰረት አድርጎ በነጻ ማሰናበቱ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ትርጉም ስህተት ተፈጽሟል ወይ? የሚለዉን አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለዉ ተጠሪዎች ላይ የቀረበዉ ክስ የወንጃል ህግ አንቀጽ 453/2/ ተላልፈዉ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት ቀርበዉ በመለወጣቸዉ ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል በመስጠት ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ነዉ፡፡የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ ተከሳሾች ደን ሲቆርጡ አይተናል ብለዉ መስክረዉ ፍርድ ቤት ቀርበዉ አላየንም በማለታቸዉ ሁለቱን የምስክርነት ቃል በማነጻጸር ልዩነት መኖሩን አረጋግጦ ፍርድ ቤት ቀርበዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል በሚል በተከሰሱበት አንቀጽ ስር የጥፋተኛነት ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን ዉሳኔ የሻረዉ በዋናነት የማስረጃ ምዘና መሰረት አድርጎ ሳይሆን የፖሊስ ተቋም የወንጀል ምርመራ ስራ በወንጀል ህግ አንቀጽ 453 ድንጋጌ መሰረት የዳኝነት ነክነት በሚለዉ ትርጉም የሚሸፈን መሆን አለመሆኑን በመመርመር ስለመሆኑ ከዉሳኔዉ ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም በዚህ ችሎት ሊመረመር የሚገባዉ ነገር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት  የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ስራ የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት በሚለዉ ሐረግ የሚሸፈን አይደለም በማለት የሰጠዉ ትርጉም አግባብነት ላይ ነዉ፡፡እንደሚታወቀዉ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስራ ዉስጥ የፖሊስ ተቋም በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ እንደሆነ እሙን ነዉ፡፡ከፖሊስ ተቋም ዋነኛ ተግባር ዉስጥ ወንጀልን መከላከል እንዲሁም ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ተገቢዉን ምርመራ ማድረግና ወንጀለኛዉን አድኖ ለህግ በማቅረብ ብሎም  ፍርድ ማሰጠት እንዲሁም ፍርዱን ማስፈጸም ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ተግባርና ሃላፊነት ስለመሆኑ የፖሊስ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጆችና የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነዉ፡፡ስለሆነም በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዓት ዉስጥ የፖሊስ ተቋም ሚና ከፍተኛ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን ከቀረበዉ ክርክር አንጻር ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ የሰጡትን የምስከርነት ቃል በፍርድ ቤት ቀርበዉ ለዉጠዋል በሚል ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል የሚለዉ የአቃቤ ህግ ክስ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 453 ስር የሚሸፈን መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲረዳን የድንጋጌዉ የተቀረጸበትን ሃይለቃል ማየት ይገባል፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/1/ ላይ የተደነገገዉ ‹‹የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሰዉ ማንኛዉንም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሀሰተኛ ምስክርነት ወይም ልዩ አዋቂነት አስተያት የሰጠ እንደሆነ ወይም እዉነቱን የደበቀ እንደሆነ ሀሳቡ ከግቡ ባይደርስም ...››  በዚህ ደንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብሎ እንደሚቀጣ እንዲሁም የተፈለገዉ ዉጤት የተገኘ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ ሁለት ስር በተደነገገዉ አግባብ የሚቀጣ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡የእንግሊዝኛዉ ቅጂም እንዲህ ይነበባል፡፡‹‹453/1/ whoever being a witness in **judicial** or **quasi-judicial proceeding**  knowingly makes or gives a false statement or expert opinion or hides the truth whether to the advantage or the prejudice of any party thereto…>>.በሚል ይገልጻል፡፡

በዚህ ድንጋጌ ዉስጥ ከተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ መሰረታዊ ፍሬነገሮች ዉስጥ አከራካሪ ሆኖ የቀረበዉ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት የሚለዉ ሃይለቃል የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ስራን ያካትታል

ወይ የሚለዉ ነዉ፡፡ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ‹‹ዳኝነት›› እና ‹‹ዳኝነት ነክነት›› ለሚለዉ ቃል ትርጉም መፈለግ ግድ ይላል፡፡የእነዚህ ቃላት ትርጉም በሀገራችን የህግ ኮዶች ወይም መዝገበ ቃላት ላይ በቀጥታ ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ተመሳሳዩን የእንግሊዘኛ ትርጉም መመልከት ተመራጭ ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህ ረገድ ታዋቂዉ የህግ መዝገብ ቃል BLAKS LAW DECTIONARY ላይ እንደተተረጎመዉ፡-

‹‹JUDICIARY-the branch of government invested with judicial power›› በማለት ትርጉም የሰጠ ሲሆን ‹‹QUASI-JUDICIAL ..hold hearings, weigh evidence; and draw conclusions from them, as basis for their official action, and to exercise discretion of judicial nature>>.በሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የመጀመሪያዉ የዳኝነት ስራ የሚያከናዉን የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አንደኛዉ የመንግስት አካል ወይም መደበኛዉን ፍርድ ቤት የሚያመለክት ሲሆን የዳኝነት ነክነት ስራ የሚካሄድበት ደግሞ በዳኝነት መልክ ወይም መሰል ሁኔታ ክርክር የሚሰማበት፣የቀረበለት ማስረጃ ተመዝኖ ከድምዳሜ የሚደረስበትና የበኩሉን ዉሳኔ የሚሰጥበት ሂደት የሚከናወንበት ተቋም የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ ረገድ ተጠቃሽ የሆኑት ተቋማት እንደግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፣የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ቦርድ፣ የግለግል ተቋማትና ሌሎችም መሰል ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸዉ አስተዳደራዊ ተቋማት ስለመሆናቸዉ ሀገራችንን ጨምሮ የተለያዩ ሀገሮች ልምድ ያመላክታል፡፡ ይህ በዘርፉ በተደረጉ ጥናቶችና በርካታ ጽሁፎች ላይም የሚጠቀስ ነዉ፡፡ ከዚህም ባሻገር የተሻሻለዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሀተታ ዘምክንያት ላይ እንደተመለከተዉ ቀደም ሲል ስራ ላይ የነበረዉ የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 447 ስር ሀሰተኛ ምስክርነትን አስመልክቶ የተደነገገዉ ያስተዳደር ፍትሐ ብሔር፣የወንጀል ወይም የሽምግልና ዳኝነት፣ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስነስርዓት የሚፈጸምበት በሚል የተዘረዘረዉ የተንዛዛ በመሆኑ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት በሚል በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453 ስር ተሻሽሎ የቀረበ ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ከዚህም አንጻር ሲታይ የወንጀል ምርመራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ስር እንዲሸፈን ያልተደረገ ስለመሆኑ ነዉ፡፡

www.abyssinialaw.com

ሲጠቃለል የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት የሚለዉ ሀረግ ጥቅል ትርጉም ዳኝነት መሰል ተግባር የሚከናወንበት ሂደት የሚያመላክት ሲሆን በህጉ የተለየ ሁኔታ ካልደነገገ በስተቀር በስነስርዓት ህጉ በተደነገገዉ አግባብ ክርክር የሚመራበትና ምስክርም ሲሰማ እዉነትን ለመመስከር ቃለመሃላ ፈጽሞ ቃሉን የሚሰጥበት አካሄድ የሚከተል መሆኑን መገንዘብ አዳጋች አይደለም ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ በፖሊስ በወንጀል ምርመራ ወቅት ምስክሩ የሚሰጠዉ ቃል ልክ እንደመደበኛዉ የዳኝነት አካል ወይም የዳኝነት ነክነት ወይም መሰል ተቋም ቃለ መሃላ ፈጽሞ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ካለመሆኑም በተጨማሪ ምስክሩ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል እና በፍርድ ቤት የሰጠዉ የምስክርነት ቃል መካከል ልዩነት በተፈጠረ ጊዜ በፖሊስ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል እዉነት ነዉ ነገር ግን በፍርድ ቤት የሰጠዉ የምስክርነት ቃል ሀሰት ነዉ ለማለት የምስክሩ ቃል መለያየት ብቻዉን በቂ ማስረጃ ነዉ ብሎ ለመዉሰድ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፡፡በእርግጥ አንድ ምስክር ለፖሊስ የሰጠዉን ቃል ፍ/ቤት ሲቀርብ ከቀየረ ከሁለቱ አንዱ የሀሰት ቃል መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ሆኖም አመልካች ክስ ከመመስረቱ በፊት ከሁለቱ ቃሎች መካከል የሀሰት ቃል የትኛዉ እንደሆነ በትክክል በሌላ ማስረጃ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉም ጉዳይ ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡት የምስክርነት ቃል እዉነተኛ የሆነዉን ለዉጠዉ በፍርድ ቤት ቀርበዉ የሀሰት የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል በማለት አቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ መሰረት በማደረግ ያቀረበዉን ክስ ለማስረዳት ያቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪዎች በፖሊስ ምርመራ ላይ የሰጡት ቃል እና በፍርድ ቤት የሰጡትን ቃል በማነጻጸር እንደመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረዉ አማራ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድንጋጌዉ በፖሊስ የወንጀል ምርመራ ሂደት የተሰጠን የምስክርነት ቃል በቀጥታ ከፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል በማነጻጸር የኋለኛዉ የሀሰት ቃል ነዉ ለማለት በፖሊስ የተሰጠ ቃል የዳኝነት ነክነት ከሚለዉ የሚያጠቃለል አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ላይ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/17096 በ05/10/09 ዓ.ም የሰተጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/70512 ላይ በ26/03/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/195/2/ለ/2 መሰረት ጸንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 149071

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች፡-** የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ

**ተጠሪ፡-** አቶ አሰግድ አባ ቦሬ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 003731 በቀን 27/10/2009 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 145134 መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ አቅርቧል ይዘቱም፡- አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ ግንቦት 23 ቀን 2008 ዓ/ም በግምት ከጥዋቱ 4:30 ሰዓት አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ካቴድራል ት/ቤት ተብሎ ከሚጠራ አካባቢ ለግል ተበዳይ አቶ ጊቱ ተፈራ ቁጥሩ 20552352 የሆነ እና ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ

www.abyssinialaw.com

በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የሚመነዘር የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፈርሞ ከሰጠው በኋላ የግል ተበዳይ በ02/03/2009 ዓ/ም ቼኩን ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የለውም በመባሉ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶት ተቃውሞ እንደሌለው ገልፆ፣ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ደርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የአመልካች ምስክሮች እንዲሰሙ ባዘዘው መሠረት ምስክር ቀርበው በሰጡት የምስክርነት ቃል ተጠሪ በ23/09/08 ዓ/ም 4፡00 ሰዓት ላይ ካንትሪ ታወር የግል ተበዳይ ቢሮ ውስጥ 5ኛ ፎቅ መጥቶ ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የሚመነዘር የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፈርሞ ከሰጠኝ በኋላ ለመመንዘር ባንክ ስሄድ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ባንክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የሌለ መሆኑን የተለገፀላቸው መሆኑን መስክረዋል ፣ አመልካች በፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ቃል እና ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል በሰጠው ብይን ተጠሪ የመከላከል ምስክሮች አቅርቧል፡፡ ምስክሮቹም ተከሳሽ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መስክርዋል፡፡ተከሳሽ እና የግል ተበዳይ የሚያደርጉት የንግድ ግንኙነት በዱቤ ሽያጭ መሆኑ ሰነድ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው ስለሆነና ቼኩን የሰጠው በመተማመኛ መልኩ እንጂ የሚመነዘር አለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ቼኩ በቸልተኝነት የተሰጠ ነው በማለት የቀረበበት ክስ ፍርድ ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113 መሰረት በመቀየር ተከሳሽን በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(2) ስር ጥፋተኛ በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ተከሳሽን፡፡ በስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት

www.abyssinialaw.com

ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ29/02/2010 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ፡- ተጠሪ በወ/ህ/ዓንቀፅ 693(1) መሰረት ጥፋተኛ ሊባል ሲገባው በቸልተኝነት የተፈፀመ ሊያስብል በወ/ህ/ዓንቀፅ 59 መሰረት የሚያሳይ ማስረጃ ሳይኖር በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(2) ስር በመቀየር የስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተሽሮ ተጠሪ በተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቅጣት እንዲሰጥበት አመልክቷል ፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርቦ በፅሁፍ መልስ እንዲሰጥ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ መልስ በፅሁፍ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የአሁኑ ተጠሪ ቼኩን ለግል ተበዳይ የሰጡት በነበራቸው ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዲሁም የዱቤ ሽያጭ ቼክ ይሰጥ የነበረው በመተማመኛ መልኩ እንጂ የሚመነዘር አለመሆኑ ተመስክሯል ተብሎ በክሱ ላይ የተመለከተውን ወ/ህ/ዓንቀፅ 693(1) ወደ በወ/ህ/ዓንቀፅ 693(2) በመቀየር ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው በማለት የተወሰነበት አግባብነት ለመመርመር ሲሆን ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ለግል ተበዳይ ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ የሚመነዘር በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፈርሞ የሰጠ መሆኑ የግል ተበዳዩ ለመመንዘር ባንክ ስሄድ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ባንክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የሌለ መሆኑን የተለገፀላቸው መሆኑን ፣ ተጠሪ በፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ቃል እና ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

የተጠሪ የመከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ተከሳሽ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያለቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መመስከራቸው ነው፡፡ ይህንን የተረጋገጠው ፍሬነገር መነሻ በማድረግ መርምረናል፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ፍ/ቤት ማስረጃ በመመዘንና ፍሬነገር በማጣራት ሥልጣኑ በደረሰበት ደምዳሜ ተጠሪ ለግል ተበዳይ ቼክ ፈርሞ መስጠቱ ሳይክድ ለዋስትና ነው የሰጠሁት በማለቱ ፍርድቤቱ ይህ የተከሳሽ እና የግል ተበዳይ ጋር ያለው የግል ግንኙነት መነሻ በማድረግ ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው በማለት ተጠሪ የተከሰሰበትን የህግ ዓንቀፅ በመቀየር የጥፋተኛ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የተያዘው ጉዳይ አመልካች ባቀረበው ክስ ተጠሪ በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ፍርድቤቱ ተከሳሽ ፈፀመ የተባለው ወንጀል ሆነ ብሎ ሳይሆን በቸልተኝነት ነው ለማለት እንደምክንያት የወሰደው ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያለቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ ይህንን የወንጀል ድርጊት የፈጸመዉ በቸልተኝነት ነዉ ለማለት በወ.ሕ.ቁ.59 /1/ መሰረት ቸልተኝነት መኖሩን የሚያሚሉ ወይም የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች በሥር ፍ/ቤት አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ስለሆነም ተጠሪ የፈፀመው የወንጀል ተግባር በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው ወይስ ሆነ ብሎ የተፈፀመ ነው የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት የተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ የወ.መ.ህግ ቁጥር 693/1/ን በምንመለከትበት ጊዜ ርዕሱ “የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት“ የሚል ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ሥር የተደነገገው ማንም ሰው ቼክ በሚያወጣበት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ / እንደሆነ በሚል ተደንግጓል፡፡

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(1) ሥር የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል ለማቋቋም እንደመስፈርት የተወሰዱት አንደኛው ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በሰጪ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቼኩ የተጠቀሰውን መጠን ገንዘብ

ለመክፈል የሚያስችል የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቼኩ ማውጣቱ አልተካደም ቼኩ በወጣበት ጊዜ ይሁን በግል ተበዳይ ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ስለመኖሩ ያቀረበው ክርክር የለም ፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበት የህግ አንቀፅ በመቀየር ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው ለማለት የቻለው ተጠሪ ቼኩ የተሠጠው ለባንክ ቀርቦ እንዲመነዘር ሣይሆን በተከሳሽ እና ተበዳይ መካከል ባለው  የብድር ግንኙነት ለዋስትና መያዣ መሰረት ተደርጎ ቼክ በገደብ የተሠጠ ነው በማለት መሆኑ ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

ይህ የሁለቱም ግንኙነት በፍትሃብሄር ክርክር ላይ ቼክ ለክፍያ ሲቀርብ  (ገንዘብ ሲጠየቅ) ሊቀርቡበት ከሚችሉት መቃወሚያዎች አንዱ ቢሆንም ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ እያወቀ ቼክ የሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ እና  ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቼኩ የተጠቀሰውን መጠን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩ እስከተረጋገጠ ድረስ የተፈፀመው ወንጀል ሆነ ብሎ የተፈፀመ እንጂ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው የሚባል አይደለም ፡፡ ስለሆነም በቼክ አውጪው እና ተቀባዩ የሚኖረው ግላዊ ግንኙነት  መሰረት በማድረግ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 67947 በሰጠው ገዥ (አሳሪ) የሕግ ትርጉም ቼክ በወንጀል ጉዳይ እንደዋስትና ተሰጥተዋል በማለት እንደመከላከያ ሊቀርብ እንደማይችል ፍርድ ሰጥተዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተሰጠ በተባለው ቼክ ለማን እንደሚከፈል ከየትኛው ባንክ እንደሚከፈል እንዲሁም ተጠሪ ፈርሞ የገንዘብ መጠኑ ተገልፆ የተሰጠ እና ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ እያወቀ ቼክ የሰጠ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሹ ባላቸው የግል ግንኙነት መሰረት በማድረግ ብቻ ወንጀሉ የፈፀመው በቸልተኝነት ነው ለማለት አይቻልም ፡፡ ምክንያቱም ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸመበት ሕጋዊ ሰነድ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ሕግ አውጭው በቼክ ላይ የሚፈፅመው ወንጀሎች ሕጋዊ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ በግልፅ ከመደንገጉ በተጨማሪ ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈፅምበት ምንም ቅድመ ሁኔታ የማይቀመጥበት ሰነድ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል ፡፡  ከዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን አመልካች የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ / መሆኑና ቼኩን ለክፍያ ተበዳይ ሲያቀርበውም በቂ ገንዘብ

የለውም ተብሎ መመለሱን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰዉ ምስክሮች ቃል እና የሰነድ ማስረጃ በመመዘን በበቂ ሁኔታ እንደ ክሱ ያስረዱ መሆናቸዉን በማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ እንዲከላከል ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ባላስተባበለበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበትን የህግ አንቀፅ በመቀየር የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(2) ጥፋተኛ ማለቱ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(1) እንዲሁም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23፤59 የተመለከተውን የህግ ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በቀረበበት ክስ በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኛ ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ የሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ የተቀየረ በመሆኑ በዚሁ አግባብ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሊስተካከል ይገባል ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለው ወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) በመሆኑ ቅጣቱ ሊሰላ የሚገባው ጥፋተኛ በተባለበት የህግ ድንጋጌ ነው ፡፡ተጠሪ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት የህግ ድንጋጌ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የወንጀል ደረጃና እርከን የወጣለት ስለሆነ የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) በመሆኑ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከኑ 23 የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከኑ 6 ይሆናል፡፡

በከሳሽ (አመልካች) በኩል የቀረበ እና በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ማክበጃ ስለሌለ የቅጣት እርከኑ ከተያዘው መነሻ እርከን ከፍ አላለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የቀድሞ ሪከርድ የሌላቸው መሆኑ እና ቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ የተያዘላቸው በመሆኑ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከኑ ከእርከን 23 ወደ እርከን 21 እንዲሁም የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከኑ ወደ እርከን 4 ዝቅ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም በእርከን 21 ስር ባለው ፍቅድ ስልጣን ከ5 አመት እስከ 6 አመት ስለሆነ ተጠሪ ጥፋተኛ በተባለበት የህግ ድንጋጌ ያስተምረዋል የተባለውን የአምስት አመት ፅኑ እስራት እና የአራት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ላይ የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 003731 ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሳኔ ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14134 መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም. የፀናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ክስ በቀረበበት የህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ሁሉ የሚታሰብላቸው ሆኖ በአምስት አመት ፅኑ እስራት እና በአራት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪ በሚገኙበት በመያዝ ለሚመለከተው ማርሚያ ቤት እንዲያስረክብ ፣ ማረሚያ ቤቱም ከፌዴራል ፖሊስ ተረክቦ ተጠሪን በጉዳዩ ላይ ቀድሞ የታሰሩበት ጊዜ ካለ ታሳቢ በማድረግ የተወሰነውን የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣትን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ የገንዘብ ቅጣቱ የሚመለከተው የፋይናንስ ክፍል ያስፈፅም ብለናል ፡፡ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ሠ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ 150803

ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ-አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ንጉስ ሀይሉ-አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪው የአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 35/1/ለ ድንጋጌን በመተላለፍ ማንም ሳይፈቅድለት በቀን 06/07/08 ዓ.ም ከቀኑ 10:00 ሠዓት በሐወልቲ ክፍለከተማ ቀጠና 10 ስፋቱ 11.28 ሜ$^2$ የሆነ የመንግሥት መሬት ጨምሮ ቤት ስለሰራበት በፈጸመው የከተማ ቦታ ያለአግባብ መያዝ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐወልቲ ፍ/ቤት ተጠሪን በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኘው ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 በማስላት በሠባት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 40,000 / አርባ ሺህ ብር / የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ የሰሩትን የድንጋይ አጥር እንዲያፈርሱ በቃል የተነገራቸው ከመሆኑ በቀር የተሰጣቸው

www.abyssinialaw.com

የ7 ቀን የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ የለም፤አዋጁ የሰባት ቀን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መሰጠት እንዳለበት የሚደነግግ ሆኖ ሳለ እና ተጠሪ በቃል በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት የሰሩትን የድንጋይ አጥር አፍርሰው ሳለ የሥር ፍ/ቤት በአዋጁ የተቀመጠው ማሥጠንቀቂያ የመስጠት ቅድመሁኔታ ባልተሟላበት ሁኔታ የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን በነጻ አሰናብቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶቸ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው የቀረበላቸው ፍ/ቤቶች የሥር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አስቀድሞ የመሬት ወረራ ወንጀል ለመስራት አስቦ መሬትን የወረረ ሰው ማሥጠንቀቂያ ካልተሰጠው በቀር በወንጀል ጥፋተኛ ሊባል አይገባም የሚል ድንጋጌ በአዋጁ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው የሥር ፍ/ቤቶች ለተጠሪ ማሥጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ምክንያት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን ተጠሪ የከተማ ይዞታውን የያዘው ከሕግ ውጪ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 721/04 አንቀጽ 27 መሠረት ማሥጠንቀቂያ ባልተሠጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዋጁ አንቀጽ 26/4 እና 27/2 የተቀመጠው ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ በአዋጁ አንቀጽ 35/1/ለ የተቀመጠው ቅጣት ክብደት አኳያ ተጠሪን የመሰሉ ሰዎች ማስጠንቀቂያ በመስጠት አሥተዳደራዊ መፍትሔ ለማምጣት እና በማስጠንቀቂያ ከተግባሩ እንዲቆጠብ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ በመገንዘ ተጠሪን በነጻ ማሰናበታቸው ተገቢ ነው፤ይህ የሚታለፍ ከሆነም ተጠሪ ለጊዜው የሰራሁትን አጥር ያፈረስኩ እና የፈጸምኩት ተግባርም ቀላል ስለሆነ ጥፋተኛ ልባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 686/1 ከመግሥት ፈቃድ ውጪ የመንግሥትን ቦታ መያዝ ወንጀል በሚል ሊሆን ይገባል፤ይህ የሚታለፍ ከሆነም ይዞታው ከባለቤቴ ይዞታ

አጠገብ የሚገኘውን ቦታ ክረምቱ እስኪያልፍ በሚል ለማገዶ የተሰራ እንጂ ቦታውን ለማካተት ስላልሆነ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ቅጣቱም ቀሎ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ ሲባል እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ተጠሪ የአዋጁን አንቀጽ ከአዋሳኛቸው ጎን ያለውን የመንግሥት ቦታ ወደ ራሣቸው ይዞታ በመቀላቀል የድንጋይ አጥር የሰሩበት መሆኑ በወረዳው ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 35/1/ለ ማንም ሰው አዋጁን ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የከተማ ቦታን አጥሮ ከያዘ ግንባታ ካካሄደበት ወይም ከአዋሳኝ ይዞታው ጋር ከቀላቀለ ከሠባት እሥከ አሥራ አምሥት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 40,000 እሥከ 200,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 26/1 አግባብ ያለው አካል ከቦታው ለሚነሳው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ የከተማ ቦታ ይዞታን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የማስለቀቅ እና የመረከብ ሥልጣን ይኖረዋል በማለት ይነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 4 አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል በማለት ይደነግጋል፡፡

የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሰሩትን የድንጋይ አጥር እንዲያፈርሱ በቃል የተነገራቸው ከመሆኑ በቀር የተሰጣቸው የ7 ቀን የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ የለም፤በአዋጁ አንቀጽ 26/4 ላይ የተቀመጠው የሰባት ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ ባልተሟላበት ሁኔታ እና ተጠሪ በቃል በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት የሰሩትን የድንጋይ አጥር ባፈረሱበት ሁኔታ ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ አይደለም ከሚል

www.abyssinialaw.com

መደምደሚያ ላይ የደረሱ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ 26/4 ላይ አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል በማለት የተቀመጠው ሀሳብ በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት በሕጋዊ መንገድ ለተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስለቀቅ የተቀመጠውን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የመስጠት እና ካሣ የመክፈል ሥርዓት ማሟላት ሳያስፈልግ በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን ማስለቀቅ የሚቻልበትን ሥርዓት የሚደነግግ እንጂ የከተማ ቦታን ወሮ ለያዘ ሰው የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስቀር አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የአዋጁን አንቀጽ 26/4 ድንጋጌን ያለአግባብ በመተርጎም ለተጠሪ የተሰጠው የሰባት ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመቐለ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20165 ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 88023 ግንቦት 02 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 98220 ጥቅምት 10 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የሐወልቲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07743 ሠኔ 01 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

**-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰበር መ/ቁ/151034

ጥቅምት 28 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አማረ ረታ

ተጠሪ፡- የፌደራል ጠ/አቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በወንጀል ጉዳይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ የወጣዉ ህግ ተከሳሹን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ እንዴት ይፈጸማል የሚል ነዉ፡፡ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ አመልካች በጉሙሩክ አዋጅ ቁ/622/01 ስር ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ዉሳኔ ተላልፎበት በማረሚያ ቤት ቅጣቱን እየፈጸመ እያለ አዲስ የወጣዉ የጉሙሩክ አዋጅ ቁ/859/06 ለተመሳሳይ ጥፋት የደነገገዉ ቅጣት አመልካችን የሚጠቅም ስለሆነ በአዲሱ አዋጅ መሰረት ቅጣቱ እንዲታይለት ለፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ ተቀባይነት ባለማግኘቱና ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በማጽናቱ ነዉ፡፡

የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ አመልካች አዋጅ ቁ/622/01 አንቀጽ 95/1/ሐ/እና 2 በመተላለፍ እሽጎችን መፍታትና ምልክቶችን ማንሳት እንዲሁም አንቀጽ 101/3 በመተላለፍ የማጓጓዝ ሃላፊነት ባለመወጣት ጥፋተኛ ተብሎ በፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በ16,000ብር እና 24 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ስለመወሰኑና በዚህ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን

www.abyssinialaw.com

ብቻ በማሻሻል18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑን ፣ይህንኑ ቅጣት እየፈጸመ እያለ አዲስ የወጣዉ አዋጅ ቁ/859/06 በዚህ ጉዳይ ከቀድሞ አዋጅ ያነሰ ቅጣት የሚያስቀጣ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 22/2/ መሰረት አዲሱ አዋጅ ተፈጻሚ እንዲሆን አቤቱታ ማቅረቡንና የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ተቀብለዉ ቅጣቱን ማሻሻል ሲገባቸዉ አቤቱታዉን አናስተናግድም ማለታቸዉ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩን ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 22/2/ እና ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 6 እና 9 እንዲሁም ከአዋጅ ቁ/859/06 አንቀጽ 170 እና 171 አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ አቃቤ ህግ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡በአቃቤ ህግ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በአዲሱ አዋጅ መሰረት መነሻ ቅጣቱ ተከሳሽን የሚጠቅም መሆኑ ታይቶ ማሻሻያ ቢደረግለት ተቃዉሞ እንደሌለዉ ገልጿል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በወንጀል ጉዳይ የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ የሚደረገዉ መቼ ነዉ እንዲህ ዓይነት አቤቱታስ እስከ መቼ መቅረብ ይችላል የሚሉት ነጥቦች መታየት ያለባቸዉ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ በሀገራችን ህገ መንግስት እና በወንጀል ህግ በግልጽ የተደነገገ ከመሆኑም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተደንግጎ የሚገኝ አለም አቀፍ ቅቡልነት ያለዉ መርሆ መሆኑ ይታወቃል፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህገ መንግስት አንቀጽ 22 /1/፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ህግ አንቀጽ 5 እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ15/1/ይመለከታል፡፡ከዚህ መርህ ልዩ ሁኔታ ተብሎ የተደነገገዉ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣዉ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣዉ ሰዉ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣዉ ህግ ተፈጻሚ እንዲሆን የማድረግ ጉዳይ ነዉ፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ22/2/፣የወንጀል ህጉ አንቀጽ 6 እንዲሁም የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 15/1 ሁለተኛ ፓራግራፍ ይመለከታል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ህጉ ተከሳሽን መብትና ጥቅም በተሻለ ሁኔታ ማስከበርን መሰረት ያደረገ

ስለመሆኑና በወንጀል ጉዳይ ህግ መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተከሳሽን በሚጠቅም አኳኋን ሊተረጎም ይገባል የሚለዉን ቅቡልነት ያለዉ የወንጀል ህግ አተረጓጎም መርህ የተከተለ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህም ቅጣትን በሚመለከት አዲሱ የወንጀል ህግ ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ወንጀል ከተፈረደበት እና ሆኖም ግን ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ ከነበረው ወንጀል ህግ ይልቅ አዲሱ ህግ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቀልለትና ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ይሄው በአዲሱ ህግ ላይ ያለው ቅጣት የሚፈጽምበት ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ ቁ. 6 ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝብ ስለመሆኑ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 95438 ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡በሌላ በኩል አዲስ የወጣዉ ህግ የቀድሞዉን ህግ የሻረዉ እንደሆነና በቀድሞ ህግ ወንጀል የነበረዉ ድርጊት በአዲሱ ህግ ይኸዉ ድርጊት ወንጀልነቱ ቀሪ ከሆነ ወይም የማያሥቀጣ ከሆነ በቀድሞ ህግ ተፈርዶበት ቅጣቱ እንደማይፈጸም ወይም እየተፈጸመ ከሆነም ቅጣቱ አፈጻጸም ወዲያዉኑ እንደሚቋረጥ የወንጀል ህግ አንቀጽ 9/1/ በግልጽ ደንግጓል፡፡

ስለሆነም ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ኂላ የወጣዉ የወንጀል ህግ ተከሳሹን ወይም የተቀጣዉን ሰዉ የሚጠቅም መሆን አለመሆኑ መመዘኛ ተደርጎ መታየት ያለበት ስለመሆኑ ነዉ፡፡ኂላ የወጣዉ ህግ የቀድሞዉን ህግ በመሻር የድርጊቱን ወንጀልነት ቀሪ በማድረጉ በቀድሞ ህግ የተሰጠዉ ፍርድ ቀሪ ነዉ በሚል በግልጽ ህጉ ደንግጎ እያለ ኂላ የወጣዉ ህግ ቅጣት ማቅለሉን መሰረት በማድረግ ተቀጪዉ ያቀረበዉ አቤቱታ ሊስተናገድ አይገባም የሚለዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22/2/ እና የወንጀል ህጉን ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 6 ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ጉዳይ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ተከሳሹ ወይም ተቀጪዉ አቤቱታ ማቅረብ የሚጠበቅበት የጊዜ ገደብ መኖር አለመኖሩ ላይ ነዉ፡፡በመሠረቱ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ለይግባኝ ማቅረቢያና ተያያዥ ጉዳዮች የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥም ፍርድ አግኝቶ የተዘጋ መዝገብ በኃላ እንደገና መከፈቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በምን ያህል ጊዜ ዉስጥ አቤቱታ ሊቀርብበት እንደሚገባ በሕግ የጊዜ ገደብ አልተቀመጠም፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት የጊዜ ገደቡ የሚወሰነዉ የጉዳዩን ሁኔታዎችና የአቤቱታዉን ዓይነት በመመልከት እንጂ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ የቀረበዉ አቤቱታ

www.abyssinialaw.com

ተቀባይነት የለዉም በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ አይደለም፡፡ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2)፣ የወ/ሕ/አንቀጽ 6 እና 9(1)ን መሠረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ በባህሪዉ እንደመደበኛ የክርክር ጉዳይ የሚታይ ሳይሆን አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚችል መሆኑን ህጉ ግልጽ የጊዜ ገደብ አለማስቀመጡ የሚያሳይ ነዉ፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በቀድሞ የጉምሩክ አዋጅ ቁ/622/01 አንቀጽ 95/1/ሐ እና 2 እንዲሁም አንቀጽ 101/3/ በተደራራቢ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነትና የቅጣት ዉሳኔ ተሰጥቶ ቅጣቱን በመፈጸም ላይ እያለ አዲስ የወጣዉ የጉምሩክ አዋጅ ቁ/859/06 አንቀጽ 170እና 171 የድርጊቱን አስቀጪነት እንዳለ ይዞ ነገር ግን ቅጣቱን በማሻሻሉ አመልካች የኀለኛዉ ህግ ይጠቅመኛል በሚል ለስር ፍርድ ቤት አቤቱታ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱ እንዲህ ዓይነት አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከላይ በዝርዝር የተመለከተዉን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ እና የወንጀል ህጉን ዓላማና ይዘት ያላገናዘበ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1ኛ/የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/81283 ላይ በ06/04/2008 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/002346 ላይ በ20/03/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በመሰረዝ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ተመርምሮ ተገቢዉ ዉሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡን በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/195 /2/ሀ መሰረት ለፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት መልሰናል ፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

የሰበር መ/ቁ/158613

ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ማስተዋል ሰፈረ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ አማራ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ተጠሪ ለችሎት ስራ እንቅፋት ሆናለች በማለት ጥፋተኛ ናት በሚል የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይህም ከማህደሯ ጋር እንዲያያዝ ትእዛዝ በመስጠቱ እና አመልካች ይህንን ትእዛዝ ለማስለወጥ አቤቱታ በማቅረቧ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ አግባብነት ከወንጀል ህግ አንቀጽ 449 አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበ ነዉ፡፡

እኛም የቀረበዉን አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ ይዘት እና አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ፍርድ ቤቱ ለትእዛዙ መሰረት ያደረገዉ መነሻ ምክንያት አመልካች የፍርድ ቤቱ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆና ለዳኞች የሚሰጥ የሞባይል ካርድ ለዳኞች ቢሮ ድረስ ለማቅረብ ፈቃደኛ አልሆነችም በሚል ምክንያት ጉዳዩን ችሎት ቀርባ እንድታስረዳ ስትጠራም ችሎት ለመቅረብ እምብተኛ ከመሆኗም በተጨማሪ በፖሊስ ተጠርታ ስትቀርብም ተገቢዉን ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኗ ለችሎት ስራ እንቅፋት ሆናለች በሚል ምክንያት

www.abyssinialaw.com

የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣትና ከማህደሯ እንዲያያዝ ትእዛዝ ስለመስጠቱ ገልጧል፡፡ችሎቱ ይህንን የቅጣት ዉሳኔ ሲሰጥ የህግ መሰረቱ ግልጽ ባለመሆኑ አከራካሪ ሆኖ ቀርቧል፡፡ለዚህም ነዉ በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 449 አንጻር አግባብነቱን መመርመር ያስፈለገዉ፡፡

በመሰረቱ የዳኝነት ስራ አካሄድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ዓይነትና ቅጣታቸዉ የሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 443 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ እንደተመለከተዉ እንደጉዳዩ ባሕርይና ጥፋት ዓይነት ቅጣት የሚጣልበት ሲሆን በተለይ ችሎት መድፈርን አስመልክቶ ችሎቱ በያዘዉ መዝገብ ላይ ወዲያዉኑ ቅጣት ሊወስን የሚችልበት አግባብ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 449 እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/480 እና 481 በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትም ሲታይ የዳኝነት ስራ በማከናወን ያለዉን ዳኛ በማናቸዉም መንገድ ማወክ፣መስደብ ፣ማፌዝ፣ መዛትና በመሰል ሁኔታ እንቅፋት መፍጠር እንዲሁም የዳኝነት ስራ አካሄድ ስነስርዓት አለማክበር፣ለችሎቱ ክብርና ለዳኝነት ስራ መልካም አመራር ተቃራኒ የሆነ ጠባይ የሚያሳይ ማንኛዉም ሰዉ ፣ የችሎት ተግባርና ስራ የሚያደናቅፉና ተገቢዉን ክብር ለማይሰጡ ለማይታዘዙና ተገቢዉን ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆን የችሎቱን ስራ የሚያደናቅፍን ማንኛዉም ሰዉ በዚያዉ መዝገብ ወዲያዉኑ ተገቢ ቅጣት መጣል የሚያስችል ነዉ፡፡የነዚህ ድንጋጌዎች ዋነኛ ዓላማ የችሎቱን ስራ አካሄድ በማስከበር ያለእንቅፋት የዳኝነት ስራዉን ማሳለጥ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በዚህ መዝገብ ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የሞባይል ካርድ ለችሎቱ ዳኞች የማቅረብ አስተዳደራዊ ግዴታ ወይም የስራ ሃላፊነት አልተወጣችም በሚል ምክንያት ወደ ችሎቱ እንድትጠራ መደረጉ የተገለጸ ሲሆን ከጅምሩ አስተዳደራዊ የስራ ሃላፊነት አለመወጣት አለ ከተባለ በአስተዳደራዊ ስነ ስርዓት ጉዳዩ ተጣርቶ ተገቢዉ እንዲወሰን ማድረግ እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ከዚህ አልፎ ግን ችሎቱ ምክንያቱን ለመገንዘብ ፈልጎ ወደ ችሎት እንድትቀርብና ተገቢዉን ምላሽ እንድትሰጥ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ አመልካች ችሎት ቀርባ የችሎቱን ትእዛዝ አልቀበልም ማለቷ እንዲሁም ለችሎቱ ተገቢዉን ክብር አለመስጠቷ ከተረጋገጠ እና ችሎቱ ይህ ተግባሯ ጥፋት ነዉ ብሎ ካመነበት ቅጣት ሊወስን የሚችለዉ ለድርጊቱ ማቋቋሚያ ድንጋጌ በመለየት በወ/ህጉ

አንቀጽ 443 ወይም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 480 ወይም 481 በተደነገገዉ አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡ከዚህ ዉጪ በህግ በግልጽ ባልተደነገገ አግባብ የሚጣል ቅጣት የህግ መሰረት የለዉም ፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጥና ይህም ከማህደሯ ጋር እንዲያያዝ በማለት የሰጠዉ የቅጣት ዉሳኔ የህግ መሰረት የሌለዉ ስለሆነ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ነገርግን አመልካች የፈጸመችዉ ድርጊት በአስተዳደራዊ መንገድ ተጣርቶ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበት ነዉ ወይስ የችሎቱን ስራ መድፈር ነዉ? በሚለዉ ላይ በመለየት ተገቢና አስተማሪ ዉሳኔ መስጠትን ይህ ዉሳኔ ቀሪ አያደርገዉም ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ትእዛዝ ሰጥተናል፡፡

## ትእዛዝ፡፡

1ኛ/የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ/03-75294 በ11/08/2010 ዓ.ም አመልካች ላይ የሰጠዉ የቅጣት ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

2ኛ/ አመልካች የፈጸመችዉ ድርጊት በአስተዳደራዊ ስነስርዓት ወይም በችሎት መድፈር የሚሸፈን ነዉ የሚለዉን በመለየት ተገቢዉን የመወሰን ጉዳይ ይህ ዉሳኔ ቀሪ አያደርገዉም ብለናል፡፡

3ኛ/ይኸዉ እንዲታወቅ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ይተላለፍ ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 152755

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-**የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ

**ተጠሪ፡-** አቶ አፍራና ሁሌ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273802 በቀን 26/03/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናቱ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ሁለት የተለያዩ መዝገቦች ክስ አቅርቧል፡፡ በመዝገብ ቁጥር 25117 የቀረበው ክስ ይዘቱም፡- አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 692/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሂሳብ ቁጥሩ ዝግ ሆኖ 1,000,000 የሆነ በቼክ ቁጥር BA.712880 የሆነ ብር 1,189,875 የቼክ ቁጥር AB.712880 ሰጥቶ የማታለል ወንጀል ስለፈፀመ ተከሷል የሚል ነው፡፡በመዝገብ ቁጥር 25121 የቀረበው ክስ ደግሞ ይዘቱም፡- አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት በቂ

www.abyssinialaw.com

ገንዘብ ሳይኖረው የብር 535,000 የሆነ ቁጥሩ BA.0776503 ቼክ ፈርሞ ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ እንዲመነዘር ሰጥቶ ቼኩ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተዘጋ መሆኑ የተረገጠ ስለሆነ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶት ተቃውሞ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ የተጠሪ ተቃውሞ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ተጠሪ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ደርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የተጠሪ ምስክሮች እንዲሰሙ ባዘዘው መሠረት የአመልካች ምስክር ቀርበው የግል ተበዳይ እና 2ኛ የዓ/ህግ ምስክር ብር 500,000 በተከሳሽ ሂሳብ ገቢ ያደረጉ መሆናቸው ብር 35,000 በእጁ ከሰጡት በኋላ ቼኩን ፈርሞ የሰጣቸው መሆኑ ተበዳይ ቼኩን በመያዝ ባንክ ሲሄድ ገንዘብ የለውም ስለተባሉ ቼኩን ያስመቱ መሆናቸው ፤ ተጠሪ ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል በሰጠው ብይን አመልካች የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ቀን ያልተፃፈበት ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መስክርዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አመልካች ባንክ በቂ ገንዘብ ሳይኖረው ቼክ የሰጠ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ እና በመከላከያ ማስረጃው ስላልተከላከለ ቼኩ ላይ ቀን ያልተጻፈበት መሆኑ ከወንጀሉ ነፃ አያደርገውም በማለት በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ ነው በማለት ቅጣቱ በመዝገብ ቁጥር 25117 ጋር በማጣመር አስልቷል፡፡ በዚህ መሰረት በመዝገብ ቁጥር 25117 ተጠሪ የተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 692/1/ ጥፋተኛ በማለት በአራት ዓመት ከአምስት ወር እስራት እና በብር ሰባት ሺህ የገንዘብ መቀጮ መነሻ ይዟል፡፡ በመዝገብ ቁጥር 25121 ጥፋተኛ ለተባለበት የህግ ድንጋጌ የስምንት ዓመት ከአምስት ወር እስራት እና በብር አስራ አምስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ መነሻ ቅጣት ይዟል፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበ 3 የቅጣት ማቅለያ በመቀበል ተከሳሽ በስድስት አመት ፅኑ እስራት እና በብር 2,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ መሰረት በማድረግ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ያከራከረ ሲሆን ተጠሪን በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 25117 የስር

www.abyssinialaw.com

ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ቅጣቱን በማሻሻል ተከሳሽ በአንድ አመት ፅኑ እስራት እና በብር 2,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል በመዝገብ ቁጥር 25121 የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር ተከሳሽ በቀረበበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል በነፃ እንዲሰናበት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ17/05/2010 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ፡- ተጠሪ በ1ኛ ክስ በመዝገብ ቁጥር 25117 ላይ የማታለል ወንጀል ክስ ዓንቀፅ 692(1) የስር ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔውን ያፀኑ ቢሆንም ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት እርከን የወጣለት ስለሆነ ደረጃ 8 እርከን 20 ስር የሚወድቅ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እና 4 ማቅለያ መጠቀሙ ስህተት ነው ሊታረም ይገባል ፡፡
2ኛ ክስ በተመለከተ ተጠሪ በቂ ስንቅ ሳይኖረው የግል ተበዳይ ኑረዲን አብዱል ሰመድ የተበደረውን ገንዘብ በቀን 28/08/2008 ዓ/ም ለክፍያ የሚቀርብ ቼክ በቀን 12/02/2008 ፅፎ እንደሰጠ ተረጋግጦ እያለ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት 2ኛ የዓ/ህግ ምስክር ቼኩ የሰጠው ለዋስትና ነው በማለት ምስክርነት ቃል ሰጥቷል በማለት ተከሳሽን በነፃ ማሰናበቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል አቅርበዋል፡፡የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርቦ በፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡በአጣሪው ችሎት የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ ለግል ተበዳይ የሰጠው ቼክ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ የተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተዘጋ እና በቂ ሂሳብ የሌለው መሆኑ በምስክሮች በተረጋገጠበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቼኩ የተሰጠው ለመተማመኛ ነው በማለት በነፃ ያሰናበተበት አግባብ ከወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) አንፃር ለመመርመር ነው ፡፡ እኛም ጉዳዩ እንዲጣራ ከተያዘው ጭብጥ ብቻ

www.abyssinialaw.com

መሰረት በማድረግ መርምረናል ፡፡እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25121 የነበረው ክርክር ሲታይ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖረው የብር 535,000 የሆነ ቁጥሩ BA.0776503 ቼክ ፈርሞ ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ እንዲመነዘር ሰጥቶ ቼኩ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተዘጋ መሆኑ የተረገጠ ስለሆነ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ይህን ክስ ለማስረዳት የቀረቡት የከሳሽ ዓ/ህግ ምስክሮች በበኩላቸው ተጠሪ በቂ ስንቅ ሳይኖረው የግል ተበዳይ ኑረዲን አብዱል ሰመድ እና 2ኛ የዓ/ህግ ማስረጃ ብር 500,000 በተከሳሽ ሂሳብ ገቢ ያደረጉ መሆናቸው ብር 35,000 በእጁ ከሰጡት በኋላ በቀን 28/08/2008 ዓ/ም ለክፍያ የሚቀርብ ቼክ በቀን 12/02/2008 ፅፎ እና ፈርሞ የሰጣቸው መሆኑ ተበዳይ ቼኩን በመያዝ ባንክ ሲሄድ ገንዘብ የለውም ስለተባሉ ቼኩን ያስመቱ መሆናቸው ፣ ተጠሪ ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል በሰጠው ብይን አመልካች የመከላከል ምስክሮች አቅርቦ ቀን ያልተፃፈበት ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መመስከራቸው መሰረት በማድረግ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ በማለት የቅጣት ውሳኔ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን ተጠሪ ቼኩን ለግል ተበዳይ የሰጠው ለመተማመኛ መሆኑ በዓ/ህግ 2ኛ ምስክር የተገለፀ በመሆኑ ተከሳሽ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት በነፃ ያሰናበተው ስለመሆኑ ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡

ተጠሪ ለግል ተበዳይ ቼክ ፈርሞ መስጠቱ ሳይክድ ነገር ግን ቼኩ የተሰጠው ለዋስትና ዓላማ ነው በማለት ተከራክረዋል ፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ፍ/ቤት ማስረጃ በመመዘንና ፍሬነገር በማጣራት ሥልጣኑ በደረሰበት ደምዳሜ ተጠሪ ቼክ ፈርሞ መስጠቱ ለዋስትና የሰጠሁት ነው የሚለው ክርክርም ተቀባይነት እንደሌለው ቼኩ ፈርሞ መስጠቱ የተረጋገጠ እና በቼኩ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ጥፋተኛ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንፃሩ ቼኩ ለዋስትና የተሰጠ መሆኑ የዓ/ህግ 2ኛ ምስክር ተገልፀዋል በማለት ተከሳሽ በተጠቀሰበት የህግ ዓንቀፅ ጥፋተኛ

www.abyssinialaw.com

ሊባል አይገባም  ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሱ ምክንያት ተጠሪ በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ .የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(1) ሥር የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል ለማቋቋም እንደመስፈርት የተወሰዱት አንደኛው ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በሰጪ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቼኩ የተጠቀሰውን መጠን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቼኩ ማውጣቱ አልተካደም ቼኩ በወጣበት ጊዜ ይሁን በግል ተበዳይ በክፍያ በቀረበበት ጊዜ የሚያሲዝበት በቂ ገንዘብ ስለመኖሩ ያቀረበው ክርክር የለም ፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 67947 በሰጠው ገዥ (አሳሪ) የሕግ ትርጉም ቼክ በወንጀል ጉዳይ እንደዋስትና ተሰጥተዋል በማለት እንደመከላከያ ሊቀርብ እንደማይችል ፍርድ ሰጥተዋል ፡፡ በቼክ አውጪው እና ተቀባዩ የሚኖረው ግላዊ ግንኙነት /personal relation/ በፍትሐብሄር ጉዳይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም በወንጀል ጉዳዮች ተፈፃሚነት እንደሌለው ከላይ በተመለከተው የሰበር ውሳኔ ተገልጸዋል ፡፡ በመሆኑም አንድ በቼክ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰው ግለሰብ ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የሚሆነው ከላይ የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋያ ፍሬ ነገሮች እንደሌሉ በሌላ አገላለጽ ቼኩ ሲወጣ ወይም ለክፍያ ሲቀርብ በቂ ስንቅ ያለው ስለመሆኑ በማስረዳት ብቻ ሲሆን ከዚህ ሌላ ፍርድ ቤቱ የሚቀበለው ሌላ ሕጋዊ ምክንያት ከሌላ በስተቀር ከተጠያቂነት ነፃ የሚያደረግ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸመበት ሕጋዊ ሰነድ ነው፡፡

ይህ በመሆኑም ሕግ አውጭው በቼክ ላይ የሚፈፅመው ወንጀሎች ሕጋዊ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ በግልፅ ከመደንገጉ በተጨማሪ ቼክ እንዳቀረበ ክፍያ የሚፈፅምበት ምንም ቅድመሁኔታ የማይቀመጥበት ሰነድ ነው ፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት ክርክር ሂደት እንደተገነዘብነው ተጠሪ ቼክ ለግል ተበዳይ መስጠቱ አልካደም ፡፡ተሰጠ በተባለው ቼክም ለማን እንደሚከፈል ከየትኛው ባንክ እንደሚከፈል እንዲሁም የገንዘብ መጠኑ በግልጽ የሰፈረ ስለመሆኑ አላከራከረም ፡፡ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ በነፃ ለማሰናበት እንደ መሰረታዊ ነጥብ የወሰደው ቼኩ ለዋስትና መያዣነት ለግል ተበዳይ የተሰጠ ስለሆነ የወንጀል ተጠያቂነት አያስከትልም በሚል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ከሥር የክርክር ሂደት መረዳት እንደተቻለው ተጠሪ የእምነት ክህደት ቃሉ ሲሰጥ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ ፈርሞ መስጠቱ አልካደም ። ተጠሪ የቼኩ ሕጋዊነት ሳይቃወም ቼኩ የተሰጠበት ዓላማ መሠረት በማድረግ መከራከሩን ተገንዝበናል ከላይ እንደተመለከተው ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸምበት ሰነድ ከመሆኑ አንፃር በወንጀል ጉዳይ ያለው ተጠያቂነት ቼክ በወጣበት ወይም ለክፍያ ለቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ መኖር ያለመኖሩን መሠረት ያደረገ እንጂ ለዋስትና የተሰጠ መሆን ያለመሆን በወንጀል ጉዳይ እንደ ሕጋዊ መከላከያ የሚወሰድ አይደለም ። የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ለክርክሩ መሠረት የሆነው ቼክ በተጠሪ ተጽፎ ተፈርሞ መሰጠቱ እያረጋገጠ ቼክ ለዋስና መስጠት የወንጀል ተጠያቂነት አያስከትልም ከሚል ድምዳሜ የደረሰው አጠቃላይ የክርክሩ ባሕሪ ያላገናዘበ ነው። ምክንያቱም ተጠሪ ቼክ ማውጣቱ አልካደም ። ቼክ የተሰጣት የግል ተበዳይም በስማቸው የታዘዘ ክፍያ መሆኑን አረጋግጠዋል ። በሌላ በኩል የሚከፈለው የገንዘብ መጠንና ከፋይ ባንክ በግልጽ ተመልክቷል ። ተጠሪ የቼኩ ሕጋዊነት ጥያቄ ባላነሳበት ፤በዋናነት ደግሞ ቼኩ ጽፎ እና ፈርሞ መስጠቱ ባልካደበት ሁኔታ  የሥር ፍርድ ቤት የሕግ ትርጉም እና ድምዳሜ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) ሥር የተመለከተው መሰረታዊ የወንጀሉ መቋቋያ ፍሬነገሮች ያላገናዘበ ፤በተጠሪ የተሰጠው  ቼክ ሕጋዊነት ባላከራከረበት ተጠሪም ቼኩን መስጠቱ ባልካደበት ጥፋተኛ አይደለም በማለት በነፃ እንዲሰናበት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል። ስለሆነም ተጠሪ በዓቃቤ ሕግ ጠቅሶ ባቀረበው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) ሥር በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 195(2) (ሀ) መሠረት ጥፋተኛ ነው ብለናል።

በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል።

## ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ  ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 257881 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273802 ህዳር 26 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ

www.abyssinialaw.com

የጸናዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 25121 በነበረው ክርክር የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/መሰረት ጥፋተኛ ሊባል ይገባል ብለናል፡፡
3. በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25117 የካቲት 15 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ፀንቷል፡፡
4. በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተመላሽ ይደረግ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር---156420

ቀን- ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ ዐ/ሕግ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሙላቱ ያለዉ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ አመልካች በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ የክሱ ይዘት፡- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቦንጋ ከተማ 03 ቀበሌ ታሕሳስ 02 ቀን 2009 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በሚያሽከረክረዉ ኮድ 3-88132 በሆነዉ ሀይሉክስ ቶዮታ መኪና ላይ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ለመቆጣጠር የወጣዉን ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 36(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ ሟች ተማሪ ወርቁ ኮንሰን በኋለኛዉ የመኪና ክፍል አሳፍሮ በማሽከርከር ላይ እያለ ሟች ወድቆ በጭንቅላቱና ጀርባዉ ላይ በደረሰዉ ከባድ ጉዳት ሕይወቱ ያለፈ በመሆኑ በፈጸመዉ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት ተጠሪ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ክሱን ክዶ በመከራከሩ የአመልካች ምስክሮች ተሰምተዉና የሰነድ ማስረጃ ቀርቦ ተጠሪ በተከሰሰበት አንቀጽ ስር እንዲከላከል ብይን የተሰጠ ሲሆን ተጠሪ የመከላከያ ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የስር

www.abyssinialaw.com

ፍ/ቤት የግራቀችኑን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የተጠሪ ምስክሮች የተመሠከረበትን ያህል አላስተባበሉም በማለት ተጠሪን የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ የጥፋተኝነት ዉሳኔ በመስጠት ተጠሪ በ3 (ሦስት) ዓመት ከ3 (ከሦስት) ወር ጽኑ እስራት እና በብር 2000(ሁለት ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራቀችኑን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ሟች መኪናዉ ሳይቆም ዘሎ እወረዳለሁ ሲል ወድቆ የሞተ በመሆኑና ተጠሪ ሟችን ከላይ በመጫኑ ደንብ መተላለፍ የፈጸመ ቢሆንን ተጠሪ ሟችን ከላይ በመጫኑ ብቻ ለሟች ሞት በቸልተኝነት ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት ተጠሪ በነጻ ሊሰናበት ይገባል በማለት በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ በመሻር በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የተመለከተዉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አቅርቦ ካከራከረ በኋላ መርምሮ ዉሳኔዉን በማጽናት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ተጠሪ መጫን በተከለከለ የመኪና የዉጭ ክፍል ላይ ሟችን እንደጫነዉ በጉዞ ላይ እንዳለ ሟች ወድቆ ጉዳት የደረሰበትና በዚያዉ ምክንያት መሞቱ ተረጋግጧል፡፡ የመንገድ ደህንነትን ለመጠበቅ የወጣዉን ደንብ ቁጥር 208/03 አንቀጽ 36(1) በመርህ ደረጃ በመኪናዉ የዉጭ ክፍል ላይ የሚያሳፍር ሰዉ በማናቸዉም ሁኔታዎች ጉዳት ሊደርስባቸዉ የሚችል መሆኑን በማያሻሚ ሁኔታ መግለጹን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ ይህን ጥንቃቄ ማድረግ ግዴታ እያለበት ይህንን ክልከላ በመተላለፍ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ ይህን ተላልፎ ሰዉ በመጫኑ የሞት ጉዳት መድረሱ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ነጻ እንዲሰናበት መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለዉሳኔዉ መሠረት ያደረገዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 24 ሲሆን በተሳሳተ ሁኔታ በመገንዘብ ነዉ፡፡ ተጠሪ በመኪናዉ የላይኛዉ ክፍል ላይ ሰዉን በመጫን ዉድቆ ሕይወቱ ሊያልፍ እንደቻለ እየተረጋገጠ የስር ፍ/ቤት በምክንያትና ዉጤት መካከል ግንኙነት የለም ማለቱ ስህተት ነዉ፡፡

የስር ፍ/ቤት ድርጊቱ አደጋ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የወ/ሕ/አንቀጽ 58(3) እና 59 በሚገባ ያላገናዘበ ነዉ፡፡ ምክንያቱም የተጠሪ ድርጊት ጉዳት ይደርሳል ቢል የተከለከለን ድርጊት አይደርስም በሚል ባለማገናዘብ በቸልተኝነት የመኪና የዉጭ ክፍል

www.abyssinialaw.com

ላይ ሟችን በመጫን ወድቆ የሞተ መሆኑ በሚገባ እስከተረጋገጠ ድረስ የሀሳብ ክፍሉ ቸልተኝነት መሆኑ በቀላሉ መረዳት እየተቻለ አደጋ ነዉ መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልን የሚል ነዉ።

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ሰዉ ለመጫን ባልተፈቀደ ቦታ ላይ ሕጻኑን ከኃላ ጭኖ ሲያሽከረክር ለመዉደቅ የተጋለጠና የሚከልለዉ ነገር በሌለበት ወድቆ መሞቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ በኋላ በኩል መጫን ቸልተኝነት አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት ከጥፋተኝነትም ሆነ ከቅጣት በነጻ ያሰናበተበትን አግባብነት ከወ/ሕ/አንቀጽ 59 እና ሰበር ሰሚዉ ችሎት በሰ/መ/ቁ 52075 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠርቶ ሊቀርብ ባለመቻሉ በሌለበት ጉዳዩ ከመታየቱም በላይ በዚሁ ችሎት እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ሊቀርብ ባለመቻሉ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል። ተጠሪ ሲያሽከረክረዉ በነበረዉ ፒካፕ ትዮታ መኪና ከኋለኛዉ ክፍል ላይ አሳፍሮ ሲያሽከረክር ሟች ወድቆ መሞቱ ተረጋግጧል። ተጠሪ ሟችን ከኋለኛዉ የመኪና አካል አሳፍሮ ያሽከረክር የነበረዉ የትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 208/03 አንቀጽ 36(1) ስር በመኪና የኋለኛ አካል ላይ ሰዉ አሳፍሮ ማሽከርከር የሚከለክለዉን ደንብ በመተላለፍ ጭምር መሆኑ አሻሚ አይደለም። የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሟች ላይ ለደረሰዉ የሞት ጉዳት ተጠሪን በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ያደረገ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪን በነጻ ሲያሰናብት የሰጠዉ ምክንያት ሟች ከመኪናዉ ዘሎ በሚወርድበት ጊዜ መዉሰድ ይገባዉ የነበረ ጥንቃቄ ርምጃ ባለመዉሰዱ የደረሰ ሞት እንጂ ተጠሪ የሟችን መሞት ለማስቀረት ማድረግ እያለበት ያላደረገዉ ወይም ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ የተገኘ ዉጤት መሆኑ ያልተረጋገጠ እንዲሁም የሟች ከመኪና ዘሎ መዉረዱ ብቻ እንጂ በተጠሪ በኩል የተፈጸመ ቸልተኝነት የለም በማለት ነዉ። የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ አብይ ጭብጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ተጠሪ ሟችን በሚያሽከረክረዉ መኪና ከኋላ ዉጭ ላይ ጭኖ ሲያሽከረክር ወድቆ የሞተ መሆኑን በተረጋገጠበት ለሟች

ሞት ምክንያቱ የተጠሪ ቸልተኝነት አይደለም ተብሎ በነጻ እንዲሰናበት መወሰኑ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በወ/ሕ/አንቀጽ 59(1/ ሀ እና ለ) መሰረት አንድ ሰዉ በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር ፈጽሟል የሚባለዉ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን ወይም ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ፣ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈጸመ እንደሆነ ነዉ፡፡ በተለይ ከአድራጊዉ የግል ሁኔታ አንጻር ሲታይ ሊደረጉ ይገባል ተብሎ በአግባቡ የሚጠበቁበትን ጥንቃቄዎች ያላደረገ እንደሆነ ቸልተኝነት አለዉ እንደሚባል ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ሟችን ከሚያሽከረክረዉ ተሽከርካሪ የኋለኛ የዉጭ ክፍል ላይ አሳፍሮ ሲያሽከረክር ሟች ከተሽከርካሪዉ ወድቆ ሕይወቱ ማለፉ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ሟችን አሳፍሮበት ይጓዝ የነበረዉ ክፍል ላይ ሰዉ አሳፍሮ ማሽከርከር በትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 36(1) የተከለከለ ተግባር መሆኑ ተደንግጓል፡፡ የትራፊክ ደህንነት ደንቡ ይህን ተግባር የከለከለበት ዋናዉ ምክንያት ለተሳፋሪ ደህንነት አደገኛ በመሆኑ በሰዉ ሕይወት ወይም አካል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ ተጠሪ የአሽከርካሪነት ሙያ ያለዉ ሰዉ እንደመሆኑ መጠን ይህን ደንብ ተላልፎ ሰዉን ከኋላ መጫን አደገኛና ተገቢዉ ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚገባዉ ሆኖ እያለ ሟችን በደንብ በተከለከለ የተሽከርካሪዉ አካል ላይ አሳፍሮ ጭኖ ሲሄድ ሟች ወድቆ ለደረሰበት ጉዳት ተጠሪ በቸልተኝነት ተጠያቂ ነዉ፡፡ ሟች ለመዉረድ ሲል መዉደቁ ወይም ለመዉረድ ሲል ዘሎ መዉደቁ የተጠሪን ቸልተኝነት አያስቀረዉም፡፡ ምክንያቱም ሟች ለተሽከርካሪ ያለዉ ግንዛቤ አናሳ ሊሆን ከመቻሉ አንጻር ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ እያለ መዉረድ የሚያስከትለዉን ጉዳት ላይገነዘብ ይችላል፡፡ ደንቡ በተጠሪ ላይ ወይም በአሽከርካሪዉ ላይ በዋናነት ግዴታ የጣለዉ ሰዎች መጓጓዛቸዉን እንጂ ከላይ መሳፈር ሊያስከትልባቸዉ የሚችለዉን ጉዳት በአግባቡ ላይገነዘቡ ስለሚችሉ ነዉ፡፡ ሟች ተሽከርካሪዉ በጉዞ ላይ መዉረድ ወይም ዘሎ መዉረድ አደገኛ ዉጤት ያለዉ መሆኑን ቢያዉቅና የተሳሳተ ግንዛቤ ባይኖረዉ ኖሮ በጉዞ ላይ ካለ ተሽከርካሪ ዘሎ ባልወረደ ነበር፡፡ እንዲሁም ለሟች ጉዳት ዋናዉ ምክንያት የሟች ከተሽከርካሪዉ መዉረድ ብቻዉን ሳይሆን ተሽከርካሪዉ በጉዞ ላይ መሆኑ ነዉ፡፡ ስለሆነም የሟችን ሞት

www.abyssinialaw.com

ያስከተለዉ በዋናነት ተጠሪ በትራፊክ ደህንነት ደንብ ጭምር አደገኛ ዉጤት እንደሚያስከትል ግንዛቤ ዉስጥ ገብቶ በተከለከለ ስፍራ ወይም የመኪናዉ የኃላ የዉጭኛ አካል ላይ ሟችን አሳፍሮ በመሄድ በፈጸመዉ ቸልተኝነት ምክንያት ሟች ለመዉረድ ሲል ወድቆ በመሞቱ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኛ ማለቱ ተገቢ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጥፋተኝነት ዉሳኔዉን በመሻር ተጠሪን በነጻ ማሰናበቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) በተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ወንጀሉ ደረጃ የወጣለት በመሆኑ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ደረጃ 1 እርከን 21 ተወስዶ የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ባለመኖሩ በተጠሪ በኩል በቀረቡት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ዉስጥ 4 ምክንያቶችን በመዉሰድና 4 እርከን በመቀነስ እርከን 17 ስር የ3 ዓመት ከ3 ወር የጽኑ አስራት ቅጣትና በገንዘብ የብር 2,000 መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመገኘቱ እንዳለ ተወስዷል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 36(1) የተመለከተዉን ግልጽ ክልከላ በመተላለፍ በተሽከርካሪዉ የኋላ የዉጭ አካል ላይ ሟችን አሳፍሮ ሲያሽከረክር ሟች ለመዉረድ ሲል ወድቆ በደረሰበት ጉዳት የሞተ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን በነጻ ማሰናበቱ የወ/ሕ/አንቀጽ 24፣ 59 እና የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻርና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ሊጸና የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ 049653 ግንቦት 02 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 05297 ጥር 30 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ የሰጠዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ተሽሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14375 የካቲት 02 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ እና ቅጣት ዉሳኔ ጸንቷል፡፡
3. የዞኑ ፖሊስ መምሪያ ተጠሪን በማፈላለግ ይዞ ለሚመለከተዉ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብና ማረሚያ ቤቱም ተጠሪ ከዚህ በፊት የታሰረዉ መታሰቡ ሳይቀር የተወሰነበትን የ3(ሦስት) ዓመት ከ3(ሦስት) ወር የጽኑ እስራትና የብር 2000(ሁለት ሺህ) የገንዘብ መቀጮ ቅጣት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር---153690

ቀን-መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች:-** አቶ ሀብታሙ ደስታ - አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ:-** የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በተሽከርካሪ በቸልተኝነት ሰዉ የመግደል፣ በሰዉ አካል ላይ ጉዳት ማድረስና በመገናኛና በማጓጓዣ ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀሎችን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በአፋር ክልል አዉሲረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ አመልካች ላይ ቀርበዉ የነበሩ ክሶች 3 ሲሆኑ 1ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቀን 14/04/2009 ዓ.ም ከቀኑ 9:45 ሰዓት ላይ ኤሊዳር ከተማ ለመግባት 6 ኪ.ሜትር ሲቀረዉ ኮድ 3-78217 ኢት የሆነ የመከላከያ ደብል ጋቢና ኒሳን መኪና እያሽከረከረ በቸልተኝነት በተቃራኒ አቅጣጫ ሲጓዝ ከነበረ ኮድ 3-86206 ኢት የሆነ ገልባጭ መኪና ጋር በመጋጨቱ ጭኗቸዉ ከነበሩ ሰዎች መካከል ኢንጅነር ሀጎስ ገ/ጊዮርጊስ የተባለዉ ሕይወቱ በማለፉ በፈጸመዉ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ 2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በፈጸመዉ ግጭት በግል ተበዳይ ሂሩት ሰለሞን ላይ የላይኛዉና የታችኛዉ መንጋጋ አጥንት ስብራትና በታችኛዉ

መንጋጋ በግራ በኩል ያለዉ አንድ ጥርሷ በመዉለቁ በፈጸመዉ ታስቦ በሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ 3ኛ ክስ ደግሞ የወ/ሕ/አንቀጽ 506(1/መ) የተመለከተዉን በመተላለፍ በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ ባደረሰዉ ግጭት የሚያሽከረክረዉ ተሸከርካሪ ጋቢና ሙሉ በሙሉ በመጨራመቱ፣ ቻንሲዉ በመታጠፉና የሞተር ሳፖርቶ በመቆረጡ እንዲሁም በሰ.ቁ 3-86206 ኢት መኪና ላይም አቫንታሪ ቦሊስትራ፣ ስፐረይ ጋቢናና ራዲያተር መሰበርና በር መታጠፍ በድምሩ ብር 1,100,000 ግምት ያለዉ የንብረት ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ መገናኛዎችና መጓጓዣዎች ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የወንጀል ድርጊቶቹን አለመፈጸሙን ገልጾ ጥፋተኝነቱን ክዶ የተከራከረ ሲሆን የዐ/ሕግ ማስረጃዎች ተሰምተዉ አመልካች እንዲከላከል ብይን የተሰጠ ሲሆን አመልካች የመከላከያ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ አመልካችን በተከሰሱበት ሦስቱም ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ በ7(ሰባት) ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 500 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝቶ ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ በ3ኛ ክስ ጉዳቱ ሆን ተብሎ የደረሰ ሳይሆን በቸልተኝነት መሆኑን በመግለጽ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ ድንጋጌ ከወ/ሕ/አንቀጽ 506 ወደ አንቀጽ 505(3) በመለወጥ ቅጣቱን በማሻሻል አመልካች በ5 ዓመት ከ1 ወር እስራት እና በብር 1,000 እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 61(3) አንጻር በአንድ ቸልተኝነት በተፈጸመ ድርጊት በሦስት ተደራራቢ ክስ ጥፋተኛ መደረጌ ተገቢ አይደለም፡፡ በ1ኛ ክስ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል በሚል በወ/ሕ/አንቀጽ 543(2) ስር ጥፋተኛ ተብዬ በተመሳሳይ ድርጊት ለደረሰ የአካል ጉዳት የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) ስር ሆን ብሎ የአካል ጉዳት በማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ መባሌ ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲሁም በወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) እና 57 መሠረት ወንጀሎችን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ጋር ተገናዝቦ ተገቢዉ ትርጉም ተሰጥቶት ዉሳኔዉ ይሻርልኝ፡፡ ቅጣቱም ቢሆን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ተደርጎ ያልተወሰነ በመሆኑ ቅጣቱ ቀልሎ

www.abyssinialaw.com

እንዲወሰንና የሚወሰነዉ ቅጣትም እስከአሁን የፈጸምኩት ግምት ዉስጥ ገብቶ በገደብ እንዲሆንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የቀረበዉ ክስ መኪና በቸልተኝነት በማሽከርከር ጉዳት ማድረስ ሆኖ ሳለ በ2ኛ ክስ በወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) ስር ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበት አግባብ ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ያቀረበዉ መልስ፡- አመልካች በቀረበበት ሦስት ክሶች የተጠቀሰዉን ጉዳት ያደረሰዉ በአንድ የቸልተኝነት ድርጊት ቢሆንም በሕግ ጥበቃ በሚደረግላቸዉ ሦስት የተለያዩ መብቶች ላይ የተፈጸመ በመሆኑ በተደራራቢ ክስ ጥፋተኛ መደረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት በ3ኛ ክስ አንቀጹን ለዉጦ ጥፋተኛ ማለቱም ሆነ ቅጣት መወሰኑ ተገቢ ነዉ፡፡ በቅጣት አሰላል ላይ የተፈጸመ ስህተት የሌለ ከመሆኑም በላይ ቅጣት የሚገደብ ከሆነ ለማህበረሰቡ አስተማሪ ሊሆን ስለማይችል የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ይደረግልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች የሚያሽከረክረዉን ተሽከርካሪ በቸልተኝነት በማሽከርከር በፈጸመዉ ግጭት አንድ ሰዉ የሞተ ሲሆን አንድ ሰዉ ላይ ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት ከመድረሱም በላይ በተጋጨት ሁለት መኪኖች ላይ ጉዳት መድረሱ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉም ሆነ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች የአንድ ሰዉ ሕይወት እንዲያልፍ ያደረገዉም ሆነ ከባድ የአካል ጉዳት በሰዉ ላይ ያደረሰዉ በቸልተኝነት በማሽከርከር በፈጸመዉ ግጭት መሆኑ አሻሚ ባልሆነበት አመልካች በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ሆን ተብሎ በተፈጸመ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡

www.abyssinialaw.com

በመሠረቱ አንድ ተከሳሽ በአንድ ቸልተኝነትና በአንድ ድርጊት በደረሱ ጉዳቶች በተደራራቢ ወንጀሎች ሲከሰስ ሌላ የተለየ ሀሳብና ድርጊት መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ አንዱን በቸልተኝነት ሌላዉን ደግሞ ሆን ተብሎ ታስቦ በተፈጸመ ወንጀል ጥፋተኛ የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ተሽከርካሪዉን በቸልተኝነት በማሽከርከር በፈጸመዉ ግጭት በ1ኛ ክስ የተመለከተዉ የሰዉ ሕይወት በማለፉ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኝነት በፈጸመዉ ግድያ ከተከሰሰና ጥፋተኛ ከተባለ በተመሳሳይ ቸልተኝነትና ድርጊት በ2ኛ ክስ የተገለጸዉ ከባድ የአካል ጉዳት ሲደርስ ደግሞ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ሆን ተብሎ በተፈጸመ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በ2ኛ ክስ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ሆን ተብሎ በተፈጸመ ከባድ የአካል ጉዳት ሳይሆን የወ/ሕ/አንቀጽ 559(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኝነት በተፈጸመ የአካል ጉዳት ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች በ2ኛ ክስ በስር ፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ አንቀጽ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 113(2) መሠረት ተለዉጦና ተሻሽሎ በወ/ሕ/አንቀጽ 559(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላዉ ቅጣትን የተመለከተዉ ሲሆን ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመዉ ሲገኙ ቅጣት ሊወሰን የሚገባዉ በተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 22(1/ሀ) መሠረት ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኋላ እነዚህን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመለየት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የስር ፍ/ቤቶች ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣቱን ጨርሰዉ ካሰሉ በኃላ በመደመር የወሰኑ መሆኑ ስህተት ነዉ፡፡ በመሆኑም ቅጣቱን እንደገና ማስላቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁም መሠረት በ1ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(2) ተላልፏል ተብሎ ጥፋተኛ ለተባለበት በስር ፍ/ቤት የተያዘዉ ደረጃ 4 እርከን 16 ሆኖ የ3 ዓመት ከ2 ወር እስራት መነሻ ቅጣት እንዳለ ይዘናል፡፡ እንዲሁም በ3ኛ ክስ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት የ1 ወር እስራት መነሻ ቅጣት የያዘዉን እንዳለ ወስደናል፡፡ 2ኛ ክስን በተመለከተ የወ/ሕ/አንቀጽ 559(2) ደረጃ 2 እርከን 8 ስር መነሻዉን 1 ዓመት ከ2 ወር እስራት ተይዟል፡፡ ለሦስቱም ክሶች የተያዘዉ መነሻ ቅጣት ሲደመር ዉጤቱ 4 ዓመት

www.abyssinialaw.com

ከ5 ወር ይመጣል፡፡ ይህም እርከን 19 ላይ ያርፋል፡፡ በአመልካች ላይ የተያዘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፡፡ አራት የቅጣት ማቅለያዎች በስር ፍ/ቤት የተያዙለት በመሆኑ እንዳሉ ወስደን 4 እርከን ሲቀነስ እርከን 15 ላይ ያርፋል፡፡ ፍቅድ ስልጣኑ ከ2 ዓመት ከ9 ወር እስከ 3 ዓመት ከ3 ወር በመሆኑ አመልካች ቅጣቱ ተሻሽሎለት በመነሻዉ በ2 ዓመት ከ9 ወር እስራት ሊቀጣ የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት አመልካች ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰዉ በቸልተኝነት መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) ተላልፏል ተብሎ ሆን ተብሎ በተፈጸመ ከባድ ጉዳት የማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉም ሆነ ቅጣት ተሰልቶ የተወሰነዉ የተሻሻለዉን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 22(1/ሀ) የተመለከተዉን ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻሻል የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. በአዉሲረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነሐሴ 03 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 4390 ታሕሳስ 11 ቀን 2010 ዓ.ም ተሻሽሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ2ኛ ክስ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 559(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኝነት ከባድ አካል ጉዳት በማድረስ ወንጀል ነዉ ተብሎ ተሻሽሏል፡፡
3. በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ተወስኖ የነበረዉ የ5 ዓመት ከ1 ወር እስራት እና የብር 1000 የገንዘብ መቀጮ ተሻሽሎ አመልካች በ2(ሁለት) ዓመት ከ9(ዘጠኝ) ወር እስራትና በብር 1000(አንድ ሺህ) እንዲቀጣ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡ በዚሁ ቅጣት መሠረት እንዲያስፈጽም አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
4. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

አ/ጉ

www.abyssinialaw.com

# የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/155789

ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች ፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠ/አቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- ነቢላ አህመድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የወንጀል ክስ የሚሻሻልበት አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች ተጠሪ ላይ ያቀረበዉ ክስ 1ኛ/የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2/ሀ በመተላለፍ ድንጋይ ወርዉራ የግል ተበዳይ አመለወርቅ ታደሰ ደረቷንና የቀኝ እግሯን በመምታት ቀላል የአካል ጉዳት በማደረስ ፣2ኛ/ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 615 በመተላለፍ በአንደኛዉ ክስ የተጠቀሰችዉን የግል ተበዳይ አስነዋሪ ስድብ ሰደበቻት በማለት ተደራራቢ ክስ ያቀረባበት ሲሆን ተጠሪ የእምነት ክደት ቃል ከመስጠቷ በፊት መቃወሚያ በሚል ምክንያት በአንደኛዉ ክስ ላይ ድንጋጌዉና የተፈጸመዉ ድርጊት አይጣጣምም በማለቷ የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንኑ መቃወሚያ በመመርኮዝ አቃቤ ህግ 1ኛዉን ክስ አንቀጽ 556/2/ሀ ወደ አንቀጽ 560/1/ አሻሽሎ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ አቃቤ ህግ የተሻሻለ ክስ ባለማቅረቡ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/122/3/ መሰረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አቃቤ ህግ ይህንኑ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

ይግባኝ ቅሬታ ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ በማጽናት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ቀርቦ በዚህ ላይ ሲሆን የአቃቤ ህግ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2/ሀ እና 560/1/ ማቋቋሚያ ፍሬነገሮችን በአግባቡ ሳያገናዝብ የሰጠዉ ትእዛዝ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲታረም የሚል ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክሱ ካልተሸሻለ አላይም በማለት የስር ፍርድ ቤት መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢነት ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲትሰጥ ተደርጓል፡፡ተጠሪም የተፈጸመዉ ድርጊት የእጅ እልፊት ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክራለች፡፡አቃቤ ህግ ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ፍርድ ቤት ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠዉ በምን አግባብ ነዉ? ህጋዊ ዉጤቱስ ምንድነዉ? የሚለዉ መታየት ያለበት ነጥብ ሆኖ አግኝተናል፡፡ የወንጀል ክስ ማመልከቻ አዘጋጃጀት አስመልክቶ ይዘቱና ዓይነቱ በምን አኳኋን እና ዝርዝር ሊኖረዉ እንደሚገባ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት አንቀጽ 111 እና 112 ላይ ተመልክቷል፡፡ከነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ክሱ በዝርዝር እንዲገልጽ ከሚጠበቅባቸዉ መሰረታዊ ፍሬነገሮች ዉስጥ በክሱ የተጠቀሰዉ የወንጀል ህግ ድንጋጌ እና ተከሳሹ የፈጸመዉ የወንጀል ተግባር የክሱ ፍሬነገር ከህጉ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንዳለበት ነዉ፡፡ የክሱ አዘገጃጀትና ዝርዝር ይዘት ላይ መገለጽ የሚገባዉ መሰረታዊ ነገር ባለመገለጹ ተከሳሹን ያሳሳተዉ እንደሆነ ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም ማመልከቻ በቀረበለት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ፣ እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል በወ/መ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 118 እና 119/1/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ ስለሆነም ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠዉ በክስ ማመልከቻ ፎርም ወይም በክሱ ማመልከቻ ላይ ስለወንጀሉ አስፈላጊ ዝርዝር ዉስጥ ስህተት ሲገኝ ወይም ሳይጠቀስ ሲቀርና ይህም

መሰረታዊ ነገር ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ስለመሆኑ እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ ሰጥቶ ኣቃቤ ህግ የተሻሻለ ክስ አዘጋጅቶ ያላቀረበ እንደሆነ ተከሳሹ ለጊዜዉ እንደሚለቀቅ የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/122/3/ ድንጋጌ ይገልጻል፡፡ ስለሆነም በፍ/ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ክሱ ተሻሽሎ ያልቀረበ እንደሆነ ዉጤቱ መዝገቡን ለጊዜዉ በመዝጋት ተከሳሹን መልቀቅ እንደሆነ ህጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ በ1ኛዉ ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2/ሀ ተጠቅሶ በክሱ ዝርዝር ላይ ደግሞ ተጠሪ በሰዉ አካልና ጤና ላይ ጉዳት ለማድረስ አስባ የግል ተበዳይ አመለቀወርቅ ታደሰ ላይ ድንጋይ ወርዉራ ደረቷንና የቀኝ እግሯን በመምታት የህመም ስሜት እንዲሰማት በማድረግ ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽማለች የሚል ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ይህ ድንጋጌ ወደ 560/1/ ተለዉጦ ክሱ ተሻሽሎ መቅረብ አለበት በማለት ትእዛዝ የሰጠዉ በኣቃቤ ህግ በኩል የቀረበዉ ክስ ዝርዝር ስህተት ስላለበት ወይም መጠቀስ ያለበት መሰረታዊ የክሱ ፍሬነገር ባለመጠቀሱ ሳይሆን ተፈጸመ የተባለዉ ድርጊት ክስ የቀረበበትን ድንጋጌ አያቋቁምም ከሚል መነሻ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሰረቱ ክስ እንዲሻሻል የሚደረግበት ምክንያት እና አቃቤ ህግ ያቀረበዉን ክስ በማስረጃ አረጋግጧል ወይስ አላረጋገጠም? በአቃቤ ህግ ማስረጃ የተረጋገጠዉ የድርጊቱ አፈጻጸምና ዉጤቱ በየትኛዉ የህግ ድንጋጌ የሚሸፈን ነዉ? የሚለዉ ጉዳይ በየራሱ ተለያይቶ የሚታይ ስለመሆኑ ከወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/119 እና 113/2/ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የክስ ማመልከቻ እንዲሻሻል የሚደረገዉ ከላይ በተገለጸዉ አግባብ በክሱ ዝርዝር ላይ መገለጽ የሚገባዉ መሰረታዊ ጉዳይ ሳይገለጽ የቀረ እንደሆነ ወይም ደግሞ ያለአግባብ የተገለጸዉ ነገር ተከሳሹን የሚያሳስት ነዉ ተብሎ ሲታሰብ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አቃቤ ህግ በክሱ መሰረት የድርጊቱን ፍሬነገር በማስረጃ ማስረዳት ወይም አለማስረዳት እና ዉጤቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ድምዳሜ ላይ ሊደርስ የሚገባዉ የአቃቤ ህግ ማስረጃ ከተሰማ በኂላ እንደሆነ ከወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.141 መገንዘብ አዳጋች አይደለም፡፡ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 112 ላይ እንደተገለጸዉ ደግሞ የክስ ማመልከቻ ስለወንጀሉና ስለሁኔታዉ የሚሰጠዉ ዝርዝር መግለጫ ወንጀለኛዉ የፈጸመዉ ተግባር ወንጀል ከሚያደርገዉ ህግ አነጋገር ጋራ በጣም የተቀራረበ መሆን አለበት ሲል ህግ አዉጪዉ በጥንቃቄ የተመለከተዉ የተፈጸመዉ ድርጊት የተጠቀሰዉን ድንጋጌ ማቋቋሚያ ፍሬነገር ማሟላት አለማሟላት ፍርድ ቤቱ

www.abyssinialaw.com

በማስረጃ የሚያረጋግጠዉ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ለዚህም ነዉ አቃቤ ህግ በክሱ በገለጸዉ ልክ ሳይሆን ከዚያ ባነሰ ሁኔታ ወይም ክስ ባይቀርብበትም በአማራጭ ክስ ሊቀርብበት የሚችል ድንጋጌ የሚሸፈን የወንጀል ፍሬነገር መፈጸሙ በማስረጃ በተረጋገጠ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነዉ ወደሚለዉ ድንጋጌ ለመለወጥ እንዲችል በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/113/2/ ስልጣን የተሰጠዉ፡፡ ከዚህም በሻገር አቃቤ ህግ እንደክሱ አቀራረብ በማስረጃ ማስረዳት ካልቻለ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን በነጻ የማሰናበት ስልጣን በህጉ የተሰጠዉ ነዉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይ 1ኛዉ ክስ የተጠቀሰዉ ድንጋጌ እና በክሱ ዝርዝር የተገለጸዉ ፍሬነገር ላይ ጉድለት ወይም ስህተት ስለመኖሩ አልተገለጸም ፡፡ይልቁንም በግል ተበዳይ ላይ የደረሰዉ ጉዳት መጠነኛ ነዉ የሚል ምክንያት ብቻ ነዉ ፡፡በድርጊቱ ምክንያት የግል ተበዳይ ላይ የደረሰዉ ጉዳት መጠን የሚረጋገጠዉ በማስረጃ ስለሚሆን ከወዲሁ ማስረጃ ሳይሰማ ድምዳሜ ላይ መድረሱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አመልካች በክሱ ማመልከቻ ላይ ጠቅሶ ያቀረበዉ የወንጀል ህጉ ድንጋጌና የክሱ ፍሬነገር ዝርዝር ላይ በስህተት የተጠቀሰ ወይም ሳይጠቀስ የታለፈ መሠረታዊ ነገር መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ የተፈጸመዉ ድርጊትና አግባብነት ያለዉ ድንጋጌ የትኛዉ ነዉ የሚለዉ የክሱ ማቋቋሚያ ፍሬነገር መሟላት አለመሟላት ማስረጃ ተሰምቶ የሚለይና ፍርድ ቤቱ በህጉ አግባብ ዉሳኔ የሚሰጥበት ሆኖ እያለ ከወዲሁ አንቀጽ ካልተለወጠ በሚል ምክንያት ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ መስጠትና ይህ ካልተፈጸመ በሚል የክሱን መዝገብ መዝጋቱ ክስ እንዲሻሻል የሚደረግብትን ህጋዊ ምክንያት እና አላማ ያገናዘበ ሆኖ አላገኘንም፡፡ከዚህም ባሻገር ተጠሪ ላይ የቀረበዉ ክስ ሁለት ሆኖ እያለ 1ኛዉ ክስ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ተሻሽሎ ባለመቅረቡ የሚዘጋ ቢሆን እንኳን ሁለተኛዉ ክስ ላይ ዉሳኔ ላለመስጠት ፍርድ ቤቱ ምንም ዓይነት ህጋዊ ምክንያት ሳይኖረዉ ማለፉም የክርክር አመራር ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1ኛ/የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/112647 ላይ በ24/06/09 ዓ.ም እና በ08/07/09 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/194971 በ02/04/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/195/2/ሀ መሰረት ተሰርዟል፡፡

2ኛ/የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ክርክሩን ሰምቶ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በወ/መ/ስ/ስ ህግ ቁ/ 195/2/ሀ መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ::

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ቅ/ሀ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.156999

ጥቅምት 27/2011 ዓ/ም

**ዳኞች:-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች:-** አቶ ከበደ ተሠራ ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ዮሐንስ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የጉዳዩ መነሻ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በ25 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ተወስኖ ቅጣቱን በመፈጸም ላይ የሚገኙ መሆኑን ገልጸዉ ጥፋተኛ የተባሉበትን ሕግ የተካዉ የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቅጣቱን አሻሽሎ የወጣ በመሆኑ ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22(2)፣ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6(9) እና ከአዲሱ አዋጅ አኳያ ታይቶ ቅጣቱ እንዲቀነስላቸዉ ማመልከታቸዉ ነዉ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በአመልካች ላይ በመጨረሻ የቅጣት ዉሳኔ የሰጠዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለእያንዳንዱ ጥፋት መነሻ ቅጣት በመያዝ ዉሳኔ ባለማስተላለፉ ይህ ፍቤት ቅጣቱን በአዲሱ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት እንደገና ለማስላት መቸገሩን ገልጾ አመልካች አቤቱታዉን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ መስተናገድ ይኖርባቸዋል በማለት በአብላጫ ድምጽ አቤቱታዉን ባለመቀበል ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙ ያስቀርባል በማለት በክርክር

www.abyssinialaw.com

ሂደት ላይ እያለ አመልካች በይቅርታ በመለቀቃቸዉ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ሆኖም ለአመልካች የተሰጠዉ ይቅርታ በስህተት ነዉ ተብሎ በመሠረዙና አመልካች ወደ ማረሚያ ቤት የተመለሱ በመሆኑ የተዘጋዉ መዝገብ ተከፍቶ እንዲንቀሳቀስ አመልካች ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በአመልካች በአቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን አመልካች በራሳቸዉ የተዉትን ይግባኝ መልሰዉ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ አይችሉም፡፡ አመልካች የይግባኝ ቅሬታዉ መሰረዙን ካወቁና ወደ እስር ቤት ከተመለሱ ከ9 ወር በላይ የሆነዉ በመሆኑ አመልካች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ያቀረቡት ምክንያት በቂና አሳማኝ ባለመሆኑ ጥያቀዉ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ለሁሉም ጉዳዮች የጊዜ ገደብና በቂ ምክንያት ያለዉ መሆኑ ሲታይ የተዘጋዉ መዝገብ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ በጊዜ ገደቡና በበቂ ምክንያት ተደግፎ ሊቀርብ የሚገባዉ በመሆኑ አመልካች መዝገቡ ከተዘጋ ከ8 ወር በላይ ቆይቶ የተዘጋዉ መዝገብ ይንቀሳቀስልኝ በማለት ያቀረበዉ ጥያቄ በቂ ምክንያት በሌለዉ ሁኔታ የቀረበ በመሆኑ ተገቢነት የለዉም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በትዕዛዙ ላይ እንዳሰፈረዉ በዚህ አግባብ የተዘጋ መዝገብ በምን ያህል ጊዜ መከፈት እንዳለበት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ አመልካች ይቅርታዉ ከተሰረዘባቸዉ በኃላ ያለአግባብ የተሰረዘባቸዉ መሆኑን በመጥቀስ የይቅርታ አዋጁ ባስቀመጠዉ አግባብ አቤቱታ ለሚመለከተዉ አቅርበዉ ዉጤቱን ሲጠባበቁ ብዙ ጊዜ ወስዶባቸዋል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት አካል ፈጥኖ መልስ ሰጥቷቸዉ ቢሆን ኖሮ የይግባኙ መዝገብ እንዲንቀሳቀስ ወዲያዉኑ ማመልከት ይችሉ ነበር፡፡ የሥነ-ሥርዓት ሕግ በራሱ ግብ ካለመሆኑም በላይ በጭፍጫፊ የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች መሠረታዊ የሆነ የተከሳሽ መብት ሊነካ አይገባም፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ የፈጸመዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ ይግባኙን ተመልክቶ እንዲወስን ይመለስለት የሚል ነዉ፡፡

www.abyssinialaw.com

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 እና 97(3)ን ተላልፈዉ ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ከተላለፈባቸዉ በኃላ ጥፋተኛ የተባሉበት አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 ስለተሻሻለ በወ/ሕ/አንቀጽ 6 እና 9(1) እንዲሁም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2) መሠረት የተወሰነባቸዉ ቅጣት እንዲሻሻልላቸዉ ለስር ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ ዉድቅ ሲደረግባቸዉ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዉ በመታዩት ላይ እያለ አመልካችን መንግስት በይቅርታ የፈታቸዉ በመሆኑ የይግባኝ መዝገቡ እንዲዘጋላቸዉ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ መንግስት ለአመልካች ሰጥቶ የነበረዉን ይቅርታ በማንሳቱ እና አመልካች ወደ እስር በመግባታቸዉ ምክንያት የተዘጋዉ የይግባኝ መዝገብ ተከፍቶ እንዲታይላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ ይህን የሚከለክል ግልጽ ሕግ መኖሩ ሳይገለጽ አቤቱታዉ ዉድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች መዝገቡን ያስዘጉት ይቅርታ ስለተደረገላቸዉ ሲሆን በሳምንት ዉስጥ ይቅርታዉ በስህተት የተሰጠ መሆኑ ተገልጾ ወደ እስር እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ አመልካች ይቅርታዉ መሰረዙን ካወቁ ከ8 ወር በኃላ አቤቱታ ሊያቀርቡ የቻሉበት ምክንያት ስለመኖሩ አላቀረቡም፡፡ አመልካች በወ/ሕ/አንቀጽ 6፣ 9(1) እና በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22(2) የተቀመጠዉን መብት ማስጠበቅ የሚችሉት በስነ-ስርዓት ሕጉ የተቀመጠዉን መርህ ተከትሎ አቤቱታ በስርዓቱ ሲቀርብ ነዉ፡፡ የአመልካች አቤቱታ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ዉስጥ ያልቀረበ በመሆኑ አቤቱታዉ ተቀባይነት ማጣቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸዉ ላይ ይቅርታዉ ቀሪ መደረጉን እንዳወቁ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ያላመለከቱት በይቅርታ አዋጁ መሠረት አቤቱታ ለሚመለከተዉ አካል አቅርበዉ ዉጤቱን ሲጠባበቁ መሆኑን ቢገልጹም በስር ያልተነሳ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለሆነም በስር የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል። መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ቀደም ብሎ ጥፋተኛ የተባለበትን ሕግ የተካዉ አዲሱ አዋጅ ለጥፋቱ የተቀመጠዉን ቅጣት አሻሽሎ የወጣ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2) መሰረት ቅጣቱ አዲስ በወጣዉ አዋጅ ድንጋጌ አግባብ እንደገና እንዲሰላለት ነዉ። የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታዉን ተቀብሎ ከመረመረ በኃላ ተፈጻሚ በመሆን ላይ ያለዉን ቅጣት የወሰነዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅጣቱን ሲወስን መነሻ ቅጣት በመያዝ ባለማስላቱ አዲሱን ሕግ ተፈጻሚ ለማድረግ እንደሚቸገር ገልጾ አመልካች አቤቱታዉን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዉ መስተናገድ እንዳለባቸዉ በመጥቀስ ወስኗል። አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ያቀረቡት ይግባኝ ያስቀርባል ተብሎ በመታየት ላይ ባለበት ወቅት አመልካች በይቅርታ በመለቀቃቸዉ የጉዳዩ መታየት አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ መዝገቡ ተዘግቷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ይቅርታዉን የሰጠዉ አካል ይቅርታዉ በስህተት የተሰጠ መሆኑን በመግለጽ ይቅርታዉን በማንሳቱና አመልካች ቅጣቱን መፈጸም እንዲጀምሩ ከተደረገ ከ8 ወር በኃላ አመልካች የተዘጋዉ መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸዉ ቢጠይቁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዘግይቶ የቀረበ አቤቱታ ነዉ በማለት ሳይቀበላቸዉ ቀርቷል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች መዝገቡ እንደገና ተከፍቶ እንዲንቀሳቀስላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ ከ8 ወር በላይ ዘግይቶ የቀረበ ነዉ በማለት ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉን ቀጥለን እንመልከት።

በመሠረቱ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ለይግባኝ ማቅረቢያና ተያያዥ ጉዳዮች የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥም በመታየት ላይ ያለ መዝገብ መዘጋቱ አስፈላጊ ሆኖ ከተዘጋ በኃላ እንደገና መከፈቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በምን ያህል ጊዜ ዉስጥ አቤቱታ ሊቀርብበት እንደሚገባ በሕግ የጊዜ ገደብ አልተቀመጠም። ይህ በሚሆንበት ወቅት የጊዜ ገደቡ የሚወሰነዉ የጉዳዩን ሁኔታዎችና የአቤቱታዉን ዓይነት በመመልከት እንጂ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ የቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ አይደለም።

በተያዘዉ ጉዳይ መዝገቡ እንዲዘጋ ምክንያት የሆነዉ የአመልካች ጥፋት ወይም ይግባኙን አለመፈለግ ሳይሆን ይቅርታዉን የሰጠዉ አካል የፈጸመዉ ስህተት ነዉ።

እንዲሁም የተዘጋዉ መዝገብ ከምን ያህል ጊዜ በኃላ ሊከፈት እንደሚችልና እንደማይችል በግልጽ በሕጉ ያልተደነገገ መሆኑ አመልካች ፈጥኖ አቤቱታዉን እንዳያቀርብ የሚያደርገዉ ከመሆኑ አንጻር በሕጉ ክፍተት ምክንያት አመልካች መብቱን ሊያጣ አይገባም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2)፣ የወ/ሕ/አንቀጽ 6 እና 9(1)ን መሠረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ በባህሪዉ እንደመደበኛ የክርክር ጉዳይ የሚታይ ሳይሆን አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚችል ከመሆኑም በላይ አቤቱታዉን በቀጥታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረብ ማስወሰን እንዲችል ከፍተኛዉ ፍ/ቤት በዉሳኔዉ የገለጸበት ከመሆኑ አንጻር መዝገቡ እንደገና አይንቀሳቀስም መባሉ ምክንያታዊ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የተዘጋዉ መዝገብ እንዲንቀሳቀስለት የጠየቀበትን አቤቱታ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በግልጽ የጊዜ ገደብ ባልተቀመጠበትና ለመዝገቡ መዘጋትም ዋናዉ ምክንያት የይቅርታ ሰጪዉ አካል ስህተት እንጂ የአመልካች ቸልተኝነት ወይም ይግባኙን አለመፈለጉ ባልሆነበት ሁኔታ የተዘጋዉን መዝገብ ለማንቀሳቀስ አመልካች በቂ ምክንያት አላቀረበም በማለት የሰጠዉ ትዕዛዝ የአመልካችን መብት የሚያጣብብና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 141372 ሚያዚያ 04 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተዘገዉን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ በይግባኙ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.abyssinialaw.com

**የሰ.መ.ቁ 152038**

ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ

ተጠሪ፡- ምንተስኖት ዶሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የተሰጠን የእምነት ቃል የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 665/1 ድንጋጌን በመተላለፍ የስርቆት ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ በመከራከሩ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ በዓቃቤሕግ በኩል የቀረቡት ምስክሮች የግል ተበዳይ እና የደረጃ ምስክሮች ሲሆኑ የግል ተበዳይ ተከሳሽን አላውቀውም ድርጊቱን ሲፈጽም አላየሁም ያለ ሲሆን ሌሎቹ ሁለት ምስክሮች የፖሊስ ጣቢያው ባልደረቦች ሆነው ተከሳሽ ለፖሊስ በነጻ ፈቃዱ ቃሉን ሰጥቷል በማለት የመሰከሩ ቢሆንም ምስክሮቹ የሰጡት ቃል በሌላ ገለልተኛ አካል የተሰጠ ቃል ስላልሆነ እና በሌላ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ምስክርነታቸውን አልተቀበለውም በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት ብይን ሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ዓቃቤሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው 1ኛ ምስክር ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም አላየሁም በማለት የመሰከረ ሲሆን ሌሎቹ ምስክሮች ተጠሪ ለፖሊስ የሰጠውን ቃል ይዘት ለማስረዳት ከመቅረባቸው በቀር ድርጊቱ ሲፈጸም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ያዩ አይደሉም፤ምስክሮቹ ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ለፖሊስ ቃል ሲሰጥ መግለጻቸው ብቻ ለፖሊስ የተሰጠው ቃል በሌላ አግባብነት ባለው ማስረጃ ተደግፏል ማለት አይቻልም፤ለፖሊስ የተሰጠ የተከሳሽነት ቃል ብቻውን በሌላ አግባብ በሆነ ማስረጃ ባልተደገፈበት ሁኔታ የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ለማሳየት በቂ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በማጽናት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ የተከራከረ በመሆኑ አመልካች ምስክሮችን እና ተጠሪው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የተሰጠውን ቃል አቅርቦ አሰምቷል፤የአመልካች ምስክሮች ተጠሪው በነጻ ፈቃዱ ወንጀሉን እንደፈጸመ በዝርዝር ቃሉን የሰጠ እና ወንጀሉ የተፈጸመበትን ቦታ መርቶ ያሳየ መሆኑን በመግለጽ በመሰከሩበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የሰጠውን ቃል የሚደግፍ ማስረጃ ዓቃቤ ሕግ አላቀረበም በማለት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ዓቃቤ ሕግ ባቀረባቸወ ምስክሮች ተጠሪ ወንጀሉን መፈጸሙን ለመርማሪ ፖሊስ ቃሉን በፈቃዱ ሲሰጥ በደረጃ ማስረጃነት የነበሩ ፖሊሶች ቀርበው ከማስረዳታቸውም በላይ ወንጀሉን እንዴት እንደፈጸመ መርቶ ሲያሳይ የነበሩ መሆናቸውንም ጭምር አስረድተው ባለበት ሁኔታ ዓቃቤ ሕግ ገለልተኛ በሆነ ሁኔታ አላስረዳም ተብሎ በነጻ የመሰናበቱን አግባብነት ከመሠረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፦ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የፖሊስ ባልደረቦች ሲሆኑ ድብደባ የፈጸሙብኝ በመሆኑ በድብዳባ ለፖሊስ የሰጠሁት ቃል ማስረጃ ሊሆንብኝ አይገባም፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃል ከመስጠቴ በፊት መብት እና ግዴታዬ የተነገረኝ ስለመሆኑ ከፖሊሶች በስተቀር በሌላ ደጋፊ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ክሱን አስረድቷል ሊባል ስለማይችል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጠው የመልስ መልስ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃሉን ለፖሊስ ከመስጠቱ በፊት የሚሰጠው ቃል በፍ/ቤት በማስረጃነት እንደሚቀርብበት የተገለጸለት እና ይህንኑ ተገንዝቦ ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ በፊርማው አረጋግጧል፤ተጠሪ ለፖሊስ የሰጠሁት ቃል በተጽእኖ የተገኘ ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም በተጽእኖ ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ የሚያስረዱለት ምስክሮች አስቀርቦ ባላሰማበት ሁኔታ በደፈናው በፖሊሶች የደረጃ ምስክርነት የተሰጠ ነው ሊባል አይችልም፤ምስክር የሆኑት የፖሊስ አባላትም በጣቢያው በተለያየ የስራ መደብ ተመድበው የሚሰሩ እንጂ መርማሪ ፖሊሶች ባልሆኑበት ሁኔታ ገለልተኛ አይደሉም የሚል ግምት መወሰዱ ተገቢ አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሠረቱ መርማሪ ፖሊስ የተሰራውን ወንጀል በሚያውቅበት ወይም በጥርጣሬ በሚረዳበት ጊዜ ሁሉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ላይ ስለፖሊስ ምርመራ በተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብ የምርመራ ተግባሩን እንደሚፈጽም ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 22 እና 23 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ማንነቱ እና አድራሻው ከተረጋገጠ በኋላ የተጠረጠረበትን ወንጀል በሚመለከት ቃል ለመስጠት ነጻ እንደሆነ እና ፈቅዶ የሚሰጠው ማንኛውም ቃል በማስረጃነት የሚቀርብ መሆኑ ጠያቂው ፖሊስ ለተጠያቂው ሊነግረው እንደሚገባ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 ይደነግጋል፡፡ መርማሪው ፖሊስ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ከተጠሪጣሪው የሚቀበለው

www.abyssinialaw.com

ቃልም ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረውን ሰው ለመመርመር ዓላማ የሚውል መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወንጀል መፈጸሙን በማወቅ ወይም በመጠርጠር ምርመራ የተጀመረ እንደሆነ ምርመራው ተጠርጣሪው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የሚሰጠውን ቃል መሠረት በማድረግ ብቻ የሚጠናቀቅ ሳይሆን እንደ አስፈላጊነቱም ስለተጠርጣሪው ማንኛውንም ተገቢነት ያለውን ማስረጃ መስጠት የሚችል ምስክር በመመርመር፤የተጠርጣሪውን ቤት በመበርበር ወይም ዕቃ በመያዝ ወይም ተጠርጣሪው ቃሉን ለፍ/ቤት እንዲሰጥ በማድረግ ምርመራው የሚከናወን መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 30፤32 እና 35 ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡ ሲሆን በነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የሚደረገው ምርመራ ዓላማም ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረውን ሰው መመርመር እና ምርመራውን በተገቢው ሁኔታ አከናውኖ ክስ ለማቅረብ ስልጣን ለተሰጠው ዓቃቤ ሕግ ራፖር መላክ እንደሆነ የፖሊስ ምርመራን አስመልክቶ ከተደነገጉት የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ዓቃቤ ሕግ በተጠርጣሪው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ ምክንያት መኖሩን ተረድቶ ክሱን ያቀረበ እንደሆነ በምርመራ ጊዜ የተገኙ ማስረጃዎች ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት ተመርምረው እና ተመዝነው የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችሉ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ተከሳሹ የሚሰጠው የእምነት ቃልም ለምርመራ ዓላማ ሲባል በምርመራ ጊዜ የተገኘ ማስረጃ በመሆኑ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤቱ ሊመረመር እና ሊመዘን የሚገባው እንጂ ከወዲሁ ተቀባይነት አለው ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት አይደለም፡፡

በያዝነው ጉዳይ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች የግል ተበዳይ እና የደረጃ ምስክር የተባሉ ሌሎች ሁለት ምስክሮች ሲሆኑ የግል ተበዳይ የመኪናው ስፖኪዮ የተሰረቀበት መሆኑን በመግለጽ ከመመስከሩ በቀር ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም አይቻለሁ በማለት የሰጠው የምስክርነት ቃል የለም፤ሌሎች ሁለት ምስክሮችም ተጠሪው በነጻ ፍቃዱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃሉን ሲሰጥ አይተናል በማለት የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ቢሆንም ምስክሮቹ ያስረዱት ተጠሪ ሰጥቶታል

www.abyssinialaw.com

የተባለውን ያንኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የተሰጠውን ቃል ነው፡፡ ምስክሮቹ ወንጀሉ ተፈጽሞበታል በተባለው አካባቢ ያልነበሩ እና ተጠሪ ወንጀሉን ሲፈጽም ያላዩ ከመሆናቸውም ባሻገር ተጠሪ ለፖሊስ ሰጥቶታል ከተባለው ቃል ውጪ ተጠሪ ወንጀሉን እንደፈጸመ የሚያውቁ መሆናቸውን በመግለጽ የሰጡት የምስክርነት ቃል እስከሌለ ድረስ ምስክሮቹ ተጠሪ ወንጀሉን እንደፈጸመ አስረድተዋል ሊባል አይችልም፡፡

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የሚሰጠው ቃልም እንደማንኛውም ማስረጃ ተመርምሮ እና ተመዝኖ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ ተጠሪ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኂላ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ክሱን ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበውን ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 ድንጋጌ መሠረት ለፖሊስ ሰጥቶታል የተባለውን ቃል መርምሮ እና መዝኖ ክሱን ለማስረዳት በቂ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመ ስለመሆኑ የሚያስረዳ አግባብነት ያለው ሌላ ማስረጃ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ያቀረበ ስለመሆኑ መዝገቡ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የሰጠውን ቃል እንደማንኛውም ማስረጃ መርምረው እና መዝነው ማስረጃው ክሱን ለማስረዳት በቂ አይደለም በማለት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 103704 የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 177314 ጥቅምት 09 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡

- **መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ጉ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 132055

ጥቅምት 8/2009 ዓ.ም.

ዳኞች- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ክፍለጽዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች - አቶ አህመድ ደርባቸው ጠበቃ ሬድዋን ከማል

ተጠሪ - ፌዴራል ዐቃቤ ህግ- ሙሉ ተስፋ ከበደ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች በተጠሪው በቀረበባቸው የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ጋር ተያይዞ ጉዳዩን የያዘው ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱ የሚሰማበት ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠቱና ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) የዋስትና መብት ተጠብቆላቸው እንዲከራከሩ ለፍርድ ቤቱ በማመልከታቸው ነው፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የዋስትና መብት ጥያቄ ተቃውሟል ተጠሪ በመቃወሚያል አመልካች ቀደም ሲል በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ በማውጣት ወንጀል ተከስሰው የሦስት ወር እሰራት በ2 ዓመት ገደብ የተፈረደባቸው ሲሆን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሌላ የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል ተብሎ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ስለዚህ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) መሠረት የዋስትና መብት ጥያቄአቸው ውድቅ ሊሆን ይገባዋል ሲል ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ቀደም ሲል የቅጣት ገደባቸው ሳያበቃ አሁን ከተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ጋር ተመሳሳይ የሆ ወንጀል ፈጽመው የተቀጡ መሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) መሠረት ሌላ ወንጀል ይፈጽሙ ይሆናል ተብሎ የሚገመት በመሆኑ የዋስትና ጥያቄው አልተቀበልነውም ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካችን ቅሬታ ባለመቀበል ወስኖአል፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ን በተሳሳተ መንገድ ተርጉመውታል ይታረምልኝ ሲሉ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ቀደም ሲል የተቀጡበት ወንጀል በዚህ መዝገብ እያከረከረ ካለው የወንጀል ክስ ጋር የተለያየ ሆኖ እያለ በድጋሚ በተመሳሳይ ወንጀል ተከስሷል መባሉ አለአግባብ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አመልካች በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ቢደረግም እዚያው ሆነው የቼክ ማጭበርበር ድርጊት ከመፈጸም የሚያግዳቸው ነገር እንደማይኖር፣ ይልቁንም በዋስ ተለቅቀው ቼክ እንዲያንቀሳቅሱ መከልከሉ አግራጭ መሆኑን ገልጸው በዋስ የመለቀቅ ሕገመንግስታዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በዋስ ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ የሚችል ስለመሆኑ ግምት ሊያስወስድ የሚችል ባህርይ ወይም የነገሮች ሁኔታ ሳይኖር የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) ን በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ዋስትና በሕገመንግሥቱ ዕውቅና ያገኘ መብት ቢሆንም በሕግ ሊገደብ እንደሚቻል የታወቀ ነው ብሏል፡፡ አመልካች ከዚህ ቀደም በቼክ አታላይነት ወንጀል በብር 5000 መቀጮ የ3 ወር እስራት በ2 ዓመት ገደብ የተቀጡ ሲሆን አሁንም እንደገና የግል ተበዳይን እምነት በመጠቀም የወጡት ቼክ እንዳይከፈል ሂሳቡ እንዲዘጋ በማድረጋቸው በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት በአንድ ዓይነት የሕግ ድንጋጌ ተከስሰው ቀርበዋል፡፡ አመልካች በዋስ ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ይፈጽማሉ ከሚል ግምት ከዚህ የበለጠ ማሳመኛ ምክንያት ሊኖር አይችልም ሲል ተጠሪ መቃወሚያውን አቅርቧል፡፡ በፍ/ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለትም ተከራክሯል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍ/ቤት በፀናው ውሳኔ የአመልካች የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት ያለፈውን የወንጀል ሪከርድ በማየት አሁንም ተመሳሳይ ወንጀል ከመሥራቱ ይቆጠባል ተብሎ አይገመትም በሚል ነው፡፡

ሆኖም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ስር የተደነገገው የዋስትና መብት ገደብ በተከሳሹ ያለፈ የወንጀል ታሪክ ላይ የሚመሠረት አይደለም፡፡ ይልቁንም የድንጋጌው ዓላማ በእጅ ላይ ያለውን የክሱ ሂደት ሊያደናቅፍ ይችላል ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ በዋስ የመለቀቅ

www.abyssinialaw.com

መብቱን ለመገደብ ነው፡፡ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ከንዑስ ቁጥሮች (ሀ) እና (ሐ) ጋር በአንድነት ሲነበብ ይገባል ሕጉ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት እየገደበ ያለው በዋስትና ወረቀት ላይ የሰፈሩትን ግዴታዎች አይፈጽምም ተብሎ ሲገመት ወይም ዋሶችን ሊያባብል ይችላል ወይም ሊያስፈራራ ይችላል ወይም ማስረጃዎችን ሊያጠፋ ይችላል ተብሎ ተከሳሹ ሲገመት ነው፡፡ የቁጥር 67 (ለ) ድንጋጌም ከንዑስ ቁጥሮች (ሀ) እና (ሐ) ጋር በጣምራ ሲነበብ "ሌላ ወንጀል ሊሠራ ይችላል ተብሎ ሲገመት" የሚለው ድንጋጌ ከተያዘው ክስና ከተጀመረው የፍርድ ሂደት ጋር በተያያዘ ጠባብ የሕግ ትርጉም በተጣጣመ መልኩ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

ፍ/ቤቶቹ የተከሳሾችን ያለፈ የቅጣት ውሳኔ ካሁን ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በማያያዝ በዋስ ቢለቀቅ ተመሳሳይ የቼክ ወንጀል ሊፈጸም ይችላል የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና ጥያቄውን አለመቀበላቸው አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍ/ቤቶቹ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በተከሰሱበትን ጉዳይ ለማድበስበስ ማስረጃ ለማጥፋት፣ ወይም ራሱ ለመሰወርና ከፍርድ ለማምለጥ በአጭር የተያዘውን የፍርድ ሂደት ለማደናቀፍ የወንጀል ድርጊት ይፈጸማል ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ን የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መወሰናቸው ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

በሌላ በኩል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 138 (1) ሕጉ በግልጽ ካልደነገገ በቀር ተከሳሹ በፍርድ ዳኝነት በግልጽ እስከአልታወቀ ድረስ የቀድሞ ጥፋተኝነቱ አይገለጽም ሲል ደንግጓል፡፡ ድንጋጌው የተከሳሽን ንጽሕ ሆኖ የመገመት ሕገመንግሥታዊ መብት የሚያመለክት ሲሆን በተጨማሪም ዳኞች የወንጀል ጉዳይ በሚመረምሩበት ጊዜ በተከሳሹ የጥፋተኝነት ሪከሪድ ጫና አድሮባቸው የተሳሳተ ውሳኔ እንዳይሰጡ ለማድረግ የሰፈረ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ስለአመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት መዝገብ ሲያቀርብ ፍ/ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ መሠረት እንዳልቀረበ በመቁጠር ሊወሰን ሲገባ ሕጉን በመጣስ በአመልካቹ የጥፋተኝነት መዝገብ ላይ በመመሥረት ማከራከራቸውን መወሰናቸውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡

በዚህ መሠረት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 21/07/2008 ዓ.ም በወ/መ/ቁ. 146424 የሰጠውና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በቀን 29/09/2009 ዓ.ም በወ/ይ/መ/ቁ. 127657 ያፀናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ዋስትና በማስያዝ በዋስ ተለቅቀው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ተወስኗል፡፡
3. ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም ታዟል፤ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

# ልዩ ልዩ

www.abyssinialaw.com

ሰበር መ/ቁ153418

ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም

**ዳኞች**፡-ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች**፡- አቶ ጉደታ አሰፋ

**ተጠሪዎች**፡- 1ኛ/ወ/ት ወደሬ ጉደታ

2ኛ/ወ/ት ፋኖስ ጉደታ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የመጥፋት ዉሳኔ ከተሰጠና ንብረቱ ለወራሾቹ ከተላለፈ በኋላ የመጥፋት ዉሳኔ የተሰጠበት ሰዉ ሲመለስ ንብረቶቹን የሚያገኝበት ሁኔታ በጊዜ የተገደበ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት የሚመለከት ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁኑ አመልካች ጠፍቷል በሚል በፍርድ ቤት ዉሳኔ በማስጠት ተጠሪዎች የአመልካቹን የመሬት ይዞታ በእጃቸዉ አድርገዉ ሲጠቀሙ ከቆዩ በኋላ አመልካች ቀርቦ የመጥፋት ዉሳኔ ተሰርዞ በተጠሪዎች እጅ የገባዉን ይዞታ እንዲመልሱ እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መቃወሚያ ይዞታዉ በእጃቸዉ ከገባ 20 ዓመት በላይ ስለሆነ የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል የሚል ሲሆን የወረዳዉ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክር ሰምቶ አመልካች ጠፋ የተባለዉ በ15/09/1989 ዓ.ም ስለመሆኑ በመ/ቁ/126/99 ላይ በ25/05/1999 ዓ.ም ዉሳኔ ስለመሰጠቱ እና አመልካች አቤቱታ ያቀረበዉ በ24/08/2009 ዓ.ም በመሆኑ 10 ዓመት አልፎበታል

www.abyssinialaw.com

በሚል በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 172 እና 173/1/ መሰረት የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ታግዷል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የይርጋ መቃወሚያ ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ህጉን በአግባቡ ያላገናዘበ ነዉ የሚል ሲሆን ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ አቤቱታዉን ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 171 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አግባብ ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ በመያዝ በጽሑፍ መልስ እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች ላይ የመጥፋት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ቀርቦ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ያቀረበዉ አቤቱታ በፍ/ብ/ህግ ቁ/171 እና 173 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ትእዛዝ ተገቢነት ለመመርመር ነዉ፡፡

በፍትሓብሔር ህግ ዉስጥ ስለሰዉና ስለሰዎች መብት በሚደነግገዉ አንደኛ መጽሓፍ ዉስጥ አንዱ የተፈጥሮ ሰዉ ላይ የመጥፋት ማስታወቂያ ዉሳኔ የሚሰጥበትና ዉጤቱን የሚደነግገዉ አንቀጽ 154 እስከ 173 ድንጋጌዎች የሚመለከት ነዉ፡፡አንድ የተፈጥሮ ሰዉ በህይወት መኖር አለመኖሩ አጠራጣሪ ሲሆንና በሕይወት ስለመኖሩ ወሬዉ ከጠፋ ሁለት ዓመት የሞላዉ እንደሆነ የመጥፋት ዉሳኔ የሚሰጥበት ስርዓትና በዚህም ፍርድ ቤቱ ተገቢዉን ማጣሪያ አድርጎ የጠፋዉ ሰዉ መሞት የሚመስል ሆኖ የታየዉ እንደሆነ ጠፍቷል ሲል እንደሚያስታዉቅ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 157/1/ ተመልክቷል፡፡በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚሰጠዉ የመጥፋት ማስታወቂያ የሚያስከትለዉ ዉጤት እንደሞተ ሰዉ ተገምቶ መብትና ግደታዎቹ ለወራሾች የሚተላለፍ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 154፣163 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡በዚህ አግባብ የመጥፋት ማስታወቂያ ሲነገር ጠፋ የተባለዉ ሰዉ እንደሞተ ግምት ተወስዶ ጋብቻዉ እንደሚፈርስ እና

www.abyssinialaw.com

በእሱ መሞት መብት የሚተላለፍላቸዉ ሰዎች በመብታቸዉ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 163 እና 165 ላይ ተደንግጓል፡፡በሌላ በኩል ጠፋ የተባለዉ ሰዉ በህግ እንደሞተ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑና ነገር ግን ደግሞ ሰዉየዉ በህይወት ቢገኝ ወይም የሞተዉ ጠፋ ከተባለበት ቀን በኋላ ቢሆን ይህ ግምት ሊፈርስ እንደሚችል በማሰብ ንብረቶቹን በይዞታቸዉ ያደረጉ ሰዎች ዋስትና ወይም ግዴታ እንዲገቡ እንዲሁም ንብረቶቹን እንደመልካም አባት እንዲጠብቁ ህግ የሚያሥገድድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 165፣166 እና 168 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ ስለሆነም በአንድ በኩል የመጥፋት ዉሳኔ ሲሰጥ ጠፋ የተባለዉ ሰዉ እንደሞተ ተቆጥሮ መብቱ በህግ አግባብ ለባለመብቶች እንደሚተላለፍ በሌላ በኩል ደግሞ ጠፋ የተባለ ሰዉ በህይወት ቢገኝ በሚል ወይም የመጨረሻ ወሬዉ የተሰማበት ሌላ ጊዜ ቢሆን በሚል ህሳቤ መብቱ እንዳይጎዳ ህጉ ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረጉን እንገነዘባለን፡፡ይህንንም ተከትሎ የመጥፋት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ የመጥፋት ዉሳኔ ዉጤት የሚቀርበት ምክንያቶች በፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 170 ላይ ተዘርዝሯል፡፡ከእነዚህ ዉስጥ አንዱ ጠፋ የተባለዉ ሰዉ በሕይወት መገኘቱ ወይም መመለሱ ነዉ፡፡ ጠፋ የተባለዉ ሰዉ በህይወት ከተመለሰ ንብረቶቹ በሚገኙበት አኳኋን መልሶ መዉሰድ እንደሚችል የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 171/1/ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ይህ ድንጋጌ የጊዜ ገደብ አላስቀመጠም፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የመጥፋት ማስታወቂያ በመ/ቁ/126/99 ላይ በ25/05/1999 ዓ.ም የተሰጠ ሲሆን የመጨረሻ ወሬ ተሰማ የተባለዉ በ15/09/1998 ዓ.ም መሆኑ በዉሳኔዉ ላይ ተገልጧል፡፡አመልካች ይህንን በመቃወም አቤቱታ ያቀረበዉ በ24/08/09 ዓ.ም ሲሆን አቤቱታዉም ተጠሪዎች የመጥፋት ማስታወቂያ ያሰጡት በድብቅ ስለመሆኑና መሬቱን እስከ 1996 ሲጠቀም ቆይቶ በአጋዞ ሰጥቶ ሲጠቀም የቆየና ስራ ፍለጋ ሌላ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ ሲሄድ ልጆቹ አጋዞ ከተሰጠዉ አቶ አሰፋ ገለታ ላይ ተቀብለዉ ለ 4ዓመት ከተጠቀሙ በኋላ አመልካች ተመልሶ ሲጠይቅ 10 ዓመት እንዳለፈዉ ተደርጎ መወሰኑ ስህተት ነዉ ህጉም ይህንን ገደብ አላስቀመጠም የሚል ነዉ፡፡አመልካችም ይህንኑ መሰረት አድርጎ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት የ10 ዓመት ጊዜ አልፎበታል በሚል የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ

172 ዋቢ. በማድረግ የአመልካችን ጥያቄ ዉድቅ አድርጓል፡፡ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 172 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ መጥፋቱን በሚወስነዉ ፍርድ ዉስጥ ከተወሰነዉ የመጨረሻ ወሬዎች ከተሰሙበት ጊዜ ወዲህ አስር ዓመት ያለፈ እንደሆነ መሞቱ የመጨረሻ ወሬዎች በተሰሙበት ሳይሆን በሌላ ቀን ለመሆኑ ማስረጃ ለማቅረብ የሚችለዉ ጠፋ የተባለዉ ሰዉ ራሱ ወይም ስለመጥፋቱ የተሰጠዉ ፍርድ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን በኋላ ልዩ የሆነዉ ወኪል ብቻ ነዉ ይላል፡፡የዚህ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ የ10 ዓመት ጊዜ ገደብ የሚያያዘዉ ጠፋ የተባለዉ ሰዉ እንደሞተ ሰዉ ተገምቶ መብቶቹ ስለሚተላለፉ እና በመብቶቹ ሊሰሩ የሚችሉ ወገኖች ላይ ይርጋና የመሳሰሉት የጊዜ ጉዳዮች አከራካሪ በሆነ ጊዜ ትክክለኛዉን ጊዜ በሚመለከት መከራከሪያ ሊቀርብበት የሚችለዉን ወገን ለማመላከት የተቀመጠ እንጂ ጠፋ የተባለዉ ሰዉ ራሱ ተመልሶ ቢመጣ ወይም በሕይወት ቢገኝ መብቱን ለመጠየቅ የሚገድበዉ ድንጋጌ ሆኖ የተቀረጸ አይደለም፡፡በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት ጠፋ የተባለዉ ሰዉ ንብረት ዉርስ ጋር በተያያዘ ይርጋ ክርክር አስመልክቶ በሰበር መዝገብ ቁ/126975 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ማገናዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህም የሰዉየዉ መጥፋት ማስታወቂያ ወይም ዉሳኔ ተሰጥቶ 10 ዓመት ካለፈዉ በህይወት የመኖር ግምት ይበልጥ መሞቱ ስለሚያመዝን ንብረቱን በእጅ ያደረጉ ሰዎች ላይ በአንቀጽ 168 እና 169 ላይ የተጣሉት ገደቦች እንደማይሰሩ አመላካች ድንጋጌ እንደሆነ ከአንቀጽ 173 ጣምራ ንባብ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡በመሆኑም ጠፋ የተባለዉ አመልካች በሕይወት ከተመለሰ ሌላ ማረጋገጫ ሳያስፈልገዉ ንብረቶቹ በሚገኙበት አኳኋን መልሶ መዉሰድ እንደሚችል የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 171/1/ በግልጽ የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ዉሳኔ ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ስለዚህም የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 172 ተመርኩዞ የአመልካች ጥያቄ በ10 ዓመት ይርጋ ታግዷል በሚል የሰጠዉ ዉሳኔ የድንጋጌዉን ይዘትና ዓላማ በአግባቡ ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡በዚሁ መሰረት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ዉሳኔ

1ኛ/ የሲ/ያ/ዋዩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/0113197 ላይ በ29/02/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የአማራ ክልለ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0125264 ላይ በ18/3/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 030-9082 ላይ የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ 348/1/መሰረት ተሽሯል ፡፡

2ኛ/ የአመልካች አቤቱታ በ10ዓመት ይርጋ አልታገደም ብለናል፡፡

3ኛ/ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ወደ ፍሬ ጉዳዩ ገብቶ በተጠሪዎች እጅ የገባዉን ንብረት አጣርቶ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ.341/1/መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ

4ኛ/ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ካ/የ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 143045

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡-

1. ወ/ሮ እሌኒ ወ/አማኑኤል - ከጠበቃ አሰፋ ደራብሳ ጋር ቀረቡ፡፡

2. ህፃን ሰለማዊት ከበደ ሞግዚት 1ኛ አመልካች ወ/ሮ እሌኒ ወ/አማኑኤል -ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ወርቅነሽ ብዙነህ - ቀረቡ፡፡

2. ህፃን እፀገነት ከበደ ሞግዚት 1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ወርቅነሽ ብዙነህ - ቀረቡ፡፡

3. ሰላም ሁለገብ አገልግሎት ኃ/የተ/ህ/ስራ ማህበር -ጠበቃ እንዳልካቸው ሞላ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች

www.abyssinialaw.com

ነበሩ፡፡ በስር ፍርድ ቤት ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- 1ኛ አመልካች ከሟች አቶ ከበደ ጌታቸው ጋር እንደባልና ሚስት አብረው በመኖራቸው፤ 2ኛ አመልካች ደግሞ የሟች ልጅ በመሆኗ በ3ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ አቶ ከበደ ጌታቸው ያለው የእጣ ድርሻ 50% የሚገባቸው መሆኑን፤ እንዲሁም 2ኛ አመልካች ሟች ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር የሌለው ቤት የአቶ ከበደ ጌታቸው ድርሻ 2ኛ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ የየካ ምድብ ፍትሐብሔር ችሎት በመ/ቁ.70021 በ8/7/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የቀረበውን የውርስ ሪፖርት በማጽደቅ ውሳኔ በመሰጠቱ በዚሁ መሰረት በተለይ የ3ኛ ማህበር ሂሳብ ተጣርቶ በሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 19/3/ መሰረት የእቃው ዋጋና ያስገኘው ጥቅም ሂሳቡ ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው በህዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ መከላከያ መልስ ከሳሾች እንዲከፈላቸው የጠየቁት ቤት ሆነ የአክስዮን ድርሻ በእጃችን ያለ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ፤1ኛ ከሳሽ ከሟች አቶ ከበደ ጌታቸው ጋር ልጅ ከመውለዳቸው በቀር እንደ ባልና ሚስት አብረው አልኖሩም፤ክስ የቀረበበት ቤትም በሟች ወላጆች አጥር ግቢ ውስጥ አንድ ጥግ ይዞ የተሰራ እንጂ ራሱን የቻለ የራሱ የከተማ ቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የተሟላለት ቤት አይደለም፡፡ ይህ ቤት የለም እንጂ አለ የሚባል ከሆነ በተጣራው መሰረት ክፍፍል ቢደረግ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑ፤የህብረት ስራ ማህበሩም ከ1ኛ ከሳሽ የምትወለደውን ልጅ እንጂ 1ኛ ከሳሽን የሚመለከት አይደለም፤ ስለሆነም ያለአግባብ የቀረበ ክስ በመሆኑ ውድቅ ተደርጎልን ወጪና ኪሳራ ተከፍሎን መዝገቡ ተዘግቶ እንድንሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ለክሱ የሰጠው ምላሽ በተመለከተ 3ኛ ተከሳሽ የህብረት ስራ ማህበር እንጂ አክስዮን ማህበር አይደለም፤ ሟች አቶ ከበደ ጌታቸው የማህበሩ አባል የነበሩ መሆናቸው በመግለጽ የውርስ ሀብቱ ባለድርሻ ወገኖች ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት ጨርሰው አስወስነው ቢመጡ 3ኛ ተከሳሽ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እና በማህበሩ ደንብ መሰረት ከመፈፀም በስተቀር ባለድርሻ ነን ባዮች በሚያደርጉት ክርክር የሚሳተፍበት አግባብ የሌለ በመሆኑ በ3ኛ ተጠሪ የቀረበው ክስ ውድቅ ተደርጎ እንዲወሰንላቸው ዘንድ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ ከሰላም ሁለገብ አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ያለው ጥቅም ወይም ድርሻ እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፤እንዲሁም ከዚሁ ዕጣ የተገኘ የተጣራ ትርፍ ብር 45,895.81/ አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም/ አመልካቾች፤1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እኩል እንዲካፈሉ፤በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነው የውርስ ሀብት መሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠው ቤት 2ኛ ከሳሽ 1/4ኛ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ ከተቻለ በዓይነት በስምምነት ግምቱን ይህ ካልተቻለ ቤቱ ተሸጦ ድርሻዋ እንዲከፈል ሲል የሰጠው ውሳኔ በመቃወም አመልካቾች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ሰኔ 5 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአንድ ላይ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ለብቻው ነሐሴ 22 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም አቤቱታቸው በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች አቶ ከበደ ጌታቸው በ3ኛ ተጠሪ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ያላቸው ድርሻ ውስጥ ለአራቱ ማለትም ለአመልካቾችና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው 1/4ኛ የሚደርሳቸው መሆኑን በውርስ ማጣራት ተረጋግጦ በፍርድ ቤት የጸደቀ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሚያከራክረው የማህበሩ አባል ሲሞት ወደ ወራሾች የሚተላለፍ ምንድነው የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ በአመልካቾች በኩል ሟች ባለው የዕጣ ድርሻ የሚያስገኘው ትርፍ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የማህበሩን ካፒታሉ/

የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረቶች/ ተጣርቶ ሊከፈልን ይገባል የሚል ሲሆን በ3ኛ ተጠሪ ደግሞ በማህበራት አዋጅ 147/1991 አንቀጽ 32 መሰረት የማህበራት ንብረት ለአባላቱም ሆነ ለሌላ ወገን የሚከፋፋል ባለመሆኑ የአመልካቾች ጥያቄ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት የተካሄደው ክርክር እና የቀረቡትን ማስረጃዎችን ይዘት መመልከቱ አስፈላጊ ሁኖ ስለአገኘው የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት ከየካ ምድብ ችሎት የመ/ቁ. 104042 የሆነው መዝገብ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ከስር መዝገብ መገንዘብ የተቻለው በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቤት የውርስ ሀብት ከሆነው ቤት የተሰበሰበው የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈል የቀረበው ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች በዝምታ መታለፉ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ሊታረም የሚገባው ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ ሌላውን ነጥብ በተመለከተ ሟች አቶ ከበደ ጌታቸው በማህበሩ 155 ዕጣ ያንዱ ዕጣ ዋጋ ብር 100.00/አንድ መቶ ብር/ መሆኑን በዚሁ ስሌት መሰረት የሟች ድርሻ የተጣራ ትርፍ ብር 45,895.81/ አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም/ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት መቅረቡን ተገንዝበናል፡፡ ተጣርቶ የቀረበው የተጣራ ትርፍ ድርሻ ሲሆን የአመልካቾች ዳኝነት ጥያቄ ከማህበሩ የሚገኘው የትርፍ ድርሻ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የማህበሩ ካፒታል የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጣርቶ ድርሻቸው እንዲከፈላቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ማጣራት ተደርጎ ውሳኔ የተሰጠ ውሳኔ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ አንድ የመሰረታዊ ማህበር አባል ሲሞት ዕጣው ወይም ጥቅሙ በማህበሩ መዝገብ ውስጥ በወራሽነት ለሰየመው ወይም ሟቹ ወራሽ ያልሰየመ ከሆነ በሕግ ለመውረስ ለሚችል ወራሹ ይተላለፋል፡ ይህም የሚሆነው ወራሹ የማህበሩ አባል ከሆነ ወይም ለመሆን ፈቃደኝነቱን የገለጸ እንደሆነ ነው፡፡ ወራሹ የማህበሩ አባል ካልሆነ ወይም አባል ለመሆን የማይፈልግ ወይም የማይፈቀድለት ከሆነ የሟቹ የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም እንደሚከፈለው በአዋጁ አንቀጽ 19 ስር ተመልክቷል፡፡ በአጠቃላይ "**የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም ይከፈለዋል**" የሚለውን የህጉ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ አመልካቾች በማህበሩ የሚቀጥሉ መሆናቸው አለመሆናቸው?፤ሊቀጥሉ የማይፈልጉ ከሆነ ከማህበሩ ካፒታል /የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት/ ተጣርቶ የሚሰጣቸው መሆን አለመሆኑ? በሚሉት ነጥቦች ላይ ተገቢውን ጭብጥ ሳይመሰረትና ሳይጣራ በስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የክርክር አመራርና የዳኝነት አሳጣጥ

www.abyssinialaw.com

ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 104042 ሰኔ 9 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 182433 መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ.ም በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348 /1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች በማህበሩ 155/አንድ መቶ ሃምሳ አምስት/ ዕጣዎች ያሉት መሆኑን የተጣራ ትርፍ ብር 45,895.81 /አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም/መሆኑን እንዲሁም የውርስ ሀብት ከሆነው በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቤት 2ኛ አመልካች 1/4ኛ ድርሻ በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአጠቃላይ "**የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም ይከፈለዋል**" የሚለውን የህጉ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ አመልካቾች በማህበሩ የሚቀጥሉ መሆናቸው አለመሆናቸው?፤ሊቀጥሉ የማይፈልጉ ከሆነ ከማህበሩ ካፒታል /የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት/ ተጣርቶ የሚሰጣቸው መሆን አለመሆኑ? በሚሉት ነጥቦች ላይ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 136 መሰረት የሚመለከተው የህብረት ስራ ማህበራት ባለሙያ ምስክርነት /ማብራሪያ/ እንዲቀርብ በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት፤ እንዲሁም የውርስ ሀብት ከተባለው ቤት ኪራይ የተሰበሰበ መኖሩን አለመኖሩን አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 156425

ህዳር 14 ቀን 2011 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች፡-**ዳሽን ባንክ- ነ/ፊጅ ዐሥራት አድማሱ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ዶሪና አቫኪያን-የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የግለሰብን ፎቶ በቴሌቭዥን ከማሳየት ጋር ተያይዞ የተነሳውን የጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች የከሳሽን እውቅናና ፈቃድ ሳያገኝ የተጠሪን ፎቶ በ2006 ዓ/ም ከሚያዚያ ወር ጀምሮ በሰኔ እና በሐምሌ ወራት በነበረው የብራዚሉ ዓለም ዋንጫ የእግር ኳስ ጨዋታዎች የሚተላለፍበት ጊዜ ተጠሪ ከእነባለቤታቸው የአመልካችን ባንክ አገልግሎት ሲጠቀሙና ተጠቅመው ሲወጡ የሚያሳይ ማስታወቂያ በማሰራት በቀን ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን እንዲተላለፍ ማድረጉን ገልፀውና ተመጣጣኝ ካሳ ሊከፈላቸው የሚገባው መሆኑን ጠቅሰው ብር 400,000.00(አራት መቶ ሺህ) እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም አድራጎቱ ሕግን የጣሰ ያለመሆኑን፣ አመልካች በማስታወቂያው የተጠቀመው የተጠሪን ፎቶ ወይም ምስል ሳይሆን አጠቃላይ የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ መሆኑን፣ በማስታወቂያው ላይ የነበረው ቪዲዮም ከአንድ ደቀቂ የበለጠ እርዝማኔ የሌለውና ለአንድ ሰንከድ ብቻ የሚታይ መሆኑን፣ አመልካች ሆን ብሎና አላማ አድርጎ የተጠሪን ምስል ያለመቅረፁንና የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንም የግለሰቦችን ነፃነት የሚዳፈሩ ድርጊቶችን የማያስተላልፍ መሆኑን፣ የተጠሪ ምስል በመታየቱም አመልካች ያገኘው ጥቅም ያለመኖሩንና ተጠሪም ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን፣ ተጠሪ ለአመልካች በሰጡት ማስጠንቀቂያ ከገለፁት ገንዘብ ውጪ በክሳቸው ላይ መጠየቃቸውም ክሳቸው ታዓማኒነት የሌለው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፣ በህጉ ያላቸው መፍትሄም ድርጊቱን ማስቆም እንጂ ካሳ መጠየቅ ያለመሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ቀረፃው የባንኩን እንቅስቃሴ

እንጂ ተጠሪን ትኩረት ያላደረገ መሆኑን ና ቪዲዮውም የታየው ለአጭር ደቂቃ ብቻ ስለመሆኑ በማስረጃዎቹ አስረድቷል በሚል ድምዳሜ የተጠሪን ክስ ውድቅ ያደረገው ሲሆን በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸውን አመልካች በመጠቀም የውጭ ሀገር ባንኮች የክፍያ ካርዶችን ሀገር ውስጥ ላሉ ወይም ለሚመጡ ደንበኞች ካርዶችን በመጠቀም ምቾትን የጠበቀ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪን ከእነባለቤታቸው ተጠቅሞ ማስታወቂያ እያስነገረ መሆኑ ማስታወቂያው ተጠሪን ዒላማ ያደረገ ሊባል የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች የተጠሪን ምስል ከፍቃዳቸው ውጪ በመጠቀም ለሰራው ማስታወቂያ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) ድንጋጌ አግባብ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የካሳ መጠኑንም ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ ብር) ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ከቀረበው ክርክር ይዘትና በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ በመሄድ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ማድረጉ የክርክር አመራርና የማስረጃ ምዘና ስርዓትን ያልተከተለና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(1)(2) ድንጋጌዎችን ይዘት ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው የካሳ ጉዳይ ውሳኔ አግባብነት ስለጉዳዩ አግባብነት ካለው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(1)(2) ድንጋጌዎች ትክክለኛ አፈፃጸም አንጻር ለማየት ይቻል ዘንድ በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን ተጠሪ በመቅረባቸውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ተጠሪ የተጠሪን ምስል ለማስታወቂያ ስራ የተጠቀመበት ስለመሆኑና ይህንንም ሲያደርግ ከተጠሪ ተገቢውን ፈቃድ ያላገኘ መሆኑ

www.abyssinialaw.com

እንዲሁም ተጠሪ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸውን አመልካች በመጠቀም የውጭ ሀገር ባንኮች የክፍያ ካርዶችን ሀገር ውስጥ ላሉ ወይም ለሚመጡ ደንቦች ካርዶችን በመጠቀም ምቾትን የጠበቀ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪን ከእነባለቤታቸው ተጠቅሞ ማስታወቂያ እያስነገረ መሆኑ ማስታወቂያው ተጠሪን ዒላማ ያደረገ ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች መገንዘቡን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰውን ድምዳሜ የሻረው መሆኑን፣ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበትን ድምዳሜም ፍሬ ነገርን የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ሙሉ በሙሉ የተቀበለው መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች አግባብ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው በመሆኑ ሁለቱም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን የደረሱበትን ድምዳሜ የማይቀበልበትን አግባብ ስላላገኘ አመልካች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን መሰረት ያላደረገ ነው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ አልፈነዋል፡፡

ወደ ህጉ ስንመጣ የፍትሃ ብሔር ሕጉ የሰው መብቶች በሚል ከአንቀፅ 8 እስከ 10 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ጠቅላላ መርሆዎችን ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህ መርሆዎች ደግሞ ተጠቃሹ ሕግ ከቁጥር 11 እስከ 30 ድረስ በደነገጋቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው፡፧ ከአንቀፅ 11 እስከ 30 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር ከተካተቱት የሰው መብቶች መካከል ደግሞ ከሰው አካል ደህንነት እና ከሰው ነፃነት ጋር የተያያዙ ተጠቃሽ መሆናቸውን ድንጋጌዎቹ ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሰረት በፍ/ሕ/ቁጥር 11፣ 13፣ ከ27 እስከ 30 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ከሰው ነፃነት ጋር የተያያዙ መብቶችን የሚጠብቁ ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ የሰው ስእል/ምስል/ በተመለከተ ጥበቃ የሚያደርገው ቁጥር 27 ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ባለፎቶግራፉ/ባለምስሉ/ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ/ምስል/ በሕዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ የሰው ምስል/ፎቶ/ ከማባዛት ጋር ተያይዞ በልዩ ሁኔታ የተቀመጡት ነጥቦች በቁጥር 28 ስር የተዘረዘሩት ሲሆኑ እነዚህም የባለስእሉ/ምስሉ ሰው ታዋቂነት፣ ህዝባዊ ስራ ጋር መያያዝ፣ በፍርድ ወይም በፖሊስ መስሪያ ቤቶች ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ጉዳዩን አስፈላጊ ማድረጋቸው፣

www.abyssinialaw.com

ወይም ለኪነ ጥበብ፣ ለስልጣኔ አስተዳደግ ወይም ለትምህርት መስጫ ጥቅም ወይም በሕዝብ ስብሰባ ላይ ከተፈፀመ ስርዓት ጋር ግንኙነት ባለው ምክንያት መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በተጠቀሱት ሁኔታዎች የሰው ፎቶ/ምስል/ ማባዛት የተፈቀደ ሲሆን በህዝብ አደባባይ መለጠፍ ወይም ማሳየት ወይም መሸጥ ግን ያለ ባለቤቱ ፍቃድና እውቅና የማይቻል መሆኑን በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የፍ/ሕ/ቁጥር 29 ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 28 ስር ከተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች ውጪ ከባለፎቶው ወይም ምስሉ ፍቃድ ውጪ ምስሉን/ፎቶውን ማሳየት/exihibition/ ወይም መሸጥ ክልክል መሆኑንና ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር መብቱ የተጣሰበት ሰው የሚኖረው መፍትሄም ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት መብቱ የተጣሰበት ሰው ምስሉ /ፎቶው በአደባባይ እንዳይለጠፍ ወይም እንዳይታይ ወይም እንዳይሸጥ የሚያደርግ ዳኝነት እንዲሰጥለት መጠየቅ ወይም ካሳ መጠየቅ የሚችል መሆኑን በንዑስ ቁጥር ሁለት እና ንኡስ ቁጥር ሶስት ስር በግልጽ አስቀምጦ ይታያል፡፡ በአጠቃላይ በፍትሃብሔር ሕጉ በዚህ ረገድ የተቀመጡ ድንጋጌዎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 14 እንዲሁም አገሪቱ በተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ የተደረገውን የሰዎች የአካል ደህንነትና የነጻነት መብቶችን የሚደግፉ በመሆኑ ተግባራዊ ሲደረጉም የድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ፣ ሊያሳኩ ያሰቡትን መሰረታዊ ዓላማ ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ይህንኑ ይዘን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣም አመልካች የተጠሪን ምስል በቴሌቭዥን ለማስተዋወቅ ያለተጠሪ ፈቃድ መጠቀሙ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27 ድንጋጌ ስር ባለፎቶግራፉ ወይም ባለስዕሉ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ ወይም ስዕል በሕዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይቻል የተመለከተ በመሆኑና በፍ/ሕ/ቁጥር 28 ስር የተመለከተው ልዩ ሁኔታ ስለመኖሩም አመልካች ጠቅሶ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የተጠሪ ምስል ጥቅም ላይ ለዋለበት የማስታወቂያ ስራ አመልካች ካሳ የማይከፍልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሌላው በዚህ ሰበር አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የካሳ መጠኑ ሲሆን ካሳው የሚከፈልበትን አግባብ በተመለከተም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የሕጉ ክፍል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29 (2) ድንጋጌ ስር አስፍሯል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በርትዕ አስፈላጊ ሆኖ ሲታይ ስዕሉን

www.abyssinialaw.com

በአደባባይ በመለጠፍ፤ በማሳየትና በመሸጥ የተጠቀመው ሰው በዚሁ ምክንያት ያገኘው ሀብት ተመዛዛኝ በሚሆንበት መጠን ዳኞች ካሳ እንዲከፍል ሊወስኑበት እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች የካሳውን መጠን ተገቢነት የለውም በማለት በመከራከሩና ተጠሪዎችም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 በተመለከተው አግባብ ትክክለኛውን የካሳ መጠን በማስረጃ ያለማስረዳታቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የካሳውን መጠን ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) እንዲሆን የወሰነ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የካሳ መጠኑን የተጠሪ ምስል በማስታወቂያው ከተገለጸው ከአመልካች ተግባር ጋር የሚኖረውና ሊያስገኝ ከሚችለው ጥቅም አንፃር፤ከነባራዊው ሁኔታ በመነሳት በመመርመር በተጠሪ የተጠየቀውን የካሳ መጠን የበዛ ሁኖ ማግኘቱን ጠቅሶ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) የካሳ መጠን ሊሆን እንደሚገባ ወስኗል፡፡ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች የካሳ ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡ ሲጠቃለልም ካሳን አስመልክቶ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸውን የጉዳት ካሳ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 180602 በ16/04/2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 153194 በ28/06/2010 በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተብሎ በርትዕ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ - 153736

ቀን - 28/01/2011ዓ.ም

**ዳኞች:-** ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

**አመልካቾች:-** 1. አረቡ አብደላ } ጠበቃ በቀለ ተፈራ እና ታምሬ ኃይሌ

2. ታከለ ለገሰ

3. አማረ ኪ. -አልቀረበም።

**ተጠሪ:-** አዱኛ ጓዴ- ከጠበቃ ሰለሞን ጋር ቀርበዋል።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካቾች ደግሞ፣ በቅደም ተከተል፣ ከ1-3ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል። ተጠሪ በቀን 01/07/07 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት ክስ:- ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በገበያ ላይ የነበሩ እና እንደገና ተሻሽለዉ በ2006 ዓ.ም ታትመዉ በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከተመዘገቡት አድቫንስድ ዎርሊድ ኢንግሊሽ ቡክ 1 እና 2 መጽሀፎችን አዘጋጅተዉ መጽሐፎቹም በ 15,000 ኮፒ ታትመዉ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ገበያ ላይ መዋላቸዉን እና በገበያ ተቀባይነት አግኝተዉ ኮፒዎቹ ሙሉ እንደተሸጡ፤ ይሁንና ያለ ከሳሽ ፈቃድ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ምሳሌዎችን፣ አገላለፆቹን እና ማብራሪያዎቹን ቃል በቃል እና በማመሳሰል በቀጥታ ከከሳሽ መጽሐፎች በመቅዳት ኢክስትሪም ስሪዬስ እንግሊሽ ፎር ግሬድ 11-12 በሚል ርዕስ አዘጋጅተዉ መሸጣቸዉን እና 1ኛ ተከሳሽም መጽሐፎቹን ማሳታሙን፤ ከሳሽ ያዘጋጃቸዉ 8,000.00 መጽሐፎችም በዚህ ምክንያት

www.abyssinialaw.com

ገዥ አጥተዉ በከሳሽ ላይ የብር 200,000.00 ኪሳራ መድረሱን ጠቅሰዉ ብር 100,000.00 የሞራል ኪሳራን ጨምሮ ብር 300,000.00 ተከሳሾች እንዲከፍሉ፣ እንዲሁም የታተሙት እንዲወገዱ እና ለወደፊትም እንዳይታተሙ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ፤ ከከሳሽ መጽሐፍ አልተገለበጠም እንጂ ተገልብጧል ቢባል እንኳ ከሳሽ የስራዬ አካል ናቸዉ የሚላቸዉ ጽንሰ ሃሳቦች ከብሔራዊ ፈተና የተወሰዱ ጥያቄዎች እና ምሳሌዎች፣ ማብራሪያዎች እና አገላለፆች የህዝብ ንብረት መሆናቸዉን፤ በመጽሐፎቹ መካከል መመሳሰል አለ ቢባል እንኳ ስራዎቹ የእንግሊዘኛ መማሪያ መፅሀፍት፣ ካሪኩለም፣ ሀገር አቀፍ ፈተናዎችን መሠረት በማድረግ የታወቁ ሳይንሳዊ የቋንቋ አፃፃፍ መርሆ ስርዓትና ህግ በመከተል ተቀራራቢ የእንግሊዘኛ ትምህርት ዝግጅት ባላቸዉ መምህራን የተዘጋጁ በመሆናቸዉ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰዉ ከሳሽ የቅጅ መብት እንደሌላቸዉ፣ የተጠየቀዉ የጉዳት ካሳ መጠንም ማስረጃን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ጠቅሰዉ የተከራከሩ ሲሆን፤ 2ኛ ተከሳሽም 1ኛ ተከሳሽ ካቀረቡት ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ክርክር በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ 3ኛ ተከሳሽ ባለመቅረባቸዉ ክርክሩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተጠሪ ያቀረቧቸዉ ማስረጃዎች አመልካቾች ከተጠሪ መጽሀፍ ቃል በቃል ወስደዋል ከማለት ዉጪ ምን ያህል ፐርሰንት እንደተወሰደ፣ የትኛዉ አገላለጽ፣ የትኛዉ ምሳሌ እና ማብራሪያ በቀጥታ እንደተወሰደ እንዲሁም የቋንቋ አፃፃፍ መርሆዎች እና ጽንሰ ሃሳቦቹ በአገላለጽ፣ ማብራሪያ እና ምሳሌዎቹ በተለያየ አገላለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር፣ የአሠራር ሂደቱ እና ዘዴዉ፣ ተጠሪ ያወጣዉ ማዉጫ እና ምዕራፍ በተለየ ሲስተም የተብራራ እና የተተነተነ መሆኑ እንዲሁም ከግራመር አጠቃቀም ሁኔታ አንፃር ሲታይ የአመልካች ስራ በቀጥታ ከተጠሪ የተወሰደ መሆኑን በአግባቡ የሚያስረዳ ማስረጃ አለመቅረቡን ጠቅሶ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ተጠሪ ካዘጋጃቸዉ መጽሐፍት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሳያ ምሳሌዎችንና ማብራሪያዎችን በቀጥታ ምንጭ

www.abyssinialaw.com

ሳይጠቅሱ ወስደዉ በጽሑፋቸዉ የተጠቀሙ ስለመሆኑ ተጠሪ ካቀረባቸዉ የሰዉ ምስክሮች በተጨማሪ የኮተቤ ዩንቨርሲቲ ኮሌጅ ለቂርቆስ ክ/ከተማ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዲቪዝዮን በላከዉ ደብዳቤ የተረጋገጠ መሆኑን፤ ይህም በአገራችን የቅጅ መብት ጥበቃ የተደረገዉ ለሃሳብ አገላለጽ ቅርጽ ከመሆኑ እና ከቅጅ መብት ጥበቃ አስፈላጊነት አንፃር ሲታይ የተጠሪ የቅጅ መብት በተጠሪ የተጣሰ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ አመልካቾች ኃላፊነት አለባቸዉ በሚል የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሮ በአመልካቾች ላይ ሊወሰድ የሚገባዉን እርምጃ በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ተገቢዉን እንዲወስን ሲል መዝገቡን ወደ ስር ፍርድ ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 07/06/2010 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ባቀረቡት 8 ገጽ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ ስራዎች በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 6(1)(ሀ) ስር የተመለከተዉን የወጥነት መመዘኛ የማያሟላ መሆኑን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፖሊስን የምርመራ መዝገብ በማስረጃነት ያስቀረበበት ሂደትም የአመልካቾችን የመከራከር መብት የሚያጣብብ መሆኑን፣ 1ኛ አመልካች የመጽሐፎቹ አሳታሚ ወይም አዘጋጅ ስለመሆናቸዉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ "አረቡ አብደላ ኤክስትሪም ቡክ ሲሪየስ" የሚል በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልነበረዉን አዲስ ስያሜ በመስጠት 1ኛ አመልካች ኃላፊነት እንዳለባቸዉ መወሰኑን እና ሌሎችንም ነጥቦች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ አመልካቾች የቅጅ መብት ጥሰት ፈጽመዋል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም፡-

www.abyssinialaw.com

1. ተጠሪ ለክሱ መሠረት ባደረጋቸዉ ሁለቱ መጽሐፎች ላይ የቅጅ መብት አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? መብት አላቸዉ የሚባል ከሆነ አመልካቾች የቅጅ መብት ጥሰት ፈጽመዋል አልፈጸሙም?
2. 1ኛ አመልካች ለተጠሪ ስለሚኖረዉ ኃላፊነት ተለይቷል ወይስ አልተለየም? የሚሉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸዉ ጭብጦች ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

በመሠረቱ የቅጅ መብት አጠቃላይ ዓላማ የፈጠራ ባለሞያዎች የፈጠራ ስራዎቻቸዉን ለማከናወን ያፈሰሱትን ዕዉቀት፣ ጊዜና ሀብት እንዲያካክሱና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ሆነዉ ለተጨማሪ የፈጠራ ስራ እንዲነሳሱ በማድረግ ቀጣይ የፈጠራ ስራን በማበረታት ኢንቨስትመንት እንዲበረታታ አቅም ለመፍጠር ሲሆን፤ ኢ- ቁሳዊ ከሆኑ የንብረት መብቶችም አንዱ ገጽታ ነዉ፡፡ በመሆኑም መንግስት በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 91(3) ስር የተመለከተዉን ኪነጥበብን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጅን ለማስፋፋት ባለበት ግዴታ መሠረት፣ የቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/96 አወጥቶ ስራ ያዋለ ሲሆን፤ ለአዋጁ መዉጣት አስፈላጊ ከሆኑት ምክንያቶች ዉስጥም አንዱ የስነ ጽሑፍ፣ የኪነ ጥበብ እና ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎች የአንድ አገር ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሳይንሳዊ እና ቴክኖሎጂያዊ ልማት በማፋጠን ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸዉ የሚበረታቱበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ስለመሆኑ ከአዋጁ መግቢያ ላይ ከተመለከተዉ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን አጠቃላይ ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም አዋጁ የቅጅ መብትን የሚያስገኙ ስራዎች፣ ጥበቃ የማይደረግላቸዉ ስራዎች ዓይነት፣ የቅጅ መብት ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎችን ጨምሮ የተለያዩ ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል፡፡ አዋጁ የስራዉ አመንጪ በስራዉ ላይ የሚኖራቸዉን ኢኮኖሚያዉ እና የሞራል መብቶችን የሚደነግግ ሲሆን፤ ኢኮኖሚያዊ መብት ስራዉን የማባዛት፣ የመከወን፣ ብሮድካስት የማድረግ፣ ወደ ሌሎች ስራዎች የመለወጥና ሌሎች ብቸኛ መብቶችን የሚያካትት ሲሆን፤ የሞራል መብቱ ደግሞ የፈጠራ ስራዉ አመንጪ የመባል፣ ስራዎቹ እንዳይዛቡ የማድረግና መሰል መብቶችን የሚያካትት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 7 እና 8 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ በመሆኑም ያለፈቃዱ በአዋጁ አንቀጽ 7(1) ስር የተመለከቱት ተግባራት በሌላ ሰዉ እንዳይፈጸሙ የስራዉ አመንጪ የመከልከል መብት ያለዉ ሲሆን፤ በዚህ ስር ከተመለከቱት ዉስጥም አንዱ ስራን ማመሳሰል፣ ማቀናበር ወይም ወደ ሌላ ዓይነት መቀየር የማይቻል መሆኑን

www.abyssinialaw.com

በተመለከተ በአንቀጽ 7(1)(ሐ) ስር የተመለከተዉ ነዉ፡፡ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄም ይህኑን መሠረት ያደረገ ሆኖ በመጽሐፎቼ ላይ የተመለከቱትን ምሳሌዎች፣ አገላለጾችን እና ማብራሪያዎችን አመልካቾች ያለ ተጠሪ ፈቃድ ወስደዉ ኢክስትሪም እንግሊሽ ፎር ግሬድ 11-12 በሚል መጽሐፍ አካተዉ አሳትመዋል የሚል ሲሆን፤ አመልካቾች በበኩላቸዉ ኃላፊነት የለብንም ሲሉ አጥብቀዉ የሚከራከሩት የተጠሪ መጽሐፍቶች የትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀዉን ካሪኩለም፣ ሲለበስ፣ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት፣ የመምህር መምሪያን ይዘትና ዓላማን መሠረት በማድረግ የታወቀና ሳይንሳዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አፃፃፍ ስርዓትን እና ሰዋሰዉ መርህን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የተጠሪ ስራ በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ የተመለከተዉን የወጥነት መመዘኛ የማያሟላ መሆኑን፤ እንዲሁም በመጽሐፎቹ መካከል መመሳሰል አለመኖሩን ስለመሆኑ የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት ያስገነዝባል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኝን የሰዉ ምስክር የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻ የተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ሲወስን እንደ ምክንያት የጠቀሰዉ የተጠሪ መጽሐፎች መርሆዎቹ እና ጽንሰ ሃሳቦቹ በአገላለጽ፣ ማብራሪያ እና ምሳሌዎች በተለያየ አገላለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገሩ፣ የአሠራር ሂደቱ፣ የአሠራር ዘዴዉ፣ ማዉጫዉ እና ምዕራፉ፣ እንዲሁም የግራመር አጠቃቀሙ የተጠሪ ስራ ስለመሆኑ፤ እንዲሁም የተጠሪዎች መጽሐፎች ቀጥታ ከተጠሪ ስራዎች የተገለበጡ ስለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ አመልካቾች ኃላፊነት አለባቸዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ አመልካቾች ያዘጋጁት መጽሐፍ ተጠሪ ካዘጋጃቸዉ መጽሐፎች ጋር ከፍተኛ መመሳሰል ያለ ስለመሆኑ የኮቴቤ ዩኒቨርሲቲ ቀደም ሲል ለወንጀል ምርመራ ዓላማ ለፖሊስ ጽ/ቤት ጽፎ የነበረዉ ደብዳቤ የሚያስረዳ መሆኑን በመጥቀስ ስለመሆኑ ከየዉሳኔዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከቅጅ መብት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች የሚጣሩበት አግባብም ሆነ ክርክሮቹን መሠረት በማድረግ የሚሰጡ ዉሳኔዎች፣ ከፍ ሲል የተመለከተዉን፣ የቅጅ መብት ጥበቃ አጠቃላይ ዓላማ መሠረት ሊያደርጉ የሚገባ በመሆኑ፤ የተጠሪ ስራ ወጥነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ እንዲሁም የአመልካቾች ስራዎች ከተጠሪ ስራዎች የተወሰዱ መሆን አለመሆኑ ይህኑን ግምት ባስገባ መልኩ መጣራት አለበት የሚል እምነት አለን፡፡

www.abyssinialaw.com

አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 2(30) የቅጅ መብት ጥበቃ የሚደረግላቸዉን ስራዎች ዓይነት ሲዘረዝር፣ የአዋጁ አንቀጽ 6 በስራዎቹ ላይ የቅጅ መብት ጥበቃ ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ መመዘኛዎችን ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ሰዉ የቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ለማግኘት፣ ስራዎቹ ሁለት መመዘኛዎቹን ማሟላት የሚጠበቅባቸዉ ሲሆን፤ የመጀመሪያዉ ወጥ (original) መሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ግዙፍነት ያለዉ መሆኑ ነዉ፡፡ ወጥነት በስራ አመንጪዉ የተሰራዉ ስራ ሙሉ በሙሉ ከሌሎች ስራዎች ያልተቀዳ መሆን እንዳለበት የሚገልጽ ሃሳብ ሲሆን፤ ስራዎቹ ከሌሎች ስራዎች ጋር በፍጹም መመሳሰል የለባቸዉም ማለት እንዳልሆነ ግን መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ይልቁንም ስራዉ ወጥነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ ረገድ መታየት የሚገባዉ ነጥብ፣ በስራዉ ላይ የተለየ የባለ ስራዉ ችሎታ (skill)፣ ጉልበት (labour) ስራ ላይ መዋሉ፤ እንዲሁም፣ በተለይም በአዋጁ አንቀጽ 4(1)(ለ) ስር ከተመለከተዉ አንፃር ሲታይ፣ የስራዉ ባለቤት ስራዉን ሲሰራ የራሱ የሆነ የአገላለጽ መንገድ፣ ዘዴ እና ስታይል የተጠቀመ መሆን አለመሆኑ ስለመሆኑ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ግዙፋዊ መሆን አለበት ሲልም፣ ስራዉ በሃሳብ ደረጃ የቀረ ሳይሆን በወረቀት ላይ የሰፈረ ሊሆን ይገባል ለማለት እንደሆነ ከድንጋጌዉ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ በአዋጁ የተመለከቱት የወጥነት እና የግዙፋዊነት መስፈርቶች መሠረተ ሃሳብ ከላይ የተመለከቱ ሲሆኑ፣ የስራዉ አመንጪ የሰራዉ ስራ እነዚህን መስፈርቶች ማሟላቱ ከተረጋገጠ ያለ ምንም ሌላ ቅድመ ሁኔታ የቅጅ መብት ጥበቃ የሚሰጠዉ ስለመሆኑም አዋጁ ያመለክታል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ አመልካቾች የተጠሪ ስራ የወጥነትን መስፈርት አላሟላም በማለት የሚከራከሩት፣ የተጠሪ መጽሐፍቶች የትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀዉን ካሪኩለም፣ ሲለበስ፣ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት፣ የመምህር መምሪያን ይዘትና ዓላማን መሠረት በማድረግ የታወቀና ሳይንሳዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አፃፃፍ ስርዓትን እና ሰዋሰዉ መርህን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት ያደረጉ መሆኑን ነዉ፡፡ በርግጥ ተጠሪ መጽሐፎቹን ሲያዘጋጅ፣ እነዚህኑን መሠረት አድርጎ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና፣ እላይ እንደተመለከተዉ፣ ተጠሪ የራሱን የተለየ ችሎታ እና ጉልበት እንዲሁም የአፃፃፍ ስታይል እና የአፃፃፍ ዘዴ በመጠቀም መጽሐፎቹን ማዘጋጀታቸዉ ከተረጋገጠ፤ መጽሐፎቹ ትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀዉን ካሪኩለም፣ ሲለበስ፣ የተማሪዎች መማሪያ

መጽሐፍት፣ የመምህር መምሪያን ይዘትና ዓላማን መሠረት በማድረግ የታወቀና ሳይንሳዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አፃፃፍ ስርዓትን እና የሰዋሰዉ መርህን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት በማድረግ ማዘጋጀታቸዉ ብቻ፣ በአዋጁ አንቀጽ 6(1) መሠረት፣ ስራቸዉ የወጥነትን መስፈርት አያሟላም ወደሚል ድምዳሜ የሚወስድ አይሆንም፡፡ በሌላ አገላለጽ ተጠሪ ከላይ የተመለከቱትን ስራዎች፣ ጽንሰ ሃሳቦችን እና መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ያዘጋጁት ለክርክሩ መነሻ የሆኑት መጽሐፎች ይዘት፤ ተጠሪ በዝግጅቱ ሂደት የራሳቸዉን የተለየ ችሎታ፣ ጉልበት፣ የአፃፃፍ ዘዴ እና ስታይል መጠቀማቸዉን የሚያሳይ ከሆነ በመጽሐፉ ላይ የቅጅ መብት የማያገኙበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ መጽሐፎች የወጥነትን መስፈርት የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት ተይዞ በማስረጃ ተጣርቶ እልባት ማግኘት የነበረበት ትክክለኛ ጭብጥ፣ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት የተጠሪ መጽሐፎች ቀደም ሲል የተሰሩ ስራዎችን እንዲሁም የእንግሊዘኛ አፃፃፍ መርሆዎችን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት ያደረጉ መሆን አለመሆናቸዉ ሳይሆን፣ መጽሐፎቹ በይዘታቸዉ የተጠሪን የተለየ ችሎታ፣ የአፃፃፍ ዘዴ እና ስታይል የሚያሳዩ መሆን አለመሆናቸዉ ነዉ፡፡ ይሁንና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አስፈላጊዉን ማጣሪያ ሳያደርግ አመልካቾች በዚህ መልኩ ያቀረቡትን ክርክር በደፈናዉ በመቀበል የተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ማድረጉን ተመልክተናል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ቢሆን፣ አመልካቾች ያዘጋጁት መጽሐፎች ተጠሪ ካዘጋጃቸዉ መጽሐፎች ጋር የሚመሳሰሉ መሆን አለመሆኑን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን የተመለከተ ሲሆን፣ የተጠሪ ስራ በአዋጁ አንቀጽ 6(1) ስር የተመለከተዉን የወጥነት መስፈርት የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር ያልመረመረ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ መነሻ የሆኑት የተጠሪ መጽሐፎች የወጥነት መስፈርት የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በጭብጥነት ተይዞ በማስረጃ ተጣርቶ እልባት ያልተሰጠዉ ሆኖ አግኝተንዋል፡፡

የተጠሪ መጽሐፎች ከላይ በተመለከተዉ ጭብጥ መሠረት ተጣርተዉ የወጥነትን መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸዉ ከተረጋገጠ፣ ቀጥሎ የሚመጣዉ ጥያቄ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ባዘጋጁት መጽሐፍ በተጠሪ መጽሐፎች የተመለከቱትን አገላለፆች፣ ምሳሌዎች እና ማብራሪያዎች ወስደዉ የመጽሐፎቹ አካል ማድረግ አለማድረጋቸዉ

www.abyssinialaw.com

ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ የተጠሪ ክርክር በመጽሐፎቹ መካከል መመሳሰል የለም እንጂ አለ እንኳ ቢባል ስራዎቹ የእንግሊዝኛ መጽሐፍት፣ የመምህር መመሪያ፣ አገር አቀፍ ፈተናዎችን መሠረት በማድረግ የታወቁ ሳይንሳዊ የቋንቋ አፃፃፍ መርሆ፣ ስርዓትና ህግ በመከተል ተቀራራቢ የእንግሊዝኛ ትምህርት ዝግጅት ባላቸዉ መምህራን የተዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት እንደሚሆን በመግለጽ የሚከራከሩ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በመሰል ጉዳይ የቅጅ መብት ጥበቃ መብት የሚሰጠዉ ሃሳቡ ሳይሆን፣ ሃሳቡ የተገለጸበት ቅርጽ፣ የተገለጸበት መንገድ እና ዘዴ ስለመሆኑ በቅጅ መብት ጥበቃ ተቀባይነት ያገኘ መርህ ነዉ፡፡ አንድ ሰዉ አንድን መጽሐፍ ሲያዘጋጅ፣ መጽሐፉ ተነባቢ እንዲሆን እና አንባቢዉ በቀላሉ ሊረዳ እንዲችል ሃሳቡን የሚገልጽበት የራሱ የሆነ ዘዴ እና ስታይል ይጠቀማል፡፡ የስራ አመንጪዉ ይህን ሲያደርግም ለስራዉ ጊዜ ሰጥቶ፣ የተለየ ችሎታዉን (skill) እና ጉልበቱን (labor) ተጠቅሞ በመሆኑ በቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ አንቀጽ 2(8) መሠረት በስራዉ ላይ የቅጅ መብት ባለቤት ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ ተጠሪ መጽሐፎቹን ሲያዘጋጅ የእንግሊዝኛ መጽሐፍት፣ የመምህር መመሪያ እንዲሁም ሳይንሳዊ የቋንቋ አፃፃፍ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ሆኖ ግን የራሱን የተለየ ችሎታ በመጠቀም፤ አንባቢ (ተማሪ) በቀላሉ እንዲረዳዉ ማድረግ በሚያስችል መልኩ፣ በመጽሐፎቹ ለተጠቀማቸዉ አገላለፆች፣ ምሳሌዎች እና ማብራሪያዎች የቅጅ መብት ጥበቃ ያገኛል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ለተገቢ አሠራር እና ዓላማ የስራዉን ምንጭ እና የተጠሪን ስም በመጥቀስ ስራዉን መጠቀም ከሚችሉ በስተቀር (የአዋጁ አንቀጽ 10 ይመለከቷል)፣ ተጠሪ በመጽሐፉ ያካተታቸዉን አገላለፆች፣ ምሳሌዎች እና ማብራሪያዎችን እንዳለ በመዉሰድ የመጽሐፎቻቸዉ አካል ማድረግ ይችሉ ዘንድ የቅጅ መብት አዋጁ አይፈቅድላቸዉም፡፡ ይህን ማድረጋቸዉ ከተረጋገጠ በተጠሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም፣ አመልካቾች በመጽሐፎቹ የተጠቀሙባቸዉ ምሳሌዎች፣ አገላለፆች እና ማብራሪያዎች ከተጠሪ መጽሐፍ የተወሰዱ መሆን አለመሆናቸዉ በጭብጥነት ተይዞ በማስረጃ ተረጋግጦ መወሰን የሚገባዉ ነዉ፡፡ ይሁንና፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ አላጣራም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህኑን በጭብጥነት በመያዝ የቅጅ መብት ተጥሷል በሚል ድምዳሜ ላይ ሲደርስ በዋነኛነት የጠቀሰዉ ማስረጃ ከኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ተልኳል የተባለን ደብዳቤ ነዉ፡፡ ይህ

www.abyssinialaw.com

ለወንጀል ምርመራ ዓላማ የተፃፈ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች በማስረጃዉ ላይ አስተያየት ያልሰጡበት በመሆኑ ብቻዉን እምነት የሚጣልበት አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከተጠሪ መጽሐፍ ምሳሌዎችን፣ ማብራሪያዎችን እና አገላለፆችን ወስደዉ በመጽሐፎቻቸዉ በመጠቀም የቅጅ መብት ጥሰት የፈጸሙ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ተረጋግጧል ለማለት አይቻልም፡፡

ወደ ሁለተኛዉ ጭብጥ ስንመለስ፣ ተጠሪ 1ኛ አመልካችን 1ኛ ተከሳሽ አድርገዉ ክስ ሲያቀርቡ መጽሐፎቹን አሳትሟል በሚል ነዉ፡፡ 1ኛ አመልካች በበኩሉ መጽሐፎቹን አለማሳተሙን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መጽሐፎቹን ያሳተመ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዞ ወደ ማጣራቱ አልሄደም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ አላጣራም፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል በዝርዝር ከተመለከቱት ዝርዝር ምክንያቶች አንፃር ሲታይ፣ በስር በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጡት ዉሳኔዎች መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ሆኖ ስላገኘን ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 162017 በቀን 02/02/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 148704 በቀን 21/05/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም ስለ ቅጅ መብት ዕዉቀትና ልምድ ያላቸዉ ባለሙያዎች የተካተቱበትን አጣሪ ቡድን በማቋቋም እንዲያጣሩ በማድረግ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት የተመለሰለት ሲሆን፣ መጣራት ያለባቸዉ ጭብጦቹም፡-

2.1. የተጠሪ መጽሐፍቶች የትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀዉን ካሪኩለም፣ ሲለበስ፣ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት፣ የመምህር መምሪያን ይዘትና ዓላማን መሠረት በማድረግ የታወቀና ሳይንሳዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አፃፃፍ ስርዓትን

www.abyssinialaw.com

እና ሰዋሰዉ መርህን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሆኖ ግን በዝግጅቱ ሂደት የራሳቸዉን (የተጠሪን) የተለየ ችሎታ፣ ጉልበት፣ የአፃፃፍ ዘዴ እና ስታይል የተጠቀሙ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ የተጠሪ ስራ ወጥነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን፤

2.2. የተጠሪ ስራ የወጥነትን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ አመልካቾች ተጠሪ በመጽሐፎቻቸዉ የተጠቀሙባቸዉ ምሳሌዎች፣ ማብራሪያዎች እና አገላለፆች ከተጠሪ መጽሐፎች የተወሰዱ መሆን አለመሆናቸዉን፤

2.3. 1ኛ አመልካች ለተጠሪ ኃላፊነት ያለበት መሆን አለመሆኑ ናቸዉ፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

4. ይህ ችሎት በቀን 21/10/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

www.abyssinialaw.com

የሰ.መ.ቁ 153527

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ ስንዴው ታደሰ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ

ነ/ፈጅ ዳኛቸው ጌቴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 05 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 23848 ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01005837 ሕዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ምክንያት የወሮታ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የቀረጥ እና ታክስ እንዲሁም ወለድ እና ቅጣት መጠናቸው በግምት ብር 2,475,000 /ሁለት ሚልዬን አራት መቶ ሰባ አምስት ሺህ / የሆኑ

www.abyssinialaw.com

ከቀረጥ ነጻ የገቡ የፏበል ዱቄት ፋብሪካ ማሽነሪዎች ያላግባብ ለሶስተኛ ወገን ተላልፈዋል በማለት ለተጠሪው መስሪያ ቤት ጥቆማ የሰጠ መሆኑን፣በጥቆማው መሠረት ምርመራ ተደርጎ ንብረቶቹ ለሶስተኛ ወገን መተላለፋቸው የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ ከዚሁ የገንዘብ መጠን ላይ ብር 495,000 / አራት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር / እንዲከፈለው ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ባልሰበሰበው ቀረጥ እና ታክስ የወሮታ ክፍያ እንዲፈጽም የማይገደድ መሆኑን፣ከቀረጥ ነጻ የገቡትን ዕቃዎች ድርጅቱ ለብድር ዋስትና በማስያዝ ከዳሽን ባንክ ብድር ተበድሮ ድርጅቱ ብድሩን መመለስ ባለመቻሉ ባንኩ በአዋጅ 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሕጋዊ ጨረታ ለቅን ልቦና 3ኛ ወገን ያስተላለፋቸው መሆኑን፣በመመሪያ ቁጥር 78/2004 ከቀረጥ ነጻ የገባን ዕቃ በማስተላለፍ የቀረበን ጥቆማ ክፍያ የሚፈጸመው ዕቃው ከተያዘ በኋላ ቀረጥ እና ታክስ ተሰልቶ ከሚገኘው ገንዘብ ሆኖ ሳለ ባልተያዘ ንብረት እና ባልተሰበሰበ ቀረጥ እና ታክስ ላይ ወሮታ እንዲከፈል የቀረበው ክስ ሕጋዊ አለመሆኑን እና በክሱ የተገለጸው የገንዘብ መጠን ያልታወቀ እና ምንም ዓይነት ማስረጃ ያልቀረበበት መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ዕቃዎቹ ለብድር በያዘው ዳሽን ባንክ ተሸጠው ለ3ኛ ወገን የተላለፉ በመሆኑ ንብረቶቹን በመያዝ እና በመሸጥ ቀረጥ እና ታክስ ለመሰብሰብ የሚቻል አይደለም፣ድርጅቱም ስራ ስላቆመ ሌሎች ንብረቶችን ማግኘት አልተቻለም፣በመመሪያ ቁጥር 78/2004 መሠረት ወሮታ የሚከፈለው ዕቃው ከተያዘ በኋላ ተሰልቶ ከሚገኘው ገንዘብ ላይ ነው፣ባንኮች ብድራቸውን ለማስመለስ ቀዳሚ መብት ስላላቸው ዕቃው የተሸጠ በመሆኑ ባልተያዘ እና ባልተሰበሰበ ቀረጥ እና ታክስ ላይ የሚከፈል ወሮታ የለም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች በሰጠሁት ጥቆማ መሠረት ምርመራ ተጣርቶ ማሽነሪዎቹ ለሌላ ሶስተኛ ወገን መተላለፋቸው ተረጋግጧል፣

www.abyssinialaw.com

አመልካች በሕግ የተፈቀደልኝን 20% የወሮታ ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍለኝ የጠየቅኩ ቢሆንም ተጠሪ መስሪያ ቤት ንብረቶቹን ገቢ ማድረግ ሲኖርበት ሀላፊነቱን ሳይወጣ ባንኮች ንብረቱን ለመሸጥ መብት አላቸው የሚል ምክንያት በመስጠት ለመክፈል ፈቃደኛ አይደለም፤ጥቆማ የቀረበባቸው ማሽነሪዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ መግባታቸው እና ቀረጥ እና ታክሳቸው ሳይከፈል ወደ 3ኛ ወገን የተላለፉ መሆኑ አልተካደም፤ ከቀረጥ ነጻ ሆኖ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ ቀረጥ እና ታክሱ ሳይከፈልበት ተመሳሳይ የቀረጥ ነጻ መብት ለሌለው ማንኛውም ሰው ማስተላለፍ ወይም የቀረጥ ነጻ መብት ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ መገልገል ወይም በሌሎች ሰዎች ይዞታ እና አገልግሎት እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ሲሆን ይህንኑ የተላለፈ ማንኛውም ሰውም የወንጀል ሀላፊነት አለበት፤ባንኮች የቀረጥ ነጻ መብት በሕጉ ከተቀመጠው ዓላማ ውጪ እንዲያውሉ አልተፈቀደላቸውም፤ባንኩ ንብረቶቹን በዋስትና ሲይዝ ከቀረጥ ነጻ የገቡ መሆናቸውን ያውቃል፤ተጠሪ ጥቆማው ከደረሰው በኋላ ምርመራውን በአግባቡ ባለማከናወኑ መጠኑ ሊታወቅ ያልተቻለ ቢሆንም አመልካች ተገቢውን ጥቆማ የሰጠሁ በመሆኑ ወሮታው ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ከቀረጥ ነጻ የገባው ዕቃ ለባንክ ብድር መያዣበመዋሉ ምክንያት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2008 እና አዋጅ ቁጥር 859/2008 መሠረት የጠየቁት የወሮታ ክፍያ ሊያገኙ አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የንጋት ጸሐይ ዱቄት ፋብሪካ ከዳሽን ባንክ ጋር ለፈጸመው የብድር ውል ማሽነሪዎቹን በዋስትና ያስያዘው ጥቅምት 29 ቀን 1999 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 622/2001 እና 859/2006 ሳይሆን በወቅቱ የነበረው አዋጅ ቁጥር 60/90 ነው፤ድርጅቱ ዕቃዎቹን በዋስትና ባስያዘበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 / እንደተሻሻለው / ከቀረጥ ነጻ የገቡ ዕቃዎችን ለባንኩ ብድር በመያዣነት ሊውሉ እንደሚችሉ በግልጽ የሚፈቅድም ሆነ የሚከለክል ድንጋጌ የለውም፤ዕቃዎቹም ከቀረጥ ነጻ የገቡ ስለመሆናቸው ባልተረጋገጠበት እና በማስረጃ ባልተደገፈበት ሁኔታ የጠቋሚ ወሮታ የሚከፈልበት

www.abyssinialaw.com

አግባብ የለም፤መመሪያ ቁጥር 78/2004 የወጣውም አዋጅ ቁጥር 622/2001 ለማስፈጸም ሲሆን ድርጊቱ ተፈጸመ የተባለው ደግሞ አዋጅ እና መመሪያው ከመውጣቱ በፊት በመሆኑ ጠቋሚው ከመጀመሪያውኑ ወሮታ የማግኘት መብት አልተጎናጸፈም፤ድርጅቱ ምን ዓይነት ዕቃዎችን እንዳስገባ? መቼ እዳስገባ? ምን ያህል ቀረጥ እና ታክስ መክፈል እንደነበረበት? ያልተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ሳይረጋገጥ ወሮታ የሚከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፤ዕቃዎቹ በቀረጥ ነጻ የገቡ ናቸው የሚባል ቢሆን እንኳን ከቀረጥ ነጻ የገቡ ዕቃዎችን ባንክ ዋስትና ይዞ በሚሸጥበት ጊዜ ወሮታ ይከፈላል የሚል ሕግ የለም፤ግለሰቡ ከመጀመሪያውም የሰጠው መረጃ እንጂ ጥቆማ አይደለም፤በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 5/1/ሀ በህዝብ የሚታወቁ ሕገወጥ ዕቃዎች የሚገኙባቸውን ቦታዎች መጠቆም ባለመብት የሚያስደርግ ጥቆማ አይደለም፤ከቀረጥ ነጻ የገቡ ቢሆንም በሕጋዊ ሁኔታ ወደ 3ኛ ወገን የሚተላለፉበት ሁኔታ አለ፤ይህ በሕግ የተቀመጠ ልዩ ሁኔታ እያለ ለመንግስት ተጨባጭ ማስረጃ ባልሰጠበት እና መንግስት ከጥቆማው ያገኘው ጥቅም በሌለበት ሁኔታ ወሮታ ሊከፈል አይገባም፤በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 16/1 እና 2 አንድ ጠቋሚ ወሮታ ሊሰጠው የሚችለው ሕገወጥ ዕቃው ከተያዘ እና ለባለስልጣኑ ገቢ ከተደረገ ነው፤ወሮታ ማግኘት የሚችለውም ለባለስልጣኑ ገቢ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ነው፤የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በባንክ በዋስትና የተያዙ ንብረቶች ሲሸጥ የተገኘው ገቢ በቅድሚያ የባንክ እዳ ለመሸፈን በማዋል ቀሪ ገንዘብ ካለ ብቻ ለመንግስት ዕዳ ክፍያ እንዲውል የወሰነ በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አመልካች ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደ ሐገር ውስጥ የገቡ የፏበል ዱቄት ፋብሪካ ማሽነሪዎች አላግባብ ለሶስተኛ ወገኖች ተላልፈዋል በማለት ለተጠሪው መስሪያ ቤት ጥቆማ የሰጠ መሆኑን፤ንብረቶቹ የተላለፉለት የንጋት ጸሐይ ዱቄት ፋብሪካ ከዳሽን ባንክ ጋር ለፈጸመው የብድር ውል ጥቅምት 29 ቀን 1999 ዓ.ም ማሽነሪዎቹን በዋስትና ያስያዘ መሆኑን፤ተበዳሪው ድርጅት ከባንኩ የተበደረውን ገንዘብ መክፈል ስላቃተው ባንኩ

www.abyssinialaw.com

በአዋጅ 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ንብረቶቹን በሕጋዊ ጨረታ ለቅን ልቦና 3ኛ ወገን ያስተላለፋቸው መሆኑን፤ከቀረጥ ነጻ ገብተዋል የተባሉት ዕቃዎች ምን ዓይነት ዕቃዎች እንደሆኑ? መቼ እንደገቡ? የቀረጥ እና ታክስ መጠናቸው ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ መሆኑን እና ተጠሪው መስሪያ ቤት ከንብረቶቹ የሰበሰበው የቀረጥ እና ታክስ ክፍያ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሠጣጥ፤አያያዝ እና አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 16/1እና2 ድንጋጌ ለባለሥልጣኑ በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ያለጥቆማ ሕገወጥ ዕቃው ከተያዘ እና ለባለስልጣኑ ገቢ ከተደረገ ጠቋሚው፤ያዥው፤ትብብር እና ድጋፍ ያደረጉት በሙሉ በመመሪያው መሠረት ወሮታ የሚከፈላቸው መሆኑን፤የወሮታው ክፍያ የሚከፈለውም ሕገወጡ ዕቃ በመመሪያው አንቀጽ 17 መሠረት ለባለስልጣኑ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ መሆኑን በመግለጽ ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደ ሐገር ውስጥ የገቡ የፈበል ዱቄት ፋብሪካ ማሽነሪዎች አላግባብ ለሶስተኛ ወገኖች ተላልፈዋል በማለት ለተጠሪው መስሪያ ቤት ጥቆማ የሰጠ መሆኑን በመግለጽ የወሮታ ክፍያው ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከቀረጥ ነጻ ገብተዋል የተባሉት ንብረቶች የተላለፉለት የንጋት ጸሐይ ዱቄት ፋብሪካ ከዳሽን ባንክ ጋር በፈጸመው የብድር ውል ጥቅምት 29 ቀን 1999 ዓ.ም ማሽነሪዎቹን በዋስትና አስይዞ ከባንኩ የተበደረውን ገንዘብ  መክፈል ስላቃተው ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ንብረቶቹን በሕጋዊ ጨረታ ለቅን ልቦና 3ኛ ወገን ገዢ በሽያጭ ያስተላለፋቸው በመሆኑ፤ከቀረጥ ነጻ ገብተዋል የተባሉት ዕቃዎች ምን ዓይነት ዕቃዎች እንደሆኑ? መቼ እንደገቡ? የቀረጥ እና ታክስ መጠናቸው ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ ከመሆኑም ባሻገር ተጠሪው መስሪያ ቤት ከንብረቶቹ የሰበሰበው  የቀረጥ እና ታክስ ክፍያ የለም፡፡

የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሠጣጥ፤አያያዝ እና አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 16/2 የወሮታው ክፍያ የሚከፈለው ሕገወጡ ዕቃ በመመሪያው አንቀጽ 17 መሠረት ለባለስልጣኑ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ነው በማለት የሚደነግግ በመሆኑ እና አመልካች ጥቆማ ሰጥቸበታለሁ

www.abyssinialaw.com

የሚለው ከቀረጥ ነጻ ሆኖ የገባው ዕቃ ባንኩ ላበደረው ብድር መክፈያ ይውል ዘንድ በሽያጭ የቅን ልቦና ገዢ ለሆነ 3ኛ ወገን የተላለፈ እና ለተጠሪው መስሪያ ቤት ያልገባ እና ቀረጥ እና ታክስ ያልተሰበሰበበት በመሆኑ በመመሪያው መሠረት ለአመልካች ሊከፈል የሚችል የወሮታ ክፍያ ስለማይኖር የስር ፍ/ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ አመልካች ወሮታ እንዲከፈለው ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 23848 ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01005837 ሕዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- **መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 151082

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች፡-** ሚ/ር አሂም ማርቲን ብራዉን- ጠበቃ ምንዳዬ አንጀሎ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሜድሮክ ፋዉንዴሽን ስፔሻሊስት ኃ/የተ/የግ/ማህበር- ጠበቃ አብደላ ዓሊ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የሥራ ውሉ በገዛ ፈቃዱ የተቋረጠበት የሥራ መሪ ያልተጠቀመበትን የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ የሚከፈልበት የሕግ አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሳሽ፣ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን የአመልካች የክስ ይዘትም፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸዉን የስራ ዉል ከሚያዝያ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በገዛ ፍቃዱ ያቋረጠ ቢሆንም ተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን ያልፈጸመለት መሆኑን ገልዖ፣ ከ05/03/2004 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ያለዉን የ5 ወር ደመወዝ ብር 1,243,758.34፣ የ280 ቀናት የዓመት እረፍት ክፍያ ብር 2,108,984.98፣ የአንድ ዓመት የቤት ኪራይ ብር 228,366.67፣ የልጆች ትምህርት ቤት ክፍያ ብር 242,894.00፣ ቀሪ የአየር ጉዞ ትኬት ብር 1,140,000.00፣ ለስራ ጉዞ ያወጡትን ወጪ ብር 192,925.59፣ የተለያዩ ክፍያዎች ብር 69,881.87፣ የ3 ወር ደመወዝ በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት ብር 652,148.20፣ በድምሩ ብር 5,686,034.00 ተጠሪ እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም፡- በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ ዉል ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሆኑን የተስማሙ መሆኑን እና ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የሚታይ ከሆነ ደግሞ የቀረበዉ የተለያዩ ክፍያዎች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆኑ መሆኑን እንደ መጀመሪያ መቃወሚያ ካነሳ በኋላ ፍሬ ነገሩን በተመለከተም አመልካች ለሰሩባቸዉ ጊዜያት ደመወዝ ሲከፈላቸዉ የነበረ መሆኑን፣ አመልካች ከደመወዝ ጋር በተያያዘ በፈጸሙት ህገ ወጥ ተግባር ለ6,000.00 ዩሮ የጀርመንና የኢትዮጵያ መንግስታት የገቢ ግብር እንዳያገኙ ያደረጉ መሆኑን፣እንዲሁም ስራዉን ያቋረጡረት በራሳቸው ፍቃድ በመሆኑ የ3 ወር ደመወዝ ክፍያ በካሳ መልክ ሊከፈላቸዉ የማይገባ መሆኑን፣ የዓመት እረፍት ክፍያም በሁለት ዓመት ባለመጠየቁና በሚመለከተዉ አካል ፍቃድ ያልተላለፈለት በመሆኑ ሊከፈላቸው የማይገባ መሆኑን፣ በዉሉ መሠረት አመልካች በራሳቸዉ ቤት እየኖሩ ስለሆነ በዉሉ መሠረት ሊከፈላቸዉ የሚገባ ደመወዝ አለመኖሩን፣ የት/ቤት ክፍያ የሚከፈለዉ ዕድሜያቸዉ ከ14 ዓመት በታች ለሆኑት ሕፃናት በመሆኑ እና ለእነማን እንደሚከፈል በክሱ በግልጽ ያልተመለከተ በመሆኑ ለት/ት ቤት ክፍያ በሚል የቀረበዉ ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን፣ አመልካች ለእረፍት ወይም ለስራ መሄዳቸዉ ባልተገለጸበት ሁኔታ የጉዞ ትኬት በማለት የጠየቁትም ተገቢነት የሌለዉ መሆኑን እና ልዩ ልዩ ክፍያዎች በሚል ያቀረቡትም አግባብነት የሌለው ነው የሚሉትን ምክንያቶችን በማንሳት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ የቀረበዉን የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ፤ ለአመልካች ደመወዝ ስለመከፈሉ ተጠሪ በማስረጃዉ ያላስረዳ በመሆኑና መጠኑንም በተመለከተ ስላልተከራከረ ብር 1,243,758.34፣ የ280 ቀናት የዓመት እረፍት አመልካች መዉሰዳቸውን ገልጾ ተጠሪ ባለመከራከሩ ብር 2,108,984.98፣ አመልካች የቤት ኪራይ ሲከፍል የነበረ መሆኑ በመረጋገጡ ብር 228,366.67፣ አመልካች ከአዲስ አበባ ፍራንክፈርት የደርሶ መልስ የአዉሮፕላን ትኬት እንደሚሰጣቸዉ በቅጥር ዉሉ ላይ በተመለከተዉ እና በአመልካች በቀረበዉ ትኬት መሠረት ብር 1,140,000.00፤ በድምሩ ብር 4,721,109.99 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት ሲወስን ቀሪዎቹን የክፍያ ጥያቄዎችን ግን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ

www.abyssinialaw.com

ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ አመልካች የጠየቁትን የ 5 ወር ደመወዝ የከፈለ መሆኑን በተመለከተ አመልካች ተገቢ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበ ባለመሆኑ ይሄዉ እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ያለመገኘቱን፣ የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጠዉ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክርክር አመልካች የዓመት እረፍት ወስደው መጠቀማቸውን ገልፆ ያልተከራከረ በመሆኑ አመልካች የዓመት እረፍቱን በየዓመቱ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል በማለት በይግባኝ ክርክር ደረጃ የሚያቀርበዉ ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 329(1) መሠረት ተቀባይነት ያለዉ ክርክር ያለመሆኑን፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌለዉ በመሆኑ አመልካች የዓመት ፍቃድ ጠይቀው እንዲተላለፍላቸው ባላስፈቀደበት ሁኔታ የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል መጠየቅ አይችልም በማለት የአዋጁን አንቀጽ 79 በመጥቀስ የሚያቀርበዉ ክርክርም ተቀባይነት የለሌለው ቢሆንም አመልካች ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት የ280 ቀናት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ የህግ መሠረት የሌለው ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰሠጠውን የውሳኔ ክፍል ውድቅ ያደረገው አድርጎታል፡፡ እንዲሁም የኪራይ ቤት ክፍያና የአየር ትኬት ለአመልካች እንዲከፈል ተብሎ መወሰኑም ያላግባብ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ ተጠሪ ለአመልካች የ5 ወር ከ15 ቀን ደመወዝ ብር 1,243,758.34 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ስምንት ከ34/100) ብቻ ከየካቲት 05 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ወስኖል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአመልካች የዓመት ፍቃድ የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ ተጠሪ ባላስረዳበት ሁኔታ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ የማይከፈልበት ምክንያት የሌለ መሆኑን፣ የቤት ኪራይና የጉዞ ትኬት ክፍያ ዉሳኔም ዉሉን መሠረት ያደረገ ሁኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መሻሩ ያላግባብ መሆኑን በመግለጽ በአጠቃላይ በእነዚህ ነጥቦች ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው ታርሞ በእነዚህ ነጥቦች ላይ የስር ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሰይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመት እረፈት በገንዘብ ተቀይሮ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን በፍትሃብሔር ሕጉ አልተመለከተም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የግራ ቀኝን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ምክንያት ከሆነዉ ዉሳኔ እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት ለመሆኑ ላይ ግራ ቀኝ ያልተካካዱ መሆኑን፣ አመልካች ያቀረቧቸዉን የተለያዩ ክፍያዎች ላለመክፈል የአሁኑ ተጠሪ ካቀረባቸዉ ክርክሮች ዉስጥ አንዱ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ የቅጥር ዉል ላይ ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሆኑ በዉሉ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች ያቀረቧቸዉ የክፍያ ጥያቄዎች በአዋጁ መሠረት በይርጋ ቀሪ የሚደረጉ ናቸዉ የሚል የነበረ ቢሆንም አመልካች የተቀጠሩበት ስራ በባህርዉ የስራ መሪ በሚል በአዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የተመለከተዉ ዓይነት በመሆኑ ላይ ግራ ቀኝ ክርክር የሌላቸው ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 377/96 የስራ መሪን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንደሌለዉ ይሄዉ አዋጅ በአንቀጽ 3(2-ሐ) ስር በግልጽ መደንገጉን፣ በአዋጁ አንቀጽ 3 ስራ የተመለከተዉ የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን በህግ አዉጭዉ አካል የተወሰነ፤ መወሰንም የሚገባዉ በመሆኑ የአዋጁን ተፈፃሚነት የመወሰን ጉዳይ በተዋዋይ ወገኖች በድርድር የሚወሰን ሊሆን እንደማይችል በምክንያትነት ይዞ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ የቅጥር ዉል አንቀጽ 10 በቅጥር ዉሉ ተፈፃሚነት ያለዉ የአሠሪና ሠራተኛ ህግ ነዉ በሚል የተመለከተ ቢሆንም፣ ይህ የዉል ቃል የአፈፃፀም ወሰኑን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 3(2-ሐ) ስር ከተመለከተዉ ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለዉ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ይሄንኑን በምክንያትነት በመጥቀስ የቀረበዉ ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የአሁኑ ተጠሪ የሚያቀርበዉ መከራከሪያ ተገቢነት የለውም በማለት ማለፉን እና በዚህ ረገድ በአሁኑ አመልካችም ሆነ በተጠሪ በኩል የቀረበ የሰበር

www.abyssinialaw.com

ቅሬታ የሌለ መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጠዉ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክርክር አመልካች የዓመት እረፍት ወስደው መጠቀማቸውን ገልፆ ያልተከራከረ በመሆኑ አመልካች የዓመት እረፍቱን በየዓመቱ ሲጠቀምበት ቆይቷል በማለት ተጠሪ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ያቀረበው ክርክር አዲስ ክርክር ነው ተብሎ ውድቅ የሆነ ከመሆኑም በላይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የሌለዉ በመሆኑ አመልካች የዓመት ፍቃድ ጠይቀው እንዲተላለፍለት ባላስፈቀደበት ሁኔታ የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል መጠየቅ አይችልም በማለት የአዋጁን አንቀጽ 79 በመጥቀስ ተጠሪ የሚያቀርበዉ ክርክርም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያለማግኘቱን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ ችሎት እንዲታይ ወደ ተያዘው መሰረታዊ ጭብጥ ስንመጣም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት የ280 ቀናት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ የህግ መሠረት ያለው አይደለም በማለት የሠጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ተመልክተናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት እንደገለጸው የዓመት እረፍት አንዱ ዓላማዉ ሠራተኛዉ የእረፍት ጊዜ ተጠቅሞ ብቁ በሆነ የአእምሮና የአካል ሁኔታ ወደ ስራዉ እንዲመለስ ማድረግ ነዉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የዓመት እረፍት ሠራተኛዉ የሚያርፍበት ጊዜ እንጅ የእረፍት ጊዜዉን በስራ ላይ አሳልፎ እረፍቱ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጠዉ መጠየቅ አይደለም፡፡ ይህ በመሆኑም በመርህ ደረጃ የእረፍት ጊዜ ወደ ገንዘብ ሊቀየር የማይችል ስለመሆኑ እና ወደ ገንዘብ የሚቀየሩት በየህጎቹ በተመለከቱት ሁኔታዎች ብቻ ስለመሆኑ የአሠሪና ሠራተኛን ግንኙነት በሚገዙ በተለያዩ አዋጆች ተቀባይነት ያገኘ መርህ ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ በፍትሐብሔር ህጉ የስራዎች አገልግሎት ለመስጠት የሚደረጉ ዉሎች በሚል ርዕስ ከአንቀጽ 2512 ጀምሮ የተደነገገዉ ሲሆን፣ በዚህ ርዕስ ከአንቀጽ 2560-2565 ስር የተመለከቱት ስለ የዓመት እረፍት በተለይ የሚደነግጉ ሲሆን፣ የዓመት እረፍት ከዓመት ዓመት ሊተላለፍ ስለሚችልበት ሁኔታ እንዲሁም የዓመት እረፍት ሲተላለፍ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈል የሚቻል መሆን አለመሆኑ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር አልተመለከተም፡፡ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የቅጥር ዉል ስለ የዓመት እረፍት የሚደነግገዉ የዉሉ አንቀጽ 5(ሀ እና ለ) ለአሁኑ አመልካች በዓመት

www.abyssinialaw.com

የ42 ቀን የዓመት እረፍት የሚሰጣቸዉ መሆኑን እና የዓመት እረፍት የሚሰጥበትም ጊዜ በግራ ቀኝ መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚወሰን መሆኑን የሚደነግግ ቢሆንም፣ የአሁኑ አመልካች ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሊሰጥ ስለሚችልበት ሁኔታ በተለይ የማይደነግግ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል። ይህ ማለት ግን አመልካች ሳይጠቀሙበት ከዓመት ዓመት የተላለፈ የእረፍት ጊዜ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው ለመጠየቅ የሚያስችል ከህግም ሆነ ከዉል የመነጨ መብት የላቸውም ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም። ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ጉዳዩን ይገዛሉ ብሎ ከጠቀሳቸው የፍትሃብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መካከል ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2563 ድንጋጌ ውሉ በተቋረጠ ጊዜም ሰራተኛው የሚገባውን የእረፍት ጊዜ ለማግኘት መብት አለው የሚል ይዘት ያለው መሆኑ ይህ መብት ተግባራዊ የሚሆነው በገንዘብ ተቀይሮ ነው ተብሎ ከሚተረጎም በስተቀር ሌላ ሰራተኛው የመብቱ ተጠቃሚ አይሆንም የሚል ትርጉም የሚያሰጥ አይደለም። ስለሆነም ለአመልካች የመብት ጥያቄ ሕግ ጥበቃ አድርጎ እያለና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2563 ድንጋጌም ይዘትና መንፈሱ ሲታይ ውሉ መቋረጡ እስከተረጋገጠ ድረስ የአመት እረፍትን የማግኘት መብቱን የጠበቀ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ድንጋጌው ተግባራዊ የሚሆንበትን አግባብ ሳያገናዘብ የአመልካች ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም። እንዲሁም ተጠሪ አመልካች የእረፍት ጊዜአቸውን መጠቀማቸውን ወይም በሕጉ አግባብ የተጠቀሙ መሆኑን ሳያስረዳ የገንዘብ መጠኑ ከፍተኛ መሆኑን በመጥቀስ በተጠሪ ላይ ኪሳራ ሊያደርስ የሚችል በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የአቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመት እረፈትን በተመለከተ የሰጠው የውሳኔ ክፍል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2563 ድንጋጌን የጣሰ እና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘውም ተከታዩን ወስነናል።

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/138726 በቀን 18/04/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 138029 በ22/01/2010 ዓ/ም የተሻሻለው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የዓመት እረፍትን በተመለከተ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠው የዉሳኔ ክፍል ተሽሮ በዚህ ረገድ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 348 መሰረት ፀንቷል
3. የመኖሪያ ቤት ኪራይ እና ቀሪ የጉዞ ትኬት ክፍያን በተመለከተ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 348 መሰረት ጸንቷል፡፡
4. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የ5 ወር ከ15 ቀን ደመወዝ ብር 1,243,758.34 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ስምንት ከ34/100) እና የ280 ቀናት የዓመት እረፍት ብር 2,108,984.98 እንዲከፍል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
5. በዚህ ችሎት በተደረገዉ ክርክር የወጣዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.abyssinialaw.com

ሰበር መ/ቁ154371

ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ አስፋዉ ተኽለ በሽሩ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የጥብቅና ሙያ የዲስፕሊን ጥፋት የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች አዋጅ ቁ/262/07 አንቀጽ 30/23/ ተላልፎ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ፈጽሟል በሚል የክልሉ የጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ሰጥቶ በዚህም ብር ሶስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ የወሰነበት ሲሆን የክልሉ ፍትህ ቢሮ ሃላፊ ይህንኑ በማጽናታቸዉ አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ የአመልካች ደንበኛ ተከሳሽ ፍፁም ገ/መድህን በተከሰሰበት ቀላል ስርቆትና በቸልተኛነት የመሸሸግ ወንጀል በሐድነት ክ/ከ ክርክር ላይ መሆኑን በመግለጽ መቃወሚያ ማቅረብ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ነዉ ተብሎ የቅጣት ዉሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም የሚል ነዉ፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በአመልካች ደንበኛና በአቃቤ ህግ መካከል በተመሳሳይ ጉዳይ በሌላ ፍርድ

ቤት ቀጠሮ ላይ መሆኑን ገልጾ መከራከሩ ፍትህን የሚያዛባ ተግባር ነዉ ተብሎ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል።በተጠሪ በኩል ያቀረበዉ መልስ ባጭሩ የአመልካች ደንበኛ በኩሓ ክ/ከ/ወረዳ ፍርድ ቤት የተከሰሰዉ ንብረትነቱ የአቶ ሃይላይ ገ/ሕይወት የሆነ የብሎኬት ማምረቻ ዲናሞ ሸሽጎ በመገኘቱ ስለመሆኑ፤በሌላኛዉ ጉዳይ በሓድነት ክ/ከ/ ወረዳ ፍ/ቤት የተከሰሰዉ ንብረትነቱ የአቶ ሃይሉ ግርማይ የሆኑ ሁለት ስላተርሽ የሚባል ማሽን ሸሽጎ በመገኘቱ ስለመሆኑና በሁለቱም መዝገብ የአመልካች ደንበኛ የተከሰሰዉ በመሸሸግ ወንጀል ቢሆንም ንብረቶቹ የተለያዩና ባለቤቶቹም የተለያዩ ስለሆነ ይህንን ሓቅ እያወቀ መቃወሚያ ማቅረቡ ፍትህን የሚያሳስት ተግባር ስለሆነ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል።አመልካችም አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ ክርክር ይዘት ከላይ ባጭሩ ተገለጸ ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል።መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ የአመልካች ደንበኛ በሁለት ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ጉዳይ ክስ ሊቀርብባቸዉ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ የክስ ክርክር የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉ በሚል የተሰጠዉ ቅጣት ዉሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ከአዋጁ አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተናል።የትግራይ ክልል የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁ/262/2007 ላይ የድስፕሊን ጥፋቶች ዓይነትና የሚወሰዱ እርምጃዎችን አስመልክቶ በክፍል ሶስት አንቀጽ 30 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ በዝርዝር ተደንግጓል።በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት የአዋጁን አንቀጽ 30/23/ተላልፈዉ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ፈጽመዋል በሚል ነዉ።የአዋጁ አንቀጽ 30 የሚደነግገዉ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶችን በመዘርዘር ሲሆን ንኡስ አንቀጽ 23 ስር የተመለከተዉ <u>የጥብቅና ሙያን የሚያጎድፍ ተግባር በደንበኛዉ ወይም በሌላ ሰዉ ላይ መፈጸም</u> ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት መሆኑን የሚደነግግ ነዉ።ከዚህ ድንጋጌ አንጻር የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ምንነት አመላካች ቃል ወይም ትርጉም በግልጽ በአዋጁ ላይ የተመለከተ ባይሆንም አመልካች ደንበኛቸዉ በተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት

www.abyssinialaw.com

መቃወሚያ ማቅረባቸዉ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉ በሚል መቀጣታቸዉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበዉ ክስ መነሻዉ የአመልካች ደንበኛ አቶ ፍጹም ገ/መድህን በሁለት ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በመሸሸግ ወንጀል መከሰሳቸዉን ተከትሎ አመልካች በደንበኛቸዉ ላይ በተመሳሳይ ጉዳይ ሁለት ፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብ አይገባም በሚል መቃወሚያ ማቅረባቸዉ የአዋጁን አንቀጽ 30/23/ በሚያሟላ ሁኔታ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉን? የሚለዉ መታየት ያለበት ነዉ፡፡የአመልካች መቃወሚያ ነጥብ ደንበኛቸዉ በመሸሸግ ወንጀል በሓድነት ክ/ከ/ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሰዉ ቀጠሮ ላይ ስለሆነ በተመሳሳይ የመሸሸግ ወንጀል በኲሓ ክ/ከ/ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ መቅረቡ ተገቢ ስላልሆነ መዝገቡ እንዲዘጋ የሚል ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡በአቃቤ ህግ በኩል የተሰጠዉ ምላሽ ሁለቱም ክሶች የመሸሸግ ወንጀል ቢሆኑም የግል ተበዳይ እና ንብረቱ የተለያየ ስለሆነ አንድ ዓይነት ክስ አይደለም የሚል ነዉ፡፡

በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/130 ላይ እንደተመለከተዉ የክሱ ማመልከቻ ላይ ተከሳሹ መቃወሚያ ሊያቀርብ ከሚችልባቸዉ ምክንያቶች አንዱ በዚሁ ነገር ክስ በሌላ ፍርድ ቤት ተጀምሮ በቀጠሮ ላይ ያለ መሆኑን መሰረት በማረጋገጥ ሲቻል ነዉ፡፡የአመልካች ጠበቃ በሁለት ፍርድ ቤቶች በመሸሸግ ወንጀል ክስ የቀረበበት መሆኑ አላከራከረም፡፡ ስለሆነም በሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተያዘዉ ክስ አንድ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን እና የቀረበዉ መቃወሚያ በህግ ተቀባይነት አለዉ ወይስ የለዉም የሚሉ ነጥቦች መዝገቡን ለያዘዉ ፍርድ ቤት የተተወና ፍርድ ቤቱ አጣርቶ ብይን የሚሰጥበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች በዚህ መልክ ያቀረቡት መቃወሚያ በህግ የተፈቀደ ስለመሆኑ ከወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/130/2/ሀ ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ የአመልካች ደንበኛ በሁለት የተለያዩ ፍርድ ቤቶች የተከሰሱት በመሸሸግ ወንጀል መሆኑን መሰረት አድርገዉ አመልካች መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን እንደአቃቤ ህግ ክርክር የክሶቹ ዝርዝር ይዘት ሲታይ የተሸሸገዉ ንብረት ዓይነትና የንብረቶቹ ባለቤቶች የተለያዩ መሆንን መሰረት አድርጎ የክሱ ነገር አንድ ነዉ ወይሥ አይደለም የሚለዉን ለይቶ መቃወሚያዉ የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ130 2/ሀ ድንጋጌ ይዘት ያሟላል ብሎ መቀበል ወይም ዉድቅ ማድረግ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የሚሰጥበት ስለመሆኑ ከወ/መ/ስ/ስ/ህግ

www.abyssinialaw.com

ቁ/131 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም  የአመልካች ደንበኛ ላይ በሁለት ፍርድ ቤቶች በመሸሸግ ወንጀል ክስ ቀርቦ ያለ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች በህግ የተፈቀደዉን መቃወሚያ ማቅረባቸዉን የሚያሳይ እንጂ አመልካች የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር መፈጸማቸዉን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ የአመልካች ተግባር በአዋጅ ቁ/262/07 አንቀጽ 30/23/ስር  የሚያሥቀጣ  ሆኖ አላገኘነም፡፡ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. በዚህ ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ ክርክር የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ፈጽመዋል በሚል የትግራይ ክልል የጠበቆች ዲስፒሊን ጉባኤ በ06/01/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/101364 ላይ በ06/06/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ  ተሽሯል፡፡ይጻፍ፡፡
2. አመልካች በደንበኛቸዉ ላይ ለቀረበዉ የወንጀል ክስ ያቀረቡት መቃወሚያ ምክንያት በህግ የተፈቀደ በመሆኑ ፍርድ ቤት መርምሮ ዉሳኔ የሚሰጥበት እንጂ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉ ተብሎ በዲስፒሊን የሚያስቀጣ ተግባር አይደለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መቁ.142851

ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ወርቅነሽ ጌታቸው

2 አቶ አስፋው አምዴ } ጠበቃ አቶ ታደለ ገ/መድህን-ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ኮሬ ባዌ

2. ወ/ሮ ፀሐይ ባዌ } 1ኛ ተጠሪ ከጠበቃቸው አቶ አብዱረሃማን መሐመድ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የነገሩ አመጣጥ የንግድ ማኅበር ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበውና የታየው በግልግል ዳኝነት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች /የሥር አመልካቾች/ ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የተሻሻለ የክስ አቤቱታ የሽርክና ውል በመፈራረም "ፐላዛ አዲስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" የተባለ ማኅበር ለማቋቋም በምንቀሳቀስበት ሂደት ውስጥ ተጠሪዎች በሽርክና ውል ለመሳተፍ የፈለጉ በመሆኑና አመልካቾችም በመስማማታቸው ይህንኑ አስመልክቶ መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመናል፤ በፐላዛ አዲስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሥር ከሚጠቃለሉት ንብረቶችና ፈቃዶች ጭምር የህንፃው ሥራ ሙሉ ለሙሉ

www.abyssinialaw.com

ከተጠናቀቀና ለሆቴሉ ሥራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና እቃዎች ሁሉ ከተሟሉ በኋላ አጠቃላይ የንብረቱ ዋጋ ብር 130,000,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ሚሊዮን/ እንዲሆን እንደዚሁም ከዳሽን ባንክ የተወሰደ ብድር በተጠቀሰው የማኅበሩ ካፒታል ውስጥ የተካተተ መሆኑን ተዋዋይ ወገኖች ተስማምተናል፤ ከዚህ ካፒታል ውስጥ የተጠሪዎች ድርሻ 40% ወደ ገንዘብ ሲቀየር ብር 52,000,000 /አምሳ ሁለት ሚሊየን/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የባንክ እዳው 40% ድርሻ ብር 24,000,000 /ሃያ አራት ሚሊየን/ ሲቀነስ ተጠሪዎች ቀሪውን ብር 28,664,000 /ሃያ ስምንት ሚሊየን ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ/ ለመክፈል ተስማምተው መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተደረገ የመግባቢያ ሰነድ ሲፈረም ከፊል ክፍያ ፈጽመው የሚፈለግባቸውን ቀሪ እዳ የመመሥረቻ ጽሁፉና መተዳደሪያ ደንብ ከመሻሻሉ በፊት ለመክፈል ግዴታ ገብተዋል፤ ይሁንና ተጠሪዎች የሚቀርባቸውን እዳ የመመሥረቻ ጽሁፉና የመተዳደሪያ ደንቡ ከመሻሻሉ በፊትም ሆነ በኋላ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆኑም፤ ተጠሪዎች በውሉ መሰረት ሊከፍሉ የሚገባቸውን በራሳቸው የታመነ ብር 6,399,782.07 /ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም/፣ ለሆቴል አግልግሎት ለሚውሉ እቃዎች ግዢ ከትራንስፖርት ጭምር ብር 3,230,687.70 /ሶስት ሚሊየን ሁለት መቶ ሰላሳ ሺህ ስድስት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሰባ ሳንቲም/ ውስጥ የተጠሪዎች 40% ድርሻ ብር 1,292,275.10 /አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አምስት ብር ከአስር ሳንቲም/ እና ለከስተም ክሊራንስ ኮንሰልታንሲ ከወጣ ብር 167,052.09 /አንድ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ሃምሳ ሁለት ብር ከዜሮ ዘጠኝ ሳንቲም/ የተጠሪዎች ድርሻ ብር 66,820.83 /ስልሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ብር ከሰማኒያ ሶስት ሳንቲም/ በድምሩ ብር 7,758,878.00 /ሰባት ሚሊየን ሰባት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ስምንት/ አልከፈሉም፤ በመግባቢያ ሰነዱ አንቀጽ 3 መሠረት የውሉን አፈጻጸም ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ ወገን የውሉን ብር 130,000,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ሚሊየን/ 10% የቅጣት ገንዘብ ውሉን ላከበረ ወገን ለመክፈል ግዴታ መገባቱን ገልጸው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1731 እና 1971 መሠረት ለውሉ አፈጻጸም የአንድነትና የነጠላ ኃላፊዎች መሆናቸው ተረጋግጦ ከላይ የተዘረዘረውን ብር 7,758,878.00 /ሰባት ሚሊየን ሰባት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ስምንት/ የመመሥረቻ ጽሁፉና የመተዳደሪያ ደንቡ ከተሻሻለበት ቀን

www.abyssinialaw.com

ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ፣ የጠበቃ አበል፣ የትርጉም፣ የዳኝነትና ልዩ ልዩ ወጪና ኪሳራ ጨምረው እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ታኅሳስ 20 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካቾች በስምምነቱ መሠረት ህንፃውን ሙሉ በሙሉ የማጠናቀቅ፣ የሆቴሉን እቃና መሳሪያ የማሟላት፣ የሆቴሉ ይዞታ የነበረውን ቦታ በ241 ካሬ ሜትር አስቀንሰው በማስመዝገባቸው በገበያ ዋጋ ለተቀነሰው ቦታ ክፍያ የመፈጸምና በውል መሠረት ሊፈጽሟቸው የሚገቡ ግዴታዎች ስላሉባቸው ግዴታዎቹን ፈጽመናል ሳይሉ ወይም ለመፈጸም ዝግጁነታቸውን ሳይገልጹ መክሰስ እንዳይችሉ የፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1757 የሚያግዳቸው ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ. 39568 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ ይህ እንዳለ ሆኖ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ፊት መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ/ም ላይ የተፈረመው የማኅበሩ የተሻሻለው የመመስረቻ ጽሁፍ ላይ የማህበሩ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል በማለት የተገለጸ በመሆኑ ተጠሪዎች ለ40 በመቶ ድርሻቸው የሚፈለግባቸውን የገንዘብ መዋጮ ለመክፈላቸው በቂ ማረጋገጫ ነው፤ በሌላ በኩል ተጠቃሹን ገንዘብ ተከሳሾች ይከፍላሉ ያሰኘው ከሳሾችና ተከሳሾች ከግልግል ዳኝነት ጉባኤው ውጪ ክርክራቸውን በሙግት ሳይሆን በእርቅ ይፈታ እንደሆነ ለመሞከር መግባባት ላይ በደረሱበት ወቅት አለመግባባት አስነስተዋል በተባሉ ነጥቦች ላይ የከሳሾችን አመለካከት ወደ ቀና መንገድ ለመመለስ " ሰጥቶ መቀበል" በሚል ቅን አስተሳሰብ ተከሳሾች ጥቅምት 20 ቀን 2008 ዓ/ም በጻፉት ማመልከቻ ተጠቃሹን ገንዘብ እንዲከፍሉ ከሳሾችም ደግሞ የመስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም ስምምነትን በመተግበር ግዴታቸውን በቅን መንፈስ እንዲወጡ ለማግባባት ይረዳል በሚል የገለጹት እንጂ ግዴታ የገቡበት አይደለም፡፡ ስለዚህ አዋዋይ በተገኙበት የተፈረመው ሰነድ ገንዘብ በተከሳሾች መከፈሉ ግራ ቀኙ " ሁሉንም ተጠቃሚ ሊያደርግ" በሚችል የእርቅ ድርድር ወቅት እንከፍላለን ያሉት ገንዘብ በፍርድ ቤት፣ በፍርድ ሰጭ አካል፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤት እንደታመነ ወይንም በቃለ መኻላ እንደተረጋገጠ እዳ ተቆጥሮ ተጠያቂነት ያስከትላል የሚለው የከሳሾች አካሄድ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በኃላ የአሁን ተጠሪዎች 14 ነጥቦችን በማንሳት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ያቀረቡ ሲሆን የአሁን አመልካቾችም /የከሳሽ ተከሳሾችም/ ከሥልጣን ጋር ተያይዞ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም ለፍሬ ነገሩ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የግልግል ጉባኤ በተከሳሽ ከሳሽነት ከቀረቡት አስራ አራት ነጥቦች መካከል በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 7 እና 14 ላይ የቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄዎችን ለመመልከት ሥልጣን እንዳላቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተራ ቁጥር 5፣ 6፣ 11፣ 12 እና 13 ሥር ተጠቅሰው የቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄዎችን መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተደረገው መግባቢያ ሰነድ መሠረት የግልግል ዳኝነት አካሉ ለመመልከት ሥልጣን እንደሌለው እንዲሁም በተራ ቁጥር 8፣ 9 እና 10 ሥር ተጠቅሰው የቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄዎችን በተመለከተ የክስ ምክንያት የሌላቸው መሆኑን ገልጾ ጥር 26 ቀን 2008 ዓ/ም ብይን ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኃላ የግልግል ጉባኤው በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከርና ምስክሮችን በመስማት እንዲሁም ሰነዶችን በመመርመር አመልካቾች ተጠሪዎች በጽሁፍ አምነዋል በማለት እንዲከፍሏቸው የጠየቁትን ብር 6,399,782.07 /ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ዜሮ ሰባት ሳንቲም/ በተመለከተ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 4,276,900 /አራት ሚሊየን ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ/ የሚሆነው በመግባቢያ ሰነዱ ላይ ተጠሪዎች ላይ ከተጣለው ግዴታ ጋር ግንኙነት የለውም በማለት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት ሳይቀበለው የቀረ ሲሆን ቀሪውን ብር 2,122,882.00 /ሁለት ሚሊየን አንድ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ሁለት/ ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ ተጠሪዎች በመግባቢያ ሰነድ፣ በተለያዩ ደረሰኞች እንዲሁም ቼክ የሚፈለግባቸው ክፍያዎችን ከፍለው በሰነዶች ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ ስለሆነ አመልካቾች ገንዘብ አልተከፈለንም በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልንም፤ አመልካቾች ለሆቴሉ አስፈላጊ የሆኑ እቃዎችና መሳሪያዎችን ለማሟላት አወጣን ያሉትን ገንዘብ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የጠየቁትን በተመለከተ መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ እቃዎችና መሳሪያዎችን የማሟላት ግዴታ የአመልካቾች በመሆኑ የጠየቁትን ክፍያ በሚመለከት ይህ ክፍያ ሆቴሉ በተገመተበት ሰላሳ ሚሊየን ብር ውስጥ የሚጠቃለል

www.abyssinialaw.com

ከሚሆን በቀር ለብቻው ተነጥሎ በመውጣት በተጠሪዎች ክፍያ እንዲፈጸምበት ሊጠየቅ የሚችልበት ሆኖ አልተገኘም፤ አመልካቾች ያቀረቡት ለከስተምስ ኪሊራንስ እና ኮንሰልተንሲ የተከፈለ ብር 66,820.83 ይከፈለን ጥያቄ የውል ድጋፍ የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በተመለከተ የግልግል ጉባኤው ሥልጣን አለኝ በማለት የተመለከታቸውን ነጥቦችን በተመለከተ 1ኛ/ ስፋቱ 1280 ካሬ ሜትር የሆነ ለመኖሪያነት በአሁን አመልካቾች ስም የተሰጠውን ይዞታ ካርታ ሲዘጋጅ ስፋቱ 1039 ሆኖ የተሰራ በመሆኑ የ241 ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ ሽያጭ ዋጋ ተመን ብር 6,319,261 /ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ/ የአሁን አመልካቾች ይክፈሉ በማለት የአሁን ተጠሪዎች የጠየቁትን በተመለከተ የግልግል ጉባዔው የተጠቀሰውን ቦታ በተመለከተ በቦሌ ክፍሌ ከተማ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሚያዝያ 3 ቀን 2008 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ የይዞታው ስፋት የቀነሰው በመንገድ ጥናት ምክንያት መንገድ የሚወስደው ተቆርጦ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ገልጾ ተጠሪዎች ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የቀነሰው የይዞታ ስፋት በአካባቢው የሊዝ ዋጋ ተሰልቶ ድርሻቸው የይዞታ ዋጋ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ጥያቄ የግልግል ጉባኤው አልተቀበለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፣ 2ኛ/ ከመተዳደሪያ እና መመሥረቻ ጽሁፍ ጋር ተያያዞ የተነሳውን ክርክር በተመለከተ መተዳደሪያ ደንቡ እና መመሥረቻ ጽሁፉ የተሻሻለ መሆኑ ማረጋገጡን፣ ተጠሪዎች በተሻሻለው ጽሁፍና ደንብ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ጉዳዮች አልተካተቱም የሚሉ ከሆነ በንግድ ህጉ እና በተሻሻለው የመመሥረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት አጀንዳ አስይዘው እንዲካተቱ ለመጠየቅ የሚችሉ ከሚሆኑ በስተቀር በመግባቢያ ሰነዱ መሠረት መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ/ም ቃለ ጉባኤ ተይዞ የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የቀረበ በመሆኑ አልተሻሻለም የሚያስብል በቂ ምክንያት የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበ የተጠሪዎች ክርክር ጉባኤው አልተቀበለውም በማለት አስቀምጧል፡፡ 3ኛ/ ከህንጻ ጋር በተያያዘ ህንጻው ጥራት የሚጎለው ከመሆኑ እንዲሁም አስፈላጊ መሳሪያዎችና እቃዎች ካለመሟላታቸው ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር በተመለከተ የህንፃው ሥራ ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቅ አለመጠናቀቁን ለመረዳት ይቻል ዘንድ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው በጉዳዩ ላይ

www.abyssinialaw.com

ከተጠሪዎች የተቆጠሩ ምስክሮችን አስቀርቦ ማዳመጡን እንዲሁም የሆቴሉን ህንፃ በቦታው ድረስ ሄዶ መመልከቱን ገልጾ አመልካቾች በክርክራቸው ሆቴሉ ስለመጠናቀቁና እቃዎችና መሳሪያዎችም አለመሟላታቸው ሆቴሉ ባለ4 ኮከብ የሚል ደረጃ የተሰጠው ስለመሆኑ አስረጅ ነው በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በተለይም ሆቴሉ የኮከብ ደረጃ ሲሰጠው ሆቴሉ ሳያልቅ እንዳለቀ፣ ለሆቴሉ ሥራ አስፈላጊ መሳሪያዎችና እቃዎች ሳይኖሩና ሳይሟሉ እንዳሉና እንደተሟሉ ተደርጎ የተሰጠው መሆኑን የተጠሪዎች ምስክሮች በተለይም 2ኛ ምስክራቸው በማያሻማ መልኩ ያስረዱ በመሆኑ አመልካቾች ሆቴሉ ስለመጠናቀቁና አስፈላጊ እቃዎችና መሳሪያዎችም የተሟሉለት ስለመሆኑ የተሰጠው ባለ4 ኮከብ ደረጃ ነው በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ ጉባኤው አልተቀበለውም ካለ በኋላ አመልካቾች  መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተፈረመ የመግባቢያ ሰነድ መሠረት የሆቴሉን ሥራ ሙሉ ለሙሉ ባለማጠናቀቃቸው እና ለሆቴሉ የሚያስፈልጉ እቃዎችና መሳሪያዎችንም ባለማሟላታቸው በራሳቸው ወጪ የህንፃውን ሥራ ሊያጠናቅቁና አስፈላጊ እቃዎችና መሳሪያዎችንም ሊያሟሉ ይገባል ሲል የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ፍርድ ሰጥቷል፡፡ **4ኛ/** ተጠሪዎች  አመልካቾች ከሆቴሉ ከውል ወጪ ገንዘብ ወጪ አድርገዋል ተብሎ የቀረበውን በተመለከተ የግልግል ጉባኤው ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር ካለፈቃዳችን ከሆቴሉ የወጣ ወጪ ከነወለዱ ተመላሽ ይደረግ ቢሉም ምን ያህል ገንዘብ፣ መቼ እንደወጣ ግን በግልጽ በክርክራቸው አላመለከቱም፣  ይልቁንም አመልካቾች በጥሬ ገንዘብ ከሆቴሉ ያወጡትን ያሳውቁን ማለታቸው በግልጽ ምን ያህል ገንዘብ እንደወጣ እየጠቀሱ ክርክራቸውን እያቀረቡ እንዳልሆነ ያሳያል፣ ይህ ብቻ ሳይሆን ከሆቴሉ ያለፈቃዳቸው ገንዘብ ስለመውጣቱ ለማስረዳት ያቀረቡት አስረጅም የለም፡፡ ስለዚህ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ ግልጽ ያልሆነና የማስረጃ ድጋፍም የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም በማለት ወስኗል፡፡ **5ኛ/** አመልካቾች ከተጠሪዎች  እውቅና ውጪ ከዳሸን ባንክ በብድር የወሰዱትን  ብር 2,000,000.00 /ሁለት ሚሊየን/ በተመለከተ ተጠሪዎች ተጠያቂነት እንደሌለባቸው ገልጸው ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ምንም እንኳን የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ጥር 26 ቀን 2008 ዓ/ም በመዝገቡ ላይ በሰጠው ብይን ከብር ሁለት ሚሊየን ጋር በተያያዘ የተነሳውን ክርክር ተመልክቶ ለመዳኘት ሥልጣን አለኝ ያለ ቢሆንም ግራ ቀኙ መጋቢት 12 ቀን 2008

www.abyssinialaw.com

ዓ/ም ባስመዘገቡት ክርክር ለክስ መነሻ የሆነው ገንዘብ መግባቢያ ሰነዱን መሰረት አድርጎ የተነሳ አለመሆኑን ከብይኑ በኃላ ያረጋገጡ በመሆኑ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ተመልክቶ ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም በማለት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 9/2/ መሠረት በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪዎችን ክርክር ውድቅ አድርጓል ሲል ወስኗል፡፡

በግልግል ጉባኤ 2ኛ ዳኛ የሆኑት አመልካቾች ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ያቀረቡት ብር 6,399,782.07 በተመለከተ በተጠሪዎች በጽሁፍ የታመነ እዳ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው እዳው የታመነበት ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ እንዲሁም ተጠሪዎች እዳ ከፍለናል በሚል ያቀረቧቸው ማስረጃዎች በጽሁፍ ከመታመኑ በፊት የተከፈሉ ናቸው፤ በመሆኑም በቅርብ በጽሁፍ የታመነ እዳ ለማስተባበል በቂነት የላቸውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ለአመልካቾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ከአብላጫ ድምፅ ተለይተዋል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች 1ኛ/ የግልግል ጉባዔው አመልካቾች ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ተብሎ የቀረበውን መቃወሚያ የግልግል ጉባዔው አልፎ ጉዳዩን መመልከቱ ያለአግባብ ነው፣ 2ኛ/ የ241 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ፣ 3ኛ/ የሥር መልስ ሰጪዎች /የአሁን አመልካቾች/ ለሆቴሉ መኝታ ለተገለገሉበትና ለሆቴሉም ምግብ ለተጠቀሙበት ለሆቴሉ ወይም ለማኅበሩ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ይወሰንልን በሚል የተጠየቀውን ዳኝነት ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ያለአግባብ እንደሆነ፣ 4ኛ/ ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሻሻል እና ከሆቴሉ ስያሜ ጋር የተነሳውን ክርክር የግልግል ዳኝነት ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፣ 5ኛ/ የአሁን አመልካቾች ከዳሽን ባንክ የወሰዱትን ብር 2,000,000 /ሁለት ሚሊየን/ ጋር በተያያዘ ግልግል ጉባኤው ሥልጣን አለኝ በማለት ካከራከረ በኂላ ተመልሶ ሥልጣን የለኝም ማለቱ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ 6ኛ/ ውል ያላከበረ ወገን የ130,000,000 ብር 10% እንደሚከፍል መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ላይ በተቀመጠው መሠረት የአሁን አመልካቾች ውሉን ባለማክበራቸው በውሉ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲከፍሉ የተጠየቀውን ዳኝነት የግልግል ጉባኤው በግልጽ ውሳኔ መስጠት ሲገባው በዝምታ ማለፉ ያለአግባብ ነው በማለት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

በሌላ በኩል የአሁን አመልካቾች ያቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ 1ኛ/ ብር 7,758,878.07 የአሁን ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የጠየቁት ዳኝነት ውድቅ መደረጉን የሚመለከት ሲሆን 2ኛው ከሆቴሉ አገልግሎት አሰጣጥ እና እቃዎች አለመሟላት ጋር በተያያዘ የግልግል ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ በየበኩላቸው ያቀረቡትን ይግባኝ ተቀብሎ ካከራከረ በኃላ የቀረቡትን ቅሬታዎችን መርምሮ የግልግል ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት እንዲሁም ከውል አለመፈጸም ጋር የተነሳውን የአንድ መቶ ሰላሳ ሚሊየን 10% ውሳኔ ሳይሰጥ በዝምታ ታልፏል የተባለውን በተመለከተ ጉባኤው በግልጽ የሰጠው ውሳኔ ባይኖርም በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው ውል ባህርይ፣ እንዲሁም መልስ ሰጪዎች /የአሁን አመልካቾች/ የሰጡት የውል ድንጋጌ የትኛው እንደሆነ ግልጽ ሆኖ የማይታወቅ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ መልስ ሰጪዎች /የአሁን አመልካቾች/ ውሉን ጥሰዋል ተብሎ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም አመልካቾች ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የጠየቁትን ብር 6,399,782.07 በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካቾች ተፈጽሞብናል ያሏቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ ተጠሪዎች በጽሁፍ ያመኑትን አይከፍሉም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ መቃወሚያ እና በአማራጭ ክፍያው ስለመፈጸሙ ዝርዝር መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የአመልካቾች ጠበቃም ጥቅምት 17 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን የአመልካቾችን የቅሬታ ነጥብ የግልግል ጉባዔው ከሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክር አንጻር

www.abyssinialaw.com

መርምረናል፡፡ በግልግል ጉባዔም ሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጡት ውሳኔዎች ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ወይስ አልተፈጸመበትም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡የአሁን አመልካቾች ካቀረቡት ዳኝነት መካከል ከብር 6,399,782.07 /ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ዜሮ ሰባት ሳንቲም/ ውስጥ 4,263,460 /አራት ሚሊየን ሁለት መቶ ስልሳ ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ / ብር በተመለከተ በመግባቢያ ሰነዱ ላይ በአሁን ተጠሪዎች ላይ ከተጣለው ግዴታ ጋር ግንኙነት የሌለው ነው በማለት የግልግል ጉባኤው አልፎታል፡፡ ቀሪውን ገንዘብ በተመለከተ ግን የአሁን ተጠሪዎች በመግባቢያ ሰነድ፣ በተለያዩ ደረሰኞች እንዲሁም በቼክ ለአሁን አመልካቾች ከፍለዋል ሲል በማስረጃ አረጋግጦ የአሁን ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ወስኗል፡፡ የግልግል ጉባዔው ውሳኔ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው የግልግል ጉባዔው መመልከት አልችልም ካለው ገንዘብ ውጪ ያለው በተለያዩ ሰነዶች ገቢ የሆነ መሆኑንና ይህም ገቢ ስለመደረጉ በሰነዶች ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑን ነው፡፡ የግልግል ጉባኤው መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም ከተደረገው የመግባቢያ ሰነድ ውጪ ነው ያለውን ገንዘብ በተመለከተ አመልካቾች መብትና ጥቅም ካላቸው ለፍርድ ቤት አቅርበው ከሚያስወስኑ ውጪ መሠረታዊ የህግ ስህተት እንደተፈጸመ አድርገው ለዚህ ችሎት ያቀረቡትን ስንመለከት ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንዲሁም ተጠሪዎች ለመክፈል በጽሁፍ አምነው የነበረውን ገንዘብ በቃለ መኻላ ሥር ሆነው ስለመክፈላቸው ቃል በመስጠታቸውና በክርክር ሂደት ያቀረቡትን ማስረጃዎችን የግልግል ጉባዔው ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በሚል የቀረበውን ቅሬታ በተመለከተ ተጠሪዎች የሚፈለግባቸውን ድርሻ ከፍለው ስለመክፈላቸውም በሰነዶችና ምዝገባ ጽ/ቤት ከተመዘገበ በኋላ የምንከፍል ገንዘብ አለብን በማለት በጽሁፍ መተማመኛ ቢሰጡ ይህ ከአዋጅ ቁጥር 334/1995 አንጻር መታየት ያለበት ነው፡፡ በዚህ አዋጅ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ፊት ቀርቦ የተረጋገጠና የተመዘገበ ሰነድ ደግሞ በውስጡ ስለሚገኘው ይዘት ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ስለመሆኑ በአንቀጽ 27/1/ ሥር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የሥር ግልግል ጉባኤም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

www.abyssinialaw.com

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር የተመለከቱትን መሠረታዊ ነገሮችን የግልግል ጉባኤው ተመልክቶ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ አከራክሮ በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የግልግል ጉባኤው ጥር 26 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ብይን እና ሰኔ 13 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 130348 በ18/08/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በግልግል ጉባኤውም ሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጡት ውሳኔዎች ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

   መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፉ/ዘ